በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች

በ

ብርሃን አሰፋ አራጋው

ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር


በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

ብርሃን አሰፋ አራጋው

አማካሪ

መላክነህ መንግሥቱ (ዶ/ር)



ሰኔ 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ማረጋገጫ

“በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ የራሴ ወጥ ስራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ መደረጋቸውንና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም ብርሃን አሰፋ አራጋው ፊርማ _______________ ቀን______________

# ምስጋና

ከውድ ጊዜያቸው ላይ ከፍለው፣ ጊዜ በማይሰጥ ኃላፊነት ውስጥ ሆነው ጥናቱን በተደጋጋሚ በማረምና በማስተካከል፣ የጎበጠውን አቃንተው፣ የረሳሁትን አስታውሰው፣ የጎደለውን አሟልተው ከፍ ያለ ሙያዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ለአማካሪዬ ለዶ/ር መላክነህ መንግሥቱ ምስጋናዬ የአንጀት ነው፡፡ የእርሳቸው ሙያዊ ድጋፍ ባይኖር ጥናቱ ምናልባትም በዚህ መልኩ ሊሆን አይችልም ነበር፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና ወሎ ዩኒቨርሲቲ የትምህርት ዕድል ስለሰጣችሁኝና የገንዘብ ድጎማ ስላደረጋችሁልኝ፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህራንና አስተባባሪዎች ሁሉም ነገር መልኩንና ጊዜውን ጠብቆ እንድከናወን ላደረጋችሁልኝ እርዳታ አመሰግናለሁ፡፡ በተለይ እውቀትን ከሥነምግባር ጋር ላካፈላችሁኝ ጋሽ ዘሪሁን፣ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ (ፈጣሪ ነፍሳቸውን ይማረው)፣ ፕሮፌሰር ሽፈራው በቀለ እና ዶ/ር ባይለየኝ ጣሰው ሁላችሁንም አመሰግናለሁ፡፡

ዶ/ር ፈቃደ አዘዘ ከሁለተኛ ዲግሪዬ አንስተው በማስተማርና በማማከር እስካሁን ስላደረጉልኝ በፍቅር የተሞላ እርዳታዎ እግዚአብሔር ውለታዎን ይክፈልዎት፡፡ ይህንን ጥናት ከርዕሱ ጀምሮ ትልመ ጥናቱን እስከሚጠናቀቅ ድረስ የረዱኝን፣ ከዚያም በኋላ በየጊዜው በስልክዎ እየደወሉ ያለሁበትን ደረጃ እየተከታተሉ በርካታ ሃሳቦችን የሰጡኝን፣ ለደረጃ ማበልጸጊያ ተቋቁሞ ያዘጋጀሁትን power point ሳይቀር በፈቃድዎ እንዳቀርብልዎት አድገው አስተያየትዎን የለገሡኝን መቼም ጊዜ አልረሳውም፡፡ ከሌሎች ለይተው ለእኔ ያደሉ እስከሚመስለኝ ድረስ ከጎኔ ነበሩ፡፡ ዕድሜና ጤና ይስጥልኝ ከማለት በስተቀር ባደረጉልኝ ልክ ለማመስገን ቃሎች የሉኝም፡፡ ከልቤ አመሰግንዎታለሁ፡፡

ዶ/ር አጋረደች ጀማነህ እና ዶ/ር አለሙ ካሳዬ የደረጃ ማበልጸጊያ "ፈታኞቼ" ሆናችሁ መጥታችሁ ግን በፈታኝነት መንፈስ ሳይሆን እንደ አማካሪ ሆናችሁ ከፊደል ለቀማ አንስቶ እስከ ጽንሰ ሃሳብ የዘለቀ እጅግ ሂሳዊነት ያለውን ምሁራዊ አስተያየታችሁን ያለ ገደብ ስለሰጣችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፡፡

አንዱዓለም አዳል (Andu ad) አንቺ እኮ ለእኔ ልዩ ነሽ፤ ስንቅና ትጥቄ፡፡ ምነው! "አንቺ" ስልህ ቅር አለህ እንዴ? ባገራችን እኮ ጀግና አንቺ ይባላል፡፡ ታዲያ ላደረግክልኝ ሁሉ ጀግና ብልህ ምን ነውር አለው? አንዱ! በተለይ ሂሳዊ እይታህ፣ ለጊዜ ያለህ

ግምት፣ ለቅርብ ጓደኛህ ያለህ ጥንቃቄ እና ያሰብከውን ለመፈጸም ያለህ ትጋት ብዙ አስተምሮኛል፡፡ ይህ ጥናት በዚህ ጊዜ እንድገባደድ ያንተ ድርሻ ትክ የለውም፡፡ ከምስጋና በላይ የጀመርከውን እንዲያስፈጽምህ ፈጣሪ ይርዳህ፡፡

ገዛኸኝ ፀጋው አንተም ባለውለታዬ ነህ፡፡ መረጃዎች ያሉበትን ቦታ በመጠቆም፣ መጻሕፍትን ከማዋስ አንስቶ በገንዘብህ ገዝተህ እስከመስጠት ያደግክልኝ ውለታ ቅንነትህን ነግሮኛል፡፡ በደረቅ ሌሊት ሳይቀር እየደወልክ ስታበረታታኝ የነበረውን ሁሉ አልረሳውም፤ አመሰግናለሁ፡፡

ዶ/ር ስለሺ አባተ፣ አቶ ሰይድ ይማም እና አቶ መስፍን ፈቃዴ ጥናቴን በደስታ ተቀብላችሁ አንብባችሁ ከጠበቅኩት ጊዜ ፈጥናችሁ ስትመልሱልኝ እጅግ ኮራሁባችሁ፡፡ ጊዜያችሁን ሰውታችሁ፣ ታግሳችሁ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡ ዶ/ር አስናቀ ታረቀኝ፣ አንተም ከባለውለታዎቼ ውስጥ ስለሆንክ እግዚአብሔር ይባርክህ፡፡

መረጃ አቀባዮቼና ረዳት መረጃ ሰብሳቢዎቼ (ጋሻው አቢ፣ አስፋው ዓሊ፣ አብዱ ሃሰን፣ ልዑልሰገድ አሰፋ) የእናንተን እርዳታ በምንም አልተምነውም፡፡ ተባባሪነታችሁ፣ ቅንነታችሁ እና ሰው አክባሪነታችሁ አሁንም ከዓይኔ ላይ አለ፡፡ ፈጣሪ እናንተን ባይጥልልኝ ምን ላደርግ እችል እንደነበረ አሁን ሳስበው ይጨንቀኛል፡፡ የምፈልገውን ሁሉ ሰጥታችሁ፣ “በጎደለ ምን ቀረህ” እያላችሁ ያላችሁን ስላካፈላችሁኝ እግዚአብሔር ይስጥልኝ፡፡

አሌክስ! እኔማ ያለ አንቺ ማን አለኝ፡፡ የስኬቴ ምንጭ ሁሉ አንቺው ነሽ፡፡ ከመጀመሪያ ዲግሪ አንስቶ እስካለሁበት ደረጃ ድረስ ታግሶ እንደ አንቺ ማን ያስተምረኝ ነበር፡፡ ጊዜው ሲቆጠር እኮ ብዙ ነው፡፡ ብቻሽን ልጆቻችንን አሳድገሽ፣ ቤታችንን መርተሽ፣ ባልቴት ጡረሽ፣ የቤቱንም የውጭውንም አንዷ ብዙ ሆነሽ ይሄው እዚህ ደረስሽ፡፡ በርታ! ከማለት በስተቀር ቅር ሳይልሽ እኔን እዚህ ማድረስሽ ክብሩ ያንቺ ብቻ ነው፡፡ አሌክስ! ላንቺ “አመሰግናለሁ” ማለት አይበቃም፡፡ ግን የችሎታ ጉዳይ ሆነና ውለታሽ ልቦናዬ ውስጥ እየተንገዋለለ ማውጣት አቅቶኝ በዚሁ ተገታሁ፡፡

ልጆቼ ሎዛ፣ አብነት፣ ናታኒም እና ሄራኒ እንደ እናታችሁ ባጠገባችሁ ተገኝቼ የአባትነቴን ባለመወጣቴ ይቅርታ አድርጉልኝ፡፡ ለትዕግስታችሁ በጣም አመሰግናለሁ፡፡ ለፍሬ ብቁልኝ፡፡

## ለእንግሊዝኛ ቃላት የተሰጡ አቻ የአማርኛ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሁሉአቀፍነት | Universality |
| ሃቲታዊ ትንተና | discourse analysis |
| ሃገረሰባዊ ልማዶች | social folk customs |
| ህንድ አውሮፓውያን | Indo-European |
| ሥርዓተ ጾታ | Gender |
| ሥርዓተ ጾታዊ ኢፍትሃዊነት (አድልዎ) | Gender inequality |
| ሥነህይወታዊ | Biological |
| ቀዳማይ ምንጮች | primary source |
| ቅጥንብር | Pattern |
| የባህል ዝግመተ ለውጥ | Cultural evolution |
| የቤተሰብ ተረቶች | House hold tales |
| ተግባራዊ ብያኔ | operational definition |
| ንጥረ ጭብጥ | motif |
| አስተማስሎ | Representation |
| አባዊ | Patriarchal |
| አዝግሞታዊ ፈለግ | Evolutionary theory |
| እንስታዊ | Feminism |
| እንስታዊ ፖለቲከኞች | political Feminists |
| አይነታዊ ምርምር | Qualitative research |
| ካልዓይ ምንጮች | Secondary source |
| ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ | Conceptual frame work |

## ሙዳየ ቃላት

| | |
|---|---|
| ለከት (ከ) ትጠብቃለች) | ጥቢኛ፣ አነስተኛ ዳቦ |
| ልቅ ይሁንብኝ | ይወሰድብኝ (በውርርድ) |
| መወስለት | ሚስት በባሏ ላይ ሌላ ወንድ ወይም ባል በሚስቱ ላይ ሌላ ሴት በስርቆት ይዘው ሲገኙ፣ ባለገ/ባለገች እንደማለት ነው። |
| ሙካሽ | የወርቅ ክርን ወይም ወርቃማ ክርን ከሌሎች የተለያየ ቀለም ካላቸው ክሮች ጋር በመቀላቀል በካባና በሌሎች መሰል የክብር ልብሶች ላይ እየተወሳሰበ የሚሰራ ጌጥ |
| መቆያ | በምሳ እና በእራት መካከል የሚበላ አነስተኛ መጠን ያለው ምግብ፣ መክሰስ፣ የእራት መዳረሻ |
| ማንሰሻ (ማሰሻ) | የሚጋገር እንጀራ ከምጣዱ እንዲለቅ ቀደም ብሎ የሚቀባ፣ ከኑግ፣ ከጎመንዘር፣ ከሱፍ፣ ወዘተ ከመሳሰሉት የቅባት እህሎች ተቆልቶና ተወቅጦ የሚዘጋጅ፣ ከቅባት እህሎቹ የተዘጋጀው “ማንሰሻ” ምጣዱ ላይ የሚቀባበት ጨርቅ አንዳንድ ጊዜ በዚሁ ስም ይጠራል፤ ብዙውን ጊዜ ግን “ማሰሻ ጨርቅ” ይሉታል። ጨርቁ ቅባት ሲጠግብ ጥቁር ይሆናል። |
| ሰለሰለ | ቀጠነ፣ መነመነ፣ |
| ሰፋ (ፋ) ትላላች | ጠንካራ የበረሃ እንጨት፣ ለብትር የሚያገለግል |
| ስሃ | እንከን፣ ችግር፣ ስህተት፣ ሳካ (ሳንካ) |
| ስትር | በባሏ/በሚስቱ ብቻ ተወስና/ተወስኖ የምትኖር/የሚኖር፣ ለባሏ/ለሚስቱ የታመነች/የታመነ |
| ቀመ[በ]ኛ | ልብስ የሚበላ ከብት |
| ቅጥንብር | የታወቀ የአሰራር ቅደም ተከተል፣ ቅጥ፣ ሂደት |
| ቆጥ | ከመሬት ከፍ ብሎ በቤት ውስጥ የሚሰራ ባህላዊ አልጋ |
| ቡይት | ከገንቦ ከፍ ከእንስራ አነስ የሚል የሸክላ እቃ፣ በአብዛኛው ለጠላ መያዣ የሚውል |
| የባቄላ ወፍጮ | ምስጢርነት የሌለው፣ ሊደብቁት የማይቻል፣ ማንም የሚሰማው |
| አቦሬ | አፈ ሰፊ የሆነ ትልቅ ሸክና፣ ለጠላ ማንሻና ማቅረቢያ የሚውል |
| አንባባ | ስሪያ የፈለገ ወጠጤ እንስቷን በአፍና በእግሩ እየቧጠጠ በመጮህ |

| | |
|---|---|
| | ለስሪያ ጎተጎተ፣ አነሳሳ |
| አይቻል | ቦረና ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የአካባቢ ስም |
| አጠፌታ | ለተፈጸመ በደል ወይም በጎ ስራ ተገቢ መልስ መስጠት ወይም ማድረግ፣ ብድርን መመለስ፣ ማካካስ |
| እናትያ | የእንጀራ እናት |
| ከስብ | የእርሻ ስራ |
| ኩስኩስት | ከሸክላ የሚሰራ፣ ለውሃ ማሞቂያ የሚያገለግል፣ የጀበና ቅርጽ ያለው እቃ |
| ውስ! | የጥጃ ማባረሪያ ንግግር ነው፡፡ ለድመት "ብስ!"፣ ለፍየል "ክስ!"፣ ለዶሮ "እሽ!" ወዘተ. እንደሚባለው |
| ዱግ | የሹም ወኪል ወይም የበታች ሹም (ቀደም ባለው ጊዜ) |
| ግመሬ | ትልቅ አውራ ዝንጀሮ፣ መንጋውን የሚመራ |
| ፈላሚ | በቀብር ቁፈራ ጊዜ ቁፈራውን የሚጀምረው ሰው፣ በጾታው ወንድ የሆነ የሟች የቅርብ ዘመድ |

# አጠቃሎ

*ይህ ጥናት "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል የተሰራ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ ግላዊና አካዳሚያዊ ገጠመኞች የገፋፉ ሲሆን እነዚሁ አነሳሽ ምክንያቶች በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች እንዴት ተሰናስለው እንደቀረቡ በዝርዝርና በጥልቀት ማሳየት ለሚለው የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ምክንያት ሆነዋል።*

*ጥናቱ ዓይነታዊ ምርምር ሲሆን መዋቅራዊ ግልጋሎታዊ፣ ድኅረ መዋቅራዊ እና እንስታዊ ንድፈ ሃሳቦችን ተከትሏል። ለጥናቱ ያገለገሉ መረጃዎች ከመስክ ከደቡብ ወሎ ሦስት ወረዳዎች (ተሁለደሬ፣ ኩታበርና ቦረና) በቃለመጠይቅ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ በመጠይቅ እንዲሁም ከሰነዶች በጥልቅ ንባብ ተሰብስበዋል። እነዚህ መረጃዎች በመዋቅራዊ ግልጋሎታዊ እና በሃቲታዊ ትንተና ስልት ተጠንተዋል። በዚህ መሰረት ወንዶችና ሴቶች በተረቶች ውስጥ ምን ዓይነት ገጽታ እንደተሰጣቸው፣ ወንዶች በሴቶች ላይ ያላቸውን የሃብትም ይሁን የሥልጣን የበላይነት በተረቶች ለማስቀጠል የተቀሙባቸው ሥልቶች እና የሴቶች ብርታት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተወከሉባቸው ተረቶች በስፋት ተዳስሰዋል።*

*ሥርዓተ ጾታዊ አድልዎ ሰፊ የባህል መሰረት እንዳለው፣ ይህም በተረቶች ውስጥ ተሰናስሎ እንደቀጠለ ጥናቱ ጠቁሟል። እንዲሁም በተረቶች ውስጥ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን እርስ በርስ መስተጋብር ያላቸው መሆኑ በጥናቱ ተገኝቷል። አባዊው ዓለም ሥልጣኑን ለማስቀጠል ይመቹኛል ያላቸውን ለምሳሌ አጥፊ ባላቸው ሴቶች ላይ ቅጣት በመሰንዘር፣ የሴቶችን ገጽታ በማበላሸት፣ የሰናይና የእኩይ ሴቶችን ገጠመኝ ከነውጤቱ በማቅረብ፣ የራሱን ገጽታና አስፈላጊነት ከፍ አድርጎ በማሳየት ወዘተ. በሴቶች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር፣ ይህም በወንድ የበላይነት የተሰራው አባዊው መዋቅር ከነርዕዮተዓለሙ በተረቶች ውስጥ ተሰናስሎ መቅረቡ ታውቋል።*

*ሆኖም ተረቶች የሴትን ከወንድ እኩል አለመሆን ለማሳየት ተብለው ቢተረኩም ከእንስታውያን ፈለግ አንጻር ሲታዩ ሴቶች ብልሆች፣ መፍትሄ አመንጪዎች፣ ለማወቅ ከፍ ያለ ጉጉት ያላቸው መሆናቸውን ወዘተ. ጥናቱ አሳይቷል።*

*ይህ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊነት በሂደት እንዲስተተካከል ብሎም እንዳይቀጥል የሴቶችን በጎ ገጽታ የሚያጎሉ ተረቶች እየታተሙ በየትምህርት ቤቶች በስፋት ቢሰራጩ፣ በሥርዓተ ጾታ እኩልነት ጽንሰ ሃሳብ ዙሪያ ለሴቶችም ለወንዶችም እኩል ሥልጠና ቢሰጥ፣ የሥርዓተ ጾታ የእኩልነት ጽንሰ ሃሳብ በራስ ባህል ቢቃኝ፣ የሴቶችን ኢኮኖሚያዊ አቅም ለመገንባት ቢሞከር፣ ወዘተ. የሚሉ ይሁንታዎች ተሰንዝረዋል።*

# ማውጫ


| ርዕስ | ገጽ |
|---|---|
| ምስጋና | I |
| ለእንግሊዝኛ ቃላት የተሰጡ አቻ የአማርኛ ቃላት | III |
| ሙዳየ ቃላት | IV |
| አጠቃሎ | VI |
| ማውጫ | VII |

## ምዕራፍ አንድ

| | |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| 1.1 የጥናቱ ዳራ | 2 |
| 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት | 11 |
| 1.2.1 ግላዊ ገጠመኞች | 11 |
| 1.2.2 አካዳሚያዊ ገጠመኝ | 12 |
| 1.3 የጥናቱ ዓላማ | 14 |
| 1.3.1 የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ | 14 |
| 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች | 14 |
| 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት (ጠቀሜታ) | 15 |
| 1.5 የጥናቱ ወሰን | 17 |
| 1.6 በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሄዎች፣ ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎችና የተገኙ ጥሩ ልምዶች | 19 |
| 1.6.1 በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች | 20 |
| 1.6.2 በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች | 21 |
| 1.6.3 በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙ ጥሩ ልምዶች | 22 |

## ምዕራፍ ሁለት፡- የደቡብ ወሎ ዞን አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊና ማኅበረ ባህላዊ ገጽታ


2.1 የደቡብ ወሎ ዞን አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊና የሥነህዝብ ሁኔታ _______ 24

2.2 የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ የዘር ሃረግ አመጣጥ፣ አሰፋፈር እና ማኅበራዊ ገጽታ _______ 26

2.2.1 የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ የዘር ሃረግ _______ 26

2.2.2 የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ አሰፋፈር _______ 28

2.2.3 የደቡብ ወሎ ዞን ማኅበረሰብ ማኅበራዊ ገጽታ _______ 30


## ምዕራፍ ሦስት፡- የአጠናን ሥነዘዴ


3.1 ንድፈ ሃሳባዊ መሰረቶችና የመተንተኛ ስልቶች_______ 35

3.2 የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና ሥነምግባራዊ ታሳቢዎች _______ 43

3.2.1 የመረጃ አሰባሰቡ ሥርዓትና ቅደም ተከተል _______ 43

3.2.1.1 የቤተመዛግብት መረጃዎች አሰባሰብ ሥርዓትና ቅደም ተከተም_ 43

3.2.1.2 የመስክ መረጃዎች አሰባሰብ ሥርዓትና ቅደምተከተም _______ 44

3.2.2 ለጥናቱ ያገለገሉ የመረጃ ዓይነቶች _______ 45

3.2.2.1 የመስክ መረጃዎች _______ 45

3.2.2.2 የቤተመዛግብት መረጃዎች _______ 46

3.2.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ _______ 46

3.2.3.1 ቃለ መጠይቅ _______ 47

3.2.3.2 ተተኳሪ የቡድን ውይይት _______ 48

3.2.3.3 የቤተ መዛግብት ዳሰሳ _______ 48

3.2.3.4 “መጠይቅ” _______ 49

3.2.4 የምርምር ሥነምግባር _______ 50

## ምዕራፍ አራት፡- ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፎች እና የቀደምት ስራዎች ቅኝት

4.1 የተረት፣ የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ትርጉምና ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፎች _ 52
4.1.1 የተረት ትርጉም፣ ጽንሰ ሃሳብ እና አገልግሎት ________ 52
4.1.2 የሥርዓተ ጾታ ትርጉም ________ 59
4.1.3 የሥልጣን ትርጉም ________ 60
4.1.4 የሥርዓተ ጾታ ጽንሰ ሃሳብ እና ከሥልጣን ጋር ያለው መስተጋብር __ 61
4.2 ሥርዓተ ጾታ እና ሥልጣን ከባህል አንጻር ________ 69
4.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ________ 80

## ምዕራፍ አምስት፡- "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" ትንተና ________ 91

5.1 የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብር ከሴቶችና ከወንዶች ገጽታ አንጻር ________ 92
5.1.1 ብልህነት እና ሞኝነት ________ 99
5.1.2 ጭካኔ እና ርኅራኄ ________ 100
5.1.3 ምስጢራዊነት እና የባቂላ ወፍጮነት ________ 109
5.1.4 ታማኝነት እና ከሃዲነት ________ 113
5.1.5 ውሸታምነት እና እውነተኛነት ________ 115
5.1.6 አዛዥነት እና ታዛዥነት ________ 122
5.2 አባዊ ሥርዓቱ ሴቶችን ከሥልጣን ለማግለል የተጠቀመባቸው ስልቶች ____ 127
5.2.1 የሴቶች አሉታዊ ገጽታ ________ 128
5.2.2 ቅጣት ________ 131
5.2.3 ሰናይ ሴቶችን በአርዓያነት ማቅረብ ________ 134
5.2.4 እኔን ያየህ ተቀጣ________ 138
5.2.5 የወንድን አዎንታዊ ገጽታና አስፈላጊነት ማጉላት ________ 140
5.2.6 የሴቶችን ፍላጎትና ባህሪ ማጉላት ________ 146
5.3 የሴቶች አዎንታዊ ገጽታዎች ሃቲታዊ ትንተና ________ 152
5.3.1 በቀጥታ የቀረቡ አዎንታዊ ገጽታዎች ________ 153
5.3.2 በአንድምታ የወጡ አዎንታዊ ገጽታዎች ________ 159

## ምዕራፍ ስድስት፡- ማጠቃለያና ይሁንታ

6.1 ማጠቃለያ ________________________________ 165

6.2 ይሁንታ ________________________________ 169

ማጣቀሻዎች ________________________________ 173

አባሪዎች________________________________ 186

አባሪ 1 የተረቶች ስብስብ________________________________ 186

ሀ. ከጥናታዊ ጽሑፎች የተሰበሰቡ ተረቶች ________________ 186

ለ. ከመስክ የተሰበሰቡ ተረቶች ________________________ 207

ሐ. ከተረት መጻሕፍት የተሰበሰቡ ተረቶች ________________ 251

አባሪ 2 የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ________________________ 282

አባሪ 3 ለተተኳሪ የቡድን ውይይት የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች __________ 286

ሀ. ለወንድ ተተኳሪ ቡድን ተወያዮች የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች ____ 286

ለ. ለሴት ተተኳሪ ቡድን ተወያዮች የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች _____ 287

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

ባህል ከሚጠናባቸው መስኮች ውስጥ አንዱ ፎክሎር ነው፡፡ በመሆኑም ፎክሎር የአንድን ማኅበረሰብ መንፈሳዊና ቁሳዊ ሃብቶቹን አካትቶ ይይዛል፡፡ እነዚህ ሃብቶች የፎክሎር ንዑሳን ክፍሎች በሆኑት በሥነቃል፣ በሃገረሰባዊ ልማድ፣ በቁሳዊ ባህል እና በሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት ይገለጻሉ፡፡ ይህ ጥናት የሥነቃል ክፍል በሆኑት ተረቶች ላይ ትኩረቱን አድርጎ "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል ርዕስ የተጠና ነው፡፡ ጥናቱንም ከግብ ማድረስ ይቻል ዘንድ በሚከተለው አደረጃጀት ቀርቧል፡፡

ጥናቱ በሰባት ምዕራፎች ተከፍሎ የተሰራ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ (በተረት ላይ የተደረጉ ቀደምት ጥናቶች እንዲሁም ሥርዓተ ፆታ በፎክሎር ውስጥ ምን መልክ እንዳለው የሚያሳዩ ምርምሮች ባጭሩ የተዳሰሱበት)፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ዓቢይና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን ከቦታና ከርዕሰ ነገር አንጻር፣ በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች፣ ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎችና የተገኙ ጥሩ ልምዶች ቀርበዋል፡፡

ሁለተኛው ምዕራፍ የመስክ መረጃዎች በተሰበሰቡበት በደቡብ ወሎ ዞን አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊና ማኅበረ ባህላዊ ገጽታዎች ላይ አተኩሮ ቀርቧል፡፡ በዚህም የዞኑ አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ የሥነህዝብ ሁኔታ፣ የማኅበረሰቡ የዘር ሃረግ አመጣጥ፣ አሰፋፈር እና ማኅበራዊ ገጽታ ተዳስሰውበታል፡፡

ምዕራፍ ሶስት በዓቢይነት የያዘው የአጠናን ሥነዘዴ ነው፡፡ ይህ ክፍል ጥናቱ ስለተከተላቸው ንድፈ ሃሳቦችና የመተንተኛ ስልቶች፣ የጥናቱ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልቶች፣ አጥኚው የተከተላቸውን ሥነምግባሮች አካትቷል፡፡

ምዕራፍ አራት "ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፎችና የቀደምት ስራዎች ቅኝት" በሚል የጥናቱ ቁልፍ ቃላት በሆኑት ተረት፣ ሥርዓተ ጾታ እና ሥልጣን በሚሉት ላይ ትርጉማዊና ጽንሰሃሳባዊ ትንታኔ ተደርጎበታል፡፡ ከዚህም ባሻገር እነዚሁ ቁልፍ ቃላት እርስ በርሳቸው ምን ዓይነት መስተጋብር እንዳላቸው ከመስኩ ምሁራን ሃሳብ አንጻር ተዳስሰዋል፡፡ በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ በኢትዮጵያ ባሉ ባህሎች ውስጥ ሥርዓተ ጾታ

እንዴት እንደተስተናገደ፣ ብሎም ከዚህ ቀደም የተደረጉ ጥናቶች ተዳስሰው ከጥናቱ ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ከተገለጸ በኋላ የዚህ ጥናት አዲስነት ተጠቁሟል፡፡

ምዕራፍ አምስት የጥናቱ ዓቢይ ክፍል ሲሆን ከመስክና ከሰነዶች የተገኙ መረጃዎች ትንታኔ የተሰጠበት፣ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን በተረት ውስጥ ህብር ስለመፍጠራቸው የተረጋገጠበት ክፍል ነው፡፡

ምዕራፍ ስድስትም ከትንተናው የተገኙት ዋና ዋና ጉዳዮች የሰፈሩበት እና ውጤቱን ተከትሎ ይሁንታዎች የቀረቡበት ነው፡፡

በመጨረሻም ይህንን ጥናት ለማካሄድ የረዱ ለንባብነት የተመረጡ መጽሐፎች፣ መጽሔቶችና የጥናት መጣጥፎች፣ ያልታተሙ የጥናት ስራዎች በዋቢነት፣ እንዲሁም የተረቶች ዝርዝር በአባሪነት ተካተዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ባህል ከሚጠናባቸው መስኮች ውስጥ አንዱ ፎክሎር ነው፤ የባህልም አንዱ የማሳያ መንገድ ነው፡፡ ፎክሎር በስሩ የተለያዩ ዘርፎች አሉት፡፡ እነዚህም ሥነቃል፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሃገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሃገረሰባዊ ልማድ ናቸው (Dundes 1965፣ Dorson 1972፣ oring 1986)፡፡ ሥነቃል በበኩሉ በርካታ ንዑሳን ዘርፎች አሉት፡፡ ከነዚህ ውስጥ ቃላዊ ትረካዎች (oral narratives) በሚል በጥቅል የሚጠሩት ሚት፣ አፈታሪክ እና ተረት ተጠቃሾች ናቸው፡፡ በመሆኑም ዳራው እነዚህን ቃላዊ ተረኮች የተመለከተ ይሆናል፡፡

የቃላዊ ተረክ[1] ጥናት በዓለም አቀፍ ደረጃ ቆየት ያለ መሆኑን ድርሳናት ያሳያሉ፡፡ በዚህ ጥናት ሁሉንም ማካተት ስለማይቻል በተወሰኑት ነጥቦ ላይ ብቻ የትኩረት ቅኝት

[1] ቃላዊ ተረኮች እንደየባሉሙያዎቹ የተለያየ ምደባ ተደርጎላቸዋል፡፡ ገና ከመነሻውም በአመዳደብ መስፈርቱ ላይ ተመሳሳይ ግንዘቤ የለም፡፡ ብዙዎቹ የሚስማሙበት ግን ቃላዊ ተረኮች ከበቀሉበት ማኅበረሰብ አንጻር ታይቶ አካባቢያዊ ምደባ መደረግ አለበት ይላሉ፡፡ ሆኖም ግን ብዙ የተሰራበትና ሁሉም አጥኚ ማለት ይቻላል አውቆም ይሁን ሳያውቅ ምደባውን ወደ Bascom (1965) የምደባ ስልት (Myth, Legend and Folktale) ራሱን ያስጠጋል፡፡ የአገራችንን የቃላዊ ተረክ አጥኚዎች አመዳደብ ስንመለከት ስያሜያቸው ይለያይ እንጂ ከዚህ አይወጡም፡፡ ለምሳሌ Bayleyegn (1999) የአኙዋክን ተረቶች ሊሬ፣ ዋኤ እና አንጋዴ፤ Yihenew (1996) የምዕራብ ጎጃምን ተረቶች አፈታሪክ፣ ተረትና ዘር ቆጠራ፤ Sahilu (1996) የቦረና ተረቶችን ዱሪ ዱሪ፣ ማማክሳና አርጋጌቲ፣ Abreham (2000) የጅማ ኦሮሞ ተረቶችን ሴና፣ ኡዱ ዱሪና ቆሳ፣ አማረ (2001) የሸካቾ ተረቶችን በመጀመሪያ ኬሞና ኢንጌሞ ብለው በሁለት ቢከፍሉም አመዳደቡ እንደማያስኬዳቸው ሲረዱ የኦክፔሁ የተረት አከፋፈልን

ተደርጓል፡፡ ታሪካዊ ቅኝቱ የተደረገው በየዘመናቱ የተደረጉ ጥናቶችን በመንተራስ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አጥኚው ያደረገው ቅኝት ውስን ነው፡፡

ቃላዊ ተረኮች ተፈጠሩ የሚባሉበትን የዘመን ግምት ስናስብ እጅግ ሩቅ ነው፡፡ ከዛሬ 3000 ዓመት በፊት ጀምሮ ነበሩ ለማለት ይቻላል (Dundes 1965፡221)፡፡ የዕድሜያቸውን ርዝመት ያህል ስለእነሱ የተደረገው ጥናት ግን ቀደምት የሚባል አይደለም፡፡ የታሰበበት ደንበኛ ጥናት (serious study) መደረግ የተጀመረው በ19ኛው ምዕተ ዓመት እንደሆነ Okpewho (1992:5) ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም ግን የቀደሙት ጥናቶች ከነድክመታቸው ለዛሬዎቹ የበሰሉ ጥናቶች መነሻ ናቸውና እነሱኑ መጥቀስ አስፈላጊ ነው፡፡

ከቀዳሚዎቹ ጥናቶች ውስጥ በመጀመሪያ ደረጃ የምናገኘው በ1812 እ.ኤ.አ `Kinder-und Hausmarchen` በሚል ርዕስ በግሪም ወንድማማቾች ተጠንቶ ለህትመት የበቃውን ነው፡፡ የወንድማማቾቹ ጥናት ከጀርመን በተሰበሰቡ የቤተሰብ ተረቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን ውጤታቸውም ጀርመናውያንን የታላቁ የህንድ አውሮፓውያን ዝርያ ቅርንጫፍ ነን የሚል ማጠቃለያ ላይ እንዲደርሱ አድርጓቸዋል (ፈቃደ1991፡34፣ Dundes1965:222)፡፡ ይሄ ጥናት በቀዳሚነቱና በአርዓያነቱ ለብዙ የቃላዊ ተረክ አጥኚዎች መነሻ ቢሆንም ሶስት መሰረታዊ ችግሮች እንደነበሩበት የመስኩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ችግሮቹ የሚመነጩት ወንደማማቾቹ አጥኚዎች የሰበሰቧቸውን ተረቶች ከ3000 ዓመት በፊት የነበሩና አሁንም ያሉ፣ ከጥንታዊው የህንድ አውሮፓውያን በቃል ተወራርሰው የመጡ ናቸው ከሚለው ነው፡፡ አባባላቸው አሁን የተፈጠረ ተረት የለም፤ ሁሉም ከላይ ከተጠቀሰው ዘመን በፊት የተፈጠሩ ናቸው[2] የሚል ነው፡፡

---

ተጠቅመው አፈታሪክ፣ ገላጭ ተረት እና ተረት በሚል በሶስት ከፍለዋቸዋል፡፡ የሁሉም አጥኚዎች ምደባ በሶስት የተወሰነ ነው፡፡ በእያንዳንዱ ምድብ ስር ያሉ ቃላዊ ተረኮችን ስንመለከታቸው (ስማቸው ይለያይ እንጂ) ከሚት፣ ከአፈታሪክና ከተረት የሚወጡ አይደሉም፡፡ ከእነዚህ ጥናቶች ስንነሳ አንድ ዓለማቀፋዊ የሆነ የተረት አመዳደብ ስልት የለም ብሎ ለመደምደም ይከብዳል፡፡ ዞሮ ዞሮ ግን ይህንን ጥያቄ መመለስ የሚቻለው በመስኩ ሰፊ ጥናት በማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ ጥናት አቅራቢ ቃላዊ ተረክ ሲል Myth, Legend እና Folktale ማለቱ ነው፡፡

[2] ግሪም ወንድማማቾች ይህንን ያሉት ከእነርሱ ቀደም ብሎ የተደረገው የቋንቋ ጥናት ቋንቋቸው ከህንድ አውሮፓውያን ቋንቋዎች ጋር ግንኙነት እንደነበረው ከመታወቁ ጋር ይያያዛል፡፡ የቋንቋው ጥናት የህዝቦችን ግንኙነት ወደ 3000 ዓመት ያርቀዋል፡፡ በሌላ በኩል ተረት ዓለማቀፋዊ ጭብጥ ያለው መሆኑን በወቅቱ ባለመገንዘብ ተረቶቻቸው ከህንድ አውሮፓውያን ተረቶች ጋር በጭብጥ ተመሳስሎ

እንዲህ ዓይነቱ አቋም ደግሞ አንደኛ በየጊዜው ተረኮች ሊፈጠሩ መቻላቸውን ከቁብ አልቆጠረም፡፡ በመሆኑም ያገኟቸውን ተረቶች ሁሉ ዕድሜያቸውን ወደኋላ የመውሰድ አዝማሚያ ታይቶባቸዋል (Dundes1965:219)፡፡ ሁለተኛም ተረቶች የባህልንና መልክዓ ምድራዊ ድንበር አልፈው በሌሎች ባህሎችና አካባቢዎች ውስጥ ሊገቡ መቻላቸውን እንዲሁም የተረት መበዳደር እንዳለ ሳይገነዘቡ ተረቶችን ሁሉ የእኛ ናቸው የማለት አዝማሚያ አላቸው፡፡ በሶስተኛ ደረጃ የሚነሳባቸው ሙግት ህንድ አውሮፓውያን ያልሆኑ በእነርሱ ውስጥ ከመገኘታቸው ጋር የተያያዘ ነው፡፡ በጀርመን ውስጥ የህንድ አውሮፓውያን ዘር የሌላቸው ነገር ግን ጀርመን ውስጥ የሚኖሩ አሉ፡፡ እነዚህ ህዝቦች ደግሞ የራሳቸው ባህል ያላቸው በመሆናቸው እንደሌላው ህዝብ ባህላቸውን የሚገልጹበት የራሳቸው ቃላዊ ተረክ ሊኖራቸው መቻላቸውን አለመገመታቸው ነው፡፡ በመሆኑም የሌሎችንም ጠቅልሎ የእኛ ናቸው እስከማለት ደርሰዋል፡፡ ፈቃደ (1991፡35) Okpewho (1992)ን ጠቅሰው ሲያስረዱ ወንድማቾቹ በአፍሪካ ውስጥ የሚነገሩ ተረቶች በአውሮፓ ከሚነገሩት ጋር ከተመሳሰሉ የታላቁ የህንድ አውሮፓዊ ቅርንጫፍ ተደርገው ወይም ከእነርሱ የተወሰዱ ሆነው መቆጠር አለባቸው ማለታቸውን አውስተዋል፡፡ ይህም በዓለም ላይ ያሉትን ተረቶች አጠቃሎ ወደ አንድ ምንጭ የመውሰድ አዝማሚያ ያለው ጥናት መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ የወንድማማቾቹ ጥናት እንደመጀመሪያነቱ ድክመቶች ቢኖሩበትም ለብዙ ሙግትና ለሌላ ጥናት እንደመነሻ ሆኖ ያገለገለ በመሆኑ በቃላዊ ተረክ ጥናት ታሪክ ከፍ ያለ ግምት የሚሰጠው ነው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በቃላዊ ተረክ ጥናት ታሪክ ውስጥ ጠቃሚ ጥናት ተደርጓል የሚባለው በ1859 እ.ኤ.አ በ Benfey አማካኝነት በህንድ ስብስብ ተረቶች (panchatantra) ላይ የተደረገው ነው (Dundes 1965:225)፡፡ Benfey የህንድ ተረቶች በአንድ ወቅት ህንድ ውስጥ ተፈጥረው ከዚያም ተተርጉመው በሥነጽሑፍና በቃል ወደ መላው አውሮፓ መሰራጨታቸውን መግለጻቸውን Sydow (1965) ን ዋቢ አድርገው Dundes (1965:225) ጠቁመዋል፡፡ ሆኖም የጥናቱ መላምታዊ ማጠቃለያ ከስህተት ላይ እንደጣላቸው እኚሁ ጸሃፍት ያስረዳሉ፡፡ ይህም Benfey እዚህ ማጠቃለያ ላይ ከመድረሳቸው በፊት

---

ሲያገኙት በግንኙነታችን ዘመን የተፈጠሩ ስለሆነ ነው ወደሚል ማጠቃለያ ደረሱ፡፡ ይህም አዲስ ተረት የለም አስብሏቸዋል፡፡

ተሰብስበው ካገኟቸው ተረቶች ባሻገር ካገራቸው ብሎም በመላው አውሮፓ ያሉ ተረቶችን ሳይሰበስቡ በመቅረታቸው ነው (Dundes 1965:225-228)።

ሌላው ከሥነመዋቅር (Structuralism) ፈለግ አንጻር የተጠናው መጀመሪያ በራሽያ ቋንቋ በ1928 ቀጥሎ በ1958 ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎመውን የVladímir Proppን "Morphology of The Folktale" እናገኛለን። ጥናቱ ከቀደሙት ጥናቶች በዓይነቱ የተለየ ነው። Dundes በ1997 "Binary Opposition in Myth: The Propp/Levi-Strauss Debate in Retrospect" ብለው ባወጡት መጣጥፍ ላይ propp በ1928 "Morphology of the Folktale" በሚል ያጠኑት በዓይነቱ ፋና ወጊ እንደሆነ Bravo (1972)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ። ፋና ወጊ የተባለበትም ምክንያት ከዚህ ጥናት በፊት ከሥነመዋቅር አንጻር የተደረገ ጥናት ባለመኖሩ ነው። በተለይ ደግሞ የተረትን ቅርጻዊ መዋቅር በመተንተን ላይ አተኩሮ በመሰራቱ ፋና ወጊ ተብሏል። በዚህ መዋቅራዊ ትንተና Propp የራሽያ ተረቶች 31 "ሁነቶች" (Functions)[3] የሚስተዋሉባቸው እንደሆነ በዝርዝር አጥንተው አሳይተዋል። ጥናታቸውን አንድ መቶ በሚሆኑ የራሺያ ተረቶች ላይ ካካሄዱ በኋላ ሁሉም የራሺያ አድባሬ ተረቶች (fairy tales) አንድ ዓይነት መዋቅር እንዳላቸው ለማረጋገጥ ችለዋል (Dundes 1986:122)። ይሄ ጥናት እንደ አርዓያ ሆኖ የተለያዩ የፎክሎር ባለሙያዎች በተለያዩ የሥነቃል ዘርፎች ላይ መዋቅራዊ ትንተና እንዲያካሂዱ ረድቷል። በተለይም Lévi-Strauss (1969) እና Dundes (1964, 1980, 1986, 1989, 1997) የእርሱን ፈለግ በመከተል በተለያዩ የሥነቃል ዓይነቶች ላይ እንዳጠኑ ስራዎቻቸው ያስረዳሉ።

በተለይ Dundes ከሥነመዋቅር አንጻር በርከት ያሉ ስራዎችን አከናውነዋል። በ1986 "Structural Typology in North American Indian Folktales" በሚል ባቀረቡት ጥናት ውስጥ ተረቶችን ከሥነመዋቅር አንጻር ማጥናት በተረቶች ላይ የዓይነት ምደባ ለማድረግ፣ የተረቶች ይዘት በባህሉ ውስጥ መኖሩን ለማረጋገጥ፣ የባህል ለውጥ በምን መልኩ ሊከሰት እንደሚችል ለመገመት፣ ተረቶችን ከሌሎች ተረቶች እና ከሌሎች

[3] እዚህ ላይ "ሁነቶች" የተባሉት በተረት ውስጥ ያሉ ቅደም ተከተላዊ ክንውኖችን ነው። ቅደም ተከተሎቹ ዝምድና ያላቸው ሆነው አንዳቸው ለአንዳቸው ምክንያት ወይም ውጤት የሆኑ ናቸው። ሁነቶች የተረቱ ዓቢይ ገጸባህሪ ደረጃ በደረጃ የሚፈጽማቸው ድርጊቶች ናቸው (Scott 1968፡8)። እነዚህን የተረት ቅደምተከተላዊ ሁነቶችን Propp "Functions" በሚል መሰየማቸውን Dundes (1997፡39) ገልጸውታል። Dundes እነዚህን "ሁነቶች" Motifeme በሚል ከሰየሟቸው በኋላ በማጠቃለል ወደ 10 ዝቅ አድርገዋቸዋል (Bronner 2007:123)። በ Scott (1968፡12-45) የትርጉም ስራም ውስጥ Propp በራሽያ ተረቶች ውስጥ አሉ ያሏቸውን 31 "ሁነቶች" ዘርዝረዋቸዋል።

የፎክሎር መልኮች ጋር ለማነጻጸር እና በሌሎች አገሮች ያሉ ተረቶችን ለማጥናትና ተመሳሳይ መዋቅር መኖሩን ለመፈተሽ እንደሚያገለግል ጠቅሰዋል (1986፡129)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ጥናቶች ተከትሎ የምናገኘው በታዋቂው አሜሪካዊ የተረት ተመራማሪ Stith Thompson በ1955 ዓ.ም "Motif index of Folk Literature" በሚል የተሰራውን ጥናት ነው፡፡ Thompson የተረቶችን የተለያዩ ጭብጦች በማውጣት ቀዳሚ የምደባ ስራ አከናውነዋል፡፡ ጥናቱ የተሰራው ከታሪካዊ መልክዓ ምድራዊ ንድፈሃሳብ አንጻር በመሆኑ ተረቶችን በንጽጽር ተመልክተዋል፡፡ በጥናቱም በተለያዩ ማኅበረሰቦች ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸው ተረቶች ከተገኙ እነዚያ ማኅበረሰቦች በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ ይገኛሉ ማለት ነው የሚለውን የአዝግሞታውያንን[4] ንድፈሃሳብ በመንቀፍ ምክንያቱን ተረቶች በአንድ የታሪክ አጋጣሚ ከአንድ ቦታ ተነስተው ወደተለያዩ አካባቢዎች ስለተሰራጩ ነው የሚል ሃሳብ ሰንዝረዋል (Finnegan 1970:321)፡፡

Finnegan (1970:322) የThompsonን የጥናት ውጤት መነሻ አድርገው እንዳስገነዘቡት በአፍሪካ ውስጥ በተደረጉ የቃላዊ ትረካ ጥናቶች ላይ ተጽዕኖ በማሳደሩ ምክንያት አብዛኞቹ አፍሪካዊ ጥናቶች በቃላዊ ተረኮች ውጫዊ ባህሪያት ላይ እንዲያተኩሩ አድርጓል፡፡ አጥኚዎቹ ከተራኪዎች የፈጠራ ብቃት፣ ከተረኮቹ ትርጉማዊ ሚና እና ማኅበራዊ ጠቀሜታ ይልቅ በስርጭትና ምደባ ላይ እንዲወሰኑ አድርጓል፡፡ Okpewhoም (1992:6) ይህንኑ ይጋራሉ፡፡

በአፍሪካ በየጊዜው የተደረጉ በርካታ የሥነቃል ምርምሮች አሉ፡፡ ሰፊ ጥናት በማድረግ የሚታወቁት Finnegan የተባሉት እንግሊዛዊት ተመራማሪ ናቸው፡፡ Finnegan "Oral Literature in Africa" በሚል በ1970 ዓ.ም የታተመ ጠንካራ ጥናት አድርገዋል፡፡ ጥናቱ ሰፊ ከመሆኑ አንጻር በርካታ ጉዳዮች የተካተቱበት ነው፡፡ ይህ ጥናት በአፍሪካ የሥነቃል ጥናት ምን መልክ እንዳለው ከማሳየቱም በላይ ቃል ግጥም፣ ቃላዊ ተረክ፣ ምሳሌያዊ

---

[4] የንድፈሃሳቡ ቀዳሚ አቀንቃኞች Lewis Henry Morgan እና B.F Tylor ናቸው፡፡ የንድፈሃሳቡ ማዕከላዊ ማጠንጠኛ ባህል እጅግ በጣም ዝቅተኛ ከሆነ ደረጃ ወደ እጅግ በጣም ከፍተኛ ወደሆነ ደረጃ (from lower savagery stage to civilized stage) አንድ መስመር(unilineal directional) ይዞ በተመሳሳይና ተጠየቃዊ በሆነ ሂደት (uniform and logical process) የሚያድግ ነው የሚል ነው (McCormick and White 2001፡458)፡፡ በመሆኑም በተለያዩ ባህሎች ውስጥ ባሉ ሥነቃሎች መካከል የቅርጽና የይዘት ተመሳሳይነት ከተገኘ ማኅበረሰቦቹ በተመሳሳይ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ናቸው የሚል ነው፡፡

አነጋገሮች፣ እንቆቅልሾችና ሌሎች የሥነቃል ቅርጾችን በተመለከተ ሰፊ ጥናት የተደረገበት የምርምር ስራ ነው፡፡

በአፍሪካ ሥነቃል ላይ ምን ተሰርቷል ብለን ስንነሳ የተሻለ መረጃ የምናገኘው ከላይ ከተጠቀሱት ባለሙያ የምርምር ስራ ነው፡፡ በአፍሪካ ሥነቃል ላይ ጥናት መደረግ የተጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ ነው (ፈቃደ 1991፡27፣ Finnegan 1970፡27)፡፡ ይህ ማለት ግን ቀደም ብሎ ጥናቶች አልተደረጉም ማለት አይደለም፡፡ Roger በ1828 ዓ.ም በሴኔጋል የዎሎፍ ጎሳ ፋቡላዎች ላይ ጥናት ማድረጋቸውን Finnegan ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ግን በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛ አጋማሽ በርከት ያሉ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ Finnegan (1970፡28) በግርጌ ማስታወሻቸው እንዳሳዩት እ.ኤ.አ. ከ1841 እስከ 1903 ዓ.ም ባሉት አመታት ከ17 ያላነሱ ስራዎች[5] መቅረባቸውን አስረድተዋል፡፡ በእነዚህም ስብስቦች ውስጥ እንስሳትንና ሰዎችን የተመለከቱ ትረካዎች፣ ታሪካዊ ትረካዎች፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ እንቆቅልሾች፣ እንዲሁም አልፎ አልፎ መዝሙሮችና ግጥሞች ተሰብስበዋል፡፡

ይሁንና ጥናቶቹ በቋንቋ ላይ ትኩረት ያደረጉ ስለነበሩ ሥነቃሎችን ከአውዳቸው፣ ከአከዋወናቸውና ከሥነጽሑፋዊ ዋጋቸው አንጻር ሲታዩ እምብዛም እንደነበሩ አጥኚዋ ያስረዳሉ፡፡ ሆኖም ግን የአፍሪካ ህዝብ ሥነቃልዊ ሃብት ያለውና ሰው ስለመሆኑ እውቅና የሰጡ ነበሩ፡፡ ለምሳሌ (Finnegan 1970፡29) Koelle (1854:vi-vii)ን እና Chatelain (1894:20)ን ጠቅሰው ሲገልጹ፡- “. . . the negro too was capable of producing works which manifests depth of feeling and artistry and showed him to be human in the fullest sense of the world?” በማለት አስረድተዋል፡፡

አውሮፓውያን ቀደም ሲል ስለ አፍሪካ ጥቁር ህዝብ ያላቸውን ዝቅተኛ አስተሳሰብ በትንሹም ቢሆን መቀየር የጀመሩት ሥነቃሉን በማጥናታቸው ነው፡፡ በዚህም የተነሳ በሥነቃል ላይ የሚደረገውን ጥናት ከፍተኛ ግምት እንዲሰጠው ያደርገዋል፡፡

[5] Finnegan (1970፡28) በግርጌ ማስታወሻቸው Curtin (1965)ን እና Greenburg (1965)ን ጠቅሰው በአፍሪካ ሥነቃል ላይ አጠኑ ያሏቸውን የውጭ አገር ተመራማሪዎች ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም፡- Casalis (1841)፣ Koelle (1854)፣ Schlenker (1861)፣ Burton (1865)፣ Bleek (1864)፣ Callaway (1868)፣ Steere (1870)፣ Christaller (1879)፣ Feraud (1885)፣ Schon (1885)፣ Theal (1886)፣ Jacottet (1895፣1908)፣ Taylor (1891)፣ Chatlain (1894)፣ Junod (1897)፣ Dennett (1898) እና Velten (1907) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ የተደረገውን የሥነቃል ጥናት Finnegan (1970:324) ሲያጠቃልሉ ቀደም ያሉት በአፍሪካ ሥነቃል ላይ የተደረጉት ጥናቶች አፍሪካዊ ባልሆኑ ልሂቃን (intellectuals) የተከናወኑ በመሆናቸውና የተከተሉትም ንድፈ ሃሳብ የራሳቸውን ሥነቃሎች መሰረት ያደረገ በመሆኑ የአፍሪካውያንን ምናብ (native imagination) አያሳይም ሲሉ ይወቅሳሉ፡፡ አስከትለውም የተሰበሰቡት ሥነቃሎች ወደ እንግሊዝኛ ሲቀየሩ የተራኪዎችን ስሜት በትክክል ስለመወከላቸው ማረጋገጫ አለመኖሩን አስረድተዋል፡፡

ከ19ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ግን አፍሪካዊ ምሁራን በራሳቸው ቋንቋ የራሳቸውን ባህል ማጥናት መጀመራቸውን ፈቃደ (1991፡38) ጠቁመዋል፡፡ በተለይም kagame (1945)፣ Niketia (1955)፣ Babalola (1964)፣ Kuneni (1971)፣ Amoonor (1974) እና Cark (1977) ያደረጓቸው ጥናቶች ተጠቃሽ መሆናቸውን Okpewho (1992)ን ጠቅሰው ያስረዳሉ፡፡

ከኢትዮጵያ የሥነቃል ጥናት ታሪክ ጋር በተያያዘ አጥኚው በመረጃ ምንጭነት የተጠቀመው Fekade (2001) "The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect" በሚል በኢትዮጵያ ጥናት መጽሄት ያወጡትን የምርምር ስራ ነው፡፡

ቀደምቱ የኢትዮጵያ ሥነቃል ጥናት የተከናወነው በሦስት አካላት ነው፡፡ እነዚህም አንደኛ በውጭ አገር ተጓዦች፣ አሳሾችና ሚሽነሪዎች፣ ሁለተኛ በኢትዮጵያውያንና በውጭ አገር ሰዎች በቅንጅት እና ሶስተኛ በኢትዮጵያውያን ነው (Fekade 2001፡44-54)፡፡ ቀደም ያሉት ጥናቶች የተደረጉት በበርካታ የውጭ አገር ሰዎች ሲሆን ጥናታቸውም በሰዋሰውና በመዝገበ ቃላት ዝግጅት ላይ እንዲሁም ሥነቃሎችን ሰብስቦ በማሳተም ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥናቶች ለሃይማኖት ስብከት አመቺ የሆኑ ሥነቃሎች የተካተቱባቸው ናቸው፡፡ በእንዲህ ዓይነት መልክ የተሰሩት ጥናቶች በ19ኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ በአውሮፓውያን ጆርናሎችና መጽሄቶች ለመታተም በቅተዋል (Fekade 2001፡49)፡፡ በእነዚህ አጥኚዎች የተሰራው ሥነቃሎችን ሰብስቦ ከማሳተም ያላለፈ ነው፡፡ በዚህ ቡድን ውስጥ ከሚካተቱት የተለየ ቦታ የሚሰጣቸው Ignazio Guidi ናቸው፡፡ ይህም ከሌሎች በተለየ መልኩ ለስብስቦቻቸው መግለጫ መጨመራቸው ነው፡፡ የቃል ግጥሞቹ ከማን እንደተሰበሰቡ፣ በምን ሁኔታ እንደተነገሩ

እና ለማን እንደተገጠሙ መግለጫ ጨምረዋል፡፡ ስራው ከመሰብሰብ ባሻገር የጥናት ምልክት የታየበት በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

በሁለተኛው ቡድን የምናገኛቸው በውጭ አገር አጥኚዎችና በኢትዮጵያውያን በቅንጅት የተሰሩትን ነው፡፡ ከነዚህ ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት Mittwoch እና አለቃ ታዬ በ1911 ዓ.ም "Abyssinian stories and fables"፣ Mittwoch እና ብላቴን ጌታ ኅሩይ "Native tales of Abyssinia" በሚል በ1925 የሰሯቸው ተጠቃሽ የቃላዊ ተረክ ጥናቶች ናቸው (Fekade 2001:50-51)፡፡ ከዚህም በተጨማሪ Cherulli ከተለያዩ ኢትዮጵውያን ጋር እና Klingenheben ከወልደማሪያም ደስታ ጋር ሥነቃልን ማጥናታቸውን Fekade (2001) ገልጸዋል፡፡

በሦስተኛው ቡድን ውስጥ የሚካተቱት ኢትዮጵያውያን አጥኚዎች ናቸው፡፡ ከላይ እንደተጠቀሱት ሁሉ ኢትዮጵያውያንም የሥነቃል ስብስቦቻቸውን ለህትመት አብቅተዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሱት ማህተመ ስላሴ ወ/መስቀል (1960)፣ ሃጂ የሱፍ አብዱራህማን (1948)፣ ካሳው ወርቅነህ (1952)፣ አበበ አይቸህ (1948)፣ መንግስቱ ለማ (1953)፣ ልዑልሰገድ ዓለማየሁ (1955)፣ ከበደ ሚካዔል (1960)፣ ደበሱ አበበ (1956)፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ናቸው፡፡ እነዚህ አጥኚዎች እንደቀደሙት ሁሉ ሰብስቦ ከማሳተም ያለፈ ስራ አለመስራታቸውን Fekade (2001:59) አስረድተዋል፡፡

ከዚህ በተረፈ ለህትመት ያልበቁ በርካታ የሥነቃል ምርምር ስራዎችን እናገኛለን፡፡ እነዚህን በተመለከተ ዋና ዋና የተባሉትን በተለይም በቃላዊ ተረክ ላይ ያተኮሩት በተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ስር በስፋት ቀርበዋል፡፡

የዚህ ጥናት ዓቢይ ጉዳይ በተረት ውስጥ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን እንዴት ተሰናስለው እንደቀረቡ ማሳየት ነው፡፡ በዚህም ረገድ በዓለም ላይ የተደረጉ ጥናቶችን መቃኘት ያስፈልጋል፡፡ ይሁንና ተረት ከሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ጋር ተገናዝቦ በዓለም ላይ፣ በአፍሪካ፣ ብሎም በኢትዮጵያ ጥናት መደረጉን የሚያሳዩ አጥጋቢ መረጃዎች አልተገኙም፡፡ የተገኙት ጥቂት ማስረጃዎች እንደሚያሳዩት በፎክሎር ውስጥ ሥርዓተ ጾታን ማጥናት የተጀመረው እጅግ ውስን በሆነ መልኩ እ.ኤ.አ በ1920ዎቹ ነው (Sawin 2011:612)፡፡ በተለይም በግንባር ቀደምትነት የሚታወቁት ጥናቶች የMark Azadovskii (1926) "The influence of gender on tale-tellers repertoire and performance

choices"፣ የMargaret Mead (1935) "Extreme cultural variability in gender roles in tribal societies" እና የ Simone de Beauvoir (1953) "Philosophical exploration of the way women have been defined as ''not man" በሚል የተሰሩት ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ጥናቶች በ1960ዎቹ አካባቢ ለተነሳው እንስታዊ ፖለቲካ (political Feminism) እንዲሁም በ1970ዎቹና 1980ዎቹ በፎክሎርና በሌሎች የትምህርት መስኮች ለተከሰተው የእንስታውያን ስኮላርሽፕ (Feminist scholarship) እንደ ዓይነተኛ ምክንያት ይጠቀሳሉ (Sawin 2011:613)፡፡ በጠቅላላው በፎክሎር በተለይ በተረት ውስጥ ሥርዓተ ጾታ አቢይ ጉዳይ ሆኖ መጠናት የተጀመረው በ1960ዎቹና 1970ዎቹ የእንስታውያን እንቅስቃሴ[6] ሲነሳ ነው፡፡ የጥናቶች ዋና ትኩረት የነበረው የምዕራባውያንን አድባሬ ተረቶች መተንተን ሆኖ በተለይ የሴቶችን ድርጊት ከሰይጣን ድርጊት ጋር በሚያያይዙት እንዲሁም ሴቶች ለሥልጣን ተገቢ አይደሉም የሚል ጭብጥ ባላቸው ተረቶች ላይ የተደረጉ ነበሩ፡፡ በወቅቱ ተሰብስበው የተቀመጡ ተረቶች ለምሳሌ የ Stith Thompson 'Motif-Index of Folk-Literature' ወንድን ከፍ ሴትን ዝቅ አድርገው የሚያሳዩ ናቸው (Ragan 2009፡227-228)፡፡ ይህ አስተሳሰብ በአንዳንድ ቀደምት ተረት ሰብሳቢዎችና አጥኚዎች የተረጋገጠ እውነት (proven truth) ተደርጎ መወሰዱ ተከታዮቹ አጥኚዎች በእያንዳንዱ ተረት ላይ በጥልቀት እንዲመራመሩ እንዳደረጋቸው Ragan ከላይ በተገለጹት ገጾች ጠቅሰውታል፡፡

ከላይ የጥናቱ ዳራዊ መነሻ በጥቅሉ የቃላዊ ተረኮች ጥናት ታሪክ ምን መልክ እንዳለው ተመላክቷል፡፡ በጠቅላላው የቃላዊ ተረኮች ጥናት በ1812 እ.ኤ.አ ተጀምሮ ደረጃ በደረጃ በይዘት፣ በቅርጽ፣ በአጠናን ስልትና በንድፈ ሃሳብ ጎልብቷል፡፡ አዳዲስ የአተያይ ስልቶችም እየተለመዱ መጥተዋል፡፡ ቃላዊ ተረኮችን ብቻቸውን ከማጥናት አልፎም

[6] በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስለ ሥርዓተ ጾታ እኩልነት ያቀነቀኑት Christine de Pizan (እንስት ናቸው) ሲሆኑ ዘመኑም በ1405 ነበር፡፡ ሃሳባቸውን "The Book of the City of Ladies" በሚል በታተመው ሥራቸው ሲገልጹ "በሴቶች ላይ የሚደረገው ጭቆና ምንም ዓይነት ተጨባጭነት በሌለው ነገር ላይ የተመሰረተ ነው"(http://www.nyu.edu/classes/jackson/causes.of.gender.inequality/) ብለዋል:: ከዚሁ ድረገጽ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በሰሜን ምዕራብ እንግሊዝ ይኖሩ የነበሩት Quaker አንድ አካል የሆኑት Shakers ወደ አሜሪካ በ1774 ከመሰደዳቸው በፊት የሥርዓተ ጾታን እኩልነት ተቀብለው ተግባራዊ በማድረግ ቀዳሚዎች እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ በኋላም እነዚሁ ቡድኖች የነበራቸውን አቋም እንዳለ ይዘው አሜሪካ ከገቡ በኋላ 1778 አካባቢ Joseph Meacham (head of the Shakers' central ministry) ሴትና ወንድ እኩል መሆን አለባቸው በሚል ጽኑ አቋም አንዲት ሴት (Lucy Wrigh) መርጠው የአስተዳደሩ መዋቅር አካል በማድረግ ሹመዋል፡፡

ከሥርዓተ ጾታና ከሥልጣን ጋር አስተባብሮ መመልከት መለመዱ የጥናት መስኩ እየዳበረ መምጣቱን ያሳያል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አቅራቢ "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል ርዕስ ዙሪያ ለማጥናት የገፋፉት ዓቢይ ምክንያቶች አሉት፡፡ እነዚህም የግል ገጠመኞቹ እና በትምህርት ላይ ሳለ ያስተዋላቸው ናቸው፡፡

### 1.2.1 ግላዊ ገጠመኞች

አጥኚው፣ ከሥርዓተ ጾታ እኩልነት ጋር በተያያዘ፣ ሁለት ያህል ገጠመኞች አሉት፡፡ የመጀመሪያው በ2004 ዓ.ም ወሎ ዩኒቨርሲቲ በማስተማር ላይ እያለ ያጋጠመው ነው፡፡ ይሄውም ከአንዲት የዩኒቨርሲቲው የፋይናንስ ባለሙያ ጋር ምሳ እየበላ ሳለ (አሁን በምን አጋጣሚ ጉዳዩ እንደተነሳ ባያስታውስም) ስለሴትና ወንድ እኩልነት ይነሳል፡፡ ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ እኚሁ የፋይናንስ ባለሙያ ከራሳቸው ገጠመኝ በመነሳት የሥርዓተ ጾታን እኩልነት ለማምጣት ያለውን አስቸጋሪ ሁኔታ ሃሳብ ይዘነዝራሉ፡፡ ጉዳዩ እንዲህ ነው፡፡ ባለሙያዋ በአንድ ወቅት የሥርዓተ ጾታ ሥልጠና ይወስዳሉ፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ የሥርዓተ ጾታ አሰልጣኙ ወንድ ነበር፡፡ አሰልጣኙ በርካታ የማሳመኛ ነጥቦችን አቅርበው ሥልጠናውን ይሰጣሉ፡፡ በዚህም በሁሉም ሰልጣኞች ዘንድ "ለመጀመሪያ ጊዜ የሴትና ወንድ እኩልነት የገባው ወንድ ተገኘ" የሚል ስሜት ያድርባቸዋል፡፡ በዚህ መሃል ባለገጠመኟ ከአሰልጣኙ ጋር የበለጠ ቅርርብ ይፈጥራሉ፡፡ ቅርርባቸው ያድግና ወደ ፍቅር ከዚያም ወደ ትዳር ያስገባቸዋል፡፡ በፍቅራቸው ወቅት የነበረው እንክብካቤ፣ መተሳሰብና የእኩልነት መንፈስ ከሥልጠናው ብዙም ያልተለየ ነበር፡፡ ወደ ትዳር ከገቡ በኂላ ግን የነበረው ሁሉ ተቀይሮ ባለቤታቸውን ፍጹም አባዊ (Patriarchal) ሆነው ያገኟቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ዋሸኸኝ በሚል ስሜት ምክንያቱን ይጠይቁታል፡፡ እሳቸውም "እንጀራና ህሊና በጣም ይለያያሉ፤ በሥልጠናው ላይ የተናገርኩት መስሪያ ቤቴን ሆኜ እንጂ እኔን ሆኜ አይደለም፡፡ ስለዚህ አንቺም እንደ ሴትነትሽ እኔም እንደ ወንድነቴ ሆነን መኖር አለብን" የሚል ምላሽ እንደሰጧቸው ለአጥኚው አውግተውታል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በአጥኚው ህሊና አንድ ጥያቄ ሲመላለስበት ቆይቷል፡፡ ይህም አሰልጣኙ ተጠየቃዊ ሆነው ማሰልጠን የቻሉትን ጉዳይ ህሊናቸው ለምን አልተቀበለውም? ይህንን እንዳያደርጉ ልቡናቸውን የከለከለው ምን

ዓይነት ዳራዊ ሁኔታ ቢኖር ነው? የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ አደረገው፡፡ ይሄው ሃሳብ በተረት እንዴት እንደተንጸባረቀ የማወቅ ጉጉት ፈጠረበት፡፡

ሁለተኛው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት አጥኚው በቤቱ የገጠመው ነው፡፡ የአጥኚው የግል ባህሪ ሊሆን ይችላል ባለቤቱን በተለይ በልማድ "የሴት ሥራ" ናቸው የሚባሉትን እንደ ልብስ ማጠብ፣ ምግብ ማብሰል፣ አልጋ ማንጠፍ ወዘተ. የመሳሰሉትን ስራዎች ያግዛታል፡፡ ይሄንን ህሊናውም ያምናል፡፡ ሆኖም ግን ይህንን እየሰራ እንዳለ እንግዳ ከመጣ ስራውን እንዳይሰራ ባለቤቱ ትከለክለዋለች፤ እሱንም ደስ አይለውም፡፡ ድንገት ደራሽ እንግዳ እንዳይተቸው ይፈራል፡፡ ባለቤቱም የመከልከሏ ምክንያት ይሄው ነው፡፡

አጥኚው ከባለቤቱ ጋር ሰርግ በተጠራበት አጋጣሚ ባለቤቱ ገንዘብ ከቦርሳዋ አውጥታ በስሟ ለማስመዝገብ ፈጽሞ ፈቃደኛ አይደለችም፡፡ ምክንያቷ "አንተ ወንዱ ተቀምጠህ እንዴት እኔ ሴቷ አስመዘግባለሁ?" የሚል ነው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ አጥኚውና ባለቤቱ ከላይ የተጠቀሰውን እንዳያደርጉ የከለከላቸው ምንድን ነው? የሚል ነው፡፡

አጥኚው ከዚሁ ከሰርግ ጋር በተያያዘ ሌላም ገጠመኝ አለው፡፡ ጥር 30/2007 ዓ.ም በአንድ የቅርብ ዘመዱ ሠርግ ላይ የገንዘብ ተቀባይ ፀሃፊ ሆኖ ነበር፡፡ ወደ ሰርጉ ከመጡት ከሚያውቃቸው ባለትዳር ሴቶች ውስጥ የራሳቸውን ስም አስመዝግበው ገንዘብ የከፈሉ ሴቶች አላጋጠመውም፡፡ ሁሉም የባሎቻቸውን ስም አስመዝግበው የከፈሉ ናቸው፡፡ አንዲት ሴት ብቻ የእርሷንና የባሏን ስም (እንደ አበበና አበበች ዓይነት) ያስመዘገበች አጋጥሞታል፡፡ ይሄ ቀደም ብሎ የተጠቀሰውን ሃሳብ ያጠናክራል፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢ ከላይ የጠቀሳቸውን ሁለት የግል ገጠመኞቹን እና አስተውሎቶቹን ይዞ ሲነሳ ምክንያቱን ከባህል ውስጥ እንዲያወጣ ፍላጎት አደረበት፡፡ እንደሚታወቀው ፎክሎር ባህልን በመረጠው ዘዴ ወክሎ የሚያስቀምጥ በመሆኑ ይህንን ውክልና የፎክሎር ዘርፍ በሆነው ሥነቃል በተለይም በተረት ውስጥ አፈላልጎ የማግኘትና ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ የመመርመር ፍላጎቱን አነሳስተውታል፡፡

## 1.2.2 አካዳሚያዊ ገጠመኝ

ሁለተኛው የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት አካዳሚያዊ ነው፡፡ ይህም አጥኚው በ2006 ዓ.ም የመጀመሪያው ወሰነ ትምህርት ላይ "Advanced Seminar in Folklore and Development (Folk 804)" የተባለውን ኮርስ ሲወስድ ለኮርሱ ማሟያ "ከ1945-1955 ዓ.ም በታተሙ

የተረት መጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ልማት ነክ ተረቶች ስብሰባ፣ ክልሰፋና ትንተና" በሚል አንድ የኮርስ ማሟያ ወረቀት አቅርቦ ነበር፡፡ ይህንን ጥናት ሲሰራ እግረመንገዱን ካቀረባቸው ስድስት አስተውሎቶች ውስጥ ሶስቱ ምርምር ቢደረግባቸው ቁም ነገር ይወጣቸዋል የሚል እምነት ነበረው፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ ለዚህ ጥናት እንደ መነሻ ሆኖታል፡፡ ይህም የሚከተለው ነው፡፡

አጥኚው ባነበባቸው አብዛኞቹ የተረት መጻሕፍት ውስጥ ዝሙት ገንኖ ይሰማል፡፡ ዝሙተኛ ተደርጋ የምትቆጠረውም ሴቷ እንጂ ወንዱ አይደለም፡፡ በሰፊው ተንሰራፍቶ የሚታየው አመለካከት ዝሙት በሴት ከሆነ ነውር፣ በወንድ ከሆነ ጀግንነት ወይም ገድል ባይሆን እንኳ የማያስነቅፍ መሆኑ ነው፡፡ በተረቶቹ ውስጥ እንደሚታየው አንዲት ሴት ባሏ በውጭ ሌላ ሴት ቢይዝባት ባሏን ወደ ራሷ ስለምትመልስበት መንገድ ማሰብ፣ ሌሎችን ማማከር፣ ጥና ሲልም አዋቂ (መላ አመላካች) እስከመጠየቅ ትደርሳለች እንጂ በባሏ ላይ ክፉ ፊት እንኳን ስታሳይ አትስተዋልም፡፡ በጣም ገፍታ ከሄደች ልታኮርፍ ትችላለች፡፡ በዚህ ረገድ የሴቷ ጉብዝና የሚለካው ባሏን ወደ ቤቱ የመለሰችበት ጥበብ ነው፡፡ በአንጻሩ ባል ሚስቱ ሌላ ወዳጅ እንደያዘች ካረጋገጠ እንደ ሴቷ በዘዴ ለመመለስ ሲጥር በፍጹም አይታይም፡፡ አንድ ዘዴ ፈጥሮ ዝሙተኛ ያላትን ሚስቱን ሲደበድባት፣ ሲገድላት ወይም ሃብት ንብረቷን ቀምቶ በራሷ ጊዜ ተመርራ እንድትጠፋ ሲያደርጋት ይታያል፡፡ ባል በእነዚህ ተረቶች ውስጥ የታገሰበት አጋጣሚ አይስተዋልም፡፡ ይህ ለአጥኚው ባህሉ ለወንድ ቅድሚያውን ሰጥቶ እሱኑ የተንከባከበበትና የሚንከባከብበት እንደሆነ ተሰማው፡፡ እንደዚህ ዓይነት ስር የሰደዱ ተረቶች ባንድ በኩል የወንዱን የበላይነትና ባለብዙ መብትነት ያረጋገጡና እውቅና የሰጡ፣ በሌላ በኩል የሴቶችን ሥነልቡና ክፉኛ ጎድተው ደፍረው እንዳይናገሩ፣ መብታቸውን እንዳይጠይቁና በራስ የመተማመን መንፈሳቸውን አሳጥተዋቸው ይሆን እንዴ በሚል አሰበ፡፡

ከላይ የተነሱት ነጥቦች በጥቅሉ ሲታዩ ዓለምን በሁለት ጎራ (ወንድነትና ሴትነት) የከፈሉ ናቸው፡፡ በክፍፍሉ ውስጥም *የሥርዓተ ፆታ አድልዎ* (Gender inequality) እና *የሥልጣን የበላይነት* (power domination) ጥያቄ እንዳለባቸው አጥኚው ተገነዘበ፡፡ በመሆኑም የሥነቃል አንዱ ክፍል የሆኑት ተረቶች እንደምን የዚህ ማስፈጸሚያ እንደሆኑ፣ የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብር በተረቶች ውስጥ እንዴት ተሰናስሎ እንደቀረበ የማወቅ ጉጉት የጥናቱ መነሻ ሆነውታል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

ይህ ጥናት "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል የተሰራ ነው፡፡ አጥኚው ይህንን ርዕስ ይዞ ሲነሳ ከግብ ሊያደርሳቸው የሚፈልጋቸው ዓላማዎች አሉት፡፡ እነዚህም አቢይና ዝርዝር ዓላማ በሚል እንደሚከተለው ሰፍረዋል፡፡

### 1.3.1 የጥናቱ አቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት አቢይ ዓላማ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች በተረቶች ውስጥ እንዴት ተሰናስለው እንደቀረቡ በዝርዝርና በጥልቀት ማሳየት ነው፡፡

### 1.3.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡

- ወንዶች ከሴቶች በተለየ መልኩ ከፍ ያለ ማህበራዊ ቦታና ሥልጣን እንዴት እንደተሰጣቸው፣ ያም ማህበራዊ ቦታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ በማድረግ ሂደት ውስጥ የተረቶችን አስተዋጥኦ ምን እንደሚመስል መመርመር፣
- የሥርዓተ ጾታና ማኅበራዊ ሥልጣን መስተጋብር ምን እንደሚመስል መመርመር፣[7]
- ማኅበረሰቡ የሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮችን ለማስረጽ ተረቶችን እንዴት እንዴት እንደሚጠቀም መመርመር፣
- የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ይጋፋሉ ከተባሉት ተረቶች በስተጀርባ ያለውን "እውነታ"[8] ተንትኖ ማሳየት ናቸው፡፡

[7] ንዑስ ዓላማውን መሰረት አድርጎ ዳሰሳ የሚደረግበት ባህል ነው፡፡ ይህህን ከሥርዓተ ፆታ አያያዝ አንጻር በአገር ደረጃ ብንመለከተው የሰፋ ልዩነት አያሳይም፡፡ ባብዛኛው ሴትን ዝቅ ወንድን ከፍ የሚያደርግ በመሆኑ መመሳሰሉ አለ፡፡ በመሆኑም በሰፊው ከኢትዮጵያ አንጻርም ይሁን አጥብበን በአንድ ወረዳ ብንዳስሰው ልዩነት አያመጣም፡፡ እንዲያውም በባህል በኩል ያለውን ሥርዓተ ጾታዊ አያያዝ በሰፊው መመልከት የሥርዓተ ጾታ አያያዛችን በተባለጥ ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ በርካታ ማሳያዎችን ለማቅረብ ይረዳናል፡፡ ሁለተኛ ነገር ለጥናቱ የተሰበሰቡት ተረቶች ከደቡብ ወሎ ሶስት ወረዳዎች ብቻ የተገኙ አይደሉም፡፡ በቤተመዛግብት ካሉ የተረት መጻሕፍት እና ከጥናት ወረቀቶችም ጭምር ተሰብስበዋል፡፡ የተረት መጻህፍቱም ሆኑ ጥናቶች በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸው ዳሰሳው ከኢትዮጵያ አንጻር ለመደረጉ ምክንያት ሆኗል፡፡

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት (ጠቀሜታ)

ይህ ጥናት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ባህል ልደቱም ሞቱም እጅግ ዘገምተኛ ነው፡፡ ባህልን በአንድ ጊዜ መፍጠርም ማጥፋትም አይቻልም፡፡ በሌላ በኩል ባህል ከባለቤቶቹ ውስጥ የሚጎዳውም[9] የሚጠቅመውም ይኖራል፡፡ ስለዚህ "ተጎጂው" የባህልን ዝግመተ ለውጣዊ ባህሪ ተገንዝቦ ለጊዜው በመታገስ እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ በተለይ ሴቶች ያለባቸውን የሥርዓተ ጾታ አድልዎ በመታገስና ስልታዊ ሆነው በሂደት እንዲታገሉት ሊያስገነዝባቸው ይችላል፡፡ ለምሳሌ Kabaji (2005:7) የ Chodorow (1978) ን ሃሳብ አጣቅሰው ሲገልጹ "femininity is not a way of being that a girl deliberately decides to assume; rather it is a slow, gradual process that seizes the psyche of a girl before she is self-consciously aware of herself as a girl" ብለዋል፡፡ እዚህ ላይ ልጃገረዷ የሴትነት ባህሪን የተላበሰችው ሆን ብላ በአንድ ጊዜ ሳይሆን በረጅም ጊዜ አብራ በመኖር ነው፡፡ አባዊ ሥርዓቱም ቢሆን አሁን ባለበት መልኩ ለመዋቀር የበቃው ቀላል የማይባሉ ዘመናትን የፈጀ ሂደት አሳልፎ ነው፡፡ Hierro and Marquez (1994፡174) ይህንኑ "The 'formation of patriarchy' did not come into being 'all of a sudden,' but instead it was a process that developed in the course of almost 2,500 years, from 3100 to 600 B.C." ሲሉ ይገልጹታል፡፡ በዚህ ዓይነት መንገድ ህያው የሆነን ሥርዓት በአንድ ቀን ጀንበር መናድ የሚቻል አይደለም፡፡ ይህንኑ በማሰብ በሚመስል መልኩ በ1997 ዓ.ም የኢትዮጵያ

---

8 "እውነታ" ሲባል ነባራዊ ሃቅ ለማለት አይደለም፡፡ እውነታነቱ ከአጥኚው እምነት አንጻር ብቻ ነው፡፡ አጥኚው አውነታ ያለውን ሌላ ሰው በራሱ ማጠየቂያ እውነት ላይለው ይችላል፡፡ በአንዳንድ ተረቶች የሴቶችን ከወንዶች እኩል አለመሆን ያሳያሉ ተብለው ቢተረኩም በግልባጫቸው ስንመለከታቸው ሴቶች ከወንዶች በልጠው የተገኙባቸውን አጋጣሚዎች ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም "እውነታ" ሲባል ከዚህ አንጻር ብቻ ነው፡፡

9 በባህል ምክንያት የሚጎዳ አለ ስንል አንጻራዊ ሆነን ነው፡፡ በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ባህል ጎጂ አይደለም፡፡ ምናልባት ተጠቃሚ ላያደርግ ይችላል፡፡ ከዚያ ውጪ ባለቤቱ አምኖ እስከተቀበለው ድረስ ባይጠቅመውም እንኳ ጎጂ ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ማህበረሰብ በራሱ አጠይቆት የሚከተለውን ባህል ትክክል ነው ብሎ ያምናልና፤ በዚህም ምክንያት አምኖ ይቀበለዋል፤ ያከብረዋል፡፡ ሆኖም ግን ባህል ዘላለማዊ አይደለምና መሻሻል ያሳያል፡፡ ተሻሽሎ ስናገኘው ጎጂ ነበር ልንል እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ የነበረው ባህል በሁለቱም ጾታዎች ተቀባይነት ኖሮት ለዘመናት ቆይቷል፡፡ ሆኖም ግን የሰው የማሰብ አቅሙ እየሰፋና የአስተሳሰብ ለውጥ እያመጣ ሲሄድ በጾታ መለያየት ምክንያት የነበረው አድልዎ ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ እየከሰመ ይሄዳል፡፡ በመሆኑም ጎጂነቱ እየጎላ ይመጣል፤ በአዲስ ባህል ይተካል፡፡

ወጣቶች፣ ስፖርትና ባህል ሚኒስቴር ባወጣው የባህል ፖሊሲ ላይ “በሴቶችና በሙያቸው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ባህሎችን ደረጃ በደረጃ ማጥፋት” የሚል ዓላማ ነድፏል፡፡ ይሄ ጎጂ የተባለውን ባህል “ለማጥፋት” ጊዜ የሚያስፈልገው መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚያም ላይ ጠንካራ ሃይማኖታዊ መሰረት ያለው፣ በህግም እየተደገፈ የመጣ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለዚህ ሥርዓቱን በመታገስ በሂደት መስተካከል እንደሚገባው ይህ ጥናት ግንዛቤ ሊሰጥ ይችላል፡፡

- በሥርዓተ ጾታ እኩልነት ላይ የሚሰሩ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ግባቸውን ማሳካት ይችሉ ዘንድ ጥናቱ ጥቆማ ሊሰጣቸው ይችላል፡፡
- ለባህልና ለሥርዓተ ጾታ ፖሊሲ አውጭዎች፣ ለሥርዓተ ትምህርትና መማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች፣ ለሃያሲያንና ለደራሲዎች ለሥራዎቻቸው መሳካት አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል፡፡ እዚህ ላይ የጠቀስናቸው አካላት የሥርዓተ ጾታን እኩልነት ለማምጣት በሚደረገው ጥረት ሚና አላቸው፡፡ የሥርዓተ ጾታን እኩልነት ማምጣት የሚቻለው ሁሉአቀፍ ተግባራትን በሂደት በማከናወን ነው፡፡ ስለዚህ መወሰድ ካለባቸው ተግባራት ውስጥ ፖሊሲዎችን ከሥነጾታ አንጻር መቃኘት፣ የመማሪያ መጻሕፍት ቴክስቶች የጾታ እኩልነትን እንዲሰብኩ ማድረግ እና በተለያዩ የፈጠራ ጽሑፎች ውስጥ ጠንካራ ሴት ገጸባህሪያትን መሳል ይጠቀሳሉ፡፡ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን በተረት ውስጥ መስተጋብር ፈጥረው አባዊ ሥርዓቱን እድሜ እንዳቆዩት ሁሉ ፖሊሲዎች፣ ቴክስቶችና የፈጠራ ስራዎች ሥርዓቱን በሂደት ማስተካከል ስለሚችሉ ባለሙያዎች ልምድ ሊያገኙበት ይችላሉ፡፡
- ከማኅበረሰብ ጋር ትስስር ያላቸው የጥናት መስኮች ለምሳሌ እንደ የማኅበረሰብ ጥናት (Sociology)፣ ማኅበራዊ ሥነልሳን (Socio linguistics)፣ ማኅበራዊ ሥነሰብዕ (Social Anthropology)፣ ሥነጽሑፍ (Literature) ወዘተ. ለመሳሰሉት መስኮች ለጥናታቸው የመነሻ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፡፡
- በሌሎች ቋንቋዎችና ብሔረሰቦች ላይ ለሚሰሩ መሰል ጥናቶች እንደ መነሻም እንደ ግብዓትም ሊያገለግል ይችላል፡፡
- ጥናቱ በቃል እየተወራረሱ የመጡ ተረቶችን በጽሑፍ የያዘ በመሆኑ በሰነድነት ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ ከቦታና ከርዕሰ ነገር አንጻር ውስን ነው፡፡ ከቦታ አንጻር በደቡብ ወሎ ዞን ላይ ትኩረቱን አድርጓል፡፡ ሆኖም ግን ከዞኑ ስፋት፣ ከመጓጓዣ እጥረት፣ ከወጪ፣ ከጊዜ እና አጥኚው ካለው የወረዳዎች እውቂያ ውስንነት አንጻር በኢላማ ናሙና ስልት በተመረጡ በሶስት ወረዳዎች ላይ ብቻ ተገድቧል፡፡ እነዚህም ተሁለደሬ፣ ኩታበር እና ቦረና ወረዳዎች ናቸው፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ቦረና ወረዳ አጥኚው ያደገበት፣ የተማረበት እና በሥራ አጋጣሚም ለሦስት ዓመታት የሠራበት ስለሆነ፣ ተሁለደሬ ወረዳ አጥኚው ለአስር ዓመታት በመምህርነት ስለሰራበት፣እንደ እንግዳ አይታይባቸውም በሚል ነው፡፡ እነዚህን ሁለት ወረዳዎች በተለያዩ የሥራ አጋጣሚዎች ቀበሌዎችን ጭምር አጥኚው በደንብ ስለሚያውቃቸው በቦታዎች እንደልብ የመዘዋወርም ሆነ የመረጃ ሰጪ እጥረት አያጋጥመውም በሚል የተመረጡ ናቸው፡፡

ኩታበር ወረዳ ከደሴ ከተማ በቅርብ ርቀት ላይ ያለ ከመሆኑም በላይ አንደኛ በ2003 እና በ2004 ዓ.ም በቦታው ላይ የሦስተኛ ዲግሪውን ይሰራ ለነበረው ጓደኛው (አባተ ጌታሁን) ረዳት መረጃ ሰብሳቢ ሆኖ ስለቆየባቸው፣ ሁለተኛ በወሎ ዩኒቨርሲቲ በክረምቱ መርሃ ግብር ያስተማራቸው ሰልጣኞች መኖራቸውን ቀደም ብሎ ያውቅ ስለነበር አካባቢውንም የማወቅም ሆነ የመረጃ ሰጪ እጥረት አያጋጥምም በሚል ነው፡፡ ይህም በመሆኑ በሁሉም ወረዳዎች ውስጥ እንደልብ ተዘዋውሮ መረጃ ሰጪዎችንም ሆነ መረጃዎችን ለማግኘት ችሏል፡፡

በዚያ ላይ ተረት ካለው ዓለማቀፋዊ ባህሪና ይዘት[10] አንጻር እንኳን ባንድ ዞን ውስጥ ባሉ ወረዳዎች ይቅርና ባገርም በአህጉርም ቢሆን የሰፋ ልዩነት አያመጣም፡፡ ይህንኑ በተመለከተ Michael (2000:44) በብሪቲሽ ካውንስል የበጀት ድጋፍ አማካኝነት ተረቶችን ከመላው ኢትዮጵያ ሲሰበስቡ ያስተዋሉትን ሲገልጹ "I was struck by the similarities of most of the folktales in many parts of the nation. In fact some of these stories even seem international" ካሉ በኋላ Bicknell and Trotman (1988) ጠቅሰው ሃሳቡን ሲያጠናክሩ ". . . the same oral stories have a tendency to appear and reappear all over the world" ማለታቸውን ያወሳሉ፡፡ ይሄ ሃሳብ የተረትን ሁሉአቀፍነት (universality) ያሳየናል፡፡

[10] ተረት ዓለማቀፋዊ ባህሪና ይዘት ያለው መሆኑን በንድፈ ሃሳባዊ ቅኝቱ ስር ሰፋ ያለ ማብራሪያ በማስረጃ ቀርቧል፡፡ አጥኚው እዚህ ክፍል ላይ በጥቂቱ ለመግለጽ የወደደው ሃያ አንድ ወረዳዎች እንዴት በሶስት ወረዳዎች ብቻ ሊወከሉ ይችላሉ የሚል ጊዜያዊ ጥያቄ ቢነሳ ምክንያት ለማቅረብ ያህል ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ዝርዝሩን ከዚያው ክፍል ማየት ይቻላል፡፡

የተረት ይዘት አብዛኛውን ጊዜ በህገ ተቃርኖ (binary opposition) በተጣመዱ እንደ ህይወትና ሞት፣ ክፋትና ደግነት፣ ጽድቅና ኩነኔ፣ ሴትና ወንድ፣ ማግኘትና ማጣት፣ መውደቅና መነሳት፣ እምነትና ክህደት፣ ልገሳና ንፍገት፣ አለቃና ምንዝር ወዘተ. በመሳሰሉት ዙሪያ የተዋቀረ ነው። ከእነዚህ ተቃርኖ የሚገኘው ውጤት የየአካባቢውን ልማዳዊ መንፈስ (traditional ethos)፣ ደንቦች (norms) እና ልምዶች (practice) ማጠንከር ነው (Kabaji 2005:160)። በዚህ ረገድ በዓለም ላይ ያለው የሰው ልጅ አስተሳሰብና ፍላጎት ተመሳሳይ ነው። የሰው ልጅ በህገ ተቃርኖ ከተጣመዱት ውስጥ በአንጻራዊነት የትኛውን እንደሚወድም የታወቀ ነው። ከዚህ ጽንሰ ሃሳብ አንጻር ስንነሳ በደቡብ ወሎ ዞን የሚገኙ ሃያ አንድ ወረዳዎች ፍጹም የሆነ የይዘት ልዩነት ያላቸው ተረቶችን ይናገራሉ ማለት አይቻልም። አጥኚው በመስክ ቆይታ ወቅት ከሰበሰባቸው ተረቶች የተረዳው ይህንኑ የይዘት ልዩነት አለመኖሩን ነው። ከ1950ዎቹና 1960ዎቹ በፊት በየአጋጣሚው ከመስክ ተሰብስበው ለህትመት የበቁት ተረቶች ዛሬ ከመስክ ከተሰበሰቡት ተረቶች ጋር ሲተያዩ የይዘትም የቅርጽም ልዩነት የላቸውም። ልዩነት ቢኖር አልፎ አልፎ የገጸ ባህሪ ብዙውን ጊዜ ግን የአተራረክ ነው። ይህ ደግሞ ከፎክሎር ተለዋዋጭ ባህሪ አንጻር የሚጠበቅ ነው። እንዲያውም የመመሳሰላቸውን ነገር ስናስብ ከዚያን ጊዜ ወዲህ አዲስ ተረት አልተፈጠረም ያስብላል።

በሌላ በኩል የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ አንድ ቋንቋና ተመሳሳይ ባህል ያለው ነው። በሃይማኖት ረገድ ልዩነት ሳይፈጥር በባልና በሚስት ደረጃ እንኳ አንዳቸው ሙስሊም አንዳቸው ክርስቲያን ሆነው በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩበት አጋጣሚ አለ። ማኅበራዊ ተቋሞቻቸው ሳይቀሩ (እንደ እድርና የአምልኮ ቦታዎች የመሳሰሉት) በጋራ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህ ነጥቦች የሚያሳዩት ማኅበረሰቡ የሥነልቡና መቀራረብ ያለው መሆኑን ነው። ይህ የሥነልቡና መቀራረብ ደግሞ በተመሳሳይ ነገር ላይ ሊኖራቸው የሚችለውን አስተሳሰብ ያመሳስለዋል። በመሆኑም ሊናገሯቸው የሚችሏቸው ተረቶች ተመሳሳይ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ በነዚህ ተጠየቃዊ ነጥቦች ምክንያት ከመስክ የሚሰበሰቡ ተረቶች[11] በእነዚህ ወረዳዎች ላይ ብቻ የተገደበ ሆኗል።

---

[11] ለዚህ ጥናት የሚሆኑ መረጃዎችን ከመስክ መሰብሰብ ያስፈለገው በሁለት ምክንያቶች ነው። አንደኛ ይህ ጥናት በመረጃነት የቤተመዛግብት መረጃዎችን ይጠቀማል። እነዚህ መረጃዎች ደግሞ በ1950ዎቹና ከዚያም በፊት ተሰባስበው ለህትመት የበቁትን ተረቶች ይጨምራል። በነዚህ በተራራቁ ዘመናት ውስጥ የሥርዓተ ጾታ አስተሳሰብን ደፍሮ ተመሳሳይ ነው ማለት ስለማይቻል የአሁኖችን ተረቶች ከጥንቶቹ ጋር ለማስተያየትና ለውጡን ለመገንዘብ ይረዳል በሚል የተደረገ ነው። ሁለተኛ

ጥናቱ ትኩረት ያደረገው ከመስክ ከተሰበሰቡ ተረቶች በተጨማሪ ከቤተመዛግብትም በተሰበረቡ ተረቶች ላይ ነው፡፡ ከቤተ መዛግብት በተለይ ለህትመት ከበቁት በጥናቱ የተካተቱት ከ1967 ዓ.ም በፊት የታተሙት ብቻ ናቸው፡፡ ይህ የተደረገበት ምክንያት ከላይ ከተጠቀሰው ዘመን ወዲህ ለህትመት የበቁት በተለይ የተረት መጻህፍት ባብዛኛው የውጭው ዓለም ተረቶች ተጽዕኖ ያለባቸው፣ በውጭ ቋንቋ የተጻፉትን በመተርጎም ላይ ያነጣጠሩና እንደ ልቦለድና ግጥም በአንድ ደራሲ እንደ ድርሰት የተጻፉ (የህዝብ ፈጠራ ያልሆኑ) በመሆናቸው ነው፡፡ ይህንን ለማረጋገጥ የህጻናት ተረቶች ተብለው ለገበያ የቀረቡትን የተፈሪ ገዳሙን (1979፣ 1989)፣ እና የአቤ ደስታን (1999) ማየት ይበቃል፡፡ እነዚህ ተረቶች ካገራችን ተረቶች ጋር ተመሳሳይ ጭብጥና ቅርጽ ቢኖራቸውም የውጭ ተረቶች በመሆናቸው የተነሳ ያገራችንን ባህል፣ የአስተሳሰብ ደረጃና ምጣኔ ሃብታዊ ሁኔታ ተንተርሶ የተዋቀረ ታሪክ አላቸው ለማለት አያስደፍሩም፡፡ በራሳችን ባህል ተንተርሰን ዓለምን እንዴት እንዳየናት፣ ስለሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብር ያለንን አመለካከት ከእኛው ሥነልቡና አንጻር በውል ያሳያሉ ለማለት አያስደፍሩም፡፡ በመሆኑም እነዚህ የጥናቱ አካል አልተደረጉም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የመስክ መረጃን መሰረት አድርገው በቀረቡ የመጀመሪያ፣ ሁለተኛና ሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ውስጥ በአባሪ ተሰባስበው የቀረቡ ተረቶች በየትኛውም ዘመን ይሰሩ የጥናቱ መረጃ ሆነዋል፡፡ መስክን መሰረት አድርገው የተሰበሰቡ ተረቶች በቀጥታ ከባለቤቶቹ የተገኙ ስለሆኑ አገርኛነታቸው ያመዝናል፡፡ በአጠቃላይ ከታተሙት መጻህፍት፣ ካልታተሙ የጥናት ወረቀቶችና ከመስክ ከተሰበሰቡት ውስጥ በይዘታቸው ከሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብር ጋር ብቻ የተያያዙት ተመርጠው የጥናቱ አካል ተደርገዋል፡፡

## 1.6 በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፣ የተወሰዱ መፍትሄዎች፣ ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎችና የተገኙ ጥሩ ልምዶች

በዚህ ስር አራት ነጥቦች ተነስተዋል፡፡ እነዚህም በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች፣ ለእነዚህም ችግሮች በማቃለያነት የተወሰዱ እርምጃዎች፣ ያልተጠበቁ ጥሩ

---

የተረቶች ትርጉምና የመነገር ምክንያት በባለቤቶቹ መረጋገጥ ስላለበት፣ ተረቶችምን ሲተርኩ ስሜታቸውን ለመገንዘብ ያስችላል በሚል ነው፡፡ በተረት ስብሰባውም ወቅት ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ተረታቸውን እንዳቀረቡ ትርጉሙን እዚያው እንዲናገሩ የተደረገው በዚሁ ስሜት ነው፡፡

አጋጣሚዎችና ሌላ አጥኚ ወደ መስክ ሲወጣ ቢገለገልባቸው ሊጠቅሙት ይችላሉ የተባሉ ጥሩ ልምዶች ናቸው፡፡

### 1.6.1 በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች፣

በመረጃ ስብሰባ ወቅት በሁሉም መረጃ አቀባዮች ዘንድ በመሰረታዊነት የገጠመ ዋና ችግር ተረትን ዝቅ አድርጎ መመልከት ነበር፡፡ በተለይ አጥኚውን ከመረጃ ሰጪዎች ጋር ያገናኙት ወዳጆቹ "ለዶክትሬት ዲግሪ መመረቂያ ስለሚፈልገው የሚጠይቃችሁን ንገሩት" ብለው በሚያስተዋውቁት ጊዜ በግልጽ "አሁን ከተረት ምን ቁም ነገር ይወጣዋልና ነው የሚጠይቀን፤ ይሄ እኮ ጥንት የቀረ ነው" ብለው በግልጽ የተናገሩ ነበሩ፡፡ እንዲያውም "እኛ ደግሞ ለቁም ነገር የተጠራን መስሎን" ያሉም ነበሩ፡፡ ነገሩንም አቅልለው እንዲመለከቱት ካደረጋቸው ምክንያት ውስጥ "ለዶክተር" ከሰጡት ከፍተኛ ግምት አንጻር ተረት አይመጥነውም በሚል ስሜት ይመስላል፡፡ "እንዴት ተረት አጥንቼ ዶክተር እሆናለሁ ይላል" የሚሉም ይመስላሉ፡፡ ይሄ በወቅቱ ለአጥኚው ትልቅ ችግር ነበር፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩን አቅልለው አይተው መረጃ ላይሰጡ ይችላሉ፤ እንዲያውም ጥለው ሁሉ ሊሄዱ ይችላሉ የሚል ስጋት ነበር፡፡ ሆኖም ግን ተረት በቀላሉ የማይገመት ቁም ነገር ያለው እንደሆነ፣ ከውጭ አገር ድረስ መጥተው ፈረንጆች የኢትዮጵያን ተረት እንደሚያጠኑ ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡ በእለታዊ ህይወታቸውም ውስጥ ነገርን በጥልቀት ለማስረዳት ሲፈልጉ፣ የተጣላን ሲያስታርቁ፣ ያጠፋን ሲመክሩ፣ ለየት ያለ፣ ተቀባይነት የሌለው ባህሪ፣ ልጆቻቸው ሲያሳዩ እና ሲያጠፉ እነሱንም ሲመክሩ ወዘተ. ሁልጊዜ እንደሚጠቀሙበት ለማስረዳት ጥረት ተደርጓል፡፡ አስከትሎም የሴትን ልጅ ጠቃሚነት፣ ሴትን ከወንድ ለማሳነስ ሲባል የሚነገሩ ተረቶችን ለምሳሌ እንደ ተረት 15 እና ተረት 97 ያሉትን በመንገር ጥሩ መልዕክት ያላቸው መሆናቸውን አጥኚው አስረድቷቸዋል፡፡ ይህንኑ ዘዴ Schoemaker (1990:27) ". . . if the conversation is slow, or if people are not yet relaxed enough to tell stories comfortably, it is perfectly acceptable for you to tell a narrative yourself in order to stimulate reactions and the telling of other narratives." ሲሉ ይደግፉታል:: በመጨረሻም እወረቀት ላይ ስላልሰፈሩና እነሱ የሚያውቋቸው ስለሆኑ ብቻ መናቅ እንደሌለባቸው ተነግሯቸዋል፡፡ ከዚህ በኋላ ቀድሞ የነበራቸው አስተሳሰብ ተቀየረ፡፡ አንደኛው "እንዲያውም እኮ ባገራችን ጥሩ ሽማግሌ የሚባለው የተጣሉትን ሰዎች በተረት በምሳሌ እያደረገ ጥፋታቸው ልክ አለመሆኑን አስረድቶ የሚያስታርቅ ነው፡፡ አንተም ተው አንተም ተው የሚለው ሁሉ

ሽማግሌ አያሰኝም፡፡ አሁን አሙሞ[12] ላይ ሽማግሌዎች ሲያስታርቁ አይታችሁ እንደሆነ ምክራቸው በሙሉ በተረት ነው" ሲል ሁሉም በመስማማት ሲያጉረመርሙ አጥኚው ለማየት ችሏል፡፡ በዚህ ዘዴ አጋጥሞ የነበረው ችግር ሊቀረፍ ችሏል፡፡ ይህ ችግር የገጠመው መረጃዎችን መሰብሰብ በተጀመረበት ተሁለደሬ ወረዳ ላይ ብቻ ነው፡፡ ሌሎች ወረዳዎች ላይ ግን ከላይ ጥቅም ላይ የዋለውን ስልት በመድገም ችግሩ ዳግመኛ እንዳይከሰት ተደርጓል፡፡

ሌላው አጥኚውን የገጠመው ፈተና መረጃ አቀባዮችን ተረት እንዲነግሩት በሚጠይቃቸው ጊዜ የሚያውቁትን አስታውሰው ለመናገር ያለመቻል ነበር፡፡ ይህ ሊሆን ያልቻለው የአውዱ አለመኖር ነበር፡፡ አንደኛ ነገር በምሽት ህጻናት በምድጃ ዙሪያ ተሰብስበው ከእነሱ በእድሜ የበለጠ ሰው ወይም እርስ በርሳቸው ተረት የሚያዳምጡበትና የሚተርቱበት አጋጣሚ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል፡፡ ሁለተኛ ነገር ተረት በባህሪው ሊወራ የሚችልበት ተያያዥ ርዕሰ ነገር ቀድሞ መነሳት ያስፈልገዋል፡፡ ያንን ርዕሰ ነገር በምሳሌ ማስረዳት ሲፈለግ ተረት ጣልቃ ይገባል፡፡ አጥኚው የተከተለው የመረጃ አሰባሰብ ስልት ግን ይህንን ታሳቢ ያደረገ አልነበረም፡፡ አጥኚውና መረጃ ሰጪዎቹ እንደተገናኙ ራሱን፣ የመጣበትን ቦታና ዓላማ ካስተዋወቀ በኋላ በቀጥታ ተረት እንዲነግሩትና እንዲተረጉሙለት ነበር የሚያደርገው፡፡ በዚህም የተነሳ ተረቱን እንዲያወሩት ምንም ቅድመ ሁኔታ ስላላመቻቸላቸው የመደነጋገርና ተረት የማጣት ችግር ነበር፡፡ ሆኖም ግን እላይ እንዳደረገው ሁሉ ተረቶችን በማውራትና ትርጉማቸውን በተረዳው መንገድ በመንገር ለማነሳሳት ጥረት አድርጓል፡፡

## 1.6.2 በመረጃ ስብሰባ ወቅት ያጋጠሙ ምቹ ሁኔታዎች

አጥኚው ለመረጃ ስብሰባ በሄደባቸው አካባቢዎች ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን ሲሰበስብ ምቹ ሁኔታዎች አጋጥመውታል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንደኛው ወሎ ዩኒቨርሲቲ እና ደሴ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ በክረምቱ መርሃ ግብር ያስተማራቸውን የክረምት ሰልጣኞች ማግኘቱ ነበር፡፡ እነዚህ ተማሪዎቹ በሁለተኛ ደረጃ መምህርነት፣ በባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት በባለሙያነት እና በሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽህፈት ቤት ተመድበው ሲሰሩ አግኝቷል፡፡ እነዚህም ሰዎች ከአጥኚው በተሻለ ፍጥነት ለተተኳሪ

[12] አሙሞ በተሁለደሬ ወረዳ ውስጥ የሚገኝ የጎጥ ስም ነው፡፡ በቦታው ላይ እስከ ግድያ የደረሱ ከባድ ግጭቶች ባህላዊ በሆነ መንገድ እርቅ የሚፈጸምበት ቦታ ነው፡፡ በጣም የሚከበርና የሚፈራ፣ የተጣላ ሰው ሳይታረቅ የማይቀርበት እጅግ የተከበረ ቦታ ነው፡፡ አስታራቂዎቹ ከፈጣሪ የተሰጡት የፈጣሪ መንፈስ አላቸው ተብሎም ስለሚታመን እርግማናቸው እጅግ ይፈራል (ነጻነት 1997)፡፡

የቡድን ውይይት የሚሆኑ ወንዶችንና ሴቶችን አፈላልጎ በማምጣትና (የሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ቢሮ ተወካዮች) ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ እንዲሁም የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ተረቶችን ከተማሪዎቻቸው በማሰባሰብ ያደረጉለት አስተዋጽዖ በጣም ጥሩና ምቹ አጋጣሚ ነበር፡፡

በሌላ በኩል አጥኚው ቀደም ብሎ የነበረው ግንዛቤ መረጃ ሰጭዎች ከአጥኚው ጋር በነበራቸው ቆይታ ምክንያት ለሚቀርባቸው ስራ ማካካሻ የሚሆን ገንዘብ ሊጠይቁ ይችላሉ በሚል ግምት ራሱን በተወሰነ ደረጃ አዘጋጅቶ ነበር፡፡ ሆኖም ሁሉም ሰዎች በአጥኚው ምርጫ መሰረት ተፈልገው ሲመጡ በሚያውቃቸው ሰዎች በኩል ስለነበረ የገንዘብ ጥያቄ አላነሱም፡፡ ይሄም ሌላው ምቹ አጋጣሚ ነበር፡፡

ሌላው ለጥናት የተመረጡት ወረዳዎች በተለይም በረና ወረዳ አጥኚው ያደገበት፣ የተማረበትና በመምህርነትም ለሶስት አመታት የቆየበት በመሆኑ፣ ተሁለደሬ ወረዳም ለአስር ዓመታት በመምህርነት ስለሰራ ለሰውም ለአካባቢውም እንግዳ አልነበረም፡፡ በመሆኑም መረጃ ሰጪዎች "ይህማ የእኛው ነው" በሚል ስሜት ያለማቅማማት የሚፈልገውን መረጃ እንዲያገኝ አድርጎታል፡፡

በኩታበር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በየጊዜው ተሰባስበው የተቀመጡ ተረቶችን ማግኘትና ባለሙያዎቹ ያለምንም ስስትና ንፍገት ለመስጠት መፍቀዳቸው፣ እንዲሁም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከመጀመሪያ እስከ ሶስተኛ ዲግሪ በተሰሩ የፎክሎር ጥናቶች ውስጥ በአባሪያቸው በርካታ ተረቶችን እንደልብ ማግኘት መቻሉ እንደ ምቹ አጋጣሚ ተቆጥረዋል፡፡

### 1.6.3 በመረጃ ስብሰባ ወቅት የተገኙ ጥሩ ልምዶች

ተረቶች ከመስክ የተሰበሰቡት በቃለመጠይቅ እና በጽሑፍ ነው፡፡ ለዚህም እንደ አንድ ዘዴ ውሎ የነበረው ስልት ከሴትና ከወንድ ጋር በተያያዘ የሚያውቁትን እንዲናገሩ ማድረግ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የሚናገሩት ተረት አጥተው ሲቸገሩ ለማየት ተችሏል፡፡ ይሄ ለምን እንደሆነ በማሰብ ስልቱን ለመቀየር ተሞከረ፡፡ ቀደም ያለው ስልት ሁለት ተግባራትን አንድ ላይ ያጣመረ ነበር፡፡ አንድም ተረት እንዲናገሩ፤ ሁለትም ከሚያውቋቸው ተረቶች ውስጥ ከሴትና ከወንድ መስተጋብር ጋር የተገናኙትን መምረጥ ነበር፡፡ ይሄ ድርብ ስራ ሆኖባቸው ከሚያውቋቸው ውስጥ ለጥያቄው ተስማሚውን መምረጥ አቅቷቸው ስለነበረ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የሚያውቁትን ማንኛውንም ተረት

እንዲናገሩ ተደረገ፡፡፡ በዚህ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ተቻለ፡፡ ያም ሆኖ ግን አጥጋቢ አልነበረም፡፡ በተደጋጋሚ የሚሉት "ተረት እናውቃለን፤ ግን አሁን አልመጣልን አለ" የሚል ነበር፡፡ እዚህ ላይ የአውዱ አለመኖር ለችግራቸው ምክንያት እንደሆነ አጥኚው በመረዳቱ ለማነሳሻ ያህል የሚያውቃቸውን ተረቶች በመንገርና ተረት እንዲነገር ምክንያት ይሆናሉ ያላቸውን እንደ እንጀራ እናት፣ የቆሎ ተማሪ፣ ፍቅር፣ ክፋት፣ አስተዋይነት፣ ሞኝነት፣ ወዘተ. የመሳሰሉትን ርዕሰ ጉዳዮች በመነካካት ተረት የማውራት ስሜታቸውን ለማነቃቃት ሞከረ፡፡ በዚህ የተሻለ መረጃ ለማግኘት ችሏል፡፡


ሌላው የመስክ መረጃ ምንጮች የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ናቸው፡፡ ከነዚሁ ተማሪዎች በጋራም በግልም ሆነው ተረቶችን እንዲናገሩ ተሞክሮ ነበር፡፡ ሆኖም ግን ይናገሯቸው የነበሩት ቀልዶች እንጂ ተረቶች አልነበሩም፡፡ እነዚህም ቢሆኑ በተለያዩ አጋጣሚዎች ታትመው ከተለቀቁ ሲዲዎች፣ ከቴሌቪዥንና ከተለያዩ የራዲዮ ፕሮግራሞች የሰሟቸው ናቸው፡፡ እንዲህ ዓይነት ሁኔታ በገጠመ ጊዜ አጥኚው ከአማርኛ ቋንቋ መምህሮቻቸው ጋር በመነጋገር በቤት ስራ መልክ ከወላጆቻቸው ጠይቀው እንዲያመጡ በማድረግ ተረቶችን ለማሰባሰብ ተችሏል፡፡ ይህ የተደረገው አጥኚው ከአባቶች እና ከእናቶች ጋር ፊት ለፊት ተገናኝቶ ከሰበሰባቸው ተረቶች በተጨማሪ ሌሎችንም ተረቶች ለማግኘት ካለው ፍላጎት ነው፡፡ እነዚህ ከመስክ የተሰበሰቡ ቢሆኑም በሁለተኛ ወገን የተገኙ ስለሆኑ እንደ ሁለተኛ (ካልዓይ) ደረጃ የመረጃ ምንጭ የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ እነዚህ እንደጥሩ ልምድ ተወስደዋል፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የደቡብ ወሎ ዞን አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊ እና ማኅበረ ባህላዊ ገጽታዎች

## 2.1 የደቡብ ወሎ ዞን አጠቃላይ መልክዓ ምድራዊ እና የሥነህዝብ ሁኔታ

ደቡብ ወሎ በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ውስጥ ከሚገኙ 10 ዞኖች መካከል አንዱ ነው፡፡ የዞኑ ርዕሰ ከተማ ደሴ ስትሆን ከአዲስ አበባ በ401 ኪሎ ሜትር እና ከክልሉ ርዕሰ ከተማ ባህር ዳር በ470 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ዞኑን በስተሰሜን፣ ሰሜን ወሎ ዞን፣ በስተደቡብ የኦሮሚያ ክልልና ሰሜን ሸዋ ዞን፣ በስተምስራቅ ኦሮሚያ ብኄረሰብ ዞንና አፋር ክልል፣ በስተምዕራብ ምስራቅ ጎጃምና በሰሜን ምዕራብ ደቡብ ጎንደር ዞን ያዋስኑታል፡፡




ምንጭ፦ የኢትዮጵያ ካርታ ስራዎች ድርጅት (Ethio GIS one)

ዞኑ 20 የገጠርና 4 የከተማ አስተዳደር ወረዳዎች አሉት (የደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት የ2008 ዓ.ም ዓመታዊ ዕቅድ)፡፡ የቆዳ ስፋቱ 18,727.24 ካሬ ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ሲሆን ይህ አሃዝ ከክልሉ 11.91 በመቶ ድርሻ አለው፡፡ በዚህ የቆዳ ስፋቱ በክልሉ ውስጥ ካሉት 10 ዞኖች መካከል ከሰሜን ጎንደር ቀጥሎ በ2ኛ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡ የህዝብ ብዛቱም ወንድ 1,248,698 ሴት 1,270,164 በድምሩ 2,518,862 ይደርሳል (EPHCC[13] 2007፡7)፡፡ ከዚህ ህዝብ ውስጥ 87.6 በመቶው በገጠር እና 12.4 በመቶ በከተማ ይኖራል፡፡ ህዝቡ ከሃይማኖት አንጻር ስንመለከተው 28.8 በመቶው ክርስቲያን፣ 70.9 በመቶው ሙስሊም ሲሆን ቀሪው 0.3 በመቶው የሌሎች ሃይማኖቶች ተከታይ ነው (EPHCC 2007፡ 198)፡፡

የደቡብ ወሎ ህዝብ 99.32 በመቶው "የአማራ ብሄር ተወላጅ" ሲሆን ሌሎች ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ አገው እና ሲዳማ ከቀሪው ውስጥ ከፍ ያለውን ቁጥር እንደየቅደም ተከተላቸው ይዘው ይገኛሉ (EPHCC 2007፡146-147)፡፡ በቋንቋ ረገድ ሲታይ 98.65 በመቶ ያህሉ አፍ መፍቻቸውን አማርኛ ያደረጉ ሲሆኑ በቁጥር ወደ 22,325 (0.9 በመቶ) የኦሮምኛ አፈፊት ተናጋሪዎች አሉ (EPHCC 2007፡172-173)፡፡

የደቡብ ወሎ ዞን ከባህር ወለል በላይ ያለው ከፍታ ከ1135-4247 ሜትር ይደርሳል፡፡ በአየር ንብረቱም ውርጭ 2%፣ ደጋ 35%፣ ወይና ደጋ 46% እና ቆላ 17% ይሸፍናል፡፡ አመታዊ አማካይ የዝናብ መጠኑም በቆላ ከ500-900 ሚሊ ሜትር እና በደጋና ወይና ደጋ 950-1100 ሚሊ ሜትር ይደርሳል፡፡ አማካይ የሙቀት መጠኑ ከ15-20 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሲደርስ የብርዕ፣ የአገዳ፣ የአበባ፣ የቅባት እህሎች እና አትክልትና ፍራፍሬ ይበቅሉበታል (ደቡብ ወሎ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት 2008)፡፡

በተፈጥሮ ሃብት ረገድ ወደ ሁለት ዋና ዋና ተፋሰሶች (አባይና አዋሽ) የሚገቡ ከ448 በላይ ወንዞች አሉት፡፡ ለጎ፣ አርድቦ፣ ማይባርና ጎልቦ የተባሉ የአራት ሃይቆችም ባለቤት ነው፡፡ ነዳጅ፣ የብረት ማዕድን፣ ኦፓል፣ የድንጋይ ከሰል፣ ክልስ ወርቅ፣ ጅብሰም፣ የሲሚንቶ ግብዓት ወዘተ. የመሳሰሉ ማዕድናትም እንደሚገኙ የማዕድንና ኢነርጂ ሃብት ልማት ማስተባበሪያ ኤጀንሲ ያደረገውን የዳሰሳ ጥናት ዋቢ አድርጎ የደቡብ ወሎ አስተዳደር ጽ/ቤት ያወጣው ማስረጃ ያሳያል፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ የቦረና ሳይንት ብሄራዊ

---

[13] Ethiopian population and Housing Census Commission

ፓርክ (ከ5,500 ሄክታር በላይ ስፋት ያለው)፣ የወለቃ አባይ ታሳቢ ብሄራዊ ፓርክ (ከ150,000 ሄክታር በላይ ስፋት ያለው) እና የሌሎችም ጥብቅ ደኖች ባለቤት ነው፡፡

## 2.2 የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ የዘር ሃረግ አመጣጥ፣ አሰፋፈር እና ማኅበራዊ ገጽታ

በርከት ባሉ ጽሑፎች ውስጥ እንደሚታየው የወሎ የዘር ሃረግ ከኦሮሞ የሚመዘዝ መሆኑ በተደጋጋሚ ይገለጻል (OCTB[14] 2006፣ ጀቤሳ 1989፣ አለቃ ታዬ 2008፣ ጌታቸው 1997)፡፡ ሆኖም ግን ቦታው የአማራ ነው ወይስ የኦሮሞ ነው በሚል ውዝግቦች አሉ፡፡ ይሄ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስለሌለው ጥቆማ ብቻ ቀርቧል እንጂ በስፋት አልተነሳም፡፡ ሆኖም ግን የወሎ አሁን ያለው የዘር ሃረግና አሰፋፈሩ ምን እንደሚመስል በአጭሩ ለማስተዋወቅና ለአጠቃላይ ግንዛቤ ባጭሩ ቀርቧል፡፡

### 2.2.1 የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ የዘር ሃረግ

የኦሮሞ ብሄር ሁለት አቢይ ጎሳዎች አሉት፡፡ እነዚህም ቦረና እና ባረንቱ[15] በሚል ይታወቃሉ፡፡ ከእነዚህ ሁለት የኦሮሞ አቢይ የዘር ግንዶች የሚመዘዙ ኦሮሞዎች በወሎ ሰፍረው እንደሚገኙ መረጃዎች ያሳያሉ (OCTB 2006፡261)፡፡ ይህንኑ በተመለከተ የሚቆጠሩት የዘር ሃረጎች በተለያዩ ጸሃፊዎችና በቃል መረጃ አቀባዮች መካከል መጠነኛ ልዩነቶች ይታያሉ (OCTB 2006፣ ጀቤሳ 1989፣ ጌታቸው 1997)፡፡

የአባ ባህሪን[16] የዘር ቆጠራ መሰረት ያደረገው የወሎ ኦሮሞ ዘር ከባረንቱ የዘር ሃረግ እንደሚመዘዝ ያሳያል፡፡ ባረንቱ ስድስት ተወላጆች ሲኖሩት ከነዚህ ውስጥ አንዱ ከረዩ

---

[14] Oromia Culture and Tourism Bureau

[15] ቦረና እና ባረንቱ በተለያዩ ጸሃፊዎች በተለያየ ስም ሲጠሩ ይስተዋላል፡፡ ቦረናን አንዳንዶቹ "በረን"ሌሎቹ ደግሞ "ቦረን" በማለት ይጠሩታል፡፡ ባረንቱንም ቢሆን የተወሰኑት "በርቱማ" ሲሉት ሌሎቹ ደግሞ "በረቱማ" ሲሉ ይጠሩታል (OCTB 2006፣ አለቃ ታዬ 2008፣ ጀቤሳ 1989 ይመልከቱ)፡፡

[16] የወሎ ኦሮሞ የዘር ሃረግን በተመለከተ በምንጭነት በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የአባ ባህሪ "History of the Galla, in Some Records of Ethiopia (1593-1646)" በሚል በ1957 የታተመው ነው፡፡ የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮም "የኦሮሞ ህዝብ ታሪክ እስከ 16ኛ መቶ ክፍለ ዘመን" በሚል ባሳተመው መጽሃፍ ውስጥ ይህንኑ የአባ ባህሪን መጽሃፍ በምንጭነት ተጠቅሟል፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም በአቢይነት የተጠቀመው የኦሮሚያ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ያሳተመውን መጽሃፍ ነው፡፡


ነው፡፡ ከረዩ እንዲሁ በስሩ ስድስት ቅርንጫፎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ ውስጥ አንዱ የወሎ ጎሳ ነው፡፡ እንደ አባ ባህሪ አገላለጽ በወሎ ጎሳ ስር ከተጠቃለሉት ንዑስ የዘር ቅርንጫፎች ውስጥ ቀዳሚ የወሎ ኦሮሞ የሚባሉት ወረቡኮ፣ ወረጎራ እና ወረኖሌ (ኢሉ) ሲሆኑ ከነዚህ የሚመዘዙ (ሰደቻ) ወረከረዩ፣ ወረኢሉ እና ወረኖሌ አሊ የሚባሉት እንደሆኑ ተጠቅሷል (OCTB 2006:260፣ ጌታቸው 1997፡181-186፣ ጀቤሳ 1989፡28)፡፡

ከወሎ አካባቢ ከሚኖሩ የወሎ ኦሮሞዎች የተገኘው የቃል መረጃ የወሎ ኦሮሞዎች ራሳቸውን በቻሉ ሰባት ጎሳዎች እንደሚከፈሉ ያሳያል፡፡ እነዚህም ወረሂበኖ፣ ወረኢሉ፣ ወረባቡ፣ ወረቃሉ፣ ለገጎራ፣ ለጋምቦ እና ለገሂዳ በሚል የሚታወቁት ናቸው (OCTB 2006:261)፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት ሰባት ጎሳዎች በምስራቃዊውና መካከለኛው ደቡብ ወሎ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ናቸው፡፡

በሌላ በኩል OCTB (2006፡261) የ Odd Erike Arnesenን ስራ ጠቅሶ እንዳሰፈረው የወሎ ኦሮሞዎች ከሁለቱም የኦሮሞ አቢይ የዘር ሃረጋት የሚመዘዙ ጎሳዎች መሆናቸውን ጠቅሷል፡፡ ከዚህ በላይ የአባ ባህሪንና የወሎ ኦሮሞ አባቶችን ማስረጃ መሰረት አድርገው የተጠቀሱት የባሬንቱ የዘር ሃረግ ያላቸው ሲሆን እነዚህም በምዕራባዊው ወሎ የሚገኙት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ዛሬ ከላላ፣ ወግዲ እና ቦረና በሚል በሚታወቁት ወረዳዎች ውስጥ ከቦረና[17] አቢይ የኦሮሞ የዘር ግንድ የሚመዘዙ ናቸው፡፡ እነዚህም ሜታ፣ ወግሎ፣ ደምቢ፣ አየና እና ከላላ ናቸው፡፡ ይሄኛው የዘር ግንድ OCTB

[17] የፖለቲካ መዋቅሩ አሁን ባለበት መልኩ በወረዳ ከመከፋፈሉ በፊት ወሎ አስራ ሁለት አውራጃዎች ነበሩት፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንዱ የቦረና አውራጃ ነበር፡፡ ይህም አውራጃ በስሩ ደብረሲና፣ ከላላ፣ ወግዲና ሳይንት በሚል የሚታወቁ ወረዳዎችን ያቀፈ ነበር፡፡ የዚህ አካባቢ ማኅበረሰብ ቦረኔ እንጂ ወሎዬ ነኝ ብሎ ራሱን አይጠራም ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን የቀደመው ስሜት ሙሉ በሙሉ የጠፋ አይመስልም፡፡ ጋብቻም ሲመሰርት ከወሎ ጋር እንዳይጋባ የዘር ሃረግ ቆጥሮ ለማረጋገጥ ሲጥር ይታያል፡፡ ከዚህ ቀደም የዚህ ምክንያት ምን እንደሆነ አጥኚው አያውቅም ነበር፡፡ ከአካባቢውም ማኅበረሰብ መልስ ለማግኘት ቢሞክርም እንዲህ ነው የሚል አላገኘም፡፡ ሲሰጠው የነበረው መልስ "እነሱ ተጋቦቻችን አይደሉም" የሚል ብቻ ነበር፡፡ ምክንያታቸው ግን ወሎን ዝቅ ቦረናን ከፍ አድርጎ የመመልከት ወይም ከዝቅተኛነት ስሜት በመነጨ እንዳልሆነ ግልጽ ነው፡፡ አሁን ግን ከላይ በቀረበው የዘር ሃረግ አከፋፈል መረዳት የሚቻለው ከተለያየ የዘር ግንድ የሚመዘዙ በመሆናቸው ያለመቀላቀል ስሜት ያመጣው ይመስላል፡፡

(2006) ካሳተመው ስራ ውጭ በሌሎች መጻህፍት አይገኝም፡፡ ይሄው በሚከተለው ቻርት[18] ተመላክቷል፡፡




ባጠቃላይ ለጥናት የተመረጠው ዞን ስያሜውን ያገኘው ከጎሳው መጠሪያ ነው፡፡ የዘር ሃረጉንም በተመለከተ የተለያየ አመዛዘዝ ቢታይም ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው የወሎን የዘር ሃረግ ከኦሮሞ በመምዘዛቸው ነው፡፡

## 2.2.2 የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ አሰፋፈር

የወሎ ኦሮሞዎች ሰፍረው በሚገኙበት አካባቢ ቦታዎች የሚጠሩት በጎሳው ስም ወይም በወሎ ልጆች ነው፡፡ የጽሑፍ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት የወሎ ኦሮሞዎች ሰፍረው የሚገኙበት አካባቢ (ወሎ) መጠሪያውን ያገኘው ከ16ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ከኦሮሞ እንቅስቃሴና በቦታው መስፈር ጋር ተያይዞ ነው (OCTB 2006:260)፡፡ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (1965) አሁን ወሎ የሚባለውን አካባቢ ቀደም ብሎ የአማራ ግዛት እንደነበረና ከኦሮሞ መስፋፋት በኋላ አካባቢው በኦሮሞ መያዙንና ስያሜውም በዚያን ጊዜ መሰጠቱን ቢጠቅሱም OCTB (2006:265) የMohammed (1994)ን መጽሃፍ

[18] የቀረበው ቻርት 1ኛ. በኢትዮጵያ ያለውን ሁሉንም የኦሮሞ የዘር ሃረግ አያመለክትም፡፡ የወሎ ኦሮሞዎችን ብቻ የሚያመላክት ስለሆነ ከወሎ ውጭ ያሉት ተትተዋል፡፡ 2ኛ. የቻርቱ አቢይ ዓላማ የወሎ ኦሮሞዎች ከሁለቱም አቢይ የዘር ግንዶች የተገኙ መሆኑን ለማሳየት ብቻ የቀረበ ነው፡፡ 3ኛ. የወሎ ኦሮሞ የዘር ሃረግን በተጠቃለለ መልኩ የሚያሳይ አይደለም፡፡ በተለይ በባረንቱ ስር ያለው የእነ አባ ባህሪንና የቃል መረጃዎችን መሰረት አድርጎ የተሰራውን ሙሉ በሙሉ አያመላክትም፡፡ በአጠቃላይ የአንድን አጥኚ (Odd Erike Arnesen) ስራ ብቻ መሰረት ያደረገ ነው፡፡

አጣቅሶ አካባቢው ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊትም ቀደም ብሎ ኦሮሞዎች ይኖሩበት እንደነበረ ማስረጃ ሰጥቷል፡፡ እንዲያውም አመክንዮዎችን አቅርቦ (ለምሳሌ የቃል ታሪኮችን፣ Abba Bahrey በ1593 እና Conti Rossin በ1938 የጻፉትን መሰረት አድርጎ) ነዋሪነታቸው ከ14ኛው ክፍለ ዘመን በፊት ጀምሮ እንደሆነ ያሳያል፡፡ ከዚህ ጋር በማይጣረስ መልኩ ጌታቸው (1997፡187) የዚያ አገር ስም ጥንት ላኮ መልዛ ይባል እንደነበር፣ ወሎ ከያዘው ወዲህ በስሙ መጠራቱን፣ ይህም የሆነው በ1363 ዓ.ም መሆኑን፣ ወሎም በህይወቱ ሳለ አገሩን ለ7 ወንዶች ልጆቹ አካፍሎ መስጠቱንና አገራቸውም በየስማቸው መጠራቱን ያስረዳል፡፡ አለቃ ታዬም (2008፡65) ይህንኑ ጠቅሰውታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በአንድ በኩል ኦሮሞዎች በወሎ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በፊት የሰፈሩ መሆናቸውን፣ በሌላ በኩል አካባቢዎቹ በወሎ ልጆች መጠራታቸው አሰፋፈራቸውን ያሳያል፡፡ ይህ ሲባል ግን ወሎ አገሩን ለሰባቱ ልጆቹ አከፋፍሎ በየስማቸው እንዲጠራ ሲያደርግ ቀደም ብለው ይኖሩ የነበሩ አማራዎች ለቀው ሄደዋል ማለት የሚቻል አይመስልም፡፡ ምክንያቱም አሁን ደቡብ ወሎ ውስጥ የሚታየው የኦሮሞና የአማራ መዛነቅ የቀደመውን ሁናቴ ያሳያል፡፡ አካባቢውም በወሎ ልጆች ስም መጠራቱ በወቅቱ ገዢዎች እነማን እንደነበሩ ያሳይ እንደሆነ እንጂ ደቡብ ወሎን ጠቅልሎ ኦሮሞ ነው ለማለት የሚያስደፍር አይደለም፡፡ በሌላም በኩል የደቡብ ወሎ የአካባቢ ስሞች በጎሳ መሪዎቹ በመጠራታቸው ብቻ ህዝቡን ኦሮሞ ነው ለማለት አያስደፍርም የምንልበት ምክንያት የቋንቋውንም ሁኔታ ስንመለከት ነው፡፡ ደቡብ ወሎ ውስጥ የተወሰኑ ኦሮምኛ ተናጋሪዎች ቢኖሩም አብዛኛው ግን አማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ነው፡፡ ይህ ኦሮሞዎች የአካባቢውን ስሞች በጎሳቸው ስም እንዳደረጉት ሁሉ ቋንቋውን ግን የራሳቸውን አላደረጉትም፡፡ ይህ የሆነው ምናልባት ከቁጥራቸው አናሳነት የተነሳ የብዙሃኑን ቋንቋ (አማርኛ) መቋቋም ስላልቻሉ ሊሆን ይችላል፡፡ የዚህን አንድምታ ብንመለከተው ህዝቡን ጠቅልሎ ኦሮሞ ነው አያሰኝም፤ ይዞታውንም የኦሮሞዎች ነው አያስብልም፡፡

የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት "የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ" በሚል በ2001 ዓ.ም ባሳተመው ስራ ላይ (V) አማርኛ ቋንቋን "ራሱን የቻለና ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች

የተለየ ሆኖ መነገር የጀመረው በበሽሎና በጀማ[19] ወንዞች መካከል በሚገኘውና ዛሬ ቤተአምሃራ ተብሎ በሚታወቀው አካባቢ እንደሆነ የሚጠቁሙ መረጃዎች አሉ" በማለት ይገልጻል፡፡ ዘመኑንም ሰባተኛው ክፍለ ዘመን አከባቢ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ አስቴር (2007፡74) ዋቢዎችን (Hussein 2001:15 እና ገብረኪዳን 1981፡31) ጠቅሰው እንደገለጹት አካባቢው ወሎ ከመባሉ በፊት ቤተአምሃራ ይባል እንደነበረ፣ በ16ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ አካባቢ ከደቡብ ከተንቀሳቀሱት የኦሮሞ ነገዶች አንዱ በሆነው ወሎ ስም መጠራቱን ገልጸዋል፡፡ ዞሮ ዞሮ ከላይ በተጠቀሱት ሁለቱ ወንዞች መካከል ያለው ደቡብ ወሎ ነው፡፡ ይሄ አገላለጽ የዞኑ ጥንተ ርስትነት የአማራ ነው የሚል አንድምታ አለው፡፡

## 2.2.3 የደቡብ ወሎ ዞን ማኅበረሰብ ማኅበራዊ ገጽታ

የደቡብ ወሎ ዞን ማኅበረሰብ ከሚታወቅባቸው ባህሪያት ውስጥ ሚዛን የሚደፋው በሃይማኖትና በዘር ልዩነት ሳያደርግ ባለው ተዛንቆ የመኖር ልማዱ (አብዛኞቹ "የሃይማኖት መቻቻል" ይሉታል) ነው፡፡ ለዚህ እንደ ምክንያት የሚጠቀሱ በርካታ ነጥቦች አሉ፡፡

አንደኛ ዞኑ እንደኦሮሞ፣ ትግሬ፣ አርጎባ፣ አገው ወዘተ. የመሳሰሉት ብሄሮች በሃይማኖት፣ በብሄር፣ በቋንቋ፣ ወይም በድንበር ሳይወሰኑ ደቡብ ወሎ ውስጥ ገብተው አንድ ላይ በመኖራቸው የተነሳ ውህደትን ስለፈጠሩ ይመስላል፡፡ በዚህም ላይ በእነዚህ ብሄሮችና በወሎ አማራዎች መካከል የጎሳም፣ የሃይማኖትም ልዩነት ሳይኖር በመካከላቸው ጋብቻ መመስረት መቻላቸው የመዛነቃቸው ምንጭ ሳይሆን አይቀርም፡፡

ሁለተኛ በ2.2.1 ስር እንደተጠቀሰው አሁን ያለው የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ የዘር ግንዱ ኦሮሞ ነው ወደሚል ያዘነብላል፡፡ ይህንን የተለያዩ የታሪክ ጸሃፊዎች ለማረጋገጥ ጥረዋል፡፡ የኦሮሞዎችን ባህሪ በተመለከተ ጌታቸው (1997፡109) እና ጄቤሳ (1989፡35) እንደገለጹት ኦሮሞዎች ሰላማዊ ህዝቦች ናቸው፡፡ በሰብዓዊ ተፈጥሮ የታደሉ፣ የዋሆች፣ አካባቢያቸውን መጋፋትና መጫን የማይፈልጉ፣ የመሰሎቻቸውን ክብረ ህሊና ለማሻከርና አቻነት እንዲዛባ የማያደርጉ ናቸው ሲሉ ይገልጿቸዋል፡፡ ይህ የኦሮሞዎች ተፈጥሯዊ

[19] በሽሎ ወንዝ ደቡብ ጎንደርን ከደቡብ ወሎ የሚለይ ሲሆን ጀማ ወንዝ ደግሞ ሰሜን ሸዋ ውስጥ ይገኛል፡፡

ባህሪ በሌሎችም ዘንድ ሰርጾ አካባቢውን "በመቻቻል" እንዲኖር ሳያደርገው እንዳልቀረ መገመት ይቻላል፡፡

ሦስተኛ የዞኑ ማኅበረሰብ ከጥንት ጀምሮ በጋራ የሚተገብራቸው በርካታ ሃገረሰባዊ ልማዶች (social folk customs) እና በጋራ የሚዋዋሉባቸው ማኅበረ ባህላዊ ተቋሞች (socio cultural institutions) አሏቸው፡፡ ከማኅበራዊ ልማዶቻቸው ውስጥ አድባር መውጣት፣ ዱዓ (ወዳጃ) ማድረግ፣ ከጋራ ተቋሞቻቸውም ውስጥ ባህላዊ የእርቅ ተቋማት፣ እድር፣ ዓመታዊ የእምነት በዓል የሚካሄድባቸው ተቋማት፣ ወዘተ ይገኙባቸዋል፡፡ በእነዚህ ውስጥ አንድ ላይ የሚኖሩ በመሆናቸው መለያየትና በአንጻር ለመተያየት እድል አልሰጣቸውም፡፡ ተቋማቱን አብሮ የመኖር ጣጣ የፈጠራቸው ሳይሆኑ እንዳልቀሩ መገመት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ተቋማቱ የክርስቲያኑም የሙስሊሙም፣ የአማራውም የኦሮሞውም ናቸው፡፡

አራተኛ ሌላው ለወሎ ማኅበረሰብ "መቻቻል" እንደምክንያት ሊጠቀስ የሚችለው በክርስትና እና በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል የሚፈጸመው ጋብቻ ነው (ውዱ 2004፡210)፡፡ አንዳንድ የቃል ተረኮች እንደሚያሳዩት በደቡብ ወሎ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል ጋብቻ መመስረት የተጀመረው በ14ኛውና በ15ኛው[20] ክፍለ ዘመን አካባቢ እንደሆነ ይገመታል፡፡

በዘመኑ የሸህ ዳውድ ዘሮች አባ ገብርኤል ከሚባሉ የክርስትና ሃይማኖት ዘሮች ጋር ጋብቻ ይመሰርቱ እንደነበር ይገለጻል (ብርሃን 2005፡20)፡፡ ይሄ በግለሰብ ደረጃ የሚደረገው ጋብቻ አድጎ በጠቅላላው በሙስሊሙና በክርስቲያኑ ዘንድ የመተሳሰብንና የመከባበርን ልማድ ሊያመጣ እንደሚችል እርግጥ ነው፡፡[21] መተሳሰቡ ደግሞ ገደቡን

---

[20] አውሮፓውያን የሃይማኖት መቻቻልን ጽንሰ ሃሳብ የጀመሩት በ16ኛው ክፍለ ዘመን ነው (ውዱ 2004፡204)፡፡ የኢትዮጵያን ሁኔታ ስንመለከተው ደግሞ በ7ኛው ክፍለ ዘመን ሙስሊም ስደተኞች ወደ ኢትዮጵያ በገቡበት ጊዜ በኢትዮጵያውያን ነገስታት በኩል ምንም ዓይነት የሃይማኖት ልዩነትና መሳደድ ሳይደረግባቸው እምነታቸውን እንዲያስፋፉ ተፈቅዶላቸዋል (ውዱ 2004፡206)፡፡ ይህንን ዘመን እንተወውና ለሃይማኖት መቻቻልና አብሮነት ሲባል በወሎ በ14ኛውና በ15ኛው ክፍለ ዘመን አካባቢ በሙስሊሞችና በክርስቲያኖች መካከል ጋብቻ መጀመሩ (የቃል ታሪኩ እውነት ከሆነ) ስለሃይማኖት መቻቻል ባለን አስተሳሰብ ከአውሮፓውያን እንድንቀድም ያደርገናል፡፡ ደግሞስ አውሮፓውያን አሳሾችና ተጓዦች ጽንሰ ሃሳቡን ከእኛው ወስደው በተደራጀና ተቋማዊ በሆነ መልኩ አሻሽለው ስላለመጠቀማቸው ምን ማረጋገጫ አለን?

[21] የወሎን የሙስሊም ክርስቲያን ጋብቻ መሰረት ባደረገ መልኩ በሚመስል አኳኋን ልጅ ኢያሱ እና ዮሃንስ 4ኛ የአፋር ሙስሊም ሴቶችን ማግባታቸው (ቀደም ያሉትን ነገስታት ለምሳሌ አፄ ልብነ

ከፍ አድርጎ ክርስቲያኑ በመስጊድ፣ ሙስሊሙ በቤተክርስቲያን የየራሱን ተሳትፎ ሲያደርግ የኖረ መሆኑን በቦታው ጥናት ያደረጉ የታሪክ ሰዎች ገልጸዋል፡፡ ለምሳሌ ውዱ (2004፡203) "የሃይማኖት መቻቻል[22] በኢትዮጵያ" በሚለው መጣጥፋቸው ውስጥ ታደሰ ታምራት ለመስከ ስራ ወሎ በሄዱበት ወቅት ገጥሟቸው በቃል የነገሯቸውን ዋቢ አድርገው በ1950ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ወሎ በሚገኝ አንድ ትልቅ ደብር ውስጥ የቤተክርስቲያን ቁልፍ ያዢ የነበሩት ሙስሊም እንደነበሩ ገልጸዋል፡፡[23]

በወሎ አንዱ የአንዱን ሃይማኖት ከማክበር አልፎ አንዱ የአንዱን ሃይማኖት የሚያምንም የሚመስልበት አጋጣሚ በሰፊው ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ አቦን በሰፊው በቤታቸው ደግሰው የሚዘክሩ ሙስሊም አጥኚው በግሉ ያውቃል፡፡ ህመም በገጠማቸው ጊዜ ወደ ጸበል ቦታዎች በመሄድ በመስቀል እየታሹ የሚጸበሉ ሙስሊሞች በርካታ ናቸው፡፡ በታቦታት ንግስ ቀን ስዕለታችን ደርሶልናል በሚል ስዕለታቸውን የሚያስገቡ ሙስሊሞች ማየት ወሎ ላይ እንግዳ አይደለም፡፡ በቤተክርስቲያን አቅራቢያ ያሉ ሙስሊሞች በታቦቱ ንግስ ቀን ጠላ ጠምቀው፣ ዳቦ ጋግረው የንግሱን ተሳታፊ የሚያስተናግዱ ብዙዎች ናቸው፡፡ አጥኚው ከ1989 ዓ.ም ጀምሮ ሐይቅ ከተማ በነበረባቸው ዓመታት የሐይቅ ኢስጢፋኖስ ገዳም ንግስ እለት ባቅራቢያው ባሉ መንደሮች ያስተዋለው ይህንኑ ነው፡፡ ታላላቅ ከሚባሉ የሙስሊም ቅዱስ መስጊዶች

ድንግል ሙስሊሟን የሃዲያዋን ኢሌኒን ማግባታቸውን ትተን) በህዝቦች መካከል ውህደትን ለመፍጠር እንደተጠቀሙበት እንገነዘባለን፡፡

22 ብዙዎቹ እንደሚሉት የሃይማኖት መቻቻል ማለት ሁሉም የየራሱን ሃይማኖት ጠብቆ የሌላውን ሃይማኖት ሳይጋፋ በመከባበር በልዩነት ውስጥ አብሮ መኖርን የሚያመለክት ነው፡፡ ሆኖም ግን በወሎ ያለውን የሙስሊምና የክርስቲያን መስተጋብር ስንመለከት ገደቡ ከመቻቻል ያለፈ ይመስላል፡፡ በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ሙስሊምና ክርስቲያን አብረው ይኖራሉ፡፡ ለጤና ነው በሚል ምክንያት አንድ የቤተሰብ አባል ብቻ ሃይማኖቱን ሊቀይር ይችላል፡፡ በሃይማኖታቸው ሙስሊምና ክርስቲያን የሆኑ ባለትዳሮች አሉ፡፡ ሙስሊሙ ጸበል ይጠመቃል፣ ያዳነውን ታቦት ደግሶ ይዘክራል፡፡ የሃይማኖት ተቋማትን ያለልዩነት ተባብሮ ይሰራል፡፡ ክርስቲያኑም ሙስሊም አባቶችን በቤቱ ወዳጃ ያሳድራል፡፡ ወረርሽኝን ከቤቱ ጠርጎ ለማስወጣት ቁርኣን ያስቀራል፡፡ እጅግ በሚገርም ሁኔታ በክርስትናው የሚታወቀውን በሙስሊም ግን በጭራሽ የማይፈቀደውን ገዳማዊ ህይወት (በእስልምና ብህትውና አጥብቆ የተከለከለ ስለመሆኑ ሐሰን (1999፡26)ን ይመልከቱ) በወሎ ውስጥ እናገኛለን (ሰሚራ 2005)፡፡ እነዚህን አጋጣሚዎች ስንመለከት በወሎ ያለውን የሙስሊም ክርስቲያን መስተጋብር ከመቻቻል ያለፈ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ህዝቡ ከመቻቻል ባለፈ ተዛንቆ የሚኖር ነው፡፡

23 ይህንን የመሰሉ ገጠመኞች በወሎ እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ በዝርዝር ማወቅ ለሚፈልግ ውዱ (2004) እና kalkelachew (1997) ይመልከት፡፡

(shrines)[24] ውስጥ አንዳንዶቹ ወደ እስልምና በዞሩ ክርስቲያኖች መመስረታቸውን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ካቤ (ከደሴ ወደ ወረኢሉ በሚያስኬደው መንገድ ላይ የሚገኝ የገጠር ከተማ ነው) ውስጥ የሚገኘው የፈርጼ መስጊድ መስራች የሆኑት ሸህ ዓሊ ዩሱፍ አባታቸው (ብርቂ) ከመንዝ የመጡ ክርስቲያን ናቸው፡፡ ከመጡ በኂላ የሸህ ልጅ አግብተው እምነታቸውን የቀየሩ ናቸው (Kalklachew 1997:51)::

በክርስቲያኑ በኩልም እንደዚያው ነው፡፡ በእድሜያቸው ከፍ ያሉ ሙስሊሞችን በቤቱ ወዳጃ የሚሳድር ክርስቲያን ማየት የተለመደ ነው፡፡ የአዕምሮ እክል ለገጠመው ቤተሰቡ ቁርኣን የሚያስቀራም ክርስቲያን የዚያኑ ያህል ነው፡፡ ብዙዎቹ ክርስቲያኖች በረመዳን ወር፣ ሙስሎሞቹ በክርስቲያኑ ዓቢይ ጾም ወቅት ሰርግ አይደግሱም፡፡ ሙስሊሙ ለክርስቲያኑ የክርስትና አባት በመሆን ዝምድናን የሚፈጥሩበትና እርስ በርስ የሚተሳሰሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡

የደቡብ ወሎ ማኅበረሰብ ያለ ሃይማኖት ልዩነት ያገኘውን እንግዳ ሁሉ ተቀብሎ የማስተናገድ ልማድ አለው፡፡ ይህ ነባር ባህሉ ነው (አማራ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ 2001)፡፡ አባ ፍቅረማሪያም በቃለ ምልልስ ወቅት (29/06/2008) እንዳሉት የደቡብ ወሎ ህዝብ በሞራል ህግ የሚኗኗር በመሆኑ "ተቻቻል" ተብሎ የሚመከር አይደለም፡፡ እነዚህ ነጥቦች በጥቅሉ ሲመረመሩ በደቡብ ወሎ የነበረውንና ያለውን አብሮነት፣ መከባበርና አንድነት ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ በወሎ ላለው ውህደት ይህ ሌለኛው ምክንያት ስለመሆኑ ማስረጃ ይሆናል፡፡

በእስልምና ሃይማኖት ዓለም እጅግ ባልተለመደ መልኩ በወሎ የሙስሊም ገዳም አለ፡፡ ይህም ጡሩሲና በሚል የሚታወቀው ነው (ሰሚራ 2005)፡፡ የጡሩሲና ገዳማዊ ህይወትና ተግባራት እንዲሁም ወደ ገዳሙ ለመግባት የተመረጡት መስፈርቶች ከክርስትናው ጋር ተመሳሳዮች ናቸው፡፡ ይህን የመሰለው ቅርርብ ከአማኞቹ ባሻገር በሃይማኖት ሥርዓቱና ተቋማቱ ላይ የመወራረስና የመመሳሰል ባህሪ እንዲታይ አድርጓል (ሰሚራ 2005:74)፡፡ ይህ ከሃይማኖታዊ መቻቻል እጅግ የዘለለ ነው፡፡ በመሆኑም ደቡብ ወሎ ያለው የክርስቲያን ሙስሊም መስተጋብር ከመቻቻል ጽንስ

---

24 በደቡብ ወሎ ጥቂት የማይባሉ የሙስሊም ቅዱስ ስፍራዎች አሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ በተለይም በዓመታዊ ክብረ በዓላቸው ቀን በሺዎች የሚቆጠሩ አማኞች የሚሄዱባቸው ጀማንጉስ (በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የነብዩ መሃመድ የልደት ቀን መከበር የተጀመረበት ቦታ ነው)፣ የቃሉው ገታ መስጊድ፣ የቦረናው ደግይ፣ እና የካቤው ፈርጼ መስጊድ ይገኙበታል (Kalklachew 1997:50)፡፡ እነዚህ ቦታዎች ላይ የበዓሉ ተሳታፊ የነበረው ክርስቲያኑም ጭምር ነበር፡፡

ሃሳብ በላይ ይመስላል። ለማንኛውም ደቡብ ወሎ እንዲህ የመሰለው ማኅበራዊ ቅርስ (social capital) ባለቤት ነው።

ይህ ሲባል ግን የቀደመውን የክርስቲያን ሙስሊም መስተጋብር ለመናድ ዳር ዳር የሚሉ ስጋቶች የሉም ማለት አይደለም። ዕድርን የማፍረስ፣ የጋራ ማኅበራዊ ተቋሞች የመናቅና ያለማክበር፣ ሃይማኖትን ብቻ መሰረት አድርጎ ወዳጅነትን መመስረት፣ የራስ ላልሆኑ ሃይማኖታዊ ተቋማት ክብር መንፈግ ወዘተ. የመሳሰሉት ዝንባሌዎች አሉ።

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ሥነዘዴ

ይህ ምዕራፍ የምርምሩን የአጠናን ሥነዘዴ የሚያሳይ ነው፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ ሲከናወን ምን ንድፈሃሳብ (theory) ጥቅም ላይ እንደዋለ፣ ንድፈ ሃሳቡን ተከትሎ መረጃዎችን በምን የመተንተኛ ስልት እንደተፍታቱ፣ እንዲሁም መረጃዎች ከየት፣ ከነማን፣ በምን ዓይነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ እንደተሰበሰቡ እና አጥኚው የተከተለው ሥነምግባር ምን እንደሆነ የሚያሳይ ክፍል ነው፡፡

## 3.1 ንድፈሃሳባዊ መሰረቶች እና የመተንተኛ ስልት

ፎክሎርን ለማጥናት የሚያስችሉ በርካታ ንድፈሃሳቦች አሉ፡፡ ንድፈ ሃሳቦቹ እንደየዘመናቱ አስተሳሰብ የተቀነቀኑ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ይሁን እንጂ ንድፈሃሳቦች ፍጹም ልዩነት አላቸው ማለት አይደለም፡፡ ባብዛኛው የቅርቦቹ በቀዳሚዎቹ ንድፈሃሳቦች ላይ እየበቀሉ፣ የቀደሙትን እያሻሻሉ፣ በቀደሙትም ንድፈሃሳቦች ያልታዩትን አቅጣጫ እየተመረኮዙ የተሰሩ ናቸው፡፡ በመሆኑም ንድፈሃሳቦች እርስ በርሳቸው እየተናበቡ አንድን ጉዳይ ከተለያየ አቅጣጫ በጥልቀት የሚያሳዩ እንጂ ሙሉ በሙሉ የሚጣረሱ አይደሉም፡፡ Gray (1978:79) ይህንኑ ሲያስረዱ “. . . all of the interpretations are correct on their own level and in their own way” በማለት ይገልጹታል፡፡

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ምርምርን (Qualitative research) የተከተለ ሆኖ በዋናነት ሁለት ንድፈሃሳቦችን (Theories) አቀናጅቶ ተጠቅሟል፡፡ እነዚህም መዋቅራዊ ግልጋሎታዊ (Structural functional) እና እንስታዊ (Feminist) ንድፈሃሳቦች ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን ሌሎች ንድፈሃሳቦች በዚህ ጥናት ውስጥ ፈጽሞ የሉም ማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ድኅረ መዋቅራዊ ንድፈሃሳብ (post structuralist theory)፣ ድኅረ ዘመናዊ እንስታዊ ንድፈሃሳብ (post modern feminist theory)፣ እና ሃቲታዊ ንድፈሃሳብ (Discourse theory) በየአጋጣሚው ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ ባለሙያዎችም እንደሚመክሩት የተለያዩ ንድፈሃሳቦችንና ሥነዘዴዎችን አቀናጅቶ መጠቀም ውጤታማ ያደርጋል፡፡ ሆኖም ግን ሁሉንም በእኩል ደረጃ መጠቀም አስቸጋሪ ስለሚሆን ለተወሰኑት ቅድሚያ ሰጥቶ (forground አድርጎ) ሌሎችን በማጠናከሪያነት መጠቀም ተገቢ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር

የዚህ ጥናት አቅራቢ በዓቢይነት መዋቅራዊ ግልጋሎታዊንና እንስታዊ ንድፈሃሳቦችን በመጠቀም ላይ ተወስኗል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ንድፈሃሳቦች ሁለት ቢባሉም የመጀመሪያው ሁለት ንድፈሃሳቦችን ያቀናጀ ነው፡፡ አጥኚው እነዚህን ንድፈሃሳቦች ለምን እንደመረጣቸው በየተራ እንመልከት፡፡

ፎክሎር የአንድን ማኅበረሰብ አኗኗን የሚያንጸባርቅ ነው፡፡ ዓለምን ስንመለከታት ደግሞ በመዋቅር የተሰራች ናት፡፡ የተሰራችበትን መዋቅር ተከትሎ ለሁሉም ነገር የየራሱ ምደባ ተደርጎለታል፡፡ ዓለም መልክ የያዘችው በዚህ መንገድ ነው፡፡ ይሄ መዋቅር ጸንቶ ይኖር ዘንድ በጠቅላላው ፎክሎር በተለይ ቃላዊ ተረክ ዓይነተኛ ሚና መጫወቱ ግልጽ ነው፡፡ ቃላዊ ተረኮች በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን መዋቅር በማሳየታቸው የተነሳ በርካታ የፎክሎር ተመራማሪዎች ከመዋቅራዊ ንድፈሃሳብ አንጻር ጥናታቸውን አድርገዋል፡፡ ብዙዎቹ የፎክሎር ተመራማሪዎች መዋቅራዊ ንድፈሃሳብን ባብዛኛው የተጠቀሙት ቃላዊ የሆኑትን የፎክሎር መልኮች ለመተንተን ነው (Sims and Stephens 2005:183፣ Finnegan 2005፡31)፡፡

በዚህ ጥናት መዋቅራዊ ንድፈሃሳብ ጥቅም ላይ እንዲውል ሲደረግ የሚከተሉትን ምክንያቶች በመያዝ ነው፡፡ የሰው ልጅ በየትኛውም ዓለም ፎክሎርን የፈጠረው ለራሱ ነው፡፡ ሰው የራሱ ነገር ያስጨንቀዋል፡፡ ስለአኗኗሩና ስለተፈጥሮ የራሱን ቅርጽና መልክ አበጅቷል፡፡ ታግሎ ሊያሸንፋቸው ለማይችላቸው እንግዳ ገጠመኞቹ የራሱን መላ ዘይዶላቸዋል፡፡ ለምሳሌ ለሞት ትንሳዔን፣ ለአፈጣጠሩ እንቆቅልሽ አምላክን፣ ለክፋት ደግነትን፣ ለንፍገት ቸርነትን፣ ለዲያብሎስ እግዚአብሔርን፣ ወዘተ. ለሁሉም በየመልኩ የሚገባውን አበጅቷል፡፡ እነዚህ ክስተቶች የሰው ልጅ ሁሉ የጋራ ገጠመኞች ናቸውና ዓለም አቀፍ ይዘት አላቸው፡፡ እንዲህ ከሆነ ደግሞ የሰው ልጅ ላለው ተመሳሳይ ችግር የሚሰጠው ምላሽ በተለያየ አገላለጽ ይሁን እንጂ መልሱ ዞሮ ዞሮ ተመሳሳይ መሆኑ አይቀርም፤ ነውም፡፡

የሰው ልጅ ይሆናል የሚለውን ግምቱን ሲያሻው ሃይማኖት ፈጥሮ፣ ሲያሻው በሚት አዋቅሮ፣ አለያም በቅርብ የሚያውቃቸውን ተጋዳሊዎች (Heros) ገድል በመነሻነት በመያዝ የራሱን ፈጠራ ጨምሮ፣ ወይም ፍጹም ፈጠራዊ የሆኑ ተረቶችን በመጠቀም እየተጠያየቀ፣ እየከወነ ታሪክ እየነገረና እያስነገረ እምነቱን፣ ፍላጎቱን፣ ይበጃል ያለውን

ዘዴ አዋቅሮ በማቆየት ለዓለም አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት ፈጥሯል፡፡ እውነትን ከእምነት ጋር ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ አቀናጅቶ፣ ለእያንዳንዱ ነገር የራሱን መዋቅር ሰርቶ፣ በየዓይነቱ መድቦ፣ እውቀትና ክህሎቱን ለተከታዩ ትውልድ ሲያስተላልፍ ቆይቷል፡፡

ከላይ በተጠቀሰው መልክ የተሰሩትን ሥነቃሎች ዛሬ ለመተንተን አሁን ያሉበትን ሁኔታና (situational context) አከዋወናቸውን (performance) ይዘን ወደኋላ ተመልሰን ከተነገሩበት ማኅበረሰብ አደረጃጀት ጋር እያስተያየን መፈከር የተረቶችን አንድምታና ግልጋሎት እንድናገኝ ያደርገናል፡፡

በተረት ውስጥ የምናገኛቸው ውክልናዎችና ተምሳሌቶች በጊዜ ብዛት ቀዳሚው ትርጉማቸው ሊሸሸግ፣ በክዋኔ ወቅት ህልው ከመሆናቸው አልፎ ለምን እንደሚደረጉ ምስጢራቸው ሊሰወር ይችላል፡፡ ሌሎች የፎክሎር ዘርፎችንም ቢሆን ትዕምርታዊነታቸውን ከከዋኙ ወይም ከሚከወኑበት አውድ ብቻ በቀጥታ ማግኘት ሊያዳግት ይችላል፡፡ በዚህ የተነሳ ለአንድ አጥኚ የትዕምርታዊነታቸውን ፍቺ መተንተን ሊያስቸግረው ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነት ችግር በሚያጋጥመን ጊዜ መፍታት የሚቻለው መዋቅሩን በመተንተን ይሆናል፡፡ የሚተነተነው ሥነልሳናዊ መዋቅሩ (Linguistic structure) ወይም ማኅበራዊ መዋቅሩ (Social structure) ሊሆን ይችላል፤ ወይም ሁለቱንም አስተባብሮ፣ አናብቦ በመፈከር ይሆናል፡፡

ቋንቋ ባህል ንክር ነውና በተግባቦት ሂደት ወቅት ያለ የቋንቋ አጠቃቀም በማኅበረሰቡ ውስጥ ያለውን የሰዎች የደረጃ ልዩነት በግልጽ ያሳያል፡፡ በመሆኑም በቋንቋ ላይ የሚደረግ ሥነመዋቅራዊ ጥናት የማኅበረሰቡን አወቃቀር እግረ መንገዱን ያሳያል፡፡ ማኅበራዊ አደረጃጀቱም ቢሆን በእኩልነት ላይ ያልተመሰረተ በመሆኑ በማኅበራዊነታቸው ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ይለያያል፡፡ በመሆኑም አንድ የፎክሎር ዘውግ ሲከወን አንድምታው ባይገባን ለማወቅ ጥረት የምናደርገው የከዋኞችን የቋንቋ አጠቃቀምና የከዋኞቹን የተሳትፎ ልዩነት ከማንነታቸው ጋር በማገናዘብ ይሆናል፡፡ ለምሳሌ ወንድ በተረቶች ውስጥ ባብዛኛው ትልቁን ቦታ ተሰጥቶታል፡፡ ከአፈጣጠሩ ጀምሮ እስከ ዝቅተኛው ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ምርጥ ምርጡ፣ በጎ በጎው የራሱ ነው፡፡ ሴቶች ደካማ መንፈስና ዝቅተኛ ሰብዕና ተሰጥቷቸው ተስለዋል፡፡ ይህንን ቋንቋውም ማኅበራዊ አደረጃጀቱም ያሳያል፡፡ ይሄ ሥርዓት ተሰርቶ፣ ተደንግጎ ከቀደመው ወደ ተከታዩ በእምነት ሲተላለፍ የቆየ ነው፡፡ ከዚህ ውጭ የተለየ ነገር ሲከሰት

ከመዋቅሩ ስለሚያፈነግጥ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም ማኅበረሰቡ ለፈጠረው መዋቅር ተገዢም እጅግ አማኝም ነውና፡፡

የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ጥያቄ የተነሳበት ዘመን ቅርብ የሚባል አይደለም፡፡ ይሁን እንጂ የዘመኑን ርቀት ያህል ያለውን ለውጥ ስንመለከት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ የእኩልነት ፍልስፍናውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያዳግተው የወንዱን ቀርቶ የችግሩ ሰለባ የሆኑትን የሴቶችን አመለካከት ለመቀየር መክበዱ ላይ ነው (Holmberg 2005፡12)፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት ነገር ዓለሙ ሁሉ ቀደም ብሎ በመዋቅር ስላለቀ ነው፡፡

እዚህ ላይ ልብ ልንል የሚገባን ችግሩ ዓለማቀፋዊ መሆኑን ነው፡፡ ለምን ዓለማቀፋዊ ሆነ? Dorson (1972:35) *levi-strauss*ን ጠቅሰው ሲገልጹ "the answer would be found in a logical structure within the human mind" ብለዋል፡፡ ከፍ ባለ እምነት አዕምሮ ውስጥ ተከትቦ የተቀመጠ ነው፡፡ ጉዳዩ ከመዋቅር ነውና ይህንን እምነቱን፣ አመለካከቱን፣ ፍልስፍናውን ወዘተ. በጠቅላላው ፎክሎራዊ ምስጢሩን ማወቅ የሚቻለው መዋቅራዊ ትንተና በማካሄድ ነው፡፡

መዋቅራዊ ፈለግ የሚመለከተው ፎክሎር ለምን ተዋቀረ[25] ሳይሆን እንዴት ተዋቀረ የሚለውም ጉዳይ ነው፡፡ እንዴት ተዋቀረ ደግሞ በጥቅሉ የፎክሎሮችን ትርጉም ፈልጎ የማውጣት ጉዳይ ነው፡፡ የፎክሎር ትርጉም ተፈልጎ ሲገኝ የሰው ልጅ ስለዓለም ያለው አመለካከት ምን እንደነበረ ወይም ምን እንደሆነ ለማወቅ ያስችላል፡፡ የሰው ልጅ ይህችን ዓለም በምን ዘዴ ሰላማዊና የተረጋጋች እንዳደረጋት፣ እውቀቱንና ገጠመኙን በመልክ በመልኩ አደራጅቶ እንዳካበተባት እንረዳለን፡፡ Bayleyegn (1999:110) ይህንኑ ሲያስረግጡ ''Genres are point of view towards the world. And each culture has its own angle of perspectives of conceptualizing realities and categorizing knowledge and experience'' ብለዋል፡፡ ይህንን በተዘዋዋሪ ብንመለከተው የመዋቅር ጉዳይ ነው፡፡

በአገራችን በባህል ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ስንመለከታቸው የሠርግ ሥርዓት፣ የለቅሶ ሥርዓት፣ ባህላዊ የእርቅ ሥርዓት፣ የምግብ አዘገጃጀት ሥርዓት ወዘተ. በሚል ተሰርተው እናገኛለን፡፡ ከርዕሶቹ የምንረዳው አንድ አፈጻጸም ደንብ መኖሩንና ከደንቡ ውጭ መፈጸም የማይቻል መሆኑን ነው (መቀየርም ካስፈለገ ተጠየቃዊነት ያስፈልገዋል)፡፡ በሰዎች አዕምሮ ውስጥ ተዋቅሮ የተቀመጠ (structured የሆነ) ስምምነት

---

[25] ይህንን በአቢይነት ይዞ የሚያቀነቅን`Functional theory` ነው፡፡

አለ፡፡ ለእያንዳንዱ የአፈጻጸም ህግ (rite) እንደየ ባህሉ የራሱ የሆነ ትዕምርታዊነት አለው፡፡ የትዕምርቱ ትርጉም መዋቅሩ ውስጥ እንጂ ከበራው (ritual) ላይ አናገኘውም፡፡ እርግጥ ከበራ በጥቅሉ ሲታይ በራሱ ትዕምርት ነው፡፡ እዚህ ላይ ለማለት የተፈለገው ግን ከበራ ላይ የሚፈጸሙት እለፍ ተቀደማዊ ዝርዝር ድርጊቶች ሲፈጸሙ እናያቸዋለን እንጂ ለምን እንደሚፈጸሙ አይነግሩንም ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ትዕምርታዊነታቸውን ማወቅ ይቻል ዘንድ መዋቅሩን መመርመር ያስፈልጋል፡፡ በእርግጥ ፎክሎሩ ያለ ክዋኔው ህልውና የለውም፡፡ ይሁንና የክዋኔው ህግጋት ያሉት መዋቅሩ ውስጥ ነው፡፡ ይህንኑ Bronner (2007:132)

> *If we are successful in isolating and describing a structural pattern present in a genre of folklore, we may have provided a useful aid to understanding the nature of the culture at large as well as the cognitive categories, ideological commitments, and concrete behavior of the people sharing that culture* *ብለዋል፡፡*

ባለሙያው ያስረዱት የፎክሎር ቅንጣትን አወቃቀር በሚገባ መለየት የባህሉን ሁናቴ ለማወቅ ከመርዳቱም በላይ የፎክ ቡድኑን አባላት የእውቀት ዓይነቶች፣ ርዕዮተ ዓለማቸውን፣ ከባህሉ የሚጋሩትን ተጨባጭ ባህሪ ለማወቅ የሚያስችል መሆኑን ነው፡፡ ትርጉም ከተረቱና ከማኅበረሰቡ ተቋማዊ መዋቅር ጋር አንዳች ዓይነት ምክንያታዊ ዝምድና ይኖረዋል፡፡ Dundes በ Bronner (2007:123) ውስጥ ይህንኑ ሲያጠናክሩ "meaning derives from causal relationships within a structure" ብለዋል፡፡ Page (2006:5) በበኩላቸው "I think more attention needs to be placed on key structures in society to see how narratives link up to the larger picture" በማለት ሃሳባቸው ገልጸዋል፡፡

ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ጾታ በተረኮች ውስጥ እንደምን እንደተገለጸና የሰፈነውን ባህላዊ ስምምነት እንዴት እንዳቆየ፣ ከሥልጣን ጋር ያለው መስተጋብር ምን እንደሚመስል ለማስተንተን የተረኮችን አወቃቀር ከማኅበረሰቡ መዋቅር ጋር ማስተያየት ያስፈልጋል፡፡ በመሆኑም መዋቅራዊ ንድፈሃሳብ ለዚህ ጥናት ተገቢነት አለው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ትንተና ሲካሄድ ቃላዊ ተረኮቹ ለምን ጠቀሙ? ማለታችን አይቀርም፡፡ ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የግድ ወደ ግልጋሎታዊ ንድፈሃሳብ (Functional theory) እንሄዳለን፡፡ በመሆኑም ይህ ንድፈሃሳብ በዚህ ጥናት ውስጥ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ ሆኖም ግን ተረኮችን ከመዋቅራዊ ንድፈሃሳብ አንጻር ስንመለከት ግልጋሎታቸውም አብሮ ስለሚነሳ ተያይዘው የሚከሰቱበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ሁለቱን

ንድፈሃሳቦች "መዋቅራዊ ግልጋሎታዊ" (Structural Functional) በሚል እንደ አንድ ንድፈ ሃሳብ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ እነ Vanderstoeop እና Johnston (2009:247) ሥነዘዴዎችንና ንድፈሃሳቦችን አዳቅሎ መጠቀም የተለመደና የሚቻል መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

ሌላው ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ቃላዊ ተረኮች በአገራችን ደረጃ ከእንስታዊ ፈለግ አንጻር አልተጠኑም ማለት ይቻላል፡፡ የጥናቱ አንዱ ዓላማም የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ይጋፋሉ ከሚባሉት ቃላዊ ተረኮች በስተጀርባ ያለውን "እውነታ" በሃቲት (Discourse) ተንትኖ ማሳየት ስለሆነ ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ይቻል ዘንድ እንስታዊ ንድፈሃሳብን አጥኚው ተገልግሏል፡፡

እንስታዊ ቲዮሪ የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥና ፍትህን ለማስፈን ያለመ ምሁራዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ነው፡፡ በሌላ አባባል እንስታዊ ቲዮሪ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነጻጸሩ መሰረታዊ ሰብዓዊ መብቶቻቸው የተነፈጓቸው፣ የተጨቆኑና ተጠቃሚነታቸው የተከለከላቸው ናቸው የሚል ጠንካራ መነሻ ሃሳብ በመያዝ የተቀነቀነ ነው፡፡ የሴቶች እኩልነትና ተጠቃሚነት የተነፈጉበት ምክንያት ተጠየቃዊ ካለመሆኑም ሌላ በገሃዱ አለም ጭራሽ የማይታይና በአድልዎ ላይ የተመሰረተ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ፡፡ በአንጻሩ ግን ሴቶች በተፈጥሯቸው የታደሉ፣ ተፈጥሯዊ ብቃት ያላቸው፣ ለየማኅበረሰባቸው የሚጠቅም ሃሳብና ተሰጥኦ የተቸራቸው ናቸው ሲሉ ያስረግጣሉ (Madsen 2000 in Birhanu 2015:65):: ባጭሩ እንስታዊ ቲዮሪ ጾታዊ አድልዎን ለማስቀም የሚደረግ ምሁራዊና ፖለቲካዊ ትግል ነው፡፡

በእንስታውያን ንድፈ ሃሳብ አቀነቃኞች መካከል ልዩነቶች ቢኖሩም አንድ የሚያደርጋቸው ግን የቆየው ልማድ (አባዊ ሥርዓት) የሴቶችን ሰብዕና ዝቅ ያደረገ፣ ከወንድ ጋር እኩል መብት እንዳይኖራቸው የነፈገ፣ ይህንንም ለማስፈጸም መዋቅሩን በዚሁ ትይዩ የሰራ ነው በሚለው ነው፡፡ በዚህ መሰረታዊ ሃሳብ ቢመሳሰሉም ልዩነቶችም ይስተዋላሉ፡፡ ልዩነታቸው የሚነሳው ለሥርዓተ ጾታዊ አድልዎ መነሻው ምንድን ነው? እንዴትስ መፈታት ይችላል? በሚለው አቋማቸው ነው፡፡ ለዚህ የሚሆነው መልሳቸው የሚመነጨው ደግሞ አቀንቃኞቹ ከሚከተሉት የፖለቲካ ሥርዓትና ርዕዮተ ዓለም ነው፡፡ ለምሳሌ በኢኮኖሚ እኩልነት ላይ የሚያምኑት ማርክሳዊ እንስታውያን ለሥርዓተ ጾታ ልዩነት የመፈጠር ምክንያት የሃብት የበላይነትና የበታችነት እንደሆነ ያምናሉ፡፡ መፍትሄውም የሴቷን የኢኮኖሚ እኩልነት ማረጋገጥ በተዘዋዋሪ በወንድ የበላይነት

የተያዘውን የኢኮኖሚ ሥርዓት ማደላደል ያስፈልጋል ይላሉ (Madsen 2000 in Birhanu 2015:70)።

ሊበራል እንስታውያን በበኩላቸው የሥርዓተ ጾታ እኩልነት እንዳይኖር ያደረገው ባህል መሆኑን ጠቅሰዋል። እንዲያውም አምላክ ሴት እና ወንድን ሲፈጥር እኩል አድርጎ ነው፤ የልዩነቱ ምንጭ የሴትና የወንድ የማህበራዊነት ሂደት (process of socialization) ልዩነት ነው በሚል ይገልጹታል:: አስከትለውም እኩልነቱን በማኅበረሰብ ደረጃ ማምጣት የሚቻለው በመጀመሪያ በሴትና በወንድ መካከል ያለው ግለሰባዊ ግንኙነት ሲሻሻል ነው የሚል አቋም አላቸው። ይህንን እውን ማድረግ ይቻል ዘንድ ወንዱን ተጠቃሚ ያደረገው ፖለቲካውና መሰረታዊ ህጉ ጥገናዊ ለውጥ ማድረግ አለበት በሚል ይስማማሉ (Tong 2009 and Madsen 2000 in Birhanu 2015:71)። በዚያም ላይ ጾታን መሰረት ያደረገው የስራ ክፍፍል ለሴቶች የተጽዕኖ ምንጭ እንደሆነ ያምናሉ። ይህንን ሃሳብ ራዲካል[26] እንስታውያን በጽኑ ይቃወሙታል። ምክንያታቸው ሥርዓቱን መሰረታዊ በሆነ መልኩ መለወጥ የሚቻለው ጥገናዊ ለውጥ በማድረግ ሳይሆን አባዊ ሥርዓቱ መሰረታዊ በሆነ መንገድ ሲለወጥ ነው የሚል አቋም አላቸው።

ሌላው የእንስታውያን ቲዮሪ ዓይነት ባህላዊ እንስታዊ (Cultural Feminism) ነው። ቲዮሪው እንደሚያምነው ለሥርዓት ጾታ ልዩነት መፈጠር ምክንያቱ በየባህሉ ውስጥ ለሴትና ለወንድ የተሰጠው ሚዛናዊ ያልሆነ ሰብዕና ነው የሚል ነው። በዚህም የወንዱን ገጽታ ይበልጥ ከፍ ማድረግ ማኅበረሰቡን ጎድቶታል፤ የሴቶችን ሰብዕና ዝቅ በመደረጉ ደግሞ ማኅበረሰቡ ጥቅም አጥቷል በሚል ይከራከራሉ። በመሆኑም ማኅበረሰቡ ባልተገባ አኳኋን ከሴቶች ያጣውን ጥቅም እንዲያገኝ፣ የሥርዓተ ጾታም እኩልነት እንዲመጣ የሴቶች ገጽታ መጉላት አለበት በሚል ይስማማሉ። ከዚህም በላይ ከፍ አድርገው የሴትነት ባህሪያት በሙሉ (አሉታዊ የሆኑትን ጨምሮ) እንደገና በአዎንታ ሊገለጹ ይገባል ሲሉ ያሳስባሉ። ምክንያታዊ ያልሆነው የወንዶች አዎንታዊ ገጽታ ምክንያታዊ ያልሆነውን የሴቶችን አሉታዊ ገጽታ አምጥቷል በሚል ይከራከራሉ።

ባህላዊ እንስታውያን የወንድን ዘላለማዊ የበላይነት አስተሳሰብ አይቀበሉም። በሂደትም ሊቀየር የሚችልም እንደሆነ ያምናሉ። አቋማቸው ሥርዓተ ጾታዊ አድልዎ በሂደት

---

26 Libral እና radical ለሚሉት የእንግሊዝኛ ቃላት ጽንሰ ሃሳቡን የሚወክሉ አቻ የአማርኛ ቃላት ስላልተገኘ ቃሎችን እንዳለ መጠቀሙ ተመርጧል።

እውን የሆነ የባህል ውጤት ነውና አለዋወጡም በሂደት መሆን አለበት ባይ ናቸው፡፡ እንዴት መቀየር እንደሚቻልም ይሆናል ያሉትን ሃሰብ ዘንዝረዋል፡፡ እነዚህም አንደኛ የወንድና የሴት ስራ ብለው ሳይለዩ ሚናን ማዋሃድ (role acculturation)፤ ሁለተኛ ሴትነትን ከራሳቸው ከሴቶች ውስጣዊ ባህሪ በመነሳት እንደገና በማግለጽና ሰብዕናቸውን በመገንባት የሚፈለገውን እኩልነት ማምጣት እንደሚቻል ያምናሉ (Marler 2003)፡፡

የዚህ ጥናት አቅራቢም በባህላዊ እንስታውያን ሃሳብ ይስማማል፡፡ በመሆኑም በትንተናው ውስጥ የሴቶችን አሉታዊ ገጽታ ያሳያሉ በተባሉት ተረቶች ውስጥ አዎንታዊ ገጽታዎቻቸውን ለማውጣት ጥሯል፡፡

የጥናቱ ትኩረት በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ ስለሆነ ከእንስታዊ ቲዮሪ አንጻር መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በማኅበረሰቡ ውስጥ ባለ ማንኛውም መዋቅር ውስጥ ከሴትና ከወንድ ጋር በተያያዘ ያለውን የሴትነትና የወንድነት አስተሳሰብና ውክልና እንደገና መርምሮ፣ ፈክሮ (reexamine አድርጎ) የቀደመው ሥርዓተ ጾታዊ አስተሳሰብ ትክክል አለመሆኑን ለማሳየት ንድፈሃሳቡ ተገቢ ነው፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ውስጥ የሰፈነውን የበላይነትና የበታችነት (dominance and subordination) ለማጠየቅ እንስታዊ ቲዮሪ ወቅታዊም ተገቢም ነው፡፡ በዚያ ላይ ከሰብዓዊ መብት አንጻር ወደፊት ምን መሆን አለበት በሚለው ሃሳብ ዙሪያ አወንታዊነት ያለው ይሁንታ ለመሰንዘርም የእንስታውያን ሃሳብ ጥሩ መሰረት ይሆናል፤ ነውም፡፡

Kabaji (2005:5) እንደሚሉት በሃይማኖት፣ በባህልም ይሁን በአባዊ መዋቅሩ አማካኝነት በተደነገጉ ህጎች ምክንያት በሴቶች ላይ የተጫኑትን ወይም ከአንድ ወገን ብቻ የተሰናዱ ደንቦችን፣ እሴቶችን፣ እና ድርጊቶችን ተገቢ አለመሆን ለመከራከር ቲዮሪው ዓይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ክርክሩም በአባዊው ማኅበራዊ መዋቅሮች፣ ግንኙነቶች፣ ማንነቶችና ርዕዮተ ዓለሞች ዙሪያ ይሆናል፡፡ እነዚህን አንጻሮች ከእንስታውያን ቲዮሪ አንጻር መመልከት ለጥናቱ የተሟላ መሆን አስተዋጽኦ አለው፡፡

ከዚህ በላይ እንደተገለጸው ይህ ጥናት የተከተላቸው ንድፈሃሳቦች መዋቅራዊ ግልጋሎታዊና እንስታዊ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ጥናቱ ከተከተላቸው ፈለጎች ጋር የሚሄድ እና ዓላማውን ከግብ ያደርሳሉ በሚል መዋቅራዊ ግልጋሎታዊ የትንተና ስልት (structural functional analysis) እና ሃቲታዊ ትንተና (discourse analysis) በጥምረት አገልግለዋል፡፡ ሃቲታዊ ትንተና Nenola (1993:52) እንደገለጹት ትርጉም

በመፈለግ ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በተለይም የእንስታውያን ሃቲታዊ ትንተና ነገረ ስሪቱ አባዊ ሥርዓቱ ከሥልጣን ጋር ያለውን ግንኙነት በተለይም ወንዱን እንደ አንድ ማህበራዊ ቡድን በተቀነባበረ ስልት የሥልጣን ተጠቃሚ ያደረገውን በአንጻሩ ሴቶችን እንደሌላ ማኅበራዊ ቡድን ከሥልጣን እንዲገለሉ፣ ተጠቃሚ እንዳይሆኑ ምክንያት የሆነውን በውል መመርመር ነው (Lazar 2007:145)፡፡ በእያንዳንዱ ማኅበራዊ ድርጊያዎች (social practices) ውስጥ ሰምና ወርቅ ሆነው የገቡትን የሥልጣንና የርዕዮተ ዓለም ጉዳዮች ብዙውን ጊዜ ለየሰዉ ግልጽ ያልሆኑትን አውጥቶ ማሳያው ሃቲታዊ ትንተና ነው፡፡

ቀደም ብሎም በዝርዝር ዓላማው እንደሰፈረው የዚህ ጥናት አንዱ ተግባር የሥርዓተ ጾታን እኩልነት ይጋፋሉ ከሚባሉት ቃላዊ ተረኮች በስተጀርባ ያለውን "እውነታ" በሃቲት ተንትኖ ማሳየት ነው፡፡ እናም ተገቢው የመተንተኛ ዘዴ ሃቲታዊ ትንተና ስለሆነ፣ እንስታውያንም እስከ ዛሬ ተሰብስበው የተጠኑት ፎክሎሮች እንደገና ከሴቶች አንጻር መጠናት አለባቸው ባሉት መሰረት (ፈቃደ 1991) ፈለጉ ለዚህ ጥናት ተመርጧል፡፡

## 3.2 የመረጃ አሰባሰቡ ሂደት፣ የመረጃ ምንጮች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና ሥነምግባራዊ ታሳቢዎች

በዚህ ስር ለጥናቱ ያገለገሉ የመረጃ አይነቶች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ ስልቶች፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ቁሶች እና አጥኚው ስለተከተላቸው የምርምር ሥነምግባሮች ተገልጿል፡፡

### 3.2.1 የመረጃ አሰባሰቡ ሥርዓትና ቅደም ተከተል

የመረጃ ስብስባው የተካሄደው በሁለት አውዶች ላይ ነው፡፡ እነዚህም በቤተመዛግብትና በመስክ ላይ የተደረጉ ናቸው፡፡ ሁለቱም የየራሳቸው ሥርዓትና ቅደምተከተል ያላቸው ስለሆነ ለየብቻ ቀርበዋል፡፡

#### 3.2.1.1 የቤተመዛግብት መረጃዎች አሰባሰብ ሥርዓትና ቅደምተከተም

የቤተመዛግብት መረጃዎችን መሰብሰብ የተቻለው የመስክ መረጃዎች ከመሰብሰባቸው በፊት ነው፡፡ የመረጃ አሰባሰቡም ሂደት የተከናወነው በቅድሚያ ተረቶች አሉባቸው የተባሉ የታተሙ የተረት መጻህፍትን እንዲሁም ጥናታቸውን በተረት ላይ ያደረጉ የታተሙና ያልታተሙ ሥራዎችን መዘርዝር በማዘጋጀት ነው፡፡ መጽሐፎችና የጥናት

ሥራዎች የተገኙት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ዓብያተ መጻሕፍት፣ ከኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ቤተመጻሕፍት፣ እንዲሁም አንዳንዶችን ከመጻሕፍ መሸጫ መደብሮች አፈላልጎ በመግዛት ነው፡፡ ከነዚህም ሥራዎች ውስጥ የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን ኢፍትሃዊ መስተጋብር ያሳያሉ የተባሉ ተረቶች ተመርጠው፣ በይዘታቸው ተከፋፍለው በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡

### 3.2.1.2 የመስክ መረጃዎች አሰባሰብ ሥርዓትና ቅደምተከተም

አጥኚው ወደመስክ ከመውጣቱ በፊት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ማንነቱን፣ የጥናት ቦታዎቹንና የጥናት ርዕሱን የሚገልጽ ደብዳቤ አስጽፎ ለደቡብ ወሎ ባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤት አቅርቧል፡፡ የደቡብ ወሎ ባህልን ቱርዝም ጽህፈት ቤትም በበኩሉ የደረሰውን ደብዳቤ መሰረት አድርጎ ለወረዳዎች የጻፈለትን አገናኝ ደብዳቤ በመያዝ ወደተመረጡት ወረዳዎች ሄዷል፡፡ ወረዳዎችም ላይ እንደደረሰ የተጻፈለትን ደብዳቤ በማሳየት ትብብራቸውን ለማግኘት ችሏል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ በሶስቱም ወረዳዎች በተመሳሳይ በቅድሚያ የተደረገው በባህልና ቱሪዝም ጽህፈት ቤቶች እና በሴቶችና ህጻናት ቢሮ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች በኩል በወረዳው ውስጥ በዕድሜ የገፉ እንዲሁም በተራችነታቸው የታወቁ ሴቶችንና ወንዶችን አፈላልጎ ማግኘት ነበር፡፡ በዚህም መሰረት ማኅበረሰቡ በተራችነታቸው እውቅና የሰጣቸውን ሰዎች በአካል በማግኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ የተደረገው ዓቢይ ሥራ በቅድሚያ ተረቶችን እንድናገሩ ማድረግ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የተረኩትን ተረት ይዘት በተመለከተ እራሳቸው ተራኪዎቹ እንዲናገሩ ማድረግ ነበር፡፡ ከአንድ በላይ መረጃ ሰጪዎ በተገኙበት አጋጣሚ በይዘቱ ላይ እንዲወያዩበት ተደርጓል፡፡ ተረቱ እና ሙሉ ውይይቱ በመቅረጸ ድምጽ ተይዟል፡፡ ይህ የተደረገው የመረጃ ሰጪዎቹ ሙሉ ፈቃድ ከተገኘ በኂላ ነው፡፡ መጀመሪያ ላይ የተገኙት መረጃ ሰጪዎች በሚሰጡት ጥቆማ መሰረት ሌሎች ተራቾችንም ለማግኘት ተችሏል፡፡

ከዚህ ቀጥሎ ተረቶችን ለማሰባሰብ የተቻለው ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ነው፡፡ ይህም የተደረገበት ምክንያት ማኅበረሰቡ እውቅና ከሰጣቸው ተራኪዎች ከተገኙት ተረቶች ባሻገር ያመለጡ ተረቶች ይኖራሉ በሚል ግምት ነው፡፡ በዚህም ጊዜ ሊድረግ ታስቦ

የነበረው ተማሪዎችን በማሰባሰብ በክዋኔ የተደገፈ መረጃ ለማግኘት ነበር፡፡ ሆኖም ኩታበርና ተሁለደሬ ላይ በተደረገው ሙከራ ተማሪዎች ተረት ናቸው ብለው ያቀረቧቸው ከተረት ውጭ የሆኑ ቀልዶችና ትረባዎች ስለነበሩ አጋጣሚው ቀዳማይ መረጃ ሳያስገኝ ቀርቷል፡፡

ይሁን እንጂ አጥኚው በሶስቱ ወረዳዎች ካገኛቸው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጋር በመስማማት ተማሪዎች ከወላጆቻቸው ተረቶችን ጠይቀው በጽሑፍ እንድያመጡ (ካልዓይ መረጃ) ተደርጓል፡፡

ከእነዚህ ሁሉ ምንጮች የተገኙት ተረቶች በየይዘታቸው ከተለዩ በኋላ የተረቶችን ጭብጥ ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ የነበረውን የተተኳሪ ቡድን ውይይት የመነሻ ጥያቄ በመከለስ የቡድን ውይይት ተደርጓል፡፡ የቡድን ውይይቱ በሴትና በወንድ ተለይቶ ሲደረግ የአጥኚው ሚና የመነሻ ጥያቄዎችን ማቅረብ እንዲሁም ተወያዮቹ ከአጥኚው ዓላማ የመውጣት አዝማሚያዎች ሲያሳዩ የመመለስ ድርሻ ብቻ ነበረው፡፡ ከዚህ በተረፈ የእያንዳንዱን ተወያይ ዝንባሌና አመለካከት ከማጤን ውጭ ተወያዮችን ወደአንድ የማስማሚያ ሃሳብ ለመሳብ ሙካራ አላደረገም፡፡ ሙሉ መረጃው የተሰበሰበው በዚህ ሂደት ነው፡፡

## 3.2.2 ለጥናቱ ያገለገሉ የመረጃ ዓይነቶች

ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው መረጃዎች የተሰበሰቡት ከቀዳማይና ካልዓይ (ከመስክ እና ከቤተመዛግብት) ምንጮች ነው፡፡ መረጃዎቹ ጥናቱ በአቢይና በዝርዝር ዓላማ መልክ ነድፎ ሊያሳካቸው በፈለጋቸው ሃሳቦች ዙሪያ ተገቢ መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የተደረጉ ናቸው፡፡

### 3.2.2.1 የመስክ መረጃዎች

እነዚህ በተለምዶ የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳማይ) የመረጃ ምንጮች የሚባሉት ናቸው፡፡ ቀደም ብሎ በጥናቱ ወሰን ላይ እንደተመላከተው ጥናቱ የመስክ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ብቻ በኢላማ ናሙና በተመረጡ ሶስት የደቡብ ወሎ ወረዳዎች ላይ አተኩሯል፡፡ ከነዚህ ወረዳዎች የተሰበሰቡት የመስክ መረጃዎች፡-

1. ጥሬ መረጃዎች፡- ከሥርዓተ ፆታ እና ሥልጣን መስተጋብር ጋር ግንኙነት ያላቸው ተረቶች፣[ከሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችና ከክረምት ሰልጣኝ መምህራን የተሰበሰቡት ቀዳማይ መረጃዎች ሳይሆኑ ካልዓይ ናቸው፡፡]
2. ከሴትና ከወንድ እኩልነት ጋር በተያያዘ ያላቸውን አስተሳሰብ ለማወቅ በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሰበሰቡ ናቸው፡፡

እንዲህ ዓይነት መልክ ያላቸው መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በየዓይነታቸው ተለይተው አስፈላጊ በሆነበት ቦታ ሁሉ በጥናቱ ውስጥ ተካትተዋል፡፡

### 3.2.2.2 የቤተመዛግብት መረጃዎች

የቤተመዛግብት መረጃዎች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች በሚል የሚታወቁት ናቸው፡፡ በእነዚህ አውዶች ለጥናቱ አካባቢ ዳራዊ መግለጫ፣ ለክለሳ ድርሳን፣ ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ላላቸው ንድፈ ሃሳቦች እና ለትንተና የሚሆኑ ጥሬ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡

ስለጥናቱ አካባቢያዊ ዳራ በጠቅላላው ደቡብ ወሎን በተመለከተ ዳራዊ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሰነዶች ተነብበ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ እነዚህም መረጃዎች ከመስክ ከተገኙት ጋር ተጣጥመው በአጭሩ አካባቢውን ለማስተዋወቅ አገልግለዋል፡፡

ከክለሳ ድርሳናት ጋር በተያያዘ፣ የተሰበሰቡትን ጥሬ መረጃዎች ለመተንተን የሚያስችሉ ንድፈሃሳቦችን ለመቀመር፣ የትንተና ማጣቀሻዎችን ለማስገባት፣ ከርዕሰ ነገሩ አንጻር ተገቢ የሆነውን ሥነዘዴ ለመወሰንና ይህንኑ በማስረጃ ለማቅረብ አገልግለዋል፡፡ በተጨማሪም ከጥናቱ ርዕስ ጋር በተያያዘ እነማን ምን ሰሩ? ይህ ጥናት ከእነርሱ በምን ይለያል? ብሎ ለመለየትና ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ ለመንደፍ ረድተዋል፡፡

## 3.2.3 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና የመረጃ ሰጪዎች አመራረጥ

ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥቅም ላይ የዋሉት ቃለመጠይቅ፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይት፣ የቤተመዛግብት ዳሰሳ እና "መጠይቅ" ናቸው፡፡

### 3.2.3.1 ቃለመጠይቅ

ዓይነታዊ ምርምር ከሚጠቀምባቸው የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ ቃለመጠይቅ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ አንድን የፎክሎር መረጃ በአውዱ ላይ ተገኝቶ ማሰባሰብ በማይቻልበት ጊዜ ተቀዳሚ ዘዴ ሆኖ ያገለግላል፡፡ በዚሁ መሰረት በሶስቱም ወረዳዎች ከተመረጡ 28 መረጃ አቀባዮች ጋር ቃለምልልስ ተካሂዷል፡፡ ቃለመጠይቁ ያተኮረበት ጉዳይ ተረቶችን ከነትርጉማቸው ለማሰባሰብ እንዲሁም ሃይማኖቶች ከሥርዓተ ጾታ ጋር ያላቸውን ትስስር ለማወቅ የተደረገ ነው፡፡

መረጃ ሰጪዎች የተመረጡት በኢላማ ናሙና (purposive sampling) ዘዴ ነው፡፡ ምክንያቱም ተረክ የመተረክ ብቃት እንዲሁም ተረኮችን በአዕምሮ ይዞ እያስታወሱ ማቅረብ ከሰው ሰው ይለያያልና ማኅበረሰቡ እገሌ ወይም አገሊት ተራች ነው/ናት ብሎ በሚያምነው መሰረት ተመርጠዋል፡፡

በመስክ ቆይታ ጊዜ 84 ያህል ተረቶችን በቃለመጠይቅ ለማሰባሰብ የተቻለ ሲሆን (ድግግሞቹን ጨምሮ) ከነዚህ ውስጥ ከጥናት ርዕሱ ጋር ቀጥተኛ ዝምድና ያላቸውን 19 ተረቶችን ማግኘት ተችሏል፡፡ በዚህ ወቅት ተራቾች ተረቶችን እንዳቀበሉ ወዲያውኑ ስለተረኳቸው ተረቶች ይዘት እዚያው እንዲናገሩ ተደርጓል፡፡ ይህ መረጃ በትንተናው ወቅት ጠቃሚ የመነሻ ሃሳብ ለማግኘት ረድቷል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሃይማኖት ከሥርዓተ ጾታ ጋር ተያይዞ ለተገለጸው በግብዓትነት ያገለገለ ቃለመጠይቅ ከአንድ የክርስትና ሃይማኖት የትርጓሜ መምህርና ከሌላ አንድ የእስልምና ሃይማኖት የተፍሲር (የቁርዓን አንድምታ) አዋቂ ጋር ተደርጓል፡፡ ምሁራኑ የተመረጡት በየተቋሞቻቸው ባላቸው እውቅና እና ሙያ አማካኝነት ነው፡፡ የመጽሐፍ ቅዱስን አንድምታና የቁርዓንን ተፍሲር በተሻለ ያውቃሉ የሚባሉትን እና መጽሐፎችንም በማስተማር ላይ ያሉትን ነው፡፡

ከሃይማኖት አባቶች ጋር የተከናወነው ቃለምልልስ አስቀድሞ የመነሻ ጥያቄዎችን በማዘጋጀት ነው፡፡ ይሄውም ሁለት መልክ ያለው ነው፡፡ አንደኛው የሃይማኖት ምሁራኑ በየሃይማኖታቸው ያለውን የሚያውቁትን የሥርዓተ ጾታ አያያዝ ከየሃይማኖት መጻሕፍቱ እያጣቀሱ ማብራሪያ እንዲሰጡ የተደረገበት ነው፡፡ ሁለተኛው አጥኚው የሃይማኖት መጻሕፍት እና ሌሎች ከሥርዓተ ጾታ ጋር በተገናኘ በሃይማኖት ሰዎች

የተደረሱትን መጻሕፍት ሲያነብ ማብራሪያ ያስፈልጋቸዋል ብሎ ባሰባቸው ነጥቦች ላይ ነው፡፡

### 3.2.3.2 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በዚህ ጥናት ውስጥ በሁለተኛነት አገልግሎት ላይ የዋለው የመረጃ ማሰባሰቢያ ስልት ተተኳሪ የቡድን ውይይት ነው፡፡ ይህ ስልት አገልግሎት ላይ የዋለው ሴቶችና ወንዶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ምን ዓይነት ማኅበራዊ ሚና እና ስፍራ እንዳላቸው ለማወቅና በተረቶች ከሚነገረው ጋር በማስተያየት ትንተናውን ለማካሄድ ነው፡፡ ለዚህም ያመች ዘንድ ለሁለቱም ጾታዎች የመነሻ ጥያቄዎች ተዘጋጅተው ቀርበዋል፡፡

ተተኳሪ የቡድን ውይይቱ በእያንዳንዱ ወረዳ በጾታ ተለይቶ በሁለት ቡድን ተካሂዷል፡፡ እያንዳንዱ ተተኳሪ ቡድንም በአማካይ ከ5-8 አባላት ያሉት ሲሆን በቁጥር 17 ወንዶች እና 19 ሴቶች በድምሩ 36 ናቸው፡፡ አመራረጡም እንደተገኘ ከተሰበሰቡት ውስጥ በኢላማ ናሙና ዘዴ ነው፡፡ ለመምረጥ በመስፈርትነት የዋለው ትዳር፣ ዕድሜና ሃይማኖት ናቸው፡፡ በዚህም መሰረት በተተኳሪ የቡድን ውይይቱ የተሳተፉት ትዳር ያላቸው ሆነው በትዳር ከ6 ወር እስከ 26 ዓመት የቆዩና በሃይማኖት ስብጥርም ረገድ ከእስልምናውም ከክርስትናውም  እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

ተተኳሪ የቡድን ውይይቱ በጾታ ተለይቶ የተደረገበት ምክንያት በመካከላቸው አላስፈላጊ የሆነ ክርክር እንዳይነሳና የመፈራራት ስሜት እንዳይኖር በሚል ነው፡፡ ሁሉም ትዳር ያላቸው እንዲሆኑ የተደረገውም ስለሥርዓተ ጾታ አድልዎም ይሁን እኩልነት እንደየዕድሜያቸው የየራሳቸውን ገጠመኝ እያነሱ ውይይቱን በተሻለ መንገድ ማካሄድ እንዲቻል ነው፡፡ የሃይማኖት ስብጥሩንም እንዲጠበቅ የተደረገው የመረጃውን ሚዛናዊነት ለመጠበቅና በየሃይማኖቶቹ ውስጥ ያሉትን ትዕዛዛትና መብቶች እያጣቀሱ ሊናገሩ ይችላሉ በሚል እምነት ነው፡፡

### 3.2.3.3 የቤተመዛግብት ዳሰሳ

ለጥናቱ በግብዓትነት ከዋሉት ውስጥ በጽሁፍ የሰፈሩ ተረቶችም ይገኙበታል፡፡ የሚገኙትም በቤተመዛግብት ውስጥ በመሆኑ የመረጃ ስብሰባው በዚያም አቅጣጫ ተካሂዷል፡፡ በዚሁ መሰረት የተረት መጻሕፍትን እንዲሁም በተረት ላይ የተደረጉ የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ እና ሦስተኛ ዲግሪ የጥናት ስራዎች በማሰባሰብና መዘርዝር

በመስራት የተከናወነ ነው። በመዘርዝሩ መሰረት መጻሕፍትና የጥናት ስራዎች በጥልቀት ተነበው ለዚህ ጥናት በግብዓትነት የዋሉ 54 ያህል ተረቶችን ለማግኘት ተችሏል።

በኩታበር ወረዳ ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ውስጥ በሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና በወረዳው ባህልና ቱሪዝም ጽ/ቤት ባለሙያዎች ተሰባስበው የተቀመጡ ተረቶችን ለማግኘት ተችሏል። ሆኖም እነዚህ ተረቶች ቀደም ብለው ተሰብስበው ከተያዙት ተረቶች ጋር ተመሳሳይ ስለሆኑ በዚህ ጥናት ውስጥ ተመርጠው የተካተቱ የሉም።

### 3.2.3.4 “መጠይቅ”

“መጠይቅ” በዚህ ጥናት ውስጥ በመረጃ መሰብሰቢያነት የዋለው መረጃ ሰጪዎች ተረቶችን በጽሑፍ የሰጡበትን ስልት ብቻ ነው። በዚህ ስልት መረጃዎችን ማሰባሰብ የተቻለው ለጥናት በተመረጡት ወረዳዎች ካሉ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች እና በክረምቱ መርሃ ግብር ከሚማሩ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ነው።

ከሶስቱ ወረዳ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተረቶችን ማሰባሰብ የተቻለው ለዚሁ ተግባር በተመረጡ ሶስት የሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አማካኝነት ነው። መምህራኑም መረጃዎችን በረዳትነት በጽሑፍ ሲያሰባስቡ እያንዳንዳቸው 25 የገጠርና 25 የከተማ በድምሩ 50 ተማሪዎችን እንዲጠቀሙ፣ የሚያሰባስቧቸው ተረቶች ተማሪዎች ከወላጆቻቸው የሚጠይቋቸው ሆነው በተቻለ አቅም ከሥርዓተ ጾታ ጋር ግንኙነት ያላቸው እንዲሆኑና በሃይማኖት ስብጥርም ማመጣጠን እንደሚገባ ቅድሚያ ስምምነት ተደርጎ ነው። በዚህ መሰረት በጥቅሉ ከሶስቱ ወረዳዎች ይጠበቁ ከነበሩት 150ና በላይ ተረቶች ውስጥ ማግኘት የተቻለው ከ74 መላሾች 80 ያህል ብቻ ነው። ከነዚህም ውስጥ ለጥናቱ ቅርበት ያላቸው 11 ተረቶች ብቻ ተመርጠዋል።

በወሎ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ጥናት-አማርኛ ትምህርት ክፍል በክረምቱ መርሃ ግብር ይማሩ ከነበሩት የአንደኛ ዓመት ተማሪዎች ተረቶች የተሰበሰቡት በአጥኚው ነው። መረጃ ሰጪዎችም ለጥናት ከተመረጡት ወረዳዎች የመጡ፣ አጥኚው ባስተማራቸው 3 ሴክሽኖች ውስጥ ሲማሩ የነበሩት በሙሉ ናቸው። ቁጥራቸውም 23 ሲሆኑ ከእነርሱም 51 ያህል ተረቶችን ማግኘት ተችሏል። ከነዚህ ውስጥ 16 ያህሉ ለጥናቱ ባላቸው ቀረቤታ ተመርጠዋል። ተረቶችም የተሰበሰቡት ነሐሴ 2007 ዓ.ም ነው። በዚህ መንገድ የተሰበሰበው መረጃ መስክ ላይ ስለተገኘ ብቻ ቀዳማይ አይባልም።

በተለይም የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች መረጃዎችን ያመጡበት ወላጆቻቸውን ጠይቀው ስለሆነ በሁለተኛ ወገን የመጣ ነው፡፡ በመሆኑም ከቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ሊመደብ አይችልም፡፡

በጠቅላላው ለጥናቱ ከተመረጡት ወረዳዎች እና ከቤተመዛግብ ከተገኙት ሰነዶች በቃለመጠይቅ፣ በመዛግብት ዳሰሳ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት እና በመጠይቅ ለጥናቱ ግብ መቺ ናቸው ተብለው የታመነባቸው አንድ መቶ (100) ተረቶች[27] ተመርጠዋል፡፡ እነዚህም በአባሪ የተያያዙ ሲሆን አብዛኞቹ በትንተናው ተካትተዋል፡፡ መደበኛ በሆነ መንገድ ቃለመጠይቅን፣ ተተኳሪ የቡድን ውይይትን፣ የቤተመዛግብት ዳሰሳንና መጠይቅን አጥኚው ይጠቀም እንጂ ሌሎች አጋጣሚዎች ታልፈዋል ማለት አይደለም፡፡ ኢመደበኛ በሆነ መንገድ ከግለሰቦች ጋር በተፈጠረ ግንኙነት ለማጠናከሪያ ያገለገሉ ሃሳቦችን ለማግኘት ተችሏል፡፡

### 3.2.4 የምርምር ሥነምግባር

አንድ አጥኚ የሚፈልገውን መረጃ ለማግኘት የተጠኚውን ማኅበረሰብ መምሰልና ባህሉን ማክበር አለበት፡፡ ከዚህም በላይ ስለራሱ ማንነት፣ ስለጥናቱ ዓላማና ስለህጋዊነቱ ለተጠኚው አካል ማሳወቅ ከአጥኚው የሚጠበቅ የምርምር ሥነምግባር ነው፡፡ በዚህም መሰረት አጥኚው ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተጻፈለትን የትብብር ደብዳቤ ለደቡብ ወሎ ዞን ባህልና ቱሪዝም ቢሮ በማቅረብ፣ በማጻፍ በሶስቱም ወረዳዎች ለሚገኙ የባህል ጽሕፈት ቤቶች እና የሴቶችና ወጣቶች ጽሕፈት ቤት በማቅረብና ማንነቱን በግልጽ በማስረዳት ፈቃዳቸውን እንዲሰጡትና ከመረጃ አቀባዮች ጋር እንዲያገናኙት አድርጓል፡፡

አጥኚው በኃላፊዎችና በሚያውቃቸው ሰዎች አማካኝነት ከመረጃ አቀባዮች ጋር እንደተገናኘ በድጋሚ ማንነቱን፣ የሚሰራበትን መስሪያ ቤት፣ የሚማርበትን ዩኒቨርሲቲ፣ እንዲሁም ለምን ዓላማ በአካባቢዎች እንደተገኘ እነሱን ለምን እንደፈለጋቸው በቻለው

[27] በአባሪ የተያየዙት ተረቶች ርዕስ ያላቸውና የሌላቸው ናቸው፡፡ ርዕስ የሌላቸው ከመስክ የተሰበሰቡት እና ከጥናታዊ ጽሑፎች የተገኙት ናቸው፡፡ ከመስክ የተሰበሰቡትን መረጃ ሰጪዎች በቃልም ይሁን በጽሑፍ ሲያቀብሉ ርዕስ ስላልሰጧቸው፣ ተረት የመተረክ ልማዱም ርዕስ እንዲሰጡ ስለማያስገድድ ርዕስ የላቸውም፡፡ ከጥናታዊ ጽሑፎች የተገኙትም ቢሆኑ አጥኚዎቹ ርዕስ አካትተው ስላልጻፏቸው በዚያው መንገድ በዚህ ጥናት ተቀምጠዋል፡፡ ከተረት መጻሕፍት የተገኙት ግን ሰብሳቢዎቹ ርዕስ ሰጥተው ስላሰፈሯቸው ያው እንዳለ ቀርቧል፡፡

አቅም አስረድቷል፡፡ ያገናኙትን ሰዎች ስለ አጥኚው እንድናገሩ አድርጓል፡፡ በዚህም ጥሩ መተማመን ለመፍጠር ተችሏል፡፡

መረጃ አቀባዮች የሰጧቸውን መረጃዎች እገሌ ወይም እገሊት ይህንን መረጃ ሰጥቷል/ሰጥታለች በሚል ስም ተጠቅሶ በጥናቱ ውስጥ እንደማይካተት[28]፣ የሰጡትም መረጃ ከጥናቱ አላማ ውጪ ጥቅም ላይ እንደማይውል፣ ለሌላ ግለሰብም ሆነ ተቋም (ጥናቱ ከሚቀርብለት ተቋም በስተቀር) መረጃው ተላልፎ ለማንም እንደማይሰጥ እና የግል ሚስጥራቸውን የአጥኚው ሚስጥር ተደርጎ እንደሚያዝ ማረጋገጫ ተሰጥቷል፡፡

[28] እዚህ ላይ አጠኚው ይህን ያደረገው ከመረጃ ሰጪዎች ፍላጎት አንጻር ነው፡፡ ከአባ ፍቅረማርያም በስተቀር ሌሎቹ ስማቸው ተጠቅሶ በጥናቱ ላይ እንዳይቀርብ ሃሳብ ስላቀረቡ ነው፡፡ የቦረና ወረዳ መረጃ አቀባዮች በጥናቱ ውስጥ ስማቸው ቢጠቀስም ባይጠቀስም ቅር እንደማይላቸው አረጋግጠው ነበር፡፡ ሆኖም እያመነቱ ከማስገባት መተው ይሻላል በሚል ስማቸው አልተጠቀሰም፡፡ አባ ፍቅረማርያም ግን ሙሉ ፈቃደኛ ስለነበሩ ስማቸውን ለማስገባት ተችሏል፡፡

# ምዕራፍ አራት

# ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፎችና የቀደምት ሥራዎች ቅኝት

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት አራት ነጥቦች ተዳሰዋል፡፡ እነዚህም በጥናት ርዕሱ የተገለጹትን ቁልፍ ቃላት ትርጉም፣ ከዚያም ጥናቱ በስፋት ከሚመለከተው የተረት፣ የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ንድፈሃሳብ ጋር በተያያዘ ያለውን እውነታ ከመስኩ ምሁራን ሃሳብ አንጻር ምን መልክ እንዳለው፣ በሶስተኛ ደረጃ ባገራችን ውስጥ በተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ባህሎች ውስጥ የሥርዓተ ጾታ አያያዙ ምን መልክ እንዳለው፣ እንዲሁም ከዚህ የጥናት ርዕስ ጋር በተያያዘ በጥናታቸው እነማን ምን አሉ? ይህ ጥናት ከእነርሱ በምን እንደሚለይ ተዳስሶበታል፡፡

## 4.1 የተረት፣ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ትርጉምና ጽንሰሃሳባዊ ማዕቀፎች

በዚህ ስር ትኩረት የተሰጣቸው በጥናት ርዕሱ የተገለጹት ተረት፣ ሥርዓተ ፆታ እና ሥልጣን ናቸው፡፡ እነዚህን የጥናቱን ቁልፍ ቃላት በተመለከተ ሁሉአቀፍና የመጨረሻ የማያሻማ ትርጉም ለመስጠት አልተሞከርም፡፡ ይደረግ ቢባልም ከጽንሰ ሃሳቦቹ የትርጉም ስፋትና አወዛጋቢነት አንጻር አይሆንምም፤ አይቻልምም፡፡ ሆኖም ግን ከጥናቱ ጋር የሚሄድ ተግባራዊ ብያኔ (operational definition) መስጠት ስለሚያስፈልግ ይሄው ተደርጓል፡፡ ከዚያም ቀጥሎ እነዚሁኑ ዋና ዋና ቃላት ተንተርሶ ያለው ጽንሰ ሃሳብ በእያንዳንዱ ስር ቀርቧል፡፡ በዚህ ስር በተረት አገልግሎት እንዲሁም በሥርዓተ ጾታና በሥልጣን መስተጋብር ዙሪያ በመስኩ ምሁራን ከቀረቡ ሃሳቦች አንጻር ለየብቻ ቅኝት ተደርጓል፡፡ በመጨረሻም ተረት፣ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን እንዴት እንደሚተሳሰሩ ለማሳየት ተሞክሯል፡፡

### 4.1.1 የተረት ትርጉም፣ ጽንሰ ሃሳብ እና አገልግሎት

ተረት የሥነቃል ዘርፍ ሆኖ በረጃጅም ትረካ መልክ ብዙውን ጊዜ በዝርው የሚቀርብ ነው፡፡ አቀራረቡም በቃል ሆኖ በሰዎች ለሰዎች ከአፍ ወደ ጆሮ የሚተላለፍ ነው (Dawkins 1951፡417)፡፡ ተረቶች ምናባዊነት የሚታይባቸው፣ ከራስ ገጠመኝና አስተውሎት የሚመነጩ የፈጠራ ትረካዎች ናቸው፡ ተረት ቃላዊ ተረክ (oral narratives) በሚል ከሚትና ከአፈታሪክ ጋር ባንድ ላይ ስያሜውን ይጋራል፡፡

Finnegan (1970) እነዚሁኑ ". . . the prose narrative genre of oral literature." በማለት አጠቃለው አስቀምጠውታል፡፡ Abrams (1999:101) ይህንኑ ደግመውታል፡፡ ቃላዊ ተረኮች[29] የአንድን ማኅበረሰብ ተፈጥሯዊ አካባቢ፣ ማኅበራዊ ግንኙነት፣ ዓለማዊ አመለካከት፣ ሥርዓተ ማኅበራዊ ደንብና መመሪያ እንዲሁም ትውልዱን በእውቀት፣ በክህሎትና በሥነምግባር ተኮትኩቶ የሚያሳድግበትን ሁኔታ ያትታሉ፡፡ የሰው ልጅ እምነቱን፣ እሴቱን፣ ደንቡን፣ ላለውና ለቀጣዩ ትውልድ በቃላዊ ተረኮች ያስተላልፋል፡፡ የቃል ተረክ ያለፈ ታሪክን፣ ገጠመኝን፣ ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከትን በማስተላለፊያና በማስረጫነትም ያገለግላል፡፡ ሁሉም ትረካዎች ከማህበራዊ ገጠመኝ የመነጩ፣ በዚህም የተነሳ ተሳታፊዎች ከተራኪው ጋር አንድ ዓይነት ማንነታዊ ግንኙነት የሚመሰርቱባቸው፣ በመዝናኛነት፣ በጊዜ ማሳለፊያነት፣ በማስተማሪያነት፣ ለአንዳንድ አካባቢያዊ ክስተቶች በመግለጫነት ወዘተ. ማኅበራዊ ጥቅም (Social use) የሚሰጡ፣ ማንነትን፣ የሥርዓተ ጾታ ደንቦችን፣ ማኅበራዊ ተቋማትንና እሴቶችን ወዘተ. ተጠየቃዊ ለማድረግና ሲያስፈልግ መጠነኛ ማሻሻያ እየተደረገባቸው በነበሩበት ለማስቀጠል ማኅበራዊ አገልግሎት (Social function) የሚሰጡ ናቸው (Georges 1969፡323)፡፡

በዚህም የተነሳ አሁን ያለው ትውልድ አሁን ያለበትን ብቻ ሳይሆን እምን ላይ እንደቆመ እንዲያውቅ፣ ካለፈውና ከዛሬው ገጠመኙ ተንተርሶ የነገውንም አኳኋኑን መልክ ለማስያዝ የቃል ተረክ እጅግ መሰረታዊ ነው (ፈቃደ 1984፣ ማኅተመስላሴ 1950፣ ሃዲስ ዓለማየሁ 1948፣ Olrik 1992)፡፡

ተረቶች፣ ተራኪው በፈጠረው ምናባዊ ዓለም ውስጥ በእንግድነት ተገኝቶ ለጊዜውም ቢሆን በሳቅና በጨዋታ እንዲኖር፣ በጊዜና በቦታ ከተወሰነበት መልክዓ ምድራዊ ክልል አልፎ በምናቡ በፈጠራቸው ዓለማት ውስጥ እንዲኖር፣ በባህል ምክንያት በተጫኑበት ደንቦች ላይ እንዲያላግጥ፣ ከአቅሙና ከችሎታው በላይ የሆኑ ተግባራትን ሲፈጽም

---

[29] ቃላዊ ተረኮች የሚባሉት ሚት፣ አፈታሪክና ተረት ናቸው፡፡ ምሁራን እነዚህን በዝርዝር ከመጥራት በጥቅል ቃላዊ ተረኮች (Oral narratives) በሚል አጠቃሎ መመልከት ይቀናቸዋል፡፡ Finnegan (1970) እና Abrams (1999) ለዚህ በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህንን ያደረጉበት ምክንያት የሚጋሯቸው ባህሪያት ስላሉ ነው፡፡ ይህም የጋራ ባህሪያቸው በረጃጅም ትረካዎች መገለጽ፣ በተቀራራቢ ቅርጻዊ መዋቅር መቅረብ፣ ለማኅበረሰቡ በሚሰጡት ግልጋሎት ወዘተ. አንጻር ነው፡፡ በዚህም ስራ ውስጥ አንዳንድ ጊዜ ቃላዊ ተረክ፣ ሌላ ጊዜ ተረት በሚል የቀረበው ይህንኑ ታሳቢ በማድረግ ነው፡፡

ያሳያሉ (ፈ.ቃደ 1993፡18-20)፡፡ ይህም በተራኪው የመተረክ ብቃት ወደ ተሳታፊው ተጋብቶ ተራኪው ባለበት ዓለም ውስጥ ገብተው፣ ለጊዜውም ቢሆን ድል የሚቀዳጅበትን ዓለም ለመፍጠር የሚያስችሉ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ተረቶች ማኅበረሰቡ ልክ አይደሉም በሚላቸው ማኅበራዊና ተፈጥሯዊ ክስተቶች ላይ ትችቱን አቅርቦና ማስተካከያዎችን ሰንዝሮ ለራሱም ለተሳታፊውም አንጻራዊ ሰላም ፈጥሮ ሌሊቱን በነጻነት መንፈስ እፎይ ብሎ ለማሳለፍ የሚረዱት ናቸው፡፡ ይሄው በ Degh (1969:87) ስራ ውስጥ "The folktales serve the purpose of spiritual nourishment to the audience. They release tension and helps induce a refreshing sleep. It forms a bridge from reality to illusion, from the state of wakefulness to that of the dreams" በሚል በግልጽ ሰፍሮ እናገኘዋለን፡፡፡

ቃላዊ ተረኮች የአንድን ማኅበረሰብ ባህልና አስተሳሰብ ለመረዳት ያስችላሉ፡፡ ባህሉና የወቅቱ አስተሳሰብ በደነገገው መሰረት እያንዳንዱ የማኅበረሰቡ አባል ማንነቱንና ልኩን አውቆ በተፈቀደለት መስመር ብቻ ይንቀሳቀስ ዘንድ ለማሳወቅ ብሎም ተግባራዊ እንዲያደርግ ሚናቸው ከፍ ያለ ነው (Swann 1993፡24)፡፡ ከዚህም በላይ የየወቅቱን ማኅበራዊ፣ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ አንድምታዎችን አምቀው ይይዛሉ፡፡ Olrik (1992፡1) እንደሚሉት የቃላዊ ተረኮች ተቀዳሚ ተግባር ሰዎች በየዘመናቱ የነበራቸውን እውቀት (human intellectual life) መቅረስ፣ የማኅበረሰቡን ማህበራዊ መዋቅር፣ አምልኮና ፖለቲካዊ ክስተት ምን እንደነበረና እንደሆነ መዘገብ ነው፡፡ በመስኩም የሚደረገው ጥናት ይህንኑ ለማወቅ ነው፡፡

Songsin (1999፡6) እንደሚሉት ተረኮች መልክ የያዙ ግንዛቤዎች (constructed perceptions)፣ እምነቶች፣ ፍርሃቶች፣ ደስታዎች፣ ወዘተ በመሆናቸው የሰውን ልጅ አጠቃላይ ሁኔታ በተሻለ መንገድ ለመገንዘብ እንደሚያስችሉ ያስረዳሉ፡፡ አስከትለውም ተረኮች የማወቂያ አውዶች ወይም የእውቀት ማዕዶች በመሆናቸው ሰዎች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ሲኖሩ የነገሮችን ትክክለኛነትና ስህተትነት ይገነዘቡባቸዋል፤ በውስጣቸውም ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶችን ስለያዙ የአካባቢያቸውን የአኗኗር ይትብሃል ይማሩባቸዋል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ Awonoor (1975:76) ደግሞ ቃላዊ ትረካዎች ስለተገቢ ሥነምግባር ሲባል የታቀዱ ሥነምግባራዊ መመሪያዎችን እንደያዙ ይገልጻሉ፡፡ ይህንኑ ሃሳብ በሚያጠናክር መልኩ Jablow (1961) ጥሩ የሚባሉ የአፍሪካ ተረኮች

ከአዝናኝነታቸው ባሻገር ስለ ማኅበረሰቡ ህይወት፣ ስለመሰረታዊ ሃሳቦችና እሴቶቹ፣ ስለ ሥነምግባራዊ ሁኔታው፣ እንዲሁም ስለ ሰዋዊ ግንኙነቶቹ ብዙ እንደሚናገሩ ያስረዳሉ፡፡

ተረቶች የሰውን ልጅ መሰረታዊ ጥያቄ ይዘው የሚቀናበሩ በመሆናቸው የሁሉ አቀፍነት (universal) ባህሪ አላቸው፡፡ Dawkins (1951፡429) ይህንኑ ሲያስረዱ "the generalized and simplified nature of folktale makes them suitable to echo the common feelings of mankind, after all the fundamental situations of human life are always much the same." ይላሉ፡፡ ተረቶች በይዘታቸው ከባህል ባህል፣ ከቋንቋ ቋንቋ፣ ከአገር አገር የመለያየት እድላቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ ምክንያቱም በአለም ላይ ያለው የሰው ልጅ መሰረታዊ ጥያቄ ያን ያህል ልዩነት አያሳይም፡፡ የቋንቋ አጠቃቀሙ በየጊዜው ለውጥ እየተደረገበት ያለማቋረጥ ይቀጥላል፡፡ በይዘቱ ላይ የሚታየው ለውጥ ግን አናሳ ነው፡፡ እንደ Olrik (1992:65-69) አገላለጽ አንዳንድ መለስተኛ ለውጦች ቢታዩ እንኳን ምክንያቶቹ፡-

1. በራሱ በተረቱ ውስጥ የሚስተዋል፡- በሴራው ውስጥ የሚታየውን ግልጽ ያልሆነ ነጥብ ለማብራራት፣ ጠቃሚ የሆኑ ክስተቶችን ለማፍታታት፣ አቢይ ገጸባህሪያቱን ከሴራውና ከተቀናቃኞቻቸው ጋር ያላቸውን ግኝኙነት ምክንያታዊ ለማድረግ፣ እንዲሁም ትረካውን ለማበልጸግና ተጠየቃዊ እንዲሆን ለማድረግ ሲባል፣
2. በተራኪው ፍላጎት የተነሳ እሱ የሚሻውን ሥነምግባር ለማስረጽ ሲያስብና በሚያውቀው ተረት ውስጥ ምክንያታዊ አይደለም የሚለውን ተጠየቃዊ ለማድረግ፣
3. ተረቶች እርስ በርሳቸው በሚደራረጉት ተጽዕኖ ምክንያት ተራቹ አንዱን ተረት ከሌላኛው ተረት ታሪክ ጋር እያወራረሰ ሲያወራ የሚፈጠር፣
4. ተራኪው ያለበት ዘመን አስተሳሰብ በቀደመው ተረት አቀራረብ ወይም ጭብጥ ላይ መጠነኛ ለውጥ እንዲያደርግ ሲያስገድደው . . . ናቸው፡፡

ይህም ሆኖ ግን መሰረታዊ የሚባሉት የሰው ልጅ ጥያቄዎች ዘመን የማይሽራቸው በመሆናቸው የተረቶችም ጭብጥ መሰረታዊ በሆነ መልኩ የመለወጥ እድላቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

በእኛ አገር ቀደም ብለው ተረቶችን አሰባስበው ለህትመት ያበቁት ሃዲስ (1948) እና ማኅተመ ስላሴ (1950) ከላይ ከተጠቀሱት ምሁራን ያልተለየ ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ተረኮች ከወቅታዊ ማኅበረሰባዊ ሁኔታዎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው፣ በቦታና በጊዜ የማይወሰኑ ስለመሆናቸው፣ የየራሳቸውን ሃሳብ በመግቢያቸው ላይ አስፍረዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ስላለፈው ብሎም ስለወደፊቱ እንደሚናገሩም አስረድተዋል፡፡ ለምሳሌ ሃዲስ[30] (1948፡5) የሚከተለውን አስፍረው እናገኛለን፡፡

> *ከተረት ታላቅነት አንዱ በጊዜና በቦታ የማይወሰን መሆኑ ማለትም ላለፈ፣ ላለ፣ ለሚመጣም መሆኑና እንዲሁም ሰዎች በማኅበራዊ ኑሮ በሚኖሩበት አገር ሁሉ ለእርስ በርሳቸውና ለእያንዳንዳቸው ባህሪ ምሳሌ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ የተረትን ትርጉም ላንድ አገር፣ ላንድ ሰው ወይም ለተወሰነ ጊዜ መስጠት የጠበበ አስተያየትና ለደራሲውም ትክክለኛ ፍርድ አለመስጠት ነው፡፡ ሁለተኛም የተረት ባህሪ ሁለት መልክ ያለው መሆኑ ነው፡፡ እነርሱም ውስጣዊና አፋዊ መልክ ናቸው፡፡ ውስጣዊ መልኩ ፈረንጆች "ሞራል" የሚሉት ነው፡፡ ለተረቱ ዋጋ የሚያሰጠው ሞራሉ ነው፡፡*

Briggs (1985፡388) ይህንኑ ሃሳብ "The narratives emerge in elder's attempts to inculcate basic moral values in their juniors." ሲሉ ደግመውታል፡፡

ከነዚህ ሃሳብ የምንገነዘበው በጥቅሉ ቃላዊ ተረክ በተለይ ተረት የአዕምሮ ዕድገትን የሚያጎናጽፍ፣ የሰውን ልጅ ማኅበራዊ ሂሶችና ገጠመኞች የሚገልጽ፣ ለማህበራዊ ኑሮ ምሳሌ የሚሆን ብዙ ጠቃሚ ምክርና ምሳሌ የሚገኝበት፣ ሞራላዊ ጽንሰሃሳቦች የሚሰበኩበት ዓለማቀፋዊ ክስተት መሆኑን ነው፡፡

ከድረገጽ (http://www.folklore.ee/folklore/vol13/bihar.htm) የተገኘውም መረጃ "Folk tales, with their hidden moral values and lesson, functioned as the promoters of personal development and socialization of the people" ሲል ያስቀምጠዋል፡፡ የተረት ሞራላዊ እሴት ለትምህርት፣ ለሰብዕና ግንባታና ለመልካም ማኅበራዊ ግንኙነት መዳበር አስተዋጽኦ አለው፡፡

ቃላዊ ተረክ የአንድን ቡድን ርዕዮተዓለም (የጋራ ሃሳቦችን፣ እሴቶችን፣ እምነቶችን) በማስረጽ በኩል ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ Abreham (2007፡61) የተለያዩ ምሁራንን ሃሳብ አጣቅሰው ይህንኑ አስረግጠዋል፡፡ የአንድ ማኅበረሰብ አባላት በሙሉ የአንድ

---

[30] ደራሲ ሃዲስ ዓለማየሁ "ተረት ተረት የመሰረት" የሚባለውን መጽሃፋቸውን ያቀረቡት ተረት ብለው ነው፡፡ ለዚህ ማስረጃ ይሆን ዘንድ መግቢያቸውን ብቻ ማንበብ በቂ ነው፡፡ ሆኖም ግን የመጽሃፋቸውን አጠቃላይ ተረቶች አንብበን ጨርሰን የተረትነታቸውን ነገር ስንመረምር መልስ ያጥረናል፡፡ ምናልባት በተረት መልክ የተጻፉ የአጫጭር ልቦለዶች መድብል እንለው ይሆናል፡፡ ምክንያቱም የመስኩ ምሁራን ለተረት ከሚሰጡት ዓይነተኛ ባህሪ ውስጥ በተለይ "ቃላዊ ተስተላልፎ" የሚባለውን አያሟሉም፡፡ The New Encyclopaedia Biriatanica (1993:314) ላይ እንደሚነበበው "The most obvious characteristic of folk literature is the fact that it is oral" ይላል፡፡ ከዚህ አንጻር የሃዲስ ዓለማየሁ ተረቶች ቃላዊ ተስተላልፎ ስለሌላቸው ተረቶች ናቸው ለማለት ይከብዳል፡፡ የትም በቃል ሲነገሩ ሰምተናቸው አናውቅም፡፡ እስካሁን በቀረቡ የተረት ስብስብ መጻህፍት ላይ አንዳቸውንም አናገኝም፡፡ ይህ ተረት ላለመሆናቸው ማስረጃ ይሆናል፡፡

ዓይነት ባህል ተገዢ እንዲሆኑና ያንኑ ተቀብለው ለዘላለም መደበኛ በሆነ መልኩ እንዲጠብቁት አስፈራሪ ወይም አለዝበው የማሳመን ብቃት ያላቸው ተረኮች ከፍ ያለ ሚና ይጫወታሉ፡፡

የቃል ተረኮች የሚቀርቡት (የሚተረኩት) አንድ ማህበረሰባዊ ውቅር (Social structure) እና ደንቦቹን (Norms) ለመናድ ዳርዳር ሲሉ ለመጠገንና ህልውናቸውን ለማቆየትም ጭምር ሲባል ነው (Abreham 2007፡63)፡፡ ቃላዊ ተረክ ህብረተሰቡ ምን ያምናል፣ ምን ይጠላል፣ ምን ይወዳል፣ ምን ዓይነት አደረጃጀት ይፈልጋል፣ እርስ በርስ ሊኖረው የሚገባው ግንኙነት ምን ይምሰል፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ባንድነት አጣምሮ ወይም በተናጠል ይይዛል፡፡

ሁሉም ባህሎች ከየባለቤቶቻቸው የተውጣጣ በኋላም የጋራ የሆነ አተያይና ግምት (perceptions and expectations) አላቸው፡፡ እነዚህ አተያዮችና ግምቶች ማህበሩ ስለ ዓለም ያለውን እይታ (ንጽረተ ዓለም- world view) ያሳያሉ (Dundes 1971:96)፡፡ በመሆኑም አንድ አጥኚ የማኅበረሰቡን አተያይ ለማወቅ በቅድሚያ እነዚያን ማኅበራዊ ሃሳቦች (folk ideas) በሚገባ መተንተን አለበት፡፡ ይህ የሚያሳየን ቃላዊ ተረኮች የማህበረሰቡን ውስጣዊ ማንነት ማሳያ መሆናቸውን ነው፡፡

ፎክሎር በአንድ ማኅበረሰብ በጋራ ስምምነት ላይ የተያዘን ገናን ባህል በነበረበት ለማቆየት፣ ትውልዱ ለባህሉ ዋጋ እንዲሰጥ የሚያስችል ጥበብ ነው፡፡ ይህንኑ Bascom (1954:344) "A second function of folklore is that which it plays in validating culture, in justifying its rituals and institutions to those who perform and observe them." ሲሉ ገልጸውታል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ Fekade (2001)፣ Dorson (1972) እና Dundes (1965) ጠቅሰውታል፡፡ ይህንን ተግባር ከሚወጡት ውስጥ አንዱ የሥነቃል ዘርፍ የሆነው ቃላዊ ተረክ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

ቃላዊ ተረኮችን ለየት የሚያደርጋቸው ነገር ቢኖር ማኅበራዊ እውነታዎችን በዝርዝር ማቅረብ፣ ለማኅበራዊ ችግሮች ትዕምርታዊነት ያለውን መፍትሄ ማመላከት መቻላቸው ነው፡፡ Young (1978:692) Levi-Strauss (1968)ን ጠቅሰው ሲያስረዱ ". . . the relationship of oral naratives to reality was a dialectical one, the ultimate purpose of which is to provide imaginary resolutions of social problems" ብለዋል፡፡ ይህ የሚያሳየው

ተረኮች አንድም የማኅበረሰቡ "እውነተኛ ነጸብራቆች"[31]፣ አንድም ትረካው የማኅበረሰቡን የጋራ ችግሮች ከነመፍቻቸው የሚያመላክቱ መሆናቸውን ነው፡፡ እያንዳንዱ ጠቃሚ የተባለ ቃላዊ ትረካ የማህበረሰቡን ችግሮች ያነሳል፡፡ ለችግሮቹ የሚሰጠውም እልባት ለፎክ ቡድኑ በጠቅላላ እንጂ ለአንድ ግለሰብ ተብሎ የሚቀርብ አይደለም፡፡ ጥረቱ ሁሉ መዋቅራቸው እንዳይፈርስ የሚያስጠብቅ ነው፡፡ ዋና የሚባሉት የትረካው ገጸ ባህሪያት ተምሳሌትነታቸው ለማህበረሰቡ ነው፡፡ በሴራውም ዙሪያ ያሉ ሁነቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ ወቅታዊ አደረጃጀቶች ያንጸባርቃሉ (Young 1978:693)፣ ማኅበራዊ ችግሮች የተፈቱበት መንገድ አንድ ማኅበራዊ መዋቅርን (Social structure) ይሰራል፡፡

የተለያዩ ባለሙያዎች ተረቶችን አስመልክተው ከራሳቸው ሙያ አንጻር የየበኩላቸውን ብለዋል፡፡ የሥነሰብዕ ተመራማሪዎች እንደሚሉት ተረቶች በቃል ከሚነገርለትና ከሚጻፍለት በላይ ስለማኅበረሰቡና ባህሉ ከነልማዱና ከነባህሪው ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ የሚያትቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም ስልታዊ በሆነ መንገድ በባለሙያ ቢጠኑ ጥልቅ የሆነ አንዳች ዓይነት የአኗኗር ይትብሃል እንደነበራቸውና እንዳላቸው ያሳያሉ (Olarinwoyr 2013:38)፡፡ እኚሁ ጸሃፊ Boas (1914)ን ጠቅሰው ሲያስረዱ ተረቶች የአንድን ማኅበረሰብ ቁሳዊ ባህሉን፣ ምጣኔ ሃብቱን፣ ማኅበራዊ መዋቅሩን፣ ሃይማኖታዊ ምግባሩን፣ ሥነምግባራዊ ጽንሰሃሳቦቹን፣ የሰዎችን የህይወት ኡደት እና የማኅበረሰቦችን ሌሎች ምስጢራዊ ተግባራት አቀናጅተው ይገልጻሉ፡፡ በዚህም የተነሳ ተረት የአንድ ጎሳ ወይም ማኅበረሰብ የህይወት ታሪክ ነው ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም ገጸባህሪቱ፣ ጭብጡ፣ መቼቱ፣ ሴራው ወዘተ. ለማኅበረሰቡ ተምሳሌታዊነት ያለው ጠቀሜታ አላቸው፡፡ የእነዚህንም ተረቶች አንድምታ በጥንቃቄ መመርመር የሰው ልጆች ሁሉ

[31] እዚህ ላይ እውነተኛ ነጸብራቅ ሲባል የማኅበረሰቡ እምነት የሚገለጽበት ለማለት እንጂ ጉዳዩ ሁልጊዜ ሃቅ (fact) ነው ለማለት አይደለም፡፡ ለምሳሌ ሴት ከወንድ እኩል አለመሆኗን የሚያመላክቱ በርካታ ተረቶች አሉ፡፡ ይሄ አስተሳሰብ የማኅበረሰቡ እውነተኛ ነጸብራቅ ነው፡፡ ይሁንና ነጸብራቁ ነባራዊ ሃቅ ነው ማለት ላይሆን ይችላል፡፡ እውነተኛ ነጸብራቅ ሲባል ነባራዊ ሃቅን ይወክል ማለት አይደለም፡፡ በተወሰነ መልኩ ተቃራኒ የሚሆኑበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ በማህበረሰቡ በመፈጸም ላይ ያሉትን ጉዳዮች ደካማ ጎናቸውን ተጠየቃዊ በሆነ መንገድ ለማሳየትና ይሆናል የሚባለውን መፍትሄ አስቀምጦ ለማሳመን ሲባል (ሃሳቡንም የጋራ ለማድረግ) ተረቱ በተቃራኒ ይዋቀራል፡፡ ሆኖም ነባራዊ ሃቅነት ወይም ሳይንሳዊ እውነትነት አለው ማለት አይደለም፡፡ ይህንኑ Young (1978፡695) "the folktale or myth is a kind of snapshot of collective thought, particularly as it weighs alternative institutional arrangements" በማለት ገልጸውታል፡፡ በመሆኑም ከላይ የቀረበው አካሄዱ በዚህ መልኩ መሆኑ ይታወቅ፡፡

የጋራ የሆኑትን ሰዋዊ ባህሪያት ለማወቅና አሁን ያለውን ሥርዓተ ጾታዊ ልዩነት ለመረዳት ያስችላል (2013፡138)፡፡

ተረቶች በማኅበረሰቡ ተቀባይነትን ያገኙ ባህሎች፣ ሥነምግባሮች፣ ልዩ ልዩ እሴቶች፣ አስፈላጊነትና ተገቢነትን በማረጋገጥ የማኅበሩ አባላትም የህይወታቸውና የኑሯቸው መርህ መግለጫ አድርገው እንዲቀበሏቸው በማድረግ ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ፡፡ በአጠቃላይ የአንድ ህብረተሰብ ህይወቱ፣ ገጠመኙ፣ እምነቱ፣ ባህሉ፣ ሥነምግባራዊ እሴቱ፣ ፍልስፍናው፣ ለተፈጥሮና ለዓለም ያለው አመለካከት እንዲሁም የአኗኗር ዘይቤው የሚዘከርበት፣ ያለፈውን መጥፎም ይሁን በጎ ነገር ወደኋላ ዞር ብሎ የሚያይበት አንደኛው መነጽሩ ተረት ነው፡፡

### 4.1.2 የሥርዓተ ጾታ ትርጉም

በዚህ ጥናት ሥርዓተ ጾታ ሲባል የእንግሊዝኛውን Gender ለማለት ነው፡፡ ሥርዓተ ጾታ፣ ከሥነህይወታዊ ደንብ ውጭ በሆነ መልኩ በማኅበራዊ ምደባ (Social stratification) ምክንያት የምናገኘው ወንድነት ወይም ሴትነት ነው፡፡ ይህንኑ ሃሳብ Reeves እና Baden (2000፡30) ሥርዓተ ጾታ ማለት የሰው ልጅ ሥነህይወታዊ ባህሪ በባህል ዋጋ ተሰጥቶትና ተፈክሮ በማኅበረሰቡ ለሴትነት ወይም ለወንድነት የሚያበቃ መስፈርት የሚበጅበት ሥርዓት ነው ሲሉ ይገልጹታል፡፡ Holmberg (2005:8) ከላይ የተባለውን ፍቺ በሚያጠናክር መልኩ ሥነህይወታዊ ጾታ (Biological sex) ማኅበራዊና ባህላዊ በሆነ መንገድ እንደገና መልክ የሚሰጥበት ነው ሲሉ አብራርተውታል፡፡ ሌሎች (Olasupo and et als. 2012:11) ደግሞ ይህንኑ ቃል ማኅበራዊ በሆነ መልኩ የተቀናጁ ሚናዎች ተለይተው ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጡበት ስልት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ Kiriti (2011፡13)ም ማኅበረሰቡ ለሴትና ለወንድ ለይቶ የሰጠው ሚና ነው፤ በመሆኑም ሥርዓተ ጾታ የሴቶችና የወንዶች ማኅበራዊ ማንነት (social identity) ነው ሲሉ ገልጸውታል፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ ማኅበረሰቡ ጾታን መሰረት ያደረገ ደንብና ማኅበራዊ ሚና አበጅቶና ሰጥቶ እናገኛለን፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ምደባ ከጾታ ጋር ምንም የሚያገናኘው ጉዳይ ካለመኖሩም በላይ ምደባው የግለሰብ ምርጫ አይደለም፡፡ ይሄ (ሥርዓተ ጾታዊ ምደባ) ባህላዊ አስተሳሰብ ስለመሆኑ Palmisano (2001:267) ሥርዓተ ጾታዊ ማንነት ሙሉ በሙሉ ግለሰባዊ ምርጫ አይደለም፤ የባህል ጫና ባረፈባቸው በሥርዓተ ጾታዊ

ሚናዎች፣ በደንቦች እና በማኅበራዊነት ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ራሳችንን ወንድ ወይም ሴት ብለን ለመወሰን ያደግንበት ባህላዊ አስተሳሰብ ወሳኝ ነው፡፡ ምክንያቱም እያንዳንዱ ባህል የየራሱ የሆነ የሥርዓተ ጾታ አስተሳሰብ አለው ሲሉ ገልጸውታል፡፡ ከዚህ አንጻር ሥርዓተ ፆታ በማኅበራዊና ባህላዊ ክንውን ውስጥ ያለ ጽንሰ ሃሳብ ነው ማለት ነው (Nenola 1993:50 in Fekade 2003)፡፡ Kabeer (1996:17) የቃሉን ፍችና ሚና ከፍ አድርገው፣ ተቋሞች የተደራጁበትና እንደገና የተዋቀሩበት መንገድና ውጤት እንዲሁም ግንኙነቱ በነዚህ ተቋማት ውስጥ የሰረጸ ሥርዓት መሆኑን አጠንክረው ገልጸውታል፡፡ አንዳንዶቹ ሥርዓተ ጾታን "The systematic domination of females by males" በማለትም በይነውታል (Palmisano 2001:266)፡፡ ባጠቃላይ ሥርዓተ ጾታ ባህላዊና ማኅበራዊ በሆነ አስተሳሰብ ተፈጥሯዊ ጾታን መነሻ አድርጎ ለሴቶችና ለወንዶች ተለይቶ ሚና የተሰጠበት፣ ይሄም ሚና ለበላይነትና ለበታችነት ምክንያት የሆነ ደንብ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ሥርዓተ ጾታ ሲባል ይህንን የተመለከተውን ማለት ነው፡፡

### 4.1.3 የሥልጣን ትርጉም

በሦስተኛ ደረጃ የተብራራው የዚህ ጥናት ቁልፍ ቃል ሥልጣን (power) ነው፡፡ ቃሉ በተለያዩ ምሁራን እና በመዝገበ ቃላት ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡ ለምሳሌ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1993:107) ሥልጣንን "አንድን ነገር ለማድረግ፣ ለመስራት ወይም ለማሰራት የሚያስችል መብት፣ አመራርን በበላይነት ለማካሄድ የሚያስችል ሃይል፣ ሃላፊነት" በሚል ፈትቶታል፡፡ Brescoll (2012:2) በበኩላቸው ሲያብራሩት "Power is defined in terms of control over resources and what is frequently referred to as ''social power,'' which highlights an individual's capacity to influence and control the behavior of others." ብለዋል፡፡ በዚህ ብያኔ ውስጥ ሥልጣን በተለይም ማኅበራዊ ሥልጣን ሃብትን በራስ ቁጥጥር ስር ለማድረግ ሲባል በሌላው ላይ የሚደረግ ተጽዕኖ እና ቁጥጥር ነው፡፡

በሥርዓተ ጾታ ውስጥ ወንዱን ከፍ ሴቷን ዝቅ የሚያድረግ የፆታ አድልዎ (gender inequlity) ይታያል፡፡ ከወንድ ላቅ ያለ ተግባር የፈጸመች ሴት ብትገኝ "የወንድ ልብ ያላት ሴት" (manly hearted woman) ትባላለች እንጂ በሴትነቷ እውቅና አይሰጣትም (Nenola 1993)፡፡ በባህል ውስጥ ያለው የሥርዓተ ፆታ ወገንተኝነትም ይሁን የባህል

አድሏዊነት ቁሳዊ ሃብቱን ወይም ከፍ ያለ ማህበራዊ ደረጃን ለመቆናጠጥ በሚደረግ ግብግብ የሚመጣ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ምክንያቶች በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ሲኖር የሚችለውን ተዋረዳዊና ጎናዊ መዋቅር እንዴት መሆን እንዳለበት ይወስኑታል (McGuire፣1983:93)፡፡ ሥርዓተ ጾታዊ ክፍፍል ግቡ ሥልጣን ነው፡፡ ሥልጣኑንም ለወንዱ የሚሰጥ ነው፡፡ በ Nenola (1993፡53) ስራ ውስጥ ይሄው ጽንሰ ሃሳብ "Gender systems are in most cases asymmetrical and hierarchical and in favour of men. Gender system, in other words, are also power systems, within which power and prestige are distributed unequally according to gender." በሚል ተገልጾ እናገኘዋለን፡፡ ይህ የሚያሳየን ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን መስተጋብር ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡ በመሆኑም ሥልጣን ሲባል በሥርዓተ ጾታ ምክንያት የመጣውን የበላይነትና የበታችነት ነው፡፡

የሥልጣንን ጽንሰ ሃሳብ በተመለከተ ብቻውን ከመግለጽ ይልቅ ከሥርዓተ ጾታ ጋር ካለው መስተጋብር አንጻር አንድ ላይ ማየት ሃሳቡን የበለጠ ግልጽ ያደርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት በዚህ ክፍል ሊነሳ የሚችለው ሃሳብ ቀጥሎ ባለው ክፍል ቀርቧል፡፡

### 4.1.4 የሥርዓተ ጾታ ጽንሰሃሳብና ከሥልጣን ጋር ያለው መስተጋብር

የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን መስተጋብር እንዴት እንደሆነ ከማሳየታችን በፊት ራሱ ሥርዓተ ጾታ መሰረቱ ምን እንደሆነ የተለያዩ ባለሙያዎች የሰነዘሩትን ሃሳብ መነሻ በማድረግ እናስቀድም፡፡ ይህ ክፍል የመቅደሙ ምክንያት የሁለቱ መስተጋብር እንዴት በጥብቅ የተቆራኘ እንደሆነ ስለሚጠቁም ነው፡፡

በሴቶችና በወንዶች መካከል ላለው ሥርዓተ ጾታዊ ሚና መለያየት ብዙ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ፡፡ አንዳንዶቹ እርስበርሳቸው የሚደጋገፉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ይለያያሉ፡፡ ከምክንያቶቹ ውስጥ በዋናነት የተጠቀሱት የአፈጣጠር ጸጋ ልዩነት (Biological differenc---Sex)፣ የጋብቻ አመሰራረት ሂደት፣ የስሜት (emotion) መለያየት፣ ባህል እና ማኅበራዊነት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ አንዳንዶችም ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑትን በማቀናጀት እንደምክንያት አድርገው ያቀርባሉ፡፡

በቅድሚያ ከአፈጣጠር ጸጋ ጋር የተያያዘውን እንመልከት፡፡ Wood & Eagly (2002, 704-705) ሲያስረዱ ሴቶች በጉልበታቸው (energy) ከወንድ ጋር ሲነጻጸሩ በአብዛኛው በማነስ ልዩነት ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም የሚሳተፉበትን የስራ መስክ ቀላል ግን

ተደጋጋሚነት ያለው (simple and routine) እንዲሆን አድርጎታል። ወንድ ግን በጉልበቱ ላቅ ያለ ስለሆነ ከባድ ስራዎችን ይሰራል። ይሄ ከጉርምስና (maturity) ጊዜ ልዩነት ጋር ይገናኛል። ሴቶች ቀድመው ለአቅመሄዋን በመድረሳቸው በሂደት ሊጨምር የሚችለው አካላቸውና አቅማቸው ባለበት ይገታል። ወንዱ ግን ዘግይቶ ለአቅመ አዳም ስለሚደርስ አካላዊ እድገቱና ሃይል የማጠራቀም እድሉ ከሴቶች የተሻለ ሆኗል። ይሄ ሥነህይወታዊ ባህሪ ሴቶችና ወንዶች የሚያከናውኗቸውን ተግባሮች እንዲለያዩ ምክንያት ሆኗል። ለሁሉም ለእያንዳንዳቸው የየራሳቸው ተግባር እንዲኖራቸው አድርጓል። በማኅበራዊ መዋቅሩም (social structure) ውስጥ ሁለቱም ጾታዎች ይበልጥ ውጤታማ በሚሆኑበት የስራ መስክ የመደበ በመሆኑ ሁለቱንም ጾታዎች በተመሳሳይ የስራ መስክ እንዳይሳተፉ አድርጓቸዋል። ይህ ማኅበራዊ ሚናም በሂደት አንድ መልክ ያለው ማኅበራዊ መዋቅር (Social structure) ለመፈጠሩ ምክንያት ሆኗል ብለዋል። ጾታ ተኮር የሆነ የስራ ክፍፍልም በመላው ዓለም ተመሳሳይነት እንዳለው በየሃገሩ የተደረጉ የባህል ጥናቶች እንደሚያሳዩ፣ እንዲህ ዓይነቱ ጾታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል በሂደት የሰው ልጅ ማኅበራዊ አደረጃጀትን እንደፈጠረ፣ ከላይ የተጠቀሱት ጸሃፍት የሥነሰብዕ ተመራማሪዎችን ጠቅሰው ሲያስረዱ

> *Many anthropologists have concluded that the division between male and female tasks is an essential feature of human social organization in the sense that it either reflects innate attributes of the human species or is a widely shared social convention.*

ብለዋል (2002:705)። ይህ በተዘዋዋሪ ሥርዓተ ጾታዊ አስተሳሰብንና ሚናን ፈጥሯል ማለት ነው።

ሌሎች ደግሞ (Eagly and etals 2009፡404, Perret and Cassidy 2010:720-729, Lau 1996:237) ለሴትና ለወንድ የሥርዓተ ጾታ ልዩነት መፈጠር አንዱ ምክንያት በዓለም ላይ ያለው የተለመደው የጋብቻ ደንብ ነው ይላሉ። ይህም ጋብቻቸውን ሲፈጽሙ ወንዱ ሴቷን ወደ ራሱ ቤተሰብ አምጥቶ ያቀላቅላል እንጂ እርሱ ሄዶ ከሴቷ ቤተሰቦች ዘንድ አይገባም[32] የሚል ነው። Hierro and Marquez (1994፡176-177)

[32] ይህ ሁልጊዜ ይሆናል ማለት ግን አይደለም። ወንዱ ከሴቷ ቤተሰቦች ዘንድ ሄዶ የሚገባበት አጋጣሚ አለ። ይህም ቢሆን ግን ሴቷ በሰርጓ እለት ወንዱ ሙሽራ እንደሚያደርገው አጃቢዎቿን ይዛ ሄዳ ሙሽራውን ከቤተሰቦቹ ዘንድ ወስዳ ወደ ራሷ ቤተሰቦች ስታቀላቅል አይስተዋልም። ወንዱም ወደ

በበኩላቸው አባዊ ሥርዓቱ በሴቶች ላይ ለመሰልጠን፣ ኃይሉን ለማሳረፍ እና ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ከተጠቀመባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ እና ዋናው “ሴቶችን መለየት” ነው ይላሉ፡፡ ይሄ በጋብቻ ጊዜ የሚፈጠረውን ከቤተሰብ መለየት ይመለከታል፡፡ በዚህም የተነሳ ሴቷ የማታውቀው ቤተሰብ ውስጥ ስለምትገባ ዝም የማለትና ጎልታ በማትታይበት የቤት ውስጥ ስራዎች ላይ እንድትጠመድ ትደረጋለች፡፡ ይህም በሂደት የዝቅተኝነት መንፈስ ያሳድርባትና ከወንድ እኩል እንዳትሆን ሥነልቡናዊ ጫና ያደርግባታል፡፡

እነዚህ ሁኔታዎች በሂደት የሴቷንና የወንዱን የኃይል ሚዛን ሊያዛቡ እንደሚችሉ ይገመታል፡፡ ምክንያቱም ሴቷ የማታውቀው ቤተሰብ ውስጥ ሄዳ ስለምትቀላቀልና የባይተዋርነት ስሜትን ስለሚያመጣባት ታዛዥነትን ትመርጣለች፡፡ በዚሁ የተነሳ በኢኮኖሚው የበላይነቱን ልትቀማ ስለምትችል ተጽዕኖው ከፍተኛ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ሴቶችና ወንዶች ባላቸውም ተፈጥሯዊ ስሜት (Emotion) እንደሚለያዩና ይሄው ልዩነታቸው ለተዋረዳዊ ግንኙነት ምክንያት እንደሆነ የሚያሳዩ ጥናቶች አሉ፡፡ በጥናቶች ውስጥ እንደተገለጸው (Fischer, Patricia and Vianen 2004፡88) ሴቶች ያላቸው ስሜት በመከፋት፣ በፍርሃት፣ በሃፍረትና በጥፋተኝነት መንፈስ፤ የወንዱ ግን በቁጣና በሌሎች መሰል ስሜቶች ይንጸባረቃል በሚል ነው፡፡ ይሄ የሴትነትና የወንድነት መለያ ሆኖ በማኅበራዊውም በባህላዊውም አውድ ውስጥ ሰርጾ ሊገባ እንደሚችል ይታመናል፡፡ እነ Fischer (2004፡87) ሌሎችን ዋቢ አድርገው ሲገልጹ “ Emotions can be considered part of the socialization into roles that men and women commonly occupy” ይላሉ፡፡ ይህን ተከትሎም ሴቶችን የቤት ውስጥ ስራና ህጻናትን የመንከባከብ ሚና፣ ወንዱን ከቤት ውጭ ገንዘብ በሚያስከፍሉ ስራዎችና በፍጆታ ቁሳቁሶች አቅርቦት ላይ እንዲሰማራ አድርጎታል ሲሉ እነ Fischer (2004፡88) ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ ሚናዎች

---

ሴቷ ቤት ሄዶ ሲገባ ያለ ምንም የሠርግ ሥነሥርዓት በመስማማት ብቻ ነው፡፡ እንዲያውም እንዲህ ዓይነቱን ጋብቻ “ተከርቸም” የሚል ስያሜ ሰጥቶ (ኢቋጥምማ 1993፡372) “ያለ ጋብቻ ውል ከሴት ቤት ውስጥ በባልነት ለመኖር ገባ” የሚል አቻ ፍቺ ተሰጥቶታል፡፡ በቦረና ወረዳም ይህንኑ ልማድ “አሴና ገባ፣ ቁልቁል ወረደ” በሚሉ አሉታዊ ስሜት ባላቸው ቃላት መግለጽ የተለመደ ነው፡፡ በሰሜን ሸዋም “ቆጥ አሰር” በሚል ወንዱ ወደሴቷ ቤት ሄዶ ጋብቻ ይፈጽማል፡፡ እነዚህ ቃላት ወንድ ከሴት ቤት ሄዶ መግባትን የሚያበረታቱ አይደሉም፡፡ እንዲያውም ተከርቸም መግባት ማኅበራዊ ዋጋና ክብር ያስነፍጋል፡፡ በዚህም የተነሳ ወንዱ ወደ ሴቷ ቤት ሄዶ በጋብቻ የመኖር አጋጣሚው ውስን ነው፡፡

በሂደት በሴትና በወንዱ መካከል የሥልጣንና የደረጃ ልዩነት አያመጡም ለማለት አያስደፍርም፡፡

የፍሩዳውያንን ሥነልቡናዊ አስተሳሰብ የሚከተሉት (psychoanalytic theorists) እንደሚሉት አንድን ግለሰብ የሚመሩት ደመነፍሳዊ (instinctive) ፈቃደ ስጋዊ ፍላጎቱና ተፈጥሯዊ ቁጡነቱ ናቸው፡፡ ይሄ ባህሪ እያደገና እየተገራ ሲሄድ ከፍ ያለ የበላይነት ስሜት ይፈጥርና አንድ ወንድ መሪን ያፈራል፡፡ ለምሳሌ በዝንጀሮዎች መንጋ ውስጥ አንድ መሪና የበላይ ግመሬ[33] አለ ሲሉ እንደማጠየቂያ ያቀርባሉ (Michael 2000:45)፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘ Wood እና Eagly (2002:715) የሰነዘሩት ሃሳብ እንደሚከተለው ይነበባል፡፡

> *Some evolutionary psychologists have argued that male sexual control is the root of patriarchy—that is, that "male power over women so often revolves around female sexuality." If sexual selection pressures shaped men to be concerned about paternity, to control female sexuality, and to be sexually jealous, social structures arranged to favor male control of female sexuality.*

ከዚህ ጥቅስ ብዙ ነገሮችን ማለት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በወንድ የበላይነት የተያዘው ፈቃደ ስጋዊ ግንኙነት ለአባዊ ሥርዓት መፈጠር እንደምክንያት ተደርጎ ተወስዷል፡፡ ሁለተኛም ወንድ ከሴት የበለጠ ቀናተኛ ነው የሚል አንድምታ አለው፡፡ በመሆኑም አባዊ ሥርዓቱ ይህንን የሚቆጣጠርበት ማኅበራዊ መዋቅር ሰርቷል ወደሚል ማጠቃለያ እንድናዘነብል ያደርጋል፡፡ ሴቶችን ሊቆጣጠር የሚችልበትን ሥርዓተ ጾታዊ ደንብ አውጥቶ በባህልም፣ በሃይማኖትም፣ በህግም መሰረት ሳያሲዘው እንዳልቀረ ግምታችንን እድናሳድር ያስገድደናል[34]፡፡

ከላይ በመነሻው ላይ ለሥርዓተ ጾታ መፈጠር በምክንያትነት ከተጠቀሱት ውስጥ የተወሰኑትን በማቀናጀት ሃሳባቸውን የሚሰነዝሩም አሉ፡፡ ለምሳሌ Jackson (2015፡29-30) ለሥርዓተ ጾታ መፈጠር ምክንያት ናቸው ያሏቸውን ሦስት ነጥቦች ጠቅሰዋል፡፡

---

[33] በአንድ የዝንጀሮ መንጋ ውስጥ መንጋውን የሚመራ አንድ ግመሬ አለ፡፡ ሌሎች ወንድ ዝንጀሮዎች አድገው ግመሬውን ከመፎካከራቸው በፊት ከመንጋው ይባረራሉ፡፡ እነሱም የሚመሩት የራሳቸውን መንጋ መስርተው ይኖራሉ፡፡ የመባረራቸውና የጥላቻው መንስኤ ሴት ዝንጀሮዎችን በብቸኝነት ከመያዝ የመጣ ነው፡፡ ጥላቻውም በሴቶች ነው፡፡

[34] ይህ እንዴት ሊሆን እንደሚችል በምዕራፍ አምስት ላይ በስፋት ቀርቧል፡፡

እነዚህም ማኅበራዊነት፣ ልማድና ሥነህይወታዊ ባህሪ (socialization, tradition, and biology) ናቸው፡፡ እንደ አጥኚው አባባል (Jackson 2015) ወንዶችና ሴቶች ትናንት እና ዛሬ የሚያስቡት፣ የሚተገብሩትና ከውጤት ላይ የሚደርሱት በተለያየ መንገድ ነው፡፡ ይህ የማኅበራዊነት ውጤት ነው፡፡ ወላጆች ልጆቻቸውን (ሴቶችንና ወንዶችን) የሚቀርጹት በተለያየ አስተሳሰብ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በልማድ መለያየት ምክንያት ነው፡፡ በየትኛውም አካባቢ ወንዶችን ከፍ ሴቶችን ዝቅ ያደረገው ሥርዓተ ጾታዊ ልማድ ምንጩ ተፈጥሯዊ አካላዊ ሁኔታቸው ስለሚለያይ ነው፡፡ እነዚህ ሦስት ነጥቦች ወደ ሥርዓተ ጾታ መፈጠሪያ ምንጭ ይወስዱናል ሲሉ ጸሃፊው ያስረዳሉ፡፡ Jackson (2015፡30) የሥርዓተ ጾታ ኢፍትሃዊነት እድሜ ጠገብ መሆኑን ጠቅሰው በተለይ ሁሉም ሃይማኖቶችና ሚቶች ይህንኑ ተጠየቃዊ ለማድረግ የፈጠራ ታሪኮችን መጠቀማቸውን ያስረዳሉ፡፡

የሥነህይወታዊ-ማኅበራዊ (biosocial theory)[35] አቀንቃኞችም የራሳቸውን ብለዋል፡፡ እንደእነሱ አስተሳሰብ ሥርዓተ ጾታዊ ልዩነትን የፈጠሩት የወንድና የሴት አካላዊ ተፈጥሯዊ ባህሪ (physical attributes of men and women) እና የሚኖሩበት ማኅበራዊ አውድ (social contexts) ናቸው (Wood & Eagly 2002፡701)፡፡

ባጠቃላይ (ለሥርዓተ ጾታ መፈጠር ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን) የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ ሲፈጠር እኩል ነው፡፡ ከተፈጠረ በኋላ ግን የአካባቢው ማኅበረሰብ የተቀበላቸው ዳብረው የቆዩ የማኅበራዊ ግንኙነት ደንቦች፣ ባህላዊ ሁኔታዎች፣ የቀደመው የቤተሰቡ የማንነት ዳራዎች፣ ተምሳሌታዊነት ያላቸው ቅሪቶች ወዘተ. አጠቃላይ ሥነልቡናዊ መዋቅሩን ይገነቡታል፤ እንቅስቃሴውንና ግንኙነቱን ይወስኑታል፡፡ ሴትነትና ወንድነትም የዚሁ ውጤት ናቸው (Skaggs 2002)፡፡

ሰዎች በማኅበረሰቡ ውስጥ ያላቸው ቦታና የቦታው አሰጣጥ የሥርዓተ ጾታ ተጽዕኖ ያለበት ነው፡፡ እንደ ደንብ ሆኖ ወንድ ከፍ ያለውን ቦታ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

---

[35] ሥነህይወታዊ ማኅበራዊ ቲዮሪ Social constructionist theoryን እና Evolutionary psychologist theoryን በማቀናጀት የተሰራ ነው፡፡ Social constructionist ለሥርዓተ ጾታ መፈጠር ማኅበራዊ አደረጃጀት ምክንያት ሆኗል ሲሉ Evolutionary psychologist ደግሞ ሥነህይወታዊ የአፈጣጠር ልዩነትን በምክንያትነት ያቀርባሉ፡፡ ሥነህይወታዊ ማኅበራዊ ቲዮሪ ሁለቱን በማቀናጀት ያፈጣጠር ልዩነት እንዳለ ሆኖ ሥርዓተ ጾታዊ አስተሳሰቡን ግን የፈጠረው ማኅበራዊ አውዱ ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ተረዳድተው በሴትና በወንድ መካከል ያለውን የበላይነትና የበታችነት አምጥተዋል በማለት ያስረዳሉ (Wood & Eagly 2002)፡፡

በመሆኑም የሥርዓተ ጾታና ሥልጣን መስተጋብር ከዚህ ስሜት ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ባጭሩ ተዋረዳዊ ግንኙነት ነው፡፡ ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በግልም ይሁን በህዝባዊ ተቋማት የሚሰጣቸው ቦታ (ሥልጣን) ከማኅበረሰቡ ሥርዓተ ጾታዊ ሚና ጋር የተገናዘበ ነው (Holmberg 2005:9)፡፡ በመሆኑም ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን የተዋሃዱም የተናበቡም ናቸው፡፡ Ostergaard (1992) በ Kabaji (2005:2) ውስጥ ይህንኑ ሲገልጹ "Gender relations are constructed in terms of the relations of power and dominance that structure the life chances of women and men" ብለዋል፡፡

ሥርዓተ ጾታ፣ ሥልጣን እንዴት መሆን እንዳለበት መልክ ይሰጠዋል፡፡ የሥልጣን ክፍፍሉ መሰረቱ ሥርዓተ ጾታ ነው፡፡ ሥርዓተ ጾታዊ ግንኙነትም ሥልጣናዊ ግንኙነት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ከዝቅተኛው ቤተሰባዊ ግንኙነት አንስቶ እስከ ከፍተኛው የፖለቲካ ውሳኔ ሰጪ አካል ድረስ ያለው የሥልጣን እርከን መልክ የያዘው በሥርዓተ ጾታ ነው (Tiani 2015)፡፡

በአብዛኞቹ ማኅበራዊ አውዶች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ሥልጣን አላቸው፡፡ ይህም ሥርዓተ ጾታንና ሥልጣንን በተፈጥሯቸው የተዋሃዱ ያደርጋቸዋል፡፡ ወንዱ በማኅበራዊ፣ በፖለቲካዊ፣ በምጣኔ ሃብታዊ እና በሌሎች ሚናዎች ላይ የበላይነቱን እንዲይዝ በልማዳዊ እምነቶችና ድርጊቶች መልክ አስይዞታል (CGSPS[36] 2001:27)፡፡ ሴቶች በቀላሉ ሊቋቋሟቸው በማይችሏቸው በሃይማኖት፣ በጥንት ባህሎችና በከበራዎች የተገገርነታቸው ተጠየቃዊነት ሰርጿል፡፡ ሴትነት ከታዛዥነት፣ ከመውለድ፣ አጥብቶ ከማሳደግና ትውልድን ከመተካት፤ ወንድነት ከመቆጣጠር፣ ከአዛዥነትና ህይወት መልኳን ጠብቃ እንድትሄድ ከማድረግ ጋር ተያያዞ ይታሰባል (Hierro and Marquez 1994፡175)፡፡ በሃይማኖትም ይሁን በባህል ውስጥ ያሉ ከበራዎች (Ritual) ይህንን ጽንፍ (dichotomy) ያንጸባርቃሉ፡፡ አጠቃላይ የሥርዓተ ጾታ ደንቦችና ሥርዓቶች ወንድ በሴቶች ላይ ሊነግስ በሚችልበት አኳኋን የተሰሩ ናቸው፡፡ በዚህም የተነሳ ሥልጣንን ራሱን ጾታዊ እንዲሆን (sexualization of power እንዲሰፍን) አድርጓል፡፡ ከዚህ፣ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ምን ያህል ጋብቻ እንደፈጠሩ ማየት ይቻላል፡፡

አጥኚዎች (Brescoll 2012:2-3) እንዳረጋገጡት የበላይነትን መያዝ በርካታ ሥነልቡናዊ አንድምታዎች (ጥቅሞች) አሉት፡፡ ለምሳሌ ሃሳብን በራስ በመተማመን ስሜት

---

[36] CGSPS - The Centre for Gender and Social Policy Studies

ለመናገር፣ ኃላፊነትን ለመውሰድ፣ የራስን ግብ ለማሳካት፣ እርምጃዎችን ለመውሰድ ወዘተ. ይጠቀማል፡፡ በእርግጥ የበላይነትን መያዝ በሚያጎናጽፏቸው ሥነልቡናዊ ጥቅሞች በሴትና በወንድ ልዩነት የለውም ፡፡ ሆኖም ሥልጣን በቀጥታ ከሥርዓተ ጾታ ጋር በመያያዙና ማኅበራዊ አውዱ ሥልጣንን ለወንዶች የሰጠ በመሆኑ የበላይነትን መያዝ የሚያስገኛቸውን ሥነልቡናዊ ጥቅሞች በአብዛኛው የሚያጡት ሴቶች ናቸው፡፡

ከሥርዓተ ጾታ አስተሳሰብ ጋር በተያያዘ ሁለት በጽንፍ የሚተያዩ አስተሳሰቦች አሉ፡፡ አንደኛው ተገቢነቱን የሚያምኑ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ደግሞ የሚቃወሙ ናቸው፡፡ ጾታን መሰረት ያደረገው የስራ ክፍፍልና ይህንኑ ተከትሎ የመጣው የሥልጣን አያያዝ ተገቢ ነው የሚሉት የግልጋሎታዊ እና የመዋቅራዊ ቲዮሪ አቀንቃኞች ሲሆኑ ተቃዋሚዎች ደግሞ የእንስታውያን ፈለግ አራማጆች ናቸው፡፡ የግልጋሎታዊ እና የመዋቅራዊ ቲዮሪ አራማጆች እንደሚሉት ከሆነ ጾታን መሰረት ያደረገ የስራ ክፍፍል አካባቢን በተረጋጋ ሁኔታ ለማኖር ያስችላል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ የዚህ ፈለግ አቀንቃኞች እንደሚያምኑት የስራ ክፍፍሉ ተፈጥሯዊ ሆኖ ከሴትና ወንድ ሥነህይወታዊ ባህሪ ጋር የተስማማ ነው፡፡ አያይዘውም ለቤተሰብ ደህንነት፣ ለልጆች አስተዳደግና ለጤናማ ማኅበራዊ ግንኙነታቸው መልካምነቱን ያሰምሩበታል፡፡ በመሆኑም በወንድና በሴት ተለይቶ የሚከናወን ስራ አወንታዊ ማህበራዊ ግንባታ ነው ሲሉ በአጽንዖት ይናገራሉ http://www.westminsterlawreview.org/Volume1/Issue1/wlr2.php)፡፡

የግልጋሎታዊ ቲዮሪ አራማጆች ሥርዓተ ጾታዊ የስራ ክፍፍል ማኅበራዊነትን ለማሳደግ ያስችላል፤ አጀማመሩም ለዚሁ ተግባር ነው ይላሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ማኅበረሰብን የሚመለከቱት የተለያዩ የማኅበራዊነት መገለጫ መልኮች ተቀናጅተው የሚሰሩበት፣ አጠቃላይነት ያለው እጅግ ውስብስብ ተቋም እንደሆነና እነዚያም የማኅበራዊነት መገለጫዎች ማኅበረሰቡን በስሜትና በድርጊት አስማምተው አንድ እንዲሆንና እንዲረጋጋ ያደረጉት እንደሆኑ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም የሥርዓተ ጾታ ልዩነት ለስራ ክፍፍል ውጤታማ ከመሆኑ የተነሳ አንዱ የማህበረሰብ ክፍል በአንድ የስራ መስክ ላይ ሃላፊነቱን ወስዶ ውጤታማ ስራ እንዲያከናውን ያደርገዋል ይላሉ፡፡ አንድን ማኅበረሰብ ማኅበረሰብ የሚያሰኙት እሴቶቹ፣ ደንቦቹ፣ ልማዶቹና ተቋሞቹ ተቀናጅተው ባንድ ላይ ሲገኙ ነው፡፡ ይህንኑ ሃሳብ Herbert Spencer መደገፋቸውን ሲያስረግጡ “እነዚህ የአንድ ማህበረሰብ አካል መገንቢያ ብልቶች ሲሆኑ ማኅበሩን ጤናማ ሊያደርጉ

የሚችሉ፣ እንደ አንድ አካል እንዲንቀሳቀስ የሚያደርጉ ናቸው” ማለታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

አያይዘውም ሴቶችን ከወንዶች ጋር እኩል ለማድረግ ሲባል የሚከናወኑት ተግባራት ጥሩ ቢሆኑም እየሆነ ካለው መረዳት ያለብን በአንዳንድ ማኅበረሰቦች ውስጥ የሴቶችን አቅም ማሳደግ (empower ማድረግ) በመጨረሻ ለቤት ውስጥ ግጭትና ለቤተሰብ አለመረጋጋት ምክንያት መሆኑን ነው፡፡ እንዲያውም አሁን እየተደረገ ካለው የቀደመው አኗኗራችን በተለይ ለሴቶች የተሻለ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ ከቤት ውጭ ባለ ክፍያ በሚያስገኝ ስራ ላይ ሴቶችን እንዲሳተፉ ማድረግ ከቀደመው በበለጠ ጫና ውስጥ ማስገባት መሆኑን ሲገልጹ “women who enter the workforce are often confronted with the ‘triple burden of employment where they must take care of the housework and child care, in addition to taking on extra paid work.” (http://www.uniteforsight.org/gender-power/module2) ይላሉ፡፡

ሆኖም ይህ ሃሳብ ከእንስታውያን ተቃውሞ ይቀርብበታል፡፡ ለምሳሌ Holmberg (2005:12) ይህንኑ ሲያጋግጡ በሴትና በወንድ መካከል ሥነህይወታዊ ልዩነት (biological difference) ቢኖርም ልዩነቱ ጾታን መሰረት ላደረገ የሥልጣን ክፍፍል እንደ ተፈጥሯዊ መመዘኛ ሊወሰድ አይገባውም በማለት ይከራከራሉ፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም በዚሁ ሃሳብ ይስማማል፡፡

ከዚህ በላይ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣንና ምን ያህል ጋብቻ የፈጠሩ እንደሆኑ አይተናል፡፡ በሌላ በኩል ተረቶች የማህበረሰቡ ፍላጎትና ስሜት እንዲሁም ማኅበራዊ ህግጋት ማስተላለፊያና ማስረጫ እንደሆኑ ተወስቷል፡፡ ይሄው በ Kabaji (2005: 1-2) ስራ ውስጥ “Every society has its own socialising engines that effectively transfer gender ideology. One such effective engine is the folktale-telling tradition.” በሚል በአጽንኦት ተገልጾ ይገኛል፡፡ ተረት ሥርዓተ ጾታዊ ርዕዮተ ዓለምን ከመሸከሙም ሌላ ራሱን ርዕዮት ዓለምንም እንደሚፈጥር Ogunsina (1996) “literature, whether oral or written, is a transmitter of ideology; but it does more than transmit ideology; in many cases it creates it” በማለት ጠንካራ ሃሳብ ሰንዝረዋል፡፡ ባጠቃላይ ተረት፣ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን መሰረታዊ የሆነ መስተጋብር እንዳላቸው እነዚህ ነጥቦች ያሳያሉ፡፡

## 4.2 ሥርዓተ ጾታ እና ሥልጣን ከባህል አንጻር

ፎክሎር የሚያጠናው ክፍለ ባህልን ነው፡፡ ማኀበረሰብ እስካለ ድረስ ፎክሎር አለ፡፡ በመሆኑም የፎክሎር ጥናት የማኀበረሰብ ባህል ጥናት ነው፡፡ አንድ ማኀበረሰብ ማኀበራዊ መዋቅሩን ሊያናጋ የሚችል ችግር በገጠመው ጊዜ በብዛት መፍትሄ ከሚያፈላልግባቸው መሳሪያዎቹ ውስጥ አንዱ ባህል ነው፡፡ ምክንያቱም ማኀበራዊ መዋቅሩ ከተሰራባቸው ማኀበራዊ ክስተቶች ውስጥ አንዱ በባህል ሳቢያ የተሰራው ነው፡፡ ተረቶች ደግሞ ማህበራዊ መዋቅሩን መሰረት አድርገው የተገነቡ በመሆናቸው ይህንኑ ያሳያሉ፡፡ በመሆኑም ተረቶች ከሥርዓተ ጾታና ከሥልጣን ጋር ያላቸውን መስተጋብር ከማህበራዊ ውቅሩ ጋር እያናበቡ፣ የተዋቀሩበትን ምክንያት ከተለያዩ አንጻሮች እያጣቀሱ ማሳየት ይቻላል፡፡

አንድ ጥናት ሲካሄድ በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ ተንተርሶ የችግሩ ምንጮች ምን እንደሆኑና እነዚያ መንስኤዎች ያሳደሩትን አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ገጽታ ከተለያዩ አቅጣጫዎች መመርመር ያስፈልጋል፡፡ መፍትሄውንም ለማፈላለግ መንስኤዎቹ ያላቸውን ውስጣዊ ተያያዥነትና ባንድ ላይ ተባብረው የሚያስከትሉትን ተጽዕኖ ማወቅ ይገባል፡፡ እሸቱ (1997፡5-6) እንደሚሉት የሥርዓተ ጾታን ጉዳይ ለመተንተን ይቻል ዘንድ አንድ ጥናት መሰረት ማድረግ ያለበት ችግሮችን ሁሉ አጠቃሎና አሟልቶ በማሳወቅ፣ የችግሮችን ውስጣዊ ተያያዥነትና ውጫዊ ተደጋጋፊነት በሚያሳይና የለውጥ ሂደትን በሚያገናዝብ መልኩ መደራጀት እንዳለበት ያሳስባሉ፡፡ ይህንን መንፈስ በመያዝ ሥርዓተ ጾታ ከባህል አንጻር ምን መልክ እንዳለው ቀርቧል፡፡ አጠቃላይ ዳሰሳውም የተደረገው ከኢትዮጵያ አንጻር ነው፡፡

ባህሎች ከሥርዓተ ጾታዊ ደንቦች ውጭ አይደሉም፡፡ አብዛኞቹ ጾታን መሰረት ያደረጉ የስራም ይሁን የሥልጣን ክፍፍሎች በአገራችን ውስጥ ተንሰራፍተው ይስተዋላሉ፡፡ ሥርዓተ ጾታ ባህልን መሰረት ባደረጉ ማኀበራዊ ግንኙነቶች ውስጥ ተወሳስቦ የሚገኝ ነው (እሸቱ 1997፡2)፡፡ ይህን መሰል ባህሪ ባላቸው ባህሎች ዙሪያ አብነቶችን እየጠቀስን እንመልከታቸው፡፡ አብዛኞቹ አብነቶች የተጠቀሱት ከተለያዩ ጥናቶች ነው፡፡

በቅድሚያ ሥርዓተ ጾታዊ እኩልነትና ሥልጣን ተዛብቶባቸዋል በሚባሉት ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋማት ላይ እናተኩር፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት ባህላዊ የግጭት

መፍቻ ተቋማት ከሚወቀሱባቸው ነጥቦች ውስጥ አንዱ ለጾታ እኩልነትና ከዚሁ ጋር ለተያያዙ የግለሰብ መብቶችና ነጻነቶች ቁብ የሌላቸው መሆናቸው ነው (ገብሬ፣ ፈቃደና አሰፋ 2004፡17)፡፡ ከበድ ያሉ በተለይም ከግድያ ጋር በተያያዘ በሚፈጸሙ የእርቅ ሥርዓቶች ላይ ባብዛኛው ሴቶች ሚና የላቸውም፡፡ በተቋሙም ውስጥ ሃላፊነት አይሰጣቸውም፡፡ የግጭት አፈታት ሥርዓታቸው በሙሉ ሴቶችን ከሥርዓቱ ሂደት ያገለሉ፣ የወንዶች የበላይነት ገኖ የሚታይባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ በተሁለደሬ ወረዳ በሚታወቀው የአበጋር ባህላዊ የግጭት መፍቻ ተቋም ውስጥ ሴቶች ፈጽሞ ሃላፊነት አይሰጣቸውም፡፡ ተቋሙ አንድን አበጋር ሲሾም መስፈርቶች አሉት፡፡ እነዚህም ዘር (የጀበርቲ[37] ዘር ያለው)፣ በሃይማኖቱ ሙስሊም የሆነ፣ የማስታረቅ ክዋኔውን ሳያጓድል የማስፈጸም እውቀቱ ያለው፣ በእድሜው የገፋና በጾታው ወንድ የሆነ ነው (ነጻነት 1998፡27-32)፡፡ ሌሎችም የግጭት መፍቻ ተቋሞች ተመሳሳይነት ያለው መስፈርት አሏቸው፡፡ ሁሉንም አንድ የሚያደርጋቸው ግን አንዲት ሴት ከጾታዋ ባሻገር ባሉ መስፈርቶች ከወንዱ ልቃ ብትገኝ እንኳ አሸማጋይ የመሆን መብት ባለመስጠታቸው ነው፡፡ በ1948 ዓ.ም ተሻሽሎ የወጣው ህገመንግስትም ባህላዊ የዳኝነት ስራ ለወንዶች ብቻ ሰጥቷል (በፍትህ ሚኒስቴር የትምህርትና የአገልግሎት ማሰራጫ መምሪያ 1983፡3)፡፡ ከዚህ አንጻር የሴቶች ሚና በቤት ውስጥ የተገደበ ሆኖ የሚበላና የሚጠጣ እያዘጋጁ በመላክ ላይ የተወሰነ ነው፡፡ ሥርዓቱ ሳይቀር ሙሉ በሙሉ አባዊ ነው፡፡

በዶኮ ጋሞ የእርቅ ሥርዓት ጊዜ ሴቶች አይታደሙም፡፡ ጉዳዩ የእነርሱ ቢሆን እንኳ በርቀት ተቀምጠው ሲጠየቁ ይናገራሉ፤ ወይም በስማ በለው ሃሳባቸው ይነገርላቸዋል እንጂ እነርሱ ቀርበው አይናገሩም (ተመስገን 2004፡95)፡፡ በአፋር ማድዓ ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓትም እንዲሁ ሴቶች በማንኛውም ጊዜ ራሳቸውን ችለው ክስ

[37] በነጻነት ጥናት ውስጥ እንደተጠቆመው (1998፡20-21) ወይም ስለአበጋሮች አመጣጥ የሚያትተው ሚት እንደሚናገረው ጀበርቲ ከኢትዮጵያ ወደአረብ አገር ለዚያራ የሄደ ሆኖ እዚያ ከደረሰ በኋላ የአገሪቱን ንጉሥ አስተናጋጅ አግብቶ እነ ሸህ ሲቢርን፣ ሸህ ዳውድን፣ ኩሊባስንና ሌሎች በጥቅሉ ሰባት ልጆችን የወለደ ነው፡፡ እነዚህ በስም የተጠቀሱት ሶስቱ ወደኢትዮጵያ የመጡት ሲሆኑ አመጣጣቸውም የሰው ነብስ በእጁ የጠፋበትን፣ ቋንጃ የቆረጠውን፣ የሰው ቤት ያቃጠለውን፣ የሰው ንብረት የወሰደውን፣ ወዘተ. እንዲያስታርቁ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ተሁለደሬ ላይ አበጋር ሲመረጥ የጅበርቲ ዝርያ ያለው መሆን ይጠበቅበታል፡፡

በማቅረብና በፍርድ ቤት ፊት በመቅረብ ስለመብታቸው መከራከር አይችሉም። ለምስክርነትም ሊቀርቡ የሚችሉት ወንድ ከጠፋ ብቻ ነው (ካህሳይ 2004:329)። በትግራይ ሴቶች በሽማግሌነትም በተሳታፊነትም ምንም ድርሻ የላቸውም (Assefa 2004:386)። አጥኚው እስካሁን ባነበባቸው ባህላዊ የግጭት አፈታት ሥርዓት ጥናቶች ውስጥ ሴቶች በታዋቂነታቸው ተመርጠው ሊሸመግሉ እንደሚችሉ ተጠቁሞ የተመለከተው በስለሺ (2004:83) ጥናት ውስጥ ብቻ ነው።

በሙሉጌታ ነጋሳ ጥናት ውስጥ (2004:238) እንደተገለጸው ከሌሎች ባህላዊ የእርቅ ሥርዓቶች ላይ ከሚፈጸመው በተለየ መንገድ አንዲት ባልቴት እናት (ቤረጭፍሬ)፣ ድንግልነት ያላት አንዲት ህጻን (ዱርበጉድሩ) እና አንድ ወንድ ህጻን ልጅ በቦታው እንዲገኙ ይደረጋል። እነዚህ ሦስት አካላት ተምሳሌታዊነት ባለው መንገድ በታራቂዎች ላይ አወንታዊ ጫና ለማሳደር ይገባሉ እንጂ በእርቁ ሂደት ላይ ምንም ተሳትፎ የላቸውም። በተለይ ቤረጭፍሬዋ የምትመረጠው የአባገዳ ሚስት ሆና በመኖሯና ልጆችን ወልዳ አሳድጋ ለአባገዳነት በማብቃቷ ነው (ሙሉጌታ 2004:248፣ Dejene 2004:276)። ማንኛይቱም ሴት እድሜዋ ስለገፋ ብቻ ለዚህ ተግባር አትታጭም፤ አትመረጥም። እዚህ ላይ አመራረጧ ባላት ግላዊ የማስታረቅ ጥበቧና እውቀቷ ሳይሆን የአባገዳ ሚስት ሆና በመኖሯ፣ ወይም ልጇን ለአባገዳ በማብቃቷ እንጂ ከወንድ እኩል ሽምግላ ታስታርቃለች ተብላ አይደለም።

የጉራጌው የአንቂት ሴራ ሴቶች የባሎቻቸውን ስምምነት ካላገኙ በስተቀር (ፍቺ ሳይፈጸምላቸው) ሌላ እንዳያገቡ ይከለክላል። በሚገጥማቸው ችግር ከቤታቸው ወጥተው ቢሄዱ እንኳ ከወላጆቻቸው ጋር ይቀመጣሉ እንጂ ሌላ ባል ማግባት አይፈቀድላቸውም። ብታገባ እሷም ቤተሰቦቿም ይቀጣሉ። ወንዱ ግን ቢያሻው ደርቦ የማግባት፣ ቢያሻው ሚስቱን በፈለገው ሰዓት ያለምንም ጥያቄ መፍታት መብቱ ነው። ሚስቱ ከቤቱ ብትወጣ እንኳ ባል አልፈታም ብሎ በአንቂት አስሮ ማስቀመጥ ይችላል (የወንድወሰን 2004:55-60)። እሷም ለገጠማት ችግር ባህላዊ ተቋሟን አልፋ ጉዳይዋን ለመደበኛው ፍርድ ቤት ብታቀርብ ለበርካታ ማኅበራዊ ችግሮች ትጋለጣለች። ለምሳሌ ከባህሉ እና ከማኅበረሰቡ እውቅና ውጭ ፍቺ ብትፈጽም ድጋሚ እንዳታገባ ቢያንስ ለሁለት ዓመታት

ያህል ትከለከላለች፤ ለወንዱ ግን እንዲህ ዓይነት ገደብ የለውም፡፡ እሷም ብትሆን በማኅበረሰቡ ለሚታመንበት ክፉ መንፈስ (Berche and Anqit) እጋለጣለሁ ብላ ትሰጋለች፡፡ በተለይ Anqit የወንዱን የበላይነት ለማረጋገጥ ሆን ተብሎ የተሰራ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም፡-

1. እርግማኑ የሚጣላው ያገቡትን ብቻ ነው፡፡
2. ካገቡት ውስጥ መርጦ ሴቶችን ብቻ ያጠቃል፡፡
3. ካገቡትም ሴቶች የ Kitcha ን ባህላዊ ተቋም ረግጠው ባሎቻቸውን የፈቱትን ብቻ መርጦ ይጠናወታል (Ayalew, 2012:34-35)፡፡

በዚያ ላይ በባሏ ተመርቃ ያልተፈታች ሴት ጤና የማታገኝ፣ ማህጸኗ የማያፈራ፣ ቢያፈራም እንኳ ልጆቿ የማያድጉላት ትሆናለች ተብሎ ይታመናል (የወንድወሰን 2004፡55-60)፡፡ ሴራው ዝም ብሎ የተደነገገ ደንብ ብቻ ሳይሆን ለዚሁ ቋሚ መሰረት የሚጥል የራሱ ሚት (የአፈጣጠር ታሪክ) ይኖረዋል፡፡ ይሄ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው? ተብሎ ማኅበረሰቡ ቢጠየቅ አሌ የማይባል የራሱን "አሳማኝ" ያለውን ምክንያት ያቀርባል፡፡ ምክንያቱም የበላይነቱን ማስፈጸሚያውና ማጽኛው እሱው ነውና፡፡ ይህ ባለበት ሁኔታ ሴትን ከወንድ እኩል ማሰለፍ እንደምን ይቻላል?

በሁሉም ባህሎች ውስጥ በተለይ ደግሞ በአማራው ባህል ውስጥ ሴት ለደም መመለሻነት አትፈለግም፤ የሚፈለገው ወንድ ብቻ ነው፡፡ ይሄ መልካም ሆኖ ሳለ[38] ግን የሚቀርበው ምክንያት የሴትን ሰብዕና የሚጋፋ ወይም ሴትን በእጅጉ ከወንድ አሳንሶ የሚመለከት ነው፡፡ ሴትን የገደለ ጀግና ሳይሆን ፈሪ ተደርጎ ስለሚታሰብ፣ ሴት ለፈሰሰው ደም ዋጋ ማካካሻ አትሆንም ተብሎ ስለሚታመን፣ የሴት ደሟ ከወንድ እኩል የደም አላባ አይሆንም በሚል እምነት ነው (ነጻነት 1998፡77-78፣ ብርሃን 2004፡149)፡፡ እንዲያውም በሁለት ቡድኖች መካከል የደም መመላለስን ለማስቀም ሴቶችን አጋና መማቻ ማድረግ (ለእርቅ ማጽኛ ማቅረብ) ልማድ ነው (ገብሬ፣ ፈቃደና አሰፋ 2004፡17)፡፡ በተመሳሳይ መንገድ በብርሃን (2002፡93) ስራ ውስጥ እንደተገለጸው ከግድያ እርቅ በኋላ ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ አንዱ የገዳይንና የሟች ወገንን በጋብቻ ማስተሳሰር ነው፡፡ በጋብቻ ሂደት ውስጥ ምንጊዜም ሴት ከገዳይ ወገን ወንድ

[38] እዚህ ላይ ሴቷ ለደም መመለሻነት አለመፈለጓ መልካም ነው ሲባል ወንዱ ግን ለዚሁ መታጨቱ መልካም ነው ማለት አይደለም፡፡

ከሚች ወገን ይሆናሉ፡፡ ይህ የራሱ ምክንያት አለው፡፡ በማህበረሰቡ እምነት (ከላይ እንደተገለጸው) ሴት ደሟ ከወንድ ደም ያንሳል ተብሎ ይታመናል፡፡ በመሆኑም በወንድ ደም ፈንታ ሴት በጭራሽ አትገደልም፡፡ ይህንን ማህበራዊ ደንብ ተከትሎ ለጋብቻ የምትመረጠው ሴት ምንጊዜም ከገዳይ ወገን ትሆናለች፡፡ ምክንያቱም የሚች ወገን እርቅ አፍርሶ ግድያ ለመፈፀም ቢፈልግ እንኳ እቤቱ ባለችው ሴት ላይ አያደርገውም፡፡ ይሄ ከማዘን የመጣ ሳይሆን ለደሙ ከሚሰጠው ሚዛን አንጻር ነው፡፡ ከአዋቂ ሴት ይልቅ በአንቀልባ ያለ ወንድ ልጅ ለብቀላ ይፈለጋል፡፡ ይህ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ሴት ከወንድ እኩል አይደለችም የሚለውን ባህላዊ አስተሳሰብ ያንጸባርቃል፡፡

በእርቁ ሥርዓት ላይ ለቂም መቁረጫ፣ ላጣላቸው ሰይጣን ማረፊያ ተብለው የሚታረዱት የመከኑ ወይም ወልደው ያበቁ ሴት በጎች፣ ፍየሎች ወይም ላሞች ናቸው (ተመስገን 2004፡99፣ ብርሃን 2004፡147፣ የወንድወሰን 2004፡53፣ ይልማ 2004፡108፣ ሙሉጌታ 2004፡242፣)፡፡ እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄ ለመስዋዕትነት የሚቀርቡት በጎችና ከብቶች በአብዛኞቹ ባህሎች ውስጥ ለምን ሴት እንዲሆኑ ተመረጡ? የሚል ነው፡፡ በእርግጥ በአንዳንዶቹ ጥናቶች ውስጥ ወንድ እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ማስወለድን ስለማያቆም እሱው ቢታረድ ጠቡ አይቆምም በሚል እምነት መውለድ ያቆሙ ወይም የመከኑ ሴት እንስሳት በመስዋዕትነት ይቀርባሉ የሚል ምክንያት ቀርቧል፡፡

ሆኖም ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሰይጣን የተዋሃዳት እባብ በሴት አንቀጽ ከመጠቀሷ፣ ሴትንም ያሳሳተችው እባብ ከአንገቷ በላይ የሴት ምስል እንዳላት መገለጹ (ቴዎድሮስ 2001፡46-52) ጉዳዩ ሃይማኖታዊ ነክነት ሊኖረው እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ Reminick (1973፡25) “Religious beliefs reflect and reinforce the norms of society by maintaining values whose nature is by and large prescriptive.” ሲል ያስቀመጠው ይህን የሚያጠነክር ነው፡፡ ገብሬ፣ ፈቃደና አሰፋ (2004፡8) ሥርዓቶች የሚመሩባቸው እሴቶች የሚመነጩት ከሃይማኖታዊ መርሆዎችም ጭምር እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም ሰይጣን ለመዋሃድ የመረጠው ሴትን ነው፡፡ በዚህ አካሄድ ሰይጣን በግብርነት (በምስነት) የሚቀበለው ሴት እንስሳትን ነው በሚል በሚመስል መልኩ በባህላዊ እርቅ ጊዜ የሚቀርቡት መስዋዕቶች ሴት እንስሳት ናቸው፡፡ በአንጻሩ አብርሃም ለፈጣሪው ያቀረበው መስዋዕት መልኩ ያማረ ወንድ በግ ነው፡፡ እነዚህን ሁለቱን ስናነጻጽር ለአምላክ ሲሆን ወንድ፣ ለሰይጣን ሲሆን ሴት መስዋዕት መቅረቡ

በሃይማኖቱም በባህሉም ያለውን የሥርዓተ ጾታ አድሏዊነት በርቀትም ቢሆን ያንጸባርቃል፡፡

ሌላው ከዚሁ ከእርቅ ጋር በተያያዘ በተለይ የደም ካሳ (ጉማ) አከፋፈል በሴትና በወንድ መካከል ልዩነት አለ፡፡[39] ለምሳሌ በኦሮሞ ባህል የሴት ከወንድ በግማሽ ያንሳል (ጌታቸው 1997፡193)፡፡ በኢሳ ብሔረሰብም ለወንድ 100 ግመል ሲከፈል ለሴት ግን 50 ብቻ ነው (ደበበ 2004፡355)፡፡ ባንዳንድ ባህሎች ውስጥ ሴቶችና ወንዶች እኩል ጉዳት ቢደርስባቸው የሚሰጣቸው ካሳ የሴቶች ከወንዶች በግማሽ ይቀንሳል (Ayalew 2012:10)፡፡ እንዲያውም በብዙ ባህሎች ውስጥ የሴቶችን የተሟላ ሰብዕና የማይቀበሉ እንዳሉ ከላይ የተጠቀሱት አጥኚ በተመሳሳይ ገጽ ላይ "Most traditions do not consider women as complete human beings" ሲሉ ይገልጹታል፡፡ ይህም ልማድ ወንድን ከፍ ሴትን ዝቅ የሚያደርግ ነው፡፡

ሌላው የሥርዓተ ጾታ ኢፍትሃዊነት ከልማዳዊ ጋብቻ ይመነጫል፡፡ በአብዛኞቹ የአገራችን ክፍሎች ያሉ ባህላዊ የጋብቻ ልማዶች ከአንድ በላይ ሚስት ማግባትን ይፈቅዳሉ፡፡ በተለይ በእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ዘንድ ሃይማኖቱም አይከለክልም፡፡ ይሄው ልማዳዊው የጋብቻ ደንብ "ማንኛውም ሰው አስቀድሞ በጋብቻ የተሳሰረ ከሆነ ይኸው ጋብቻው ፀንቶ ባለበት ጊዜ ሌላ ጋብቻ መፈጸም አይችልም" (የአማራ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 22፣ የትግራይ ክልል የቤተሰብ ህግ አንቀጽ 20 ወዘተ.) በሚል በቤተሰብ ህጉ የተቀመጠው አንቀጽ ቢታወጅም ተፈጻሚነቱ የላላ ይመስላል፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስችሉ ምክንያቶች አሉ፡፡

አንደኛው ቦረና ወረዳ ቃለመጠይቅ በተደረገበት ወቅት (02/08/2008) የተነገረ ተጠየቃዊ የሚመስል ሃሳብ ነው፡፡ ቃለመጠይቅ የተደረገላቸው ግለሰብ የወንድንና የሴትን ግንኙነት

---

[39] በሴት ላይ የሚፈጸም ግድያ ከወንድ ጋር ሲነጻጸር ያን ያህል ብዙ አይደለም፡፡ ለምሳሌ በደቡብ ወሎ የተለያዩ ወረዳዎች እስከ ሰኔ 30/2008 ዓ.ም ድረስ (በ10 ወር ውስጥ) ከተፈጸሙ 166 ግድያዎች 17 ያህሉ (10%) ብቻ በሴቶች ላይ የተፈጸሙ ናቸው፡፡ እነዚህም ቢሆኑ ከቂም በቀልና ደምን ከመመለስ ጋር የተያያዙ እንዳልሆኑ ሳጅን ታምሩ ደምሴ ከዓመታዊ የወንጀል ስታትስቲክሳቸው ውስጥ መረጃውን ሲሰጡ አክለው ገልጸዋል (ቃለመጠይቅ 25/10/2008)፡፡ ይሄ የሆነው ያለ ምክንያት አይደለም፡፡ በባህሉ ሴትን መግደል ስለማያስፎክር፣ ስለማያስመሰግንና እንደጀግናም ስለማያስቆጥር ነው፡፡ ሳጅን ታምሩም እንዳሉት የወንዱ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ከሴቶች የሰፋ ስለሆነ ከነዚህ ተሳትፎዎች ጋር በተያያዘ ለግጭት የሚጋለጡት ወንዶች በመሆናቸው ነው፡፡ በዚህም ረገድ ብናየው የሴቶች ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ውስን መሆኑ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን አድልዎ ያለበት መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

ከእንስሳት ወንዶችና ሴቶች ግንኙነት ጋር በማስተያየት አንድ ወንድ ከብዙ ሴቶች ጋር ግብረስጋ ቢፈጽም ወይም ወንዱ ከአንድ በላይ ሚስት ቢያገባ ነውርነት የሌለው መሆኑን ያምናሉ፡፡ ምክንያታቸውንም ሲያቀርቡ የግብረ ስጋ ዋናው ዓላማ ዘርን ማብዛት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ዘርን በፍጥነት ማብዛት የሚቻለው አንድ ወንድ ከብዙ ሴቶች ጋር ግንኙነት ቢያደርግ እንጂ አንዲት ሴት ከብዙ ወንዶች ጋር ግንኙነት ብታደርግ አይደለም ይላሉ፡፡ አክለውም ሲያብራሩ በአንድ የዶሮ፣ የበግ፣ የፍየል ወይም የከብት መንጋ ውስጥ አንድ አውራ በቂ ነው፡፡ እንዲያውም በአንድ መንጋ ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ አውራዎች ቢኖሩ በመካከላቸው ባለው ሽኩቻ መንጋው ይበጠበጣል፡፡ ሴቶች ግን ተስማምተው ይኖራሉ፡፡ በመሆኑም ለእያንዳንዷ እንስት ለየብቻዋ አንድ አንድ አውራ አያስፈልጋትም በሚል በንጽጽር የወንድን ብዙ ሚስት ማግባት ባይደግፉትም አይቃወሙትም፡፡ በጋብቻ ላይ ጋብቻን ህጉ ቢከለክልም ከአንድ በላይ ለማግባት ያላቸው ስሜት ግን ህጉን የሚያፈርስ ነው፡፡

ሌላው በእሸቱ (1997፡156-157) ስራ ውስጥ የተገለጸው ነው፡፡ እሸቱ በቴሌቪዥን የቀረበውን ዜና መሰረት አድርገው እንደጻፉት ሃምሌ 1/1995 ዓ.ም ስብሰባውን ያበቃው የኦሮሚያ ጨፌ ሰባተኛ መደበኛ ጉባኤ በክልሉ የቤተሰብ ህግ ረቂቅ ላይ ሲመክር ቢቆይም በጋብቻ ላይ ጋብቻን የሚከለክለው አንቀጽ በአብላጫ ድምጽ ውድቅ በመደረጉ በጊዜው ሳይጸድቅ መቅረቱን ጠቁመዋል፡፡ እዚህ ላይ ጉዳዩን ይበልጥ አነጋጋሪ የሚያደርገው የድምጽ ሰጪዎችን ጾታ ስንመለከት ነው፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ በሂሳብ እንመልከተው፡፡

ጠቅላላ የጨፌው አባላት 537 ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የሴት መማክርት አባላት ቁጥር 70 ናቸው፡፡ ከነዚህ የሴት መማክርት አባላት ውስጥ በእለቱ የተገኙት 63 ናቸው፡፡ በጋብቻ ላይ ጋብቻ የሚከለክለውን አንቀጽ የደገፉት ከ537 የምክር ቤት አባላት ውስጥ 29 ሰዎች ብቻ ናቸው (ሴትም ወንድም ሊሆኑ ይችላሉ)፡፡ በወቅቱ ድምጽ ያልሰጡት ሰዎች 14 ናቸው፡፡ በጋብቻ ላይ ጋብቻ መከልከል አለበት ያሉት እና ድምጽ ያልሰጡት አንድ ላይ ሲደመሩ በእለቱ ከተገኙት ሴት የምክር ቤት አባላት ቁጥር ያንሳሉ፡፡ በዚህ ስሌት መሰረት በጋብቻ ላይ ጋብቻ መከልከሉን የደገፉት እና የታቀቡት ሁሉም ሴቶች ቢሆኑ እንኳ ቁጥራቸው 43 (29+14) ይሆናሉ፡፡ ይህ ማለት 20 (63-43) ያህሉ ሴቶች

በጋብቻ ላይ ጋብቻ መፈጸምን ከወንዶች ጋር ሆነው ደግፈዋል ማለት ነው። ይሄ ባህሉ እጅግ ስር የሰደደ መሆኑን ያሳያል።

ይህን የመሰለው ስር የሰደደ እምነትና አመለካከት የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን እኩልነት ለማምጣት የሚደረገው ጥረት በራሳቸው በሴቶች በኩል ፈተና ያለበት መሆኑን እንረዳለን። ምክንያቱም ይሄ ልማዳዊ ህግ በቁጥር በማይገመት ዘመን ውስጥ በሂደት አልፎ መሰረቱን ያደላደለ፣ ህያው የሆነ፣ በቀላሉ በአዋጅና በመመሪያ ባንዳፍታ ንደን ልናስተካክለው የማንችለው ክስተት ነው። ዞሮ ዞሮ የልማዳዊ ህጉ ዓላማ፣ የመጨረሻ ግብ የወንዱን የበላይነትና ሥልጣን ማስጠበቅ ነው።

ሌላው የሥርዓተ ጾታ አድሏዊነት በዘር ሀረግ ቆጠራና ሰዎች እንዲኖሯቸው ከሚፈልጓቸው ልጆች ጾታ አንጻርም ይገለጻል። የዘር ሃረግ የሚቆጠረው በወንዱ መስመር ነው። ይሄ ሃይማኖታዊውን ደንብ የተከተለ ይመስላል። በመጽሃፍ ቅዱስ ውስጥ የምናስተውላቸው የዘር ቆጠራዎች አብዛኞቹ በወንድ መስመር የተደረጉ ናቸው። ለምሳሌ በማቴ.1፣1-17፣ ዘፍጥ.10፣1-32፤11፣1-32 ወዘተ. እና በብዙ ቦታዎች ውስጥ በጉልህ ተንጸባርቋል።

የአገራችንም የዘር ቆጠራ ከዚህ የተለየ አይደለም። የደቡብ ወሎን የዘር ሃረግና አሰፋፈር ባየንበት ክፍል ውስጥ እንደተገለጸው የወሎ ኦሮሞ ዘር ከግንዱ ጀምሮ ሲመዘዝ ወንድን ብቻ መሰረት ያደረገ ነው (አለቃ ታዬ 2008፣ OCTB 2006):: ሴት በሃረግነት አልተመዘዘችም። በሁሉም ቦታ ላይ “የዘር ግንድ የሆኑት አባቶች” በሚል የተቀመጠ ነው። ይህ ሴት በዘር ሃረግ መቁጠሪያነት አለማገልገሏ በባህሉ ውስጥ የተሰጣትን ዝቅተኛ ቦታ ያሳያል። በዚያም ላይ አንድም ጊዜ ሥልጣን ያልያዘች በመሆኑ እንደወንዶች በስሟ የተጠራ ቦታ የለም። አባትም አካባቢዎችን ከሥልጣን ጋር በእርስትነት ሲያከፋፍሉ የተጠቀሰች ሴት አንድም ቦታ አታጋጥምም። በኦሮሞ ባህል ሴት ርስት አትወርስም (ጀቤሳ 1989፡71) የሚለውን የቆየ እምነት ከመፈጸም የተነሳ ሊሆን ይችላል።

ሰዎች እንዲኖሯቸው ከሚፈልጓቸው ልጆች ጾታ አንጻርም ብንመለከት ባብዛኛው ወላጆች እንዲወለድላቸው የሚፈልጉት ልጅ ወንድ ነው ማለት ይቻላል[40]። ለዚህ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ አባባሎችን፣ ቃልግጥሞችን፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. መመርመር ይበቃል። ሥነቃሎች የሰውን ልጅ ውስጣዊ ፍላጎት ቁልጭ አድርገው ያሳያሉና ተኣማኒነታቸው በመጠይቅና በቃለመጠይቅ ከሚሰበሰብ አስተያየት የተሻለ ነው።

ከላይ ባለው አንቀጽ የቀረበውን ሃሳብ የሚያጠናክር አንድ ገጠመኝ እንመልከት። አጥኚው በ1993 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሲማር የገጠመው ነው። በክፍሉ ከነበሩት ሴት ተማሪዎች ውስጥ አንዷ ትወልዳለች። በወቅቱ “English for teaching purpose” የተባለውን ኮርስ የሚሰጡን መምህር ክፍል ውስጥ ገብተው ስም ቁጥጥር ሲያደርጉ የወለደችዋን “ምን ሆና ቀረች?” ይላሉ። ምክንያቱ ይነገራቸዋል። ከኪሳቸው ብር አውጥተው “በሉ እናንተም እዚህ ላይ ጨምሩና ጠይቋት” ይላሉ። ኋላ ላይ ግን “ምን ወለደች?” ይላሉ። “ሴት!” አልናቸው። በዚህ ጊዜ ቅር ብሏቸው “አይይይ…! ትሁን!” ማለታቸውን እናስታውሳለን። ወንድ ልጅ ሲወለድ ለወላጆቹ ይቅርና ለዘመድም፣ ለጎረቤትም ለሰሚም ደስ ይለዋል። የአብዛኞቻችን ምክንያት መከታ ፍለጋ ይመስላል።

በሥነቃሎችም ረገድ ያለውን ስንመለከት የሴቶችን ሰብዕናና ህሊና የሚፈታተን፣ ድፍረትንና በራስ የመተማመን መንፈሳቸውን የሚያሳጣ በብዙ ነገር ከወንድ ማነሳቸውን የሚያሰርጽ ሆኖ ይስተዋላል። ለምሳሌ በምሳሌያዊ አነጋገሮች በኩል ያለውን ብንመለከት ሴት አግብተው ሴት ቢወልዱ የታለ ንግዱ፣ ሴት የወለደ መቅ የወረደ፣ ሴት የወለደ ተዋረደ፣ ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ፣ ሴትን ያማከረ ሽክሙን በሳር ያሰረ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ይገኛሉ።

ከላይ ያለውን ሃሳብ ከቃል ግጥምም አንጻር ብንመለከተው እንደዚያው ነው። ይህን በተመለከተ ለአጥኚው ልዩ ትርጉም የሰጠውን በ Kalklachew (1997፡80-89) ስራ

---

[40] Kiriti (2011፡14) ይሄው ፍላጎት በዓለም ላይ ተመሳሳይ መሆኑን ሲያስረግጡ “Gender inequality exists in most parts of the world and manifests itself in the form of parents wanting the new born to be a boy rather than a girl” ብለዋል።

ውስጥ ያገኘውን እንመልከት፡፡ ቃል ግጥሙ ከፍርድ አለማስተካከል ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ሴትዮዋ አንድ ልጅ ብቻ ትወልድና እርሱው ይሞትባታል፡፡ ጎረቤቷ ግን አስር ወልዳ አስሩም በህይወት ይኖራሉ፡፡ ይህን ጊዜ በሃዘንም በቅናትም የተንገበገበችው፣ ምንም ማስረሻ የሌላት እናት የክርስቶስን የተዛባ ፍርድ በሙሾዋ፡-

አስር አስቀምጠህ አንዱን ትገድላለህ፣
<u>የሴት ልጅ</u> ነህና ምን ፍርድ ታውቃለህ፡፡

ስትል ገጥማለች፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጉዳያችን ሁለተኛው ስንኝ ላይ ያለው ሃሳብ ነው፡፡ እንደሚታወቀው ክርስቶስ ስጋዊ አባት የለውም፡፡ በድንግልና ተረግዞ፣ በድንግላና ተወልዶ፣ ያለስጋዊ አባት በእናት እጅ (በሴት) ያደገ ነው፡፡ የዚህ ቃልግጥም አንድምታ የሚነግረን ሴት በተፈጥሮዋ የተስተካከለ ፍርድ ለመስጠት የሚያስችል አዕምሯዊ ብቃት የላትም የሚለውን ባህላዊ አስተሳሰብ የሚያጎላ ነው፡፡ ምክንያቱም የተስተካከለ ፍርድ የመስጠት ብቃት ኖሯት ቢሆን ልጇንም ባምሳሏ ልትፈጥረው ትችል ነበር የሚል ነው፡፡ ይሄ በአንድምታ የሚመጣ ነው፡፡ እንዴት ቢሉ ልጅ አሳዳጊውን ይመስላልና ነው፡፡

ግጥሙ ላይ "ሴት" ለማርያም ብቻ የተነገረ ሳይሆን በጥቅሉ ለሁሉም ሴቶች በጅምላ የተሰነዘረ ነውና ፍርድ አለማስተካከል የሴት ባህሪ ተደርጓል፡፡ ሙሾ አውራጇ ሙሾዋ እሷንም ጭምር የሚነካ መሆኑን ብታውቅም ከማኅበረሰቡ የጋራ አስተሳሰብ ልትወጣ አትችልምና ልማዱ "ልክ ነው" ብሎ በደነገገው መሰረት (የሴት ልጅነት) ልትገጥም በቅታለች፡፡ ዞሮ ዞሮ ቃልግጥሙ የወንድን የበላይነትና የሴትን የበታችነትን ለማስረጽ ታልሞ መነገሩን ልብ እንላለን፡፡

በሌሎችም ለምሳሌ ተምሳሌታዊ ትዕምርቶችን እና ተፈጥሯዊ ክስተቶችን ተከትለው ያሉት ሁኔታዎች በሥርዓተ ጾታ ረገድ ያለውን አስተሳሰብ ያሳያሉ፡፡ በትዕምርቶች ረገድ ያለውን እንመልከት፡፡ ለዚህ በኦሮሞ የጋብቻ ባህል መሰረት ተጋቢዎች በጋብቻቸው ቀን ወንዱ ከአባቱ፣ ሴቷ ከእናቷ የሚሰጧቸው ብትሮች አሉ፡፡ በተለይም የአባ ገዳውንና የሚስቱን ብትሮች[41] ብንመለከት በሁለቱ ጫፎቻቸው በኩል የወንድንና የሴትን

[41] የወንዱ ብትር 'Bokkuu' ሲባል የሴቷ ደግሞ 'Siinqee' ይባላል፡፡ የቃል ታሪኮች እንደሚያሳዩት እነዚህ ትዕምርታዊነት ያላቸው ብትሮች ለአባገዳው ከቃሉ የተሰጡ ናቸው፡፡ 'Bokkuu'ውን አባገዳው ብቻ ሲይዘው 'Siinqee'ን ግን ያገቡ ሴቶች ሁሉ ይይዙታል፡፡ 'Siinqee' ሴቶች ባለትዳር መሆናቸውን

ሃፍረተስጋዎች እንዲወክሉ ተደርገዋል፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ ትዕምርትነቱ ላይ ሳይሆን አያያዙ ላይ ነው፡፡ አያያዙ ምንጊዜም የወንዱ ወደ ላይ ሲሆን የሴቷ ግን ወደ ታች ሆኖ ነው፤ ፈጽሞ ተገላብጦ ሊያዝ አይችልም፡፡ ይህንን ባህሉ ደንግጓል፡፡ ይህም በባህሉ ወንድ ከሴት በተሻለ የተሰጠውን ግምት እንድንገነዘብ ያደርገናል፡፡

እህል በሚወቃበትም ጊዜ ሴት አውድማ ውስጥ አትገባም፡፡ በባህሉ ሴት አውድማ ብትገባ በረከት ታሳጣለች፣ ምርት ትበትናለች ተብሎ ይታመናል፡፡ በዚሁ አስተሳሰብ በመነጨ በሚመስል መልኩ ሴት ማዕድም አትባርክም፣ ቡራኬም አትሰጥም፡፡ በዚህ አስተሳሰብ ምሳሌነቱ ሴት በረከት የለሽ ናት በሚል ይታሰባል፡፡

ከእንጨትም ሳይቀር ሴቴና ወንዴ አለው፡፡ ለምሳሌ በቦረና ወረዳ ውስጥ በብዛት ለብትርነት የሚያገለግለው ሰፋ (ጠንካራ የእንጨት ዓይነት ነው) በዓይነቱ ሁለት ነው፡፡ አንደኛው ወንዴ ሲባል ሁለተኛው ሴቴ ይባላል፡፡ በእንጨቶቹ መካከል ያለው ልዩነት ወንዴው ጠንካራ ሲሆን ሴቴዋ ግን ያን ያህል አይደለችም፡፡ በቀላሉ ትሰበራለች፤ ትሰነጠቃለች፡፡  ከጭረት ተክልም ወንዴና ሴቴ አለው፡፡ ስያሜው ከእንጨቱ ጋር ትይዩ ነው፡፡ በልብስ ቁልፎች (አዝራሮች) ያለውንም ስንመለከት እንዲሁ ያጋጥመናል፡፡ ትንንሾቹ አዝራሮች ሴቴ ሲባሉ ትልልቆቹ ወንዴ ይባላሉ፡፡ እዚህ ላይ የሚገርመው ነገር ምንዛሬውን ስንመለከት ነው፡፡ አንድ ወንዴ አዝራር በሁለት ሴቴ አዝራሮች ይለወጣል፡፡ እዚህ ላይ አስተማስሎዎቹ በአጋጣሚ የተባሉ አይደሉም፡፡ ከተናጋሪዎቹ ወይም ከተነገረላቸው አካሎች ጋር በባህላዊ ስምምነት ላይ የተመሰረተ አስተሳሰብ ያንጸባርቃሉ (Skeggs 2002፡21)፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን የመሰሉ የተባለጥ ባህሎች በየብሔረሰቡ እንደሚገኙ እሙን ነው፡፡ ተጽዕኗቸውም እስከ አሁኑ ዘመን ድረስ መዝለቃቸው ብቻ ሳይሆን አሁን አሁን በሚሰሩ ሎጎዎች ላይ ተንጸባርቆ ይታያል፡፡ ለዚህ እንደ አብነት የቀድሞውን የኢትዮጵያ ቤተሰብ መምሪያን እና የህይወት ትረስት ኮንዶምን ሎጎዎች ማስተዋል ይበቃል፡፡ ወንዶቹ ከፍ ሴቶቹ ዝቅ ተደርገው ተስለዋል፡፡ ማሳያዎች ብዙ ናቸው፡፡

ይሁን እንጂ በየባህሉ ሴቶችን ከወንዶች የሚያስቀድሙ ማሳያዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ በምሳሌያዊ አነጋገሩ፣ በአባባሉ፣ በተረቱ ውስጥ የምንጠቅሳቸው እናገኛለን፡፡

---

ያመላክታል፡፡ በተጨማሪም በወንዶች ሊደርስባቸው የሚችልን ጥቃት ለመከላከልና የክብራቸው መግለጫ በመሆን ያገለግላል (Tolosa 2011፡282-283)፡፡

ሆኖም ግን ይዘታቸውን ስንመረምር ለወንዱ ብሎም ለቤተሰባቸው ከሚሰጡት ግልጋሎት አንጻር በሚመስል አኳኋን የተነገሩ ይመስላል፡፡ በምሳሌያዊ ንግግሮች በኩል ያለውን ስንመለከት እንደ "በሴት የበከረ ከእግዜር የተማከረ፣ የታደለች ሴት በፊት ትወልዳለች ሴት፣ የሴት ምክር የእሾህ አጥር፣ የሚስት አሳቢ የጥንድ በሬ ሳቢ ይስጥህ" (መስፍን 1991) ወዘተ. የመሳሰሉት ስለሴት ጥሩነት ቢናገሩም የተነገረበት መንገድ ለወንድ ወይም ለቤተሰባቸው ከሚሰጡት ጥቅም አንጻር ነው፡፡

## 4.3 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ተረትን በተመለከተ በመጀመሪያ፣ በሁለተኛ እና በሦስተኛ ዲግሪ የተሰሩ በርካታ ጥናቶች አሉ፡፡ በዚህ ጥናት ሁሉንም ማካተት ስለማይቻል ይበልጥ የርዕሰ ነገርና የይዘት ቅርበት አላቸው በተባሉት እንዲሁም ይህ ጥናት አዲስና የተለየ መሆኑን ያሳያሉ በተባሉት ላይ ብቻ ትኩረት ተደርጓል፡፡

ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡት የሥነቃል ጥናቶች ባጭር ስራ ውስጥ በርካታ ነገሮችን ለማካተት ሙከራ የተደረገባቸው ናቸው፡፡ ለምሳሌ የተረት ቅርጾች፣ የተረት ዓይነቶች፣ የተረት ይዘቶች፣ የአተራረክ ስልቶች ወዘተ. የመሳሰሉትን አካትተው ለማጥናት የጣሩ ናቸው፡፡ እንዲህ መሆናቸው በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትኩረት ሰጥተው እንዳያጠኑ ያደረጋቸው ይመስላል፡፡ ቢሆንም ለደረጃው አይመጥኑም ማለት አይደለም፡፡

ቀደም ካሉት የመጀመሪያ ዲግሪ አጥኚዎች ውስጥ ያዕቆብ (1974)፣ ድሃብ (1974)፣ አወቀ (1975)፣ ሙሉጌታ (1976)፣ ጥላሁን (1980)፣ ተስፋዬ (1993)፣ ሙሉነህ (1993) ተመሳሳይነት ያላቸውን ጥናቶች አድርገዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና አካል አድርገው የወሰዱት ተረቶችን ከቅርጽና ከይዘታቸው አንጻር መድቦ ማጥናት ላይ ነው፡፡ የሁሉም አጥኚዎች አካሄድ ተመሳሳይ ሲሆን ለይዘትነት የመረጧቸው ርዕሰ ነገሮችም ተመሳሳይነት ይታይባቸዋል፡፡ ባብዛኛው ስለ ብልጠት፣ ተንኮል፣ ሞኝነት፣ ደግነት፣ ብቀላ፣ ስርቆት፣ ወዘተ የሚተነተኑ ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥናቶቻቸው በጥቅሉ ሲታዩ ተረትን መነሻ አድርገው ይስሩ እንጂ በይዘት ረገድ ስለ ሥርዓተ ጾታ ወይም ስለ ሥልጣን አላነሱም፡፡ አጥኚዎቹ ከሚወስዷቸው ኮርሶችና በደረጃው ከሚሰጠው የፎክሎር ጽንሰ ሃሳብ ውስንነት አንጻር ጥናቶች በቂ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

እንግዳ (1974)፣ አበበ (1982)፣ ሰውነት (1984)፣ ሱሩር (1992) እና ጥሩነህ (1982) በበርካታ የይዘት ትንተና ርዕሶቻቸው ውስጥ ስለ እንጀራ እናት ጨካኝነት አንስተዋል፡፡

በዚህም በተወሰነ መልኩ ሴቶች በተረት ውስጥ ምን ዓይነት አሉታዊ ገጽታ እንደተሰጣቸው ያሳያሉ፡፡ በዚህ ረገድ ከዚህ ጥናት ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ የሰውነት (1984) ከሌሎች አጥኚዎች በተለየ ስለሴቶች በአወንታዊ መልኩ የሚያወሱ ተረቶችን መርጠው ለመተንተን ጥረዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከሌሎች በተሻለ መልኩ ከሰውነት ጥናት ጋር ቅርበት አለው፡፡ በጠቅላላው ሲታይ ይህ ጥናት ተረት ከሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ጋር ያለውን መስተጋብር ከማሳየቱም በላይ ሴቶችና ወንዶች በተረቶች ውስጥ በአሉታና በአዎንታ እንደምን እንደተሳሉ በዝርዝር ስለሚያሳይ ከቀደሙት የመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች ልዩነት አለው፡፡

በሁለተኛ ዲግሪ ደረጃም እንዲሁ የተሰሩ በርካታ ጥናቶች አሉ፡፡ እነዚህን ተራ በተራ እንመልከታቸው፡፡

የ Abdulkadir (1982) ጥናት ዋና ዓላማ የሱማሌን ተረቶች ይዘት መሰረት በማድረግ በዓይነት መመደብ ብሎም የማኅበረሰቡ ባህላዊ ገጽታዎች እንዴት እንደተንጸባረቁባቸው ማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ከመስክ የሰበሰቧቸውን ተረቶች ይዘታቸውን መነሻ አድርገው በስምንት ክፍል መድበው አጥንተዋቸዋል፡፡ በሰባቱ ምድብ ውስጥ ገላጭ ተረት፣ የብልህነት ተረት፣ የእውቀት ተረት፣ የፍትህ ተረት፣ ሃይማኖታዊና ሥነምግባራዊ ተረት፣ የጋብቻ ተረት፣ የተፈጥሮ አደጋ ተረት በሚል በቀረቡ ንዑስ ርዕሶች የሚስተዋሉት ጭብጦች በነገረ ይዘታቸው ከዚህ ጥናት ጋር ሲተያዩ ግንኙነት የላቸውም፡፡

በገላጭ ተረቶች ውስጥ የተመደቡት ተረቶች የሶማሊ ጎሳዎችን አመጣጥና ለተፈጥሯዊ ክስተቶች ምክንያት ከማበጀት ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የብልህነት ተረቶች ሰዎች ለሚገጥማቸው እለታዊ ችግር የተወጡበትን ብልሃት (በሴትና በወንድ ሳይለይ) እና ፈጣን መፍትሄ አሰጣጥን በተመለከተ እንዴት እንደተገለጸ አሳይተውበታል፡፡ የእውቀት ተረቶች በሚል ስር የሶማሌን ማኅበረሰብ ደንቦች ጠንቅቆ ከማወቅና ከመተግበር ጋር የሚያያዙ እንደሆኑ ጠቅሰዋል፡፡ ከፍትህ ጋር የተያያዙት ተረቶች ሰዎች ለሃይማኖታቸው ወይም ለእውነት ሲሉ በጎ ነገር ሊያደርጉ እንደሚገባ፣ ባያደርጉ ችግር እንደሚገጥማቸው፣ በጎ ነገር በማድረጋቸው ጥቃት ቢመጣባቸው ፈጣሪያቸው እንደሚያድናቸው የሚያትቱና የብልህ ሰዎችን የፍርድ አሰጣጥ ጥበብ የሚያሳዩ በጠቅላላው ሃይማኖታዊና ሥነምግባራዊ እሴቶችን የሚያሰርጹ እንደሆኑ ተብራርቷል፡፡ ይሄ በዚህ ጥናት አቅራቢ ያልታየ በመሆኑ ሁለቱ ጥናቶች ልዩነት አላቸው፡፡

ሆኖም በምድብ ክፍለው ካጠኗቸው ውስጥ “ሴቶችና ቅናት” በሚል ትንተና የሰጡበት ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር መጠነኛ መመሳሰል ይታይበታል፡፡ Abdulkadir በዚህ ንዑስ ርዕሳቸው ሴቶችና ቅናት የማይነጣጠሉ ተደርገው በሶማሌ ማኅበረሰብ እንደሚታመኑ ተረቶችን እያጣቀሱ አስረድተዋል፡፡ ሴቶች በሶማሌ ማኅበረሰብ የግድ አስፈላጊዎች ቢሆኑም በወንድ ተጽዕኖ ስር መሆን እንደሚገባቸው መታመኑን ጠቅሰዋል፡፡ በተጨማሪም ሴቶች ለወንድ ልጅ መከራ አምጭዎች (እንደ ሀዋ) እና ውስጣቸው የማይታወቅና የማይጨበጡ ፍጡር ተደርገው መታሰባቸውን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ወንዶች ልጆች ከልጅነታቸው ጀምረው የሴቶች ሰይጣናዊ ባህሪ እየተነገራቸው እንዲያድጉና ሲያገቡም መብት እንዳይሰጧቸው እንደሚመከሩ ያሳያል፡፡ ይህንን በተነተኗቸው ሦስት ተረቶች ውስጥ ለማስረገጥ ጥረዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የሴቶች ቅናት እና ግትርነት ወንዱን በማጥቃት ላይ ያነጣጠሩ ቢሆንም ያሰቡት ሳይሳካላቸው ራሳቸው ተጎጂ መሆናቸውን ተረቶች ማሳየታቸውን ገልጸዋል፡፡ በዚህ ረገድ የ Abdulkadir ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ቢያንስ ለሴቶች ዝቅተኛ ግምት መስጠቱን ስለሚያረጋግጥ መመሳሰሉ አለ፡፡ ሆኖም ግን ለሴቶች የተሰጠው ዝቅተኛ ግምት በተራዛሚ ያስከተለባቸውን የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን አድልዎ አላመላከቱም፡፡ ይህ ጥናት ይህንን ተጨማሪ ይዘት ያካተተ በመሆኑ ይለያል፡፡

Yihenew (በ1996) በምዕራብ ጎጃም በአማርኛ በሚነገሩ ቃላዊ ተረኮች ላይ ትኩረታቸውን አድርገው አጥንተዋል፡፡ የጥናታቸው ዋና ዓላማ ለተረቶች ምደባ ማድረግ ሲሆን አስቀድሞ ለተረቶች ዓለማቀፋዊ የሆነ ሁሉንም የሚያስማማ የተረት መመደቢያ መስፈርት እንደሌለ ገልጸው ነገር ግን የተረቶችን ክዋኔ፣ የተረቶችን ዓላማ፣ የተረቶችን ጭብጥ፣ የአተራረክ ዘዴ፣ እንዲሁም የገጸባህሪያትን አሳሳል በመመርመር የራሳቸውን ምደባ አድርገዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተረት፣ አፈታሪክና ዘር ቆጠራ በሚል በሦስት ከፍለዋቸዋል፡፡ በእያንዳንዱ ክፍፍል ስር ሌሎች ክፍፍሎችን እያደራጁ ጭብጣቸውን፣ አወቃቀራቸውን፣ የአተራረክ ስልታቸውንና ገጸባሪዎቻቸውን በጥሩ ሁኔታ ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ ይሁንና በተረቶቹ ውስጥ የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን ኢፍሃዊ መስተጋብር የተመለከቱ ተረቶች ቢኖሩም የተነሱበት ዓላማ እነዚህን እንዲዳስሱ አያደርጋቸውምና አልተመለከቷቸውም፡፡

Abreham (2000) የጅማ ኦሮሞ ቃላዊ ተረኮችን መነሻ አድርገው ገላጭ ትንተና ሰርተዋል፡፡ ምርምራቸው ከ Yihenew (1996) ብዙም ያልተለየ ነው፡፡ ሁለቱም

ለተረቶች አካባቢያዊ ምደባ ካደረጉ በኋላ ከማኅበራዊ አውዱ ጋር እያገናዘቡ ትንተና ሰጥተዋል፡፡ ሁለቱም የተረቶችን ትርጉም መግለጽ እንጂ በማህበረሰቡ ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ አጉልተው አላሳዩም፡፡ ሁለተኛም በጾታ ለያይተው የተመለከቱበት አጋጣሚ ስለሌለ ከዚህ ጥናት ይለያሉ፡፡

Sahilu (2002) በቦረና ኦሮሞ ተረቶች ላይ አውዳዊ ጥናት አድርገዋል፡፡ ከቦረና የሰበሰቧቸውን ተረቶች ቅርጽና ይዘታቸውን መሰረት አድርገው ከመደቡ በኋላ ከመዋቅራዊ ንድፈ ሃሳብ አንጻር ትንተናቸውን እንደሚያካሂዱ በምዕራፍ አንድ መግቢያ ላይ ጥቆማ ሰጥተዋል (2002፡3)፡፡ በዚሁ መሰረት በተለይ የህጻናት ተረቶችን መዋቅር ሲያጠኑ ከ Propp እና Dundes የተረት መዋቅራዊ ሂደቶች (Functions) አንጻር ተመልክተው (ገጽ 19፣ 26-27) ከቦረና ተረቶች ጋር በመዋቅር መመሳሰል እንዳለ አሳይተዋል፡፡

Sahilu ለተረቶች ትንተና የሰጡት ከአውዳቸው አንጻር ነው፡፡ ተረቶችንም በሦስት ከመደቡ በኋላ (duri-duri, Mamaksa, Arga-Ageti) እያንዳንዳቸውን ከአውዳቸው አንጻር እያስተያዩ የይዘት ትንተና አድርገዋል፡፡ አመዳደብን በተመለከተ Ben Amos (1975፡168-171) ባህላዊ የዝርያ አመዳደብ ተገቢ መሆኑን ባመላከቱት መሰረት ምደባ ቢያደርጉም እንደገና ደግሞ በ Bascom (1965) ና በ Okpewho (1992) አመዳደብ መሰረት እነዚያኑ ተረቶች ሌላ ምደባ ሊደረግላቸው እንደሚችል ጠቅሰው ምደባም አድርገዋል፡፡ ለትንተና የተጠቀሙትም የተራኪዎችን ትርጉም ነው፡፡

በ Sahilu (2002) ጥናት ውስጥ ተረቶች ከአገልግሎታቸው አንጻር ሃሳብን የበለጠ ግልጽ ለማድረግና ግጭትን ለማብረድ እንደሚረዱ፣ ከአጠቃቀማቸው አንጻር እያንዳንዱ ተረት ሊነገር ከተፈለገበት ጉዳይ ጋር የሰመረ እንደሆነ፣ እንዲሁም የቋንቋው አጠቃቀም የተዋበና ከባህሉ ጋር የተዋሃደ እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ በጠቅላላው የ Sahilu ጥናት ዋናው ትኩረቱ ክዋኔ ላይ ነው፡፡ ይዘታቸውንና ፋይዳቸውን በተመለከተ ያሉት የለም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በተረት ላይ በመሰራታቸው ይመሳሰሉ እንጂ የነገረ ይዘት ዝምድና የላቸውም፡፡

Melakineh (1990) የጎጃም ደቡባዊ አገዎችን ተረቶች አጥንተዋል፡፡ የጥናታቸውም ዋና ትኩረት የተረቶችን ዋና ዋና ጭብጦችና ንጥረ ጭብጦች (Theme and Motifs) አውጥቶ በማሳየት ላይ ያነጣጠረ ነው፡፡ ለዚህም ይመቻቸው ዘንድ በቅድሚያ ለተረቶች

ምደባ አድርገዋል፡፡ ቀደም ብሎ ዳሰሳ እንደተደረገባቸው የሁለተኛ ድግሪ ጥናቶች ይሄኛውም ጥናት የተከተለው መንገድ ተመሳሳይ ነው፡፡ ጥናቱ በእያንዳንዱ ምድብ ስር የጭብጥ ተመሳሳይነት ያላቸውን ተረቶች እያጣቀሰ የሰውን ልጅ ባህሪያትና ሥነምግባር የሚሰብኩበትን መንገድ ለመግለጽ ጥሯል፡፡ ተረቶች ከሥርዓተ ጾታና ከሥልጣን ጋር ተዛምደው የቀረቡበት አጋጣሚ ስለሌለ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰልበት አጋጣሚ የለም፡፡

ለማ ንጋቱ (1999) በየም ብሔረሰብ ተረቶች ላይ ጥናት አድርገዋል፡፡ በጥናታቸውም የየም ተረቶች የወንዶችን እና የሴቶችን ገጽታ እንዴት እንዳሳዩ ትኩረት ሰጥተው ተንትነዋል፡፡ በዚህ ይዘቱ "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል ከቀረበው ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ለማ በሥርዓተ ጾታ ላይ ትኩረት አድርገው ሰርተዋል፡፡ በጥናታቸው ከየም በሰበሰቧቸው ተረቶች አማካኝነት በወንዶችና በሴቶች ዙሪያ በአሉታና በአወንታ የቀረቡ ተረቶችን ተንትነዋል፡፡ አጥኚው ይህንንም ያደረጉት የተረቶችን ቀጥተኛ ትርጉም በመያዝ ብቻ ነው፡፡ በአንጻሩ በዚህ ጥናት የሴቶችን ጥንካሬ ለማሳየት የተቻለው በቀጥታ በተነገሩት ተረቶች ውስጥ ብቻ ሳይሆን የወንዶችን ሰብዕና ለመገንባት ሲባል ከተተረኩት ተረቶች ብሎም የሴቶችን ሰብዕና ከሚያጣጥሉ ተረቶች ውስጥ አንድምታ በማውጣት ወይም በመፈከር ነው፡፡ ይሄ ለማ ያልተመለከቱት አቅጣጫ ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ ጥናት በተሰበሰቡት ተረቶች አማካኝነት ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ተቀናጅተው የቀረቡበት ስለሆነ ጥናቱ በስፋቱም በይዘቱም የተለየ ነው፡፡

ሌላው Abreham (2007) በአፍሪካ የባህል ጥናት ጆርናል ላይ ለህትመት ያበቁትን በጅማ ኦሮሞ ተረቶች ላይ የሰሩትን ጥናት እናገኛለን፡፡ የጥናቱ አቢይ ዓላማ ቃላዊ ተረኮች ሴቶችን ለመጨቆን እንዴት እንደ ርዕዮተ ዓለማዊ መሳሪያ እንዳገለገሉ ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው የጥናቱን ማኅበረ ባህላዊ ዳራ መግለጽ ሲሆን በዚህም የጂማ ኦሮሞ ሴቶች በማኅበረሰባቸው ውስጥ ያላቸው ደረጃና ሚና የተገለጸበት ነው፡፡ በዚህም ሴቶች ያሉበትን ወቅታዊ ሁኔታ መመርመር፣ ከሥርዓተ ጾታ ደንቦች ጋር በተያያዘ ያለውን የጋራ አስተሳሰብ ተጠቃልሎ የቀረበበት ነው፡፡፡ በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ከመስክ የተሰበሰቡ ሥርዓተ ጾታ ተኮር ቃላዊ ተረኮችን ርዕዮተ ዓለማዊ ሚና በማኅበረ ባህላዊ አውዳቸው ውስጥ በመተንተን የሴቶችን ዝቅተኝነት እንዴት እንዳሰፈኑ ማስረጃዎች እየተጣቀሱ የቀረቡበት ነው፡፡

Abreham (2007:58) በጥናታቸው የጅማ ኦሮሞ ወንዶች ብዙ ሚስቶችን ማግባት ከመቻላቸውም በላይ በማንኛውም አጋጣሚ የበላይነቱን እንደሚይዙ፣ ሴቶች ግን እንደ ተንቀሳቃሽ እቃ ተቆጥረው ለወንዶች ታዛዥ የመሆን ግዴታ እንዳለባቸውና የወንዶች ጥገኛ እንደሆኑ አቅርበዋል፡፡ ሆኖም ከመድረክ በስተጀርባ ሴቶች በፖለቲካውም በኢኮኖሚውም መድረክ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ Jones (1981:152)ን ጠቅሰው ከላይ በተገለጸው ገጽ አስፍረዋል፡፡

Abreham ባቀረቡት ጥናት ውስጥ በሁለቱ የተረት ዓይነቶች (Seenaa እና Oduu durii) ሴቶች ተስለው የሚታዩት የወንድ የበታች፣ ጨካኝ፣ የማሰብ ችሎታ የሌላቸው፣ ተጠየቃዊነት በውስጣቸው የሌለ፣ ምንጊዜም የወንድ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው፣ የመምራት ብቃት የሌላቸው ደካማ ፍጡሮች ተደርገው ነው፡፡ ይሁንና ሴቶች ከወንዶች ተሽለው የሚገኙባቸውን አጋጣሚዎች የሚያሳዩ ተረኮችን አልተመለከቱም፡፡ በጅማ ኦሮሞ ተረት ውስጥ ይሄ የለም ለማለትም አያስደፍርም፡፡ ሁለተኛም  የJones እና የ Abreham ማጠቃለያ የተለያየ ነው፡፡ Jones የገለጹት ሃሳብ ሴቶች በፖለቲካውም በኢኮኖሚውም መድረክ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ሲሆን በ Abreham ጥናት ግን በተቃራኒው ተስለዋል፡፡ ይህንን የሃሳብ ልዩነት Abreham በሰበሰቧቸው ተረቶች ለማረጋገጥ ሙከራ አላደረጉም፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢ ግን ከመስክ በሰበሰባቸው እና ባነበባቸው ተረቶቸ ውስጥ የሴቶችን ብልህነትና ከወንድ መሻላቸውን የሚያመላክቱ አግኝቷል፡፡ Abreham ምናልባት የጥናታቸው ወርድና ቁመት ገድቧቸው ከአንድ አቅጣጫ (ሴቶችን ለመጨቆን በሚል ተነጣጥረው በተነገሩት ላይ ብቻ) እንዲመለከቱት አድርጓቸው ሊሆን ይችላል፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት እንዲህ ዓይነቱን ክፍተት ይሞላል በሚል እምነት ተሰርቷል፡፡ በተጨማሪም ስለ ሥርዓተ ጾታ ሲነሳ በሴቶች ላይ ብቻ ተወስኖ ሳይሆን ከወንዱም አንጻር ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

ሌላው ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበው ጥናት የAhmed (2010) ነው፡፡ Ahmed በጥናታቸው ያሳዩት የአርሲ ኦሮሞ ሴቶች በተረቶች፣ በባህላዊ ዘፈን ግጥሞች እና በምሳሌያዊ አነጋገሮች ውስጥ የተሰጣቸውን ገጽታ ነው፡፡ ጥናቱ የሴቶች አዎንታዊ እና አሉታዊ ገጽታዎች በሚል ተከፍሎ ተሰርቷል፡፡ ሴቶች በአዎንታ የተሳሉባቸው አጋጣሚዎች በብልሃተኛነታቸው በተለይም ለድንገተኛ ክስተቶችና ችግሮች ፈጣን መልስ በማበጀትና ለአብራኮቻቸው ክፋዮች ባላቸው ፍቅር ነው፡፡ በተቃራኒው ግን የማኅበረሰቡን ደንብ የሚጥሱ ሃፍረተ ቢሶች፣ ለባሎቻቸው የማይታመኑና ዝሙተኞች፣ በቀላሉ የሚታለሉ

ፍጡሮች፣ በእንጀራ ልጆቻቸው ላይ ግፍ የሚፈጽሙ ጨካኖች፣ ራስ ወዳዶች፣ ምቀኞች፣ የወንድ ብሎም የማኅበረሰብ የስቃይና የመከራ ምንጮች፣ ሰይጣናዊነት የተጠናወታቸው ወዘተ. ናቸው ተብለው በማኅበረሰቡ መታመኑን ትንተናው ያሳያል። Ahmed በጥናታቸው የገለጹት ሴቶች በአዎንታም ሆነ በአሉታ ቢገለጹም የሁሉም ዓላማ ሴቶችን በወንዶች ስር የማድረግ፣ የመቆጣጠርና የመምራት ፍላጎት መኖሩን ነው። በዚህ ረገድ ሲታይ የ Ahmed ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው። ሆኖም ጥናቱ በተረቶች ውስጥ የተንጸባረቁት የማኅበረሰቡ ፍላጎቶች በሴቶች ላይ ያሳደሩትን ተጽዕኖ እና በተነገሩት ውስጥ ያልተነገሩትን የሴቶችን ብቃት ለማሳየት አልሞከሩም። ከዚህም በላይ የሴቶችን አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች ከወንዶች ጋር አነጻጽረው (የጥናቱ ርዕስ ገድቧቸው ሊሆን ይችላል) ያሉበትን ደረጃ ለመዳሰስ አልጣሩም። በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን አስተሳሰብ እንዳለ ማቅረብ እንጂ የአጥኚው ሂሳዊነትም አይታይም። ስለዚህ ይህ ጥናት Ahmed ያልተመለከቷቸውን ጨምሮ ስለሚያሳይ በይዘቱ ይለያል።

ከዚህ ጥናት ጋር ቅርበት ያላቸው በተረት ላይ የተሰሩ ሁለት የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ለማግኘት ተችሏል። እነዚህም በ Desta (2015) እና በ Berhanu (2015) የተሰሩ ናቸው። በ Desta (2015) የተካሄደው ጥናት በቱለማ ኦሮሞ ቃላዊ ትረካዎች ግልጋሎት ላይ የተደረገ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ የቱለማ ኦሮሞ ቃላዊ ተረኮች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚሰጡትን ትምህርታዊ፣ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ግልጋሎት ማሳየት ነው። በትምህርት በኩል ህጻናት ተረቶችን በጉጉት ስለሚያዳምጧቸውና መልሰው ስለሚተርኳቸው ለቋንቋ ችሎታቸው አስተዋጽኦ እንዳላቸው፣ ብሎም ተረቶች አካባቢን በማስተዋወቅ ረገድ ሚና ስላላቸው የማስተማር ግልጋሎት መስጠታቸው በጥናቱ ተወስቷል።

በባህላዊ ግልጋሎትም ረገድ ሲታዩ የቱለማ ኦሮሞ ተረቶች የማኅበረሰቡን የቆየ ባህል የተሸከሙ በመሆናቸው ልጆች እነሱን እየሰሙ ሲያድጉ በማኅበሩ ውስጥ ሲኖሩ እንደየ እድሜ ክልላቸው ማድረግ የሚጠበቅባቸውን ድርጊቶችና ማክበር ያለባቸውን ማኅበራዊ ደንቦች በማስተዋወቅና በማስረጽ ረገድ እንደሚያገለግሉ አጥኚው ገልጸዋል። ይህንንም ከጋብቻ ሥርዓት፣ ከግጭት አፈታት ሥርዓት እንዲሁም መከበር ካለባቸው ደንቦች ጋር እያስተያዩና በተረቶች እያዋዙ አቅርበዋል። ይህንን ማወቅ ለማኅበራዊነት ጥቅም እንዳለው አሳይተዋል።

ከሃይማኖት አንጻር በተለይም ከ Waaqaa እምነት ጋር በተያያዘ ሚቶች ለእምነቱ መጠንከርና ለቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ ያላቸውን ከፍተኛ አስተዋጽኦ አጥኚው አሳይተዋል፡፡ በዚህም የእምነቱን ተጠየቃዊነት ለማስረጽና ተከታዩ ትውልድ እምነቱን እንዲቀበል ያላቸውን ሚና አሳይተዋል፡፡

የ Desta (2015) ጥናት ከነዚህ ይዘቶቹ አንጻር ሲታይ ከዚህ ጥናት (በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች) ጋር ሲተያይ በይዘቱ ግንኙነት የለውም፡፡ Desta “Myths in Gender related issues” በሚል አነስተኛ ዳሰሳ ያደረጉበት ክፍል ግን ከዚህ ጥናት ጋር መጠነኛ ግንኙነት ይታይበታል፡፡ አጥኚው በዚህ ክፍል ማሳየት የቻሉት ሄዋን የ Waaqaa ን ትዕዛዝ በመተላለፏ ለሰው ልጅ ሁሉ መከራ እንዳመጣች መታመኑን ነው፡፡ በዚያም ላይ (በተረት አጣቅሰው ባያብራሩትም) ሴት እምነት የማይጣልባትና ታዛዥነት የጎደላት ናት ተብሎ መታመኑን ገልጸዋል፡፡ ይህም በማኅበረሰቡ ዝቅተኛ ግምት የተሰጣት መሆኑን ያሳያል፡፡ በዚህ ረገድ ሲታይ የ Desta ጥናትና ይህ ጥናት መጠነኛ ግንኙነት አላቸው፡፡ ሆኖም Desta እንደሌሎች አጥኝዎች ሁሉ የወንድ አወንታዊ ገጽታና የሴት አሉታዊ ገጽታ በወንድና በሴት መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት መዋቅራዊ እንዳደረገው፣ ለወንድ የበላይነት እንዴት ምክንያት እንደሆነ አስተሳስረው አላጠኑትም፡፡ በመሆኑም Desta ያላዩትን አቅጣጫ ይህ ጥናት በስፋት ስለሚያሳይ የተለየ ያደርገዋል፡፡

ለሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበው ሌላው ጥናት የ Birhanu (2015) ነው፡፡ ጥናቱ በመጫ ኦሮሞ ቃላዊ ጥበቦች[42] ውስጥ የተገለጹትን ሥርዓተ ጾታዊ ሚና እና ማኅበረሰቡ ስለሴቶች ያለውን አስተሳሰብ ከእንስታውያን ፊለግ አንጻር ተንትኖ ለማሳየት የጣረ ነው፡፡ የጥናቱ ትንተና ክፍል በሁለት አቢይ ርዕስ ነገሮች ተከፍሎ የተሰራ ነው፡፡ እነዚህም ቃላዊ ጥበቦቹ ለሥርዓተ ጾታዊ ሚና (gender role) ያላቸው አስተዋጽኦ እንዲሁም የመጫ ኦሮሞ ማኅበረሰብ በቃላዊ ጥበቡ ከሴቶችና ከወንዶች የሚጠበቁ ባህሪያት ያላቸውን በማንሳት ሰፊ ትንተና የተካሄደበት ክፍል ናቸው፡፡ በተለይ ሁለተኛው ክፍል የሴቶችና የወንዶች ባህሪያት እየተነጻጸሩ የቀረቡበት ክፍል ነው፡፡ በዚህ ትንተናቸው ሴቶችና ወንዶች በቤትም ውስጥ ይሁን በህዝባዊ ማዕከላት የተለያየ ቦታ ያላቸው መሆኑን አስረግጠዋል፡፡

---

[42] ቃለዊ ጥበብ የተባሉት ተረትና ምሳሌያዊ አነጋገሮች ናቸው፡፡ አጥኚውም ትኩረት አድርገው የሰሩት በነዚሁ ላይ ነው፡፡

Birhanu (2015) በጥናታቸው ለሴትና ለወንድ የተሰጠው ገጽታ የልዩነታቸው ማሳያ ተደርጎ መወሰዱን ጠቁመዋል፡፡ ሴቶች ጨካኞች፣ የማይታመኑ፣ ሂያጆች (ዝሙተኞች)፣ ለወንድ አደገኞች፣ የመታዘዝ እንጂ የማዘዝ ተፈጥሮ የሌላቸው፣ ንፉጎች፣ በስሜት የሚነዱ እና ለሃላፊነት የሚያበቃ አካለዊና አዕምሯዊ ብቃት የሌላቸው እንደሆኑ ተደርጎ በማኅበረሰቡ መታመኑን አጥኚው በትንተናቸው ጠቁመዋል፡፡ ሴቶች በአወንታ የተሳሉበት አጋጣሚ ለአብራኮቻቸው ክፋዮች ካላቸው ፍቅር አንጻር ብቻ ነው፡፡ ይህ በ Ahmed (2010) ጥናት ውስጥም ተጠቅሷል፡፡ በአንጻሩ ወንድ የቤቱና የንብረቱ አዛዥና ጠባቂ፣ ለማዘዝ የሚያበቃ ተፈጥሯዊ ተሰጥዖ ያለው፣ ሃቀኛ፣ ታማኝ፣ ሃላፊነትን መወጣት የሚችል፣ ርኅሩኅ፣ ለጋስና ምክንያታዊ ነው ተብሎ መታመኑን አስረግጠዋል፡፡ በዚህም የተነሳ አባዊ ሥርዓቱ እነዚህን ባህሪያት ምክንያት አድርጎ በራሱ መዋቅር ውስጥ ሴቶችን ላለማስገባት እንደምክንያት መጠቀሙን አብራርተዋል፡፡

በዚህ ረገድ የBirhanu ጥናትና ይህ ጥናት ቀደም ብለን ከተመለከትናቸው ጥናቶች በበለጠ የቅርብ መመሳሰል ይታይባቸዋል፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጥናት እንደ Birhanu ጥናት ማህበረሰቡ የሚለውን ብቻ በማስፈር የተጠናቀቀ አይደለም፡፡ አንደኛ አባዊው ሥርዓት ሴቶችን እንደ አንድ ማኅበራዊ ቡድን በስሩ ለማድረግ የተጠቀማባቸውን ስልቶች በመልክ በመልክ አደራጅቶ ለመዳሰስ ጥሯል፡፡ ሁለተኛ ስለሴቶች በአሉታ በተነገሩት ተረቶች ላይ ሃቲታዊ ትንተና በማድረግ አወንታዊ ገጽታዎችን ለማሳየት ጥሯል፡፡ በተነገሩት ውስጥ ያልተነገሩትን ጉዳዮች ከባህላዊ እንስታውያን ፈለግ አንጻር እንደገና ተመልክቶ የሴቶችን ብርታት አሳይቷል፡፡ በነዚህ ሁለት ነጥቦች ምክንያት ይህ ጥናት ከ Birhanu ጥናት ይለያል፡፡

በጠቅላላው በመጀመሪያ ዲግሪ ጥናቶች አጥኚዎች በዘረዘሯቸው በርካታ ይዘቶች ውስጥ የሴቶችን ጭካኔ ከእንጀራ እናት ጋር ብቻ አያይዘው አንስተዋል፡፡ ይህም ከአሉታዊ ገጽታቸው አንጻር ብቻ የታየ ነው፡፡ ከአጥኚዎቹ ውስጥ የሴቶችን አወንታዊ ገጽታ በማንሳት ያጠናው ሰውነት (1984) ብቻ ነው፡፡

ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩ ጥናቶችን ስንመለከት ደግሞ Abdulkadir (1982)፣ እና Melakineh (1990) ጭብጣዊ ትንተና፣ Yihenew (1996) እና Sahilu (2002) ንጽጽራዊና አውዳዊ ትንተና እና Abreham (2007) የትረካው ዓላማ በተለይ ማኅበራዊ ፋይዳዎች ላይ አተኩረዋል፡፡ Sahilu (2002)፣ Abreham (2007)፣ እና Yihenew

(1996) በተረቶች ውስጥ ወንዶችና ሴቶች እንደምን እንደተሳሉ ለማሳየት ጥረት አላደረጉም፡፡ ከእነርሱ በተሻለ Abdulkadir (1982) በተለይ የሴቶችን ከወንዶች ጋር እኩል አለመሆን በሚያሳዩት ተረቶች ላይ አተኩረው አጥንተዋል፡፡ ከእነሱ በተለየ መንገድ ደግሞ ለማ (1999) እና Ahmed (2010) ወንዶችንም ሴቶችንም አካትተው በመስራታቸው ከዚህ ጥናት ጋር የበለጠ ቅርበት አላቸው፡፡

አብዛኞቹ ጥናቶች በሰበሰቧቸው ተረቶች ላይ አካባቢያዊ ምደባ ካደረጉ በኋላ የይዘት ትንተና ሰጥተዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለትንተናቸው የሚያገለግሏቸውን ተረቶች ያገኟቸው ለጥናት በመረጧቸው አካባቢዎች በመሄድ አንዳንዶቹ በቃለመጠይቅ ብቻ አንዳንዶቹ ደግሞ በቃለመጠይቅና "አውዱ ላይ በመገኘት" በምልከታ ነው፡፡ በሁሉም አጥኚዎች ስራ ውስጥ የታየው ያገኟቸውን ተረቶች ሁሉ በይዘታቸው በመከፋፈል ትንተና ማድረግ ነው፡፡ አንድን ርዕሰ ጉዳይ ለይቶ ሰፊ ጥናት ለማድረግ ከለማ (1999)፣ ከ Ahmed (2010) እና ከ Abreham (2007) በስተቀር ሌላ አላጋጠመም፡፡ ሌላው ቀደም ብለው በተለያዩ የተረት ሰብሳቢዎች ተሰባስበው ለህትመት የበቁትን ተረቶች አሁን እየተነገሩ ካሉት ጋር አጣምሮ ለማጥናት የሞከረም አጥኚ አልተገኘም፡፡

ለሦስተኛ ዲግሪ የተሰሩ ጥናቶች ከሁለተኛ ዲግሪ ጥናቶች በበለጠ ከዚህ ጥናት ጋር የጎላ ተመሳሳይነት ታይቶባቸዋል፡፡አጥኚዎቹ በተነገሩት ተረቶች ውስጥ የሚስተዋለውን የማኅበረሰቡን እምነትና የተረቶችን የመነገር ምክንያት በቀጥታ በመተንተን ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ተረቶቹን እንደገና በመመርመር በግልባጫቸው ያላቸውን ትርጉም በሃቲት አላሳዩም፡፡ በዚያም ላይ አባዊ ሥርዓቱ ተረቶችን መነሻ አድርጎ ሴቶችን ለመቆጣጠርና ከሥልጣን ለማራቅ የተጠቀማባቸውን ስልቶች አላነሷቸውም፡፡ ይህ ጥናት ከሁለቱ ጥናቶች ጋር ተመሳሳይነት ያለውን ያህል ልዩነትም ስላለው በዚሁ መንገድ ተጠንቷል፡፡ የእነሱንም ክፍተት ይሞላል በሚል እምነት ተሰርቷል፡፡

የቀደሙት ጥናቶች ይህ ጥናት የራሱን ፈር እንዲይዝ አመላካች ሃሳቦች ተገኝቶባቸዋል፡፡ የሁለተኛና የሦስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በአብዛኛው የተሰሩት ከግልጋሎታዊ ንድፈሃሳብ (Functional theory) አንጻር ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የዚህ ጥናት አቅራቢ ተረቶች በማኅበረሰቡ ውስጥ የሚሰጡትን ግልጋሎት ተረድቶባቸዋል፡፡ በተጨማሪም በነዚሁ ጥናቶች ውስጥ (አጥኚዎቹ በግልጽ ባያስቀምጡትም) ማኅበረሰቡ በታወቀ ማዕቀፍ ውስጥ እንዴት ራሱን እንዳስቀመጠ ተገንዝቦባቸዋል፡፡ በግልጽ የተቀመጠው የተረቶች ግልጋሎት እና በግልጽ ያልተጠራው ተረቶች የገለጹት መዋቅር

በጥምረት መዋቅራዊ ግልጋታዊ ንድፈሃሳብን ለመጠቀም ፈር ቀዳጅ ሃሳብ ተገኝቶባቸዋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አጥኝው አስቦ ለተነሳው የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብር ማሳያ ተረቶችንና ሃሳቦችን አግኝቶባቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ የወንዶችን እና የሴቶችን ገጽታ በንጽጽር መመልከት የሥርዓተ ጾታን እና የስልጣንን ጉዳይ ለመረዳት እንደሚያስችል ግንዛቤ ተገኝቶባቸዋል፡፡

ሆኖም ግን "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች" በሚል የተሰራው ይህ ጥናት ከቀደሙት ጥናቶች በተለየ መልኩ የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን ኢፍትሃዊ መስተጋብር በተለይ አተኩሮ ስለሚመለከት፣ ከመስክ ከተሰበሰቡ መረጃዎች በተጨማሪ የተጻፉ ተረቶችንም ስለሚያጠና እና የሴቶችን ገጽታ ያዛባሉ የሚባሉ ተረኮችን ከእንስታውያን ፈለግ አንጻር እንደገና ሃቲት በመስጠት የሴቶችን በጎ ገጽታ ለማሳየት የጣረ በመሆኑ ጥናቱ በዓይነቱ የተለየ ነው፡፡ የቀደሙት ጥናቶችም ይህ ክፍተት ያለባቸው በመሆን ያንን ክፍተታቸውን ሊሞላ ይችላል ተብሎ የተሰራ ነው፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች ትንተና

በተረቶች ውስጥ በስፋት የሚታዩት ገጸባህሪያት ሰዎች፣ እንስሳት፣ የሰው ባህሪ የሌላቸው ፍጥረታት፣ ወዘተ. ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ገጸባህሪያቱ የመጨረሻ ግባቸው ሰው ነው፡፡ ጥረታቸው ሁሉ ይህ ዓለም አንድ መልክ ኖሮት ከመዋቅሩ ዝንፍ ሳይል ቀድሞ በተሰራው መንገድ በሠላም እንዲሄድ ማድረግ ነው፡፡ ጥረቱ ሁሉ መጥፎም ይሁን በጎ ባህላዊና ማኅበራዊ እሴቶች እንዳይናጉ ማድረግ ነው፡፡

በዚህ ሂደት ውስጥ የሚሳሉት ገጸባህሪያት በህገ ተቃርኖ (Binary opposition) የተጣመዱ ናቸው፡፡ በተረት ውስጥ የምናገኛቸው ገጸባህሪያት ባብዛኛው ሁለት ሆነው የተሰጣቸው ባህሪ የደካማና የብርቱ፣ የንፉግና የለጋስ፣ የጨካኝና የሩህሩህ፣ የባለጸጋና የድሃ፣ የአለቃና የምንዝር፣ የብልጥና የሞኝ፣ የታማኝና የከሃዲ ወዘተ. ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ከመስክና ከቤተመዛግብት የተሰበሰቡት ተረቶች በተለይም ገጸባህሪዎቻቸው ሴትና ወንድ የሆኑት በአብዛኛው ከላይ በተጠቀሱት ባህሪያት ተቀርጸው እናገኛቸዋለን፡፡ ተረቶቹ በስፋት እንደሚያሳዩት በጎ በጎ የሆኑት ባህሪያት እንደ ብርቱ፣ ለጋስ፣ ርህሩህ፣ አዛዥ፣ ታማኝ ወዘተ. ያሉት ለወንድ፣ ከእነዚህ በተቃራኒው ያሉት ደግሞ ለሴት ተደርገው ቀርበዋል፡፡ አንዳንዶቹ ባህሪያት ባህሉ ጾታን መሰረት አድርጎ ከሰጣቸው ማኅበራዊ ሚና (Social role)፣ አንዳንዶቹ ደግሞ የሥነህይወታዊ አፈጣጠር ልዩነትን (Biological difference) መሰረት ካደረጉ አስተሳሰቦች የመነጩ ይመስላሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ አባዊው ዓለም ለራሱ በማድላት ደግ ደግ የሚላቸውን ለወንድ፣ እኩይ የሚላቸውን ለሴት የሰጠ ይመስላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ምደባ ሥርዓታዊ ነው እስከሚባል ድረስ የኃይል ሚዛኑን ወደ ወንድ ያደላ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህ ደግሞ ሙሉ በሙሉ ሥርዓተ ጾታዊ ነው፡፡ ይህ በማኅበረሰቡ እያንዳንዱ ድርጊያ ውስጥ ሰርጾ በመግባት ልዩነትን ፈጥሯል፡፡ Lazar ይህንኑ ሲያስረግጡ ሥርዓተ ጾታዊ ባህሪ ያላቸው ማህበረሰባዊ ድርጊያዎች (social practices) በሁለት ዓይነት መንገድ ህያው ሆነዋል ይላሉ (2007፡145)፡፡ አንደኛ የሴቶችንና የወንዶችን ባህሪና ማንነት በመተንተንና በጽንፍ እንዲተያዩ በማድረግ በሴትና በወንድ መካከል ተባለጣዊ መዋቅር የመስራት፤

ሁለተኛ በሌሎች ማኅበረሰባዊ ግንኙነቶች እና እንቅስቃሴዎች ውስጥ በመግባት ሚና የመስጠትን ተግባር ተወጥቷል ሲሉ ያስረግጣሉ፡፡

ይህንኑ ማየት ይቻል ዘንድ በቅድሚያ ሴቶችና ወንዶች በተረቶች ውስጥ ምን ዓይነት ሰብዕና እንደተሰጣቸው፣ ሰብዕናው ለልዩነት እንዴት ምክንያት እንደሆነ እና ሥልጣን ለመያዝ እንዴት እንዳስቻለ እንመልከት፡፡

## 5.1 የሥርዓተ ጾታ እና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብር በሴቶችና በወንዶች ገጽታ

በዚህ ስር ለማሳየት የተሞከረው በተረቶች ውስጥ የሥርዓተ ጾታ አድልዎ መኖሩ እና ይህም አድልዎ በሥልጣን አያያዝ ላይ ተጽዕኖ ማሳደሩን ነው፡፡ ይህንንም ማሳየት ይቻል ዘንድ የሴቶችና የወንዶች ገጽታ ጎን ለጎን በንጽጽር ቀርቧል፡፡ ምክንያቱም የሴቶችና የወንዶች ገጽታ በህገ ተቃርኖ የተጣመዱ ናቸውና (እንደ መዋቅራዊ ንድፈ ሃሳብ አቀንቃኞች) ለየብቻ የሚታይ አይደለም፡፡ በአንድ ተረት ውስጥ የአንዳቸው አወንታዊ ገጽታ በሌላኛው ስሃ ይደምቃል፡፡ በመሆኑም ሴቶችና ወንዶች የቀረቡባቸው ገጽታዎች በየመልኩ በንጽጽር ቀርበዋል፡፡

### 5.1.1 ብልህነት እና ሞኝነት

ብልሃት እውቀት፣ ጥበብ፣ ዘዴ በሚል ይተረጎማል (ኢቋጥምማ[43] 1993፡244)፡፡ ይሄው መዝገበ ቃል በተመሳሳይ ገጽ የዚሁ (ብልሃት) ባለቤት የሆነን ሰው ጥበበኛ፣ ዘዴኛ፣ አዋቂ፣ አስተዋይ ሲል ይፈታዋል፡፡ በሌላ በኩል የዚህን ቃል ተቃራኒ የሆነውን “ሞኝ”ን ይሄው መዝገበ ቃል (ገጽ 86) የዋህ፣ ገር፣ በቀላሉ የሚታለል በሚል ይበይነዋል፡፡ ቃሎቹ በዚሁ ትርጉማቸው በጥናቱ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

በአብዛኞቹ ተረቶች ውስጥ ብልህነት ከሴት፣ ሞኝነት ከወንድ ጋር ተያይዘዋል፡፡ ሴቶች አዋቂዎች፣ ባለፈጣን አዕምሮ፣ ከገጠማቸው ችግር በፍጥነት የሚወጡ፣ የነገሮችን ምስጢር ፈጥነው የሚገነዘቡ ተደርገው ተስለዋል፡፡ በአንጻሩ ወንዶች ግን ተታላይ፣ በራሳቸው መፍትሄ የማያመነጩ፣ ገራገር ወዘተ. በሚል ተገልጿል፡፡ ለምሳሌ ተረት 9ን እንመልከት፡፡

[43] የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል

*አንድ ግዶ የለሽ ንጉሥ አንድ ገበሬ ያገኝና እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል፡፡ "ወዲያ ወዲህ ማለት የለም! ለምጠይቅህ ጥያቄ ቀጥ ያለ መልስ ትሰጠኛለህ:: . . . "በሰማዩ ላይ ስንት ኮኮቦች አሉ?" . . . "ለመሆኑ የመሬት መሃል የት ነው?" በማለት ይጠይቀዋል፡፡ ገበሬውም "ጌታዬ አላውቀውም! ይህንንም የነገረኝ የለም" ሲል ይመልሳል፡፡ ንጉሡ ይህን ጊዜ ተናድዶ "የዚህን መልስ ነገ ካላመጣህ በህዝብ ፊት ትሰቀላለህ" ብሎ ያሰናብተዋል፡፡*

*ገበሬው በዚህ እጅግ አዝኖ ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ . . . ይህንን ጊዜ ገበሬው ለሚስቱ "ወደቤቴ ስመጣ ንጉሡን መንገድ ላይ አገኘኋቸው፡፡ . . . "በሰማይ ላይ ያሉት ከዋክብት ስንት ናቸው? የምድር መሃሉስ የት ላይ ነው?" ብለው ጠየቁኝ፡፡ . . . እሷም ነገሩን አቅልላ "ላንተ ሁልጊዜ ሁሉ ነገር ከባድ ነው፡፡ በል ታጠብና እራታችንን እንብላ" ትለዋለች፡፡ እሱም "አይ አልበላም፡፡ ጾሜን አድሬ ፈጣሪዬን ስለምን አድራለሁ" ይላል፡፡*

*እሷም "አትጨነቅ፡፡ አሁን ታጠብና እራታችንን እንብላ፡፡ መልሱን ጧት እነግርሃለሁ" ትለዋለች፡፡ ከዚያም እራታቸውን በልተው በሰላም ያድራሉ፡፡ ሲነጋ "በይ መልሱን ንገሪኝ" ይላታል፡፡ እሷም አንድ አቅማዳ ሙሉ ጤፍ ታመጣና ትሰጠዋለች፤ ጦሩንም ታስይዘዋለች፡፡ አስከትላም "የሰማይ ከዋክብት ስንት ናቸው ብሎ ሲጠይቅህ እዚህ አቅማዳ ውስጥ ባለው ጤፍ ልክ ነው በለው፡፡ የመሬትን መካከል ሲጠይቅህ ጦርህን ፊት ለፊቱ ቸክለህ ይሄ ነው በለው፡፡ ከተጠራጠረህ ቆጥረህና ለክተህ አረጋግጠው በለው" ትለዋለች፡፡ . . . ንጉሡ የገበሬውን እውቀት አድንቀው ሸልመው አሰናበቱት ይባላል (ተረት 9)፡፡*

በተረቱ ውስጥ እንደምናስተውለው አንድ ጥጋበኛ ንጉሥ ምስኪኑን ገበሬ የሰማይ ከዋክብትን ብዛትና የመሬት መሃል ካላወቅክ በህዝብ ፊት እሰቅልሃለሁ ባለውና በተጨነቀ ጊዜ ነብሱን የታደገችው ሚስቱ ናት፡፡ እንዲያውም ጥያቄውን በጣም አቅልላ "ላንተ ሁልጊዜ ሁሉ ነገር ከባድ ነው" ስትል የብልህነቷን ከፍታ ራሷ ታረጋግጣለች፡፡ ገበሬው ለንጉሡ፣ የከዋክብቱ ብዛት በዚህ አቅማዳ ውስጥ ባለው ጤፍ ልክ ነው፤ የመሬት መሃሉም ይሄ ነው፤ ካላመኑኝ ቆጥረውና ለክተው ያረጋግጡ ባላቸው ጊዜ እውቀቱን አድንቀው ሸልመውታል፡፡

በዚህ ተረት ውስጥ ተያያዥ ነገሮችን እናስተውላለን፡፡ አንደኛ ንጉሱ የማይጠየቅና መልስ የሌለው ጥያቄ አቅርበዋል፡፡ ምናልባት ዓላማቸው አዋቂ ለመሰኘት፣ ለመደነቅና ልዕልናቸውን ለማሳየት፤ በዚህም ገበሬው አላዋቂነቱን ተረድቶ የተገዢነት መጠኑን ከፍ እንዲያደርግ ሊሆን ይችላል፡፡ ሁለተኛ የገበሬው ሚስት መልስ ለሌለው እና ለማይጠየቀው ጥያቄ ማረጋገጫ የማይገኝለት እና ለማመሳከር የማይቻል መልስ አቅርባለች፡፡ ክፉን በክፉ መልሳለች፡፡ በዚህ ብቃት ሴቷ ከባሏ መብለጥ ብቻ ሳይሆን ከንጉሡም ተገዳድራለች፤ አሸንፋቸዋለች፡፡ ብቃቷ የሚጎላው ደግሞ ባሏ ውሎ ያደረበትን፣ ያስተከዘውን፣ ያስጨነቀውንና እራት እስካለመብላት ያደረሰውን ጥያቄ

ሳታወጣና ሳታወርድ እንደዋዛ በቀላሉ መልስ ማግኘት በመቻሏ ነው፡፡ የንጉሡም ሽልማት የመስጠት ምክንያቱ ይሄው ነው፡፡

ተረቱ ንጉሡንና ገበሬውን ባንድ በኩል፣ የገበሬውን ሚስት በሌላ በኩል ከፍለን እንድንመለከታቸው የሚያደርግ ነጥብም አለው፡፡ ንጉሡ ጥያቄውን ሲያቀርቡ ማንም አይመልሰውም በሚል እርግጠኛ መንፈስ ነው፡፡ ገበሬውም ለተጠየቀው መልሱን ማግኘት እንደማይቻል ያመነ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ለጥያቄው መልስ ማቅረብ እንደማይችል አምኖ ግን በዚሁ ጣጣ ህይወቱን እንዳያጣ ፈጣሪውን ሲለምን ለማደር ሲያስብ እናስተውላለን፡፡ ሚስቱ "እራታችንን እንብላ" ባለችው ጊዜ "አይ አልበላም፤ ጾሜን አድሬ ፈጣሪዬን ስለምን አድራለሁ" ሲል ይደመጣል፡፡ ፈጣሪውንም የመለመኑ ዓላማ መልስ እንዲነግረው ሳይሆን በምህረቱ ነብሱን እንዲታደግለት ነው፡፡ በመሆኑም ሁለቱ ወንዶች (ንጉሡና ገበሬው) ጥያቄው መልስ የለውም በሚለው መንፈሳቸው ባንድ ላይ ሊመደቡ የሚችሉ ናቸው፡፡ ይህም አንድምታው (ከሴቷ ጋር ሲነጻጸር) ከብልህ የሚያስመድብ አይደለም፡፡ በአንጻሩ ሴቷ በጥያቄው መልስ ዙሪያ ያላት ግምት የተለየ ነው፡፡ ጥያቄው መልስ ባይኖረውም እንኳን የመረታት፣ የመሸነፍ መንፈስ አይታይባትም፡፡ የጠያቂውን ፍላጎት (መንፈስ) ተረድታ ተገቢ ነው ያለችውን መልስ ሰጥታለች፡፡ ይህንን ስታደርግ እንደባሏ ፍጹም የመረበሽ ስሜት የላትም፡፡ እንዲያውም ተራኪው "እሷም ነገሩን አቅልላ . . ." ሲል ይነግረናል፡፡ ከእርሷም አንደበት የሚሰማው "ላንተ ሁልጊዜ ሁሉ ነገር ከባድ ነው" ስትል ነው፡፡ ጥያቄውን አቅልላ መመልከቷ ብቻ ሳይሆን ተገቢ ላልሆነው ጥያቄ ተገቢ መልስ በማቅረቧ ከሁለቱ ወንዶች ፍጹም ተለይታለች፡፡ ይህም ብልህነቷን ያሳያል፡፡

በፈተና ረገድ የአንድን ጥያቄ መልስ ከመላሹ ይልቅ ጠያቂው ያውቀዋል ተብሎ ይገመታል፡፡ ከላይ በቀረበው ተረት ውስጥ የተገለጸውን ጥያቄ መልስ ግን ንጉሡ እንደማያውቁት ሴቷ ግምት ያሳደረች ይመስላል፡፡ ምክንያቱም ባሏን መልስ አስይዛ ስትልከው በመጨረሻ "ከተጠራጠረህ ቆጥረህና ለክተህ አረጋግጠው በለው" ብላዋለች፡፡ ንጉሡ መልሱን ያውቁታል የሚል እምነት ቢያድርባት ኖሮ ይህንን ሃሳብ አትሰነዝርም ነበር፡፡ ይህንንም ያደረገችበት ምክንያት እንዳላት እንረዳለን፡፡ ንጉሡ የጥያቄውን መልስ ካለማወቃቸው የተነሳ መልስ ተብሎ የቀረበላቸውን ለማረጋገጥ በሚያደርጉት ጥረት ባሏ በተጨማሪ ጥያቄ እንዳይወጠር እንደ መከላከያ ተጠቅማበታለች፡፡ አባባሉ (ከተጠራጠረህ ቆጥረህና ለክተህ አረጋግጠው) "እኔ መልስ ያልኩትን አቅርቤያለሁ፤ አይ ካልክ እራስህ

ድረስበት እንጂ ዳግመኛ አልጠየቅም" የሚል መልዕክት አለው፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከብልህ ካልሆነ ከማን ሊመነጭ ይችላል?

ተረት 92 ከተረት 9 ጋር ተመሳሳይ ሆኖ ነገር ግን ወደ መጨረሻ ባለው ተጨማሪ ታሪክ የሴትን ሌላ ብልህነት እናስተውልበታለን፡፡ ባል ሚስቱ የነገረችውን የጥያቄውን መልስ ለመኮንኑ ባቀረበ ጊዜ መኮንኑ መልሱን ማን እንደነገረው አጥብቀው ይይዙታል፡፡ ባል ሚስቱ እንደነገረችው ያስረዳል፡፡ በዚህ ጊዜ መኮንኑ ሴትዮዋ ለገበሬው እንደማትገባ ነግረው ራሱ ደግሶ እንድድርላቸው ያዝዙታል፡፡ ይህንኑ ገበሬው ለሚስቱ ይነግራል፡፡ የሴቷ ብልህነት የሚመጣው እዚህ ላይ ነው፡፡ ይህንን የተረቱን የመጨረሻ ክፍል አቅርበን እንመልከተው፡፡

> *. . . . እሱም [ባል] ከፊተኛው የበለጠ ድንጋጤ ወደቀበትና ወደቤቱ ሄዶ እህልም አልበላ፣ ውሃም አልጠጣ፣ አልተኛምም በማለት በአሳብ ባህር ገብቶ ይዋኝ ጀመር፡፡ ሚስቱም "ደግሞ ዛሬ ምን አገኘህና ነው አሳብ ገብቶ የሚወዘውዝህ" አለችው፡፡ እሱም መኮንኑ እንደነገረው አድርጎ ነገራት፡፡ እሷም ብልህነት ያደረባት ሴት ናትና "ይህስ ትንሽ ጉዳይ ነው፡፡ ይምጡና ይውሰዷት በላቸው፡፡ . . . ለድግሱም ብዙ ድስት ሰበሰበችና በሁሉም ተልባ በጠበጠችበት፡፡ በመጀመሪያው ድስት የወርቅ ሙካሽ፣ ቀጥሎም የሃር፣ የከፋይ፣ የሹት፣ ማንሰሻ እስከለበሰው ድረስ አልብሳ አቀረበች፡፡ መኮንኑም ባለበት አዳራሽ ድስቱ ሁሉ ቀረበና የመጀመሪያው የወርቅ ሙካሽ የለበሰው ቢገለጥ በውስጡ ያለው ተልባ ሆነ፡፡ ሁሉንም መደዳውን ያለውን ቢከፍቱት እንደዚያው ተልባ ሆነ፡፡ በዚህ ጊዜ መስፍኑ ተቆጣና "ምንድን ነው ይሄ ነገር?" ሲል ጠየቀ፡፡*
>
> *ያቺም ሴት ወደዚያው ከባሏ ጋር ሆና ቀረብ አለችና "ጌታዬ ሆይ! እኛ ሴቶች የውጭ መልካችን በየዓይነቱ ቢሆን የውስጡ አካላችን የሁላችንም አንድ ዓይነት ነው፡፡ ስለዚህ የእኔን የውጭ መልክ አይተው ይህንን ባሌን በማሳዘን እግዚአብሔርን እንዳያስቀይሙት" አለችው፡፡ መስፍኑም ሴትዮይቱን በማመስገን የእርዳታ ገንዘብ ወርቅና ብር ሰጥቶ ከግፍ ስራ ታግሶ ወደነበረበት ተመለሰ . . . . (ተረት 92)፡፡*

እዚህ ላይ ገጸባህሪዋ የተጠቀመችው ዘዴ ብልህነቷን የሚያሳይ ነው፡፡ መኮንኑን ለማሸነፍ የበቃችው ራሷን ዝቅ አድርጋ ነው፡፡ በብልህነቷ (በአዋቂነቷ) ልቃ መገኘቷ እንዳስመረጣት ብታውቅም ከወጥመዱ ለመውጣት የመረጠችው ዘዴ ግን እሷ ከሌሎች ሴቶች ያልተለየች መሆኗን በማረጋገጥ ነው፡፡ ውስጠ ይዘቱ ተመሳሳይ የሆነውን ወጥ (የተልባ ብጥብጥ) የያዙትን ድስቶች በተለያዩ ጨርቆች ሸፍና ማቅረቧ ይህንን ለማስረዳት የተጠቀመችበት ስልት ነው፡፡ ስልቷ፣ ፍልስፍናዊ ከሆነው ንግግሯ (እኛ ሴቶች የውጭ መልካችን በየዓይነቱ ቢሆን የውስጡ አካላችን የሁላችንም አንድ ዓይነት ነው) ጋር አብሮ መቅረቡ ደግሞ መኮንኑ አምነው ከመቀበል ውጭ ሌላ መፈናፈኛ እንዳያገኙ ሲያደርጋቸው እንመለከታለን፡፡ ይህም ያሰቡት እንዳይሳካና ፍላጎታቸው

በሽንፈት እንዲጠናቀቅ አድርጓል፡፡ በዚህም የተነሳ የገበሬውን ሚስት ለማግባት ማሰባቸውን ከመተው አልፈው ከክፉ ስራም ታግሰዋል፡፡

በተረቱ ውስጥ የተገለጸው የሴቷ ብልጠት መኮንኑን እንዲሸነፉ ከማድረጉም በላይ በድርጊታቸው አፍረዋል፡፡ መኮንኑ አሸነፉ ልንል የምንችለው እንዳሰቡት የገበሬውን ሚስት አግብተው ወስደው ቢሆን ኖሮ ነበር፡፡ በእርግጥ መኮንኑ ሥልጣናቸውን እና ጉልበታቸውን መሰረት አድርገው የገበሬውን ሚስት ለመውሰድ ማሰባቸው ከተረት ባህሪ አንጻር ፍጻሜው እንደማያምር እናውቃለን፡፡ ምክንያቱም ተረት በባህሪው ዝቅተኛ ሰብዕና የተሰጣቸው ገጸባህሪያት በመጨረሻ ሲያሸንፉ የምናይበት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ውጤቱ የምንጠብቀው ነው፡፡ መኮንኑ ከሽንፈታቸው ባሻገር አፍረዋል የምንልበትም አጋጣሚ አለ፡፡ ለዚህም እንደመነሻ የሚሆኑን አንድም በህዝብ (ሠርገኞች) ፊት በብልሃት ከገበሬው ሚስት አንሰው መገኘታቸው፣ አንድም “ባሌን በማሳዘን እግዚአብሔርን እንዳያስቀይሙ” ስትላቸው ከፈጣሪም ጋር እየተጣሉ መሆናቸውን ስናይ ነው፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ለማፈራቸው እንደ ማስረጃ የሚሆነን ራሳቸው የሚያደርጉት ነው፡፡ ለሃፍረታቸውና ለሽንፈታቸው መሸፈኛ ሲሉ ገንዘብ፣ ወርቅ እና ብር ሰጥተዋታል፡፡ እነዚህ ስጦታዎች የሚያሳዩት የመኮንኑን ቅንነትና አድናቂነት ሳይሆን ሃፍረቱን ነው፡፡ ስጦታዎችም የተደረጉት ከብልህነት በመነጨ ስሜት ሳይሆን መደናገጥ በፈጠረው ስሜት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ የሚያሳዩን በተረቱ ውስጥ የተሳለችው ሴት ከወንዶቹ ብልህ መሆኗን ነው፡፡ ተራኪውም ስለብቃቷ “እሷም ብልህነት ያደረባት ሴት ናትና” ሲል ይመሰክርላታል፡፡

በሌሎችም ተረቶች ውስጥ ይሄው የሴት ብልህነትና የወንድን የዋህነት በግልጽ ተንጸባርቋል፡፡ ተረት 21ን ባጭሩ እንመልከት፡፡ አንድ ለልጁ ሚስት ፍለጋ የሚሄድ ሰውና ሌላ መንገደኛ ሲጓዙ በየአጋጣሚው ከሚስት ፈላጊው የሚሰነዘሩትን ቅኔያዊ አቀራረቦች ሌላኛው መተርጎም ሲያቅተው እናያለን፡፡ እንዲያውም መመለስ ሲያቅተው ድክመቱን ለመሸፈን በሚመስል መልኩ ስድብ አዘል ምላሾችን ይሰጣል፡፡ ለመረዳት ያቃቱትም ንግግሮች ዳገቱን ወይ አዝለህ አውጣኝ ወይ አዝዬ ላውጣህ፤ በመካከላቸው አውራ የሌለባቸው ብዙ ከብቶች ጥቂት ናቸው ያለው፣ በመካከላቸው አውራ ያለባቸውን ጥቂት ከብቶች ብዙ ናቸው ያለው፣ የታጠረችውን ትንሽ ጎጆ ትልቅ፣ ያልታጠረውን ትልቅ ቤት ትንሽ ያለበትንና ባለሁለት አንገት ልጃገረድ ለልጄ ሚስት ፈልግልኝ ያለው

ነበሩ፡፡ ለነዚህ አነጋገሮች አጥጋቢ ትርጉም ሲሰጥ የምናየው በግራ ተጋቢው ሴት ልጅ ነው፡፡ ይህንኑ ከተረቱ ጠቅሰን እንመልከተው፡፡

> *. . . . መንገደኛው ሰውዬ ቤቱ ከደረሰ በኋላ ለቤተሰቡ፣ "አንድ ተሳዳቢ ሰውዬ አጋጥሞኝ ሲያደርቀኝ ዋለ" ብሎ የተነጋገሩትን በሙሉ አወራላቸው፡፡ ከቤተሰቡ መካከል ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጅ ነበረችና በጥሞና አዳምጣ እንዲህ አለችው፡፡ "አንተን መስደቡ አይደለም እኮ! እንዲያውም አዋቂ ሳይሆን አይቀርም" አለችው፡፡ እንዴት ብሎ ቢጠይቃት "ዳገቱን ተሸካክመን እንውጣ ሲል እያወራን ዳገቱን ብንወጣ አይደክመንም ማለቱ ነው፡፡ ጥቂት ከብቶች አይቶ ብዙ ናቸው ሲል ኮርማዎች ስለተቀላቀሉባቸው ነገ ብዙ ይሆናሉ፤ ኮርማ የሌሉባቸው ግን ታርደው ወይ ሞተው ሊያልቁ ይችላሉ ማለቱ ነው፡፡ ግቢው ያልታጠረ ትልቅ ቤት ደግሞ ማንም ሊደፍረው ስለሚችል ክብር የለውም፡፡ ትንሽ ሆኖ ግቢው የታጠረ ጎጆ ግን በቀላሉ ስለማይደፈር ይከበራል፡፡ ስለዚህ ትልቅ ነው ሲል ይህንን ማለቱ ነው፡፡ ባለ ሁለት አንገት ልጃገረድ ማለቱ ክብረ ንጽህናዋ ያልተደፈረች ልጅ ማለቱ ነውና ከመጣ እኔኑ ለልጁ ዳርለት" . . . . (ተረት 21)*

አባት ከሴት ልጁ በእድሜ፣ በህይወት ልምድ፣ ሰፋ ባለ ማኅበራዊ ገጠመኝ ይበልጣሉ፡፡ ይሁንና ከቀረቡለት አመስጥሯዊ ንግግሮች ውስጥ አንዳቸውንም መፍታት አልቻሉም፡፡ በብልህነት ከእርሳቸው ሴት ልጃቸው በልጣለች፡፡ እዚህ ላይ ተረቱ ሊያስርጽ የፈለገው ምንድን ነው? በአብዛኛው ሲታይ ስለሴቶችና ስለወንዶች ምን ይነግረናል? ብሎ መጠየቅ ያስፈልጋል፡፡ መልሱንም ለማግኘት ተረቱን መፈከር ይገባል፡፡

በብዙ ባህሎች ውስጥ እንደሚታየው አባት ለልጁ ሚስት ለማጨት ሲነሳ ይሆናሉ ባላቸው ልጃገረዶች ዙሪያ በራሱ መለኪያ የራሱን ማጣራት ያደርጋል፡፡ በተረት 21 ውስጥ የተደረገው ይሄው ይመስላል፡፡ የልጅቷን ብልህነት ለማወቅ ያዋጣኛል ያለውን ቅኔያዊ ጥያቄ ባባቷ በኩል እንዲደርስ አድርጓል፡፡ ተራኪውም ተረቱን ሲያዋቅር ከተሰነዘሩት አራት ንግግሮች ውስጥ የልጅቷ አባት አንዱንም እንዳይረዱ ያደረገው ልጃገረዷን ለመፈተን ካለው ፍላጎት ይመስላል፡፡ የሚስት አጭታው ዓላማ ለልጁ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የምታገለግለውን ሚስት መፈለግ እንጂ ለአገርም ለወገንም የምትጠቅም ሴት ፈልጎ ኃላፊነት ለመስጠትና ለሥልጣን ለማብቃት አይደለም፡፡

እንዲህ ዓይነቱ አድራጎት በተለያዩ አፈታሪኮችም ውስጥ ይታያል፡፡ ለምሳሌ በብሌን መጽሔት ቁጥር 6 ውስጥ "ሞቲቴ ማናት?" በሚል የቀረበው የሲዳማ አፈታሪክ ይህንኑ ያሳያል፡፡ በጥንት ዘመን ሲዳማን ሲያስተዳድሩ የነበሩት ንጉሥ እናታቸው የሚኖሩበት አካባቢ ላሉ ሰዎች "የእናቴን ዜና የሚነግሩኝን ወደኔ ላኩ፡፡ ነገር ግን መልዕክተኞቹ እናትህ ሞታለች ወይም በህይወት አለች ብለው ሊነግሩኝ እንደማይችሉ ሲያውቁ

ይገባል" የሚል እንቆቅልሽ ይልኩባቸዋል፡፡ እንቆቅልሹን ያገሩ ሰው መፍታት ባልቻለበት አጋጣሚ የረዳቻቸው ትንሿ ሞቲቴ ነበረች፡፡ ንጉሡም ይህንን በሰሙ ጊዜ ብልኂን ልጅ ለከፍተኛ ሹመት በማብቃት ፋንታ ለሚስትነት ለማጨት ሲሞክሩ ይታያሉ (2002፡9-17)፡፡

በተረት 92 ውስጥ ንጉሡ የሴቷን ብልሃት አይተው ለሚስትነት እንጂ ለሥልጣንና ለማዕረግ አላጯትም፡፡ እርሷም (በተረት 21 ውስጥ ያለችው ሴት) "ባለ ሁለት አንገት ልጃገረድ ማለቱ ክብረ ንጽህናዋ ያልተደፈረ ልጅ ማለቱ ነውና ከመጣ እኔኑ ለልጁ ዳርለት" ስትል ለሚስትነት ብቻ መታጨቷን ታረጋግጣለች፡፡

ሌላው የሴቶች ብልህነት ጎልቶ ከታየባቸው ድርጊቶች ውስጥ ሌላ የለመዱ ባሎቻቸውን ወደራሳቸው ለመመለስ ያደረጉት ብልጠት የተሞላበት ጥረት ነው፡፡ ይህ በተረት 28 እና 79 ውስጥ ተንጸባርቋል፡፡ በተለይ በተረት 28 ውስጥ በምሳሌ ተደግፎ የቀረበው ሚዛን ይደፋል፡፡ ባል አረጀሽ በሚል ስሜት ወጣት ፍለጋ ውጭ ማደር ይጀምራል፡፡ ይህንኑ እንዳወቀች የራሷን መላ ታበጃለች፡፡ አንድ ቀን ባንድ ድስት የዶሮ፣ በሌላ ድስት የተልባ ወጥ ሰርታ የተልባውን ድስት ባዲስ ጨርቅ፣ የዶሮውን ድስት ባሮጌ ጨርቅ ሸፍና በሚታይ ቦታ ታስቀምጣለች፡፡ ባሏም እንደመጣ ምግቡን ታቀርብና ከየትኛው ድስት ወጥ ልጨልፍልህ ትለዋለች፡፡ እሱም በአዲስ ጨርቅ ከተሸፈነው ድስት ፈቃዱን ያደርጋል፡፡ ሆኖም ወጡ ባልጣመውና በዚያኛው ድስት ውስጥ ያለው ወጥ የምን እንደሆነ ጠይቆ በተረዳ ጊዜ "አሃ! ካሮጌም ጥቅም አለ!" በማለት ወደቀድሞዋ ሚስቱ ለመመለስ በቅቷል፡፡ ብልሃቷ ባሏን ወደቤቷ መልሶላታል፡፡

እዚህ ላይ የባልየው ድርጊት በሴቷ ተፈጽሞ ቢሆን ኖሮ ባል የሚስቱን ዘዴ ይጠቀም ነበር ወይ? ብንል ልባችንን ሞልተን ደፍረን ያደርገዋል አንልም፤ አያደርገውም፡፡ አጥኚው ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ባደረገባቸው አጋጣሚዎች ለማስተዋል የቻለውም ይህን ነው፡፡ ለምሳሌ ቦረና ወረዳ ውስጥ ከወንዶች ጋር ተተኳሪ የቡድን ውይይት ሲያደርግ "ሚስትህ ተይ ካልክባት ቦታ ባትመለስ ምን ታደርጋለህ?" ብሎ ላቀረበው የመነሻ ጥያቄ አንዱ ተወያይ "እውነት እውነቱን ከተነጋገርን ሚስቴ ተይ ካልኳት ቦታ ባትመለስ መጀመሪያ እቆጣለሁ፡፡ ካላስተካከለች እመታታለሁ፡፡ በዚሁ ካላቆመች እፈታታለሁ" (27/05/2008) ሲል አቋሙን ገልጿል፡፡ በርግጥ ይህንን ሞኝነቱ የፈጠረው ሳይሆን አባዊው ዓለም የሰራው መዋቅርና የሰጠው ፈቃድ ነው፡፡ በተረቱ ውስጥ ያለችው ሚስትም ያንን ዘዴ የፈጠረችው የቆየው ልማድ እንደዚያ ስለሆነ ነው፡፡ ሚስት

ባሌ ባለገ ብላ ምንም ዓይነት የጉልበት እርምጃ መውሰድ እንደሌለባት የሚያስገነዝብም ነው፡፡ ከእሷ የሚጠበቅባት ጉልበት እንደሌላት አውቃ፣ በዘዴ በምክንያት አባብላ ወደ ቤቱ መመለስ ነው፡፡ ይህን የመሰሉት ተረቶች በተከታዩ ትውልድ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩና የወንድን ባለብዙ መብትነት የሚያረጋግጡ ይሆናሉ፡፡ ይህ በተራዛሚ ወንዱን ከፍ ሴቷን ዝቅ አድርጓል፡፡

ሴቶች አስተዋይነትና የማመዛዘን ብቃት ያላቸው፣ ነገሮችን መርምረው፣ አገናዝበው አንድ መልክ ያለው ቅጥንብር (pattern) መቀመር እንደሚችሉ የሚያሳዩ ተረቶች አሉ፡፡ ተረት 82 እና 83 ለዚህ አብነት ይሆናሉ፡፡ በተለይ "ከአንተ የባሰ እንዳይመጣ ነው" በሚል ርዕስ የተቀመጠው ተረት 83 ስለሴቶች ብልህነት ከፍ ያለ ግምት ያሰጣል፡፡ በታሪኩ አንዲት ለክፉ ንጉሥ ዕድሜ የሚለምኑ ባልቴት ያጋጥማሉ፡፡ ይህንኑ ንጉሥ ሰምተው ለማረጋገጥ ወደ ባልቴቷ ይሄዱና ይጠይቋቸዋል፡፡

> *"እኔ ክፉና ኃይለኛ ነኝ፡፡ ሰው ሁሉ ሞቴን እንጂ መኖሬን አይደግፍም፡፡ አንቺ በምን ምክንያት ነው ለእኔ ዕድሜ የምትለምኚው? ለመሆኑ እንደ እኔ አሳብ ቢሆን ሁሉም ይጠላኛል እንጂ ለእኔ ዕድሜ የሚጸልይ ይኖራል አላልኩም ነበር" ብለው ቢናገሩ አሮጊቷ "ንጉሥ ሆይ! በእኔ ዕድሜ ከአንተ ጋራ አራት ንጉሥ ማየቴ ነው፡፡ የፊተኛው ደግ ነበር፤ የኋለኛው ክፉ ሆነ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ሦስተኛው የበለጠ ክፉ ሆነ፡፡ አንተ ደግሞ ከሁሉ የባስክ ክፉ ሆንክ፡፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንተ የባሰ እንዳይመጣ ለአንተ ዕድሜ እለምናለሁ" ሲሉ መለሱላቸው ይባላል (ተረት 83)፡፡*

አሮጊቷ አገር ለሚጠላው ክፉ ንጉሥ እድሜው እንዲረዝም መጸለያቸው ንጉሡን ጭምር አስገርሟቸዋል፡፡ ሆኖም አመክንዮዋቸው ግልጽ የሚሆነውና የማመዛዘን ብቃታቸው የሚጎላው የፊተኞችን ነገሥታት አድራጎት አይተውና ገምግመው፣ ከዛሬው ጋር አነጻጽረው የወደፊቱ ምን ሊሆን እንደሚችል መገመት መቻላቸው ነው፡፡ ይህ አስተሳሰባቸው ደግሞ አንድ ቀመር መሰል ቅጥንብር ለመፍጠር አስችሏቸዋል፡፡ ይህም ከአምናው የካቻምናው፣ ከዛሬው የአምናው፣ ከተሻለ የግዴታ የዘንድሮው ከከርሞው ይሻላል የሚል ፍልስፍናዊ ቀመር መሰንዘር ነው፡፡ ይህንን ለማለት ወደፊት ወደኋላ ብሎ ነገሮችን መርምሮ፣ አነጻጽሮና አወዳድሮ መመልከትን ይጠይቃል፡፡ ይሄም ሌላው የሴትን ብልህነት ማሳያ ይሆናል፡፡

ከመስክና ከቤተመዛግብት ተሰብስበው ለዚህ ንዑስ ርዕስ ማሳያነት የተመረጡት ባብዛኛው የሴትን ብልሃትና የወንድን ሞኝነት ያሳያሉ፡፡ ተረት 34 የውሽማዋ ሃፍረተ ስጋ በባሏ እንዳይቆረጥ የቀየሰችው ፈጣን ብልሃት፣ ተረት 50 ሴት አስመስላ ቤቷ

ያሳደረችው ውሽማዋ ወንድነቱ ሲነቃበት ከደባው ንጹህ ለመሆን ባሏን ያታለለችበት ዘዴ፣ ተረት 53 ባሏን በምሽት ከቤቱ አስወጥታ ከውሽማዋ ጋር ለማደር የተማከረችው ሴራ ወዘተ. ጥሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ባንጻሩ ወንድ ፍጹም ሞኝ የሆነባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው፡፡ በተለይ በተረት 72 የቀረበው ታሪክ ብልጫ አለው፡፡ ሚስት ጌታዋ ወደዘመቻ በሄደበት ወቅት ከአገልጋዩዋ ጋር ባልጋ ታረግዛለች፡፡ ስህተቷ እንዳይታወቅባትም አስወርዳለሁ ስትል በዚሁ ምክንያት ትሞታለች፡፡ ይህንኑ ጌታው ከአገልጋዩ በሰማ ጊዜ ምክንያቱን ሲጠይቅ አገልጋዩ የሰጠው መልስ እሜቴ የሞተችው አርግዛ አስወርዷት ነው፡፡ ያረገዘችው ሰዎች ከአንተ ነው ይሉኛል፤ እኔ ግን አይደለም! እላለሁ ሲል የመለሰው ፍጹም የሞኝነት አስተሳሰብ ነበር፡፡ ይህንን ሲባል ግን ሁሉም ወንድ የዚህ ዓይነት ሞኝነት አለበት ለማለት አይደለም፡፡ ጥረቱ በየዋህነት ከጥፋቱ ነጻ ለመሆን እንጂ የጌታውን ሚስት ስለማባለጉ ምስክርነት መስጠቱን ትዝ አላለውም፡፡ በተረት 74 ባል በሚስቱ በመታለል በሬውን ያረደበት፣ በተረት 91 ሴቷ አንድ ዓይና ባሏን አታልላ ውሽማዋን ከቤት ያስወጣችበት ወዘተ. ስንመለከት የወንድን ሞኝነት የሴትን ብልህነት እናጤናለን፡፡ ይሁንና አባዊው ዓለም ብልህነታቸውንና ከእርሱ መሻላቸውን አምኖ (ምናልባት ለማጽናኛ ያህል ብሏቸው ካልሆነ በስተቀር) ሃላፊነት ሊሰጣቸው ሲገባ ለምን እኩልነታቸውን[44] እንደነፈጋቸው ከፍ ያለ ጥያቄ ያስነሳል፡፡

## 5.1.2 ጭካኔ እና ርኅራኄ

ጨካኝነትና ርህሩህነት ተቃራኒ ትርጉም አላቸው፡፡ ርህራሄ ከአዛኝነት፣ ከደግነት፣ ከአስተዋይ ልቡና፣ ከየዋህነት ወዘተ. ይመነጫል፡፡ ጭካኔ ደግሞ ራስን ከማስቀደም፣ ከምቀኝነት፣ ከቅናት ወዘተ. ይወለዳል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል

---

[44] ሴት ከወንድ እኩል መሆን አለባት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በራሱ መሰረታዊ የእሳቤ ችግር አለው፡፡ የአባባሉ አንድምታ ሴት ምንም ቢሆን ከወንድ በላይ ልትሆን የምትችልበት አጋጣሚ አይፈጠርም የማለት ነው፡፡ በመሆኑም እኩልነት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ ግቡ ሴቶች መሰረታዊ የሥርዓተ ጾታዊ መብታቸውን በማረጋገጥ ፋንታ ለወንድ ባደላው ሥርዓት ውስጥ ለመሰግሰግ ብቻ ይሆናል ማለት ነው፡፡ Lazar (2007:154) ይህንኑ ሲያረጋግጡ "Instead of a radical shift in the gender order, women are required to fit into prevailing androcentric structures." ብለዋል፡፡ ለምሳሌ ከወንድ እኩል ሥልጣን መያዝ፣ በንብረቷ ላይ ከባሏ እኩል የማዘዝና የማስተዳደር መብት፣ በሃይማኖት ተቋማት እኩል አገልግሎት የመስጠት መብት ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ቦታዎች በወንድ የበላይነት እንደተያዙ ሁሉ በሴቶች የማይያዙበት ምክንያት የለምና ለምን መብታቸው በእኩልነት ላይ ብቻ ያነጣጥራል? ብለን ስንጠይቅ አባባሉ ዝንፈት ያለበት መሆኑን እንረዳለን፡፡ ከወንዱ በላይ ሊሆኑ የሚችሉበት አጋጣሚ በመርህ ደረጃ የተዘጋ ይመስላል፡፡

ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት (1993፡571) ላይ እንደተገለጸው “ጨካኝ” ርኅራኄ ወይም ሃዘኔታ የሌለው ማለት ሲሆን ርኅሩኅ ደግሞ አዛኝ፣ ደግ፣ ቸር፣ ክፉ ያልሆነ ማለት ነው (1993፡99)፡፡ ከዚህ አንጻር ሴቶችና ወንዶች በተረቶች ውስጥ የተሰጣቸውን ገጽታ ስንመለከት በአብዛኛው ወንዶች ርኅሩኆች፣ በቀላሉ የሚታለሉ፣ የነገሯቸውን የሚያምኑ፣ እንዲያውም አደጋ ላይ የወደቁ ሴቶችን የሚታደጉ ተደርገው ተስለዋል፡፡ በአንጻሩ ሴቶች ግን ጨካኞች፣ ግፈኞች፣ የሚፈልጉትን ለማግኘት ማንኛውንም ርምጃ ከመውሰድ ወደኋላ የማይሉ ሆነው ቀርበዋል፡፡ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት በሴቶች ሳይቀር ተመሳሳይ ሃሳብ ተሰንዝሯል፡፡ ለምሳሌ ቦረና ወረዳ ውስጥ አንዲት “እኛ [ሴቶች] የበላይነት ከተሰማን ብዙውን እንደማንቻል መጽሐፍ ቅዱስ ቁልጭ አድርጎ ይናገራል፡፡ ግን ተሳስበን እንድናድር ወንድ የበላይ ሆኖ እንዲያስተዳድረን ነው፡፡ ሴት የበላይ ሆና ብታስተዳድር እርግጠኛ ነኝ አንቻልም፡፡ በጣም ከባድ ነን፡፡ . . . መጽሐፍ ቅዱስ ያስቀመጠው ትክክለኛ ነው” (27/05/2008) ሲሉ አስረድተዋል፡፡

ሴቶች በተለይ በእንጀራ ልጆቻቸውና በባሎቻቸው ዘመዶች ላይ የሚያደርሱት በደልና የሚወስዱት ርምጃ በተረቶች ውስጥ በጉልህ ተንጸባርቋል፡፡ ይህ ሲባል ግን ወንዶች ጨካኞች፣ ሴቶች ደግሞ ርህሩሆች ሆነው የተሳሉባቸው አጋጣሚዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ይበልጥ ጉዳዩን ግልጽ ለማድረግ ተረቶችን እያጣቀስን እንመልከት፡፡

የሴቶች የጨካኝነት ገጽታ የሚመነጨው ቅናት ከወለደው ስሜት፣ ምክንያቱን ካላወቅኩ ከሚል አቋም፣ ከጥላቻ ስሜት፣ ራስ ብቻ ለመጠቀም ካለ ፍላጎት ወዘተ. የሚመስሉባቸው አጋጣሚዎች በተሰበሰቡት ተረቶች ውስጥ ይታያሉ፡፡ እነዚህ አጋጣሚዎች ጾታ ሳይለዩ የጭካኔ ተግባርን ለመፈጸም ሊያነሳሱ እንደሚችሉ እርግጥ ነው፡፡ ይሁንና እነዚህ ምክንያቶች የሴት ብቻ እንደሆኑ ተደርጎ በስፋት መነገሩን ስናስብ ለምን የሚል ጥያቄ ማንሳታችን አይቀርም፡፡ ለጥያቄው መልስ ከመስጠታችን በፊት ሴቶች ጨካኝ የተባሉባቸውን ተረቶች እያነሳን እንይ፡፡

ከፍ ባለው አንቀጽ እንደተጠቀመው ለሴቶች የጭካኔ ተግባር አንዱ ምክንያት ቅናት ነው፡፡ ይሄ በብዛት ከእንጀራ ልጆቻቸው አያያዝ ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ከነአባባሉ “እንጀራ እናት ምን አጠናሽ እንደ ጅማት” ይባላል፡፡ በተረቶች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በሰፊው ማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ እንጀራ እናት ጥሩ ስም የላትም፡፡ የእንጀራ ልጇን በእንክብካቤ ብታሳድግም እንኳ ስሟ ያው ክፉ፣ ጨካኝ ነው፡፡ ተረት 14 ይህንኑ ያጸናልናል፡፡

በተረቱ ውስጥ እንደተገለጸው እንጀራ እናት እንጀራ ልጇን ከራሷ ልጅ ለይታ ታሰቃያታለች፡፡ ከእሷ ልጅ ለይታ ስራ ታበዛባታለች፤ በምግብ ትጎዳታለች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የተበዳዩዋን ሙያ፣ እውቀትና "ሰው ቀና ብሎ አለማየት" የተመለከተ ሰው ለልጁ ሚስት እንድትሆነው ያጫታል፡፡ ከላይ የተጠቆመው አድልዎ እንዳለ ሆኖ የእናትያዋ ቅናት መሰረት ያደረገው ጭካኔ የሚመጣው ከልጂቱ መታጨት ጋር ነው፡፡ የእሷ ልጅ ተቀምጣ የእንጀራ ልጇ በመታጨቷ ቅናት ያንገበገባት እንጀራ እናት የእሷ ልጅ የምትዳርበትን ዘዴ ማውጠንጠን ትጀምራለች፡፡ ከተረቱ ጠቅሰን እንመልከተው፡-

*. . . . የተከሰተላት ዘዴም የእንጀራ ልጇን በአቅራቢያው በሚገኘው ዘንዶ ማስዋጥ ነበር፡፡ ይህን ለማድረግም ለልጇ እንዲህ ስትል ነገረቻት፡፡ "ከዚያች ከጎደሎ ጋር አብራችሁ ወንዝ ውረዱ፡፡ ከዚያም እዘንዶው ጉርጓድ አፍ ተቀመጭና እሾህ ወጋኝ ብለሽ ጩሂ፡፡ ልታወጣሽ ስትመጣ ወደ ጉርጓዱ ገፍትረሽ ጣያት" አለቻት፡፡ ልጅቱም እናቷ እንደነገረቻት እጉርጓዱ ውስጥ ገፍትራ ከተተቻት፡፡*

*ይህ ሁሉ ሲሆን አባት ለሙሽራ ልጁ ጌጣጌጥና ልብስ ለመግዛት ወደ እሩቅ አገር ሄዶ ነበር፡፡ ከሄደበት ሲመለስ ልጁ ካገር መጥፋቷን ሲነግሩት እጅግ አዝኖ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ ሚስቱም "ባይሆን ድግሱ ተደግሶ ከሚበላሽ ይህችኛዋን እንዳርበት" በማለት ባሏን አግባባችው . . . (ተረት 14)፡፡*

እንጀራ እናት በእንጀራ ልጇ ላይ ሶስት በደሎችን አድርሳባታለት፡፡ አንደኛ ከልጇ ለይታ ስራ በማብዛት አሰቃይታታለች፡፡ ሁለተኛ ብቃቷ (ሙያ፣ እውቀት እና "ሰው ቀና ብሎ አለማየት") ያመጣላትን ባል ለማሳጣት ጥረት አድርጋለች፡፡ ሶስተኛ በዘንዶ ተውጣ እንዲትሞትላት ሞክራለች፡፡ እነዚህ ሲደማመሩ ሴትዮዋን ፍጹም ጨካኝ አድርገዋታል፡፡ የሴትዮዋ ጭካኔ ሳያንስ የአብራኳን ክፋይ ሳይቀር ጭካኔ አስተምራታለች፡፡ እህቷን በእጇ እንድታጠፋ ጭካኔያዊ ምክሯ ምክንያት ሆኗታል፡፡

በዚህ ተረት ውስጥ የሴትዮዋ የጭካኔ ሰለባ ከሆኑት ውስጥ የራሷ እና የልጇ ባልም ይገኙበታል፡፡ አባት፣ እናት የሌላትን ልጁን በመዳር ሊያገኝ የነበረውን ደስታ አሳጥታዋለች፤ አሳዝናዋለች፡፡ ለሠርጉ ሲያደርግ የነበረውን ዝግጅት ከነልጁ ጭምር መና አስቀርታዋለች፡፡ የልጇ ባልም ቢሆን ያልፈቀዳትን፣ በራሱ መስፈርት መርጦ ትሆነኛለች ያላትን አሳጥታ ሌላኛይቱን እንዲያገባ ማድረጓ ለእርሱ በደል ነው፤ ጭካኔ ነው፡፡

ከዚህ ብዙም ባልተለየ መልኩ በተረት 42 ውስጥ ቅናትን መሰረት ያደረገ የሴትን ጭካኔ እናገኛለን፡፡ ታሪኩ ገና ሲጀምር፣ ". . . ክፉ ስለነበረች ለባሏ ልጆች ምግብ

አትሰጣቸውም ነበር፡፡ በዚያ ላይ የባሏን ልጆች ብቻ ከብት እንዲጠብቁ ወደ ዱር ትልካቸው ነበር” ይላል፡፡ ልጆቹ በዱር ከብት ሲጠብቁ ይርባቸው ስለነበር የጠየቁትን የማይነሳ አምላክ ወተትና ለከት እየሰጣቸው ይመገቡ ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ልጆቹ ሲያምርባቸውና እንደ ፀሃይ ማብራት ሲጀምሩ መቅናት ያዘች፡፡ ምክንያቱን በልጇ በኩል ስታጣራ ታውቃለች፡፡ ለከብት ጥበቃ ወደ ዱር እንዳይሄዱ ትከለክላለች፤ በምትካቸውም የእሷን ልጅ ትልካለች፡፡ ባለእናቷ ልጅ እንደ ተበዳዮቹ ልጆች ለከትና ወተት እንዲሰጣት ፈጣሪዋን ብትለምንም ሳይሳካላት ይቀራል፡፡ ይህንኑ ልጂት ለእናቷ ስትናገር እናት የባሰውኑ ተናድዳ የእንጀራ ልጇን ለመግደል ታስባለች፡፡

*. . . . “ነገ ዱር ስትሄዱ ሁለቱንም ገፍትረሽ ባህር ውስጥ አስገቢያቸው” ስትል ልጇን መከረቻት፡፡ ልጂትም እንደተመከረችው በማግስቱ ከባህሩ ዳርቻ ሲጫወቱ ሴቷን ልጅ ገፍትራ ባህሩ ውስጥ ጣለቻት፡፡ ታናሽ ወንድሟ እህቱ ልትሞት መሆኗን ሲገነዘብ አለቀሰ፡፡ እያለቀሰም “እትየ! እትየ! አባታችን መጣ ከዘመቻ፣ ድሪውን ይዞ አልቦውን ይዞ” አለ፡፡ ልጅቱም*

*“ድሪውም ይሁን እናት ላላት፣*
*አልቦውም ይሁን እናት ላላት፣*
*እኔስ ተይዣለሁ በዘንዶ ጅራት” በማለት መለሰችለት . . . (ተረት 42)*

እንደ ተረት 14 እዚህም ውስጥ እንጀራ እናት በእንጀራ ልጆቿ ላይ ሶስት ጊዜ ጨክናለች፤ ምግብ በመከልከል፣ ፈጣሪያቸውን ለምነው ምግብ እንዳያገኙ እቤት በማዋል እና ወደ ባህር ውስጥ ተወርውረው በዘንዶ እንዲበሉ ማድረግ ናቸው፡፡ ጭካኔዋ ይበልጥ የሚገባን የልጆቹን ሁኔታ በምናባችን ስናስበው ነው፡፡ ወንድምየው እህቱ ከባህር እንድትወጣለት የተማጸነበት መንገድ እና እህትየዋ ተስፋ በቆረጠ ስሜት የተናገረችው አንጀት ያላውሳል፡፡

ወንድምየው ከጭንቀቱ የተነሳ ዋሽቶ እህቱ ከባህር እንድትወጣለት ጥሯል፡፡ የልጅ ነገር ሆነና በዘንዶ መያዟን ባለማወቅ በራሷ ፈቃድ እባህሩ ውስጥ እንደተቀመጠች ሁሉ አጓጉቶ (በስጦታ አማልሎ) እንድትወጣ ለማድረግ በለቅሶ ጭምር ሞክሯል፡፡ ይሁንና ያገኘው መልስ ግን እሷ ተስፋ ቆርጣ እሱንም ተስፋ ያስቆረጠ ነበር፡፡ ተስፋ መቁረጧም በዘንዶ ልትበላ መሆኗን ብቻ የሚያረጋግጥ አይደለም፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ ከዘንዶው ልታመልጥ ብትችል እንኳ እናት እንዳላቸው ልጃገረዶች በአልቦ እና በድሪ አጊጣ ልታገባ እንደማትችልም ጭምር ነው፡፡ እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄያችን ይህ ሁሉ በምን መጣ? የሚል ነው፡፡ መልሳችን በእንጀራ እናት ጭካኔ የሚል ይሆናል፡፡

ሌላው በተረቶች ውስጥ ያሉት ሴቶች ጭካኔያዊ ተግባር የሚመነጨው የነገሮችን ምክንያት ለማወቅ ካለ ጉጉት ነው፡፡ በእርግጥ ነገሮች የሆኑበትን ምክንያት ለማወቅ መጓጓት የሚያስመሰግን ባህሪ ነው፡፡ ለእውቀትም፣ አዲስ ነገር ለመፍጠርም ምክንያት ነው፡፡ ሆኖም ጭካኔ ሲታከልበት ጥረቱን በጎ አያስብለውም፡፡ ይህንን በተረት 24 ማሳያነት እናፍታታው፡፡

ተረት 24 አንድ ድሃ ከወንድሙ ተለይቶ እሱ ለምን ድሃ እንደሆነ ፈጣሪውን ሊጠይቅ በመንገድ ላይ ሳለ ፈጣሪውን ሰው ተመስሎ ያገኘዋል፡፡ ከፈጣሪውም ከተነጋገረ በኋላ የእንስሳትን ሁሉ መግባቢያ እንዲያውቅ የፈጣሪው ፈቃድ ይሆናል፡፡ በዚህም የተነሳ ሃብት አግኝቶ ትዳር ይመሰርታል፡፡ በዚህ ሂደት ላይ እንዳለ አንድ ቀን ከሚስቱ ጋር ተኝቶ እንዳለ የፍየል ወጠጤ ከጉረኖው ሆኖ ሁሉንም እንስት ፍየሎች ሲያንባባ ይሰማል፡፡ ይህን ጊዜ ከቆጥ ላይ ያለው ዶሮ፣ ፍየሉን “አንድ ለሚወልድ ስንቱን ያንባባል” ብሎ ሲያማ ባልዮው ሰምቶ ይስቃል፡፡ ሚስት ባሏ ለምን እንደሳቀ ምክንያቱን ትጠይቃለች፡፡ ባል ሚስጥሩን ቢናገር እንደሚሞት ከአምላኩ ተነግሮታልና መናገር አልቻለም፡፡ ከነገራት ሊሞት እንደሚችል ቢያስረዳትም ሃሳቧን የምትቀይር አልሆነችም፡፡ እንዲያውም “በዚህ የተነሳ እፈታሃለሁ” ስትል በማስጠንቀቅ የማወቅ ጉጉቷን ትገልጽለታለች፡፡ እርሱ ግን ከምፈታ ሞቴን እመርጣለሁ ብሎ የቁም ተዝካሩን ለማውጣት ደግሷል፡፡

እዚህ ላይ የሴቷን የማወቅ ጉጉት በአወንታ ብንመለከተውና ብናደንቅም ማወቋ ባሏን የሚያሳጣት ሆኖ ስታገኘው ሃሳቧን ለመቀየር አለመቻሏ ከጭካኔ ሌላ ምንም ሊባል አይችልም፡፡ የጭካኔ ተግባሯም ውላ እያደረች ስትሄድ ነገሩን አብሰልስላ ቢቀርብኝስ አለማለቷ፣ የጭካኔዋን ደረጃ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ባልየው አቋሙን ቀይሮ አንቺን ከምፈታ ሞቴን እመርጣለሁ ብሎ መደገስ ሲጀምር እሷ በበኩሏ “አይ አንተ ከምትሞትስ ጉዳዩን ሳላውቀው ይቅር” አለማለቷ፣ የባሏ የመሞቻ ጊዜ መቃረቡ እየታወቃት ሲመጣ ሃሳቧን አለመቀየሯ ነገሩን ያከብደዋል፡፡ ይህንን የምንልበት ምክንያት ነገሩ ከተከሰተበት ቀን አንስቶ እስከ ተዝካሩ ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ረጅም በመሆኑ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ ነገሩን አሰላስላ ሃሳቧን ለመቀየር አለመሞከሯ ጨክናለች ያስብለናል፡፡

በአንጻሩ ወንዱ በዚህ ተረት ውስጥ ርኅሩኅ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ሚስቱ የምትፈልገውን ለመፈጸም ሲል ሞቱን ሲመርጥ ይታያል፡፡ እንዲያውም “በህይወቴ ሳለሁ አንቺን ከምፈታ ምስጢሬን ነግሬሽ ብሞት ይሻለኛል” ሲል ይደመጣል፡፡ በዚህ አቋሙ

እስከተዝካሩ ቀን ደርሷል፡፡ አቋሙንም ከራሱ ጋር መክሮ ሲቀይር አይስተዋልም፡፡ ከሞት ለመዳን የበቃው በውሾቹ ምክር እንጂ ራሱ አስቦት አይደለም (እንዲህ ዓይነት የወንድ ባህሪ - ለችግሩ ራሱ መፍትሄ መፈለግ አለመቻል በተረቶች ውስጥ በብዛት ይስተዋላል)፡፡ ውሳኔውም እርሷን የሚጎዳ ሳይሆን ራሱን ከሞት የሚታደግ በመሆኑ ሚዛናዊ እንጂ ጨካኝ አያስብለውም፡፡ ከእርሷ ውሳኔም ጋር ሲነጻጸር ርኅሩኅነቱን ያሳያል፡፡

ሶስተኛው የሴቶች ጭካኔ ከጥላቻ ስሜት የመነጨ መስሎ ይታያል፡፡ በተለይ አማትና ምራት ምክንያቱ ይህ ነው ተብሎ ለመግለጽ በሚያስቸግር መልኩ አይዋደዱም፡፡ ሁላችንም ከማኅበራዊ ገጠመኞቻችን እንደምናስተውለው (ሁልጊዜ ባይሆንም እንኳ) እናት የልጇን ሚስት፣ ሚስትም በተለይ የባሏን እናት አትወድም፡፡ ይሄ ማህበራዊ ገጠመኝ በተረቶች ውስጥ በስፋት ተተርኳል፡፡ ለምሳሌ ያህል ሁለት ተረቶችን ጠቅሰን እንመልከት፡፡

በተረት 33 ውስጥ አንዲት እናት በወንድ ልጃቸው ቤት እየተጦሩ ሳለ በምራታው ክፉኛ ይራቡ ነበር፡፡ እናት አንድ ቀን ረሃቡ ሲጠናባቸው ለምራታቸው "ዛሬስ ሆዱን ሙሉ በልቶ የሞተ ሰው አስቀናኝ፤ ሆዴ እስኪሞላ ብበላ ታንቄ እሞት ነበር" እያሉ አወሩ፡፡ ልጂትም ጥሩ ወጥ ሰርታ በእርጎ ፈትፍታ ካበላቻቸው በኋላ የመታነቂያ ገመዳቸውን ስታሰናዳ ትታያለች፡፡ ይህን ሁሉ ለማድረግ የሚያነሳሳ በደል ግን በዚህ ጊዜ ፈጸመችብኝ ስትል አልታየችም፤ ዝም ብሎ ጥላቻ ብቻ ነው፡፡

በተረት 39 አንዲት ሴት የባሏን አባት ከምንም ተነስታ እንዲሁ ዓይኔ እንዳያየው በሚል በጭካኔ በወንድ ልጁ ጫካ እንዲጣሉ ታደርጋቸዋለች፡፡ ሆኖም ልጅ አባቱ እንዴት እንዳደሩ ለማየት በሄደ ጊዜ አካባቢው ለምልሞ አባቱ በብዙ ከብቶች ተከብበው ያገኛቸዋል፡፡ ልጅ አባቱን ይዞ ከብቱን እየነዳ ወደ ቤቱ ይሄዳል፡፡ ይህንን የተመለከተችው ጨካኝ ሚስት ለሃብት በመጓጓት የራሷን አባት ጫካ ውስጥ ጥላቸው ትመጣለች፡፡ ሆኖም አባቷ በከብቶች በመከበብ ፋንታ በጅብ ተበልተው ያድራሉ፡፡ እዚህ ላይ ሴቷ ፍጹም ጭካኔ የተሞላበት ተግባር ፈጽማለች፡፡ ባሏ ግን ከእርሷ በተቃራኒው ርኅሩኅ ሆኖ ቀርቧል፡፡ አንደኛ አባቱን በሚስቱ ተገድዶ ጫካ ውስጥ ቢጥልም ፈጣሪ የልቡናውን አይቶ ከሞት አትርፎለታል፡፡ ሁለተኛም አባቱን በጣለበት ሌሊት እንቅልፍ ሳይወስደው ፈጣሪውን ሲለምን አድሯል፡፡ ሶስተኛ ሚስቱ አባቷን እንዲጥልላት ለማድረግ ብትሞክርም እምቢታውን ገልጾላታል፡፡ በመሆኑም ባል ፍጹም ርኅሩኅ ሆኖ ቀርቧል፡፡

በመጨረሻ የምንመለከተው ራስ ብቻ ለመጠቀም ካለ የጉጉነት ፍላጎት በመነጨ የተፈጸመውን ጭካኔ ነው፡፡ ተረት 48 እንደሚያሳየን ከልጅነታቸው ጀምረው አብረው ያደጉና እጅግ የሚዋደዱ ሴትና ወንድ፣ ሴቷ በምግብ አብሳይነት፣ ወንዱ ደግሞ በአቅራቢነት ለንጉሥ ያድራሉ፡፡ በዚሁ ስራቸው ላይ እንዳሉ አንድ ቀን ሴቷ በጓደኛዋ መቅናት ጀመረች፡፡ ያዋጣኛል ያለችውንም ሴራ ሸረበች፡፡ ከተረቱ ጠቅሰን እንየው፡፡

> *. . . . "የንጉሡ ምግብ አቅራቢ ብሆን የተረፋቸውን እየበላሁና እየጠጣሁ ያንን በልቼና ጠጥቼ መልኬ እንደ ፀሃይ ሲያበራ ንጉሡ ሚስት አድርጎ ያኖረኛል" በማለት አሰበች፡፡ ይህንን ፍላጎቷን ለማሳካት የራሷን መላ አበጀች፡፡ ወደ ንጉሡ ሄዳ "ጌታዬ! የቀጠሩት ምግብ አቅራቢ 'የንጉሡ አፍ በጣም ይሸታል፤ ስለዚህ እኔ ምግብ ይዤ ስሄድ አፉን በመሃረብ ይሸፍን' ብሏል" በማለት ነገሯን ሰካች፡፡ ከዚያም ወደ ጓደኛዋ እንደተመለሰች "ንጉሡ 'አፍህ ሸቷል፤ ስለዚህ ምግብ ይዘህ ወደ እኔ ስትመጣ አፍህን በመሃረብ ሸፍን' ብለውሃል" በማለት ሁለቱን ለማጣላት አመቻቸች፡፡ ንጉሡም እንደ ንጉሥነታቸው ነገሩን በጥልቀት ለማየት ፈለጉና ዝም ብለው ሲከታተሉ ምግብ አቅራቢው አፉን በመሃረብ ሸፍኖ ምግብ ይዞ ቀረበ፡፡ ንጉሡም የተነገረው ነገር ትክክለኛ እንደሆነ አመነና በልቡ የሞት ፍርድ ፈረደበት . . . (ተረት 48)*

በዚህ ተረት ውስጥ የሴቷ የመጨረሻ ግብ የንጉሡ ሚስት መሆን ነው፡፡ ሚስት ለመሆን ማማር ይጠበቅባታል፡፡ እንደ እሷ አባባል "እንደ ፀሐይ ማብራት" አለባት፡፡ እንደ ፀሐይ ለማብራት ደግሞ የንጉሡን ትራፊ መብላት የመጨረሻው አማራጭ አድርጋ ይዛዋለች፡፡ ይህንኑ ማግኘት ትችል ዘንድ የንጉሡ ምግብ አቅራቢ ጓደኛዋ ቦታውን መልቀቅ አለበት፡፡ ይህ ይሆንላት ዘንድ እሷ አንድ መላ መፍጠር ስለነበረባት ሁለቱ (ንጉሡና ምግብ አቅራቢው) ሳይግባቡ እንዲጣሉ አድርጋለች፡፡ ለማጣላት የቀየሰችውን ስልት ስንመለከተው በእርግጥም ሊያጣላና ቢያንስ የምግብ አቅራቢውን ስራ ሊያስነጥቅ የሚችል ነው፡፡

ንጉሡ "አፍዎ ይሸታል" በመባላቸው ምክንያት በምግብ አቅራቢው ላይ እርምጃ ሊወስዱ እንደሚችሉ እንገምታለን፡፡ ምክንያቱም ለንጉሡ እንደዚያ መባል ያውም ባገልጋያቸው፣ ድፍረት ነው፡፡ በመልዕክት ደረጃ የተነገራቸውም "የንጉሡ አፍ በጣም ይሸታል፤ ስለዚህ እኔ ምግብ ይዤ ስሄድ አፉን በመሃረብ ይሸፍን" በሚል በድፍረትም በንቀትም መንፈስ የተነገረ የሚመስል ነው፡፡ ይሄ የከፋ ቅጣት ሊያስከትል እንደሚችል ይታወቃል፡፡ በዚያ ላይ ንጉሡ ሚዛናዊ ሆነው ነገሩን አጣርተው ተገቢ የሚሉትን ቅጣት እንዳይሰጡ ምግብ አቅራቢው አፉን በመሃረብ ሸፍኖ ምግብ ሲያቀርብላቸው ተመለከቱ፡፡ ይሄ ምስክርነት የሚያሻው አይደለም፡፡ በእርግጥ አገልጋዩ ይህንን ያደረገው አፉ ንጉሡን እንዳይሸታቸው በሚል ቅን መንፈስ ነበር፡፡ ነገር ግን በንጉሡ ዘንድ ነገሩ የተገላቢጦሽ

ስለሆነ ፈጣን ውሳኔ (የሞት ፍርድ) አሳልፈዋል፡፡ ይህንን ስንመለከት በተረቱ ውስጥ የተሳለችው ሴት ገጸባህሪ ጨካኝ አይደለችም አንልም፡፡ እንዲያውም የሰራችውን ቅንብር ስንመለከት በረጅም ጊዜ የታሰበበት የጭካኔ ተግባር መሆኑን እናጤናለን፡፡ ገና ለገና የንጉሥ ትራፊ በልታ አምሮባት ንጉሡ ያገቡኛል ብላ በመጓጓት የሚወዳትን አብሮ አደግ ጓደኛዋን ለሞት አሳልፋ መስጠቷ ጭካኔዋን ያሳያል፡፡ በተረት ላይ በተደረጉ ሌሎች ጥናቶች ውስጥ የሴት ጭካኔ ጉልህ ይዘት ሆኖ የቀረበበት አጋጣሚ አለ፡፡ ለምሳሌ በ Desta (2015:147) ጥናት ውስጥ ይህንኑ እናገኛለን፡፡ የሚስትህን አንገት ቆርጠህ ራሷን ብታመጣ አገር እሰጥሃለሁ የተባለው ወንድ ማድረግ ሳይችል ሲቀር በተመሳሳይ ይሄው ትዕዛዝ የተሰጣት ሴት ግን የባሏን አንገት በጭካኔ ቆርጣለች፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ ትንተና በተሰጠባቸው ተረቶች ውስጥ የሴቶች የጭካኔ ተግባራት ሴት ባለታሪኮቹ በሚፈልጉት መንገድ ሙሉ በሙሉ ሰምሮ ለውጤት ሲበቃና በሚፈልጉት መንገድ ሲሆን አይታይም፡፡ ተረቱ የታለመለትን ግብ ይመታ ዘንድ በተራኪው ሆን ተብሎ በታቀደና በተቀነባበረ የታሪክ አካል ምኞታቸው ከንቱ ሲሆን ይታያል፡፡ ለምሳሌ በዘንዶ የተዋጠችው ልጅ (ተረት 14) በተዓምር በእጮኛዋ ምክንያትነት ትተርፋለች፤ ያገባታልም፡፡ ቀድሞ ያገባትን (የጨካኟን ልጅ) ግን ምላሷን ቆርጦ እህል ፈጪ አድርጓታል፡፡ ይባስ ብሎ (በዚሁ ተረት ውስጥ) እናት የገዛ ልጇን በራሷ እጅ እንድትገድላት ሁኔታዎች ተመቻችተዋል፡፡ በተረት 42 ውስጥ በዘንዶ ጅራት የተያዘችው የእንጀራ ልጅ በተለያዩ ተዓምራዊ ሂደቶች ድና የእንጀራ እናቷ ልጅ (እህቷ - ያባቷ ልጅ) ያገባችውንና እጮኛዋ የነበረውን በትልቅ ሠርግ በክብር አግብታለች፡፡ እጮኛዋን ያገባችባትን እህቷን ምላሷን በምላጭ ቆርጣ እንድትሞት አድርጋታለች፡፡ በተረት 39 ውስጥ ሴቷ በአማቷም ባባቷም ላይ ያደረገችው ተግባር እሷ በፈለገችው መንገድ እንዳይሆን ተደርጓል፡፡ እንዲሞት የፈለገችው አማቷ ሃብት ይዞ ሲመለስ፣ ሃብት እንዲያመጣ የፈለገችው አባቷ ደግሞ በጅብ ተበልቷል፡፡ በዚህም ሁለት ጊዜ ተቀጥታለች፡፡ አንድም አባቷን በጅብ አስበልታለች፤ አንድም ወንድሞቿ በወሰዱባት የበቀል ርምጃ ታስራ በጅብ ተበልታለች፡፡

በተረቶች ውስጥ በጨካኝነት የተሳሉት ሴቶች ሁሉም ማለት በሚቻል መልኩ ራሳቸው ባዘጋጁት ወጥመድ ተጠልፈዋል፡፡ እዚህ ላይ ይህ ለምን ሆነ? ሴቶቹ የእጃቸውን እንዲያገኙና ወንዱ በአሸናፊነት እንዲወጣ ለምን ተደረገ? ርኅሩኅ የሆኑ ሴቶች የሉም

ወይ? ጨካኝ የሆኑ ወንዶችስ በዚህ ዓለም አልተፈጠሩም ወይ? በዚህ ዓይነት የተቀናጁ ተረቶች በጠቅላላው ምን ይነግሩናል? ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡

በብዙ ተረቶች ውስጥ እንደሚስተዋለው ወንዱ በተሸናፊነት ሴቷ በአሸናፊነት እንዲወጡ አልተፈለገም፡፡ ምክንያቱም ጉዳዩ እየቆየ ሲሄድ የወንዱን የበላይነት፣ ባለሙሉ ሥልጣንነት አደጋ ላይ የሚጥልና የሚጋፋ ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ ሴቷን በጭካኔ ስሎ ሙከራዋ በውድቀቷ እንዲጠናቀቅ ማድረግ የተመረጠ ዘዴ ነው፡፡ ይህንን ያዩ ሴቶችም ተመሳሳይ ሙከራ እንዳያደርጉ ሥነልቡናዊ ጫና ማሳደር፣ ቢያደርጉ እንኳ ወንዱ እንዲጠነቀቅ ንቃት መስጠት ነው፡፡ ይህ ዞሮ ዞሮ ማሳረጊያው የሴትን የበታችነት ማስረጽ፣ በወንዱ ቁጥጥር ስር የምትውልበትን መንገድ ማመቻቸት፣ ቀደም ብሎ በተሰራው የበላይነትንና የበታችነትን በሚያሳየው መዋቅር ውስጥ ሴቶችን ለማስገባትና ለመዋቅሩ ለማስገዛት ነው፡፡

እዚህ ላይ ከላይ የተጠቀሱት ተረቶች አድሏዊ እና የአባዊውን ዓለም አንጸባራቂዎች መሆናቸው ማየት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ወንዱ ከሴቷ ባልተናነሰ መንገድ በቀለኛና ጨካኝ ሆኖ ሳለ ግን ጨካኝ የሆነበትን አጋጣሚ አመክንዮአዊ ለማድረግ በእጅጉ ተጥሯል፡፡ የሁለቱ የጨካኝነታቸው መንስዔ የተለያየ ተደርጓል፡፡ ወንዱ በሴቷ ላይ ወይም በማንኛውም ሌላ ሰው ላይ የጭካኔ ተግባራትን ሲያከናውን የሚታየው ቀደም ብሎ ለተፈጸመበት በደል አጠፌታውን ለመመለስ በሚል ነው፡፡ ለምሳሌ በተረት 31 ውስጥ ባል ሚስቱ ውሽማዋን መቅጠሯን ሲያውቅ ገድሏታል፡፡ በተረት 51 ውስጥ ከሚስቱ ጋር ተኝቶ ያገኘውን ሰው አንገቱን ከቆረጠ በኋላ ሚስቱ ካገር እንድትጠፋ አድርጓታል፡፡ በተረት 67 ውስጥ ባል ሚስቱን በገበያ መሃል አዋርዶ ካገር መንና እንድትጠፋ ምክንያት ሆኗል፡፡ ተረት 60፣ ተረት 62 እና ተረት 66 ተመሳሳይ አፈጻጸም አላቸው፡፡ ወንድ ፍጹም ጨካኝ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ጭካኔው ግን ለበደሉ ማካካሻ ሆኖ ጨካኝ ሳያሰኘው ቀርቷል፡፡

በብዙ ተረቶች ውስጥ እንደሚታየው ወንዱ በሴቷ ላይ ፍቺ ከመፈጸም አንስቶ እስከመግደል የደረሰ እርምጃ የሚወስደው አንድም በላዩ ላይ ዝሙት ስትፈጽምበት፣ አለያም እንጀራ እናት በመሆኗ ምክንያት ልጆቹን ስትበድልበት ነው፡፡ ለጭካኔው ትክክለኛነት አሳማኝ ምክንያቶች ተቀምጠውለታል፡፡ አሳማኝ ምክንያት ባይቀርብ እንኳ የጭካኔው መንስዔ እሱ እንዳልሆነ ተቆጥሮ በሌላ ይሳበባል፡፡ ለምሳሌ ተረት 46 ውስጥ የባልና ሚስቱን የጋራ ንብረት እየሸጠ የሚደብቀውን ባል "ዳቢሎስ ልቡን በተንኮል

ሞላውና በጋራ ሰርተው ያፈሩትን ሃብት መደበቅና መሰወር ጀመረ" በሚል የጭካኔውን መንስዔ በዳቢሎስ ያመካኛል፡፡ የሴቷ ጭካኔ ግን ከላይ እንደተዘረዘረው ቅናት ከወለደው ስሜት፣ ምክንያቱን ካላወቅኩ ከሚል ግትር አቋም፣ ከጥላቻ ስሜት፣ ራስ ብቻ ለመጠቀም ካለ ፍላጎት ወዘተ. ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ምክንያትና ሰብዕና ለወንድና ለሴት ተለያይቶ በተረቶች ውስጥ መንጸባረቁ ወንድ በሴት ላይ እንዲሰለጥን ካለ ፍላጎት ይመስላል፡፡

## 5.1.3 ምስጢራዊነትና የባቄላ ወፍጮነት

ምስጢር በአንድ ግለሰብ ወይም በጥቂት ሰዎች ዘንድ ብቻ ተወስኖ ያለ ድብቅ መረጃ፣ ለሌላው የተሰወረ ነገር፣ የግል ጉዳይ የሆነ ማለት ነው፡፡ ምስጢር፣ ይፋ ያልሆነ ነገር፣ ድብቅ ጉዳይ ማለትም ነው (ኢቋጥምማ 1993፣49፣ ደስታ ተክለ ወልድ 1962፡818)፡፡ ይሄ ድብቅ የሆነ ነገር ይፋ ከወጣ ምስጢርነቱ ይቀራል፡፡ ምስጢር አውጭው ነገረኛና የማይታመን ተብሎ ምስጢር ይከለከላል፤ ማንም በበጎ ዓይን አይመለከተውም፡፡ ቁም ነገረኛ ከሚባሉ ሰዎች አይመደብም፤ ለበጎ ነገር ወይም ለኃላፊነት አይታጭም፡፡

ተረቶች ይህን አድራጎት በጽኑ ሲቃወሙትና ሲያጣጥሉት ይታያል፡፡ በዚህ ረገድ ደግሞ ብዙ የምትታማው (ምስጢር ባለመጠበቅ) ሴቷ ሆናለች፡፡ በተረት 5 ውስጥ እንደተጠቆመው አባት ወንድ ልጃቸውን ሲመክሩ "ለሚስትህ ምስጢር አትንገር" ይላሉ፡፡ በየትኛውም ተረት ውስጥ ሴቷን "ለባልሽ ምስጢር አትንገሪ" ተብሎ የተገለጸበት አላጋጠመም፡፡ ግን ይህ እውነት ነውን? ምስጢር ጠባቂ ሴት እና ምስጢር አባካኝ ወንድ የለምን? ነገሩ ግራ የሚያጋባ ቢመስልም የማይናጋ የሚመስለው አባዊው ርዕዮተ ዓለምና መዋቅሩ ይህንን ሊያደርግ እንደሚችል እንገምታለን፡፡ ምክንያቱም ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዙትን ተረቶች ስንመለከታቸው ሴቶች ለወንድ በሚጠቅም መልኩ በጎ ስራ ካላከናወኑ በስተቀር ስማቸው በጥሩ ሲነሳ አይስተዋልም፡፡ ራሷን ማዕከል አድርጋ በራሷ ውሳኔ ለራሷ የሚጠቅማትን ተግባር ብትፈጽም ትብጠለጠላለች፡፡

ምስጢርን ከመጠበቅና ካለመጠበቅ ጋር በተያያዘ ከተገኙት ተረቶች ውስጥ የሴትን ምስጢር አባካኝነት የሚያሳዩ አሉ፡፡ እንደ አብነት ተረት 5፣ 19 እና 73 ይጠቀሳሉ፡፡ እያንዳንዳቸውን በየተራ እንመልከት፡፡

ተረት 5 ላይ አባት ልጃቸውን ሲመክሩ "ለሚስትህ ሚስጥር አትንገር፣ ገመድ በቤትህ አትስቀል፣ ከበርህ አካባቢ ዛፍ አትትከል፣ ሎሌ አታስገባ፣ ከመንገድ ዳር እሸት አትዝራ"

ይሉታል። ልጁም ያባቱን ምክር ባለመቀበል ለማረጋገጥ ያህል ዛፍ ከግቢው ተከለ፤ ሎሌም አስገባ፤ ገመድም ከቤቱ ሰቀለ፤ መንገድ ዳርም ባቄላ ዘራ። እንዳጋጣሚ ሆኖ ባቄላውን አንድ ልጅ ሲበላ አገኘውና ልጁን ሌላ አገር ወስዶ በአደራ አስቀመጠው። ልጁም ካገር ሲጠፋ ሞቷል ተባለ። ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ቀን ሌሊት የአባቱን ምክር በመተላለፍ "የእገሌን ልጅ እኔ ነኝ ገድዬ የቀበርኩት" ሲል ለሚስቱ ነገራት። ሚስትም ስትቁነጠነጥ አድራ በጧት ተነስታ ምስጢር ነው ብላ ለጎረቢቷ ነገረቻት። ምስጢሩ እየተጣጣለ ሄዶ ከልጁ አባት ዘንድ ደረሰ። የልጁ አባትም በዳኛ ሞት አስፈረደበት።

እዚህ ላይ የሴቷን አበሳ ለማብዛት ሲባል ምስጢሩ በሴቷ በኩል እንዲዛመት ተደርጓል። በእርግጥም የባሏን ምስጢር አሳልፋ በመስጠቷ እንደ ጥፋተኛ ልትቆጠር ትችላለች። ይሁንና ምስጢር ተጠበቀ የሚባለው በባለቤቱ ብቻ ሲያዝ ነው። ከዚህ አንጻር ለምስጢሩ መዛመት ባልየው አስተዋጽኦ የለውም ወይ? እርሱ ያልቻለውን ምስጢር እንዴት ሌላ ሰው ሊጠብቅለትስ ይችላል? ይህንን ምስጢርስ ለወንድ ቢናገረው ኖሮ ሳይዛመት ይቀር ነበር? ባለምስጢሯ ሚስት ሆና ለባሏ ብታካፍለው ለሌላ ሳይናገር ይቀር ነበር? እነዚህን ሁሉ አስተውለን፣ ተጠየቃዊ ሆነን ነገሩን ብንመረምረው ሴቶች ሁሉ ምስጢር አባካኝ ናቸው በሚል "ምስጢርህን ለሚስትህ አትንገር" የሚል ማጠቃለያ ላይ አንደርስም ነበር።

እንደ አጥኚው እምነት የተረቱ አንድምታ በእጅ አዙር የአባዊውን ሥርዓት ርዕዮተ ዓለም ከነመዋቅሩ ሳይናጋ ማስጠበቅ እና ማስቀጠል ነው። የአባትየውም ምክር እዚሁ ላይ ያነጣጠረ ነው። የተረቱ የነገር መነሻ "ምስጢርህን ለሚስትህ አትንገር" የሚለው ምክር ነው። ሌሎቹ ምክሮች (ገመድ በቤትህ አትስቀል፣ ከበርህ አካባቢ ዛፍ አትትከል፣ ሎሌ አታስገባ፣ ከመንገድ ዳር እሸት አትዝራ) የዚህ ምክር ማጀቢያዎች፣ ያባትን ምክር አለመስማት የሚያመጣውን ጣጣ ምሳሌ በማቅረብ ለማስረዳት ያገለግላል ተብሎ በተነገረው ተረት ውስጥ የገቡ ናቸው። የታሪኩ ዋና ማጠንጠኛ እና የተራኪው ዓቢይ ዓላማዎች አይደሉም። ስለዚህ አባት "ለሚስትህ ምስጢር አትንገር" ሲሉ እግረ መንገዳቸውን ልጃቸው በሚስቱ ምስጢር አባኝነት እንዳይጎዳና በዚሁ ሳቢያ ጠንቃቃ እንዲሆን የማድረግ ፍላጎት እንዳላቸው እንገምታለን። ይሄ በሃይማኖትም የተደገፈ ይመስላል። ለምሳሌ በመጽሐፈ ሲራክ (25፡5) ውስጥ "ለሴት የልብህን ምስጢር

አታውጣ" በሚል የተቀመጠ ይገኛል፡፡ ይህም በምስጢር አያያዝ ሴትን እና ወንድን እኩል ባለማድረግ ስሜት ተገልጿል፡፡

ተመሳሳይ ጭብጥ ግን ለየት ያለ የታሪክ አካሄድ ያለው ተረት 19 ከላይ የቀረበውን የሴትን ምስጢር አባካኝነት አጉልቶ ያሳያል፡፡ ምስጢሩን ለባለቤቱ ካልሆነ በስተቀር ለማንም የማያወራው ባል ምስጢሩ እየባከነ እንደሆነ ያውቃል፡፡ ለዚሁም ባለቤቱ እንደሆነች ጠርጥሮ በጓደኛው መካሪነት ሊፈትናት ይነሳል፡፡

> *ባል. . . . ማታ እንደተኛ ጠዋት ሳይነሳ ይቀራል፡፡ ሚስቱም በመጨነቅ "ምን ነካህ? አመመህ እንዴ? . . . " ትለዋለች፡፡ ባሏም "በጣም አሞኛል፡፡ ሆዴ ይጮሃል፡፡ ይገለባበጥብኛል" ይላታል . . . ብዙ ከቆየ በኋላ ሚስቱን ይጠራና "ጉድ! ጉድ! ዛሬ ጉድ ሆንኩኝ፡፡ ይኸውልሽ ተገላገልኩ" ብሎ ደብቆ ይዞት የነበረውን እንቁላል ያሳያታል. . . . ቁርሱን አቅርባለት ከበሉ በኋላ ውሃ ልትቀዳ ትወጣለች፡፡ የወሬ ጓደኛዋን አብረው ውሃ እንዲቀዱ ትጣራና ወደ ውሃ መቅጃ ይወርዳሉ፡፡ ከመንገድም "ዛሬ በባሌ ላይ የደረሰውን ማውራት ያሳፍረኛል፤ . . . ጧት ሆዴን አመመኝ ብሎ ከመኝታው ላይ አርፍዶ ወዲያው እንቁላል ወልዶ ዳነ" ትላታለች፡፡ . . . . ወሬው እንዲህ እንዲህ እያለ ይዛመታል፡፡ ወሬውን ከሰሙት ውስጥ አንዷ ታመምኩ ወዳለው ሰው ቤት በፍጥነት ትሄድና ከተኛበት ጠጋ ብላ "እንኳን ማርያም በሠላም ገላገለችዎት" ትላለች፡፡ ሰውየውም "ምን ስለሆንኩ ነው ትቀልጃለሽ እንዴ?" ይላታል፡፡ ሴትዮዋም "እኔ ምን እቀልዳለሁ፤ ጧት ባለቤትዎ ውሃ መቅጃ ላይ አወራች ነው የተባለው . . . (ተረት 19)*

በዚህ ሁኔታ ጧት ለሚስቱ ያካፈላት ምስጢር ያውም ከጥብቅ አደራ ጋር የተናገረው በዚያው ቀን መልሶ ለራሱ ይደርሰዋል፡፡ ምስጢሩን ሊያወጣ የሚችል ሌላ የተደበቀ ወይም ባጋጣሚ በአቅራቢያቸው የነበረ ሰው ሰምቶ አወራብኝ እንዳይል እንኳ ወሬውን ከሰሙት ውስጥ አንዷ "ጧት ባለቤትዎ ውሃ መቅጃ ላይ አወራች ነው የተባለው" ስትል የሚስቱን ምስጢር አባካኝነት እቅጩን ነግራዋለች፡፡ ከዚህ አንጻር በተረቱ ውስጥ ያለችው ገጸባህሪ ምስጢር አባካኝ ተደርጋ ተስላለች፡፡

እዚህ ላይ ሴቷ ምስጢር አባካኝ ብቻ ሳትሆን ምስጢሩን ለሌላ ለማድረስ ካላት ችኩልነት የተነሳ ነገሮችንም ማገናዘብ የማትችል ተደርጋ ተስላለች፡፡ ሰው እንቁላል ሊጥል እንደማይችል ለቅንጣትም ቢሆን አላሰበችውም፡፡ በርግጥ ምስጢሩን ለሌላ ቶሎ ለማድረስ ካላት ጉጉትና ችኮላ የተነሳ እንዳታስበው አድርጓት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ በኩል ብናስበው ሴቶች ምስጢርን ለመሸከም አቅም የሚያንሳቸውና ምስጢርም መነገር የሌለባቸው እንደሆኑ አድርጎ ተረቱ ያሰርጻል፡፡

ተረት 80 ሴቶች ከምስጢር አባካኝነታቸው የተነሳ ለኃላፊነት ስለማይበቁ ሥልጣን እንደተከለከላቸው ያሳያል፡፡ በተረቱ ሴቶች ተሰብስበው መሳፍንት፣ መኳንንት፣ አገር ገዢዎችም ሁሉ ባሉበት "እኛስ ብንሆን ሰዎች አይደለንም?! ምነው አገር ግዛት ሹመት አይሰጠን" ሲሉ ያመለክታሉ፡፡ የተሰበሰቡት ታላላቅ ሰዎችም መልስ ለመስጠት ስለተጨነቁ ምክር ያደርጋሉ፡፡ ተሰብሳቢዎችም "ብንሾማቸው ሥርዓትና ፍርድ አያውቁ፤ አይሆንም ብንላቸው በየቤታችን ይበድሉናል" የሚል ክርክር ያነሳሉ፡፡ ብዙ ከተከራከሩ በኋላ "ወፍ እንያዝና ባገልግል ቆልፈን ከንጉሡ ዘንድ እንላካቸው፤ ያደረሱ እንደሆነ ይሾሙ ካላደረሱ ግን ይቅርባቸው" ብለው ወሰኑ፤ ለንጉሡም ይህንኑ ገለጹለት፡፡ ሲልኳቸውም "ይህንን እቃ ለንጉሡ አድርሱ፤ ነገር ግን ምስጢር ነውና ከፍታችሁ እንዳታዩት" ብለው አስጠንቅቀው ይልኳቸዋል፡፡ ሆኖም በውስጡ ያለውን ለማወቅ አንዲት እንኳ ከልካይ ሴት በሌለችበት አገልግሉን ከፈቱት፤ ወፏም በረረች፡፡ በወፏ ምትክ ባገልግሉ ውስጥ ሌላ ነገር አስገብተው ለንጉሡ አቀረቡለት፡፡ ንጉሡም የተላከው ያ እንዳልሆነ ባወቁ ጊዜ "በትንሹ ነገር ያልተጠነቀቃችሁ፣ ምስጢር ያልጠበቃችሁ ከፍ ያለ ሃላፊነት እንዴት ሊጣልባችሁ ይችላል?" ብለው ሹመት ከልክለዋቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ "ምስጢር ነው ከፍታችሁ እንዳታዩ" የሚል ማስጠንቀቂያ ቢሰጣቸውም አገልግሉን ከፍተውታል፡፡

ይሄ ተረት ሁሉንም ሴቶች በጅምላ ምስጢር አባካኝ ናቸው ያለ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም አገልግሉን ከፍተው ለማየት በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ሁሉም አንድ ዓይነቶች መሆናቸውን ለመጠቆም "በመካከላቸው አንድ እንኳ አይሆንም ባይ ጠፍቶ ባደራ የተቀበሉትን አገልግል ከፈቱት" በሚል ኮንኗቸዋል፡፡ ሁለተኛም በጅምላ መወቀሳቸውን በአንድምታ ልናወጣ እንችላለን፡፡ እነዚህ ሴቶች ሥልጣን ጠያቂዎች ናቸው፡፡ ለዚህ የበቁትም ከሌሎች በተሻለ የሴትና የወንድ እኩልነት ስለገባቸው፣ ሥልጣን ቢይዙ ከወንድ እኩል መስራት እንደሚችሉ በማመናቸው ሊሆን ይችላል፡፡ ስለዚህ እቤት ካሉት ሴቶች ጋር ስናነጻጽራቸው በእውቀትም በክህሎትም ሊሻሉ እንደሚችሉ እንገምታለን፡፡ በዚያ ላይ ሥልጣን ተሰጥቷቸው ቢሆን ኖሮ የሴቶች ተወካዮች ይሆኑ ነበር፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሥልጣን ጠያቂ ሴቶች ሌሎችን ሴቶች ሁሉ የወከሉ በመሆናቸው በእነርሱ ላይ የደረሰው ወቀሳ ለሁሉም ይሆናልና ሴቶች ምስጢር አባካኞች ናቸው የሚለው ሃሳብ ለሁሉም በጅምላ የተሰነዘረ ነው ለማለት መንገድ ይከፍታል፡፡

በሌሎችም ጥናቶች ውስጥ ከዚሁ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ተረቶች ያጋጥሙናል፡፡ ለምሳሌ በዩርባዎች ማንኛውንም ምስጢር ትጠብቃለች ተብላ የታመነባት የመጀመሪያዋ ሴት ምስጢሯን ለወንድ ጣዖት አሳልፋ በመንገሯና ባለመታመኗ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ሴቶች ሚስጥራዊ በሆነ ነገር እንዳይሳተፉ ተከልክለዋል፡፡ ይህ የተደረገው አንዷ ሴት ብቻ ምስጢር ስላወጣች ሁሉም እንደ እሷ ናቸው በሚል እምነት ይመስላል፡፡ ይሄ እስከ ቅኝ ግዛት ዘመን ድረስ ባህላዊ ወንድ መሪዎች ሥልጣናቸውን እንዳይነጠቁ በብዙ እንደረዳ እነ Olasupo and et al. (2012:14-15) Guardian (2003)ን ጠቅሰው ጽፈዋል፡፡ ሄዋን በሃይማኖቱ (ዘፍጥ. 3፡12-18)፣ ፓንዶራ በሚቱ (ቴዎድሮስ 2001፡46-52) ምስጢር በመተላለፋቸው ለምድር አበሳና መከራ አስከትለዋል መባሉን ልብ ይሏል፡፡ ይህ የአስተሳሰቡን ጥንታዊነት ያመለክታል፡፡

ከፍ ብሎ የቀረበው ትንተና ማኅበረሰቡ፣ ሴቶች ምስጢር አባካኝ ናቸው የሚልበትን ምክንያት በምሳሌ አቅርቦልናል፡፡ በዚህ ትይዩ ወንድ ሲገለጽ ግን አይስተዋልም፡፡ ይህም አለመሆኑ ሚዛናዊ ካለመሆኑም በላይ ተረቶች ራሳቸው በአባዊ ሥርዓቱ የተሰሩ ስለመሆናቸው፣ በወገናዊ ስሜት ስለመቀናበራቸው ምስክር ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ አንድ ነገር ሁልጊዜ ወደ አንድ አቅጣጫ ካደላ ልቡናችን መጠርጠሩ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ሴቶች ሁሉ ምስጢር አባካኝ ናቸው የሚል ድምዳሜ ላይ አያደርሰንም፡፡

## 5.1.4 ታማኝነት እና ከሃዲነት

ታማኝነት እውነትን ከመናገር፣ ቃልን ከመጠበቅ፣ ከማጭበርበርና ከማታለል ራስን ከማራቅ፣ የተሰጠን ሃላፊነት በብቃት ከመወጣት ወዘተ. ጋር ይገናኛል፡፡ ደስታ ተክለወልድ (1962፡109) ታማኝን እውነተኛ፣ ጻድቅ፣ የማይጠረጠር ብለው ይፈቱታል፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ በ1993 ዓ.ም ያሳተመው የአማርኛ መዝገበ ቃላት (ገጽ 388) "ካደ"ን ውል፣ ቃልኪዳን አፈረሰ ወይም ጣሰ፣ ቃሉን አጠፈ ሲለው ከሃዲን ደግሞ እምነት የማይጣልበት በሚል ይተረጉመዋል፡፡ እነዚህ ቃላት በዚሁ ትርጉማቸው ጥናቱ ላይ ውለዋል፡፡

እነዚህ በአንጻር የቆሙ ጽንሰ ሃሳቦች በተደጋጋሚ በተረቶች ውስጥ ይስተዋላሉ፡፡ ይህንኑ ከሴትና ከወንድ አንጻር ስንመረምረው በአብዛኛው ወንዱ በታማኝነት ሲመሰገን ሴቷ ደግሞ ባለመታመኗ ምክንያት አካላዊ ቅጣት ይደርስባታል፤ ግድያ ይፈጸምባታል፤ ንብረቷን ተቀምታ ከቤትና ከልጆቿ ተነጥላ እንድትባረር ይደረጋል፡፡ ብዙውን ጊዜ በሴቷ

ላይ እንዲህ ዓይነት ቅጣት የሚፈጸምባት በሚስትነቷ በባሏ ሳትረጋ ስትቀርና ከሌሎች ወንዶች ጋር ስትባልግ ከተገኘች ነው፡፡ ሆኖም ወንዱ ተመሳሳይ ነገር ቢያደርግ በሴቷ ትይዩ ቅጣት ሲፈጸምበት አይታይም፡፡

ቀደም ብሎ በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ እንደተጠቆመውና በተረቶች ውስጥ እንደተንጸባረቀው አንዲት ሴት በባሏ ላይ ስትወሰልት ብትያዝ ይቅርታ የሌለው ቅጣት ያስከትልባታል፡፡ ለወንዱ ግን እንደ ጀብዱ ባይቆጠር እንኳ ጠንካራ ነቀፌታ አይደርስበትም፡፡ ሴቷ በወንዱ ላይ የኃይል እርምጃ የመውሰድ ባህላዊ ፈቃድ ያላት አይመስልም፡፡ አጥኚው ይህንን ስሜት በሴቶች በተደረጉ ተተኳሪ የቡድን ውይይቶች ላይ (ኩታበር 15/08/2008፣ ቦረና 30/05/2008) ለመገንዘብ ችሏል፡፡ ለምሳሌ ለሴቶቹ "ባልሽ ባንቺ ላይ ሌላ ሴት ቢይዝብሽና ብታረጋግጪ ምን ታደርጊያለሽ?" ተብሎ ለቀረበው ጥያቄ ያለ ልዩነት "እንፈታዋለን" ሲሉ፣ ተመሳሳይ ጥያቄ የቀረበላቸው አንዳንዶች ወንዶች ግን ከመፍታት በተጨማሪ ሊደበድቡ እንደሚችሉ ጠቁመዋል (ቦረና 27/05/2008)፡፡ ይህ አንዱ የሥርዓተ ጾታዊ አድልዎ (gender inequality) ማሳያ ነው፡፡ ይህንን ከመስክና ከሰነድ በተገኙ ተረቶች ማሳያነት እንመልከት፡፡

በብዙ ተረቶች ውስጥ ሴት የማትታመን ወንድ ግን የሚታመን ሆነው ቀርበዋል፡፡ ለዚህ ተረት 8፣ 34፣ 48፣ 51፣ 55፣ 56፣ 65፣ 72፣ 73፣ እና ተረት 84 ጥሩ ምስክሮች ናቸው፡፡ ወንድ የማይታመን ሆኖ የቀረበበት አጋጣሚ በተረት 17 ብቻ ነው፡፡

ተረት 8 ውስጥ ባሏ ወደ ዘመቻ የሄደባት እመቤት ባለመታመን ከጠባቂዋ ጋር ለመወስለት ከፍተኛ ጥረት አድርጋ ጠባቂዋ ለጌታው ባለው ታማኝነት ጥያቄዋን ሳይቀበል ይቀራል፡፡ ይህንንም ባለማድረጉ እመቤቲቱ ለባሏ ሃሰተኛ ነገር አቀብላ የአገልጋዩን ህይወት ለማስቀጠፍ ጥረት ታደርጋለች፡፡ ሆኖም እሷው ባጠመደችው ተጠልፋ ትሞታለች፡፡

ሴቶች በተረቶች ውስጥ ውሸታሞችም ሆነው ቀርበዋል፡፡ በተለይም በባሎቻቸው፣ በእንጀራ ልጆቻቸው ላይ ሊፈጽሙት የነበረው በደል በአንድ አጋጣሚ ሊጋለጥባቸው ሲል የራሳቸውን ዘዴ ተጠቅመው በውሸት ለማምለጥና ሁኔታውን ለመቀየር ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ሆኖም ተራኪው በዘየደው ቴክኒክ ሴቷ በፈጠረችው የውሸት ሴራ ራሷ ተጠልፋ ቅጣቷን ስትቀበል ይታያል፡፡ ለዚህ ተረት 8 እና 48 ጥሩ ማሳያዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ተረቶች ቀደም ብለው እንደቀረቡት ሁሉ ሴቶች በወንዶች መዳፍ ስር እንዲሆኑ ሥነልቡናዊ ጫና የሚያሳድሩ፣ ወንዱን በአንጻሩ ሴቶች የሚያቀርቡትን ሃሳብ በጥርጣሬ ዓይን እንዲመለከት ትምህርት የሚሰጡ ናቸው፡፡ ተከታዩም ትውልድ ቢሆን በዚሁ ተቃኝቶ የአባዊው ማኅበረሰብ አባል እንዲሆን የማድረግ ሚና አላቸው፡፡ ይህንን ከመዋቅራዊ ግልጋሎታዊ ንድፈ ሃሳብ አንጻር ብንመለከተው የወንዶችን ሁለንተናዊ የበላይነት አስጠብቆ መዋቅሩ ባለበት እንዲቀጥል የማድረግ ሚና አላቸው፡፡

በተረት 55 ውስጥ ደግሞ ሴትዮዋ በባሏ ላይ በደል የፈጸመችውና ባሏ የጣለባትን እምነት ያጓደለችው ውሎ የማይመለስበት አገር እንደሄደላት ነው፡፡ በመሆኑም በወቅቱና በቦታው ተገኝቶ ጥፋቷን አረጋግጦ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አጋጣሚ የለውም፡፡ ሆኖም ግን በጥፋቷ ሳትቀጣ እንዳትቀር ባለ ፍላጎት ብቻ በተረቱ ውስጥ በተዋቀረ ተጠየቃዊ ቅንብር በአድሮ ሂያጅ መንገደኛ ተመትታ እንድትሞት ተደርጋለች፡፡ ይህ እንዴት እንደሆነ ከተረቱ ጠቅሰን እንመልከተው፡፡

> *. . . ውሽማ ቶሎ ብሎ ወደቆጡ አልጋ ወጣና ተሳፈረ፡፡ ሴትዮዋም እንደነገሩ ለመንገደኛው እራቱን አቅምሳ ውሽማዋን ተከትላ ወደ አልጋው ወጣች፡፡ ሴትዮዋ እንደገና ተመልሳ በመውረድ ለመንገደኛው፣ "ቀመ[በ]ኛ ጥጃ አለችና ልብስህን እንዳትበላብህ፤ ከመጣችብህ በዚህ ብትር ምታት" ብላ ብትር ሰጥታው ተመልሳ ወደ ውሽማዋ ሄደች፡፡*
>
> *በዚህ ጊዜ መንገደኛው ተንኮል አሰበ፡፡ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ ልቅም አድርጎ መብላትና መጠጣት ፈለገ፡፡ እናም ውሽማውና ውሽሚት ጉዳያቸውን ሲጀምሩ እንግዳው ቀስ ብሎ ተነስቶ የዶሮ ወጡንም ጠላውን ልቅም ካደረገ በኋላ ምንም እንዳልነካ ጥቅልል ብሎ ተኛ፡፡ ሴትዮዋ ጉዳይዋን ስትጨርስ ምግቡ ትዝ አላትና ልታመጣ ካልጋ ወረደች፡፡ ድስቱንም ገንቦውንም ብታይ ባዶ ሆኗል፡፡ "ጥጃይቱ ደፍታው ይሆን እንዴ" ብላ ጥጃይቱን ብታሸታት ምንም የለም፡፡ "አይ ይሄ እንግዳ በልቶታል፤ ጠጥቶታል ማለት ነው" ብላ እንግዳውን ቀረብ ብላ ልታሸት ስትጠጋ እንግዳውም ሁኔታዋን ነቅቶ እየጠበቀ ነበርና "ውስ!" ብሎ በተሰጠው አጭር ብትር አፍንጫዋን አላት፡፡ የመታትም እክፉ ቦታ ላይ ስለነበረ በዚሁ ምክንያት ሞተች . . . (ተረት 55)*

አድሮ ሂያጅ መንገደኛው ወደ እርሱ የመጣችው ሴትዮዋ እንጂ ቀበኛዋ ጥጃ አለመሆኗን ያውቃል፡፡ ምክንያቱም ነቅቶ ሲከታተላቸው ነበር፡፡ ሁለተኛም ሰውየው የሴትዮዋ ባል ይሁን ውሽማ በእርግጠኝነት የሚያውቀው ነገር የለም፡፡ ግን ጥርጣሬው ነበረው፡፡ ምክንያቱም ቤት ውስጥ ያለውን የሴትዮዋን ዝግጅትና ተፍ ተፍ ማለት ሲያስተውል የሰውየውን እንግዳነት ጠርጥሯል፡፡ ሴትዮዋ ምንም እንኳ እምነት አጉዳይ ብትሆንም መንገደኛው ግን እሷን ለመግደል የሚያበቃ ምንም ምክንያትና ሞራላዊ ብቃት

የለውም፡፡ የቀደመ እውቂያም ይሁን ከባሏ ጋር የስጋ ዝምድና ወይም ወዳጅነት የለውም፤ እንዲጠብቅም አደራ አልተሰጠውም፡፡ ተፈጥሯዊ የቅናት መንፈስ ካልሆነ በስተቀር የሚጠቀስ ምክንያት የለም፡፡ እንደ ምክንያት የተቀመጠችው ግን "ቀበኛ ጥጃ አለችና ልብስህን እንዳትበላብህ፤ ከመጣችብህ በዚህ ብትር ምታት" ብላ ሴትዮዋ ያስጠነቀቀችው ብቻ ናት፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ሴት ምንጊዜም በባሏ ቁጥጥር ስር እንድትውል ለማድረግ ነው፡፡ የተረቱ አንድምታ ባልሽ ባያይሽ እግዜር አይቶ እንዲህ ይፈርድብሻል ዓይነት ነው፡፡

ቅጣቱንም ስንመለከተው የመጨረሻ (የሞት) ነው፡፡ አባዊው ዓለም የሰራው መዋቅር ይህንን የሚታገስበት ሥርዓት ስለሌለው ከሞት ልታመልጥ አልቻለችም፡፡ በአብዛኞቹ ተረቶችም ውስጥ የሚያጋጥመን ይሄው ነው፡፡ ይህ በቀጥታ የወንድን የበላይነት የሴትን የበታችነት ያሳያል፡፡ ይህንን የምንልበት ሌላም አጋጣሚ አለ፡፡ ጥፋተኞቹ ወንዱም ሴቷም ናቸውና በተረቱ ውስጥ ሁለቱም ሲቀጡ ማየት ነበረብን፡፡ ተራኪው በመረጠው ዘዴ ወንዱ ሊቀጣ የሚችልበትን አጋጣሚ አልፈጠረም፡፡ ታሪኩ በሴቷ ሞት ብቻ ተጠናቅቋል፡፡ ይህ የሆነው ተረቱ የራሱ የሆነ አባዊ ዓላማ ስላለው፣ በሴቶች ላይ ያለውን የበላይነት ለማስጠበቅ ስለሚረዳው ነው፡፡

እንዲህ ዓይነቶቹ ተረቶች ሴቶች ለባሎቻቸው ታማኝ እንዲሆኑ በመፈለግ ለማስተማር ብሎም በሚያስከትለው ቅጣት ሌሎችን ለማስጠንቀቅ ያለሙ ናቸው፡፡ ለወንዱም ቢሆን ሴቶች ለባሎቻቸው ታማኝ አለመሆናቸውን አሳውቀው የቅርብ ክትትል እንዲያደርጉና እንዲቆጣጠሩ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ እነዚህን ነጥቦች ስንመረምራቸው ሴቷን የበታች ወንዱን የበላይ የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ይህ የበላይነትና የበታችነት ከጋብቻ መዋቅር አልፎ በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካው፣ በማህበራዊ ግንኙነቱና በባህላዊ ተቋማቱ ውስጥ ሰርጿል፡፡ እነዚህ ሁኔታዎች እውን ይሆኑ ዘንድ ሃይማኖት፣ ባህል እንዲሁም ህግ ያገዛቸው መሆኑን ለመረዳት በምዕራፍ አምስት (ሥርዓተ ጾታ እና ሥልጣን ከሃይማኖት፣ ከባህልና ከህግ አንጻር) የተገለጸውን ማየት ይበቃል፡፡ ዞሮ ዞሮ ዓላማው ወንዱ የፈጠረውን አባዊ ሥርዓት ተጠቅሞ ሴቷን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ተገልግሎበታል፡፡

ወንድ የማይታመን ሆኖ የቀረበበት አጋጣሚ ተረት 17 ላይ ነው፡፡ አንድ ሃብታም ነጋዴ ከአባቱ በውርስ ያገኘውን መሬት ለማስወሰን ወደ ገጠር ይሄዳል፡፡ ከአንድ ገበሬ ቤትም ያድራል፡፡ መሬቱን አስወስኖ ገበሬውን ወኪል ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ነጋዴው ባለመታመን የገበሬውን ሚስት አስከድቶ ይወስድበታል፡፡ ገበሬውም ቆይቶ ይህንን

ሲሰማ የነጋዴውን መሬት አንድም ሳያስቀር ሽጦ ይበላበታል፡፡ ነጋዴው ባለመታመኑ የተወሰደበት ርምጃ በህይወቱ ወይም በአካሉ ላይ ችግር የሚያመጣ ሳይሆን ተዳድሮበትና ጥቅም አግኝቶበት በማያውቀው መሬቱ ላይ ነው፡፡ እንደ ሴቶች በድብደባ ወይም በግድያ ሲቀጣ አይታይም፡፡

እዚህ ላይ ግልጽ ያልሆነው ነገር ሴቷ ብቻ ተለይታ ዝሙተኛና የማትታመን የተባለችበት ምክንያት ነው፡፡ መቼም በእኛ አገር ባህል ሴቷ ከሴት ጋር ዝሙት አትፈጽምም፡፡ ያው ከወንድ ጋር ነው፡፡ በዚያ ላይ የቆየው ልማድ የሚያሳየው ለፈቃደ ስጋዊ ግንኙነት ጠያቂው (መነሳሳትን ፈጣሪው) ወንዱ እንጂ ሴቷ አይደለችም፡፡ በእርግጥ ቀድማ አንዳንድ ምልክት እያሳየች ልታግባባው ትችል ይሆናል፡፡ ነገር ግን አፍ አውጥታ አትጠይቀውም፡፡ ታዲያ በወንዱ አግባቢነት (አታላይነት) ሴቷ ብትሳሳት የተለየ ቅጣት የሚፈጸምባት ለምንድን ነው? በወንጀል ረገድ የወንዱ አይበልጥም? ከእንስታውያን ወገን ሆነን ብንመለከተው ተረቶቹ የተነገሩበት ምክንያት ተጠየቃዊነት ይጎድላቸዋል፡፡ ጠቅለል ብሎ ሲታይ በተረቶች ውስጥ ሴቶች ለባሎቻቸው የማይታመኑ ሆነው ተስለዋል፡፡ ይህም በወንድ ቁጥጥር ስር እንዲውሉ እና ከሌላ ሰው ጋር በማይገናኙበት በቤት ውስጥ ስራ ላይ እንዲወሰኑ እንደ ምክንያት ተደርጎ ተወስዷል፡፡

ከላይ ስለመታመንና አለመታመን ስናነሳ በአብዛኛው ችግሩ ያለባቸውና እንደ ነውረኛ የተቆጠሩት ሴቶች ሆነዋል፡፡ ሌሎች ተረቶችም ይህንኑ በመድገም ሲያጠናክሩት ይታያል፡፡ እንዲያውም ሴቶች ከወንዶች በተለየ መልኩ የፈቃደ ስጋዊ ፍላጎታቸው ከፍ ያለ እንደሆነ ለማረጋገጥ ሲጥሩ ይታያል፡፡ ለማስረጃ ያህል ተረት 26ን እንመልከት፡፡

> *ጥንት ዱሮ ገና ሴትና ወንድ እንደተፈጠሩ ፈጣሪ የሴትንና የወንድን ስሜት ለማወቅ ፈልጎ ሙከራውን በሴትና በወንድ ፈረስ አደረገ አሉ፡፡ ፈጣሪ ከፍተኛ የመጠቃቃት ፍላጎት ያላቸውን ሴትና ወንድ ፈረሶችን አመጣ አሉ፡፡ ሁለቱንም ጥልቅ ገደል ካለበት አካባቢ ይወስዳቸዋል፡፡ ከዚያም ወንዱን ከገደል አፋፍ፣ ሴቷን ከገደሉ ስር ያደርግና ወንዱ ሊሰማት በሚችል መልኩ ሴቷ ፈረስ እንድትጮህ ትደረጋለች፡፡ ይህንን ጊዜ ድምጿን የሰማው ወንድ ፈረስ ወደ ገደሉ አፋፍ ብቅ ብሎ ሴቷን እንዳየ የአጸፋ መልሱን አስካክቶ ወደ ኋላ ይመለሳል፡፡ በተቃራኒው ሴቷን ፈረስ ከገደሉ አፋፍ፣ ወንዱን ከገደሉ ስር ሆነው ወንዱ እንዲያስካካ ይደረጋል፡፡ ድምጹን የሰማችው ሴት ፈረስ ወደ ገደሉ አፋፍ ብቅ ብላ ከገደሉ ስር ስታየው ስሜቷን መቆጣጠር አቅቷት ወደ እሱ ለመድረስ ስትል ገደሉ ውስጥ ዘልላ በመግባቷ ለሞት ተዳረገች፡፡ ይህንን የተመለከተው ፈጣሪም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ድፍረትን ለወንድ፣ ሃፍረትን ለሴት ሰጠ ይባላል (ተረት 26)፡፡*

በተረቱ ውስጥ እንደተመለከተው የፈቃደ ስጋዊ ስሜቱ ከወንድና ከሴት የማን እንደሚበልጥ ሙከራውን ያደረገውና ያረጋገጠው ፈጣሪ ሆኗል፡፡ ገና ተረቱ ሲጀምር ይህንኑ እናገኘለን፡፡ የሙከራው ባለቤት ፈጣሪ እንዲሆን የተደረገው ሆን ተብሎ በሙከራው ውጤት ላይ መታመንን ለማምጣትና ይሄው አስተሳሰብ እንዲሰፍን ለማድረግ በማሰብ ይመስላል፡፡ በፈጣሪ የተደረገ ነገር ቅሬታ አይቀርብበትም፡፡ ሙከራው በሰው ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ተዓማኒነቱ ዝቅተኛ ሊሆን ቅሬታም ሊያስነሳ ይችል ነበር፡፡

በተረቱ ውስጥ የተደረገው ሙከራ ተጨማሪ ውሳኔንም አስከትሏል፡፡ አንድ ሙከራ ተደርጎ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ "ምን ይደረግ?" መባሉ አይቀርም፡፡ እናም ፈጣሪ ውጤቱን መሰረት አድርጎ ድፍረትን ለወንድ፣ ሃፍረትን ለሴት ሰጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ ሴቷ ፈረስ ከወንዱ የበለጠ ፍላጎት ያላት ከሆነ ከወንዱ የበለጠ ለዝሙት ትጋለጣለች የማለትን ትርጉም ያመጣል፡፡ በመሆኑም ይሄ ባህሪዋ ከልክ በላይ እንዳይሆንና በፈለገች ጊዜ እንዳታደርገው ሃፍረት ባህሪዋ እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ወንዱ ግን ባሳየው የመረጋጋት ባህሪ ምንም ዓይነት እገዳ አልተጣለበትም፡፡ እንዲያውም በፈለገ ጊዜ እንዲፈጽመው የድፍረት ፈቃድ ተሰጥቶታል፡፡ ይህ ዞሮ ዞሮ ወንዱ ሴቷን በበላይነት መቆጣጠር እንዲችል የታቀደ ዘዴ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ዓይነት ተረት በናይጀሪያ የዩርባ ተረቶችም ውስጥ ይገኛል (Olasupo, Victoria and Ajuwon 2012:12)፡፡ ጥንት በዩርባ ሴቶችና ወንዶች በየራሳቸው ንግስትና ንጉስ ለየብቻቸው በተለያየ ከተማ ይኖሩ ነበር፡፡ ሆኖም ሴቶቹ ታግሰው ብቻቸውን መኖር ስላልቻሉ በንግስታቸው እየተመሩ ወደ ወንዶች ከተማ ይሄዳሉ፡፡ ከወንዶች ጋር ሳይቀላቀሉ ባቅራቢያቸው ይሆናሉ፡፡ የወንዶችን ስሜት ለማነሳሳትና ወደ እነርሱ እንዲመጡ የተለያዩ ምልክቶችን በእጃቸውም በአካላቸውም በማሳየት ለማባበል ቢሞክሩም ወንዶች የሚነኩ አልነበሩም፡፡ ወንዶችም ባሉበት ሆነው እንዲሁ ያደርጉ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ብዙ ከቆዩ በኋላ ወንዶች ወደ ሴቶች ሄደው ጋብቻ ፈጽመዋል፡፡ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ወንድ ጠያቂ ሴት ተጠያቂ ሆነዋል፡፡ በዚህም ተረት ውስጥ ስሜታቸውን ባለመቆጣጠር የታሙት ሴቶች ናቸው፡፡ ምክንያቱም ወደ ወንዶች ከተማ ለዚሁ ተግባር መሄዳቸውን ይጠቁማል፡፡ በዚህም ባህሪያቸው ቁጥጥር እንደሚያስፈልጋቸው በማመን ጠያቂ እንዳይሆኑ ተደርገዋል፡፡ በተመሳሳይ በ Sahilu (1996 234-235) ጥናት ውስጥ ሴት ፈቃደ ስጋዊ ፍላጎቷን ልትቆጣጠር እንደማትችል ከመስክ ያገኙት ተረት ያሳያል፡፡ እነዚህ የአስተሳሰቡን ተመሳሳይነት ያሳያሉ፡፡

በጥቅሉ ከላይ ትንተና የተሰጠባቸው ተረቶች የሴቶችን ገጽታ አዛብተው ከወንድ አንሰው እንዲታዩ አድርገዋል፡፡ ይህ የሰብዕና ዝቅተኛነት ሴቶች ከቤት ወጥተው ወንዱ በዋለበት እንዳይውሉ፣ ወንድ የያዘውን እንዳይዙ፣ በቤታቸው እኩልነት እንዳይኖራቸው ወዘተ. ተጽዕኖ ሊያደርጉ ይችላሉ፡፡ ከዚያም በላይ በባህሉ ውስጥ ያለውን ሥርዓተ ጾታዊ አስተሳሰብ ያንጸባርቃሉ፡፡

## 5.1.5 ውሸታምነት እና እውነተኛነት

በማኅበረሰቡ ውስጥ ከማይፈለጉ ባህሪያት ውስጥ አንዱ ውሸታምነት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሚፈልጉትን ለማግኘት ወይም ከገቡበት ችግር የመውጫ አማራጭ ሲያጡ መዋሸትን እንደ አማራጭ የሚጠቀሙ ይኖራሉ፤ አሉም፡፡ መዋሸት ባህሪያቸው ስለሆነ ብቻ ያለምንም አስገዳጅ ምክንያት እንዲሁ ሃሰት የሚናገሩ፣ የሚያወሩ ይኖራሉ፡፡ ይህንን ተግባር የሚያንኳስሱና ለመቆጣጠር ጥረት የሚያደርጉ ተረቶች በብዛት ይስተዋላሉ፡፡ ከሴትና ከወንድ በአንፃራዊነት በንጽጽር ስንመለከተው በተረቶች ውስጥ የበለጠውን የውሸታምነት ድርሻ ይዞ የሚገኘው ወንዱ ነው፡፡ ሴቶች እንዲያውም በመዋሸት ፋንታ በድፍረት ሂሶችን ሲሰነዝሩ ይታያሉ፡፡ ይህ ሲባል የሴት ውሸታም የወንድ እውነተኛ የለም ማለት አይደለም፡፡ በዚያ ላይ ወንድንና ሴትን ከእውነተኛነትና ከውሸታምነት አንጻር እያነጻጸርን የተሰጣቸውን ገጽታ ስንመለከት ከሴትና ከወንድ መስተጋብር ጋር ባለው ሁኔታ የጠበበ አውድ ይዘን ነው፡፡ ይህንን ባጭሩ በተረቶች እያዋዛን እንመልከተው፡፡

ብዙውን ጊዜ በወንዶች በኩል የሚታየው ውሸት፣ ያልሆነውን ሆኖ ሴቶችን ለመቅረብና በፍቅር ለማማለል ነው፡፡ በተረት 54 ውስጥ ዝንጀሮው የአንበሳውን ሚስት የቀረበውና ያታለላት በዚሁ መንገድ ነው፡፡

> *በድሮ ጊዜ አንድ አንበሳና አንዲት ዝንጀሮ ተጋብተው አብረው ይኖሩ ነበር . . . አንበሳውም ሚስቱ ስትወልድ አልጋ ሰርቶ ማረስ ጀመረ፡፡ ከእለታት አንድ ቀንም ለማረሻ የሚሆን ምግብ ፍለጋ ወደ ጫካ ሄደ፡፡ አንድ መሄዱን ያየ ግመሬ ዝንጀሮ ወደ አንበሳው ቤት እየተንጎማለለ ሄደ፡፡ ከቤቱ አጠገብ እንደ ደረሰም "እዚህ ቤት!" አለ፡፡ የአንበሳው ሚስትም ከቤት ውስጥ ሆና "አቤት!" አለች፡፡ "አያ አንበሶ የለም እንዴ?" አለ፡፡ "የሉም" አለችው፡፡ ዝንጀሮ "የእኔና የእሱ ወንድነት ዛሬ ይለያል ብዬ ነበር" አለ፡፡ "ይግቡ ማነሁ? አሁን ወጣ ብለው ነው" አለች አራሷ ዝንጀሮ፡፡ ዝንጀሮውም ገባና ቁጭ አለ፡፡ የአንበሳውም ሚስት "ጥያቄ ባቀርብልሁ ቅር ይልኋል?" አለችው፡፡ ዝንጀሮም "ምንም ችግር የለም ጠይቂኝ" አለ፡፡ እሷም "ለመሆኑ የቀድሞ ስራዎ ምን ነበር?" አለችው፡፡ "ወታደር" አለ፡፡ "ዓይንዎ የጎደጎደው ምን ሆኖ ነው?" በማለት ጥያቄዋን*

*ቀጠለች፡፡ "ጥይት ተኳሽ ስለሆንኩኝ የማነጣጥርበት ነው" ብሎ መለሰ፡፡ "ጣትዎ የሰለሰለውስ" ብላ ስትጠይቀው "ምላጭ የምስብበት ነው" ብሎ መለሰ፡፡ "ቂጥዎ የተመለጠውስ?" ስትለው "ፈረስ ጋላቢ ስለሆንኩኝ ነው" አለ፡፡ በመጨረሻም "ደረትዎ የተመለጠውስ?" በማለት ስትጠይቀው "ይሄማ ሰደፍ የማስደግፍበት ነው" በማለት መለሰላት፡፡ ዝንጀሮዋ በጣም በመገረም፣ ባሏንም በልቧ በመናቅ የሚበላ ጥሩ ምግብ ሰጠችው፡፡ በልቧም የእኔ ባል ቢሆን ብላ ተመኘች፡፡ በዚህም አልቀረች እንደምንም አግባብታ አብራው ተኛች፡፡ ዝንጀሮው የልቡን አድርሶ የቀረበለትን ጥሩ ምግብ በልቶ ወደ መጣበት ተመለሰ፡፡*

*ከትንሽ ቆይታ በኋላ አቶ አንበሳ ከሄደበት ተመለሰ፡፡ እንደመጣም ሚስቱ ጥቅጥቅ ብላ አኮረፈችው፤ ጀርባዋን ሰጠችው፡፡ አቶ አንበሳም "ምን ሆነሽ ነው ያኮረፍሽኝ?" ሲል ጠየቃት፡፡ እሷም በመቆጣት ስሜት የዝንጀሮን የጀግንነት ታሪክ ከነገረችው በኋላ "አንተ ደግሞ ምን ወንድ ነህ? አለችው . . . (ተረት 54)*

ዝንጀሮው ውሸቱን የተጠቀመበት የአንበሳውን ሚስት በፍቅር ለመጣል ካለው ፍላጎት ነው፡፡ እውነት አስመስሎ ያወራው ውሸት ለአንበሳው ሚስት እውነት መስሎ ስለታያት ለባሏ የነበራት ታማኝነት ቀስ በቀስ ተሸርሽሯል፡፡ ለማረጋገጥም ካላት ፍላጎት አጥብቃ ስትጠይቅ ትታያለች፡፡ ደግሞም በዝንጀሮው አካል ላይ የሚታዩት "የጀግንነት ምልክቶች" እና ለምልክቶች እሱ (ዝንጀሮው) የሰጣቸው ምክንያቶች ተገጣጥመዋል፡፡ ዝንጀሮው ለዓይን መጎድጎድ - ማነጣጠርን፣ ለጣት መሰልሰል - ምላጭ መሳብን፣ ለቂጥ መመለጥ - ፈረስ ጋላቢነትን፣ ለደረት መመለጥ - ሰደፍ ማስደገፍን በምክንያትነት አቅርቧል፡፡ በዚህም የተነሳ ለዝንጀሮው ፍቅር ታሳያለች፡፡ ቀስ በቀስም ይህንኑ ፍላጎቷን ባሏን በልቧ በመናቅ፣ ለዝንጀሮው ጥሩ ምግብ በመስጠት፣ ዝንጀሮውን የእኔ ባል ቢሆን ብላ በመመኘት ገልጻለች፡፡ እንዲያውም ለዝንጀሮው ካላት ፍቅር የተነሳ ባሏን "አንተ ደግሞ ምን ወንድ ነህ?" ስትል በድፍረት ተናግራለች፡፡ ይህ ሁሉ የሆነው ዝንጀሮው አቀነባብሮ ባቀረበው ውሸት የተነሳ ነው፡፡

ዝንጀሮው ውሸቱ ተሳክቶለት የፈለገውን ፈጽሟል፡፡ ውሸቱ ከተጋለጠበት በኋላ ግን የአንበሳው ሚስት ለባሏ እጥፍ ከበሬታ አድርጋለታለች፡፡ የተረቱም ዋና ጭብጥ ይሄው ነው፡፡ ምክንያቱም የተረቱ አብዛኛው ታሪክ በዝንጀሮው ውሸት ላይ ያነጣጠረ ቢሆንም ማሳረጊያው ግን ምንም ቢሆን ሴት ለባሏ ከበሬታ መስጠት የሚገባት መሆኑን ማሳየት ነው፡፡ ሚስቶች በሌሎች ወንዶች ውሸት የባሎቻቸውን ክብር መቀነስ የለባቸውም፤ ምንም ቢሆን ከባሎቻቸው ውጭ ሌላ ነገር እንዳያስቡ ለማድረግ የተሰራ ነው፡፡

ወንድ ድክመቱን ለመሸፈን ውሸትን እንዳማራጭ ሲጠቀም ይታያል፡፡ ለምሳሌ በተረት 27 ውስጥ ዝንጀሮው ጠንክሮ ከመስራት ይልቅ ስንፍናን መርጧል፡፡ ሚስቱ የሰጠችውን

የባቄላ ዘር ቆርጥሞ በልቶ ግን ዘርቻለሁ ብሏታል፡፡ በአዝመራ ስብሰባም ወቅት እሌላ የባቄላ ሰብል ውስጥ ቤተሰቡን አስገብቶ ባለቤቱ ቢያባርራቸው ለሚስቱ "አይ! በጉልበት ሲቀሙን አታውቂም? እንግዳ ይህ ዓይንሽ የሚያየው የባቄላ ሰብል በሙሉ የእኛ ነበር" ሲል ዋሽቷታል፡፡

በአንጻሩ ሴት ውሸትን ፊትለፊት ስትጋፈጥ ትታያለች፡፡ ትልልቅ ማኅበራዊ ሂሶችን በድፍረት ትሰነዝራለች፡፡ አንዳንዶቹ ትችቶቻቸው ማኅበራዊ ስምምነቶችን ሁሉ የጣሱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በእኛ አገር ልማድ የሞተ ሰው አንገተ ቅጥል ነው እስከሚባል ድረስ ያልሆነውን እንደሆነ አድርጎ እና ደካማ ጎኖቹን ትቶ የሚችን የህይወት ታሪክ ጽፎ በቀብር እለት ማንበብ የተለመደ ነው፡፡ ይህ ባለበት አጋጣሚ ሴቶች በተረቶች ውስጥ የሚሰነዝሩት ሃሳብ ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው፡፡ ተረት 59 ይህንኑ ይናገራል፡፡ ዝንጀሮው ከልጁና ከሚስቱ እየተነጠለ በመሄድ ያገኘውን በልቶ ሆዱን ሞልቶ በየጊዜው ወደቤቱ ይመለስ ነበር፡፡ ለልጁና ለሚስቱ ግን ምንም አያመጣላቸውም ነበር፡፡ በዚህም ልጅ እና ሚስቱ የአባወራነቱን ሚና ባለመወጣቱና በብቻ በልነቱ ያዝኑበት ነበር፡፡ ልጅና ሚስቱ ቢያገኙ ቀምሰው፣ ካገኙት እሱንም አቃምሰው፣ ካጡ ግን እንዲሁ ያድሩ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ሲኖሩ ባል ሲሰርቅ ይያዝና ይገደላል፡፡ በቀብሩም እለት ሚስቱ በሙሾ፣

እንኳን ጥይትና ይፍላብህ በረዶ፣

አላቀመስከኝም ከሰረቅከው ነዶ፡፡

ስትል ክፉነቱን አጋልጣለች፡፡ ሴቶች ለሃቅ ሲሉ ማኅበራዊ ስምምነቱን የጣሰ ግን እውነት የሆነን ከማኅበራዊ ስምምነቱ አፈንግጠው ከመናገር ወደኋላ የማይሉ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ይህንኑ ይዘት የሚያረጋግጥ በተረት 46 ላይ እናገኛለን፡፡

ባል ሚስቱን መፍታት ይፈልጋል፡፡ ንብረታቸውንም እንዳትካፈለኝ በሚል ከፍቺ በፊት ሙልጭ አድርጎ ይሸጥና ይደብቅባታል[45]፡፡ ይህንን ካደረገ በኋላ በሽማግሌ ፍቺ ይጠይቃል፡፡ እሷም ንብረት እንዳላት ብታውቅም ይሄ አለን ብላ ለሽማግሌ ማሳየት

[45] ይህ አቀራረብ ወንዱ በቤተሰቡ ውስጥ ያለውን የኢኮኖሚ ቁጥጥር በበላይነት መያዙን እንመለከትበታለን፡፡ ምክንያቱም ባልና ሚስቱ አንድ ላይ እየኖሩ ንብረታቸውን እያወጣ ሲሸጥ ሴቷ ጥያቄ አታነሳም፡፡ ለምን ዓላማ እየሸጠ እንደሆነ፣ ንብረት ተሽጦ የተገኘው ገንዘብ ምን ላይ እንደዋለ ወይም ምን እንዳሰበ ስትጠይቅ አትስተዋልም፡፡ ይህ በቀጥታ በጋራ ንብረታቸው ላይ የማዘዝ ሥልጣን እና መብት እንዳልተሰጣት ያሳያል፡፡ ይህ ጾታን መሰረት ያደረገ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በዚህ ተረት፣ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን መስተጋብር መፍጠራቸውን እንመለከትበታለን፡፡

ስላልቻለች ባዶ እጇን ትወጣለች፡፡ ለየብቻቸው እየኖሩ እንዳሉ አንድ ቀን ሞተልሽ ተብላ ለቅሶ ትሄዳለች፡፡ በእለቱም፡-

ያንተማ አቀባበር መቼ እንደዚህ ነበር፣

ከስር ቀጋ አድርጎ ከላይ አጋም ነበር፡፡

ስትል በቀብሩ ቀን እንኳን ዋሽታ ከእውነታው ፈቀቅ ለማለት አልሞከረችም፡፡ ጎረቤቶቿ፣ "ተይ እንደዚህ አይባልም፡፡ እሱ እንደሁ አንድ ጊዜ ሙቷል ተነስቶ አይሰማሽ፡፡ ለምን ሙት ወቃሽ ትሆኛለሽ! ደግሞ እኮ ሊሞት ሲል በሬና ላም ተናዞልሻል" ቢሏት እንኳ፣

ላሚቱንም ሰጥቶኝ ከእንግዲህ አልወደው፣

በሬውንም ሰጥቶኝ ከእንግዲህ አልወደው፣

ተሸክሞት ይሂድ እሱን ካልከበደው፡፡

በማለት ለእውነት መቆሟን በድጋሚ አረጋግጣለች፡፡ ሌሎች ሊያስዋሿት ቢሞክሩ እንኳ ፈቃደኛ አልሆነችም፡፡ ከመስክም የተገኘው መረጃ ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡ አንድ ቁልፍ መረጃ አቀባይ (ወንድ) በጎረቤታቸው ገጠመ ያሉትን ሲገልጹ፡-

> *". . . አጋጣሚ ምሳሌውም አለኝ፡፡ እዚህ ኮሸሚ (የሰፈር ስም ነው) አካባቢ ነው፡፡ ሰውየው እቤቱ ሰክሮ ይሄዳል፡፡ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል፡፡ (የሰውየው ስም ተጠቅሷል) እና ሲገባ ከብቶቹ ጮሁ፡፡ ሴትዮይቱ (ሚስቱ) ውስጧ ተቆጥቷል፡፡ መናገር ግን ትፈራለች፡፡ "ኧረ ዛሬ ከብቶች ጮሁሳ! አላገኙም እንዴ?" ሲላት "አይ አተላው ሽቷቸው እንደሆነ እንጂ ገለባስ ሰጥቻቸዋለሁ" አለችው (ቦረና ወረዳ፣ ተተኳሪ ቡድን ውይይት 27/05/2008)*

በማለት የሴቶችን እውነተኛነትና በድፍረት ተናጋሪነት አስረድተዋል፡፡ ሰትዮዋ "አተላው ሽቷቸው እንደሆነ እንጂ" ሲሉ የባላቸውን ሰካራምነት በአሽሙር ነግረውታል፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን ተረቶች እና ገጠመኙ በጥቅሉ የሚያሳዩት ሃቅን በመናገርና ማኅበራዊ ህጸጾችን በማረም ሴቶች የተሻሉ መሆናቸውን ነው፡፡ ምናልባት ይህን የመሰለው ብቃታቸው ለአባዊው ሥርዓት አይመችም ካልተባለ በስተቀር ችሎታቸው እየታወቀ ህዝብን ሊያገለግሉ በሚችሉባቸው ቦታዎች ለመታጨት አለመቻላቸውና ሃላፊነቶችን የወንድ ያህል አለመያዛቸው እንቆቅልሽ ነው፡፡

## 5.1.6 አዛዥነት እና ታዛዥነት

በዚህ ጥናት ውስጥ አዛዥነትና ታዛዥነት ጥቅም ላይ የዋሉት የበላይና የበታች፣ ተገልጋይና አገልጋይ፣ አሳዳሪና ተዳዳሪ ወይም መሪና ተመሪ ለሚሉት ጽንሰ ሃሳቦች

ነው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993፡333) “አዛዥ”ን የበላይ ሃላፊ፣ አለቃ፣ የንብረት ሹም፣ አስተዳዳሪ እንዲሁም ታዛዥን እሺ ባይ፣ አገልጋይ በማለት ይፈታዋል፡፡ ቃሎቹ የተሰጣቸው ትርጉም ከዚህ ጥናት ሃሳብ ጋር የሚሄድ በመሆኑ በዚሁ ትርጉማቸው ውለዋል፡፡

ከጥንት ጀምሮ የተሰሩት ቤተሰባዊም ይሁኑ ማኅበራዊ መዋቅሮች ሴቶች ባብዛኛው የባሎቻቸው ታዛዥና አገልጋይ እንዲሆኑ ይደነግጋሉ፡፡ ሃይማኖቶችም ይህን ይሰብካሉ፡፡ ለምሳሌ በክርስትናው ዘፍጥ.2፡18፤ ኤፌ.5፡22፤ 1ኛ ጴጥ.3፡1-6 እንዲሁም በእስልምናው ሱራ 4፡34 በዋናነት የሚጠቀሱ አንቀጾች ናቸው፡፡ ይህንን የመሰለው አስተሳሰብ በበርካታ ተረቶች ውስጥ ተንጸባርቆ ይታያል፡፡ አስተሳሰቡ አሁንም ድረስ ያለ ስለመሆኑ በቡድን ውይይት ወቅት አብዛኞቹ ሴቶችና ወንዶች አረጋግጠዋል፡፡ ለምሳሌ በረና ወረዳ አንዲት መረጃ አቀባይ ስለ አዛዥና ታዛዥ ተጠይቀው ሲመልሱ “እንኳ በራሴ ዝም ብዬ ሳስበው እንደ አባወራም እንደ ትልቅነትም ያው የበታችነታችን ስላልወጣልን በእሱ ነው የምተዳደረው” (27/05/2008) ሲሉ አስረግጠዋል፡፡ ወንዶችም በቡድን ውይይት ወቅት ይህንኑ ደግመውታል፡፡ “እንዲያውም የእኔን ካልተቀበለች እቆጣለሁ . . . በኢኮኖሚ እኔ ባልኩሽ ሂጂ ነው የምላት፡፡ ከመቶ ሰማኒያ የሚሆነውን ያህል እኔ ባልኳት ይሆናል፡፡ የበላይነቴና አዛዥነቴ አሁንም አለ” ሲሉ አንድ አባት ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል፡፡ በተረቶችም በተጠያቂዎችም ዘንድ ያለው ሃሳብ ሴቶች በአካላዊ፣ በአዕምሯዊ እና በመንፈሳዊ ጥንካሬያቸው ከወንዶች ያንሳሉ የሚለውን አባዊ ርዕዮተ ዓለም፣ እንዲሁም ባህላዊና ማኅበራዊ አስተሳሰብ ያጠናክራል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሴቶች ካለባቸው የጉልበት (energy) ውስንነት አንጻር (ከወንዶች ጋር ሲነጻጸሩ) የወንዶችን ጥበቃ የሚሹ ይመስላል፡፡ ለዚህ ማሳያው በስፋት የሚነገሩት ተረቶች ናቸው፡፡

በአንጻሩ ደግሞ ወንድ ጉልበተኛ ተደርጎ ስለሚወሰድ በሴቶች ላይ የአዛዥነት ሚናን ተጎናጽፏል፡፡ በዚያ ላይ ወንድ ልጅ ጀብደኛ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡ አሽንፎ እንጂ ተሸንፎ እንዲገባ አይፈለግም፡፡ ይህን የመሰለው መዋቅራዊ አስተሳሰብ በሴትና በወንድ በኩል ያለውን የሥልጣን ክፍፍል የአዛዥነትና የታዛዥነት ሳያደርገው እንዳልቀረ የመስኩ ምሁራን ያስረዳሉ (Wood & Eagly 2002, 704-705)፡፡ ባል ሚስቱን እንዲገስጽ፣ እንዲቀጣ፣ የቤቱ ኃላፊ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ ይህም ብቻ አይደለም ባል የሚስቱን ባህሪ እሱ ያዋጣኛል ባለው መንገድ የማስተካከል፣ የመገሰጽ እና በእርሱ መንፈስ

የመቅረጽ እድሉም የተሰጠው ይመስላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ አድራጎት ሳይደናቀፍ እንዲቀጥልና ተከታዩም ትውልድ በዚሁ እንዲታነጽ በማድረግ ተረቶች ሚናቸው ትልቅ ነው፡፡ ለዚህ ማሳያ የሆነውን ተረት ጠቅሰን እንመልከት፡፡

> *አንበሳ ሚስት አግብቶሲኖር በጠና ታመመ ይባላል፡፡ የዱር እንስሳት እየተሰበሰቡ መጥተው ይጠይቁታል፡፡ ሚስቱ የመጡትንና ያልመጡትን ስትመለከት ያልመጣው ቀበሮ ብቻ ሆኖ ታገኘዋለች፤ እሷም ለባሏ "ቀበሮ ምን ቢንቅህ ነው መጥቶ ያልጠየቀህ?" ስትል አንበሳን ትጠይቀዋለች፡፡ "ስለዚህ እሱን ጠርተህ መግደል አለብህ" ስትል ትነግረዋለች፡፡ አንበሳም በሚስቱ የሚመራ ነበርና ቀበሮን ለመግደል ይጠራዋል፡፡ ቀበሮ ሳይመጣ ይቀራል፡፡ አንበሳም "ይሄ ጠግቧል ቢታዘዝ እንዴት ሳይመጣ ይቀራል" ይልና ይናደዳል፡፡ ከዚያ ቀበሮ ብዙ ዘግይቶ ይመጣል፡፡ አንበሳም "ትዕዛዜን ለምን አልፈጸምክም? ባልኩህ ቀን ለምን አልመጣህም?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ቀበሮም "ስራ ላይ ሆኜ ነው ሳልመጣ የቀረሁት እንጂ የእርስዎን የአለቃዬን ትዕዛዝ ላለመፈጸም አይደለም" ይለዋል፡፡*
>
> *አቶ አንበሳም "ምንድን ነው ከእኔ ትዕዛዝ ያስቀረህ?" ይለዋል፡፡ "እኔ የያዝኩት ስራ ከዛፎች መካከል የደረቁትንና ያልደረቁትን፤ ከሰዎች መካከል ደግሞ ሴቶችንና ወንዶችን ስቆጥር ነበርኩኝ" ይለዋል፡፡ አንበሳም "ታዲያ ማን በዛ?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ "ከዛፎቹ መካከል ሊደርቁ ያሉትን ከደረቁት ጋር ስደምራቸው ካልደረቁት ይበልጣሉ፡፡ ከሰዎች መካከል ደግሞ የሴቶችን ትዕዛዝ የሚቀበሉትን ወንዶች ከሴቶች ጋር ስደምራቸው ሴቶቹ በዙ" ይለዋል፡፡*
>
> *አንበሳ ደንገጥ ይልና "ታዲያ የሴቶችን ወሬ የሚሰማ ከሴቶች ጋር ነው የሚመደበው?" ይለዋል፡፡ "ታዲያስ! በሴት የሚመራ ወንድ ዞሮ ዞሮ ጾታው ወንድ ቢሆንም ከሴት ተመድቧል" ይለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ "አንበሳ ታዲያ ከሴት ልቆጠር ነው?" ይልና ቀበሮውን ሳይገድለው ቀረ ይባላል (ተረት 15)፡፡*

በተረቱ ውስጥ የማኅበረሰቡ የአዛዥነትና የታዛዥነት አስተሳሰብ እንዴት እንደሰረጸ ሴት፣ በሴት የሚታዘዝ ወንድ እና ለሴት የማይታዘዝ ወንድ የተመሰሉበትን እንመልከት፡፡ ሴት በደረቅ እንጨት፣ በሴት የሚታዘዝ ወንድ ሊደርቅ ባለ እንጨት እና ለሴት የማይታዘዝ ወንድ በእርጥብ እንጨት ተመስለዋል፡፡ ተረቱ ከሰጠው ውክልና አንጻር ሴትንና በሴት የሚታዘዝን ወንድ ባንድ መድቧቸዋል፡፡ ተረቱ ለሴት ባለው ዝቅተኛ ግምት በሴት የሚታዘዘውን ወንድ ማንነቱን ቀይሮ ከሴት ወገን መድቦታል፡፡ እየሞተ ባለ እርጥብ እንጨት መስሎታል፡፡ ይህም መሆኑ ሴት በወንድ ላይ ምንም ዓይነት ያዛዥነት ሥልጣን እንዳይኖራት ከመንፈጉም ሌላ በሚታዘዙት ላይ የማንነት ለውጥ አድርጓል፡፡ ቀበሮ በሚስቱ ለታዘዘው አንበሳ "በሴት የሚመራ ዞሮ ዞሮ ጾታው ወንድ ቢሆንም ከሴት ተመድቧል" በሚል ቁርጥ ያለ ማስጠንቀቂያ መሰል ሃሳብ ሰንዝሮለታል፡፡ በዚሁ ምክንያት ለጊዜውም ቢሆን በሚስቱ ቀስቃሽነት ቀበሮን ሊገድል የነበረው አንበሳ በሴት ታዘዘ ላለመባል ቀበሮን በሰላም አሰናብቶታል፡፡ አንበሳው ይህንን ያደረገው በደሉ ሳይሰማው ቀርቶ ወይም ቀበሮ ሳይጠይቀው የቀረበት ምክንያት

አሳምኖት ሳይሆን ክብሩን ለመጠበቅ ካለው ፍላጎት (በሴት ታዘዘ ላለመባል) ነው፡፡ ከዚህ በኋላ አንበሳው በሚስቱ ሊታዘዝ እንደማይችል እንረዳለን፡፡ በመሆኑም ተረቱ በቀጥታ የወንድን አዛዥነትና የሴትን ታዛዥነት አስርጿል፡፡ ይህ ተረት ወንድ አዛዥ ሴት ታዛዥ መሆናቸውን እንደ ደንብ የሚቆጥር ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሴቷን የወንዱ ጥገኛ የሚያደርግና ከሥልጣን የሚከለክል፣ ቀደም ብለን እንዳልነው የአባዊ ሥርዓቱን መዋቅር የማስጠበቅ ፍላጎት ነው፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ተረት ለሴትና ለወንድ በሰጠው ተምሳሌታዊ ውክልና አድሏዊነትን እናይበታለን፡፡ ሴት በደረቅ እንጨት ተመስላለች፡፡ ወንድ ደግሞ በእርጥብ እንጨት ተወክሏል፡፡ የወንድነት ባህሪውን ያላሟላ (አዛዥነትን) ወንድ ደግሞ ሊደርቅ ካለ እንጨት ጋር አነጻጽሮታል፡፡ በየባህሉ ለእርጥብና ለደረቅ የሚሰጠው ውክልና በተቃራኒ የቆመ ነው፡፡ እርጥብ የበጎ ነገር ተምሳሌት፣ መልካም ነገር አስከታይ እንደሆነ ሲታሰብ ደረቅ ግን ከዚህ በተቃራኒው ነው፡፡ ለምሳሌ "እከሌ እርጥብ ነው" ከተባለ በበጎ ነገር አምጭነቱ ይታሰባል፡፡ ባንጻሩ "እግረ ደረቅ" ከተባለ አጉል ነገር አስከታይ፣ ገደቢስ ሆኖ ይታሰባል፡፡ በተረቱ ውስጥ ሴት በደረቅ እንጨት ወንድ በእርጥብ እንጨት መወከላቸው አሳማኝ ካለመሆኑም ሌላ ተጠየቃዊ አይደለም፡፡ ሆኖም በተረት ውስጥ የተገለጸው የማኅበረሰቡ በተለይም የአባዊው ሥርዓት ርዕዮተ ዓለም ነውና ሥርዓቱ ለሴት የሰጠው ዝቅተኛ ግምት ምን ያህል እንደሆነ ያንጸባርቃል፡፡

በተረት 22 ውስጥ በሚስቱ ባህሪ የተቸገረ ባል ትስተካከልለት ዘንድ ወንድሚን በመካሪነት ይጠራል፡፡ ወንድምየውም እህቱን ሲመክር "ምን እበላለሁ ብለሽ ከማሰብ ምን አበላለሁ ብለሽ አስቢ! ምን እላለሁ ከማለት ምን እባላለሁ ብለሽ ፍሪ! የት ትሄዳለህ ከማለት የት እሄዳለሁ ብለሽ አስቢ!" በማለት የባሏ ተንከባካቢና ቃሉን አክባሪ እንድትሆን አስገንዝቧታል፡፡ በተረት 63 ውስጥ አንዲት ልጃገረድ የበረዶውን ንጉሥ ፈቃድ በመሙላቷ "ለመልካምነትሽ ስጦታ ተቀበይኝ" ብሎ ራሱ የበረዶው ንጉሥ በወርቅ፣ በነሃስና በእንቁ የተሞላ ሳጥን ሰጥቷታል፡፡ በዚያው ተረት ውስጥ የተፈታተነችውን፣ በበጎ ዓይን ያላየችውን እና መልካምነት የጎደላትን ልጃገረድ በበረዶ ውሽንፍር ተገርፋ እንድትሞት አድርጓታል፡፡

በሌላ በኩል በባህሪዋ ከሁለት ታናናሽ እህቶቿ ተለይታ ጠብ ጫሪ፣ የማትታዘዝ እና ሠላም የማትሰጥ ሆና በተረቱ ውስጥ (ተረት 71) ተስላ የነበረች ሴት ባሏ በወሰደው ተከታታይ የማስተካካያ እርምጃ ፍጹም ታዛዥና ቃሉን አክባሪ ሆናለች፡፡ በዚህም በጣም

ጨዋ ከሚባሉት ሁለት ታናናሽ እህቶቿ በልጣ በመገኘቷ አባቷ እውቅና ሰጥተዋት በብዙ ዘመን ያጠራቀሙትን አንድ ማሰሮ ወርቅ ሸልመዋታል፡፡ ተረቱ የታዘዥነቷን መጠን ሲነግረን ባሏ በር ላይ ቆሞ "ፍቅሬ እስቲ አንዴ ነይ" ባላት ጊዜ "የሚቀበላት ብታጣ ማማሰያውን ወርውራ ያራል አያርም ሳትል ከመቅጽበት ባሏ ወዳለበት መጣች" ይለናል፡፡ ይህ የሚያሳየን ማኅበረሰቡ ታዛዥ ሚስትን ማበረታታቱንና እውቅና መስጠቱን ነው፡፡

ሌላው "የሚስት ዓይነቷ ሶስት ነው" በሚል በተረት 81 ላይ የተገለጸው ሴቶች ለወንድ ካላቸው የአገልጋይነት ሚና ጋር በተያያዘ በጎ ነው ያለውን ከሌሎች ጋር አነጻጽሮ ለማሳየት ጥሯል፡፡ በተለይም ለወንድ ተስማሚ ናት ያላትን አስቀድሞ "እናት ለምኔ" የሚል ስያሜ ሰጥቶ ከሚስት የሚጠበቁትን በጎ ተግባራት (ከወንድ ተጠቃሚነት አንጻር) በሙሉ ሰጥቷታል፡፡ ለምሳሌ በተረቱ ውስጥ የሚከተለው ይገኛል፡፡

> *. . . እናት ለምኔ . . .  ቀደም ብላ ተነስታ ለባሏ ሙሽት ለቤ አሰናድታ ከመኝታው ቀስቅሳ ታቀርባለች . . .  ሞፈሩን አንስቶ ወደ እርሻው ለመሄድ ሲዘጋጅ ቶሎ ብላ ቀንበሩን ተሸክማ ትሸኘዋለች፡፡ . . . የምሳ ሰዓት ሲደርስ ደግሞ የባሏን ምግብ በደህና አገልግል ፈትፍታ የሚጠጣውንም ጠላ በቡይት ይዛ እርሻው ድረስ ትሄዳለች . . . ስትመለስ . . .  ወደ ቤቷ ገብታ መቆያውንና እራቱን ታሰናዳለች፡፡ መሸት ሲል ታይና ወደ ውጭ ወጥታ ከመንገድ ላይ ቀንበሩን ከባሏ ተቀብላ እያጫወተችው ወደ ቤት ትገባለች  . . . ወዲያው ለባሏ መቆያውን ካቦሬ ጠላ ጋር ከሰጠችው በኋላ የማታ ስራዋን ታሰናዳለች፡፡ . . . ውሃ በኩስኩስት ታሞቅና እግሩን አጥባ በቅባት ታሸለታለች፡፡ እራት ከበሉም በኋላ ቆጡን አንጥፋ ታስተኛውና . . . (ተረት 81)*

እናት ለምኔ ሚናዋ በሙሉ የአገልጋይነትና ባሏን ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ማስደሰትና መንከባከብ ነው፡፡ ይሄ ተረት የሴቶችን ባህሪ ለወንዶች እንዲመች አድርጎ የመቅረጽ አላማ ያለው ነው፡፡ እናት ለምኔ ለወንድ ምቹ የሆኑ የሴቶች ባህሪያት ከያሉበት ተለቃቅመው የተሰጧት ናት፡፡ በዚያም ላይ አንዲት ሴት ከጧት እስከ ማታ ልታከናውናቸው የሚገቧትን ስራዎች በዝርዝርና በቅደም ተከተል እንደ ደንብና ግዴታ ዘርዝሮ አስቀምጧል፡፡ አብዛኞቹ ስራዎች ባሏን በማገልገል ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ የእናት ለምኔ ተግባር (የወንድ አገልጋይነት ሚና) በአርዓያነቱ ወደ ሌሎችም እንዲደርስ ታስቦ በጎን የሚያደምጡ እረኞች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም ጉዳዩን ወደ መንደራቸው ሄደው ያወራሉ፡፡ እንዲህ ዓይነቱ በጾታ ልዩነት ላይ የተመሰረተው ሥርዓተ ጾታ ሚና የአባዊውን ርዕዮተ ዓለም ለማስጠበቅ ያለው ሚና ከፍ ያለ ነው፡፡

የወንድ ያዛዥነት ድባብና የበላይነት፣ በሴቶች ዘንድ ፍርሃትንና የመብት የለኝምን ስሜት እንዲሁም በራሳቸው ተነሳሽነት ነገሮችን የመፈጸም እምነታቸውን ያጠፋዋል

ሲሉ Berhanu (2015:129) የእንስታውያንን ሃሳብ አጣቅሰው ገልጸዋል፡፡ ሆኖም የመዋቅራዊ ግልጋሎታዊ ንድፈ ሃሳብ አራማጆች እንደሚሉት በየትኛውም ማኅበረሰብ ያለ ሰው ያለበትን ማኅበረሰብ ደንቦች (norms) አክብሮ መኖር ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ደንቦች አንድም ማኅበራዊ መዋቅሩ የተሰራባቸው ናቸው፡፡ አንድም አንድ ሰው የማኅበሩ አባል መሆኑን ማረጋገጫዎች ናቸው፡፡ ስለዚህ አንድም መዋቅሩን በማፍረሱ እንዳይገለልና እንዳይቀጣ፣ አንድም በመመስገን ክብር ለማግኘት ደንቦችን መጠበቅ ይገባዋል ሲሉ ሃሳቡን ይቃወማሉ፡፡

የአባዊ ሥርዓቱ ሴትነታዊ አስተሳሰብ (concept of femininity) በተለይም አቅም የላቸውም ብሎ ማሰብ፣ ባህሪያቸውን ከዝምተኛና ከታዛዥነት ጋር ማያያዝ፣ በራስ መተማመን የሚነሳቸው አድርጎ መገመትና ይህንኑ እውነተኛ አድርጎ ማስረጽና ማመን ሴቶች ወደ ሥልጣን እንዳይመጡ በር ይዘጋል (Berhanu 2015:134 Tyson 2006ን ጠቅሰው)፡፡ በሴቶች ዝቅተኝነት ላይ ተንተርሰው የሚነገሩ ተረቶች ሴቶችን በባሎቻቸው ቁጥጥር ስር እንዲኖሩና አርፈው እንዲቀመጡ ተጽዕኖ ማድረግ፣ በአንጻሩ ግን ለወንዱ የልብ ልብ ሰጥተው በአዛዥነትና በነጻነት በሴቷ ላይ እንዲነግስ ማድረጋቸው እርግጥ ነው፡፡ የተለያዩ እንስታውያን ይህ ተጠየቃዊ ያልሆነ የተቃራኒ ጾታን ግንኙነት፣ የተዛባ ሥርዓተ ጾታዊ አስተሳሰብንና ኢፍትሃዊ የሥልጣን ክፍፍልን እንዳሰፈነ ያስረዳሉ (Eagleton 2003 በ Berhanu 2015፡137 ውስጥ)፡፡ ስለዚህ በተረቶች ውስጥ ለሴቶች የተሰጠው ዝቅተኛ ሰብዕና ዓላማው አንደኛ ሴቶችን ከወንዶች እኩል እንዳይሰለፉ በማድረግ ወደ ሥልጣን እንዳይመጡና ወንዱን እንዳይሻሙ ለማድረግ፣ ሁለተኛ ወንዱ በሴቶች የመገልገል እድሉ ከፍ እንዲልና ዘላለማዊ እንዲሆን ነው፡፡

## 5.2 አባዊ ሥርዓቱ ሴቶችን ከሥልጣን ለማግለል የተጠቀመባቸው ሥልቶች

ቀደም ባለው ትንተና ወንዶች የሴቶች አዛዥና የበላይ እንደሆኑ ስልቶችን ሳንጠቅስ አይተናል፡፡ ነገር ግን ስልቶችን እየጠቀሱና በተረቶች እያዋዙ ማቅረብ ተገቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ወደፊት የሥርዓተ ጾታን እኩልነት እንደምን ማምጣት እንደሚቻል የሚታሰበው ስልቶቹ ሲታወቁ ነው፡፡ በዚህም መሰረት አባዊ ሥርዓቱ ሴቶችን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግና ከሥልጣን ለማግለል የተጠቀመባቸውን ሥልቶች እንመለከታለን፡፡

### 5.2.1 የሴቶች አሉታዊ ገጽታ

የሴቶችን ገጽታ የሚያዛቡ በርካታ ተረቶች አሉ፡፡ ዓላማቸውም ሴቶች ከወንድ ጋር እኩል ነን ብለው እንዳያስቡ፣ የወንድን የበላይነት እንዲቀበሉና ወንድ የዋለበት ቦታ እንዳይገኙ ለማድረግ የሚጥሩ ናቸው፡፡

የሴት ገጽታ መዛባት የሚጀምረው ከአፈጣጠሯ አንስቶ ነው፡፡ ይህንን በተመለከተ ተረት 69ን ማየት ጠቃሚ ነው፡፡ በተረቱ እንደቀረበው ሄዋን ከአዳም የግራ ጎን አጥንት ሳይሆን ከሰይጣን ጅራት እንደተሰራች ያትታል፡፡ ጉዳዩን ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ ከተረቱ እንጥቀስ፡፡

> *. . . ፈጣሪም በሰራው ሁሉ እየተደሰተ . . . የሰራውን ሲክልስና ሲያርም ሰነበተ፡፡ አንድስ እንኳ ስህተት አልነበረውም፤ አዳምን ብቻውን ከመፍጠሩ ውጭ፡፡ በዚህም ፈጣሪ ተጸጽቶ ለአዳም አገልጋይ ሊሰራለት ፈለገ፡. . . ታዛዡን ሚካኤልን ጠርቶ . . . "አዳም እንቅልፍ ሲወስደው አይተህ ከግራ ጎኑ አንዲት አጥንት አምጣልኝ" ሲል ላከው፡፡ ሚካኤልም እንደታዘዘው ወደ አዳም ሄደና . . . የታዘዘውን የግራ ጎን አጥንት አወጣ . . . ጉዞውን ወደ ፈጣሪው አደረገ፡፡*
>
> *ሚካኤል በመንገድ ላይ እያለ ሰይጣን . . . ሚካኤል ሲዘናጋ አይቶ ያቺን አጥንት ከእጁ ላይ ይነጥቀውና ወደ እንጦርጦሱ ሩጫውን ይቀጥላል፡፡ ሚካኤልም የተነጠቀውን አጥንት ለማስመለስ . . . ተከታትለው ሲሮጡ ዳቢሎስ ሊደረስበት ሲል አንድ ዋሻ ውስጥ ጥልቅ ይላል፡፡ ሆኖም የዋሻው በር ጠባብ ስለነበረ እንደልቡ ቶሎ አላስገባው ይልና ጅራቱ ወደ ኋላ ይተርፍበታል፡፡ ሚካኤልም ያቺን ጅራት . . . በሰይፉ ይቆርጣታል . . .የቆረጣትን የሰይጣን ጅራት ይዞ ወደ ፈጣሪው ይቀርባል፡፡ ፈጣሪም . . . ሴት አድርጎ ሰራት . . . (ተረት 69)*

ይህ ተረት በእምነቱ ውስጥ ያለውን የሥነፍጥረት ታሪክ (ዘፍጥ. 2፡21-23) በማዛባት ሌላ መልክ ለመስጠት የሞከረ ነው፡፡ የተረቱ ዓላማ ሴት ከወንድ እኩል እንዳትሆን ይባስ ብሎ ስሪቷን ከሰይጣን ወገን ያደረገ ነው፡፡ በዚህም ደረጃዋን እጅግ ዝቅ አድርጎ (ከሰይጣን ወገን መድቦ) ከክፋት በስተቀር ምንም በጎ ነገር መስራት እንደማትችል ለማሳየትና ከወንድ ጋር ላለማወዳደር ነው፡፡ አለማወዳደሯ ወንድ ያለውን (የበላይነት፣ የንብረት ባለቤትነት፣ ሥልጣን) እንዳትካፈል ለማድረግ የሚጥር ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ገጽታ በሌሎች ጥናቶችም ውስጥ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ Abdulkadir (1982፡86) በሶማሌ ማኀበረሰብ ውስጥ በምሳሌያዊ አነጋገር "A woman is an indispensible evil" [ሴቶች እጅግ አስፈላጊ ሰይጣኖች ናቸው] ሲሉ እንደሚገልጿቸው ጠቅሰዋል፡፡ አባባሉ ከላይ ከተጠቀሰው ተረት ጋር የአንድምታ ዝምድና አለው፡፡ ሁለቱም ሴትን

"ሰይጣን" በሚል ገልጸዋታል፡፡ ይህ በጠቅላላው ገጽታቸውን የማዛባት እና ቀና ብለው እንዳይሄዱ የማድረጊያ ዘዴ ነው፡፡

ተረት 69 ለሴቶች (ከአፈጣጠር አንጻር) ዝቅተኛ ግምት የሰጠ ብቻ ሳይሆን የሃይማኖትንም እሴት የተፈታተነ ሆኖ ይታያል፡፡ በእርግጥ ተረቱ የተነገረበት ዓላማ የሴቶችን ሰብዕና ዝቅ ለማድረግ ተብሎ ነው፡፡ ይሁንና ሃይማኖታዊ ተግዳሮትም አለው፡፡ ይህ በሁለት አቢይ ነጥቦች ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡ የመጀመሪያው ፈጣሪን ከስህተት ያልጸዳ አድርጎ የሚያሳየው ነው፡፡ ለዚህ በማስረጃነት የሚጠቀሰው "ፈጣሪም . . . አንድስ እንኳ ስህተት አልነበረውም፤ አዳምን ብቻውን ከመፍጠሩ ውጭ" በሚል በተረቱ ውስጥ የሰፈረው ነው፡፡ አባባሉ ሌሎችን እንስሳት በተመሳሳይ ጊዜ ሴት እና ወንድ (ጥንድ ጥንድ) እያደረገ እንደፈጠራቸው ሁሉ አዳምና ሄዋንንም በዚያው መንገድ መፍጠር ነበረበት የሚል ነው፡፡ ይህ እንከን ሃሰት እንዳይባል ደግሞ ተረቱ የፈጣሪን ምስክርነት "በዚህም ፈጣሪ ተጸጽቶ ለአዳም አገልጋይ ሊሰራለት ፈለገ" ሲል ያጣቅስልናል፡፡ ይህ ተረት በተዘዋዋሪ ፈጣሪ ስህተቱን አምኗል የሚል ነው፡፡ ስህተቱ በተራዛሚ ችግር ማስከተሉንም ተራኪው ለማስረገጥ ጥሯል፡፡ ምክንያቱም የተራኪውን ስሜት ስናጤነው አዳም እና ሄዋን በተመሳሳይ ጊዜ ተፈጥረው ቢሆን ኖሮ ሰይጣን እድል አያገኝም ነበር፤ ሄዋንም ከሰይጣን ጅራት አትፈጠርም ነበር የሚል ነው፡፡

ሁለተኛው ተረቱ የሃይማኖት እሴትን የተፈታተነበት አቅጣጫ ከአዳም በኋላ ያለው የሰው ዘር በሙሉ (ክርስቶስን ጨምሮ) የዘር ሃረጉን (ከሴት ወገን ያለውን) ከሰይጣን ወገን መምዘዙ ነው፡፡ ትክክለኛዋን የአዳምን የግራ ጎን አጥንት (እውነተኛዋ ሄዋን ልትሰራበት የነበረውን) ሰይጣን የት እንዳደረሳት ተረቱ ባይነግረንም አሁን ያለው የሰው ዘር እናት (ሄዋን) ግን ሃረጓ ከሰይጣን ወገን እንደሆነ ይተርካል፡፡ ይህ የሃይማኖት እሴቱን ከመፈታተኑም በላይ በተለይ ለሴት ከተሰጡት አሉታዊ ገጽታዎች ዋናው እና ለሌሎች አሉታዊ ገጽታዎቿ እንደ ማጠንጠኛ ሆኖ የሚጠቀስ ነው፡፡

ሌላው ገጽታቸው ተዛብቶ የሚታይበት አጋጣሚ ከፈቃደ ስጋዊ ፍላጎት ጋር ይገናኛል፡፡ ለዚህ ጥናት የተሰበሰቡት ተረቶች በአብዛኛው ሴትን ዝሙተኛ አድርገዋል፡፡ እንዲያውም በፈቃደ ስጋዊ ፍላጎት ሴቶች ከወንዶች እንደሚበልጡ ያሳያሉ (ተረት 26 እና ተረት 87)፡፡ በዚህም የተነሳ አንድም ወንዱ በሴቶች ላይ ቁጥጥሩን እንዲያጠብቅ አንድም ይሄ ባህሪያቸው ለኃላፊነት እንደማያበቃ ለማስገንዘብ ተጠቅመውበታል፡፡ ለምሳሌ በሚቶሎጂው ውስጥ የጅማ ኦሮሞዎችን መርታ ወደ አካባቢው የሄደችውን ንግስት

(Makka Ware) ንግስናዋን ያጣችው በዚሁ ምክንያት ነው፡፡ ወንዶች ተሰብስበው ተማክረውና በምትኳ ሌላ ንጉሥ መርጠው እንስከሚጨርሱ ድረስ ወደ ችሎቱ እንዳትመጣ ማድረግ የቻሉት በፍቅር የሚቀርባት ወንድ ወደ ቤቷ በመላክ በማዘናጋት ነበር (Abreham 2007፡65)፡፡ ይህ ሴቶች ከስራቸው ይልቅ ዝሙትን ይመርጣሉ በሚል ሥልጣንን ለመንፈግ የተዘጋጀ ነው፡፡

ቀደም ብሎ በምዕራፍ አምስት ስለ ሴት አሳሳችነት በተመለከትንበት ክፍል ውስጥ የአገራቸውንና ህዝባቸውን ህልውና የሚገዳደሩትን ጠላቶቻቸውን ለማንበርከክ ሴትነታቸውን ተጠቅመው ከግብ የደረሱ ሴቶችን ለሌላው የሞት ምክንያት በመሆናቸው ተግባራቸው ከአሳሳችነት ተቆጥሯል፡፡ በሚቶሎጅውም ውስጥ ሴትነት በተለይም ከጾታዊ ግንኙነት ጋር ተሳስሮ ሲመጣ በአሳሳችነትና አጥፊነት እንደሚተረጎም ተጠቅሷል (ቴዎድሮስ 2001፡46-52)፡፡ ከላይ በጠቀስነው በ Abreham (2007፡65) ጥናት ውስጥ ግን Makka Ware ወደ ችሎት እንዳትመጣ በፈቃደ ስጋዊ ግንኙነት አታልሎ ያቆያት ወንድ ተግባር ከቅዱስ ስራ ተቆጥሯል፡፡ ከሃጢያት የተቆጠረው የንግሥቷ መሳሳት ብቻ እንጂ የወንዱ ንግሥቷን ማሳሳት አይደለም፡፡ ይህ የተዛባ አመለካከት ምን ይነግረናል? ሴት እና ወንድ ተመሳሳይ የሆነ ነገር ሲፈጽሙ ተግባሩ ለሷ ብቻ ተለይቶ ለምን ሃጢአት ተባለ? ሚዛናዊ ለማድረግ ያልተፈለገው ለምንድን ነው? ሁሉም የሆነው የወንድን የበላይነት ለማስረጽ ካለ ፍላጎት ነው፡፡

በሌሎች ተረቶች ውስጥ ከተለያየ አቅጣጫ የሴትን ገጽታ የሚያበላሹ ብዙ አሉ፡፡ ለምሳሌ ተረት 21 ውስጥ ኮርማ ያለባቸውን ጥቂት ከብቶች ብዙ ናቸው፤ ኮርማ የሌለባቸውን ብዙ ላሞች ጥቂት ናቸው የተባለበት፣ ተረት 52 ውስጥ "ከብት ዘሩ ሊጠፋ ሲል ወንድ ወንድ ይወልዳል፤ ሰው ዘሩ ሊጠፋ ሲል ሴት ሴት ይወልዳል" በሚል የተነገረው፣ ተረት 58 ውስጥ ባል የሌላት ሴትና አጥር የሌለው ቤት ደፋሪው ብዙ ነው በሚል የቀረበው ለገጽታቸው መበላሸት ዋና ማስረጃዎች ናቸው፡፡ በተረት 87 ውስጥ ሴቶችን ምስጢር አባካኝ ናቸው በሚል ደካማ ገጽታ ተሰጥቷቸው ሥልጣን ተከልክለዋል፡፡ እነዚህ በሙሉ ሴቶች በወንዶች ቁጥጥር ስር እንዲውሉና ወንዱን እንዳይጋፉ እንደ አንድ ጥሩ የመከልከያ ስልት አገልግለዋል ማለት ይቻላል፡፡

## 5.2.2 ቅጣት

አባዊ ሥርዓቱ ሴቶችን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ እና ከኃላፊነት ወይም ከሥልጣን ለማራቅ ከተጠቀመባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ ቅጣት መሰንዘር ነው፡፡ ቅጣቱም ሲፈጸምባቸው የሚታየው በድብደባ፣ በሞት፣ከንብረቷ አፈናቅሎና ካገሯ እንድትሰደድ በማድረግ፣ በወገኖቿ ላይ መከራ እና ሞት በማምጣት በሃዘን መቅጣት ናቸው፡፡ Lazar (2007:148) እንደሚያስረግጡት ልማዳዊ የሆኑ ግልጽ የሥርዓተ ጾታ ተባለጥ ማሳያዎች ከሚባሉት ውስጥ አካላዊ ቅጣት፣ ወሲባዊ ትንኮሳ፣ ሥራቸውን ማቃለል እና ከአንዳንድ ማኅበራዊ ተግባራት ማገድ እንደሚገኙ ጠቅሰዋል፡፡ ከላይ የጠቀስናቸውን በዝርዝር እንመልከታቸው፡፡

ወንዶች ሚስቶቻቸው እንዲታዘዟቸው፣ ያሏቸውን እንዲፈጽሙላቸው እና ከእነርሱ አልፈው ሌላ እንዳያዩባቸው ከሚያስፈራሩባቸው እና ከሚያስገድዱባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ የኃይል እርምጃ መጠቀም ነው፡፡ የሚወሰደው የጉልበት ርምጃ ከተራ ድብደባ እስከ ሞት ይደርሳል፡፡ ሴቶች አጥፍተዋል ተብሎ ሲታመን (በወንዶች ዓይን) እንደማስተካከያ የሚወሰደው እርምጃ ይሄው ነው፡፡ ሃይማኖቱም ለምሳሌ እስልምና ሳካ (የአካል ጉዳት) የማያደርስ ድብደባን ይፈቅዳል (ሱራ 4:34)፡፡ ከዚህም አልፎ ይቅርታ የሌለው ጥፋት ለምሳሌ እንደ ዝሙት ያለ ፈጽመው ሲገኙ በተረቶች ውስጥ ከድብደባ ያለፈ ግድያ ሲፈጸምባቸው ይታያል፡፡ በጥቃቅን ጥፋቶችም ቢሆኑ በምክርና በተግሳጽ ሲታለፉ አይታዩም፡፡

ቅጣቱ የሚፈጸምባቸው በባሎቻቸው እንዲሁም አጋጣሚውን ባገናኘው ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል፡፡ ቀጪው ባል ከሆነ የሚወስደው እርምጃ ድብደባ እና አልፎ አልፎ ደግሞ ንብረታቸውን ቀምቶ ከቤታቸው ማባረር ነው፤ ግድያም አለ፡፡ ተረት 51ን ብንወስድ ከሚስቱ ጋር ያገኘውን ውሽማዋን በጨቤ አንገቱን ከቆረጠው በኋላ እሷን ግን ካገር እንድትጠፋ አድርጓታል፡፡ ተረት 67 እንዲሁ በዱር ስራ የማታግዘውን ሚስቱን በተቀነባበር ዘዴ ተቅማጥ እንዲይዛት ካደረገ በኋላ ያንኑ (ተቅማጧን) አሽክሞ ገበያ በመውሰድና ባገር ፊት የያዘችበትን እቃ በመስበር አዋርዷታል፡፡ በዚህም ካገር ለመጥፋት በቅታለች፡፡ ተመልሳ ወዳገሯ እንዳትመጣ እንኳ ያገሩ ስም በሷው "ቅዘን ልብሱ አገር" ተብሎ ተሰይሟል፡፡ ከዚህ አነስ ካለ ግን በግርፋት እንዲስተካከሉና

ፈርተው እንዲኖሩ ማድረግ ነው፡፡ ለምሳሌ ተረት 60 እና 62 ውስጥ በግርፋት ብቻ እንዲስተካከሉ ተደርጓል፡፡

በሌሎች ተረቶች ውስጥ ደግሞ ባሏን በድላለች ከተባለችው ሴት ጋር የጋብቻ ዝምድናም ሆነ ሌላ ቀረቤታ የሌላቸው የማያገባቸው ወንዶች አጥፊ በተባሉት ሴቶች ላይ ግድያ ሲፈጽሙባቸው ይታያሉ፡፡ ለምሳሌ በተረት 55 ውስጥ አድሮ ሂያጅ መንገደኛው ሴቷ ያስገባችው ሰው ውሽማዋ መሆኑን እንኳ ሳያውቅ ሊገድላት በቅቷል፡፡ ገዳይ በግሉ ተበደልኩ፣ ተደፈርኩ ባይ አይደለም፡፡ ተራኪው ይህንን በግልጽ ባይነግረንም ወንድ ለወንድ ካለው ወገናዊነት በመነጨ ፍላጎት ለባሏ ለምን አልታመነችም በሚል ስሜት ሊያስገድላት እንደቻለ እንገምታለን፡፡ ይህ የተደረገው አባዊ ሥርዓቱ የዘረጋው ለወንድ ያደላው መዋቅር እንዳይፈርስ ከማሰብ የመነጨ ይመስላል፡፡

ሚስቶች በእንጀራ ልጆቻቸው፣ በባሎቻቸው ወላጆችና ዘመዶች ላይ በቅናት ወይም በጥላቻ ኢሰብዓዊ የሆነ ድርጊት ፈጽመው የሚገኙ ከሆነ ወይም ዋሽተው በሌላ አካል ላይ እርምጃ ለማስወሰድ ሲጥሩ ከተገኙ የሚወሰድባቸው እርምጃ ራሳቸው ባዘጋጁት ወጥመድ ውስጥ ገብተው እንዲሞቱ ወይም የራሳቸው የሆነ ሰው በዚያው ሴቶቹ ሌሎችን ሊያጠቁ ባዘጋጁት እንዲሞቱ ወይም እንዲጎዱ ማድረግ ነው፡፡ ለዚህ የሚሆኑ በርካታ አብነቶች አሉ፡፡ ተረት 36 ዓይነ ስውር ባሏን በመርዝ ለመግደል በማሰቧ በእርሷና በዘመዶቿ ላይ የደረሰባትን መከራ ያሳያል፡፡ ታሪኩን ቀነጫጭበን እንየው፡፡

> *. . . ሴትዮዋ በህመሙ ሰልችታ [በከፊል ዓይነ ስውር ባሏ] በብዙ ታማርር ነበር፡፡ አንድ ቀን በመርዝ መግደል አሰበችና . . . እምግቡ ላይ መርዝ ጨምራበት አሳይታው ወደ ገበያ ሄደች፡፡*
>
> *ያን እለት የሴትዮዋ 3 ወንድሞች የእህታቸውን አዝመራ ለመሰብሰብ ተቃጥረው ነበርና ሲያጭዱ ውለው እንደጨረሱ . . . ዓይነ ስውር አማቻቸው "እህታችሁ እንጀራውን በሌማት፣ ወጡን በድስት እና ጠላውን በገንቦ አስቀምጣላችኋለችና ብሉ! ጠጡ!" ይላቸዋል፡፡ እነርሱም . . . ያንን ምግብና መጠጥ ከነመርዙ ግጥም አድርገው ይበላሉ፤ ሁሉም በያሉበት ፍንግል ፍንግል ብለው እህታቸው ታገኛቸዋለች . . . "አንተ ትበላለህ ብዬ ነው እንጂ እንዲህ አድርገህ ወንድሞቼን ትገልብኛለህ?" ብላ እብድ ሆነችበት፡፡ ባልዮውም "በቃ ገመድ አምጭልኝና ልታነቅልሽ" አላት፡፡ በፍጥነት ገመዱን ሰጠችው፡፡ ሙቀጫ ላይ ወጥቶ ገመዱን ጣራ ላይ አሰረውና ለመታነቅ ዝግጁ ሆነ፡፡ . . . "በደንብ መታሰሩን ፈትሽልኝ፡፡ በዚያውም ቶሎ ይገድለኝ እንደሆነና እንዳልሆነ ሞክሪው" ይላታል፡፡ እሷም ሙቀጫው ላይ ወጥታ በደንብ መታሰሩን አረጋገጠች፡፡ ሸምቀቁ በትክክል መታሰሩንም ለማረጋገጥ አንገቷን አስገብታ ስትሞክር ባል . . . ያንን ሙቀጫ በእግሩ ሲፈነግለው ሴትዮዋ ታንቃ ሞተች፡፡*

*. . . አማቱ ምግብ እያዘጋጀች ልትረዳው አብራው መኖር ጀመረች . . . እሷም ቂም አርግዛ ቀን እየጠበቀች . . . አንድ ቀን . . . መርዝ የተጨመረበት ውሃ በድስት ትጥድና ውሃ ልትቀዳ ትሄዳለች። ዓይነ ስውሩ ሁሉንም ነገር አይቷልና የተጣደውን የድስት ውሃ አፍስሶ በንጹህ ውሃ ይተካዋል። አማቱም እንደተመለሰች ገንፎዋን አዘጋጅታ ታቀርብለታለች። . . . ሳያስተርፍ ሙልጭ አድርጎ ይበላዋል። በማግስቱ እልልታውን ያቀልጠዋል። "ምን ሆንክ? ምን አገኘህ?" ሲሉት አማቴ ያበላችኝ ገንፎ አይኔን አበራልኝ" ይላል . . . ውሸቱን . . . አማቱ አንድ ዓይና ነበረችና "ይሄማ መድሃኒት ከሆነ እኔም እበላዋለሁ" ትልና የመርዙን መጠን ከፍ አድርጋ በገንፎዋ ትበላለች። አማትም እንደልጆቿ ትሞታለች . . .(ተረት 36)*

የዚህ ተረት አንድምታ እንደ ሥርዓት (as a system) ወንድ እስከ ህይወቱ ፍጻሜ በሴት የመገልገል ፍላጎት እንዳለው እና ይህንኑ ዘላለማዊ ለማድረግ እንደሚጥር እናጤናለን። በዚህም የተነሳ ከሴት ጥሩ እንክብካቤ ስለሚፈልግ ይህንን በማያደርጉት ላይ ይቅርታ ሲያደርግ አናይም። ለምሳሌ ከላይ በተጠቀሰው ተረት ዓይነ ስውሩ ባል የመግደል ሙከራ ስለተደረገበት በአምስት ሰዎች ላይ የማያዳግም የበቀል እርምጃ ወስዷል። ሚስት የሞተችው በጥፋቷ ነው ብንልም እንኳ የወንድሞቿ አሟሟት ግን ያለ ጥፋታቸው ነው። ተረቱ ይዞት ከተነሳው ዓላማ አንጻር ግን ሞታቸው የራሱ ሚና አለው። ይህም ሚስትየዋ በባሏ ላይ ባደረገችው የመግደል ሙከራ ምክንያት በሃዘን ለመቅጣት ታስቦ ነው። ቅጣቱንም በዚሁ ሊያቆምና ሚስትየዋንም በማስተማር ሊያልፋት ስላልፈለገ እሷንም በሞት ቀጥቷታል። ወንድንም እስከ መጨረሻው ለመጠበቅ ካለው ፍላጎት የተነሳ የልጆቿን ደም ለመመለስ ያሰበችውንም እናት እራሷ ባሰበችው እና ባዘጋጀችው ተንኮል ህይወቷን አጥታለች።

ከላይ የተጠቀሰውን የሚያጠናክር በተረት 42 ውስጥ እንዲሁ ተንጸባርቋል። አንዲት ሴት የታጨችውን የእንጀራ ልጇን በዘንዶ ካስያዘች በኋላ የራሷን ልጅ ለአጪው ድራለች። ሆኖም በዘንዶ የተያዘችው ልጅ በብዙ ተዓምራት ከዘንዶው አምልጣ የተነጠቀችውን እጮኛዋን አግብታለች። ባሏን የቀማቻትንም እህቷን (ያባቷን ልጅ) ምላሷን ቆርጣ እንድትሞት አድርጋታለች። በዚህም ምክንያት እናት በልጇ ሞት እንድትቀጣ ተደርጋለች። ተረት 14 ውስጥም ተመሳሳይ ሂደት አለ። እዚህ ላይ እናት የገዛ ልጇን በድንጋይ እንድትገድላት ይደረጋል። ተረት 33፣ 36፣ 39፣ 47፣ 48 ወዘተ. ሴቶች ለሌሎች ባዘጋጁት ወጥመድ ሲያዙና ሲቀጡ ያሳያል።

እነዚህ ተረቶች ሴቶች ክፉ ነገር እንዳይሰሩ እንደማስጠንቀቂያ ቢያገለግሉም ተቀዳሚው ዓላማቸው ግን ለባሎቻቸው ታማኝ እንዲሆኑና ከፈቃዳቸው እንዳይወጡ ማድረግ፣

የእንጀራ ልጆቻቸውን እንደራሳቸው ልጆች እንዲንከባከቡ መምከር ነው፡፡ ይህን ባያደርጉ ግን በተረቱ ውስጥ እንዳለው ቅጣት ዓይነት ሊደርስባቸው እንደሚችል ማስጠንቀቅ ነው፡፡ ይህ ዞሮ ዞሮ በባሎቻቸው ሙሉ ፈቃድ እንዲተዳደሩ የሚያደርግና ጥገኛነታቸውን የሚያጠናክር ነው፡፡

## 5.2.3 ሰናይ ሴቶችን በአርዓያነት ማቅረብ

በዚህ ጥናት ውስጥ ሰናይ ሴቶች ሲባል ለባሎቻቸው ምቾት ከፍተኛ ጥረት የሚያደርጉትን፣ ባሎቻቸውን የሚያከብሩትንና ከቃላቸው የማይወጡትን፣ በመጥፎ ተግባራቸው ባሎቻቸውን የማያሰድቡትን፣ በቤት አያያዛቸው፣ በእንግዳ አቀባበላቸው ባሎቻቸውን የሚያስመሰግኑትን፣ ባለሙያዎችን፣ ባህሪ ከእውቀት ጋር የተቸራቸውን (ከባሎቻቸው አንጻር)  ወዘተ. ማለት ነው፡፡ ይህን መሰል ታሪክ ያላቸው እንስት ገጸባህሪያት በታሪኩ ውስጥ ሲመሰገኑ፣ ሲሸለሙና ሲወደሱ ይታያሉ፡፡ እንዲህ መሆኑ ምድራዊ ሴቶች የእነርሱን አርዓያ ተከትለው ለባሎቻቸው ምግባረ ሰናይ እንዲሆኑላቸው፣ ባህሪ እንዲወርሱላቸው ለማድረግ የሚጥሩ ናቸው፡፡ የወንድ የበላይነት በነገሠበት ማኅበረሰብ ውስጥ ሴቶች ምን ዓይነት ባህሪ ሊላበሱ እንደሚገባቸው ተረቶች ማስገንዘባቸውን Swann (1993:24) ሲያስረዱ “The tales offer some instruction about how society expects females to behave, part of which is drawn from idealized and sexist conceptualizations of women fostered by a male-dominated society . . . the tales seem to be able to inculcate social norms and values” ብለዋል፡፡ ከዚያም አልፎ ህጻናት ይህንኑ እየሰሙ ስለሚያድጉ የዚሁ ሥነምግባር ተከታይ ለማድረግም ያለሙ እንደሆኑ ግምት እናሳድራለን፡፡

ይህንኑ ጉዳይ የሚያረጋግጡ በርካታ ተረቶች አሉ፡፡ ገና አጀማመራቸው ላይ ይህንኑ አተኩረው ይናገራሉ፡፡ ለምሳሌ ተረት 22 ገና ሲጀምር “አንድ ካዋቂ ቤተሰብ የተጋባ ሰው ባንድ አገር ይኖር ነበር፡፡ ሚስቱም አስተዳደጓ ጥሩ ስለነበር ትንከባከበው ነበር” ይላል፡፡ በነዚህ ሁለት ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ ከፍ ያለ ትርጉም ያላቸው ሶስት ሃረጋት አሉ፡፡ እነርሱም አዋቂ ቤተሰብ፣ ጥሩ አስተዳደግ እና ባልን መንከባከብ የሚሉት ናቸው፡፡ ከላይ የጠቀስነው የ Swann (1993:24) ሃሳብ በተለይ ተረቶች ማህበራዊ ደንቦችንና እሴቶችን አምቀው ይይዛሉ የተባለው “ሚስቱ አስተዳደጓ ጥሩ ስለነበር ትንከባከበው ነበር” ከሚለው ጋር ይናበባል፡፡ ቤተሰቦቿ ጥሩ አድርገው ሲያሳድጓት ባልን እንዴት አድርጎ መንከባከብ እንደሚቻል አስተምረዋታል፡፡ በዚህ አባባል ባልን መንከባከብ

ከፍ ያለ ዋጋ የሚያስጥ ማኅበራዊ እሴት ሆኗል፡፡ ምክንያቱም አግቢው "ካዋቂ ቤተሰብ የተጋባ" የሚል የማንነት መግለጫ ተሰጥቶታል፡፡ ከአዋቂ ቤተሰብ መጋባቱም ለእሱ የትልቅነቱ ማሳያ ሆኗል፡፡ እዚህ ላይ የምናነሳው ዋና ጥያቄ የሴቷ ቤተሰብ አዋቂ የተባለበት ምክንያቱ ምንድን ነው? በምን ተመዝኖ ታወቀ? የሚል ይሆናል፡፡ ለዚህ ጥያቄ ከተረቱ ውስጥ የምናቀርበው ብቸኛ ምክንያት "ሚስቱም አስተዳደን ጥሩ ስለነበር ትንከባከበው ነበር" የሚለው ዓረፍተ ነገር ነው፡፡ ለባሏ ያደረገችው እንክብካቤ የእሷን ሰብዕና ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦቿንም አሳይቷል፡፡ በአዋቂ ቤተሰብ ማደን ለባሏ ባደረገችው እንክብካቤ ተመዝኗል፡፡ እንደ ተረቱ አቀራረብ ሴቷን ለዚህ ምስጋና እንድትበቃ ያደረጋት ያላት ግላዊ ሰብዕና ሳይሆን አስተዳደን ነው፡፡

በመሆኑም አንዲት ሴት ባሏን በጥሩ ሁኔታ ብትንከባከብ ምስጋናውና ክብሩ ለቤተሰቦቿም ጭምር ነው፡፡ ድንገት ከማኅበራዊ ደንቡና ስምምነቱ ያፈነገጠ ተግባር ብታደርግ እንኳ "ባለጌ ያሳደጋት" የሚል ትችት ለቤተሰቦቿ ታተርፋለች፡፡ በዚሁ ተረት ውስጥ ያለችውን ባለታሪክ የአዋቂ ቤተሰብ የሆነው ወንድሟ ሲመክራት፣ "ምን እበላለሁ ብለሽ ከማሰብ ምን አበላለሁ ብለሽ አስቢ! ምን እላለሁ ከማለት ምን እባላለሁ ብለሽ ፍሪ! የት ትሄዳለህ ከማለት የት እሄዳለሁ ብለሽ አስቢ!" ብሏታል፡፡ እዚህ ውስጥ በተለይ "ምን እባላለሁ" የምትለዋ ንግግር ከምንም በላይ የክብር ጥያቄን የምታስነሳ ናት፡፡ አኗኗሯና ለባሏ የምታደርገው እንክብካቤ የቤተሰቧም የማንነት መለኪያ እና የክብር መግለጫ ስለሆነ ልታከብራት ግዴታዋ ነው፡፡ ከተሰራላት ማኅበራዊ መዋቅር አልፋ ሥርዓቱ ያልሰጣትን ሥርዓተ ጾታዊ ሚና ልታከናውን አትችልም፡፡ የወንድሟም ማስጠንቀቂያ ይሄው ነው፡፡ ይሄ ደግሞ በተዘዋዋሪ ሴቷን ራሷን እንዳትሆን እና መኖሯ እራሱ ስለወንዱ እንደሆነ ያሳያል፡፡ በሂደት ጥገኝነቷንም ያጠናክርና የዝቅተኝነት መንፈስ ይፈጥርባታል፡፡ ይህ የዝቅተኝነት መንፈስ ከቤቷ አልፋ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚው እና በማኅበራዊ ተቋማቱ የሚገባትን ቦታ እንዳታገኝ ይከለክላታል፡፡

ተረቶች በጎ ሥነምግባር መስበክ አንዱ ዓላማቸው ነው፡፡ በተረት ውስጥ ያሉ ገጸባህሪያት የነባራዊው ዓለም ሰዎች ነጸብራቆች ናቸውና የሚሰጣቸው ባህሪ የሰው ነው፡፡ ገጸባህሪያቱ እንስሳት ወይም ከሌላ ወገን ቢሆኑም እንኳ የተራኪው ግብ ሰዋዊ ባህሪ ነው፡፡ በትረካ ሂደት ውስጥ በጎ የሆነው ሰዋዊ ሥነምግባር የበላይነቱን ይዞ እንዲያሸንፍ ይደረጋል፤ የተረት ባህሪም ነው፡፡ እንዲህ ሲሆን ግን ባብዛኛው ማኅበራዊ መዋቅሩን ሊያናጉ በማይችሉበት መልክ ይቀናጃሉ፡፡ ሰናይ የተባለውን ያሞግሳል፤

እኩዩን ይነቅፋሉ፡፡ ከዚህም በላይ ማኅበረሰቡ ቢሆኑ ብሎ የሚያስባቸውን ባህሪያት ከያሉበት ለቃቅሞ በፈጠራቸው ገጸባህሪያት አማካኝነት ወደ ሌላው ለማስረጽ ይጥራል፡፡ ቀጥሎ ያሉት ከተለያዩ ተረቶች የተወሰዱት ቅንጭብ ተረኮች ሴቶች ቢኖሯቸው ተብለው የታሰቡ ባህሪያትን ይዘዋል፡፡ በሌላ አባባል ባል በሚስቱ እንክብካቤ የተደሰተበትንና ሚስቱን ሰናይ ያስባለበትን አጋጣሚ ያሳያሉ፡፡

> *. . . ስትንደረደር እወንዝ ወርዳ ውሃዋን ቀድታ ተመለሰች፡፡ ወዲያው ቶሎ ብላ ድስት ጥዳ ለእጅ መታጠቢያ ውሃ በኩስኩስት ወዝታ ማታ ካባት ከእናቷ ቤት ይዛው የመጣችውን የቅቤውን፣ የድልሁን፣ የሽሮውን ቅል አቅርባ ማማሰያዋን አበጅታ ወጧን አሳምራ ከሰራች በኋላ እጁን በሙቅ ውሃ አስታጥባ ምሳውን በደንብ አብልታ "በሉ እንግዲህ ወደ እርሻዎ ይሂዱ" አለችው፡፡ እሱም የማያውቀውን ምሳ በማግኘቱ ሰውነቱ በደስታ ተሞልቶ ከብቶቹን ነድቶ ወደ ግብርና ስራው ሄደ (ተረት* 78)፡፡

> *. . . መሸት ሲል ታይና ወደ ውጭ ወጥታ ከመንገድ ላይ ቀንበሩን ከባሏ ተቀብላ እያጫወተችው ወደ ቤት ትገባለች፡፡ ለበሮቹ አስቀድማ ገለባ አቅርባ ወዲያው ለባሏ መቀያውን ካበሬ ጠላ ጋር ከሰጠችው በኋላ የማታ ስራዋን ታሰናዳለች፡፡ ከብቶችም ከዱር ሲገቡ ከረኞቹ ተቀብላ የቀንድ ከብቶችን ከበረት፣ በግና ፍየሉን ከጋጣ፣ ታጉራለች፡፡ ባሏ ንም ጥቂት ረፍት እንዳደረገ አይታ ከብቶችን አውሬ እንዳይበላቸው "የላላውን አጥር ውጣና አጥብቅ" ትለዋለች፡፡ እሱም ደስ እያለው በጓሮ ያስቀመጠውን አረግ ወይም ገመድ በውሃ ያርስና የላላውን አጥርና በር ያጠብቃል፡፡ ጨርሶ ወደ ቤቱ ሲገባ ውሃ በኩስኩስት ታሞቅና እግሩን አጥባ በቅባት ታሸለታለች፡፡ እራት ከበሉም በኋላ ቆጡን አንጥፋ ታስተኛውና የቀራትን ስራ ታጠናቅቃለች (ተረት 81)፡፡*

> *. . . እሷም ውሃ ቀድታ፣ ወቅጣና ፈጭታ ወጥና እንጀራውን መልክ ባለው ሁኔታ አዘጋጅታ፣ የዶሮ ዓይን የመሰለ ጠላዋን ጠምቃ፣ እግሩን በሙቅ ውሃ አጥባ፣ ሰውነቱን ገደፍ የሚልበትን አንድ ምቹ ነገር አሰናድታ፣ በእኔ ሞት እያለች በማጉረስ ደስ በማሰኘት አስመሸችው (ተረት 86)፡፡*

እነዚህ የተረት ቅንጫቢዎች ሴቶች ለባሎቻቸው ማድረግ የሚገባቸውን ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ተግባራት ለሌሎች ሴቶች አርዓያዎች እንዲሆኑ ተፈልጎ የተነገሩ ናቸው፡፡ በተጠቀሱት ሶስት ተረቶች ውስጥ ሴቶቹ የባሎቻቸው የደስታ ምንጮች ሆነዋል፡፡ በዚህ ትይዩ ግን ባል የሚስቱ የደስታ ምንጭ ሆኖ የታየበት አጋጣሚ ለዚህ ጥናት በተሰበሰቡት ተረቶች በአንዱ እንኳ አዎንታዊ በሆነ ገጽታው አልታየም፡፡ እንዲህ እንዲህ አድርጎ ሚስቱን ደስ አሰኛት የሚል ተረት አላጋጠመም፡፡ በእርግጥ ለሚስቱ ጥሩ ነገር አድርጎ የሚያስደስት ባል ጭራሹኑ ጠፍቶ ወይም የመንከባከብ ፍላጎቱ ሳይኖር ቀርቶ አይደለም፡፡ ምናልባት በተረት በይፋ እንዳይነገር ከመፈለግ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ቢነገር ከባሎቻቸው እንክብካቤ ያላገኙ ሴቶች ቅር እንዳይላቸው፣ ልማዱን እንደበጎ ባለመቁጠር፣ ወንድ ሁሉ ሚስቱን በመንከባከብ እንዳይቸገር፣ በሌሎች ወንዶችና ሴቶች

እንዳይተች በመፍራት ሊሆን ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜም ሚስቴ ትንቀኛለች በሚል የሴት ስራን ለመስራት ፈጽሞ የማይፈልግ ይኖራል፡፡ እንዳይሰራላቸው የሚከለክሉ ሴቶችም ያጋጥማሉ፡፡ እነዚህና እነዚህን መሰል አስተሳሰቦች በሚያሰርጹት ልማድ የተነሳ ባል ሚስቱን ያስደሰተባቸው አጋጣሚዎች በተረት እንዳይቀርቡ አድርገው ሊሆን ይችላል፡፡ ቢያጋጥም እንኳ በበጎ ዓይን አልታየም፡፡

ለምሳሌ ተረት 78 ውስጥ የቀረበውን እንመልከት፡፡ ለተረቱ የተሰጠው ርዕስ "አንድ ሚስቱ የተጫወተችበት ሰው" ነው የሚለው፡፡

> *አንድ ሰው ሚስት አግብቶ ይኖር ነበር፡፡ ነገር ግን እሷ ሳያማት ዘወትር አሞኛል እያለች ዝም ብላ በመተኛት ጊዜዋን ስታሳልፍ እሱ ውሃውን ቀድቶ፣ ወፍጮውን ፈጭቶ፣ ከበረት የከብት እበት አውጥቶ ጠፍጥፎ፣ በወንዶች ሙያ ረገድ እርሻውን አርሶ፣ ቆፍሮና አጭዶ ከስራው ሲመለስ ምጣድ ጥዶ እየጋገረ ወጥም እየሰራ ይኖር ነበር፡፡ ከቶ በእድሜው ልክ ምሳ የሚባል ነገር አያውቅም፡፡ ማታ ከስራው ሲገባ መክሰሱንም ሆነ እራቱን እሱው ራሱ አሰናድቶ ይበላል፡፡ ሚስቱ ግን ከሰው ቆጥራ ደክሞታል ብላ ማናቸውንም ነገር ቢሆን አሰናድታለት አታውቅም . . . (ተረት 78)*

ተራኪው በሥርዓተ ጾታ እኩልነት የሚያምን አይደለም፡፡ ይህንን ለተረቱ በሰጠው ርዕስ እናውቃለን፡፡ ርዕሱንም በዚያ መልክ እንዲሆን ያደረገው ባልዮው የሴት ስራ (ውሃ መቅዳት፣ ወፍጮ መፍጨት፣ እበት መጠፍጠፍ፣ ወጥ መስራት፣ እንጀራ መጋገር) ማከናወኑን እንደ ነውር ስለቆጠረው ነው፡፡ እርግጥ ነው ሚስቱ ሳያማት አመመኝ ማለቷ ትዳሯን እንደትዳር ቆጥራ የሚገባትን አለመስራቷ ባሏን ተጫወተችበት ያሰኛል፡፡ ነገር ግን ይህንን ለምን አደረገች? ብንል ንቃው ሊሆን እንደሚችል እንገምታለን፡፡ ምክንያቱም ማኅበራዊ ደንቡ ያልፈቀደለትን "የሴት ስራ" ሲሰራ አይታዋለች፡፡ ተራኪው ይህንኑ ሲነግረን "ሚስቱ ግን ከሰው ቆጥራ ደክሞታል ብላ ማናቸውንም ነገር ቢሆን አሰናድታለት አታውቅም" ይለናል፡፡ እዚህ ላይ ተረቱ የሁለቱንም ድርጊት እንደ አርዓያ አልቆጠረውም፡፡ ባል የሴትን ስራ መስራት የለበትም፣ ሚስትም ባሏን መንከባከብ አለባት የሚል አቋም አለው፡፡ በተለያዩ ተረቶች ውስጥ ባሎቻቸውን የተንከባከቡ ሴቶችን ያሞግሳቸዋል፡፡ ለምሳሌ ተረት 78 ውስጥ ያለችውን ታታሪ ሴት "አሁን አንቺም ትሞቺ ይሆን?" ይላታል፡፡ ተረት 81 ውስጥ ያለችውን "እናት ለምኔ" የሚል በጎ ስም ሰጥቷታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ይዘት ያላቸው ተረቶች በቤት ውስጥ እየተነገሩ መቀጠላቸው በልጆች ሥነልቡና ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው አይቀርም፡፡ ለሴቷም

ሴትነቷን ለወንዱም ወንድነቱን ያሰርጻሉ፡፡ በዚህም የተነሳ በተባለጥ ላይ የተመሰረተው ሥርዓት እድሜውን ማራዘሙ አይቀርም፡፡

በሌላ በኩል ከተረት ቅንጫቢዎቹ እንደተረዳነው የሴት የሥራ ድርሻ በቤት ውስጥ፣ የወንዱ ደግሞ ከቤት ውጭ ባለ ስራ ላይ እንዲወሰን ያደረገ ነው፡፡ ሴቶች ወጣ ብለው ሌላውን ዓለም እንዳያዩ፣ ትኩረታቸው በሙሉ ወደ ቤት ውስጥ ስራዎችና ወደየባሎቻቸው እንዲሆን የሚያደርግ ነው፡፡ ይሄ በተራዛሚ ወንዱ የኢኮኖሚውን የበላይነት እንዲይዝ ረድቶታል፡፡ ባጠቃላይ ሆን ተብሎ ሰናይ ታሪክ ስላላቸው ሴቶች በተረቶች በተደጋጋሚ ማውራት የወንዱን የበላይነትና የሴቶችን የባሎቻቸው አገልጋይነት ለማጠናከር ይረዳል ለማለት ያስደፍራል፡፡

## 5.2.4 እኔን ያየህ ተቀጣ

ይህ ንዑስ ርዕስ ከላይ በተራ ቁጥር 6.2.3 ከተጠቀሰው በተቃራኒ የሚታይ ነው፡፡ በተረቶች ውስጥ ሰናይ የተባሉት ሴቶች ራሳቸውም አሳዳጊዎቻቸውም ይመሰገናሉ፤ በባሎቻቸው ይወደዳሉ፡፡ ኑሯቸውም የተቃና እና የፍቅር ይሆናል ተብሎ ይታሰባል፡፡ እንዲህ ዓይነቶቹ ሴቶች ለምድራዊ ሴቶች አርዓያ በመሆንና በጎ ተጽዕኖ በማሳደር ሴቶችን ለባሎቻቸው ፍጹም ታዛዦች ለማድረግ ያስችላሉ፡፡ በተቃራኒው ያሉት ሴቶች ደግሞ በመጥፎ ድርጊታቸው እስከሞት የሚያደርስ ቅጣት ይፈጸምባቸዋል፡፡ ይህም እንደቀደመው ትምህርት በመስጠት የሴትን ባህሪ ለወንድ በሚመች መልኩ ለማመቻቸትና ፈርተው እንዲኖሩ ተጽዕኖ ያደርጋል፡፡ ለወንዱም ቢሆን ሚስቱን በዚያ መንገድ እንዲቀርጽ ግንዛቤ ይሰጣል፡፡

በብዙ ሚቶሎጅዎች ውስጥ በተደጋጋሚ ሲጠቀስ እንደሚስተዋለው የቀደምት ሴት ነገስታት በጨካኝነታቸውና በአስቸጋሪ ጥያቄዎቻቸው ይታወቃሉ፡፡ በዚህም ባህሪያቸው በአብዛኛው በመጥፎ አርዓያነት ይታወሳሉ፡፡ ለምሳሌ የሲዳማዋ ንግሥት ሞቲቴ (ብሌን 2006 ቁጥር 6)፣ የጉጂ ኦሮሞዋ ንግሥት Akko Manoyye (Ayalew 2012:49)፣ የጅማ ኦሮሞዋ ንግሥት Makka Ware (Abreham 2000) እና በዚህ ጥናት በተረት 25 ውስጥ ስሟ ያልተጠቀሰው የአይቻሏ እመቤት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ የእነዚህ ነገሥታት ታሪካቸው ሲታይ ሥልጣናቸውን ክፋት እንጂ እድሜ አልቀማቸውም፡፡ የማይሆን ነገር በህዝባቸው ላይ ሲጥሉና እናደርጋለን ሲሉ ሞታቸውን ጠርተዋል፡፡ አርዓያ ሆነው አልተጠቀሱም፡፡ ከእነርሱም በኋላ በሚቶሎጂው ታሪክ ውስጥ ሴቶች

የነገሱበት አጋጣሚ አልተከሰተም፡፡ ወንዱም ሴት ሁለተኛ እንዳትነግሥ ክፋታቸውን እያጎላ፣ በየተረቱ እየሰበከ ሲያጸናው ቆይቷል፡፡ በሰናይ ባህሪያቸውና በአርዓያነትም አልጠቀሳቸውም፡፡ እነዚህ ታሪኮች በጥቅሉ የሚናገሩት ከባህሪያቸው የተነሳ ለሴት ሥልጣን የማይገባ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን በዓለም ታሪክ አገራቸውን በጥሩ ሁኔታ የመሩና በዓለም ስማቸው የተጠራ የሉምን? ብንል መልስ ያጥረናል፡፡ ባጭሩ የኛዋን ንግሥተ ሳባን መጥራት ይቻላል፡፡ እዚህ ላይ ለማለት የተፈለገው አባዊው ዓለም የማይመቸውን የሴት ባህሪ በተረት እየሰበከ፣ በዚያው ተረት ውስጥ እነሱኑ ከባድ ቅጣት እየቀጣ ዝቅተኛነታቸውን አምነው እንዲቀበሉ ጥሯል፡፡ ይሄ እንዴት ሊሆን እንደቻለ አብነቶችን ጠቃቅሰን እንመልከተው፡፡

አማቷን በረሃብ ስትቀጣና በኋላም በገመድ እንድትታነቅላት ስታደርግ የነበረችው ሴት ባዘጋጀችው ገመድ ራሷ ታንቃለች (ተረት 33)፡፡ የባሏን የማይነገር ጥብቅ ምስጢር (በፈጣሪው የተነገረውን እና ማስጠንቀቂያ የታከለበትን) ካላወቅሁ ያለች ሚስት ፍቺ አጋጥሟታል (ተረት 24)፡፡ ዓይነ ስውር ባሏን ባግባቡ መንከባከብ ያልፈለገች፣ እንዲሁም ከምግብ ጋር መርዝ ቀላቅላ ለመግደል ጥረት ያደረገችው ሚስት እሷው ባዘጋጀችው ሶስት ወንድሞቿን፣ ራሷንና እናቷን ለሞት አሳልፋ ሰጥታለች (ተረት 36)፡፡ የባሏን አባት ጫካ ውስጥ እንዲጣል ያደረገችው እንዲሁ የራሷን አባት በጅብ አስበልታለች (ተረት 39)፡፡ እነ ተረት 47፣ 48፣ 63፣ በዚሁ ዓይነት መንገድ የተዋቀሩ ናቸው፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ሴት ባለታሪኮች ድርጊታቸው ፍጹም ጭካኔ ቢሆንም የደረሰባቸው መከራ ግን ከሚዛን በላይ ነው፡፡ እንዲህ የሆነው እነዚያን ሴቶች መቀጣጫ በማድረግ በየቤቱ ያሉትን ሴቶች ለማስተማር ነው፡፡ በተረቶች ውስጥ የተወሰደው እርምጃ ፍጹም የማያዳግም፣ ይቅርታ ያልተደረገበት ነው፡፡ ይህ በሴቶች አዕምሮ ውስጥ ምን ሊፈጥር እንደሚችል ግልጽ ነው፡፡ ባንድ በኩል ደግሞ በአብዛኛው ቀጪው ወንድ (ባል) አለመሆኑ ወይም ፈጣሪ አይቶ የስራቸውን ሰጣቸው የሚባል ዓይነት ስለሆነ የፍርሃት መጠናቸውን ይጨምራል፡፡ ባጠቃላይ ሥነልቡናዊ ተጽዕኖ ያሳድርባቸዋል፡፡ በዚህ መልክ ግን ወንድ ሲቀጣ የሚታይበት አጋጣሚ አይስተዋልም፡፡ ወንድ በንግሥናው ዘመን ሳያጠፋ ቀርቶ አይደለም፡፡ እንደ ሴቶቹ ነገሥታት ሁሉ ህዝባቸውን በማይሆንና መልስ በሌለው ጥያቄ አስቸግረዋል፡፡ ለምሳሌ ተረት 9 እና 92 ይጠቀሳሉ፡፡ በነዚህ ተረቶች ውስጥ ንጉሦቹ እንደ ንግሥቶቹ ቅጣት ሲሰነዝርባቸው አይታይም፡፡ ተግባራቸው ቅጣት

ሊያስነዝርባቸው ቀርቶ ቅሬታ እንኳን አይነሳባቸውም፡፡ ቀደም ብለን ተረቶች ለወንድ ያደሉ ናቸው፤ የወንድን መብት በጥቅሉ አባዊ ሥርዓቱን በነበረበት ለማስቀጠል ያለሙ ናቸው ያልነው ለዚህ ነው፡፡

## 5.2.5 የወንድን አወንታዊ ገጽታ እና አስፈላጊነት ማጉላት

ወንዶች በሴቶች ላይ የበላይነታቸውን ከሚያሳዩባቸው አጋጣሚዎች ውስጥ አንዱ የራሳቸውን ገጽታ እና አስፈላጊነት ከፍ አደርጎ በማጉላት ነው፡፡ በእንግሊዝኛ ብዙ ጊዜ ተደጋግሞ የሚሰማ የህይወት መመሪያ የሚመስል ጥቅስ አለ፤ "The first impression is the last impression." የሚል፡፡ ጥቅሱ አንድ ቀን ገጽታህን ከገነባህ ወይም ካበላሸህ ለዘላለሙ በዚያው ትታወቃለህ የሚል አንድምታ አለው፡፡ በእኛም አገር "ሱሪ አንድ ቀን ነው" ይባላል፡፡ ሱሪ እዚህ ላይ ጀግንነት ወይም ወንድነት ለማለት ነው፡፡ አባባሉ አንድ ቀን እንደምንም ተሚሙቶ ጀብዱ መፈጸም ዘላለም ያስከብራል ለማለት ነው፡፡ ይህ የተባለው ባል በሚስቱ አዕምሮ ውስጥ የሚቀርጸው የእርሱ ማንነት ለሚስቱ ተገዥነት አስተዋጽኦ ያደርጋል ለማለት ነው፡፡

"የመጨረሻዋ ታዛዥ ሚስት" በሚል በተረት 71 የቀረበው ታሪክ የዚሁ ማሳያ ነው፡፡ በተረቱ ውስጥ አቢይ ባለታሪክ የሆነችው ሴት ከሁለት ታናናሽ እህቶቿ ተለይታ በቁንጅና፣ በቅልጥፍና እንዲሁም በብልሃት የላቀች ስትሆን ግን ጠብ ጫሪና የማትታዘዝ ሆናለች፡፡ የርኅሩኅ አባቷን ቃል እንኳ ዘወትር ታጥፍ ነበር፡፡ ቁንጅናዋን አይተው ሊያጯት የመጡት ሁሉ ባህሪዋን ካባቷ ሲሰሙ ይተዋት ነበር፡፡ እንዲያውም አባትዮው "ጠብ ቆስቋሽ፣ ያሏት የማይገባት ተከራካሪና ግትር ናት" እያሉ ያሳጧት ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ሁለት ባሎች ካለፏት በኋላ ሶስተኛው ግን "ምንም ዓይነት ጥፋት ቢኖራት እኔ በጣም እፈልጋታለሁ" ብሎ አግብቷታል፡፡

ከጋብቻቸው ቀን ጀምሮ የሚያሳያት የእሱ ማንነትና አቋም፣ ፍጹም ትዕዛዙን እንድታጥፍ የሚያደርግ አልነበረም፡፡ አግብቶ ሲወስዳት ማንም ሰው (አጃቢ) አልነበረውም፡፡ ገና በመጀመሪያው ቀን በፈረስ ወደ ቤቱ ሲወስዳት እጅግ ቆራጥና ከውሳኔው ወደ ኋላ የማይል መሆኑን አሳይቷታል፡፡ ይህንን እንዴት እንደተጠቀመበት ከተረቱ እያጣቀስን እንመልከተው፡፡

> *. . . ወዲያው በሚጓዙበት መንገድ የነበረ አንድ የሚያቋርጡት ጫካ ገቡ፡፡ በጫካው መካከል ሙሽራው ከፈረሱ ጡብ ብሎ ወርዶ አንድ ሃረግ ቆረጠና እንደቀለበት ገምዶ*

*"ይህ የሰርግሽ ስጦታዬ ነውና በምንም ጊዜ እንደ ነብስሽ እንድትይዢው" . . . "ከጅሽ እንዳይለይ፤ ይህንን ብታደርጊ አያጸጽትሽም" አላት። ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ እንግዳ ነገር ቢመስላትም ወዲያው ኪሷ ከተተችው (ተረት 71)።*

ይህ ክስተት በሙሽሮቹ የመጀመሪያ ግንኙነት ቀን (በሠርጋቸው እለት) ወደ ሙሽራው ቤት በመሄድ ላይ እንዳሉ የገጠመ ነው። ሙሽራው የበላይነቱን ለማሳየት እና ሰብዕናውን ለመገንባት ካጀማመሩ ቆራጥና ኮስታራ ሆኗል። ነገረ ስራው ሁሉ ኮምጠጥ ያለ ነው። ለዚህ ከፈረሱ ላይ የወረደበት ትዕይንት [ጡብ! ብሎ ወርዶ] አንድ ማሳያ ነው። ሥነልቡናዊ አቀራረቡ ወታደራዊ ዓይነት ባህሪ ያለው ሆኖ ይሰማል። ይህንኑ ተከትሎ ያለው ድርጊቱም ባህሪውን ያሳብቃል። ምክንያቱም "ትዕዛዜን ማክበርና ስጦታዬን መቀበል ግዴታዋ ነው" የሚል አቋም ስላለው በጋብቻ ቀን ለእጮኛ ሊሰጥ የማይችል ያልተለመደ ነገር በድፍረት አድርጓል። ይህን ያልንበት ምክንያት አንደኛ ሆኖም ተሰምቶም በማያውቅ መልኩ በወርቅ ቀለበት ምትክ ሃረግ ጎንጉኖ ሰጥቷታል። ሁለተኛ በስጦታው አያያዝ ላይ ያለው አቋም ሙሽራዋን የሚያስደነግጥ ሆኗል። "ይህ የሠርግሽ ስጦታዬ ነውና በምንም ጊዜ እንደ ነብስሽ እንድትይዢው" የሚለው አነጋገር ግዴታ መጣል ነው። ግዴታ ከላይ ወደ ታች፣ ካዛዥ ወደ ታዛዥ፣ ከአለቃ ወደ ምንዝር የሚተላለፍ መሆኑን ልብ ይሏል። ሶስተኛ የተባለችውን ባትፈጽም የማያዳግም ቅጣት ሊደርስባት እንደሚችል "ከጅሽ እንዳይለይ፤ ይህንን ብታደርጊ አያጸጽትሽም" በሚል ቁርጥ ባለ አቋም ተነግሯታል። በዚህ ድርጊትና ንግግር የገነባው የእርሱ ማንነት በሙሽራዋ ውስጥ ሰርጾ ማንነቱን ስለነገራት ስጦታውንም ትዕዛዙንም ሳትወድ በግድ ተቀብላለች። ይህንኑ ተራኪው ሲያስረግጥልን "ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ እንግዳ ነገር ቢመስላትም ወዲያው ኪሷ ከተተችው" ይለናል።

የተረቱ ቅንጫቢ፣ ሙሽራዋ ሽንፈቷን "ሀ" ብላ የጀመረችበት ቅጽበት መሆኑንም አብሮ ነግሮናል። የባለታሪኳ ቀደም ያለው የህይወት ታሪኳ የነገረን ጠብ ቆስቋሽ፣ ግትር፣ ለፊቷ ፈገግታ ያልፈጠረባት፣ የተረገመች፣ ለማንኛውም ጥያቄ አይደለም! እንጃ! የሚል መልስ የምትሰጥ እና የማትታዘዝ ልጅ እንደሆነች ነበር። እንዲህ ዓይነት ባህሪ የነበራት ልጅ ባንድ ጊዜ ተቀይራ ትዕዛዝ ተቀባይ ለመሆን የበቃችው ሙሽራው ባሳያት አቋም የተነሳ በመፍራት ነው።

ከተረቱ የተወሰደው ተከታዩ ትዕይንት የሙሽራውን የማይናወጥ አቋም ያየንበት፣ ማንነቱን ይበልጥ ለሙሽራዋ ያሰረጸበት ነው።

*ከዚህ በኋላ ጥቂት እንደተጓዙ ሙሽራዋ የእጅ ሹራቧ ወደቀባት፡፡ በድንጋጤ ጩኸቷ ዞር ብሎ ሙሽራው ውሻውን አዘዘው፡፡ "እሱን የእጅ ሹራብ አንስተህ እንድትይዘው" አለው፡፡ ውሻው ግን አላስተዋለምና ዝም ብሎት አለፈ፡፡ ሙሽራው ሄድ እንዳለ ቢመለከት ውሻው የእጅ ሹራብ እንዳልያዘ ልብ ስላለ ሽጉጡን አውጥቶ ውሻውን አዳፈነበትና መንገዱን ቀጠለ፡፡ "ምነው ምነው አያሳዝንህም እንዴ?" አለችው፡፡ "አዎ" አላት መልሶ፡፡ "ግን ትዕዛዜን አልደገምም"*

*ከዚህ በኋላ በጸጥታ ሲጓዙ ቆዩና አንድ የሚያቋርጡት ወንዝ ጋ ደረሱ፡፡ ድልድይ ስላልነበረው በወንዙ ውስጥ መሻገር ግድ ነበረባቸውና ሰውየው ለፈረሱ አለው "ተጠንቀቅ! ምንም ዓይነት ፍንጣቂ የሙሽራዬን ልብስ እንዲያበላሽ አልፈልግም" አለው፡፡ ሆኖም በተሻገሩ ጊዜ ይኸ የጎርፍ ውሃ የመሰለው የሙሽራይቱን ልብስ ብክት አድርጎት ርሶ ተገኘ፡፡ ባልየውም ሚስቱን ተሸክሞ ከፈረሱ አወረዳትና ሽጉጡን አውጥቶ ፈረሱን ገደለው፡፡*

*"ውይ! ምስኪኑ ፈረስ! ምን አለህ ምነው ገደልከው ምን ጨካኝ ነህ" አለችው፡፡ "አዎ ነገሬንና ትዕዛዜን አልደግምም" አለና ኮርቻውንና ልጓሙን ፈትቶ ኮርቻውን ለሚስቱ ሰጥቶ ልጓሙንና ሞቹውን ራሱ ተሸክሞ መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ አንቺ ያንን ተሸከሚ ብሎ ኮርቻውን ሲሰጣት ለማንገራገር ሞክራ ነበር፡፡ ግን ትዕዛዙ አንዴ ብቻ መሆኑን እስካሁን በተፈጸመው አውቃለችና ወዲያው ኮርቻውን አንስታ ጀርባዋ ላይ ጣል አድርጋ ተከተለችው (ተረት 71)፡፡*

ሙሽራው አቋሙን ያሳይባቸው ዘንድ ሁለት ምክንያቶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህም የሙሽራዋ ሻሽ መውደቅ እንዲሁም በመንገዳቸው ላይ ያለው ወንዝ መሙላትና መደፍረስ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ሙሽራው መፍትሄ ይሆናሉ ያላቸው ውሻውና ፈረሱ ናቸው፤ ውሻው ሻሹን አንስቶ እንዲከተል፣ ፈረሱ የሙሽራዋ ልብስ ሳይበላሽ እንዲያሻግር ማዘዝ ናቸው፡፡ ሆኖም ውሻውና ፈረሱ ሰዎች አይደሉምና የጌታቸውን ቃል ሰምተው፣ በቋንቋ ተግባብተው ትዕዛዙን ሊፈጽሙ አይችሉም፡፡ የተፈለገውም ይሄው ነው፡፡ ምክንያቱም ታዛዦቹ ሰዎች ተደርገው ቢሆን ኖሮ ሙሽራው አቋሙን የሚያሳይበት እድል አይኖረውም ነበር፡፡ በታሪኩ ውስጥ የሙሽሮች አጃቢ እንዳይኖሩ የተደረገው ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ስለተፈለገ ይመስላል፡፡ በዚህም የተነሳ ውሻውና ፈረሱ የሽጉጥ ሰለባ ሆነዋል፡፡ በሁለቱ ንብረቶቹ መስዋዕትነት የሚስቱን ባህሪ እሱ በሚፈልገው መንገድ ለመቅረጽ ተጠቅሞባቸዋል፡፡

ሙሽራው እንስሶችን የገደለበት ዓቢይ የመነሻ ምክንያቱ ትዕዛዙን ባለመፈጸማቸው አይደለም፡፡ እንስሳት ናቸውና ይህንን እንደማያደርጉ ቀደም ብሎም ልቡናው ያውቃል፡፡ ዋና ዓላማው ከሚስቱ ጋር ወደፊት በትዳር ሲኖር ትዕዛዙን ፈጽሞ ሊደግምላት እንደማይችል ለማሳየትና ፍጹም ታዛዥ ለማድረግ ነው፡፡ ሙሽራዋ እንስሶችን ለምን

እንደገደላቸው ስትጠይቀው "ነገሬንና ትዕዛዜን አልደገምም" ሲል የመለሰላትም የዚሁ ማሳያ ነው፡፡ በሙሽራዋ አዕምሮ ውስጥ ቀስ በቀስ እየሰረጸ የመጣውም ይሄው ነው፡፡ ከሞተው ፈረሱ ላይ የፈረስ እቃዎቹን አንስቶ ከሌሎች የከበደውን ኮርቻውን ሲያሸክማት ለማንገራገር ሞክራ ግን ትዕዛዙን የማይደግም መሆኑን ስትረዳ የተባለችውን አድርጋለች፤ ታዛዥነቷንም አስመስክራለች፡፡ ሙሽራው የራሱን ሰብዕና ግልጽ በሚያደርግበት ሂደት ውስጥ እግረመንገዱን የሚስቱን ታዛዥነት እያረጋገጠ ሄዷል፡፡ ቀደም ተብሎም "The first impression is the last impression." የተባለው እንዲህ ዓይነቱን ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ይቺን ሙሽራ ባሏ አንድ ነገር ቢያዛት ቃሉን ልታጥፍ ትችላለች? አትችልም፡፡ አለመቻሏን ተራኪው "ባልዮውም ለሚስቱ ማንኛውንም ነገር በድጋሚ ሳይናገር በአንድ ቃል ስትታዘዘው ስድስት ወራት አለፉ" ሲል አስረግጦልናል፡፡

ይህንን በተመለከተ በተረቱ ውስጥ ሌሎች ተጨማሪ ማስረጃዎች አሉ፡፡ ወደ ተረቱ መጨረሻ አካባቢ የምናስተውለው የዚሁኑ ውጤት ነው፡፡ ውጤቱም የሴቷን ቤተሰቦች ለመጠየቅ በመንገድ ላይ እየሄዱ ሳለ የተከሰተ ነው፡፡ ክስተቱ የባሏ ሃሳብ ትክክል ባይሆንም እንኳ እሱ የተናገረውን ሁሉ ያለ ተቃውሞ ለመቀበል መገደዷን፣ በዚህም እስከማመን መድረሷን ያስገነዝባል፡፡ ከተረቱ ጠቅሰን በምሳሌ እንየው፣

> *መንገዳቸውን ቀጥለው ግማሽ ጉዞ እንዳደረጉ ብዙዎቹ ጥቋቁር የዝይ መንጋ በላያቸው ላይ አንዣበው ሲያልፉ አየ [ባልየው]፡፡ "ውይ እንደምን ያሉ ነጫጭ ቆንጆ ዝዪዎች ናቸው" አለ ባልዮው፡፡ "የለም ጥቁር እኮ ናቸው" አለችው፡፡ "እረ ሊዘንብ ነው መሰለኝ" ብሎ ፈረሶችን መልሶ ወደ ቤቱ ገባ፡፡ ከዚህ በኋላ አንድ ወር እንዳለፈ "ዛሬ ቀኑ ደህና ይመስለኛል" አሁን ወላጆችሽን ማየት አትፈልጊም?" አለ፡፡ እንደቀድሞው ተዘጋጅተው ሲጓዙ የተሰማሩ ብዙ በጎች አዩ፡፡ "ውይ ምኖቹ ቆንጆ የተኩላ መንጎች ናቸው?" አለ፡፡ "የለም በጎች ናቸው" ስትል መለሰች፡፡ "እረ ዛሬም ሊዘንብ ነው መሰለኝ" ብሎ ተመለሰ፡፡ እቤትም እስከደረሱ ድረስ በሰላም ስለትዳራቸው ተወያዩ፡፡*
>
> *አሁንም አንድ ወር ካለፈ በኋላ እንደቀድሞው ዘመዶቿን ለመጠየቅ መሄድ ትፈልግ እንደሆነ ጠየቃት፡፡ ደግሞ እንደ ቀድሞው ሰረገላውን ጭኖ ተሳፈሩና ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ጥቂትም ሳይሄዱ ዳክዬዎችን በአንድ ጉርንድ ሲዋኙ አዩ፡፡ "እንዴ ምኖቹ ቆንጆዎች ቁራዎች ናቸው?" አለ፡፡ "አዎ እስከዛሬ የእነሱን ዓይነት አይቼ አላውቅም፡፡ በጣም ቆንጆዎች ቁራዎች ናቸው" አለች፡፡ . . . በሰላም አባቷ ቤት ደረሱ. . . (ተረት 71)*

እዚህ ላይ ባልዮው የተጠቀመው ስልት ፍጹም የተቀነባበረ ነው፡፡ ጥቋቁሮችን ዝይዎች ነጫጮች፣ በጎችን ተኩላዎች፣ ዳክዬዎችን ቁራዎች ሲል የተናገረው ሚስቱ ምን ያህል የሃሳቡ ተገዢ እና ቃሉን የማታጥፍ እንደሆነች ለማረጋገጥ ነው፡፡ ይህንን የምናውቀው ሚስቱ እሱ ያለውን ሳይሆን ያየችውንና እውነተኛውን ስትናገር ወይም እሱ ያለውን

ሳትደግም ስትቀር ቤተሰበቿን ለማየት የነበራትን ጉጉት አደናቅፎ ወደ ራሳቸው ቤት ሁለት ጊዜ መልሷታል፡፡ ምናልባትም መጀመሪያ ላይ ጥቋቋሮችን ዝይዎች ነጫጭ ናቸው ሲላት "አዎ! ነጫጭ ናቸው" ብላ ቢሆን ኖሮ መንገዳቸው አይሰናከልም ነበር፡፡ እሷም ብትሆን ባሏ ምን እንደፈለገ ያወቀችው ሁለተኛው ጉዟቸው ከተደናቀፈ ወዲህ ነው፡፡ ምክንያቱም ሶስተኛው ላይ ስህተት አልፈጸመችም[46]፡፡ ያለውን ደግማዋለች:: እንዳሰቡት ጉዟቸውን የቀጠሉት ዳክዬዎችን አይቶ "እንዴ ምኖቹ ቆንጆዎች ቁራዎች ናቸው?" ሲል እሷም የተናገረውን ላለመቃወም ዳክዬ መሆናቸውን እያወቀች "አዎ እስከዛሬ የእነሱን ዓይነት አይቼ አላውቅም፡፡ በጣም ቆንጆዎች ቁራዎች ናቸው" ስትል ነው፡፡ ቃሉን በመጠበቋና ፍጹም የሆነ ተገዥነቷን በማሳየቷ መንገዳቸውን ቀጥለዋል፡፡ አባቷም ከሌሎቹ ልጆቹ ለይቶ ያጠራቀመውን ወርቅ የሰጣት ለባሏ ያላትን ፍጹም ታዛዥነት አስተውሎና ከሌሎች ልጆቹ ጋር አነጻጽሮ ነው፡፡

እዚህ ላይ ዋናው ጥያቄ ይህ ሁሉ በምን መጣ? ያንን እኩይ ባህሪዋን እንዴት ተወች? የሚል ነው፡፡ ይህ የሆነው ባል ማንነቱን በመረጠው ዘዴ በማሳየቱና እንድትፈራ በማድረጉ ነው፡፡ ለውሻውና ለፈረሱ ያልራራ ለእኔም እንደዚያው ነው የሚል ስጋት በልቡናዋ ስላሰፈነ ትዕዛዙን ሳትወድ በግድ እንድትቀበል አድርጓታል፡፡ ይህም ቀስ በቀስ ባህሪዋ ሆኗል፡፡ ቀደም ብሎ የራስን ሰብዕና ከፍ አድርጎ ማሳየት ለመቆጣጠር አንዱ ዘዴ ነው የተባለው ለዚህ ነው፡፡ ይህም የኃይል ሚዛኑን ወደ ወንዶች እንዲያዘነብል የሚያደርግ፣ ቀጥታ ከሥልጣን ጥያቄ ጋር ግንኙነት ያለው ተረት ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ሴቶች ያለ ወንድ ምንም መሆናቸውን ደጋግሞ በማሳየት ልዕልናውን ለማጎልበት ጥረት የተደረገባቸው ተረቶች አጋጥመዋል፡፡ በተረት 21 ውስጥ አውራ የሌላቸው ብዙ ላሞች ጥቂት፣ አውራ ያለባቸው ጥቂት ላሞች ብዙ ተብለዋል፡፡ በተረቱ ውስጥ የተጠቀሱት ሁለቱ ብቻ ናቸው፡፡ ላሞች ስለሌሉባቸው ኮርማዎች ምንም አልተናገሩም፡፡ እዚህ ላይ የተረቱ አንድምታ ለእርባታ ወሳኙ ወንድ ነው የሚል ነው፡፡ እንዲህ መታሰቡም የወንዱን ገጽታ ያጎላዋል፡፡ ነገር ግን ሴት ከሌለ እርባታ አለ ወይ ቢባል መልስ

---

[46] እዚህ ላይ ስህተት አልፈጸመችም ስንል ባሏ ከፈለገው አንጻር እንጅ ዳክዬዎችን ቁራዎች ናቸው ማለቷን አይደለም፡፡ ተሳሳተች ልንል እንችል የነበረው ቀደም ብላ እንዳደረገችው ዳክዬዎችን ቁራዎች ናቸው ሲላት "አይ! ዳክዬዎች ናቸው" ብትል ነበር፡፡ አልተሳሳተችም የምንለው የእሱን ፍላጎት በትክክል በመረዳቷ፣ በዚህም የተነሳ ጉዟቸው ሳይደናቀፍ በመቅረቱ ብቻ ነው፡፡

ያጥራል፡፡ በተረት 52 ውስጥም እንዲሁ "ፈላሚ ማጣትስ ውርደት አይደለም እንዴ"[47] ሲባል የተነገረው ወንድ ልጅ ካለው የበለጠ ተፈላጊነት አንጻር ነው፡፡

ወንድ የራሱን ገጽታ በአወንታዊ መልኩ የገነባበት አጋጣሚ ለሴት አስፈላጊ ነው ከሚል አንጻር ነው፡፡ ሃሳቡ ሴትን ሊደርስባት ከሚችል ጥቃት ሊጠብቃት፣ መከታ ሊሆናት የሚችለው ወንድ ነው የሚል ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት ስሜት ያላቸው ተረቶች አሉ፡፡ ከነዚህ ውስጥ አንዱ በተረት 58 ወስጥ የተገለጸው ነው፡፡

> *. . . ያለ ትዳር መኖሯን የጠሉት አባቷ "እባክሽ አንዱን ያዢና ትዳርሽን መስርቺ" አሏት በልመና፡፡ እናት ጣልቃ ገባችና "የሚሆናትን እስከምታገኝ ድረስ ማግባት መፍታቷ የማይቀር ነው፤ ያ ከሚሆን የሚስማማትን እስከምታገኝ ድረስ ብትታገስ አይሻልም?" አለች፡፡ ባልየው በቁጣ "ኤዲያ! አንቺ ደግሞ የራስሽን ይዘሽ! ባል የሌላት ሴትና አጥር የሌለው ቤት ደፋሪው ብዙ ነው፡፡ ምንም ይሁን ማግባቱ ይሻላል" አሉ . . . (ተረት 58)*

በዚህ ጥቅስ ውስጥ ሴትና ቤት እንዲሁም አጥርና ባል በንጽጽር ቀርበዋል፡፡ ቤትና ሴት ተደፋሪ ሲሆኑ አጥርና ባል ደግሞ መከታዎች ሆነዋል፡፡ አጥር ለቤት እንደሚያስፈልግ ሁሉ ባልም ለሴት የግድ እንደሚያስፈልጋት ታምኖበታል፡፡ አባትም "ባል የሌላት ሴትና አጥር የሌለው ቤት ደፋሪው ብዙ ነው" ሲሉ አጥብቀው የመከሩት ለዚሁ ነው፡፡ አባት ለልጃቸው የሚሆናትን ባል የመምረጫ ጊዜ እንኳን ሊሰጧት ፈቃዳቸው አይደለም፡፡ አቋማቸው ከባለቤታቸው ተቃራኒ ነው፡፡ እናት "የሚሆናትን እስከምታገኝ ትታገስ" ሲሉ አባት ግን "ትደፈራለች" በሚል የመጣላትን እንድታገባ ሲያስገድዷት ይታያል፡፡ ምርጫ እንድታደርግ እንኳ መታገስ የፈለጉ አይመስሉም፡፡ እንዲያውም "ምንም ይሁን ማግባቱ ይሻላል" ሲሉ በቁጣ ተናግረዋል፡፡

"ምንም ይሁን" የሚለው አገላለጽ አባት [ወንድ] ለሴት ያለውን ንቀት ያሳያል፡፡ ንግግሩን የምንሰማው ባልና ሚስቱ በልጃቸው ትዳር ምክንያት ሲጨቃጨቁ ነው፡፡ ልጂት ባሏ ከሞተባት በኋላ ሁለት ባሎችን በተከታታይ አግብታ በራሷ መስፈርት መሰረት እንደማይሆኗት ስታረጋግጥ ፈትታቸዋለች፡፡ በዚህም የተነሳ ከማግባት አለማግባት

[47] የመቃብር ቦታ ሲዘጋጅ ቁፋሮውን የሚጀምረው ሰው ፈላሚ ይባላል፡፡ ይህ ሰው የሟች/የሟቿ ልጅ፣ አባት፣ ወንድም፣ ወይም የቅርብ ዝምድና ያለው ወንድ ነው፡፡ የጥናቱ መረጃዎች በተሰበሰቡባቸው ወረዳዎች ውስጥ (በክርስትናውም በእስልምናውም) ሴት ፈጽሞ ቀብር ፈላሚ አትሆንም፡፡ ሟቹ/ሟቿ ወንድ ልጅ ካለው /ካላት የግዴታ የመጀመሪያው ልጅ ፈላሚ ይሆናል፡፡ የሟቾቹ ልጆች ሴቶች ብቻ ሆነው ፈላሚ ወንድ ልጅ ከሌላቸው ክብራቸው ይቀንሳል፡፡ በተረት 52 ውስጥ ያሉት አባት ልጃቸው አከታትሎ ሁለት ሴቶችን በመውለዱ ተቆጭተው "ፈላሚ ማጣትስ ውርደት አይደለም እንዴ!" ያሉት ከዚህ አንጻር ነው፡፡

ይሻላል በሚል እንደተቀመጠች፣ በአጋጣሚም ባል ሳይመጣላት በመቅረቱ ሳታገባ ብዙ ትቆያለች፡፡ የእናትና የአባት የጭቅጭቃቸው መነሻ ይሄ ነው፡፡ እናት “የሚሆናትን እስከምታገኝ ትቆይ” ይላሉ፡፡ አባት ደግሞ “አይ! ማግባት አለባት” ይላሉ፡፡ በዚህ ውዝግብ መሃል አባት ተበሳጭተው “ምንም ይሁን ማግባቱ ይሻላል” ይላሉ፡፡ ይህንን ለማለት ያበቃቸው አንድም ልጃቸው እያገባች መፍታቱን በመጥላታቸው፣ ሁለትም እናት የልጃቸውን ሃሳብ በመደገፋቸው ይመስላል፡፡ አንድምታው እናትና ልጅን “እናንተ እነማን ናችሁና ነው ባል የምታማርጡት፤ ምንስ ቢሆን ወንድ መሆኑ ብቻ አይበቃም ወይ? እናንተ ምንስ ያህል ብትበረቱ ራሳችሁን ከመደፈር ልትከላከሉ ትችላላችሁ ወይ?” የሚሉም ይመስላል፡፡ ይህንን ለማለት የሚያስደፍረን “ባል የሌላት ሴትና አጥር የሌለው ቤት ደፋሪው ብዙ ነው” ሲሉ የተናገሩት ከዚህ ሃሳብ ጋር የሚተባበር በመሆኑ ነው፡፡ ይህንን ደግሞ በጥቅሉ ስንመለከተው በአዕምሯቸው ውስጥ ለሴት ያላቸው ግምት ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ወንድ ለሴት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ለማስረጽም ተጠቅመውበታል ለማለት ይቻላል፡፡

በጠቅላላው ከላይ ባየናቸው ተረቶች ውስጥ ወንድ ከሴት ያስበልጡኛል ብሎ ባመነባቸው ነጥቦች ዙሪያ የራሱን ሰብዕና መገንባቱን ተመልክተናል፡፡ በሴቶች ላይ የበላይነቱን ያስይዙኛል ያላቸውንም ድርጊቶች ሲፈጽም አስተውለናል፡፡ እንዲህ ዓይነት ይዘት ያላቸው ተረቶች በተደጋጋሚ ሲነገሩ በአድማጮች ላይ ተጽዕኖ ማሳደራቸው፣ የባህሪ ለውጥ ማምጣታቸውና ሰዎች በዚያው ውስጥ እንዲኖሩ ማድረጋቸው አይቀርም፡፡ በመሆኑም ሴቶችን ለመቆጣጠርና የበላይነቱን ለመያዝ እንደ አንድ ስልት አገልግለዋል ለማለት ያስደፍራል፡፡

## 5.2.6 የሴቶችን ፍላጎትና ባህሪ ማጉላት

ማንኛውም ሰው የየራሱ ፍላጎትና ከሌላው የሚለየው ባህሪ አለው፡፡ እንዲሁም በጥቅል በተፈጥሮ ካለ ተመሳሳይነት የጋራ የሆነ ፍላጎትና ባህሪም ይኖራል፡፡ ሴትና ወንድ በጋራ ሰው በመሆናቸው የሚጋሯቸው ፍላጎቶችና ባህሪዎች አሏቸው፡፡ እንዲሁም በጾታ በመለያየት ምክንያት ወንዶች ከሴቶች በተለየ መንገድ የግላቸው የሆነ ፍላጎትና ባህሪ ይኖራቸዋል፤ ሴቶችም እንደዚሁ፡፡ በዚህ የተነሳ ሁለቱም ጾታዎች ካላቸው የየግል ፍላጎትና ባህሪ ወንዱ ከሴቷ፣ ሴቷ ከወንዱ እንዲሆኑላቸው የሚጠብቁት ባህሪ ይኖራል፡፡

ወንዱ የምትታዘዘው፣ የምትንከባከበው፣ ከቃሉ የማትወጣ፣ በሃብትም በትምህርትም ከእርሱ ዝቅ ያለች፣ የቤት ውስጥ ሙያ ያላት ሚስት ይፈልጋል፡፡ ካገባም በኂላ ይህንኑ ለማስጠበቅም ጥረት ያደርጋል፡፡ ሴቷም በበኩሏ ጀግና፣ ደፋር፣ ሃይለኛ፣ አትንኩኝ ባይ፣ መከታ የሚሆናት፣ ጥቃት የማይወድ፣ በሃብትም በትምህርትም ከእርሷ የተሻለ፣ በምቾት ሊያስተዳድራት የሚችል ባል ትፈልጋለች፡፡ እንዲህ ዓይነቱን የባል እና የሚስት ቅንጅት ለጥናት በተሰበሰቡት ተረቶች ውስጥ በቀጥታ ተጠቅሶ አናገኘውም፡፡ ይህንን የምናገኘው ተረቶቹ በመግቢያቸው ላይ ገጸባህሪዎቻቸውን ሲያስተዋውቁ ከሚጠቅሷቸው አመላካቾች ነው፡፡ በተረቶች ውስጥ ያለው የባል እና የሚስት ቅንጅት በማኀበረሰቡ ውስጥ ያለው ነጸብራቅ ስለሆነ ይህንኑ እናያለን፡፡ ወንዱ ባብዛኛው ከሴቷ ቁንጅናን እና ሙያን ሲጠብቅ፣ ሴቷ በበኩሏ ከወንዱ ሃብትን፣ ጥሩ ሰውነትንና ጀግንነትን ትፈልጋለች፡፡ ለዚህ ማሳያ የሚሆኑ ተረቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ "በአንድ አገር ውስጥ አንድ የታወቀ ባለጸጋ ነበር፡፡ ባለጸጋው ብዙ አሽከሮችና በቁንጅናዋ አንቱ የተባለች ሚስት ነበረችው" (ተረት 8)፣ ሚስትየዋ ማንም የሚመኛት ውብ ስትሆን ባልየው ደግሞ ጥሩ ሰው የሚባል ነበር (ተረት 55)፣ ልዑሉ ታዲያ በጣም ጀግና፣ ታዋቂ እና በጣም ደፋር ነበር፡፡ ልዕልቷ በበኩሏ በውበቷ ወደር የለሽ ቆንጆ ነበረች (ተረት 64) ወዘተ. እያሉ በተዘዋዋሪም ቢሆን ማን ከማን ምን እንደሚፈልግ ያመለክታሉ፡፡ ምሁራንም በድርሳኖቻቸው ጠቅሰውታል፡፡ ለምሳሌ እነ Eagly, Eastwick and Schmdit (2009:404) እና David (2010:720-729) ሴቷ በዕድሜ የሚበልጣትንና ሃብት ያለውን ስትመርጥ ወንዱ ደግሞ በዕድሜ ከእሱ የምታንሰውን፣ ቆንጆና ጥሩ የቤት ውስጥ ሙያ ያላትን ይመርጣል ሲሉ ያስረዳሉ፡፡[48] እንዲህ ዓይነቱ የትዳር አጋር ምርጫ በተለይ ሴቶች ሃብት ያለውን ሃይለኛውን መምረጣቸው በተጽዕኖ ስር ለመውደቃቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

---

[48] ይህ በአብዛኛው ለማለት እንጂ ሁልጊዜ ነው ለማለት አይደለም፡፡ በጣም ሃብታም ሴቶች ድሃ እና በዕድሜ ከእነሱ ያነሱ ወንዶችን አግብተዋል፡፡ ለምሳሌ የነብዩ ሙሃመድን እና የከድጃን ጋብቻ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ነጋዴዋና ሃብታሟ ከድጃ በርካታ ሃብታም ባሎች ቢመጡላቸውም አንዳቸውንም አልፈቀዱም፡፡ ሆኖም ግን ሃብት የሌላቸውን፣ በ25 ዓመት የሚበልጡትን ወጣቱን ሙሃመድን በራሳቸው ፈቃድና ጠያቂነት (በቅርብ ጓደኛዋ በነፊሳ አግባቢነት) ለማግባት በቅተዋል፡፡ በእርግጥ ለዚህ ጋብቻ መፈጸም ምክንያት ነበረው፡፡ አንደኛ ሙሃመድ ነብይ ከመሆናቸው በፊት በንግድ ላይ እያሉ ደክሟቸው ጥላ ስር እንደተኙ ፀሐይ እንዳያቃጥላቸው ሁለት መላዕክት በደመና እንደከለሉላቸው ከድጃ ሰምተዋል፡፡ ወደፊት ነብይ የመሆናቸው ነገር በከድጃ ልቡና ውስጥ ቦታ አግኝቷል፡፡ ሁለተኛም ከድጃ በህልማቸው ግቢያቸው በብርሃን ሲሞላ አሳይቷቸዋል (https://en.wikipedia.org/wiki/Khadija_bint_Khuwaylid)፡፡፡ ይህም ከሙሃመድ ነብይነት ጋር ሊያያዝ እንደሚችል ህልም ፈቺዎች ነግረዋቸዋል፡፡ የእነዚህ የሁለቱ ክስተቶች ግጥምጥሞሽ (የአላህ ፈቃዱ

የወንድ ሃይለኛ መሆንና ሴቶች ይህንን የወንድ ባህሪ መውደዳቸው ሌላው የተጽዕኖ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡ ባልና ሚስቱ በትዳራቸው መሃል ችግር በገጠማቸውም ጊዜ ለመስማማት የሚደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ ከዚህ ካለፈ ግን ወንዱ ብዙውን በማስገደድ፣ በቁጣ፣ ከፍ ሲል በድብደባ እና በኃይል ነገሩን ለመፍታት ይጥራል፡፡ ሴቷ ግን ምርጫ ስታጣ የምታደርገው አንድም በፍቅር ቀርቦ በማግለልና በማባበል፣ አንድም በለቅሶ በማሳዘን ሃሳብ ለማስቀየር ሙከራ ታደርጋለች [ምእራፍ አምስት ላይ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ ያሉ ሴቶች ተልዕኳቸውን ማሳካት የቻሉት በፍቅር ቀርበው መሆኑን ልብ እንላለን]፡፡ ከዚህ ያለፈ እርምጃ ለመውሰድ ብዙም ስትጥር አትታይም፡፡ እነዚህን እና ሌሎችንም ባህሪያት ሴቶችም ወንዶችም የሚያምኑባቸው ይመስላል፡፡

ወንዱ በሴቷ ላይ ተጽዕኖ ለማሳደር እነዚህን ፍላጎቶችና ባህሪዎች ተንተርሶ ሁኔታዎችን ያመቻችባቸዋል፤ ሴቷም በወንዱ ስር ጥገኛ የመሆንና የመሸነፍ ስሜት ተዋህዷት እንድትኖር ያደርጋታል፡፡ ይህ ከትዳሩ ዓለም አልፎ በማኅበራዊው፣ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው ውስጥ የራሱን ተጽዕኖ በማሳደር ለሥርዓተ ጾታ ኢፍትሃዊነት መስረጽ አስተዋጽዖ ያደርጋል፡፡

ይህንን የመሰለውን ሃሳብ የሚሰብኩ ተረቶች በስፋት ይስተዋላሉ፡፡ ወንዱም የበላይነቱን ለማረጋገጥ ከሚጠቀምባቸው ስልቶች ውስጥ አንዱ ሴቶች የሚፈልጉትን ግን በተዘዋዋሪ በወንዱ ቁጥጥር ስር ለመዋላቸው ምክንያት ናቸው የሚላቸውን ተረቶችን በተደጋጋሚ በመተረክ ነው፡፡ ይህን በተረት እንመልከት፡፡

ተረት 15 ላይ የአንበሳው ሚስት፣ “ቀበሮ ምን ቢንቅህ ነው መጥቶ ያልጠየቀህ?” ስለዚህ እሱን ጠርተህ መግደል አለብህ!” ብላ ታሞ የነበረውን ባሏን ትመክረዋለች፡፡ እዚህ ላይ ምክሯ የኃይል እርምጃ እንዲወስድ ነው፡፡ የኃይል እርምጃ እንዲወስድ ደግሞ የግድ ኃይለኛ መሆን አለበት፤ ሚስቱም ክብር ትሰጠው፣ ታደንቀው ዘንድ ያለችውን ማድረግ አለበት፤ ሴት የላከው ጅብ አይፈራም እንዲሉ፡፡ ተረት 41 ላይ አንዲት ሚስት ባሏ አምሽቶ ሲመጣ “ለምን አመሸህ?” ስትለው “ይገርምሻል መንገድ ላይ ሁለት ሆነው ጠብቀውኝ አንዱን በቡጢ አንዱን በእርግጫ ብያቸው መጣሁ” ይላታል፡፡ እሷም በባሏ ጀግንነት ተደስታ ጥሩ እራት ሰርታ ጋብዛዋለች፡፡ ተረት 54 ውስጥ አንድ ዝንጀሮ

---

ሆኖ) ከድጃ ሙሃመድን ለማግባት በቅተዋል፡፡ ጋብቻውም ተራ ጋብቻ ሳይሆን በርዕይ የተመራ ቅዱስ ጋብቻ ነው፡፡

ለአንዲት አንበሳ የዓይኑ የጎደጎደው ያነጣጠረበት፣ ጣቱ የሰለሰለው ምላጭ የሳበበት፣ ቂጡ የተመለጠው ፈረስ የጋለበበት፣ ደረቱ የተላጠው የመሳሪያ ሰደፍ ያስደገፈበት መሆኑን ዋሽቶ ሲነግራት በፍቅር ወድቃለች፡፡ እንዲያውም ባሏን በመናቅ ዝንጀሮውን በልቧ "የእኔ ባል ቢሆን" ብላ ተመኝታለች፡፡ እዚሁ ተረት ውስጥ ባሏ (አንበሳው) ውሸታሙን ዝንጀሮ በፈርጣማ ክንዱ አንቆ ሲያስጨንቀው አይታ እንደገና ሃሳቧን ቀይራ ለባሏ እጥፍ ከበሬታ አድርጋለች፡፡ እነዚህን ተረቶች መለስ ብለን ብናያቸው የሴቶች ፍላጎት ምን እንደሆነ እናጤንበታለን፡፡ ባጭሩ ሃይለኛ ወንድ ይወዳሉ ለማለት ያስደፍራል፡፡

በአንዳንድ የአገራችን አካባቢዎች የጀግና ወይም የገዳይ ሚስት በውሃ መቅጃ ቦታዎች ወረፋ ሳትጠብቅ እንደደረሰች ቀድታ የመሄዷ ምክንያት በባሏ ጀግንነት የመከበሯ ነገር ነው፡፡ ሌሎችም ሴቶች ያለ ወረፋዋ ቀድታ ስትሄድ "ለምን?" አይሉም፤ እሷም ማንንም አትጠይቅም፡፡ ምክንያቱም ባሏ ገዳይ ነዋ! ሴቶች እንዲህ ዓይነቱን ማኅበራዊ ክብር ለማግኘት ጀግና ባል ይፈልጋሉ፡፡ አንበሳዋም ይህንን ማኅበራዊ ክብር በመፈለግ የዝንጀሮውን ባልነት አጥብቃ ፈልጋ ነበር፡፡ ጥሩ ምግብ አብልታ ከእሱ ጋር ለመተኛት የገፋፋትም ይሄው ነው፡፡ ይህን የመሰለው አድራጎትና ፍላጎት በሂደት ምን ያመጣል? ዋና ጥያቄ ነው፡፡

እነዚህ የተረት ቅንጫቢዎች የሴትን ኃይለኛ ወንድ ወዳድነት ይናገራሉ፡፡ ቀድሞውኑ ጀግንነት ለወንድ ተሰጥቷልና በተረቶች ውስጥ ሴት ስታደርገው አትታይም፡፡ ጀግንነት የወንድ ባህሪ ነውና ሚስቱም ብታስቀይመው የከፋ ባይሆን እንኳ ያንኑ በእሷ ላይ ማድረጉ አይቀርም፡፡ በዚህም ሴቷ ባሏን ፈሪ ሆና ትቀራለች፡፡ ፍርሃቷም ወንዱን የሚፈታተን ጥያቄ እንዳታቀርብ ያደርጋታል፡፡

ተረት 58 ውስጥ ባሏ የሞተባት አንበሳ ሃዘኗን እንደጨረሰች አንድ ጥቁሬ እና ሌላ ነጬ ዝንጀሮዎችን በተከታታይ አግብታ ነበር፡፡ ሆኖም በመልካቸው ማማርና በአረማመዳቸው ተስባ ብታገባቸውም እወንድነቱ (ጀግንነት) ስራ ላይ ስለሌሉበት ሁለቱንም ወዲያውኑ ፈትታቸዋለች፡፡ ይህንን እውነታ ተረቱን ጠቅሰን እንመልከት፡፡

> *. . . ያ የዝንጀሮ ግመርም በግርማ ሞገሱ፣ በኩሩ አረማመዱ ገምሽር! ገምሽር! ገምሽር! እያለ አካሄዱን አሳያት፡፡ አንበሲትም በአካሄዱ ተመስጣ ወደደችው . . . አገባችው፡፡ አንድ ቀን ሌሊት ለአደን . . . ተያይዘው ሄዱ፡፡ አንበሲት "እኔ በረት ገብቼ አንዱን በሬ አስበርግጌ ሳስወጣልህ ውጭ ላይ ይዘህ ጠብቀኝ" አለችው፡፡ . . . ዝንጀሮ*

*የደነበረውን በሬ ሲያይ . . . በፍርሃት ቧ…ቧ…ቧ…ቧ… እያለ በሬውን ሳይዘው ቀረ፡፡ አንበሲትም . . . ተናደደችና "አንተ ባሌን ስለማትተካው ፈትቸሃለሁ" ብላ ጥላው ተመለሰች፡፡*

*በሌላ ጊዜ ደግሞ ይቺኑ የአንበሳ ቆንጆ . . . ነጭ የዝንጀሮ ግመር ለሚስትነት ሊጠይቅ ወደ አንበሲት ቤተሰቦች ዘንድ ሄደ፡፡ . . . ጋብቻው ተፈጸመ፡፡ . . . ለአደን ወደ አንድ ጫካ ሄዱ፡፡ በጫካውም ውስጥ አንድ ባለ ሹል ቀንድ ትልቅ አጋዘን አዩ፡፡ አንበሲት . . . ከዚያ በኩል ቀድማ ወደ ዝንጀሮው በኩል ስታሯሩጠው አጋዘኑ ቀንዱን ቀስሮ ወደ ዝንጀሮው ፈረጠጠ፡፡ ዝንጀሮው ያንን የሾለ ቀንድ ሲመለከት እግሬ አውጭኝ ብሎ ዛፉ ላይ ተንጠላጠለ፡፡ በዚህ የተበሳጨችው አንበሳ "አንተ ጅል! ዛላው መልካም" በማለት ተሳድባ ጥላው ሄደች፡፡*

*. . . አቶ ነብር አንበሲትን ለሚስትነት ሊጠይቅ . . . መጣ፡፡ . . . አንበሲት ግን ፈቃደኛ አልሆን አለች፡፡ "ደግሞ ይህንን ለባቃ አካሄዱ የማያምር ላገባ ነው እንዴ?" በማለት አይሆንም አለች፡፡ ነገር ግን ባባቷ ተጽዕኖ ምክንያት እንድታገባ ሆነ፡፡ ከተጋቡ በኋላ . . . አደን ሄዱ፡፡ . . . እንደልማዷ "ከበረት ገብቼ የማስወጣልህን ኮርማ በሬ ውጭ ጠብቀህ አንገቱን ጠምዝዘህ ጠብቀኝ" አለችው፡፡ ነብሩም ከበረት የወጣለትን ትልቅ በሬ ብዙም ሳይርቅ በመያዝ አንገቱን ጠምዝዞ፣ ቀንዱን ከመሬት ቸክሎ በፉከራ እያጉራራ ጠበቃት፡፡ አንበሲትም "ዛሬ ነው ባሊቱን ያገኘኋት" በማለት እያመሰገነች በሥጋ ኖረች . . . (ተረት 58)*

ይህ ተረት የሴቶች የትዳር አጋር ምርጫ መለኪያ ከቁንጅና ይልቅ ጀግንነት መሆኑን ያመለክታል፡፡ በቁንጅና ቢሆን ኖሮ ከሁለቱ ዝንጀሮዎች አታልፍም ነበር፡፡ የመጀመሪያው ዝንጀሮ ግርማ ሞገስ ያለው ባለኩሩ አረማመድ ነበር፡፡ ሁለተኛውም እንዲሁ መልካም ዛላ ያለው ነበር፡፡ ሁለቱም ለዓይን ሲታዩ ውቦች ነበሩ፡፡ አንበሳይቱም የዝንጀሮዎችን ጀግንነት ልታረጋግጥ ባልቻለችበት ጊዜ እንደ መምረጫ መስፈርት የተጠቀመችው ውበታቸውን ነበር፡፡ ሆኖም በኑሯቸው ውስጥ የሁለቱንም ፍርሃት ስታረጋግጥ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፈትታቸዋለች፡፡ ምክንያቱም ዋናው መለኪያዋ ጀግንነት ስለነበረ ነው፡፡ የቦረና ወረዳ ወጣቶች በሆታ[49] ግጥም፡-

አንተም ሴት እኔም ሴት አለችው ወዳጁ፣
የሰፋ ስባሪ ብታጣበት በእጁ፡፡

የሚለውም ይህንኑ የጀግና ምርጫ ያሳያል፡፡ በተረቱ የመጨረሻ ቅንጫቢ ላይ ግን መልኩ ያላማራትን ነብር አላገባም በሚል እንቢታዋን ገልጻ ነበር፡፡ እንዲያውም "ለባቃ" ስትል ተሳድባለች፡፡ ሆኖም ባባቷ ጫና በእስኪ ይሁን አግብታዋለች፡፡ ለአደን በሄዱበት

[49] ወንዶች የሚከውኑት ባህላዊ ጨዋታ ነው፡፡ ጨዋታው አንድ አቀንቃኝና በርካታ ተቀባዮች ያሉት ሲሆን ሁሉም ብትራቸውን ወደላይ አቁመው በዝግታ ሩጫ (ሶምሶማ) እየተንቀሳቀሱ የሚከውኑት ነው፡፡ በሰርግ፣ በዓመታዊ ክብረ በዓላት፣ በደቦ ላይ ይዘወተራል፡፡

ወቅት ግን በጀግንነት ትልቁን በሬ አንገቱን ጠምዝዞ፣ ቀንዱን ከመሬት ቸክሎ በፉከራ እያጉራራ ስታገኘው ለማመስገንም ለመውደድም በቅታለች፡፡

ተረት 71 ውስጥ ክፉ የነበረችውን ሴት ባሏ ታዛዥ ያደረጋት በሚፈጽመው የማያዳግም ርምጃ ነው፡፡ ጀግንነቱንና ቆራጥነቱን ባትወደው ኖሮ ልትፈታው ትችል ነበር፡፡ በምክር ቢሆን ኖሮ የእናትና የአባቷ ምክር ጥሩና ታዛዥ ሴት ሊያደርጋት ይችል ነበር፡፡ ትዕዛዝ ሰጥቷቸው ነገር ግን ትዕዛዙን ባፈልፈጸሙት እጅግ በሚወዳቸው ፈረስና ውሻው ላይ ቆራጥነቱን ስላሳያት ወድዳው አክብራው ተቀምጣለች፡፡

ተረት 77 ላይ አንዲት ገበያተኛ ሴት ለአዳር የፈለጓትን የአራት ወንዶች ጥያቄ ተቀብላለች፡፡ በዚህ ጊዜ ማሽላ ጠባቂውን አንድ ሽክም የማሽላ እሸት፣ የላም እረኛውን አንድ ቅል እርጎ፣ የፍየል እረኛውን አንድ ጠቦት ይዘው እንዲመጡ አድርጋቸዋለች፡፡ በሰጋር በቅሎ ተቀምጦና አሽከሩን ነፍጥ አስይዞ ሲሄድ በመንገድ ላይ ያገኛትን ዱግ[50] ግን ምንም ነገር እንዲያመጣ አልጠየቀችውም፡፡ ማታ ላይ አራቱም በየተራ ሲመጡ ፍየል ጠባቂው፣ የላም እረኛውና ማሽላ ጠባቂው ጓዳ ገብተው እንዲደበቁ ሲደረጉ ዱጉ ግን ቤቱ ተነጥፎለት በዝግጅት ተጠብቆ ደህና ቦታ ላይ እንዲቀመጥ ተደርጓል፡፡ ይሄ ሰው ስጦታ ሳያመጣ፣ በአራተኛነት ጠይቆ እያለ እሱን ከሌሎች ምን አስመረጠው?

ከሌሎች በተለየ ሁኔታ እዚህ ሰው ላይ ሶስት ነገሮችን እናስተውላለን፡፡ አንደኛ አሽከር አስከትሏል፡፡ ሁለተኛ ጠመንጃ አለው፡፡ ሶስተኛ በቅሎ ጋልቧል፡፡ በቅሎውና አሽከሩ የጌትነትና የባለጠግነት ምልክት ናቸው፡፡ መሳሪያው ደግሞ የጀግንነት፡፡ ስጦታ ያልተጠየቀበትና ከሌሎች ያስመረጠው ይሄው ነው፡፡ ቀደም ብሎ መነሻው ላይ እንደተጠቆመው ይሄ በተረቱ ውስጥ የታየ የሴቶች ፍላጎት ነው፤ በሃብቱና በጀግንነቱ መምረጥ፡፡ ሴቷ በዚህ መስፈርት አጋሯን መምረጧ ምክንያታዊ ቢያደርጋትም በመብቷ ላይ ግን ችግር ማምጣቱ አይቀርም፡፡ የፍላጎትና የባህሪ ልዩነቱ ለሴቷ የእኩልነት ማጣት ለወንዱ እንደልቡ የማዘዝና የበላይነት ምክንያት ይሆናል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ተረቶች ወንዱ የበላይነቱን ለማስፈን እንዲችል እገዛቸውና ሚናቸው ቀላል አይደለም፡፡

---

50 ዱግ ቀደም ባለው ጊዜ የሹም ወኪል ወይም የበታች ሹም ማለት ነው (ኢቋጥምማ 1993፡476)

## 5.3 የሴቶች አዎንታዊ ገጽታዎች ሃቲታዊ ትንተና

ለዚህ ጥናት በተሰበሰቡት አብዛኞቹ ተረቶች ውስጥ እንደታየው የሴቶች ደካማ ጎኖች እየተነቀሱና በድክመቶቻቸው ትይዩ አስፈላጊ የተባሉት እርምጃዎች እየተወሰዱ ከወንዶች ቀድመው ወይም እኩል ሆነው እንዳይገኙ ጥረት ተደርጓል፡፡ ለዚሁ ጥናት በተሰበሰቡ የተወሰኑ ተረቶች ውስጥ ደግሞ ሴቶች ለወንዶች ካላቸው ቅን አገልጋይነት አንጻር ሲወደሱና ሲመሰገኑ፣ ብሎም ይህ ባህሪያቸው እንደ አርዓያ ተቆጥሮ ከወንድ ለየት ያለ ቦታ ተሰጥቷቸዋል፡፡ ይሁንና በዚህ ቅን አገልጋይነታቸው ከሚስትነት ባለፈ ለሌላ ማዕረግ ሲታጩ አይታይም፡፡

ሴቷ ለወንድ ጠቅማ እስከተገኘች ድረስ ጠንካራና ብልህ ትባላለች፡፡ እንደገና እሱ የማይፈልገውን የማይመቸውን ባህሪ ስታሳይ ገጽታዋን አበላሽቶ ከእርሱ እንዳትገዳደር ያደርጋታል፡፡ ሲፈልግ ያደንቃታል፤ ሲፈልግ ያጣጥላታል፡፡ ጥሩ ነገር ስትሰራ አበጀሽ! አበጀሽ! ብሎ የበለጠ ተገዢነቷን ያጠናክራል፡፡ እሷም አበጀሽ ከተባልኩ አይቀር ብላ የበለጠ በአገልጋይነቷ እንድትገፋበትና እንድትተጋ ያደርጋታል፡፡

በአንጻሩ ወንዱ በቀላሉ የሚታለል፣ ለክስተቶችና ድንገት ደራሽ ችግሮች ፈጣን ብልሃት ማመንጨት የማይችል፣ ሁልጊዜ የሌሎችን ምክር ጠያቂ ሆኖ ተስሎ እያለ በሴቷ ላይ ያለውን የበላይነትና ክብር ሲያጣ ግን አይታይም፡፡ በሴቷ ሃሳብ አመንጪነትና አማካሪነት አንድ ጉዳይ ቢፈጽም ምስጋናው የእሱ እንጂ የሴቷ አይደለም፡፡ "ምንም ሴት ብታውቅ በወንድ ያልቅ" የሚለው የአበው ብሂል ይህንኑ ያረጋግጣል፡፡

በተረቶች ውስጥ ይህንን የመሰለው አድራጎት ይገለጽ እንጂ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተቀመጡ የሴቷን አቅምና አዕምሯዊ ብቃት የሚያመለክቱ በርካታ ማሳያዎች አሉ፡፡ ይህንን ልናገኝ የምንችለው ተረቶችን እንደገና ከእንስታውያን ንድፈ ሃሳብ አንጻር በመፈከር ነው፡፡ እንስታውያን ፎክሎረኞች ለምሳሌ Kousaleos (1999:19) እንደሚሉት ስለሴቶች ብቃትና ማንነት ለመናገር፣ በየባህሉና በየአውዱ ውስጥ ያሉበትን እውነተኛ ህይወታቸውን ለማወቅ ልምዶቻቸውን እንዲሁም ልምዶቻቸው የተገለጹባቸውን መንገዶች መፈከር ያስፈልጋል ሲሉ ያስረግጣሉ፡፡ እነ ፈቃደ (1993) እና Nenola (1993) ይሄው አካሄድ ተገቢ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

የሴቶች ጥንካሬ በተረቶች ውስጥ የተገለጸው በሁለት መንገድ ነው፡፡ ይህም በቀጥታ እና በተዘዋዋሪ ነው፡፡ ይህንኑ በሁለት ከፍለን እንመልከተው፡፡

## 5.3.1 በቀጥታ የቀረቡ አዎንታዊ ገጽታዎች

ስለሴቶች በቀጥታ የቀረቡ አዎንታዊ ገጽታዎች ሲባል በተረቶች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች በልጠው የተገኙበትና ይህም ስለመሆኑ በግልጽ የተተረከበትን አጋጣሚ ለማለት ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በተረቶች ውስጥ በብቃታቸው እውቅና ተሰጥቷቸዋል ማለት አይደለም፡፡ ወይም ተረቶቹ የሴቶችን ብቃት ማሣየትን ዓላማ አድርገው ቀርበዋል ማለትም አይደለም፡፡ እንከናቸውን ለማሳየት ተብለው በቀረቡት ተረቶች ውስጥ ብቃታቸው አሸንፎ ጉልህ የሆነበት አጋጣሚ አለ ለማለት ነው፡፡

ከዚህ አንጻር ሴቶች አስተዋዮች፣ ብልጦች፣ ለድንገተኛና አጣብቂኝ ክስተቶች ፈጣን መፍትሄ የመስጠት ብቃት ያላቸው የውሳኔ ሰዎች ሆነው ፊት ለፊት የቀረቡባቸው አጋጣሚዎች በርካታ ናቸው፡፡ ሁኔታዎችን አገናዝቦና አናብቦ ወቅታዊ ምክንያት ከመስጠት ብቃት ጋር በተያያዘ ተረት 6ን እንመልከት፡፡ ተረቱ የሴትን አለመታመን ለማሳየት ተብሎ ቢተረክም ከውሽማዋ ጋር ለመገናኘት ስትል ባሏን ከቤት ያስወጣችበት ዘዴ እና ባጋጣሚ ባሏ ሲደርስባቸው ከችግሩ ያመለጡበትን ስልት ስንመለከት ለአዕምሯዊ ብቃቷ (ከባሏ ጋር ስትነጻጸር) ምስክር ይሆናል፡፡  ከተረቱ የተወሰነውን ክፍል ወስደን እንመልከተው፡፡

> *. . . ውሽማ የያዘች የቄስ ሚስት. . . ውሽማዋ በቀን ሲገባ ሲወጣ ቢታይ አደጋ ላይ ስለሚወድቁ በሌሊት ልታስተናግደው ዘዴ ፈጠረች፡፡ ውሽማዋ ማታ መጥቶ በታዛ እንዲቀመጥ ከተማከሩ በኋላ ከባሏ ጋር ትንሽ እንደተኙ ቀሰቀሰችና “ይነሱ! ረፈደብዎ! ወደ ቤተክርስቲያን ይሂዱ” አለቻቸው፡፡*
>
> *ቄሱም . . . ልብሳቸውን በመልበስ ወጥተው ሄዱ፡፡ . . .  ውሽማ ወደ ቤት ገብቶ አልጋው ላይ ተጋድሞ ገንፎ ይገነፋለት ጀመር፡፡ ቄሱ ትንሽ እልፍ እንዳሉ አውሬ አላስኬድ ብሏቸው ወደ ቤት ተመልሰው በሩን ሲቆረቁሩ ውሽማ አልጋ ስር ገብቶ ተደበቀ፡፡ ቄሱ ወደ ቤት እንደገቡ ድስት ተጥዶ በማየታቸው ተገርመው “እንዴት በሌሊት ገንፎ ታገነፊያለሽ?” ብለው ሲጠይቋት በማዘን ብርድ ስለገደላቸው ለእርሳቸው እየሰራች መሆኗን ትነግራቸዋለች፡፡ . . . ገንፎውን ሰርታ አቀረበች፡፡ . . . አልጋው ስር ለተደበቀው ውሽማዋ ልታጎርስ እጇን ስትልክ አጎንብሶ አውጭኝ አውጭኝ በሚልበት ቂጡ ላይ ትኩሱን ገንፎ ታጣብቅበታለች፡፡ . . . ውሽማው ደንብሮ ሲነሳ ቄሱን ከነገንፎው ገልብጦ መሬት ላይ ይዘርራቸዋል፡፡ ቄሱም . . .   “ምንድን ነው አንቺ?” ብለው ሲጠይቁ “ከእርስዎ ጋር መጥቶ የገባ ሰይጣን ነው በስመአብ ይበሉ” ትላቸዋለች፡፡ . . . ውሃ የምትደፋ መስላ ቀስ አድርጋ ውሽማዋን አስወጥታ ትልከዋለች፡፡*
>
> *ቄሱ ዳዊታቸውን እየደገሙ . . . የውሽማ ቀይ ፎጣ ወድቆ ያዩታል፡፡ “ምንድን ነው እሱ አንቺ?” ሲሏት ”የሰይጣኑ ዋጋ ነው አበስኩ ገበርኩ እየው በስመአብ ሲሉት ደንግጦ*

*ጥሎት ሄደ!" . . . ፎጣውን በወጥ እንጨቱ አንጠልጥላ ውጭ ትጥለዋለች . . . (ተረት 6)*[51]

ተረቱ የተነገረበት ዓላማ የሴትን አለመታመንና ዝሙተኛነት ለማሳየት ተብሎ ነው። በእርግጥም የፈጸመችው ስህተት ከባድ ነው። ምክንያቱም በባሏ የቅስና ማዕረግ ላይ አደጋ ያስከትላል። ለቅስና ለመብቃት ሃይማኖታዊ ትምህርቱ እንዳለ ሆኖ በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻ መመስረትም አንዱ ነው። የተቀደሰ ጋብቻ እስካልመሰረተ ድረስ ምንም ያህል በትምህርቱ የረቀቀ ቢሆንም እንኳ ቄስ ሊሆን አይችልም። በዚህ አኳኋን የተገኘው ቅስና ሊፈርስ ከሚችልባቸው አጋጣሚዎች ውስጥ አንዱ ከሁለት አንደኛቸው ዝሙት ሲፈጽሙ ነው። ስህተቷ ከባድ ነው ያልነውም ለዚሁ ነው።

በዚህ አኳኋን ተረቱ የሴቷን አበሳ ቢያበዛውም ከዚሁ ተረት በስተጀርባ ሴቷን የምናደንቅበት አጋጣሚ አለ። ምንም እንኳ ድርጊቷ ዝሙተኛ ቢያስብላትም የፈለገችውን ነገር ለመፈጸም የተጠቀመችበት ዘዴ ግን አዕምሯዊ ብቃቷን ያሳያል። ውሽማዋን ለማስገባት ከተጠቀመችው ብልሃት አንስቶ ከቤት እስካስወጣችበት ድረስ ያለውን ስናይ አካሄዷ በሙሉ ተጠየቃዊና በብልሃት የተሞላ ነው።

ውሽማዋን በሌሊት ለማስገባት ለምን ፈለገች? ይሄስ ይሁን ባሏን እንዳይነቃ ምን ታደርጋለች? ብለን ስንጠይቅ የምናገኘው መልስ ተጠየቃዊ ሆኖ ቀርቧል። ለዚህ ሁለት ተያያዥነት ያላቸውን መልሶች እናገኛለን። አንደኛ በባል ወይም በሚስት ላይ ዝሙት መፈጸም በሃይማኖቱም በባህሉም የተወገዘ ስለሆነ ቀን ስታስገባና ስታስወጣ ሌላ ሰው ቢያይባት ላለመታማት ነው። ደግሞም እርሷ የቄስ ሚስት ናትና ብትታይ ወዲያውኑ የባሏ ማዕረግ ስለሚቀማ ከዚህ ሁሉ ስህተት ለመዳን ምሽትን መምረጧ ትክክል ነበር፤ ምክንያታዊም ነው። ሁለተኛ ይህንን ጊዜ የመረጠችው ከጊዜው አመችነት አንጻር ነው።

---

[51] የተረቱ ታሪክ (ተረት 6) እግረ መንገዱን በሃይማኖቱ ውስጥ ያሉ ሰዎችን የወቀሰ ይመስላል። የቄስ ሚስት ለሌሎች የቄስ ሚስት ላልሆኑ ሴቶች በሃይማኖቱ ረገድ አርዓያዎች ናቸው ተብሎ ይታሰባል። ብዙውን ጊዜም በሴቶች የጽዋ ማኅበር ውስጥ ሙሴ የምትደረገው የቄስ ሚስት ነች። ይህ የሚደረገው ካላት የእምነቱ ቀረቤታ አንጻር ነው። ሆኖም ይቺ ሴት በዝሙት ምክንያት ራሷ ረክሳ ባሏንም አርክሳለች። የቄሱ መርከስ ቤተክርስቲያንንም ያረክሳል። ተራኪው እንዲህ ዓይነት ሁኔታ አለ በሚል የሃይማኖት ሰዎችንና ቤተክርስቲያን ይተቻል። ይህንን ተረት በሌላ መልኩ ማየት ይቻላል። ቀሳውስቱ የሃይማኖቱን ነገር ብቻ ሲያተኩሩ የቤታቸውን ጉዳይ ይዘነጉታል፤ ሌሎችን ለማሳመንና ተከታይ ለማድረግ መጀመሪያ ከሚስት መጀመር፣ የሚስትን ፈቃድ መሙላት አለባቸው የሚል አንድምታ ሊወጣ ይችላል። በጥቅሉ ተራኪው ይህንን የማጋለጥ ፍላጎት ባይኖረው ምናልባት ባለታሪኳን የቄስ ሚስት ላያደርጋት ይችል ነበር።

ምክንያቱም ባሏ ቅዳሴ ከገባ አቋርጦ ሊመጣ እንደማይችል ስለምታውቅ ጉዳይዋን ያለስጋት ለመፈጸም ነው፡፡ በዚያ ላይ የባሏን ቄስ መሆን ተጠቅማበታለች፡፡ ወደ ቤተክርስቲያንም እንደሚሄድ በማወቋ በዚያ ወቅት ለመጠቀም መሞከሯ ትክክል ነበር፡፡ ነገር ግን የቅዳሴ ጊዜ የሚጀመርበትን ወቅት አለመገመቷ እና ችኮላዋ ስህተት ላይ ጥሏት ነበር፡፡ ይህንንም ባላት ፈጣን መፍትሄ የማበጀት ችሎታዋ ፈትታዋለች፡፡

እዚህ ላይ ባሏን ከእሷ ጋር ስናነጻጽረው ማስተዋል ጎድሎታል፡፡ ምክንያቱም ሊጠራጠርባቸው የሚችልባቸው በርካታ ምልክቶች (አጋጣሚዎች) ነበሩት፡፡ ሆኖም በቅልጥፍናዋ ነገሩን ሁሉ አጥፍታበታለች፡፡ አንዱም ላይ ሲጠረጥር አይታይም፡፡ ባልተለመደ ሁኔታ በሌሊት ሲገነፉ ማግኘቱ፣ አልጋው እንደዚያ ሲገለባበጥበት “ከእርስዎ ጋር መጥቶ የገባ ሰይጣን ነው በስመአብ ይበሉ” ብላ እንዳይጠረጥር ብሎም ዳዊቱን እንድደግም መደረጉ፣ ይባስ ብሎ የማያውቀው ፎጣ እወለሉ ላይ ወድቆ ሲያይ ጭራሽ አለመጠርጠሩ የመገንዘብ ችሎታውን ከሚስቱ እጅግ አሳንሶታል፡፡ እንዲያውም ከቤተክርስቲያን የመለሰው፣ አውሬ ሳይሆን ሰይጣን እንደሆነና ከቤቱ ድረስ እንደተከተለው ማሰቡን እንገምታለን፡፡ በእሱ መንፈሳዊ ሃይልም አብሮት የመጣውንና አልጋውን የገለባበጠበትን ሰይጣን በዳዊት ደገማው ፎጣውን አስጥሎ እንዳባረረው ማሰቡን እንጠረጥራለን፡፡

በታሪኩ መጨረሻ ላይ ያለውን ትዕይንት ስንመለከት ብቃቷ ጭራሽ ጎልቶ ይታያል፡፡ ገብቶ የነበረው ውሽማ ጥሎት በወጣው ፎጣ እንኳ እንዳይታወቅና ነውሯ እንዳይገለጥባት ፎጣውን በወጥ እንጨቷ አንጠልጥላ ለውሽማዋ አቀብላዋለች፡፡ በጠቅላላው ተረት 6 ሴቷን ነውረኛ ለማለት ታስቦ ቢተረክም በታሪኩ ሂደት ውስጥ የምንመለከታቸው ድርጊቶች በእውቀት ያደረገቻቸው ናቸውና በብልሃቷ ከፍ ያለ ቦታ እንድንሰጣት ያስገድደናል፡፡

በተመሳሳይ ተረት 12 ውስጥ አንድ ቀረጥ ሰብሳቢና ሌላ አንድ ገንዘብ ያዥ ውሽሞች የነበሯት ሴት ውሽሞቿን ካደጋ ለመታደግና የእሷንም ክብር ለመጠበቅ ስትል ባሏን ያታለለችበት ስልት ከብቃቷና ነገሮችን ከማያያዝ ችሎታዋ የመነጨ ነው፡፡ ቀረጥ ሰብሳቢው ገብቶ እያለ ከኂላው ገንዘብ ያዡ ይመጣል፡፡ የደነገጠው ቀረጥ ሰብሳቢ ጓዳ ገብቶ ይሸሸጋል፡፡ እንዲሁ ባል ከኂላ መጥቶ ሲገባ ገንዘብ ያዡም ጓዳ እሸሸጋለሁ ሲል ከቀረጥ ሰብሳቢው ጋር ይገናኛል፡፡ በዚህን ጊዜ ሚስት ውሽሞቿን በሰላም ለማስወጣት ስትል ለባሏ ”ግብራችንን እንድትከፍል ደጋግሜ ነግሬህ ነበር፤ ግን ልትከፍል

አልቻልክም፡፡ በዚህም የተነሳ ይሄው ገንዘብ ያገዙና ቀረጥ ተቀባዩ ትልቁን ጋን በዕዳ ሊወስዱ ማጀት ገብተዋል” ትለዋለች፡፡ ባልም ለምኖ ግብሩን ከፍሎ ጋኑን ያስቀራል፡፡ እዚህ ላይ ባልየውን በሴቷ ቦታ ብናስቀምጠው እንዲህ ዓይነት ብልሃት ሊያመነጭ ይችል ነበር?

ሌላው የሴቶች እጅግ ብልሃተኛነት በግልጽ የታየው ተረት 9 እና 92 ውስጥ ነው፡፡ በሁለቱም ተረቶች ውስጥ ባሎቻቸው በከባድ ጥያቄ ተወጥረው እጅግ ተቸግረውና መልስ አጥተው በጭንቀት ውስጥ በነበሩበት ጊዜ ለጠያቂዎቹ አስቸጋሪ መልስ በመስጠት ባሎቻቸውን ከሞትና ከሽንፈት ያዳኑትና ጠያቂዎችን እንዲደነቁ ያደረጉት ብልሃተኛዎቹ ሴቶች ናቸው፡፡ በተረት 9 ውስጥ ያገሩ ንጉሥ ገበሬውን “በሰማዩ ላይ ስንት ኮኮቦች አሉ? የመሬት መሃል የት ነው?” ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ በተረት 92 ውስጥ እንዲሁ ሰውየው ከጓደኞቹ ጋር ሲጨዋወት “የምድር እምብርቱን፣ የኮከብ ብዛቱን፣ ሳላውቅ ብቀር ንብረቴ ሁሉ ልቅ ይሁንብኝ” ብሎ የማይሆን ውርርድ ይገጥማል፡፡ በሁለቱም ተረት ውስጥ ያሉት ወንዶች መልስ አጥሯቸው እጅግ ይጨነቃሉ፡፡ ባያውቁ የመጀመሪያው ሊገደል ሆነ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ንብረቱን ሊያስወስድ ነው፡፡ በዚህ ጭንቀት ውስጥ እያሉ ነው ሚስቶቻቸው የሚያገኟቸው፡፡ ሚስቶቻቸውም ጥያቄውን እጅግ አቅልለው ነገር ግን ጠያቂዎች ራሳቸው የመልሱን ትክክለኛነት ሊያረጋግጡ በማይችሉበት መንገድ መልሱን ይሰጧቸዋል፡፡ በተረት 9 ውስጥ ያለው መላሽ አድናቆት ተችሮት ሽልማት አግኝቷል፡፡ ግና እውቅና ላለመስጠት መልሱ ከሚስቱ መምጣቱን ሲናገር አልተሰማም፡፡

የተረት 92 መልስ ግን ዳኛ በነበረው መኮንን ሌላ መዘዝ አመጣበት፡፡ መልሱን የነገረችው እጅግ ብልህ፣ አዋቂና ቆንጆዋ ሚስቱ መሆኗን ሲናገር መኮንኑ “ይቺ ሴት ለእኔ እንጂ ላንተ አትገባም፤ ስለዚህ ደግሰህ ቆየኝ እወስዳታለሁ” የሚል የሚያስደነግጥ ትዕዛዝ አስከተለበት፡፡ ለዚህም መፍትሄ ያበጀችውና ከጭንቅ የገላገለችው አሁንም ሚስቱ ናት፡፡ የባልዮው አስተዋጽዖ ምንም የለበትም፡፡ እንዲያውም ለመኮንኑ የሚስቱን እጅግ ብልህነት፣ አዋቂነት እና ቁንጅና በመናገሩ በጉልበትም በሥልጣንም ለማይጋፋው ሰው አሳልፎ ለመስጠት መንገዱን ከፍቶ ነበር፡፡

በብልሃትና በዘዴ ከመኮንኑ እንዴት እንዳመለጠች እና የባሏን ጭንቀት እንዴት እንዳስወገደች ቀጥሎ የተጠቀሰው የተረቱ ክፍል ያስረዳል፡፡

*. . . እሱም [ባልየው] መኮንኑ እንደነገረው አድርጎ ነገራት። እሷም ብልህነት ያደረባት ሴት ናትና "ይህስ ትንሽ ጉዳይ ነው። ይምጡና ይውሰዷት በላቸው። ድግስም እንደግስ" ብላ ድግሱን ደግሳ መኮንኑ እንዲጠራ አደረገች። ለድግሱም ብዙ ድስት ሰበሰበችና በሁሉም ተልባ በጠበጠችበት። የመጀመሪያውን ድስት በወርቅ ሙካሽ፣ ቀጥሎም የሃር፣ የከፋይ፣ የሹት፣ ማንሰሻ እስከለበሰው ድረስ አልብሳ አቀረበች። መኮንኑም ባለበት አዳራሽ ድስቱ ሁሉ ቀረበና የመጀመሪያው የወርቅ ሙካሽ የለበሰው ቢገለጥ በውስጡ ያለው ተልባ ሆነ። ሁሉንም መደዳውን ቢከፍቱት እንደዚያው ተልባ ሆነ። በዚህ ጊዜ መስፍኑ ተቆጣና "ምንድን ነው ይሄ ነገር?" ሲል ጠየቀ።*

*ያቺም ሴት ወደዚያው ከባሏ ጋር ሆና ቀረብ አለችና "ጌታዬ ሆይ! እኛ ሴቶች የውጭ መልካችን በየዓይነቱ ቢሆን የውስጡ አካላችን የሁላችንም አንድ ዓይነት ነው። ስለዚህ የእኔን የውጭ መልክ አይተው ይህንን ባሌን በማሳዘን እግዚአብሔርን እንዳያስቀይሙት" አለችው። መኮንኑም ሴትዮይቱን በማመስገን የእርዳታ ገንዘብ ወርቅና ብር ሰጥቶ ከግፍ ስራ ታግሶ ወደነበረበት ተመለሰ . . . (ተረት 92)*

አብዛኛውን ጊዜ ከብዙ ገለጻና ማብራሪያ ይልቅ ጥቂት ተምሳሌትነት ያለው ነገር ማቅረብ ጉዳይን የበለጠ ለማስረዳትና ለማሳመን ይመረጣል። ከላይ በተጠቀሰው ተረት ውስጥ ያለችው ገጸባህሪ ያደረገችው ይህንኑ ነው። የሰበሰበቻቸው ድስቶች እና በውስጣቸው ያስቀመጠችባቸው ወጥ አንድ ዓይነት ነው። አንዱን ከአንዱ ለመምረጥ የሚያስችል የተለየ ነገር በአንዱም ላይ የለም። ልዩነቱን የምናየው እያንዳንዳቸው ከለበሱት የጨርቅ ስሪት አንጻር ብቻ ነው። ለተመልካች በወርቅ ሙካሽ የተሸፈነው ድስት ከሌሎች የተሻለ ወጥ ተሰርቶ ቀርቦበታል በሚል እንዲያስብ ያደርገዋል። መኮንኑም ከዚሁ ድስት ወጡ ሲጨለፍላቸው ለመቆጣት የበቁት እንደዚህ ዓይነት ግምት ስለነበራቸው ነው። ሆኖም ሁሉም ድስቶች የያዙት አንድ ዓይነት ወጥ (የተልባ ብጥብጥ) ነው።

ሴቷ ይህንን ተምሳሌትነት ያለው አቀራረብ መኮንኑን ለማሳመን ተጠቅማበታለች። እዚህ ላይ ሴቷ የመኮንኑን ሥነልቡና በሚገባ ያወቀችው ይመስላል። ባሏ ቆንጆ ናት ብሎ ስለነገረው ውበቷ አንጉቶት ሊወስዳት እንደመጣ በሚገባ ገብቷታል። በብልህነቷና ባዋቂነቷ የመረጣት አይመስልም። ምክንያቱም ብቃቷ አንጉቶት ቢሆን ኖሮ ከባሏ ሳያፋታ በግዛቱ ውስጥ ባለው የሥልጣን እርከን ባንዱ ላይ አስቀምጦ ሊያሰራትና ችሎታዋን ሊጠቀምባት ይችል ነበር። የመኮንኑ ዓላማ እሷን የግሉ ማድረግ ነው። ይህንን የምንልበት ምክንያት እርሷ ለማሳመን ከተጠቀመችው ውክልና አንጻር ነው። ከሙካሽ እስከ ማንሰሻ ጨርቅ ያለውን በሴቶች ልብስ፣ ድስቶችን በሴቶች እና የተልባውን ብጥብጥ በሴት "ገላ" መስላቸዋለች። አባባሏም የሴቶች የውስጥ ገላ አንድ

ዓይነት ነውና መልኬን አይተው የተለየ ነገር ያለኝ እንዳይመስልዎት እንዳይሳሳቱ ማለቷ ነው፡፡ በብልህነቷ እና በአዋቂነቷ መርጧት ሊወስዳት መምጣቱን ብታስብ ኖሮ “እኛ ሴቶች የውጭ መልካችን በየዓይነቱ ቢሆን የውስጡ አካላችን የሁላችንም አንድ ዓይነት ነው፡፡ ስለዚህ የእኔን የውጭ መልክ አይተው ይህንን ባሌን በማሳዘን እግዚአብሔርን እንዳያስቀይሙት” አትልም ነበር፡፡ ምክንያቱም እውቀትና ብልህነት ከሰው ሰው ይለያያልና ሴቶችን ሁሉ አንድ ዓይነት ናቸው አትልም ነበር፡፡ ይህንን ሁሉ አካሄዷንና አመክንዮዋን ስንመለከት የእውቀት ባለቤት እንደሆነች እንረዳለን፡፡

በሌሎች ተረቶች ውስጥ ሴቶች ነገሮችን የመመርመርና ምስጢሮችን ፈጥኖ የመረዳት ብቃት እንዳላቸው በቀጥታ ቀርቧል፡፡ በተለይ ተምሳሌታዊና ቅኔያዊ አቀራረብ ያላቸውን፣ ማስተዋል የሚፈልጉ ንግግሮችን በመፍታት፣ እንዲሁም በዚሁ መንገድ ሃሳባቸውን በመግለጽ ብልጫውን እንደሚወስዱ ተረቶች ይናገራሉ፡፡ ለዚህ በተረት 3፣ 21፣ 35፣ እና 82 ውስጥ የቀረቡት ዓቢይ ማሳያዎች ናቸው፡፡

ተረት 21 ውስጥ ከፍ ያለ ማስተዋልን፣ ብዙ መመራመርን፣ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር ማስተያየትን፣ ባህላዊ ስምምነትን ማወቅን የሚጠይቁ እጅግ ረቂቅ የሆኑ ሶስት ንግግሮችን እናገኛለን፡፡ አንደኛው ኮርማ ያለባቸውን ጥቂት ላሞች አይቶ “እነዚህ ከብቶች እኮ ብዙ ናቸው” ማለት፣ ሁለተኛው ኮርማ የሌለባቸውን ብዙ ላሞች አይቶ “እነዚህ እኮ ጥቂት ከብቶች ናቸው” የሚልና በሶስተኛ ደረጃ አጥር የሌለውን ትልቅ ቤት “ትንሽ ቤት” አጥር ያላትን ትንሽ ጎጆ “ትልቅ ቤት” የማለት ናቸው፡፡ የእነዚህ እንቆቅልሽ ምስጢር ከተናጋሪው ሰው ጋር አብረው በነበሩት አባት ሲፈታ አይታይም፡፡ እንዲያውም ነገሩ ሲከብድባቸው “አንድ ተሳዳቢ ሰውዬ አጋጥሞኝ ሲያደርቀኝ ዋለ” በሚል ለቤተሰባቸው ይናገራሉ፡፡ ለአቅመሄዋን የደረሰች ልጃቸው ግን የሁሉንም ምስጢር አፍታትታ ስታስረዳ ትታያለች፡፡ መመራመር፣ ነገሩን ከባህላዊ ስምምነቱና ከማኅበራዊ አስተሳሰቡ ጋር አገናኝቶ መፍታት ማለት ይሄ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ሲደረግ የታየው በሴቷ ነው፡፡ ተረት 35ም ተመሳሳይ አንድምታ አለው፡፡

ከዚሁ ሃሳብ ሳንወጣ ሴቷ ሃሳብን አመስጥሮ፣ በነገር አስታኮና ከሁኔታዎች ጋር አገናዝቦ በመናገርም ጎልታ ትታያለች፡፡ ከጥንት እስከዛሬ የገጠሙ ሁኔታዎችን ተመልክተው ወደፊት ምን ሊሆን እንደሚችል ግምታቸውንም ሲሰነዝሩ የሚታዩትም ሴቶች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በተረት 83 “ከአንተ የባሰ እንዳይመጣ ነው” በሚል የቀረበው ይህንን ያሳያል፡፡ አንዲት ባልቴት ለአንድ ከሁሉ ለከፋ ንጉሥ “ለንጉሥ እድሜ ስጥልኝ”

እያሉ ጧትና ማታ መጸለያቸውን ንጉሡ ይሰማሉ፡፡ ለምን እንደሚጸልዩም ሲጠይቋቸው አሮጊቷ "ንጉሥ ሆይ! በእኔ ዕድሜ ከአንተ ጋራ አራት ንጉሥ ማየቴ ነው፡፡ የፊተኛው ደግ ነበር፤ የኋለኛው ክፉ ሆነ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ሦስተኛው የበለጠ ክፉ ሆነ፡፡ አንተ ደግሞ ከሁሉ የባስክ ክፉ ሆንክ፡፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንተ የባሰ እንዳይመጣ ለአንተ ዕድሜ እለምናለሁ" ሲሉ መልሰውለታል፡፡ እንዲህ መዝኖ አይቶ ስለወደፊቱ መናገር ከአስተዋይነት የሚመነጭ ነው፡፡ አባትም ወንድ ልጁን ሲመርቅ "የሴትን መላ ይስጥህ" (ተረት 20) ያለው ከዚሁ በመነሳት ነው፡፡ እነዚህ ሁሉ ስለሴት ብቃት በግልጽ የተነገሩ ነገር ግን ትኩረት ያልተሰጣቸው ናቸው፡፡ የሴቶችን ብቃት አጉልቶ ማውጣትና ማስረጽ በሴቶች ላይ የሚሰነዘሩትን አሉታዊ ገጽታዎች ያዳክማል፡፡ በሂደትም የእኩልነትን ሃሳብና እምነት ያሰርጻል፡፡ ባህላዊ እንስታውያንም (cultural Feminists) የሚሉት ይህንኑ ነው፡፡

## 5.3.2 በአንድምታ የወጡ አዎንታዊ ገጽታዎች

ስለሴቶች ከተረቶች በአንድምታ የሚወጡ አወንታዊ ገጽታዎች ሲባል ቀደም ብለን እንዳየነው በቀጥታ ያልተነገሩ፣ የሴቶችን ጭካኔ፣ ክፋት፣ ችኩልነት ወዘተ. ያሳያሉ ተብለው ከቀረቡት ተረቶች በስተጀርባ ማኅበረሰቡ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ያረጋገጣቸው የማይካዱ ሃቆች አሉ ለማለት ነው፡፡ ይህንን የተመለከቱትን አንዳንድ ተረቶች እየጠቀስን እንመልከት፡፡ በቅድሚያ ተመሳሳይ[52] አንድምታ ያላቸውን ሁለት ተረቶችን እንይ፡፡

ተረክ 23 እና 25 ስለ ሴት ንግሥቶች ያወራሉ፡፡ የሁለቱም ተረኮች አንድምታ ሴት ለሥልጣን ብትበቃ በህዝቧ ላይ ግፍ በመፈጸም ታስመርራለችና ለሴት ሥልጣን

---

[52] ለዚህ ጥናት በተሰበሰቡት ተረቶች ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸው አሉ፡፡ ለምሳሌ ተረት 23፣ 25 እና 100፣ ተረት 24 እና 68፣ ተረት 31 እና 37 ይጠቀሳሉ፡፡ እንዲህ ያለ የአንድ ተረት የተለያዩ ዓይነቶች (Variants) ያጋጥማሉ፡፡ Julius Krohn በ1870ዎቹ (እ.ኤ.አ) "Historical Geographical Theory" በሚል የፎክሎር ንድፈ ሃሳብ ለማቀንቀን የበቃውም ተመሳሳይነት ያላቸው ቃላዊ ተረኮች በተለያዩ አካባቢዎች ስላጋጠመው ነው (McCormick and White 2011፡662)፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ተረቶች ለተመሳሳይ ዓይነት ዓላማ የተነገሩ ቢሆኑም በተራኪዎች የማስታዎስ ብቃት፣ ተረቶቹ ከተነገሩበት ወቅታዊ ሁኔታ፣ ተራኪዎቹ ዓላማቸውን ይበልጥ ለማስረጽ ከሚያክሉት የራሳቸው ፈጠራና ተጨማሪ ታሪክ እንዲሁም ተረቶቹ እንደተነገሩበት አካባቢያዊ ሁኔታ ወዘተ. ልዩነቶች ያጋጥማሉ፡፡ ይህ ልዩነት መኖሩ ለትንተና ተጨማሪ ሃሳቦችን ይሰጣል፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ ተመሳሳይነት ያላቸው ተረቶች የተገኙት ከዚህ ሃሳብ በመነጨ ስሜት ነው፡፡

አይገባትም የሚል ዓላማ ይዘው የተተረኩ ናቸው። ለዚህም እንደ አብነት የቀረቡት ሊፈጸሙ የማይችሉ ትዕዛዞችን ለምሳሌ ከከብቶቿ በረት በር ላይ አልጋዋን አዘርግታ ከብቶቿ እሷን ሳይነኳት እንዲወጡ ማዘዝ (ተረት 23)፣ በምድርና በሰማይ መካከል ቤተመንግሥት እንዲሰራላቸው ማስቸገር (ተረት 23 እና 25)፣ ቅቤ በጠራራ ፀሐይ፣ ዱቄት በንፋሳማ ቀን በአደባባይ እንዲከመርላት ማዘዝ (ተረት 25)፣ የዱር አጋዘን (በሮፋ) ይዘው በበቅሎ እቃ እንዲጭኑላቸው ማስገደድ (ተርተ 23 እና 25) ወዘተ. ይጠቀሳሉ። በተመሳሳይ የሲዳማዋ ንግሥት ሞቲቴ (ብሌን ቁጥር 6፣ ከገጽ 9-20) እና የጉጂ ኦሮሞ ንግሥት Akko Manoyye (Ayalew 2012:49) ይህንኑ ማድረጋቸውን ልብ ይሏል። ይህም ታላቅ ጥፋት ሆኖ መጨረሻቸው ሞት ሆኗል። ሆኖም ግን እነዚህን ከእንስታውያን አተያይ (Feminist perspective) አንጻር ብንፈክራቸው የንግሥቶችን የእውቀት ባለቤትነት እናስተውላለን። ምክንያቱም ንግሥቶቹ ህዝባቸውን በማይቻሉ ነገሮች ወጥረው፣ የክህሎት ትንሽነቱን አሳይተው ለእነርሱ እንዲታመኑና የንግሥትነታቸውን ተገቢነት ለማስመስከር ነው። ትዕዛዛቸውም የተላለፈው ህዝቡ ከእነርሱ ጋር በእውቀት ሊስተካከል እንደማይችል ለማሳየትና አቅሙን አውቆ ተገዥነቱን እንዲያጸና ለማድረግ ነው። ይህንን ከተረቶቹ እየጠቀስን እንየው።

> *ባንድ ዘመን ባንድ አገር ውስጥ አንዲት ገዢ ሴት ነበረች። ይቺ ገዢ ጨካኝ ስለነበረች ሊሰሩ የማይችሉትን ድርጊቶች ፈጽሙ ብላ በግዛቷ ላይ ያሉትን ሰዎች ታስቸግር ነበር። በዚሁ ሳለች አንድ ቀን ሽማግሌዎችና አጫጭር ሰዎች ሥልጣኔን ያስለቅቁኛል የሚል አሳብ ስላደረባት ህዝቧን ሰብስባ "ሽማግሌዎችንና አጫጭር ሰዎችን እንድትጨርሱ!" የሚል ትዕዛዝ ታስተላልፋለች። . . . ይቺ ገዢ አንድ ቀን . . . ህዝቡ ሲሰበሰብ "ነገ ማታ አልጋዬን ከቤት አውጥታችሁ በከብቶቹ በረት በር ላይ አድርጉልኝ። እኔም እዚያው እተኛለሁ። ነገር ግን ከእንቅልፌ ከመንቃቴ በፊት እኔን ሳይነኩ ከብቶቹን ከበረት አውጡና ጠብቁ" አለቻቸው። - - - ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ደግሞ ድግስ አዘጋጅታ ህዝቡ እንዲበላና እንዲጠጣ አደረገች። ህዝቡ ከበላና ከጠጣ በኋላ . . . "የማርፍበት ቤት በሰማይና በምድር መካከል ስሩልኝ" አለቻቸው። . . . ይህ ካለፈ በኋላ እንደ ልማዷ . . . "አገሬን አይቼ ለማዳረስ ስላልቻልኩ 'በሮፋ' የሚባል የዱር እንስሳ ይዛችሁ አምጡና በኮርቻ ጫኑልኝ" አለቻቸው። (ተረት 23)*

> *በድሮ ጊዜ አንዲት የሴት ንግሥት በአንድ አካባቢ ትገዛ ነበር . . . ንግሥቲቷ ካስቸጋሪነቷ የተነሳ ሊሆን የማይችል ነገር ህዝቧን ታዝ ነበር።. . . አስከትላም "በሉ በዚህ በተከበረ አደበባይ መሃል የቅቤ ክምር እንዲከመርልኝ እፈልጋለሁና ፈጥናችሁ አድርጉ" ትላለች። . . . ንግሥቲቱ አስቸጋሪ ትዕዛዟን ትቀጥላለች። ህዝቡ በሙሉ እንደተሰበሰበ . . . በሰማይና በመሬት መሃል ቤተመንግሥቱን ስሩልኝ" በማለት ትዕዛዟን ታስተላልፋለች።. . . ንግሥቲቱ . . . የመጨረሻ ትዕዛዝ ትሰጣለች። ይህም አጋዘን ከዱር ይዘው በበቅሎ እቃ ጭነው እንዲያመጡላት ነበር።. . . (ተረት 25)*

በመጀመሪያ ደረጃ ህዝቡ የንግሥቶችን ትዕዛዝ ሲቀበል ተፈጻሚ ሊሆን አይችልም የሚል ጥርጣሬ የለውም። ሸሽገው ወዳስቀመጡት ድንክ ሽማግሌም[53] የሄዱት እንዴት ሊሰራ እንደሚችል መላ ለመጠየቅ እንጂ ሊሰራ የማይችል መሆኑን ለማረጋገጥ አይደለም። እነርሱም (ንግሥቶቹ) ቢሆኑ ቀድመው ሽማግሌዎችንና አጫጭር ሰዎችን ካገር አጥፉ የማለታቸው ምክንያት ብልሃታቸውን ውድቅ የሚያደርግባቸው እንዳይኖር፣ በሥልጣናቸው ላይ ክፉ መካሪ ሊሆኑ ይችላሉ ብለው በማሰብ እንጂ ያሉት ነገር እንዲፈጸምላቸው ፈልገው አይደለም። ሲጀመርም ትዕዛዛቸው ተግባራዊ ሊሆን እንደማይችል ያውቁታል። ዋና ዓላማቸው ህዝቡን የመቆጣጣር እና እነርሱ ላሉበት ቦታ ተገቢነታቸውን ለማሳመን ብሎም ህዝቡ ለንግሥትነት ብቁ ናቸው ማለትን እንዲያመጣ ነው። በተለይ ተረት 23 ላይ "አንድ ቀን ሽማግሌዎችና አጫጭር ሰዎች ሥልጣኔን ያስለቅቁኛል የሚል አሳብ ስላደረባት . . ." የሚለው አገላለጽ ይህንኑ ያሳያል። ተረት 100ም ይህንኑ ያንጸባርቃል።

ይህን የረቀቀ ዘዴ ስናስብ ሴቶች ምን ያህል አዋቂዎች እንደሆኑ እንረዳለን። ይህ ብቃታቸው በወንድ የበላይነት የተሰራውን አባዊ መዋቅር አፈራርሶ በእማዊ ሥርዓት የተዋቀረ የሴት የበላይነትን ያሰፍናል ባንልም እንኳ ቢያንስ እኩልነትን ሊያደላድል ይችል እንደነበረ መገንዘብ ይቻላል። ይህንን ሁሉ ስናስብ ጾታ ተኮር የሆነው ማኅበረሰባዊ ውቅር በተጠየቅ ላይ ያልተንተራሰ መሆኑን ያስገነዝባል።

---

53 ተረቶችን እርስ በርሳቸው ስናናብባቸው ብዙ የረቀቀ ነገር አላቸው። ለምሳሌ ተረት 23ን፣ ተረት 25ን እና ተረት 100 ባንድ በኩል፤ ተረት 9ን፣ ተረት 21ን እና ተረት 92ን በሌላ ወገን መድበን ለአማካሪነት ከታጨት ሰዎች አንጻር ብናስተያያቸው ተቃራኒ መስለው ይታያሉ። ምክንያቱም በመጀመሪያው ምድብ ባሉት ተረቶች ውስጥ አማካሪዎችና እንቆቅልሽ ፈቺዎች ወንዶች ሲሆኑ በሁለተኛው ምድብ ባሉት ተረቶች ውስጥ ደግሞ እንቆቅልሾችን ሴቶች ሲፈቱ ይታያሉ። በተረቶቹ ውስጥ ሴቶቹ የባሎቻቸውን፣ ወንዶቹ ደግሞ የህዝብን እንቆቅልሽ ፈትተዋል። ለዚህ ጥናት በተሰበሰቡት ተረቶች ውስጥ ሴቶች በአደባባይ የህዝብን እንቆቅሽ ሲፈቱ አይታይም። ይህ የተደረገው የህዝብን እንቆቅልሽ ሊፈቱ የሚችሉ ሴቶች ጠፍተው ሳይሆን አባዊ ሥርዓቱ ለሴቶች ብቃት በአደባባይ እውቅና ላለመስጠት ካለ ፍላጎት ይመስላል። አባዊ መዋቅሩም ይህንን የማድረግ ፍላጎት የለውም። ምክንያቱም ርዕዮተ ዓለሙ የእርሱን ልዕልና ማስጠበቅ ነው። ሆኖም በባሎቻቸው ላይ የገጠመን ችግር በቀላሉ መፍታት የቻሉ ሴቶች የህዝብን ችግር የመፍታት ብቃት ያንሳቸዋል ተብሎ አይገመትም። ይሁንና ሴት ከተሰራችበት የባል አገልጋይነት (ዘፍጥ.2፡18፤ ኤፌ.5፡22 ) ሚና አንጻር ተግባሯን በቤት ውስጥ ብቻ እንዲወሰን ካለ ፍላጎት መዋቀሩን እናይበታለን። በመሆኑም ከላይ በምድብ የተለዩት ተረቶች ግባቸው አንድ ነውና ተቃራኒነት የላቸውም። ጠቅለል ባለ መልኩ ተረቶችን በዚህ ረገድ ስንመዝናቸው የሥርዓተ ጾታን አድልዎ ከሥልጣን ጋር አስተባብረው ይዘዋል ለማለት ያስችለናል።

ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ከፍተኛ የማወቅ ጉጉትና ውስጣዊ ተነሳሽነት ያላቸው መሆኑ በተዘዋዋሪ የተነገረበት አጋጣሚ አለ፡፡ በእርግጥ ተረቶቹ ከተነገሩበት አውድ አንጻር በግርድፉ ስንመለከታቸው የተተረኩበት ዓላማ ሌላ ነው፡፡ ለምሳሌ የተረት 80 የመተረኩ ዓላማ ሴቶች ምስጢር ጠባቂ አይደሉምና ለሃላፊነት አይበቁም የሚል ነው፡፡ በተረት 24 ውስጥ ባሏ፣ "ከተናገርኩኝ እሞታለሁ" እያላት እሷ የራስህ ጉዳይ ማለቷ ለጭካኔዋ በማሳያነት ቀርቧል፡፡ ሆኖም እነዚህን ተረቶች ከእንስታውያን ወገን ሆነን ብንመለከታቸው በተዘዋዋሪ ስለሴቶች አወንታዊነት አላቸው፤ ውስጣዊ ማንነታቸውንም ያሳያሉ፡፡ ይህንኑ እንይ፡፡

በተረት 80 ውስጥ ሴቶችን ለሹመት ያላበቃቸው በአገልግል ተለጉማ የተሰጠቻቸውን ወፍ ንጉሡ ዘንድ ከማድረሳቸው በፊት ከፍተው በማየታቸው ነው[54]፡፡ በተረቱ ላይ ". . . የተሰጣቸውን እቃ ይዘው ሲሄዱ ሳለ በመንገድ ላይ በውስጡ ያለው ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉ፡፡ በመካከላቸው አንድ እንኳ አይሆንም ባይ ጠፍቶ . . ." በሚል ይነበባል፡፡ ከዚህ አቀራረብ የምንረዳው ወንዶቹ የተረጎሙበት መንገድና ሴቶቹ ያሰቡበት አቅጣጫ የተለያየ መሆኑን ነው፡፡ ሴቶቹ ያንን ያደረጉት ለማወቅ ካላቸው ጉጉት በመነጨ ስሜት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያ ላይ በአገልግሉ ውስጥ ያለው ነገር ሥልጣን የሚፈቅድ ይሁን የሚከለክል ለማወቅ ያጓጓል፡፡ ከዚህ አንጻር ሴቶቹ ያደረጉት አደራን ካለመወጣት ስሜት የመነጨ ነው ብለን ሙሉ በሙሉ አንደመድምም፡፡ በእርግጥ ለማወቅ መጓጓት የሁሉም ሰው ባህሪ ቢሆንም ከተረቶች አንጻር ስንመለከተው የሴቶቹ ክፍ ብሎ ያታያል፡፡ ለዚህ ደግሞ ማረጋገጫው ቢያንስ ከመካከላቸው አንዲትም ሴት እንኳ አይከፈትም አለማለቷ ነው፡፡ ይህ የሁሉንም የማወቅ ጉጉት ያሳያል እንጂ ሁሉንም ሴቶች ጠቅልሎ አደራን አይወጡምና ሥልጣን ይቅርባቸው ሊያስብል የሚችል አልነበረም፡፡

---

54 ይህንን ያልነው ከፈተናው አንጻር እንጂ ፈተናውን ካዘጋጁት ሰዎች ፍላጎት አንጻር አይደለም፡፡ ፈተናው በእስኪ ይሁን ዓይነት ቀረበላቸው እንጂ ቢያልፉ ሊሾሙ እንደማይችሉ ልቡናችን ያውቀዋል፡፡ ምክንያቱም ታላላቆቹ ሰዎች ከሴቶች የሥልጣን ይገባናል ጥያቄ ሲቀርብላቸው ፈተና ከማዘጋጀታቸው በፊት ነገሩን አብላልተው "ብንሾማቸው ሥርዓትና ፍርድ አያወቁ፤ አይሆንም ብንላቸው በየቤታችን ይበድሉናል" ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ "ብንሾማቸው ሥርዓትና ፍርድ አያውቁ" የሚለው አባባል ፍጹም ሥልጣን የመከልከል ፍላጎት ነው፡፡ ፈተናውን ቢያልፉም ሥልጣን አይሰጣቸውም ነበር ያልነው ከዚህ አንጻር ነው፡፡ ነገር ግን ያለ ፈተና ሥልጣን ቢከለክሏቸው ደግሞ በቤታቸው ሊበድሏቸው ሆነ፡፡ ስለዚህ የሥልጣን ጥያቄያቸውን ለመፈታተን የይስሙላ ጥያቄ አዘጋጁ፣ ሴቶቹም ሳያልፉ ቀሩ፡፡ ይህ ወንዶች ሴቶችን "ያልሾምናችሁ ፈተናውን ስላላለፋችሁ እንጂ እኛ መከልከል ፈልገን አይደለም፡፡ ስለዚህ የሚመለከታችሁንና አቅማችሁ የሚፈቅደውን ስራ በቤታችሁ ሆናችሁ ስሩ" ለማለት የተመቻቸ ሁኔታ ፈጥረዋል፡፡ ይህም የሥርዓተ ጾታ አድልዎ በተረቶች ውስጥ መስረጹን ያሳየናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ሄዋን ከተከለከለችው ዛፍ (ዕፀ በለስ) ለመብላት የበቃችው በሰይጣን አሳሳችነት ነው ቢባልም ግን "ብበላ ምን እሆናለሁ" በሚል ከማወቅ ጉጉት የተነሳ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰይጣን በእባብ ተመስሎም ይህንን ብትበይ ታውቂያለሽ በሚል እንዳሳሳታት ተገልጿል (ዘፍጥ.3፡5-6)፡፡ በተለይ ዘፍጥ.3፡5-6 "ሴቲቱም ዛፉ ለመብላት ያማረ እንደሆነ ለዓይንም እንደሚያስጎመጅ፣ ለጥበብም መልካም እንደሆነ አየች" በሚል መገለጹ ከተከለከለው ዛፍ መብላቷ ለማወቅ ፈልጋ ነው የሚል ትርጉም ያመጣል፡፡[55] ሎጥ እና ቤተሰቡ ከሰዶምና ገሞራ ሲወጡ ዞራችሁ እንዳታዩ (ዘፍጥ.19፡17) ተብለው ቢታዘዙም ሚስቱ ግን ዞራ በማየቷ የጨው አምድ ሆናለች (ዘፍጥ.19፡26)፡፡ ዞራ ያየችበት ምክንያት በየዋህነት ለማወቅ ያላት ውስጣዊ መነሳሳት ወይም አገሩ ሊቃጠል መሆኑን ስታውቅ በማዘን ዞራ አየች ተብሎ ሊተረጎም ይችላል፡፡

በተረት 75 ውስጥ እንዲሁ ተመሳሳይ ነገር ያጋጥመናል፡፡ ባል ከፈጣሪ በተሰጠው ልዩ አምላካዊ ሃይል ፍየሎችና ዶሮዎች የሚነጋገሩትን ሰምቶ መሳቁን ተከትሎ ሚስት በጥያቄ ስትወጥረው ይታያል፡፡ ባልም፣ "አይ! ከተናገርኩ እሞታለሁ" ቢላትም መጠየቋን አላቆመችም፡፡ ባል በመናገሩ እንደሚሞት አውቆ ቅድሚያ ተዝካሩን ለማውጣት ሲደግስ እያየችም አቋሟን አልቀየረችም፡፡ ይቅር ባለማለቷ ብንወቅሳትም ለማወቅ ያላትን ፍላጎት እና ጽናት ስናስተውል ግን እናደንቃታለን፡፡

ለዚህ ጥናት በተሰበሰቡ ተረቶች ውስጥ ወንዱ እንደ ሴቷ ያለውን የማወቅ ጉጉት የሚያሳዩ አልተገኙም፡፡ ችግር በገጠመውም ጊዜ ጉዳዩን ይዞ እቤቱ ወዳለችው ሚስቱ ወይም በተለየ ሁኔታ አዋቂ ወደሚባሉ ወንዶች ዘንድ በመሄድ እርዳታቸውን ሲጠይቅ ይታያል እንጂ በራሱ ጊዜ መፍትሄ ሲሰጥ አይስተዋልም፡፡ ከዚህም በላይ በሚስቱም ሆነ በሌላ አካል የተነገረውን አምኖ ሲቀበል እንጂ ለምን ብሎ ሲጠይቅ አያጋጥምም፤ አይስተዋልም፡፡ የንግግሮች አዝማሚያ፣ ምስጢርና የጎንዮሽ ትርጉሞች (አመስጥሮዎች) ገብተውት ምላሽ አይሰጥም፡፡ ከዚህ አንጻር ሁለቱን ስናነጻጽራቸው ሴቷ ብልጫ ታሳያለች፡፡ ሆኖም ግን የሥልጣን ባለቤት ወንዱ ነው፡፡

---

[55] አንዳንድ እንስታውያን ፖለቲከኞች የሄዋንን ከአዳም በኋላ መፈጠሯንና እንደ አዳም ከአፈር አለመሰራቷን የብልጫዋ ማረጋገጫ አደርገው ይወስዱታል (Stuurman, 1998 in Bryson 2003:6)፡፡ ከአዳም በኋላ መፈጠሯን የፈጣሪ የመጨረሻ የጥበቡ መገለጫ፣ ከአዳም የግራ ጎን አጥንት መሰራቷንም ከአፈር በተሻለ ቁስ የተሰራች አድርገው ያዩታል፡፡

በአጠቃላይ ሴቶችን ከሚያጣጥሉ ተረቶች በስተጀርባ ትልቅነታቸውን የሚያመላክቱ በርካታ ማሳያዎች አሉ፡፡ እነዚህን በውል መረዳትና ለማስረጽ መጣር በሥርዓተ ጾታ ዙሪያ የሚፈለገውን እኩልነት ለማምጣት ያግዛል፡፡

# ምዕራፍ ሥድስት

# ማጠቃለያና ይሁንታ

በዚህ ምዕራፍ የቀረቡት ሁለት ዓበይት ጉዳዮች ናቸው፡፡ እነዚህም በጥናቱ የተገኙ ዋና ዋና ውጤቶች በማጠቃለያ የሚቀርቡበት አንዱ ሲሆን ሌላው ደግሞ የጥናቱን ዋና ዋና ግኝቶች መሰረት በማድረግ የቀረቡ አስተያየቶች (ይሁንታዎች) ናቸው፡፡

## 6.1 ማጠቃለያ

ፎክሎር የአንድ ማኅበረሰብ አጠቃላይ ማንነት፣ የህይወት ፍልስፍና፣ ስለዓለም ያለውን አጠቃላይ አተያይና አመለካከት እንዲሁም ውስጣዊ መዋቅሩ (አደረጃጀቱ)፣ ወዘተ. ምን መልክ እንዳለው ማሳያ ነው፡፡ የፎክሎር ንዑስ ዘርፍ በሆነው ሥነቃል ስር የምናገኘው ተረት ይህንኑ ወክሎ ለትውልድ በማስተላለፍ ረገድ ሚናው ትልቅ ነው፡፡ ይህ ጥናት "በተረቶች ውስጥ የታዩ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍርሃዊ መስተጋብሮች" በሚል ርዕስ በተረቶች ውስጥ የሥርዓተ ጾታና የሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮች በተረቶች ውስጥ እንዴት ተሰናስለው እንደቀረቡ በዝርዝርና በጥልቀት ማሳየት ዓቢይ ዓላማ አድርጎ ተሰርቷል፡፡ ዓቢይ ዓላማውን እውን ማድረግ ይቻል ዘንድ፣ ወንዶች ከሴቶች በተለየ መልኩ ከፍ ያለ ማህበራዊ ቦታና ሥልጣን እንዴት እንደተሰጣቸው፣ ያም ማህበራዊ ቦታቸው ተጠብቆ እንዲቆይ በማድረግ ሂደት ውስጥ የተረቶችን አስተዋጥኦ ምን እንደሚመስል መመርመር፣ የሥርዓተ ጾታና ማኅበራዊ ሥልጣን መስተጋብር ምን እንደሚመስል ማጥናት፣ ማኅበረሰቡ የሥርዓተ ጾታና ሥልጣን ኢፍትሃዊ መስተጋብሮችን ለማስረጽ ተረቶችን እንዴት እንዴት እንደሚጠቀም መመርመር እና የሥርዓተ ጾታ እኩልነትን ይጋፋሉ ከተባሉት ተረቶች በስተጀርባ ያለውን "እውነታ" ተንትኖ ማሳየት የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን ይዞ ተሰርቷል፡፡

ጥናቱ የመስክና የቤተመዛግብት ምርምር በመሆኑ መረጃዎች በቃለመጠይቅ፣ በቤተመጻህፍት ዳሰሳ፣ በተተኳሪ የቡድን ውይይት እና "በመጠይቅ" ከመስክና ከቤተመዛግብት ተሰብስበዋል፡፡ የተገኙት መረጃዎች ከመዋቅራዊ - ግልጋሎታዊ እና እንስታዊ ንድፈ ሃሳቦች አንጻር ትንተና ተጥቶባቸዋል፡፡ በዚህም መሰረት የሚከተሉትን ውጤቶች ለማግኘት ተችሏል፡፡

ለሥርዓተ ጾታ መፈጠር ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን አባዊው ሥርዓት የራሱን ርዕዮተዓለም ፈጥሮ በሴትና በወንድ መካከል ተዋረዳዊ ግንኙነት መስርቷል፡፡ ወንድን የሥልጣን ባለቤት አድርጓል፡፡ በዚህም የተነሳ ሥርዓተ ጾታና ሥልጣን የተዋሃዱም የተናበቡም ሆነዋል፡፡ ይህ ውህደት ዘላቂነት እንዲኖረውና መልክ ይዞ እንዲቀጥል ባህሎችና ህጎች (አሁን ማሻሻያ ቢደረግባቸውም) የድርሻቸውን ተወጥተዋል (CGSPS 2001:27)፡፡ የባህል መገለጫ የሆነው ፎክሎር በተለይም የዚህ ጥናት አቢይ ርዕሰ ነገር የሆነው ተረት የሥርዓተ ጾታን ርዕዮተዓለም ተሸክሞ በማስተላለፍ እና የወንዱን ባለሥልጣንነት በማረጋገጥ በኩል የራሱን ሚና ሲወጣ ይታያል፡፡ ተረቶች የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን መስተጋብር ተጠየቃዊ ለማድረግና ለተከታዩ ትውልድ ለማስተላለፍ አስችለዋል፡፡

በተረቶች ውስጥ በስፋት እንደታየው ባብዛኛው የደግነት ባህሪን ለወንድ፣ እኩዮቹ ደግሞ ለሴት ተሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ ወንዶች በአብዛኛው የዋሆች፣ ርህሩሆች፣ ምስጢር ጠባቂዎች፣ ታማኞች፣ ከዝሙት የጸዱና ለማዘዝ ብቁዎች ተደርገው ተስለዋል፡፡ በአንጻሩ ሴቶች ጨካኞች፣ ምስጢር አባካኞች፣ እምነት የማይጣልባቸው፣ ለዝሙት ያደሩ፣ ዋሾዎችና ግትሮች ሆነው ተስለዋል፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ለየት ባለ መልኩ ብልህነት ከሴት፣ ሞኝነት ከወንድ ጋር ተያይዘዋል፡፡ ሴቶች አዋቂዎች፣ ባለፈጣን አዕምሮ፣ ከገጠማቸው ችግር በፍጥነት የሚወጡ፣ የነገሮችን ምስጢር ፈጥነው የሚገነዘቡ ተደርገው ተስለዋል፡፡ በአንጻሩ ወንዶች ለገጠማቸው ችግር መፍትሄ የማያመነጩ፣ በቀላሉ የሚታለሉ፣ ለምን ብለው የማይጠይቁ ወዘተ. ተደርገው ተስለዋል፡፡

እዚህ ላይ የሴቷ የብልህነት ደረጃ ተለክቶ የምናገኘው ወንዱ በቸገረው ጊዜ ባላት ረዳትነት አንጻር ነው፡፡ ብልህም ያሰኛት ለወንዱ ካላት አገልጋይነትና ተራዳኢነት አንጻር ነው እንጂ ብልህነቷ አስመስግኗትና አስመርጧት ወደ ኃላፊነት ለማምጣት አይደለም፡፡ ቢበዛ ይህ ብልህነቷ ሲያስመርጣት የታየው ለሚስትነት ብቻ ነው፡፡

በሌላ በኩል ብልህ ተደርጋ የተሳለችው በወንድ ላይ ግፍ ፈጽማ (ለምሳሌ ዝሙት) ሲታወቅባት ከዚያ ችግር ለመውጣት በምትፈጽማቸው ድርጊቶች፣ ወይም በወንድ ቤተሰብ ላይ ግፍ ለመፈጸም በምታዘጋጃቸው ወጥመዶች ነው፡፡ ይህ ለሴቷ ብልህነት ቢሆንም ወንዱን የሚጎዳ በመሆኑ ፍጻሜዋ የከፋ (እስከ ሞት የደረሰ) ሲሆን ታይቷል፡፡ ትንተናው እንደሚያሳየው የአብዛኞቹ ተረቶች ታሪክ በወሲብ ላይ የተንተራሰ ነው፡፡

እንዲህም ሆኖ ወንዱ የበላይነቱን እንዲይዝ ሆነው የተዋቀሩ ናቸው፡፡ ሴቶች በወሲብ ረገድ ከባሎቻቸው አልፈው ሌላ እንዳይመለከቱ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የሚሰብኩ ሆነው ታይተዋል፡፡ ዓላማቸው ሴቶች በባሎቻቸው እንዲረጉ የሚያስገድዱ ናቸው፡፡ ከዚህ አንዳዊ አመለካከት ለማፈንገጥ በሚሞክሩት ሴቶች ላይ ባሎቻቸው እስከሞት የሚያደርስ ቅጣት እንዲያሳርፉባቸው ተረቶች ሰብከዋል፡፡ ሴቶች ይህንን ሲፈጽሙ ባሎቻቸው ባይደርሱባቸውና መቅጣት ባይችሉ እንኳ በአንድ በሆነ ኃይል ረዳትነት ያላሰቡት ቅጣትና መከራ እንዲደርስባቸው ሆኗል፡፡ ይህ ሥነልቡናዊ ጫና በማሳደርና እንዲፈሩ በማድረግ በሌሎችም የባልና የሚስት ግንኙነቶች ዙሪያ በባሏ ብቻ እንዲትመራ ማድረጋቸውን በጥናቱ ታይቷል፡፡

በሌሎችም ተረቶች ውስጥ ሴቶች ባሎቻቸውን ወደ ራሳቸው ለማምጣት የተጠቀሙበት ስልት ብልሃተኛ አድርጓቸዋል፤ አስመስግኗቸዋል፡፡ ይህ በጥቅሉ ሲታይ ተረቶች ሴቷን በተቀነባበረ የመቆጣጠሪያ ስልት በወንዱ መዳፍ ስር ለማድረግ ማገልገላቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡

ከላይ የሴትን እኩይነትና የወንድን ሰናይነት ከተረቱ ዓለም ወጥተን አመክንዮአዊ ሆነን በነጻ ህሊና ብንመለከታቸው የወንድ የሴትም እኩይና ሰናይ ያጋጥመናል፡፡ ይሁንና ከጥንት ጀምሮ አባዊው ዓለም ሥልጣንን በብቸኝነት ለመቆጣጠር ካለው ፍላጎት የተነሳ ተረቶች ከላይ በተጠቀሰው ስልት እንዲዋቀሩ ተደርገዋል፡፡ ሥርዓተ ጾታ ከወንዱ ባለሥልጣንነት ጋር ተዋህዶ በተረቶች እንዲገለጽ ተደርጓል፡፡

አባዊው ዓለም በሴቶች ላይ የበላይነቱን እና ሥልጣን ለእርሱ የሚገባ መሆኑን በተለያዩ ስልቶች በተረት አንጸባርቋቸዋል፡፡ ከነዚህም ውስጥ አንደኛው በፈጠራቸው ታሪኮች ውስጥ የሴቶችን ገጽታ ከአፈጣጠራቸው አንስቶ አዛብቶ በማቅረብ ነው፡፡ ገጽታቸውን ለማዛባትም አፈጣጠራቸውን ከሰይጣን፣ ምግባራቸውን ከዝሙት ጋር አያይዞ ለኃላፊነት የሚያበቃና ወንድን ለመምራት የሚያስችል ምንም ነገር እንደሌላቸው በተረቶች ለማስረጽ ተጥሯል፡፡ እግረ መንገዱንም ወንዱ በሴቶች ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥርና ክትትል እንዲያጠብቅ የሚያሳስቡ መሆናቸው በጥናቱ ተገኝቷል፡፡

ሌላው ጥናቱ ያረጋገጠው ሴቶችን ለመቆጣጣርና ተገዢነታቸውን ለማጽናት ወንዱ አካላዊና ሌሎች ቅጣቶችን እንደ አማራጭ መጠቀሙን ነው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ጎልተው

የታዩት ድብደባ፣ ግድያ፣ ከቤታቸውና ከንብረታቸው ማፈናቀልና ደግመው እንዳይመለሱ ማሰደድ፣ ባዘጋጁት ወጥመድ ራሳቸውን ማስጠለፍ የመሳሰሉት መሆኑ ታውቋል፡፡

ሴቶች ለወንድ የሚመች ሥነልቡናዊ አቀራረብ እንዲኖራቸው የሰናይ ሴቶችን ታሪክ በማቅረብ ልምድ እንዲጋሩ ማድረግ እንደ አንድ አማራጭ መያዙን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ሰናይ ሴቶች የተባሉት ለባሎቻቸው ስጋዊ ምቾት የሚያደገድጉ፣ ባሎቻቸውን የሚያከብሩና ከቃላቸው የማይወጡ፣ ባሎቻቸውንና ወላጆቻቸውን የማያሰድቡ፣ በቤት አያያዛቸውና በእንግዳ አቀባበላቸው የተመሰገኑ፣ ውሏቸው ከቤት ያልራቀ ወዘተ. ናቸው፡፡ ከዚህ በአንጻር የቆሙትን (እኩይ የሚላቸውን) በማቅረብ፣ ሰናይ ባለመሆናቸው የደረሰባቸውን መከራ በማተትና ሥነልቡናዊ ጫና ውስጥ በማስገባት ሊቆጣጠሯቸው እንደቻሉ ጥናቱ ጠቁሟል፡፡

ተረቶች የወንድን ማንነት ገንብተውና ከፍ አድርገው በማሳየት በሴት ላይ እንዲሰለጥኑ ምቹ ሁኔታ መፍጠራቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ ወንድ ዘርን በመተካት ሂደት ዋናው ተደርጎ መወሰዱ፣ ሴት ባል ከሌላት ክብር የሌላት ተደርጎ መታሰቡ፣ ወንድ ልጅ መውለድ እንደ ክብር መቆጠሩ ወዘተ. ለሴት ልጅ የሚሰጠውን ክብር የሚያሳንስና ከወንድ በታች የሚያደርግ መሆኑ በጥናቱ ግልጽ ሆኗል፡፡

ባጠቃላይ አብዛኞቹ ተረቶች አጠንክረው የሚነግሩን ሴቶች ከወንድ ጋር እኩል ነን ብለው እንዳያስቡ፣ የወንድን የበላይነት እንዲቀበሉና ወንድ የዋለበት ቦታ እንዳይገኙ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም በላይ ሴቶች ለባሎቻቸው ታማኝ እንዲሆኑና ከፈቃዳቸው እንዳይወጡ፣ ይህን ባያደርጉ ግን በተረቱ ውስጥ እንዳለው ዓይነት ቅጣት ሊደርስባቸው እንደሚችል ማስጠንቀቅ፣ ተከታዩንም ትውልድ በዚሁ ረገድ መቅረጽ ነው፡፡ ይህ በጥቅሉ የሚያሳየው ተረቶች የሥርዓተ ጾታንና የሥልጣንን መስተጋብር ከአባዊው ሥርዓት መዋቅር ጋር አናብበው የሚያሳዩ መሆናቸውን ነው፡፡

በሌላ በኩል በጥናቱ የታየው የሴትን ጠንካራ ጎኖች የሚያሳዩ በርካታ እውነታዎች በተረቶች ውስጥ መኖራቸው ነው፡፡ እነዚህ እውነታዎች በግልጽም በስውርም የቀረቡ ናቸው፡፡ ሁሉም ግን በጥቅሉ ሴቶች ለድንገተኛ፣ አደገኛና አጣብቂኝ ክስተቶች ፈጣን መፍትሄ በመስጠት፣ ነገሮችን፣ ክስተቶችንና ሁኔታዎችን አገናዝቦ አንድ ቅጥ ያለው ነገር በመሰንዘር፣ ከባድ ለሚባሉ ጥያቄዎች መፍትሄ በማፈላለግና የማይቻለውን

እንዲቻል በማድረግ፣ ምስጢሮችን ፈጥኖ በመረዳት፣ እንዲሁም ለማወቅ ያላቸው ጉጉት ከወንዱ  ከፍተኛ መሆኑን ተረቶች ማሳየታቸው በጥናቱ ሂደትና ውጤት ታይቷል፡፡

## 6.2 ይሁንታ

የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ እጅግ ውስብስብ ከመሆኑም በላይ መሰረቱን በሃይማኖት፣ በባህልና በህግ የጸና ሆኖ ቆይቷል፡፡ ቀደም ብሎ በህግ የተደገፈ የሴቶች ጭቆና ስለመኖሩ ጥናቶች ጠቁመዋል (ፍሚትህማመ 1983፡2)፡፡ አሁን ግን እየተቀየረ መጥቶ ለመሻሻል ችሏል፡፡ በባህል በኩል ያለው ግን የተነካ አይመስልም፡፡ ለዚህ ባለንበት ዘመን ፖለቲካዊ መፍትሄ ለመስጠት ቢሞከርም የጎላ ለውጥ አምጥቷል ለማለት አያስደፍርም፡፡ የዚህ ምክንያቱ ምንጩን መሰረት ያላደረገ መፍትሄ ለመስጠት የሚደረግ ሙከራ ይመስላል፡፡

ባህልን ባጭር ጊዜ ውስጥ መቀየርም ማጥፋትም አይቻልም፡፡ ባህል ትንሳዔውም ሞቱም እጅግ አዝጋሚ ነው፤ በአዋጅም ሊጠፋ አይችልም፡፡ ምናልባት አዋጅ መውጣቱ በሂደት ሊደረግ የሚችለውን ለማገዝ ይረዳ ይሆናል፡፡ ከዚያ ባለፈ ለዘመናት በህዝብ አዕምሮ ውስጥ ሰፍኖ የኖረውን ገናን ባህል፣ መሰረቱን አደላድሎ የተቀመጠን ልማድ በአንድ ጊዜ አውልቆ መጣል አይታሰብም፡፡ በመሆኑም የሥርዓተ ፆታና የሥልጣንን ጉዳይ በምንፈልገው መንገድ እንዲሆን ለማድረግ ጊዜና ትዕግስት ያስፈልገዋል፡፡ ከዚህም በላይ ሂደቱ በእውቀት ሊመራ ይገባዋል፡፡ ፖለቲካዊ ጥቅም ለማግኘት ሲባል በጥድፊያና በችኮላ ከተሰራ ትርፉ የትዳር መፍረስና መበጣበጥ ብሎም ማኅበራዊ ሁከት መፍጠር ይሆናል፡፡

እዚህ ላይ ማንም እንደሚያምነው እንስታውያንም እንደሚያስረግጡት ሴቶችን ብቁ እንዳልሆኑ፣ ከወንዶች ጋር ሊፎካከሩና የማይችሉ አድርጎ ዝቅ አድርጎ መገመት ተገቢ አይደለም፡፡ ሴት መሆናቸውን ብቻ አስቦ በከፍተኛው የሥልጣን መዋቅር ላይ ተሳታፊ አለማድረግ አንድ ሃገር በምታልመው እድገት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አለው (Birhanu 2015፡116)፡፡ በመሆኑም ማኅበራዊ እሴቶችን፣ የአመራር ይትብሃሎችን (leadership styles)፣ ተቋማዊ መዋቅሮችን፣ ወዘተ. ለማሻሻና ለማበልጸግ በህዝባዊም ይሁን በግል ተቋማት ውስጥ ሴቶችም ወንዶችም በተመሳሳይ መልኩ ሊፈቀድላቸው ይገባል፡፡ ይህ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በሂደት እያደገ ሲሄድ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ይረጋገጣል፡፡ ይህ ይሆን ዘንድ የሚከተሉት ተግባራት በሂደት ቢፈጸሙ መልካም ነው፡፡

1. የትምህርት ሚኒስቴር፣ ከባህል ሚኒስቴርና ከህጻናትና ሴቶች ሚኒስቴር ጋር በመተባበር የሴቶችን በጎ ገጽታ አጉልተው የሚያሳዩትን ቃላዊ ተረኮች በማሰባሰብ ለህትመት በማብቃትና ባገሪቱ ባሉ ትምህርት ቤቶች በማሰራጨት ለንባብ ቢያበቃ፣
2. እስከዛሬ ከሥርዓተ ጾታ ጋር በተያያዘ በአብዛኛው በርካታ ስራዎች የሚሰሩት ከሴቶች ጋር ነው፡፡ የሥርዓተ ጾታ ቢሮም ሲባል የሴቶች ብቻ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በመሆኑም በወንዱ ላይ አጥጋቢ ስራ ባለመከናወኑ አስተሳሰቡ እንዳለ ነው፡፡ በሴቶች ላይ ብቻ አነጣጥሮ የሥርዓተ ጾታ ስራን ማከናወን ከግብ አያደርስም፡፡ ይህንኑ Holmberg (2005፡18) ሲያረጋግጡ "The silence on men as a group, and poor interest in working for organization of men for gender equality collides with gender mainstreaming. If the only visible group is women, then it becomes difficult to mainstream gender" ብለዋል፡፡ የሥርዓተ ጾታ ጉዳይ የወንዱም የሴቱም ነውና ሥርዓተ ጾታዊ ሥልጠናዎችና ንቃት ፈጠራዎች ተከታታይነት ባለው መልኩ በወንዱም ላይ ቢያተኩሩ መልካም ነው፡፡ ይህንንም ሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር ኃላፊነቱን በግንባር ቀደምነት ወስዶ ቢሰራ፣
3. እንደ በዓሉ ግርማ እና ፀሃይ መላኩ ዓይነት ጠንካራ ሴት ገጸ ባህሪያት የሚስሉ ደራሲዎችን ማበረታታት፣ ማድነቅና ስራዎቻቸውን በመገናኛ ብዙሃን ሰፊ ሽፋን እንዲያገኙ ቢደረግ፣
4. የሴትንና የወንድን እኩልነት ለማምጣት በቅድሚያ ወደራስ ባህል መመልከት ይገባል፡፡ የምዕራባውያንን እንስታውያን ፈለግ ተከትሎ ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ሌላ ውድቀት ላይ ይጥላል፡፡ የችግሩ ምንጭ ራሳችን ነንና መፍትሄውንም ከራሳችን ባህል መፈለግ ይገባናል፡፡ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ዓለማቀፋዊ ባህሪ ቢኖራቸውም በያገሩ ላሉ የተለያዩ የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ችግሮች መፍትሄ ሊገኝ የሚችለው በያገሩ ብሎም በየብሔር ብሔረሰቡ ባህል ውስጥ ነው፡፡ በአንድ አገር እንኳ ቢሆን ለየባህሎችና ሃይማኖቶች የሚስማሙ በዳሰሳ ጥናት ላይ የተመሰረቱ የተለያዩ ህጎች (legal pluralism) ቢወጡ የሥርዓተ ጾታን ችግር በተሻለ መንገድ ለመፍታት ያስችላልና (Allehone 2000:1350) ይሄው በሚገባ ቢታሰብበትና የፍትህ ሚኒስቴር ድርሻውን ቢወስድ፣

5. የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ጥያቄን ለማንሳትና ተግባራዊም ለማድረግ ቀላል አይደለም፡፡ በተለይ ሥርዓተ ጾታ ከሥልጣን ጋር ያለው ትስስር ሲነሳ ጥያቄው ይከብዳል፡፡ ምክንያቱም ማኅበረሰቡ በሴትና በወንድ መካከል ባሉ መስተጋብሮች የሚስተዋሉትን ደንቦችና እሴቶች ትክክለኛ፣ ነባራዊና የሚታመንባቸው አድርጎ ስለሚቆጥር (Holmberg 2015፡42) እነሱን ጥሶ ለመግባት የሚያጋጥመው ችግር ፈታኝ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስትና ባለድርሻ አካላት ለምሳሌ ሴቶችና ህጻናት ሚኒስቴር፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ቢሮ እና የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች የተቀናጀ ስራ ለመስራት ቢጥሩ፣
6. አንድን ሥርዓት መቀየር የሚቻለው በአስተሳሰብ ነው፡፡ አስተሳሰብ ሳይቀየር ወደተግባር ቢገባ አንድም ተቃዋሚ ይበዛበታል፣ አንድም የተፈለገው ግብ ሳይሳካ ይቀራል፣ አንድም ማኅበራዊ ቀውስ ሊያስከትል ይችላል፡፡ ከጽንሰ ሃሳብ አንጻርም ብንመለከተው ሴቶችን ለሃላፊነት ማብቃት (empower ማድረግ) ማለት በወንዶች ተይዞ የነበረውን ቦታ እንዲነጥቁ ማድረግ ማለት አይደለም፡፡ ጽንሰ ሃሳቡ በተዛባ የሥርዓተ ጾታ አመለካከት ምክንያት የሰፈነውን የሥልጣን ግንኙነት (power relation) መቀየር ማለት ነው (Reeves and, Baden 2000፡25)፡፡ የእኛን አገር ሁኔታ ስንመለከተው ደግሞ ከዚህ በተቃራኒው ይመስላል፡፡ በመሆኑም የሚመለከተው አካል በተለይም ፖለቲካውን የሚመሩት አካሎች ቆም ብለው ቢያስቡበት፣
7. የአገራችን ተረቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ የመተረት እድላቸው እየቀነሰ ብሎም ራሳቸው ተረቶች እየተረሱና እየጠፉ ይመስላል፡፡ በመስክ ቆይታ ከወጣቶች ተረት ማግኘት አለመቻሉ የዚህ ምስክር ነው፡፡ ለዚህ በርካታ ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡፡ ከነዚህም ውስጥ፡- ማኅበረሰቡ የራሱ ባልሆኑ ተረቶች እየተሳበ መምጣትና የራሱን ተረቶች ዋጋ በማሳነስ ለመተረት ፈቃደኛ አለመሆንና በሂደት የራሱን ተረቶች እየረሳ መምጣት፣ የመነገሪያ አውዱ በሌሎች ዘመናዊ በሆኑ እንደ ቴሌቪዥን፣ የኤፍ ኤም ራዲዮ መርሃ ግብሮች፣ የሞባይል ሙዚቃዎች፣ የተለያዩ የማኅበረሰብ ድረገጾች ወዘተ. አማካኝነት መቀማት፣ በባህል ለውጥ ምክንያት ግለሰቦች ወይም ማኅበረሰቦች ለተረቶቻቸው ጭራሹኑ ትኩረት አለመስጠት ወይም እጅግ ዝቅተኛ ትኩረት መስጠት (Olrik, 1992:63 በከፊል በዚህ ይስማማል) በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡ ይህንን ማኅበራዊ ክስተት ወደኋላ መመለስ ባይቻልም እንኳ ተረቶች የታሪክም የእውቀትም ምንጮች ናቸውና

ጭራሹኑ ከመጥፋታቸው በፊት አገራዊ ፕሮጀክት ተነድፎ በየብሄር ብሄረሰቡ ያሉትን ተረቶች ለማሰባሰብና ለማጥናት ጥረት ቢደረግ፤ ለዚህ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የኢትዮጵያ ባህል ማዕከል፣ የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ስራውን እንዲያከናውኑ ቢደረግ መልካም ነው፡፡

# ማጣቀሻዎች


ሀዲስ ዓለማየሁ፣ *ተረት ተረት የመሰረት፣* አዲስ አበባ፣ ትንሳኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት 1948፡፡

ለማ ንጋቱ፣ "በየም ብሔረሰብ ፆታ ተኮር ተረቶች የወንድና የሴት ምስል ትንተና" ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1999፡፡

ሉልሰገድ ዓለማየሁ፣ *ጠንቋ ሬት፣ ተከታታይ የሌሊት ስንቅ 2ኛ ምሽት፣* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣1955፡፡

መስፍን መሰለ፣ "ስለሴቶች በተቃርኖ የሚነገሩ የአማርኛ ምሳሌያዊ ንግግሮች"፣ *የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዘጠነኛ ዓመታዊ ጉባዔ፣* አዲስ አበባ የኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ተቋም፣ 1991፡፡

ሙሉነህ ጉግሳ፣ "የክስታኔ ተረቶች"፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993፡፡

ሙሉጌታ ነጋሳ፣ "በጅባትና ሜጫ አውራጃ የተሰበሰቡ የገበሬን ህይወት የሚያንጸባርቁ ኦሮምኛ ተረቶች"፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1976፡፡

……… "በአድአ ሊበን ወረዳ የኦሮሞ ሴረጉማ ከግጭት አፈታት አንጻር" *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 27-250፡፡

ማኅተመ ስላሴ ወልደ መስቀል፣ *እንቅልፍ ለምኔ፣* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1950፡፡

ምትኩ አበራ፣ *ምጥን ቅመም፣* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 2006፡፡

ሰሚራ መሃመድ፣ "ጡሩሲና የሙስሊም 'ገዳም' እና 'በገዳሙ' ውስጥ የሚከበሩ በአላት ሥርዓተ ክዋኔ" በአማርኛ ቋንቋ ለሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ የ2ኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2005፡፡

ሰውነት መኮንን፣ "በሞጣ አውራጃ የሚነገሩ የአማርኛ ተረታ ተረቶች"፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት

ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1984።

ሰይድ ሙሐመድ ሳድቅ እና ሐጂ ሙሐመድ ሳኒ ሐቢብ (ተርጓሚዎች)፣ *ቅዱስ ቁርኣን*፣ 2ኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ ነጃሺ አሳታሚ ድርጅት፣ 1997።

ሱሩር በድሩ፣ "የስልጢ ተረቶች ይዘት ትንተና"፣ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ ኢቋስ፣ አ.አ.ዩ፣ 1992።

ስለሺ አባተ፣ "የሸካቾ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት *ሥርዓት*"፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 63-84።

ብርሃን አሰፋ፣ "*የዳውዶ ሚቶሎጂ እና አንድምታዎቹ*" ለSeminar in Oral History ኮርስ *ማሟያ* የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2005።

---------፣ "የአማሬ ፍርድ በወግዲና በቦረና ወረ*ዎች*"፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 133-156።

---------፣ "ባህላዊ የግጭት አፈታት በወግዲ እና በቦረና ወረዳዎች"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 2002።

*ተመስገን ምንዋጋው፣ "የግጭት መፍትሔ ሥርዓት* በዶኮ-ጋሞ"፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ስርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 85-102።

ተስፋዬ ሊሞሬ፣ "የሃድይኛ ተረታ ተረቶች"፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1993።

ተስፋዬ አካሉ (ተርጓሚ)፣ *የኣማራ ህዝብ ተረቶች፣* አዲስ አበባ፣ (አሳታሚ ድርጅቱ አልተገለጸም)፣ *2007።*

ተክለጻድቅ *መኩሪያ*፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከዐፄ ልብነድንግል እስከ ዐፄ ቴዎድሮስ፣* 5ኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት፣1965።

ተፈሪ ገዳሙ፣ *አንድ ሺህ አንድ ሌሊት ምርጥ አስደናቂ ታሪኮች፣* ቅጽ 1፣ 1979፡፡ (አሳታሚ ድርጅቱ አልተገለጸም)

______፣ *አንድ ሺህ አንድ ሌሊት 16 ምርጥ አስደናቂ ታሪኮች፣* አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፣ ቅጽ 1፣ 1989፡፡

ታየ ገብረማርያም (አለቃ)፣ *የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ፡ ባጭር ቃል የወጣ፣* አዲስ አበባ፣ አላታ ማተሚያ ቤት፣ 2008፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፣ *በይነ-ዲሲፐሊናዊ የሥነጽሑፍ ንባብ፣* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2001፡፡

ነጻነት መኮንን፣ "አበጋር ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም.ኤ.ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1998፡፡

አማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፣ *የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ፣* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 2001፡፡

አማራ ብሔራዊ ክልል የቤተሰብ ህግ፣ *ዝክረ ህግ*፣ አዋጅ ቁጥር 79፣ 8ኛ ዓመት፣ ቁጥር 3፣ 1995፡፡

አስቴር ሙሉ፣ "ተከታታይነትና ለውጥ በወሎ አዝማሪዎች የኑሮና የዘፈን ልምድ"፣ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረበ የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ጥናት፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 2007፡፡

አበበ አይቼህ፣ *ጉራማይሌ ግሩማዊ የሆኑ ተረቶችና ምሳሌዎች እንዲሁም አስቂኝና አስደናቂ ንግግሮች በያይነቱ፣* አዲስ አበባ፣ ትንሳዔ ዘጉባዔ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

አበበ ከበደ፣ "በሰላሌ አውራጃ አካባቢ በአማርኛ የሚነገሩ ተረቶች"፣ የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ ኢቋስ፣ አ.አ.ዩ፣ 1982፡፡

አቤ ደስታ፣ (ተርጓሚ)፣ *ተረቱን መልሱ አለም አቀፍ የልጆች ተረት፣* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ 1999፡፡

አወቀ ውቤ፣ "የወላይትኛ ተረቶች"፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1975፡፡

የኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበር፣ *መጽሐፍ ቅዱስ፡ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት*፣ አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1980።

የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር፣ *ብሌን፡ የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበር የሥነጽሑፍ መጽሔት፣* ቁጥር 6፣ አዲስ አበባ፣ ብራና ማተሚያ ድርጅት፣ 2002።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣ *ኣማርኛ መዝገበ ቃላት፣* አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993።

እሸቱ ድባቡ፣ *ተባዕታይ አገዛዝ በኢትዮጵያ፡ ችግሩና የመፍትሄው መንገድ፣* አዲስ አበባ፣ አዲስ ጥራት ማተሚያ ቤት፣ 1997።

እንግዳ ወልደ ሰማያት፣ "በጭላሎ አውራጃ በአማርኛ የሰማኋቸው ተረቶች"፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974።

ካህሳይ ገብረ፣ "ማዕድ-የአፋር ህዝብ ባህላዊ የፍትህ ሥርዓት" *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 323-340።

ውዱ ጣፈጠ፣ "የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ"፣ *ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፡ በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ የውይይት መድረክ ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሑፎች*፣ አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 202-218።

የወንድወሰን አውላቸው፣ የኧጆካ ቂጫ- የሰባት ቤት ጉራጌ የግጭት አፈታት ሥርዓት"፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 37-62።

ያዕቆብ ወ/ማርያም፣ "የከፊኛ ተረታ ተረቶች"፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974።

ይልማ ተፈሪ፣ "የሽምግልናና እርቅ ሥርዓት በወላይታ ብሔረሰብ"፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 103-120።

ደስታ ተክለ ወልድ፣ *ዐዲስ ያማርኛ መዝገበ ቃላት*፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1962።

ደበበ ዘውዴ፣ "የኢሳ ማህበረሰብ የግጭት አፈታት ሥርዓት"፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ (2004)፡ 341-360።

ዲበኩሉ ዘውዴ፣ *ፍትሐ ነገስት ዘብሔረ ሀግ ወቀኖና ስያሜ፣ ጽንሰሃሳቡና ምንጮቹ፣* አዲስ አበባ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1986።

ድሃብ ትኩዕ፣ "የትግሪኛ ተረቶች"፣ ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1974።

ጀቤሳ ኤጀታ፣ *የኦሮሞ ብሔርና ባህል አጭር ታሪክ፣* 1ኛ መጽሐፍ፣ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣1989።

ገብሬ ይንቲሶ፣ ፈቃደ አዘዘ እና አሰፋ ፍስሃ (አዳቾች)፣ *ባህላዊ የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በኢትዮጵያ፣* አዲስ አበባ፣ ኤክሊፕስ አሳታሚ ድርጅት፣ 2004።

ጌታቸው ኃይሌ፣ *የአባ ባርይ ድረሰቶች፡ ኦሮሞን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋር፣*አዲስ አበባ፣ (አሳታሚ ድርጅቱ አልተጠቀሰም) 1997።

ጥላሁን ገ/ጻድቅ፣ "በአብዮታዊት ኢትዮጵያ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በልጆች ፕሮግራም የተላለፉ ተረቶች ጥናት"፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የቀረበ የኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1980።

ጥሩነህ አበራ፣ "የቦኩ ቁኒ ኦሮምኛ ተረቶች" ከኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የአርትስ ባችለር ዲግሪ ለማግኘት ከሚያስፈልጉት ነጥቦች ከፊሉን ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ 1982።

ፈቃደ አዘዘ፣ *የሥነቃል መምሪያ፣* አዲስ አበባ፡ ኢንተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣1991።

---------፣ *የኢትዮጵያ ብሄረሰቦች አፋዊ ኪነተ ቃል ጥናት፣* የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ መጽሔት ቁጥር 2፣ 1984 (2-30)።

Abdulkadir Haji Jama. "Some cultural elements as reflected in Somali folktale" MA Thesis In Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Literature, Addis Ababa Univrsity,1982.

Abrams, M.H. *Glossary of Literary Terms*. 5th ed.. New York: Holt, Rinehart, and Winston, 1999.

Abreham Alemu . "Oral Narrative as Ideological Weapon for Subordinating Women: the case of Jimma Oromo." *Journal of African Cultural Studies*, Vol. 19, No. 1 (June 2007):55–79. (http://dx.doi.org/10.1080/13696810701485934. Accessed 14:14 10 August 2007)

______, "Jima Orormo Oral Prose Narratives: A Preliminary Descriptive Analysis" MA Thesis, Addis Ababa ,University, 2000.

Ahmed Dego. "Images of Women in Selected Oromo Folktales, Folksongs and Proverbs with Particular Reference to East Arsi Zone." A Thesis Presented to the School of Graduate Studies: Adiss Ababa University, 2010.

Allehone Mullugeta. "Women, State, and the Family; Issues of Legal Pluralism and Challenges of Family Law." *Ethiopian Studies at the End of the Second Millennium, Proceedings of the XIV$^{th}$ International Conference of Ethiopian Studies.* Addis Ababa. Vol. 3. Nov, 6-11, (2000): 1334-1358.

Assefa Fisha. "Customary Dispute Resolution Mechanism in Tigray". *Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia*. Addis Ababa: Eclipse printing press, (2011): 361-386.

Awonoor, K.. *Breast of the Earth: A Survey of the History, Culture and Literature of Africa South of the Sahara*. New York, London, Lagos, Enugu: Nok Publishers International, 1975

Ayalew Getachew Assefa. *Customary Laws in Ethiopia: A Need for Better Recognition? A Woman's Rights Perspective*. Copenhagen: Danish Institute For Human Rights. 2012.

Bascom, William R. "The Four Functions of Folklore" *Journal of American Folklore*, Vol. 67.266. (Oct. - Dec., 1954): 333-349. Accessed- Fri Apr 13 03:14:28 2007.

________, "The Forms of Folklore: Prose Narratives." *Journal of American Folklore*,. Vo. 78.307, (1965): 3-20.

Bayleyegn Tasew. "Aguaa Oral Prose Narratives, Ethnic Genre and Social Functions." A Thesis Presented to the School of Graduate Studies: Adiss Ababa University, 1999.

Ben-Amos, Dan. "Folklore in African Society." *Research in African Literature*. Vol. 6: 2. (1975): 165-198. (http://www.jstor.org Accessed-Tue Oct 23 04:46:48 2007)

Berhanu B. Sura. "Gender Roles and the Societies Perception of Women in Mecha Oromo Verbal Art: A Feminist Approach." A PhD Dissertation Submitted to the Department of Foreign Language and Literature. Addis Ababa University, 2015.

Brescoll, Victoria L. "Who Takes the Floor and Why: Gender, Power, and Volubility in Organizations." Administrative Science Quarterly XX(X), (2012): 1–20. (http://asq.sagepub.com/content/56/4/622.short) Accessed: 04-05-2015 11:22)

Briggs, Charles L. "Treasure Tales and Pedagogical Discourse in Mexicano New Mexico*." Journal of American Folklore.* Vol. 98.398, (1985): 287-314. (http://links.jstor.org/sici?28198507 Accessed wed may 17 /2006, 10:22:52 )

Bronner, Simon J. (ed.) "Structuralism and Folklore" *The Meaning of Folklore: The Analytical Essays of Alan Dandes.* Utah: Utah State University Press, (2007):123-144.

Bryson,Valerie. *Feminist Political Theory: An Introduction*. 2nd ed. Palgrave Macmillan: Creative Print & Design. 2003.

The Centre for Gender and Social Policy Studies. *Culture, Gender and Development.* A Report submitted to the African Institute for Economic Development and Planning (IDEP), Dakar, Senegal, October 2001. http://www.mcgill.ca/files/ids/culture.pdf

Dawkins, R. M. "The Meaning of Folktales." *Folklore.* Vol. 62.4 (Dec., 1951): 417-429. (http://www.jstor.org/stable/1257125 Accessed: 04-03-2015 06:22)

Degh, Linda. *Folktales and society.* Illinois: Indiana University Press, 1969.

Dejene Gemechu. "The Customary Courts of Waliso Oromo". *Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia*. Addis Ababa: Eclipse printing press. (2011): 251-278.

Desta Desalegn. "A Functional Study of Tulema Oromo Oral Prose Narratives." A Dissertation Submitted to the Department of Foreign Languages and

Literature in Fulfillment for the Requirements of the Degree of Doctor of Philosophy. Addis Ababa University, 2015.

Dorson, R.M. (ed). *Concept of Folklore and Folklife: Introduction.* Chicago: The University of Chicago press, 1972.

Dundes, Alan . (eds). *The Study of Folklore.* London: Prentice-Hall, inc, 1965.

_______, "Binary Opposition in Myth: The Propp/Levi-Strauss Debate in Retrospect". *Western Folklore*, Vol. 56. 1. (Winter, 1997): 39-50. (http://www.jstor.org /stable/1500385 Accessed: 19/04/2008 12:15.)

_______, "Folk Ideas as Units of Worldview." *Journal of American Folklore*, vol. 84.331, (1971): 93-103,. http://www.jistor.org. Accessed- may 17/2006.

________,"Structural Tyapology in North American Indian Folklore*" Journal of Anthropological Research.* Approaches to Culture and Society Vol. 42.3, (Autumn, 1986): 417-426. http://www.jstor.org/stable/3630045 Accessed: 04-03-2015 06:33

Eagleton, Mary (ed). *A Concise Companion to Feminist Theory*. Malden: Blackwell Publishing Ltd. 2003.

Eagly, Alice H. ,Eastwick, Paul W and Schmdit Mary Johanneson. "Possible Selves in Marital Roles:The Impact of the Anticipated Division of Labor on the Mate Preferences of Women and Men.*" Personality and Social Psychology Bulletin*. Vol. 35.403. Jan,.22, 2009.

Federal Democratic Republic of Ethiopia Populatlon Census Commission. *Summary and Statistical Report of the 2007 Population and Housing Census Results*. Addis Ababa, Dec.2008**.**

Fekade Azeze.. "The State of Oral Literature Research in Ethiopia: Retrospect and Prospect." *JES*. Vol. XXXIV, No. 1, Addis Ababa University: IES, 2001.

Finnegan, R. *Oral Literature in Africa*. Oxford: Clarendon Press, 1970.

__________, Oral Traditions and the Verebal Art: A Guide to Research Practices. New York: Routledge, 2005.

Fischer, Agneta H., Mosquera, Patricia M. Rodriguez, and Vianen, Annelies E. M. van. "Gender and Culture Differences in Emotion." *Journal of American Psychological Association*. Vol. 4.1, (2004): 87–94.

"The Functionalist Perspective." *Boundless Sociology*. Boundless, 14 Nov, 2014. (https://www.boundless.com/sociology/textbooks/412/gender-stratification-and-inequality-11/sociological-perspectives-on-gender-stratification-87/the-functionalist- perspective-503-4583/) Retrieved 16 Apr. 2015.

Georges, Robert A. "Towards an Understanding of Storytelling Events." *The Journal of American Folklore.* Vol.326. (Oct – Dec, 1969): 313-328.

Gray, J. Patrick. "Structural Analysis of Folktales: Techniques and Methodology." As*ian Folklore Studies*. Vol.37.1 (1978): 77-95. http://links.jstor.org/sici?sici=03852342%281978%2937%3A1%3C77%3ASAOFTA%3E2.0.CO%3B2-P (Accessed = Sat Dec 15 09:14:41, 2007.

Gopal, Gita and Salim, Maryam. (eds.) *Gender and Law፡ Eastern African Speaks.* Proceedings of the Conference Organized by the World Bank and the Economic Commission for Africa. Washington, D.C. 1998.

Harrison, Lawerence E. and Huntington, Samuel P. (eds). *Culture Matters: How Values Shape Human Progress*. New York: Basic Books, 2000.

Hierro, Graciela and Marquez, Ivan "Gender and Power." *Hypatia*. Vol. 9.1 (winter, 1994):173-183. (http://www.jstor.org/stable/3810443).Accessed:10/06/2014 11:25

Holmberg, Annica. *Doing Gender – A Question of Power.* Stockholm: Forum Syds förlag. 2005. http://www.ipu.org/press-e/pressrelease201503101.htm

Jablow, A. *Yes and No: The Intimate Folklore of Africa*. New York: Horizon press, 1961.

Jackson, Robert MaxAnalyzing the Persistence of Gender Inequality: How to Think about the Origin. 2015. https://www.nyu.edu/classes/jackson/causes.of.gender.inequality/ Readings/ DownSoLong- Persistence & Origins.pdf)

Kabaji, Egara Stanley."The Construction of Gender through the Narratice Process of the African Folklore: A Case Study of the Maragoli Folktale." PhD Dissertation in Literature and Philosophy, University of South Africa. 2005.

Kalklachew Ali. "Religion, Ritual, and Mutual Toerance in Wollo: The Case of Kabe South East Wollo." M.A Thesis in Social Anthropology. AAU, 1997.

Kiriti, Nganga, Tabitha W. *Institutions and Gender Inequality: A Case Study of the Constituency Development of Fund in Kenya*. Addis Ababa: Eclipse Printing Press. 2011.

Kousaleos, Nicole. *Feminist Theory and Folklore*. Folklore Forum.Vol.30:1/2. (1999):19-34

Lazar, Michelle M. "Feminist Critical Discourse Analysis: Articulating a Feminist Discourse Praxis." *Critical Discourse Studies*, Vol. 4: 2, (2007): 141-164. (http://dx.doi.org/10.1080/17405900701464816)

Leslaw,Wolf and Kane,Thomas L. *Amharic Cultural Reader: Amharic Text and English Translation*. Wiesbaden: Harrassoitz Verlag. 2001.

Lau, Kimberly J. "Structure, Society, and Symbolism: Toward a Holistic Interpretation of Fairy Tales" Western Folklore, Vol. 55.3 (1996):233-243. http://www.jstor.org/stable/1500483. Accessed: 09-03-2015 04:38).

Marler, Joan. The *Myth of Universal Patriarchy: A Critical Response to Cynthia Eller's Myth of Matriarchal Prehistory* .2003. (http://www.belili.org/marija/legacy)

McCormick, C. T. and White, K. K. (eds.).. *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.* (2001): 662-668.

-------------, (eds.). *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art.* (2001.):457- 462.

McGuire, Randall H. "Breaking Down Cultural Complexity: Inequality and Heterogeneity." *Advances in Archaeological Method and Theory*. Vol.6. (1983): 91-142. (http://www.jstor.org/stable/20210066. Accessed: 09-03-2015 04:43 UTC)

Melakineh Mengistu. "The major Themes and Motifs of Southern Agaw Foktae." MA Thesis In Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Literature, Addis Ababa, University, 1990.

Michael Daniel Ambachew. "A Thematic Description of Ethiopian Folktale*.*" *Proceedings of the 12th Annual Conference of the Institute of Language Studies*. Institute of Language Studies, Addis Ababa University, (2000): 44-58.

Nenola, Aili. "Folklore and the Genderized World." (1993) In Fekade Azeze. (comp). *Readers for EtLi 621: Folklore*. Adiss Ababa University, Nov. 2003.

*The New Encyclopaedia Britainica*. 15th ed. Vol.19. Chicago: The University of Chicago press (Encyclopedia Britannica, Inc), 1993.

Olasupo F.A , Victoria Olugbemi Kikelomo & Ajuwon Jumoke Adeniran. "Proverbs and Gender Equalities and Equities in African Cultures: Yoruba Culture as A Case Study*." Global Journal of Human Social Science, Arts & Humanities*. Global Journals Inc. (USA). Vo. 12.13.10. 2012.

Ògúnṣina, Bisi. "Gender Ideology: Portrayal of Women in Yùrbá Ìjálá" *African Languages and Cultures*. Vol. 9.1 (1996): 83-93. (http://www.jstor.org/stable/1771794. Accessed: 31-03-2015.)

Okpewho, Isidore. *African Oral Literature: Backgrounds, Character, and Continuity.* Bloomington and Indianapolis: Indiana University Press, 1992.

Olarinwoyr, Adeyinka Wulemat *"*The Images of Women in Yoruba Folktales" *International Journal of Humanities and Social Science. Vol. 3.4 [Special Issue – February 2013]:* 138-149.

Olrik, Axel. *Principles of Oral Narrative Research*. Bloomington: Indiana university press. 1992.

Oring, Elliot. *Folk Group and Folk Genres: An Introduction*. Long Utahh: Utah University press, 1986.

Oromia Culture and Tourism Bureau. *History of the Oromo to the Sixteen Century.* Addis Ababa: Oromia Culture and Tourism Bureau. 2006.

Page, Sarah. "Feminism and the Third Wave: Politicising the Sociology of Religion?" *Conference Proceedings* – Thinking Gender – the NEXT Generation UK Postgraduate Conference in Gender Studies. University of Leeds, UK. 21-22 June 2006,

Palmisano, J.M. (ed). *World of Sociology*.Vol.1. New York: Farmington Hills, 2001.

Perret, David I. and Cassidy, Clare. "The Effect of Control of Resources on Magnitude of Sex Difference in Human Mate Preference." *Journal of Evolutionary Psychology*. University of St. Andrew;s. Scotland. Vol.8.4 , (2010): 720-735.

Ragan, Kathleen. "What Happened to the Heroines in Folktales? An Analysis by Gender of a Multicultural Sample of Published Folktales Collected from Storytellers" Marvels &Tales. Vol. 23.2 (2009): 227-247. http://www.jstor.org/stable/41388925 Accessed: 04-03-2015 05:24.

Reeves, Hazel and Baden, Sally. *Gender and Development: Concepts and Definitions.* Brighton: Institute of Development Studies, 2000.

Reminick, A. Ronald. "The Structure and Function of Religious Belief among the Amhara of Ethiopia." *Proceedings of First United States Conference on Ethiopian Studies. Michigan: Braun-Brumfield Inc, (*1973): 25-42.

Sahilu Kidane. "Borna Oromo prose narratives" MA Thesis In Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Literature, Addis Ababa University, 1996.

Sawin, Patricia E. "Gender Identification of a Person as Male or Female According to Culture-Specific Criteria." *Folklore: An Encyclopedia of Beliefs, Customs, Tales, Music, and Art*. (2011): 612-616.

Schoemaker, George H. *The Emergence of Folklore in Everyday Life: A Field Guide and Sourcebook.* Indiana: Trickster Press, 1990.

Sims Martha C, and Stephens, Martine. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Traditions.* Utah *:* Utah State University Press, 2005.

Skeggs, Beverley. *Formation of Class and Gender: Becoming Respectable*. London: Sage Publications, 2002.

Songsin, p. *Study and Analysis of Khmer Legends and Folktale Regions*. 1-9. Bangkok: Thai Language field of Study, Faculty of Human and Social sciences, Thonburi Rajabahat institute, 1999.

Swann, Steven Jones. "The Innocent Persecuted Heroine Genre: An Analysis of Its Structure and Themes." *Western Folklore*, Vol. 52.1 (Jan., 1993): 13-41. http://www.jstor.org/stable/1499491 Accessed: 28-03-2015, 11:22

Sydow, C.W. Von. "Foktale Studies and Philology: Some points of View." *The Study of Folklore.* London: Prentice-Hall, inc, 1965.

Sylvia, Pankhrust. "The Notable Women." *Ethiopian Observer: Journal of Independent Opinion, Economics, History and Arts*. Vol. 1.3. (1957):84-87.

Tesfaye GebreMariam. "The Study of Major Themes in Jablawi Folktales". MA Thesis In Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Literature, Addis Ababa University, 1990.

Tiani, Anne Marie. *Gender and Power: Six Links and One Big Opportunity*, 21st May 2015. (http://www.ipu.org/press-e/pressrelease201503101.htm)

Tolosa Mamuye. "The Quest for the Servival of the Gada System's Role in Conflict Resolution". *Customary Dispute Resolution Mechanism in Ethiopia*. Addis Ababa: Eclipse printing press. (2011): 299-322.

Tyson, Lois. *Critical Theory Today: A User-Friendly Guide*. 2nd ed. New York: Routledge. 2006.

Vanderstoep, Scott W. and Johnston, Deirdre D. *Research Methods in Everyday Life.* San Francisco: PB publishers, 2009.

Wood, W., & Eagly, A. H. "A Cross-Cultural Analysis of the Behavior of Women and Men: Implications for the Origins of Sex Differences." *The American Psychological Association Bulletin*, Vol. 128. 5. (2002): 699-727.

Yehenew Jembere. "A Generic Classification of Amharic Oral Prose Narratives of Western Gojam" MA Thesis In Partial Fulfillment of the Requirements for the Degree of Masters of Arts in Literature, Addis Ababa University, 1996.

Young, Frank W. "Folktales and Social Structure: A Comparison of Three Analyses of the Star-Husband Tale." *The Journal of American Folklore*, Vol. 91.360, (1978): 691-699. (http://www.jstor.org/stable/538921 Accessed: 04-03-2015 06:05)

# አባሪዎች

## አባሪ 1፡- የተረቶች ስብስብ

## ሀ. ከጥናታዊ ጽሑፎች የተሰበሰቡ ተረቶች

### ተረት 1

ከእለታት አንድ ቀን አንዲት ልጃገረድ አባቷን እንድትጠራ እናቷ ትልካታለች፡፡ እንዳጋጣሚ ሆኖ አባትዮው ከጓደኞቹ ጋር የእርሻ ስራውን ያከናውን ነበር፡፡ ልጅቷ እንደደረሰች የአባቷ ጓደኞች ለምን እንደመጣች ይጠይቋታል፡፡ "ለአባትሽ ምን መልዕክት ነው ይዘሽ የመጣሽው? ንገሪው!" ይሏታል፡፡ እሷም "አይ! ምስጢር ነው፡፡ እናንተ ባላችሁበት አልናገርም፡፡" ስትል ትመልስላቸዋለች፡፡ እነርሱም ልጅቷን ለማሞኘት ሲሉ "ግደለም ንገሪው፡፡ እኛ እንዳንሰማ ዓይናችንን እንጨፍናለን" ይሏታል፡፡ ልጅቷም "በጣም ጥሩ! ነገር ግን በገባችሁት ቃል መሰረት ዓይናችሁን በደንብ መጨፈን አለባችሁ" ትላቸዋለች፡፡ ሰዎቹ በገቡት ቃል መሰረት ዓይናቸውን በደንብ ይጨፍናሉ፡፡ ይሄኔ ልጂት ፊቷን ወደ አባቷ አዙራ በምልክት ለምሳ መጠራቱን ታስረዳዋለች፡፡ ይህንን ስታደርግ አንዲት ቃል አልተነፈሰችም፡፡ በዚህም የተነሳ ትንሿ ልጅ ትልልቆችን ሰዎች አታለለቻቸው ይባላል (Abraham፣ 2000፡111)፡፡

### ተረት 2

አንድ ቀን ባልና ሚስቱ እቤታቸው ተቀምጠው ሳለ አንድ ያልተጠበቀ እንግዳ ሊጠይቃቸው ይመጣል፡፡ ቤታቸው ጎጆ ቤት ነበረችና ምግብ ማብሰያቸውም ማረፊያቸውም አንድ ላይ ነበር፡፡ በዚያው እለት ሚስት ለእራት የሚሆን ገንፎ በማዘጋጀት ላይ እንዳለች ባል የሚስቱን መጥፎነት ለእንግዳው ያወራል፡፡ በዚህን ጊዜ ሚስት ባልታሰበ ሁኔታ በምታገነፋበት እንጨት ባሏን አፉ ላይ ታቀምሰዋለች፡፡ በዚህን ጊዜ ባል ክብሩ ተዋርዶና አፍሮ እንግዳው ባለበት የሚያደርገው ጠፍቶበት የሚለው ቢያጣ "የገንፎሽ ጥፍጥና የገንፎ እንጨቱን ሊያስውጠኝ ነበር" አላት ይባላል (Abraham፣2000፡113)፡፡

### ተረት 3

አንዲት ሴት ልጅ የነበረቻቸው አንድ ሰው ነበሩ፡፡ ገና ትንሽ ልጅ ናት ብለው ስለሚያስቡ ለጋብቻ የሚጠይቁ ሽማግሌዎች ሲመጡ "ትንሽ ናት" እያሉ ይመልሱ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አሁንም ሽማግሌዎች ወደ ቤታቸው ይመጣሉ፡፡ ሰውየው ተናድደው "ልጄ ገና ትንሽ ልጅ ናት" ብለው ሽማግሌዎችን ይመልሳሉ፡፡ ይህንን ሁሉ ልጂት ስትወጣ ስትገባ የሚሉትን ሁሉ ትሰማ ነበር፡፡ ልጂቱ ምድጃ ላይ ትንሽ የጎመን ማብሰያ ድስት ጥዳ ድስቱ የማይችለውን ጎመን ከጓሮ ቆርጣ ይዛ መጣች፡፡ አባትዮው ይህንን አይተው "ምነው ልጄ ድስቱ ትንሽ ይህንን ሁሉ ጎመን ለምን ይዘሽ መጣሽ? ይችለዋል?" ይሏታል፡፡ ልጂቱም "አባዬ የሜትና የድስት ትንሽ የለውም ለምን እንዲህ ትለኛለህ?" ትላቸዋለች፡፡ አባትዮው ነገሩ ወዲያው ገባቸውና ሽማግሌዎቹ ሳይርቁ ሮጠው ሄደው በመጥራት ልጃቸውን ሰጥተው ወቅቱ ሲደርስ ዳሩ ይባላል (ለማ ንጋቱ 1999፡88)፡፡

### ተረት 4

በድሮ ጊዜ ከብት እያረቡ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ሰውዬው ከብት ሲጠብቁ ውለው ወደ ማታ ወደቤታቸው ይመለሳሉ፡፡ ሲመለሱም ሚስታቸው የእግር ውሃ አሙቃ፣ ቡና አፍልታ፣ ምግብ አዘጋጅታ፣ አልጋዋን አስተካክላ አንጥፋ ትጠብቅና ከብቶቹን አስገብታ አስራ የባሏን እግር ወዲያውኑ አጥባ ቡናውን ምግቡን ታቀርባለች፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሴትዮዋ ባሏን በማክበር ኑሯቸውን ይመሩ ነበር፡፡

ከእለታት አንድ ቀን ሰውዬው ከብቶቹን ሲጠብቅ እንደ ሰመመን አድርጎት ከዛፍ ስር ተኝቶ እያለ ሰይጣን ከዛፉ ላይ ሆኖ "ዛሬ ይህንን ሰው አጋጭተን ደሙን መጠጣት አለብን" ሲል ይሰማል፡፡ ብንን ሲል ምንም ነገር የለም፡፡ ሰውዬው ሰይጣን መሆኑን ያውቃል፡፡

ወደማታ እንደተለመደው ከብቶቻቸውን ይዘው ወደ ቤታቸው ሲገቡ ሚስቲቱ ያለወትሮዋ ከብቶቹን አስገብታ በማሰር ፈንታ ታናግራቸዋለች፡፡ ሰውየውንም ትቆጣቸዋለች፡፡ እሳቸው ግን ሁሉንም በትዕግስት ችለው ከብቶቹን አስገብተው እራሳቸው እያሰሩ እንዳለ ከጎረቤት ጩኸት ይሰማል፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስቲቱ "እንዴ! እነእገሌ ቤት ጩኸት ተነሳ" ትልና እየሮጠች ትሄዳለች፡፡ ከዚያ ደርሳ ስትመለስ ንዴቷ ሁሉ በርዶ "እኔ አፈር ልብላ እኔ እኮ ምን እንደሆንኩ አላውቅም" ብላ ከባሏ እግር ላይ

ወድቃ ይቅርታ በመጠየቅ ውሃ አሙቃ አጠበቻቸው፡፡ ምግብም እንደተለመደው አቅርባላቸው በሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ሁሉም ነገር እንደተለመደው ሆኖ ኖሩ ይባላል (ለማ ንጋቱ 1999፡88-89)፡፡

**ተረት 5**

አንድ ልጅ የነበራቸው አባት ነበሩ፡፡ ልጃቸውን ሲመክሩ "ለሚስትህ ሚስጥር አትንገር፣ ገመድ በቤትህ አትስቀል፣ ከበርህ አካባቢ ዛፍ አትትከል፣ ሎሌ አታስገባ፣ ከመንገድ ዳር እሸት አትዝራ" አሉት፡፡ ይህንን መክረውት ሲኖር ሲኖር የአባቱን ቃል ችላ በማለት ዛፍ ከግቢው ተከለ፤ ሎሌም አስገባ፤ ገመድ ከቤቱ ሰቀለ፤ መንገድ ዳርም ባቄላ ዘራ፡፡ ባቄላው ሲያሽት የጎረቤት ልጅ ከዚያ ገብቶ ሲበላ አገኘ፡፡ ልጁን አፍኖ ሩቅ አገር ከሰው አስጠግቶ ተመለሰ፡፡ ልጁ በመጥፋቱ ሞቷል ተብሎ ሲኖር ሲኖር አንድ ቀን ለባለቤቱ ሌሊት እንደተኙ "የእገሌን ልጅ እኔ ነኝ ገድዬ የቀበርኩት" ብሎ ይነግራታል፡፡

ሚስቲቱም ስትቁነጠነጥ አድራ ጧት እሳት ልትጭር ወደ ጎረቤት ትሄዳለች፡፡ ከዚያም ለጎረቤቷ "ለሰው እንዳትናገሪ ምስጢር ልንገርሽ" ትልና "የእገሌን ልጅ እሸት ውስጥ አግኝቶ ገድሎ የቀበረው የኔ ባል ነው " ብላ ትነግራታለች፡፡ ሚስጢር ስለሆነ ለሌላ ሰው መንገር እንደሌለባት ታስጠነቅቃታለች፡፡

ይህቺ ምስጢሩን የሰማች ጎረቤት "እሷ ያልደበቀችውን እኔ ምን ቸገረኝ" በማለት ለባሏ ትነግረዋለች፡፡ ባልዮው በቀጥታ ይሄድና ለልጁ አባት ይናገራል፡፡ የልጁም አባት ሰዎችን ሰብስቦ ወደ ገዳይ ቤት ይመጣና ይይዙታል፡፡ ከዚያም የልጁ አባት "እንዲህ ያለ ወንጀል ፈጽሟልና ምን ይገባዋል?" ሲል ተሰቅሎ መገደል አለበት ተብሎ ይፈረዳል፡፡ "የት ነው የምንሰቅለው" ሲባል ሎሌው "ያውና ዛፍ" ብሎ ያሳያቸዋል፡፡ "ገመድስ የት እናገኛለን" ሲሉ "ይሄው ገመድ" ብሎ የተሰቀለውን ገመድ ይሰጣቸዋል፡፡

ከዚያ ሰዎቹ ተጋግዘው ሊሰቅሉት ሲሉ ሰውየው "ከመሰቀሌ በፊት አንድ ነገር ልንገራችሁ፡፡ ከዚያ እኔም ለመሰቀል ፈቃደኛ ነኝ" ሲል ይለምናቸዋል፡፡ ሰዎቹም "ምንድን ነው የምትነግረን! በል እሺ ተናገር" ሲሉ ፈቀዱለት፡፡ ከዚያ ሰውየው "ይሄውላችሁ ልጁ በህይወት አለ፡፡ "እኔ ይህንን ሁሉ ያደረግኩት የአባቴን ምክርና ምስጢር ለማወቅ ነበር፡፡ አባቴ 'ምስጢር ለሚስትህ አትንገር፤ ዛፍ ከግቢህ አትትከል፤ ገመድ ከቤትህ አትስቀል፤ ከመንገድ ዳር እሸት አትዝራ' ብለው የመከሩኝን ባለመስማቴ ለዚህ ሁሉ ችግር አጋልጦኛል፡፡ አሁን እግዚአብሔር በጥበቡ አትርፎኛል፡፡ ይህ በእኔ

የደረሰው ለእናንተ ምክር ይሁናችሁ፡፡ ያባታችሁን ምክር አትተለለፉ” ብሎ ለሰዎቹ ምክር ሰጥቶ ልጁንም ከደበቀበት አምጥቶ አስረከበ ይባላል (ለማ ንጋቱ 1999፡94)፡፡

**ተረት 6**

በድሮ ጊዜ አንዲት ውሽማ የያዘች የቄስ ሚስት ነበረች፡፡ ባሏን እያታለለች ስትኖር ስትኖር ከእለታት አንድ ቀን ውሽማዋ በቀን ሲገባ ሲወጣ ቢታይ አደጋ ላይ ስለሚወድቁ በሌሊት ልታስተናግደው ዘዴ ፈጠረች፡፡ ውሽማዋ ማታ መጥቶ በታዛ እንዲቀመጥ ከተማከሩ በኋላ ከባሏ ጋር ትንሽ እንደተኙ ቀሰቀሰችና “ይነሱ! ረፈደብዎ! ወደ ቤተክርስቲያን ይሂዱ” አለችው፡፡

ቄሱም ሰዓት ስላልነበራቸው ተደናግጠው ልብሳቸውን በመልበስ ወጥተው ሄዱ፡፡ በዚህ ጊዜ ውሽማ ወደ ቤት ገብቶ አልጋው ላይ ተጋድሞ ገንፎ ይገነፋለት ጀመር፡፡ ቄሱ ትንሽ እልፍ እንዳሉ አውሬ አላስኬድ ብሏቸው ወደ ቤት ተመልሰው በሩን ሲቆረቁሩ ውሽማ አልጋ ስር ገብቶ ተደበቀ፡፡ ቄሱ ወደቤት እንደገቡ ድስት ተጥዶ በማየታቸው ተገርመው “እንዴት በሌሊት ገንፎ ታገነፊያለሽ?” ብለው ሲጠይቋት በማዘን ብርድ ስለገደላቸው ለእርሳቸው እየሰራች መሆኗን ትነግራቸዋለች፡፡ እሳቸውም እውነት መስሏቸው አልጋቸው ላይ ወጥተው ሲጠብቁ ገንፎውን ሰርታ አቀረበች፡፡ መብላት እንደጀመሩ እሳቸው ሳያዩ አልጋው ስር ለተደበቀው ውሽማዋ ልታጎርስ እጇን ስትልክ አጎንብሶ አውጭኝ አውጭኝ በሚልበት ቂጡ ላይ ትኩሱን ገንፎ ታጣብቅበታለች፡፡ በዚህ ጊዜ ውሽማው ደንብሮ ሲነሳ ቄሱን ከነገንፎው ገልብጦ መሬት ላይ ይዘርራቸዋል፡፡ ቄሱም እሷም ደንግጠው ከወደቁበት እየተነሱ “ምንድን ነው አንቺ?” ብለው ሲጠይቁ “ከእርስዎ ጋር መጥቶ የገባ ሰይጣን ነው በስመአብ ይበሉ” ትላቸዋለች፡፡ እሳቸውም ዳዊታቸውን መድገም ሲጀምሩ ውሃ የምትደፋ መስላ ቀስ አድርጋ ውሽማዋን አስወጥታ ትልከዋለች፡፡

ቄሱ ዳዊታቸውን እየደገሙ ዓይናቸውን ወደ ወለሉ ላክ አድርገው ሲመለከቱ የውሽማ ቀይ ፎጣ ወድቆ ያዩታል፡፡ “ምንድን ነው እሱ አንቺ?” ሲሏት ”የሰይጣኑ ዋጋ ነው አበስኩ ገበርኩ እየው በስመአብ ሲሉት ደንግጦ ጥሎት ሄደ! ቶሎቶሎ ይድገሙማ” እያለች የተጣደፈች መስላ ፎጣውን በወጥ እንጨቱ አንጠልጥላ ውጭ ትጥለዋለች፡፡ ውሽማም በር ቆሞ ይጠብቅ ኖሮ ፎጣውን ይዞ ሄደ፡፤ በዚህ ሁኔታ ባሏን አታለለችው ይባላል (ለማ ንጋቱ 1999፡100)፡፡

## ተረት 7

ሁለት ባልና ሚስቶች ትዳር መስርተው ሲኖሩ በመካከላቸው ጠብ ይፈጠራል፡፡ ሚስት ባልን ባል ሚስትን እንደጥፋተኛ በመቁጠር ተወያየተው ከመግባባት ይልቅ እየተጨቃጨቁ ጠቡን አከረሩት፡፡ ሽማግሌ ለማስታረቅ ቢሞክር ሴቷ እምቢ አለች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የልጂቱ ቤተሰቦች በተገኙበት ሽምግልናው ቀጥሎ ሴቷን ለማግባባት ቢሞከር አሻፈረኝ ትላለች፡፡ በዚህ ሁኔታ የተናደዱት ሽማግሌዎች “እንግዲህ አልታረቅም ካለች ባሏ ያለበሳትን ልብስ እዚህ እሽማግሌ ፊት አውልቃ እርቃኗን ትመለስ” ሲሉ ይወስናሉ፡፡ እሷም በሽምግልናው ላይ ፊቷን ወደ እናትና አባቷ ዞራ ጀርባዋን ለባሏ ሰጥታ የነበረችው ወደ ባሏ ዞራ ልብሷን ታወልቃለች፡፡ በዚህ ጊዜ ሽማግሌዎቹ “የልጂቱ ጥል ካንጀት ሳይሆን ካንገት ነው” ብለው እንደገና በመሽምገል ወደቤቷ መለሷት፡፡ ቤተሰቦቿም በድርጊቷ ተናድደው ጥለዋት ሄዱ ይባላል (ለማ ንጋቱ 1999፡106)፡፡

## ተረት 8

በአንድ አገር ውስጥ አንድ የታወቀ ባለጸጋ ነበር፡፡ ባለጸጋው ብዙ አሽከሮችና በቁንጅናዋ አንቱ የተባለች ሚስት ነበረችው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አገሩ በጠላት ይወረርና ወደ ዘመቻ ለመሄድ ይነሳል፡፡ ከሰው መርጦ ለሹመት ከእንጨት መርጦ ለታቦት እንዲሉ ከአገልጋዮቹ አንዱን መርጦ የንብረቱና የሚስቱ ጠባቂ ያደርገዋል፡፡ ባለጸጋው ለአገልጋዩ “ብሞትም እንኳ በምድር የሰጠሁህን በሰማይ እቀበልሃለሁ” በማለት አደራውን ይሰጠዋል፡፡

የጌታው ሚስት ግን ባለቤቷ እያለ እንኳ ከዚህ አገልጋይ ጋር የመማገጥ ስሜት ታሳይ ነበር፡፡ ምቹ ጊዜ እስከምታገኝ እንኳን አትታገስም ነበር፡፡ ባሏ ከሄደ በኋላ ምንም ጊዜ ማባከን አልፈለገችም፡፡ ለአገልጋይዋ የነበራት አመለካከት ሁሉ ተቀየረ፡፡ የሴት አገልጋይዋን ጥሩ ምግብ እንድታዘጋጅለት ታዝዛት ጀመር፡፡ ሆኖም ግን አደራ ተቀባዩ አገልጋይ ስሜቷን በፍጹም አልተረዳም ነበር፡፡ እንዲያውም እሱ የሚመስለው ጌታው የጣለበትን አደራ በሚገባ እንዲወጣ ጌታው አዝዘው ይመስለው ነበር፡፡ ጌታውን እያመሰገነ ይበላ ነበር፡፡ አንድ ቀን እግሯን በራሷ እልፍኝ ውስጥ እንዲያጥባት አድርጋ ጭኗን አሳየችው፡፡ በሁለተኛው ቀን ደግሞ አልጋዋ ላይ ተጋድማ ጀርባዬን እሸኝ አለችው፡፡ በዚህ ጊዜ አገልጋዩ የእመቤቱን ስሜት በሚገባ ተረዳ፡፡ የታዘዘውን ፈጽሞ

ከክፍሉ ከመውጣቱ በፊት እመቤቲቱ ዘልላ ተነስታ አልጋዋ ላይ ወረወረችው፡፡ ሆኖም አገላጋዩ በፍጥነት ከክፍሏ ሮጦ ወጣ፡፡

ከጥቂት ቀናት በኋላ ባለጸጋው በድል ተመለሰ፡፡ ለክብሩም ትልቅ ድግስ ተደረገ፡፡ ወዲያው ሚስቱ እንባዋን በቁንጮቿ ላይ እያወረደች አሽከሩ አስገድዶ ሊደፍራት ሲሞክር አምርራ በማልቀሷና እሪታዋን በማሰማቷ ሳይደፍራት መቅረቱን ነገረችው፡፡ ባለጸጋውም "አዬ! ካሽከሮቼ ሁሉ አስበልጬ ሃላፊነት ብሰጠው ሊደፍርሽ ሞከረ? እኔ ይቅር ብለው ፈጣሪዬ ይቅር አይለውም " አለና አሽከሮቹ በሙሉ እንዲሰበሰቡ አደረገ፡፡ ሁሉም እንደደረሱ "በወንዙ ዳርቻ ጉርጓድ ትቆፍራላችሁ፡፡ ከዚያም የሆነ ሰው መጥቶ ትዕዛዙን እንድትፈጽሙ ሲነግራችሁ ከነህይወቱ ከወገቡ በታች ትቀብሩትና ከብት ትነዱበታላችሁ" ይላቸዋል፡፡ ከዚያም ጥፋተኛ የተባለውን አገልጋይ ይጠራና "ወንዝ ወዳሉት ጓደኞችህ ትሄድና ትዕዛዜን እንዲፈጽሙ ትነግራቸዋለህ" ይለዋል፡፡ እሱም ወደዚያው እየሄደ እንዳለ አንድ እግሩን ጋሬጣ የወጋው መነኩሴ ያገኛል፡፡ እንዲህ ሆኖ ጥየው ብሄድ ደግ አይደለም ይልና ቁጭ ብሎ ጋሬጣውን ማውጣት ይጀምራል፡፡ በዚህ ምክንያት አገላጋዩ የተላከበት ቦታ ሳይደርስ ይዘገያል፤ የትዕዛዙም መፈጸም አለመፈጸም ወደ ባለጸጋው ሳይደርስ ይዘገያል፡፡ የባለጸጋው ባለቤት የአሽከሩን ከነነብሱ የመቀበር ዜና ለመስማት ብትጓጓም ይዘገይባታል፡፡ አላስችል ብሏት ወደ ወንዙ በፍጥነት ትሄዳለች፡፡ አግጋዮቹም የሚቀብሩትን እየጠበቁ ነበር፡፡ እንደደረሰች "ትዕዛዙን ፈጸማችሁ?" ትላቸዋለች፡፡ አሽከሮችም "አንቺ ነሽ ማለት ነው" ብለው ከወገቧ በታች ከቀበሯት በኋላ እስከምትሞት ድረስ ከብቶችን አመላለሱባት፡፡

ባልዮው የሆነውን ሁሉ በሰማ ጊዜ ማመን አቅቶት ሃላፊነት የተሰጠውን አሽከር ያደረገውን ሁሉ ይጠይቀዋል፡፡ አሽከሩም የሆነውን ሁሉ ከመነሻው እስከ መጨረሻው ይነግረዋል፡፡ ባለጸጋውም "የስራዋን አግኝታለች" ይላል፡፡ ከዚህ በኋላ ጌታና ሎሌው በደስታ ኖሩ ይባላል (Yehenew Jembere 1996፡154-155)

## ተርት 9

አንድ ግደለሽ ንጉስ አንድ ገበሬ ያገኝና እንዲህ ሲል ይጠይቀዋል፡፡ "ወዲያ ወዲህ ማለት የለም! ለምጠይቅህ ጥያቄ ቀጥ ያለ መልስ ትሰጠኛለህ" ይለዋል፡፡ ገበሬውም ታዛዥነቱን ይገልጻል፡፡ "በሰማዩ ላይ ስንት ኮኮቦች አሉ?" ሲል ይጠይቀዋል፡፡ ገበሬውም "ይህንን ማንም የነገረኝ የለም" ሲል አለማወቁን ይነግረዋል፡፡ ንጉሱም ይህንን አስከትሎ "ደህና!

ለመሆኑ የመሬት መሃል የት ነው?" በማለት በድጋሚ ይጠይቀዋል፡፡ ገበሬውም "ጌታዬ አላውቀውም! ይህንንም የነገረኝ የለም" ሲል ይመልሳል፡፡ ንጉሱ ይህን ጊዜ ተናድዶ "የዚህን መልስ ነገ ካላመጣህ በህዝብ ፊት ትሰቀላለህ" ብሎ ያሰናብተዋል፡፡

ገበሬው በዚህ እጅግ አዝኖ ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ ሚስቱ ለእጁ ውሃ ይዛ ልታስታጥበው ስትል እጅግ አዝኖና ተክዞ ታየዋለች፡፡ እጅህን ታጠብና እንብላ ስትለው አልበላም ይላታል፡፡ እሷም ምን እንደሆነ ትጠይቀዋለች፡፡ ይህንን ጊዜ ገበሬው ለሚስቱ "ወደቤቱ ስመጣ ንጉሱን መንገድ ላይ አገኘኋቸው፡፡ እናም ንጉሱ 'በሰማይ ላይ ያሉት ከዋክብት ስንት ናቸው? የምድር መሃሉስ የት ላይ ነው?' ብለው ጠየቁኝ፡፡ መልሱን አላውቀውም ስላቸው 'ነገ የዚህን መልስ ካላመጣህ በህዝብ ፊት ትሰቀላለህ' አሉኝ፡፡ ለዚህ ነው የተጨነቅኩት፡፡ ከዚህ በላይ ምን የሚያስጨንቅ ነገር አለ?" ይላታል፡፡ እሷም ነገሩን አቅልላ "ላንተ ሁልጊዜ ሁሉ ነገር ከባድ ነው፡፡ በል ታጠብና እራታችንን እንብላ" ትለዋለች፡፡ እሱም "አይ አልበላም፡፡ ጾሜን አድሬ ፈጣሪዬን ስለምን አድራለሁ" ይላል፡፡

እሷም "አትጨነቅ፡፡ አሁን ታጠብና እራታችንን እንብላ፡፡ መልሱን ጧት እነግርሃለሁ" ትለዋለች፡፡ ከዚያም እራታቸውን በልተው በሰላም ያድራሉ፡፡ ሲነጋ "በይ መልሱን ንገሪኝ" ይላታል፡፡ እሷም አንድ አቅማዳ ሙሉ ጤፍ ታመጣና ትሰጠዋለች፤ ጦሩንም ታስይዘዋለች፡፡ አስከትላም "የሰማይ ከዋክብት ስንት ናቸው ብሎ ሲጠይቅህ እዚህ አቅማዳ ውስጥ ባለው ጤፍ ልክ ነው በለው፡፡ የመሬትን መካከል ሲጠይቅህ ጦርህን ፊት ለፊቱ ቸክለህ ይሄ ነው በላው፡፡ ከተጠራጠረህ ቆጥረህና ለክተህ አረጋግጠው በለው" ትለዋለች፡፡

ገበሬው ሚስቱ በመከረችው መሰረት ጤፉንና ጦሩን ይዞ በመቅረብ "ጌታየ! መልሱን ይዤ መጥቻለሁ" ይላቸዋል፡፡ እሳቸውም "እሺ ለመሆኑ የሰማይ ከዋክብት ስንት ናቸው?" ሲሉት "በዚህ አቅማዳ ውስጥ ባለው ጤፍ ልክ ናቸው" ይላቸዋል፡፡ ንጉሱም "እኸ! የመሬት መሃሉስ" ሲሉት ጦሩን ከፊታቸው ቸክሎ "ይሄ ነው፡፡ ካላመኑኝ ቆጥረውና ለክተው ያረጋግጡ" ይላቸዋል፡፡ ንጉሱ የገበሬውን እውቀት አድንቀው ሸልመው አሰናበቱት ይባላል (Yehenew Jembere 1996:184-185)

### ተረት 10

አንድ በየጊዜው አግብቶ የሚፈታ ሰው ነበር፡፡ ዛሬ አግብቶ በማግስቱ ይፈታል፡፡ ሁኔታው ግራ ያጋባቸው ዘመዶቹ በቁንጅናዋ እዚህ ቀረሽ የማትባል ሚስት ፈልገው

ያጋቡታል። ምንም እንኳ ያጋቡት እዚህ ቀረሽ የማትባል ብትሆንም እሷንም በማግስቱ ፈታት። አንድ ቀን በመልኳ የማትመረጥ ፉንጋ ያገባል። ልክ አግብቶ እንደፈታቸው ሁሉ ለዚችም ሁለት እፍኝ ገብስ ሰጥቶ ለእነርሱ፣ ለፈረሱና ለውሻው ምግብ እንዲታዘጋጅ ያዝዛታል። ወዲያውኑ ቆሻሻውን ከለቀመች በኋላ ትወቅጠዋለች። ከዚያም ፍሬውን ከአሰሩ ከለየች በኋላ ፍሬውን ትፈጫለች። አሰሩንም ለፈረሱ ታስቀምጣለች። ከዚያም ከላመው ዱቄት ለእነርሱ ከክርቱ ለውሻው እራታቸውን ታዘጋጃለች።

ወቅቱ ሲመሽ ባልዩው ከብቶቹን እየነዳ ከቤት ይደርሳል። ወዲያውም "እንዳልኩሽ ራታችንን ለእኛ፣ ለፈረሳችንና ለውሻችን አዘጋጀሽ?" ይላታል። እሷም "አዎ" በማለት ታሳየዋለች። ይሄኔ "እስከ ዛሬ በየእለቱ ሳገባና ስፈታ የኖርኩት እንደ አንቺ ዓይነት ሴት አጥቼ ነው። ዛሬ እስከ ህይወቴ ፍጻሜ የምትሆነኝን ሚስት አግኝቻለሁ" አላት። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ጥንዶቹ እስከ ህይወታቸው ፍጻሜ በደስታ ኖሩ ይባላል (Yehenew Jembere 1999፡193-194)

### ተረት 11

ባለጸጋና ብዙ አሽከሮች የነበሯቸው ሁለት ባልና ሚስቶች ነበሩ። አንድ ቀን ባልዮው ይሞታል። የሙት ዓመቱ ካለፈና ተስካሩ ከወጣ በኋላ ዘመዶቿ እንድታገባ ይመክሯታል። "ከዚህ በኋላ ማግባት ይገባሻል። እንዳለመታደል ሆኖ ባልሽን አጣሽ። ልክ እንደ አንቺ ብዙ ሴቶች ባሎቻቸውን በሞት አጥተዋል። ሆኖም ግን ሃዘናቸውን ሲጨርሱ አግብተው በደስታ ኖረዋል። ብቻሽን ይህን ሁሉ ቤተሰብና ንብረት ማስተዳደር ይከብድሻል። በዚያም ላይ ልጅ ነሽና ቀሪ ጊዜሽን ብቻሽን አትገፊውም። ሴትነትሽንም አይቶ ወንድ ሊደፍርሽ ይችላል። እንደዚያ ቢሆን ደግሞ ለቤተሰቡ ውርደት ነው" በማለት ሲያግባቧት ለማግባት ፈቃዷን ገለጸች። አስቀድማ ግን የራሷን ሃሳብ እንዲህ ስትል አቀረበች። "ለማግባት ከምትመርጡልኝ ሰው ጋር ጋብቻ ከመመስረቴ በፊት ያ ሰው ለተወሰኑ ቀናት ለብቻ በተሰራች ጎጆ ውስጥ መሰንበት አለበት" ስትል ቅድመ ሁኔታ አስቀመጠች።

ለጋብቻ የተመረጠው ሰው ወደ ግቢዋ እንደመጣ ወደተዘጋጀለት ጎጆ ገባ። ሲመሽ እራቱንና ጠላ በእንስራ አስደርጋ ለአገልጋዮቿ ላከችለት። አገልጋዮቹ ሲመለሱ "ምን አደረገ?" ስትል ትጠይቃቸዋለች። "ሁሉንም በላ ጠጣ። ከዚያ እቃውን መልሰን አመጣን" ይሏታል። ሲነጋም ከአሽከሮቹ ጋር ስራ እንዲያከናውን ወደ እርሻ

ትልከዋለች፡፡ መሸቶ አሽከሮቹ ሲመለሱ “ምን ሲያደርግ ዋለ?” በማለት ትጠይቃቸዋለች፡፡ እነርሱም “ቀኑን ሙሉ ዛፍ ስር ተጎልቶ ዋለ” ይሏታል፡፡ በመጨረሻ እመቤቲቱ “አላገባህም!” ብላ ታሰናብተዋለች፡፡ በዚህ ዓይነት ሁኔታ ዘመዶቿ ያመጡላትን በርካታ ባሎች እየፈተነች ታሰናብታቸዋለች፡፡

ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰው አጪተው ያመጡላታል፡፡ እንደተለመደው በዚያች ጎጆ ውስጥ ሌሊቱን ብቻውን እንዲያልሳፍ ታደርገዋለች፡፡ ጠላና እራትም ትልክለታለች፡፡ እርሱ ግን ድረሻውን ተጠቅሞ “ይህንን ለእርሷ ውሰዱላት፤ እናንተም ይህንን ብሉ ጠጡ” ይል ነበር፡፡ አመቤቲቱ እንደሌሎቹ ሁሉ “ምን አደረገ?” ብላ ትጠይቃለች፡፡ ያደረገውን ሁሉ ይነግሯታል፡፡ በማግስቱ ጧትም ወደ እርሻ ካሽከሮቹ ጋር ትልከዋለች፡፡ እሱም ከአሽከሮቹ ጋር ቀኑን ሙሉ ሲሰራ ይውላል፡፡ በስራው ከሁሉም አሽከሮች ይበልጥ ነበር፡፡ ምሽት ላይ ከስራ ሲመለሱ አሽከሮችን “ምን አደረገ?” ስትል ትጠይቃቸዋለች፡፡ የሆነውን ሁሉ ይነግሯታል፡፡ ከዚህ በኋላ እመቤቲቱ “አሁን ባሌን አግኝቻለሁ” በማለት አገባችው፡፡ ከዚያ በኋላ ከባሏ ጋር በደስታ ኖሩ ይባላል (Yehenw Jembere 1999፡194-195)፡፡

## ተርት 12

በአንድ ወቅት አንድ የመንግስት ቀረጥ ሰብሳቢና ገንዘብ ያዥ በአንድ አገር ውስጥ ይኖሩ ነበር አሉ፡፡ በዚያው አገር አንዲት በባሏ ላይ የምትማግጥ ሴት ነበረች፡፡ ይቺ ሴት የነዚህ ሁለት ሰዎች ውሽማ ነበረች፡፡ አንድ ቀን ታዲያ ቀረጥ ሰብሳቢው ቀደም ብሎ ገብቶ ፍቅሩን ሲሰራ ከቆየ በኋላ ጠላ እየጠጣ እንዳለ ገንዘብ ያዡ ይገባል፡፡ በዚህ የተደናገጠው ቀረጥ ሰብሳቢ ዘልሎ ማጀት ይገባል፡፡ እንዲሁ ገንዘብ ያዡ እየተስተናገደ እንዳለ ባልዮው ይመጣል፡፡ ገንዘብ ያዡም እንደ ቀረጥ ሰብሳቢው ማጀት ይገባል፤ ይገናኛሉ፡፡ ባልዮው መደቡ ላይ እንደተቀመጠ ሚስት ሆዬ ”ግብራችንን እንድትከፍል ደጋግሜ ነግሬህ ነበር፤ ግን ልትከፍል አልቻልክም፡፡ በዚህም የተነሳ ይሄው ገንዘብ ያዡና ቀረጥ ተቀባዩ ትልቁን ጋን ሊወስዱ ማጀት ገብተዋል” ትለዋለች፡፡ ይሄኔ ማጀት ያሉት ውሽሞቿ ስትናገር ሰምተው ኖሮ ጋኑን ለመሸከም ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ይሄኔ ሞኙ ባል ወደማጀት ገብቶ እንዳይወስዱበት ይለምናል፡፡ ወዲያውም ግብሩን ከፍሎ ጋኑን ያስቀራል፡፡ በስምምነቱ የተደሰተቸው ሚስት ጠላ ሰጥታቸው ሲጫወቱ ካመሹ በኋላ በሰላም ተለያዩ ይባላል (Yehenw Jembere 1996፡214-215)፡፡

## ተርት 13

አንድ ሰው ከውሽማው ጋር ተኝቶ እንዳለ ሃፍረተ ስጋው አልነሳለት ይላል፡፡ እናም በሃፍረት ከጎኗ ይተኛል፡፡ “ሲነጋ እንዴት ብዬ ነው አይኗን የማየው?” እያለ ይጨነቃል፡፡ በዚህ መሃል ሴቷ ፈሷን ትለቀዋለች፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬው ደስ ይለዋል፡፡ ምክንያቱም እሷም አሳፋሪ ነገር በማድረጓ ታፍራለች በሚል ነበር፡፡ እንዲህ ሆኖ እያለ እንዳታፍር ብሎ “የሚጮኸውን ጅብ ሰማሽው?” ይላታል፡፡ እሷም “የሞተውን አህያ ሊበላ ይሆናል” ብላ የሃፍረተ ስጋውን መሞት በዘዴ ነገረችው ይባላል (Yehenw Jembere 1996፡234)፡፡

## ተርት 14

በድሮ ጊዜ ሁለት እህትማማቾች ነበሩ፡፡ አንደኛዋ እናቷ ሞታባት ነበር፡፡ በቤት ውስጥም እንጀራ እናቷ በጣም ታሰቃያት ነበር፡፡ የራሷን ልጅ ግን ምንም ስራ አታሰራትም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሰው ለልጁ ሚስት ለማጨት ወደ ቤታቸው ይመጣል፡፡ በቤት ውስጥም ከሁለቱ እህትማማቾች በስተቀር ማንም አልነበረም፡፡ ሰውየው እቤት ውስጥ ተቀምጦ የልጆችን ሁኔታ ሲመለከት እናት ያላት ልጅ እህል እየቆላች ትበላና ትጠጣ ነበር፡፡ እናት የሌላት ልጅ ደግሞ ያንን ሰውዬ ቀና ብላ ሳትመለከት ቤቱን ጠርጋ እቃውን ሁሉ ሰታተራ እህል ትፈጭ ነበር፡፡

ሰውየው የልጆችን ሁኔታ ሲያስተውል ቆይቶ በመጨረሻ ልጂቱ ከምትቆላው ባቄላ ሰባት ፍሬ ካነሳ በኋላ እንደገና በትኖ ሄደ፡፡ እናቲቱ ማታ ስትመለስ የሆነውን ሁሉ ልጇ ነገረቻት፡፡ ሴትዮዋ ይህንን ስትሰማ ልጇን ሙልጭ አድርጋ ሰደበቻት፡፡ ቀጥላም ሰውየው ሰባት ፍሬ ባቄላ በትኖ መሄዱ ምን ማለት እንደሆነ የእንጀራ ልጇን ጠየቀቻት፡፡ ልጂትም “ከሰባት ቀን በኋላ እመጣለሁ ማለቱ ነው” ስትል ነገረቻት፡፡ ሴትዮዋ ልጄ አትዳርም ብላ ስጋት አደረባት፡፡

ያቺ ልጅ እንደተናገረችው ሰውየው ልክ በሳምንቱ እናቷ የሞተችባትን ልጅ ለማጨት ሽማግሌ ይዞ መጣ፡፡ ከልጅቷ አባት ጋርም ከተነጋገረ በኋላ ተስማተው የሰርጉ ቀን ተወሰነ፡፡ ያቺ የእንጀራ እናትም የራሷ ልጅ ቀርታ የእንጀራ ልጇ በመታጨቷ በጣም ተናደደች፡፡ የእንጀራ ልጇ ቀርታ የራሷ ልጅ የምትዳርበትን ዘዴ ትፈልግ ጀመር፡፡ የተከሰተላት ዘዴም የእንጀራ ልጇን በአቅራቢያው በሚገኘው ዘንዶ ማስዋጥ ነበር፡፡ ይህን ለማድረግም ለልጇ እንዲህ ስትል ነገረቻት፡፡

“ከዚያች ከጎደሎ ጋር አብራችሁ ወንዝ ውረዱ፡፡ ከዚያም እዘንዶው ጉርጓድ አፍ ተቀመጭና እሾህ ወጋኝ ብለሽ ጩሂ፡፡ ልታወጣሽ ስትመጣ ወደ ጉርጓዱ ገፍትረሽ ጣያት” አለቻት፡፡ ልጅቱም እናቷ እንደነገረቻት እጉርጓዱ ውስጥ ገፍትራ ከተተቻት፡፡

ይህ ሁሉ ሲሆን አባት ለሙሽራ ልጁ ጌጣጌጥና ልብስ ለመግዛት ወደ እሩቅ አገር ሄዶ ነበር፡፡ ከሄደበት ሲመለስ ልጁ ካገር መጥፋቷን ሲነግሩት እጅግ አዝኖ ስቅስቅ ብሎ አለቀሰ፡፡ ሚስቱም “ባይሆን ድግሱ ተደግሶ ከሚበላሽ ይህችኛዋን እንዳርበት” በማለት ባሏን አግባባችው፡፡

የሰርጉ እለት ሲደርስም ሰርገኞች ሙሽራውን አጅበው፣ ለሙሽራይቱም ልብስና ጌጣጌጥ ጥሎሽ ሁሉ ይዘው መጡ፡፡ እናት ያላት ልጅም ተሞሽራ ተቀምጣ ስለነበር ሰርገኞች ያመጡትን ካባ አለበሷት፡፡ በዚህ ጊዜ ለዘንዶ የተሰጠችው ልጅ ወንድም በእህቱ ሁኔታ በጣም አዝኖ ስለነበር ሁኔታውን ቀስ ብሎ ለሙሽራው ነገረው፡፡ ያ ሙሽራ ነገሩን ለጊዜው ችላ ያለ መስሎ እናት ያላትን ልጅ ይዞ ወዳገሩ ተመለሰ፡፡ እቤት እንደደረሰ ለእናቱ ያላጫትን ልጅ በዘዴ እንደዳሩለት ነገራት፡፡ እውነተኛዋ ሙሽራ ግን በዘንዶ መዋጧን ነገራት፡፡ እናቱም ዘንዶው ልጅቷን የሚተፋት መሆኑን ካረጋገጠችለት በኋላ ዘንዶው እንዲተፋትም ነጭ በግ አርዶ እጉርጓዱ አፍ ላይ መጣል እንዳለበት ነገረችው፡፡ ነጭ በግ አርዶ ሲጥል ዘንዶው ልጅቷን ተፋት፡፡ ወደቤት ይዟት መጣና በዘዴ የተዳረችውን ልጅ ልብስ አለበሳት፡፡ እናት ያላትን ልጅም ምላሷን ቆርጦ፣ ክሰል ቀብቶ እህል ፈጪ አደረጋት፡፡

በዚህ አኳኋን ጊዜያት ካለፉ በኋላ አንድ ቀን ልጇን ለመጠየቅ እናት መጣች፡፡ እቤት ስትገባ ግን ልጇን ባለማየቷ ደንግጣ ወደ የት እንደሄደች ጠየቀቻቸው፡፡ ባልዮውም ልጅቱ ወደ ሩቅ አገር እንደሄደችና ቶሎ እንደማትመለስ ነገራት፡፡ እሷም የልጇን መጥፋት ስትሰማ በጣም አዝና ወደቤቷ ለመመለስ ጉዞ ጀመረች፡፡ ምላሷን ተቆርጣ እንድትፈጭ የተደረገችው ልጅ ግን እናቷን ብትለያትም ማንነቷን ለመናገር ስላልቻለች እንዲሁ ተከተለቻት፡፡ ሴትዮዋ ዞር ስትል በቤት ውስጥ ስትፈጭ የነበረችውን ልጅ አየች፡፡ በዚህ ጊዜ የባሰውኑ ተናድዳ “የእኔን ልጅ የትም ሰድደው አጥፍተው አሁን ደግሞ ገረዳቸውን ይልኩብኛል!” በማለት በድንጋይ የገዛ ልጇን ጭንቅላቷን ብላ ገደለቻት ይባላል (ሰውነት መኮንን 1984፡103-104)፡፡

## ተረት 15

አንበሳ ሚስት አግብቶ ሲኖር በጠና ታመመ ይባላል፡፡ የዱር እንስሳት እየተሰበሰቡ መጥተው ይጠይቁታል፡፡ ሚስቱ የመጡትንና ያልመጡትን ስትመለከት ያልመጣው ቀበሮ ብቻ ሆኖ ታገኘዋለች፡፤ እሷም ለባሏ "ቀበሮ ምን ቢንቅህ ነው መጥቶ ያልጠየቀህ?" ስትል አንበሳን ትጠይቀዋለች፡፡ "ስለዚህ እሱን ጠርተህ መግደል አለብህ" ስትል ትነግረዋለች፡፡ አንበሳም በሚስቱ የሚመራ ነበርና ቀበሮን ለመግደል ይጠራዋል፡፡ ቀበሮ ሳይመጣ ይቀራል፡፡ አንበሳም "ይሄ ጠግቧል ቢታዘዝ እንዴት ሳይመጣ ይቀራል" ይልና ይናደዳል፡፡ ከዚያ ቀበሮ ብዙ ዘግይቶ ይመጣል፡፡ አንበሳም "ትዕዛዜን ለምን አልፈጸምክም? ባልኩህ ቀን ለምን አልመጣህም?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ቀበሮም "ስራ ላይ ሆኜ ነው ሳልመጣ የቀረሁት እንጂ የእርስዎን የአለቃዬን ትዕዛዝ ላለመፈጸም አይደለም" ይለዋል፡፡

አቶ አንበሳም "ምንድን ነው ከእኔ ትዕዛዝ ያስቀረህ?" ይለዋል፡፡ "እኔ የያዝኩት ስራ ከዛፎች መካከል የደረቁትንና ያልደረቁትን፤ ከሰዎች መካከል ደግሞ ሴቶችንና ወንዶችን ስቆጥር ነበርኩኝ" ይለዋል፡፡ አንበሳም "ታዲያ ማን በዛ?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ "ከዛፎቹ መካከል ሊደርቁ ያሉትን ከደረቁት ጋር ስደምራቸው ካልደረቁት ይበልጣሉ፡፡ ከሰዎች መካከል ደግሞ የሴቶችን ትዕዛዝ የሚቀበሉትን ወንዶች ከሴቶች ጋር ስደምራቸው ሴቶቹ በዙ" ይለዋል፡፡

አንበሳ ደንገጥ ይልና "ታዲያ የሴቶችን ወሬ የሚሰማ ከሴቶች ጋር ነው የሚመደበው?" ይለዋል፡፡ "ታዲያስ! በሴት የሚመራ ዞሮ ዞሮ ጾታው ወንድ ቢሆንም ከሴት ተመድቧል" ይለዋል፡፡ በዚህ ጊዜ "አንበሳ ታዲያ ከሴት ልቆጠር ነው?" ይልና ቀበሮውን ሳይገድለው ቀረ ይባላል (ሞላ ጀንበሬ 2002፡12)፡፡

## ተረት 16

አንድ ገበሬ መልከ ቀና ሴት ያገባል፡፡ ሆኖም ሙያ አልነበራትም፤ ሰነፍም ነበረች፡፡ አንድ ቀን ታዲያ ማኅበር ይደርስበትና ሚስቱን እንድትደግስ ይነግራታል፡፡ ሙያ የሌላት ሰነፏ ሚስት ሆዬ ምኑን ከምኑ ታድርገው፡፡ አንድ ቀን ጠቅልላ መግዛት የምትችለውን አንድ ቀን ጌሾ፣ ሌላ ቀን ብቅል በሌላ ጊዜ ደግሞ ስንዴ ከገበያ ስትገዛ ቀኑ ሄደ፡፡ የምታደርገው ጨነቃት፡፡ ምክርም ከጎረቤት ብትጠይቅ ፊታቸውን ነፈጓት፡፡ እንዲህ እንዲህ እያለች ሳለች አንዲት መልከ ጥፉ ለማኝ ሴት ከበሯ ቆማ "በእንተ ስማ

ስለማርያም" ስትል ትለምናለች። ወይዘሮዋ ቁራሽ ይዛ ትወጣለች። በዚህ አጋጣሚ ድግሱ ያሳሰባት ወይዘሮ ለማኟን "አንቺዬ! ድግስ መደገስ ትችያለሽ?" ስትል ትጠይቃታለች። ለማኟም "እሱንስ እችል ነበር፣ ግን ማን ይለምንልኛል?" ስትል ትመልስላታለች። ሰነፏም "እሱን እኔ እለምንልሻለሁ። ብቻ አንቺ ደግሽልኝ" ስትል ትነግራታለች። በዚሁ ተስማምተው ወደየስራቸው ይገባሉ።

ለማኟ አባወራው ከስራ እንደሚመጣ አውቃ ያማረ ወጥ ሰርታ፣ ጥሩ ጠላ ከጎረቤት ገዝታ፣ ለእግሩ ውሃ አሙቃ ትጠብቀዋለች። የድግሱን ስራም ታከናውናለች። ባል ከስራ እንደመጣ እንግዳይቱን ሴት በማግኘቱ ግራ ገብቶት "የት ሄዳ ነው?" ብሎ ይጠይቃል። እሷም የተሸከመውን የእርሻ መሳሪያ ከትከሻው እያወረደች፣ ለበሮቹ የሚበሉት እያቀረበች "ልመና" ትለዋለች። በዚሁ አጋጣሚ እግሩን በሞቀ ውሃ አጥባ፣ ምግቡን ጠላውን አቅርባለት ይበላል፤ ይጠጣል። መልኳንና ሙያዋን ከሚስቱ ጋር ሲያስተያየው ይገርመዋል። "መልክ ምን ያደርጋል?" እያለ በሆዱ ሲያስብ ሚስት ልመናዋን ጨርሳ ወደቤቷ ትመጣለች። በዚህ ጊዜ ባል "ሁላችሁም የምትችሉትን አግኝታችኋል። አንቺም ወደ ልመናሽ አንቺም ወደ የቤት እመቤትነትሽ" ብሎ ሚስቱን አባርሮ ለማኟን ሚስት አደረገ ይባላል (አበበ ከበደ 1982፡50-51)።

### ተረት 17

አንድ ሃብታም ነጋዴ ከአባቱ በውርስ ያገኘው መሬት ለማስወሰን ወደ ገጠር ይሄዳል። የአባቱ መሬት ከዘመዶቹ ራቅ ያለ በስተርጅና ከሌላ ሰው የገዙት ነበር ይባላል። ነጋዴው በቦታው ዘመድ ስለሌለው አንድ ገበሬ ቤት በእንግድነት ያድራል። ከገበሬው ቤት በእንግድነት ተቀምጦ ክርክሩን ጀመረ። የገበሬው ሚስት ገና ልጅ እግርና በጣም ቆንጆ ነበረች። ነጋዴው ከክርክሩ ሲመለስ የገበሬው ሚስት ምግብ እየሰጠችው ጠላ ጠምቃ እያጠጣቸው እንደ ዘመድ ተቀራረቡ። ነጋዴውም እያደር እየወደዳት ሄደ። ማታ ማታ አልጋ ላይ ሆኖ የሚያስበው የገበሬውን ሚስት ነበር። "ሰርቂ ብወስዳትና አግብቻት ብኖር" እያለ ይመኝ ነበር። አንድ ቀን እክርክሩ ቦታ ሳይሄድ ቤት ዋለ። ገበሬው ለእርሻ በጧት ሄደ። ነጋዴው ከአልጋ ላይ ሳይነሳ ቁርስ ሰጠችው። አተኩሮ ሲመለከታትም እንደወደደችው አወቀ። አጋጣሚውን በመጠቀም እንደወደዳት ነገራት። ሰርቆ ይዟት ለመሄድም እንደወሰነ ነገራት። እሷም "ይዘሽኝ ብትሄድ ምን ታደርግልኛለህ" ስትለው "እኔ እንደገበሬው ባልሽ በስራ የምገድልሽ አይደለሁም። በብዙ ገረዶች ታጅበሽ ተኝተሽ እንዲትበይ አደርጋለሁ" ይላታል። ይዟት እንዲሄድ ይስማማሉ። ነጋዴው ከመሄዱ

በፊት እንዳይጠረጠር አስቀድማ ጠፍታ ከተማ እንድትጠብቀው ይስማማሉ፡፡ በማግስቱ የገበሬው ሚስት ትጠፋለች፡፡ ነጋዴው ገበሬውን ያጽናናዋል፡፡ “አይዞህ እንግዲህ ላለፈ አትቆጭ፤ ለሚመጣው ግን አትቀደም፡፡ ሌላ ጥሩ ሚስት አግብተህ መኖር ትችላለህ” ይለዋል፡፡

የዋሁ ገበሬ ነጋዴውን “እርስዎ ትልቅ ሰው ነዎት” ብሎ ምክሩን ተቀብሎ ቀብጣ የጠፋች አልፈልግም ብሎ ይቀመጣል፡፡ በማግስቱ ነጋዴው ጉዳዩ ስላለቀለት ገበሬውን የመሬቱ ወኪል አድርጎ ለአራሽ አሰጥቶ እንዲያሳርስለት አዝዞት ይሄዳል፡፡ ከተማም የገበሬውን ሚስት አግኝቶ ይዞ ወዳገሩ ይሄዳል፡፡ ገበሬው ከብዙ ጊዜ በኋላ በእንግድነት ያስቀመጠው ነጋዴ ሚስቱን ሰርቆ ወስዶ እንዳገባት ይሰማል፡፡ “ቆይ! እሱ እንደሰራልኝ እኔም ሳልሰራለት ይልና መሬቱን በሙሉ ሸጦ ይጠብቀዋል፡፡ ነጋዴው ባመቱ ሲመለስ መሬቱ በሙሉ ተሸጦ ያገኘዋል፡፡ “ምነው ትልቅ ሰው ነህ ብዬ አምኘህ ይህን ትሰራኝ” ይለዋል፡፡ ገበሬውም “አይ! እርስዎ ትልቅ ሰው አልነበሩም፡፡ አሁን ታዲያ ላለፈ ነገር ምን ያበሳጨዎታል? እኔን ላለፈ ነገር አትበሳጭ፤ ለመጪው ግን አትቀደም” ትል አልነበረም እንዴ!? እኔም ትልቅ ሰው ነህ ብዬ አምኜ እቤቴ ባስቀምጥህ ሚስቴን የሰረቅከው?” ብሎ መለሰለት ይባላል (አበበ ከበደ 1982፡62)፡፡

### ተረት 18

ሰውየው ሚስቱን ይጠረጥራታል፡፡ እቤት በገባ ቁጥር የሚያየው የጫማ ምልክት ወንድ እንደሚገባ አስጠረጠረው፡፡ አንድ ቀን ቤቱን በእበት ለቅልቂ ይልና “በይ! አንድ የሰው እግር እንዳይረግጠው፡፡ ቢረገጥ ስመለስ ስለሚያስታውቅ ወይ እኔ ወይ አንቺ!” ብሎ ዝቶባት ይወጣል፡፡ ባልዮው የሄደ መስሎ ወደ ጓዳ ገብቶ ቆጥ ላይ ይቀመጣል፡፡ ሚስቱም ቤቱን በእበት ትለቀልቅና ለባሏ ሰርታ የማታውቀውን ምግብ ትሰራለች፡፡ ቀጥሎም የወንድ ድምጽ ወደ በር ይሰማል፡፡ ሚስቲቱም ቆይ እንዳትገባ ትለዋለች፡፡ እሱም ”ምነው ያ ከረፈፍ ባልሽ ሄዶ የለም እንዴ?” ይላታል፡፡ እሷም “እሱ እንኳ ሄዷል፡፡ ነገር ግን እኔ ጋ ስትገባ የመንደር ሰው አይቶህ እንደሆነ አላውቅም መጠርጠር ጀምሯል፡፡ ዛሬ ምን አለኝ መሰለህ! ቤቱን አስለቅልቆ አንድ የእግር ምልክት ባይበት ዋ! ወይ እኔ ወይ አንቺ ብሎኝ ነው የሄደው” አለችው፡፡ “ለማንኛውም አዝየ ባስገባህ ይሻላል” ትልና በጀርባዋ አዝላ ታስገባዋለች፡፡ ልታስቀምጠው ቀና ስትል ባሏ ቆጡ ላይ ተቀምጧል፡፡ ትደነግጥና “የት ላድርገው? ስትለው “የት አባትሽ ልታስቀምጭው ነው

ያስገባሽው?” ቢላት “አይ! የተለቀለቀውን ሰው እንዳይረግጠው ስላልክ ነው” አለችው ይባላል (አበበ ከበደ 1982፡65)።

**ተርት 19**

ሰውየው ሚስጥሩን ከሚስቱ በስተቀር ለማንም አያወራም ነበር። ነገር ግን ማታ ለሚስቱ የነገራትን እርሻ ውሎ ሲመለስ ሴቶቹ ውሃ ቀድተው ሲመለሱ ሲያወሩት ይሰማል። በጣም ይገረምና “ሚስጥሬ ብዬ የማወራው ለሚስቴ ነው። ታዲያ እንዴት ነው ከሌላ ጆሮ ደርሶ መተረቻ የምሆነው?” እያለ ይገረማል። ይህ ሁኔታ ስለተደጋገመበት በጣም ይጨነቅና ለሚወደው ጓደኛው ያማክረዋል። ጓደኛውም “ሚስጥርህን ለሚስትህ ብቻ ከሆነ የምትነግራት ፈትናት” ብሎ ይመልስለታል። ሰውየውም ሚስቱን የሚወዳትና የማይጠረጥራት ስለነበር “ስነግራት ሰይጣን ሰምቶ ይሆናል እንጂ እሷስ ለማንም አውጥታ አትናገርም” ብሎ ያስባል። በመጨረሻ ግን ሊፈትናት ያስባል።

ማታ እንደተኛ ጠዋት ሳይነሳ ይቀራል። ሚስቱም በመጨነቅ “ምን ነካህ? አመመህ እንዴ? አለወትሮህ ካልጋ ያረፈድከው” ትለዋለች። ባሏም “በጣም አሞኛል። ሆዴ ይጮሃል። ይገለባበጥብኛል” ይላታል። ሆዱን ይዞ ጥቅልል ብሎ ይተኛል። ብዙ ከቆየ በኋላ ሚስቱን ይጠራና “ ጉድ! ጉድ! ዛሬ ጉድ ሆንኩኝ። ይኸውልሽ ተገላገልኩ” ብሎ ደብቆ ይዞት የነበረውን እንቁላል ያሳያታል። “በይ ጉዴ ጉድሽ ነውና ይሄ ወሬ ከእኔና ከአንቺ እንዳይወጣ” ብሎ ይነግራታል። ሚስትም “ይሄማ የአንተ ብቻ ሳይሆን የእኔም ጉድ ነው። እንኳን አንተን በዚሁ በቃህ አለህ እንጂ ምን ብዬ ጉዴን አወጣለሁ” ብላ ቁርሱን አቅርባለት ከበሉ በኋላ ውሃ ልትቀዳ ትወጣለች። የወሬ ጓደኛዋን አብረው ውሃ እንዲቀዱ ትጣራና ወደ ውሃ መቅጃ ይወርዳሉ። ከመንገድም “ዛሬ በባሌ ላይ የደረሰውን ማውራት ያሳፍረኛል፤ ቁጣ ነው” ትላለች። ጎረቤቷም “ምን ሆነ? ደህና ነው” ትላለች። ሚስትም “ጧት ሆዴን አመመኝ ብሎ ከመኝታው ላይ አርፍዶ ወዲያው እንቁላል ወልዶ ዳነ” ትላታለች። ጓደኛዋም በጣም ትገረምና ጉድ ጉድ ብለው ውሃ ቀድተው ይለያያሉ። ወዲያው ጓደኛዋ እንስራዋን አስቀምጣ ሮጣ ወደሌለኛይቱ ጓደኛዋ ቤት ትሄድና ነገሩን ታወራለች። ወሬው እንዲህ እንዲህ እያለ ይዛመታል። ወሬውን ከሰሙት ውስጥ አንዷ ታመመኩ ወዳለው ሰው ቤት በፍጥነት ትሄድና ከተኛበት ጠጋ ብላ “እንኳን ማርያም በሰላም ገላገለችዎት” ትላለች። ሰውየውም “ምን ስለሆንኩ ነው ትቀልጃለሽ እንዴ?” ይላታል። ሴትዮዋም “እኔ ምን እቀልዳለሁ፤ ጧት ባለቤትዎ ውሃ

መቅጃ ላይ አወራች ነው የተባለው፡፡ ለዚህ ነው ልጠይቀዎት የመጣሁት” ብላ ከቤት ትወጣለች፡፡ ባልም “ለካስ የሚስጥሬ አባካኝ የገዛ ግማሽ አካሌ ሚስቴ ነች” ብሎ ሚስጥሩን ለሚስቱ ማውራት ተወ ይባላል (አበበ ከበደ 1982፡73)፡፡

ተረት 20

ሰውየው አንድ ወንድ ልጅ ነበረው፡፡ ልጁም አባቱን በቅንነት ሲያገለግለው ስለኖረ የሴትን መላ፣ የጉንዳን ጉልበት ይስጥህ ይለው ነበር፡፡ ዘወትር የሚለው ይህንኑ ነበር፡፡ ይሄ ያላስደሰተው ልጅ “አባቴን በቅንነት ሳገለግለው ኖሬ አያመሰግነኝም፡፡ ብቻ የሴትን መላ፣ የጉንዳንን ጉልበት ይስጥህ ይለኛል” ብሎ ተቀይሞ ወደማያውቀው አገር ለጌታ ለማደር ይሄዳል፡፡ በመንገድ ላይ አንድ ትልቅ ሰው ያገኛል፡፡ ያ ትልቅ ሰው “የት ትሄዳህ?” ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ልጁም “አባቴን በቅንንት ሳገለግለው አንድም ቀን አመስግኖኝ አያውቅም፡፡ ብቻ የሴትን መላ፣ የጉንዳንን ጉልበት እያለ ይመርቀኛል” ሲል ይነግረዋል፡፡

ያ ሰው ብልህ ኖሮ ያንን ልጅ ብዙ ጉንዳን ወዳለበት ቦታ ይወስደዋል፡፡ አንዱን የሞተ ጉንዳን አንዱ ጉንዳን ተሸክሞ ሲወስደው ያሳየዋል፡፡ “ያውልህ ወዳጄ! የአንዱን ሰው አስከሬን አንድ ሰው ይወስደዋል? አይችልም፡፡ ስለዚህ የጉንዳንን ጉልበታምነት በዚሁ ተረዳው” በማለት ያስረዳዋል፡፡ “የሴትን መለኛነት ደግሞ እቤቴ አሳይሃለሁ” ብሎ ወደቤቱ ይወስደዋል፡፡ “ይሄውልህ ባለቤቴ ከጓዳ ጠላ ልታመጣ ስትገባ ተከትለሃት ትገባና ትቆነጥጣታለህ፡፡ ያን ጊዜ የሚሆነውን ታያለህ” ብሎ ትዕዛዝ ይሰጠዋል፡፡

ሴትዮዋ ወደ ጓዳ ጠላ ልታመጣ ስትገባ ላሽክምሽ ብሎ ተከትሎ ይገባና ሴትዮዋን ይቆነጥጣታል፡፡ ይሄኔ ሴትዮዋ “ውይ!” ትላለች፡፡ ይህን ጊዜ ባሏ “ምን ሆንሽ?” ሲላት “ጉንዳን ቆነጠጠኝ” ትለዋለች፡፡ ልጁም የሴትን ብልሃት በዚሁ ተረድቶ ወደ አገሩ ተመለሰ ይባላል (ደሃብ ትኩእ 1974፡44)፡፡

ተረት 21

አንድ ለአካለ መጠነ የደረሰ ልጅ ያለው ሰው ነበር፡፡ ይህ ሰው ልጁን ልዳርህ እያለ ይጨቀጭቀው ነበር፡፡ ልጁም በነገሩ ብዙም ሳይከፋበት በባህሉ መሰረት “ባለ ሁለት አንገት ልጃገረድ” እንዲያጭለት ካልሆነ በነገሩ የማይስማማ መሆኑን ይገልጻል፡፡

አባቱም ባለሁለት አንገት ልጃገረድ ምን ዓይነት እንደሆነች ስለሚያውቅ እንደሚያጭለት ቃል ይገባል፡

አንድ ቀን አባቱ ይቺን ባለሁለት አንገት ልጃገረድ ፍለጋ ካገር ይሰደዳል፡፡ ሲሄድ ሲሄድ ካንድ ሰው ጋር ይገናኛል፡፡ ሰላምታ እንደተለዋወጡ ባለሁለት አንገት ልጃገረድ ለልጁ ለማጨት እንደሚሄድ ይነግረዋል፡፡ መንገደኛው ሰውዬ በነገሩ ግራ ተጋብቶ ምን ማለት እንደሆነ ሲጠይቀው መልስ አይሰጠውም፡፡ ቀጥለው ሲሄዱ ሲሄዱ ዳገት ያለበት ቦታ ይደርሳሉ፡፡ እዚያም የልጁ አባት መንገደኛውን ጠርቶ "ዳገቱን ተሸክመህ አውጣኝ ወይ ተሸክሜ ላውጣህ" አለው፡፡ ያኛውም አሁንም ግራ ተጋብቶ እንደዚሁ ለየራሳችን መውጣት አለብን ብሎት ዳገቱን ይወጣሉ፡፡ ዳገቱንም ወጥተው አንድ ሜዳ ሲያቋርጡ ኮርማዎች የተቀላቀሉበት ጥቂት ከብቶች ጋ ደረሱ፡፡ በዚህም ጊዜ የልጁ አባት ከብቶችን አይቶ "እነዚህ ከብቶች እኮ ብዙ ናቸው" አለው፡፡ አሁንም መንገደኛው ሰውዬ ምን ማለት እንደሆነ አልተረዳም፡፡ ከዚያም አልፈው ብዙ ከብቶች ያሉበት በመካከላቸው ግን ኮርማ የሌለበት ቦታ ደረሱ፡፡ እዚያም "እነዚህ እኮ ጥቂት ከብቶች ናቸው" አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውዬው በጣም ተናድዶ "ዝም ብለህ ለጥቂቱ ብዙ፣ ለብዙው ጥቂት እያልክ አትቃዥ" ብሎ ይሰድበዋል፡፡ ያንን ስድቡን በትዕግስት አሳልፎ አብረው ሲሄዱ አንድ ግቢው ያልታጠረ ትልቅ የሳር ቤትና ግቢው የታጠረ ትንሽ ጎጆ ቤት ዘንድ ይደርሳሉ፡፡ አሁንም የልጁ አባት እንደበፊቱ ለትንሹ ትልቅ፣ ለትልቁ ትንሽ ብሎ ተናገረ፡፡ ከዚያም ያኛው "አንተ! ልትለክፈኝ ነው እንጂ ትንሽና ትልቅ መለየት አቅቶህ አይደለም" ብሎ ሲመልስለት "ነገሩን ስለማታውቀው ነው እንጂ አንተን ለመልከፍ አይደለም" አለው፡፡ በዚህ እየተጨቃጨቁ ከቆዩ በኋላ የልጁ አባት "ባለ ሁለት አንገት ልጃገረድ ፈልግልኝና ነገ በዚህ ስመለስ መንገድ ላይ ጠብቀኝ" ብሎት ተለያዩ፡፡

መንገደኛው ሰውዬ ቤቱ ከደረሰ በኋላ ለቤተሰቡ "አንድ ተሳዳቢ ሰውዬ አጋጥሞኝ ሲያደርቀኝ ዋለ" ብሎ የተነጋገሩትን በሙሉ አወራላቸው፡፡ ከቤተሰቡ መካከል ለአቅመ ሄዋን የደረሰች ልጅ ነበረችና በጥሞና አዳምጣ እንዲህ አለችው፡፡ "አንተን መስደቡ አይደለም እኮ! እንዲያውም አዋቂ ሳይሆን አይቀርም" አለችው፡፡ እንዴት ብሎ ቢጠይቃት "ዳገቱን ተሸካክመን እንውጣ ሲል እያወራን ዳገቱን ብንወጣ አይደክመንም ማለቱ ነው፡፡ ጥቂት ከብቶች አይቶ ብዙ ናቸው ሲል ኮርማዎች ስለተቀላቀሉባቸው ነገ ብዙ ይሆናሉ፤ ኮርማ የሌሉባቸው ግን ታርደው ወይ ሞተው ሊያልቁ ይችላሉ ማለቱ ነው፡፡ ግቢው ያልታጠረ ትልቅ ቤት ደግሞ ማንም ሊደፍረው ስለሚችል ክብር

የለውም። ትንሽ ሆኖ ግቢው የታጠረ ጎጆ ግን በቀላሉ ስለማይደፈር ይከበራል። ስለዚህ ትልቅ ነው ሲል ይህንን ማለቱ ነው። ባለ ሁለት አንገት ልጃገረድ ማለቱ ክብረ ንጽህናዋ ያልተደፈረች ልጅ ማለቱ ነውና ከመጣ እኔኑ ለልጁ ዳርለት" አለችው።

የልጂቱ አባት በነጋታው መንገድ ላይ ቁጭ ብሎ የልጁን አባት መጠባበቅ ጀመረ። የልጁም አባት የሚፈልገውን አጥቶ ሲመለስ ተገናኝተው ሰላምታ ተለዋወጡ። ከዚያም "ትናንትና እኮ ተሳስቼ አስቀየምኩህ። አንተ ያልከው እውነት መሆኑን አምኛለሁ" አለው። "ማን ነገረህ?" ቢለው "አንዲት የደረሰች ልጅ አለችኝና እሷ ነገረችን" አለው። ባለ ሁለት አንገት ልጅ መሆኗንም ገለጸለት። የልጁም አባት የሚፈልገው ይቺን አይነት ስለነበረ ጋብቻ ጠይቆ አጋቧቸው ይባላል (ሙሉጌታ ነጋሳ 1976፡42-43)።

### ተረት 22

አንድ ካዋቂ ቤተሰብ የተጋባ ሰው ባንድ አገር ይኖር ነበር። ሚስቱም አስተዳደጓ ጥሩ ስለነበር ትንከባከበው ነበር። ከጊዜ በኋላ ግን ባህሪዋ እየተለዋወጠበት ሄደ። ቢመክራትም አልሰማህም አለች። አንድ ቀን ይህንኑ ለወንድሟ ነግሮ እንዲመክራት ጠየቀው። እሱም እቤቷ መጥቶ እንደሚመክራት ተስማምቶ የሚገናኙበትን ቀን ተቀጣጥረው ወደ ቤቱ ይመለሳል። ባልዮውም እቤቱ እንደገባ ለሚስቱ "ወንድምሽ ይመጣልና ዝግጅት እናድርግ" ብሏት ተሰናድተው ጠበቁት።

ያም ወንድሟ በጧት ፈረሱን ጭኖ በቀጠሮው እለት መጣላቸው። እነርሱም ደህና አቀባበል አደረጉለት። አማቹ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ ከመጋበዝ ሌላ ምንም ነገር አላነሳም። የጠራውም አባወራ ሃፍረት ተሰምቶት ስለ ነገሩ አላስታወሰውም። በኋላ አማቹ ፈረሱ ተይዞለት ውጭ እንደቆመ ወደ እህቱ ዞር ብሎ እንዲህ አላት፡- "ምን እበላለሁ ብለሽ ከማሰብ ምን አበላለሁ ብለሽ አስቢ! ምን እላለሁ ከማለት ምን እባላለሁ ብለሽ ፍሪ! የት ትሄጃለህ ከማለት የት እሄዳለሁ ብለሽ አስቢ!" ብሏት ተሰናብቶ ወደቤቱ ተመለሰ።

አባወራውም ሁኔታው ስላልገባው ሳይመክርልኝ ብሎ በጣም ተበሳጨ። ሚስቱ ግን ነገሩን ወዲያው ተረዳቸው። ከዚያ ቀን ጀምራ ምግቡን በደንብ እያበላች በእንክብካቤ መያዝ ጀመረች። አንድ ቀን ማታ ባልዮው አልጋው ላይ ጋደም ብሎ ሚስቱን ጠርቷት "ባለቤቴ! ከዚህ በፊት አስቀይመሽኝ ስለነበረ ወንድምሽ እንዲመክርሽ ጠይቀው መጣ። እሱ ግን ምንም ሳይመክርሽ ወደ ቤቱ ተመለሰ። ቢሆንም የእርሱ ምልኪ ከመካከላችን

ቅሬታን አስወግዷል" አላት፡፡ በዚህ ጊዜ ታዘበችውና "በጣም መክሮኛል፡፡ ከመምከርም አልፎ ሰድቦኛል፡፡ ያን ቀን "ምን እበላለሁ ብለሽ ከማሰብ ምን አበላለሁ ብለሽ አስቢ! ምን እላለሁ ከማለት ምን እባላለሁ ብለሽ ፍሪ! የት ትሄዳለህ ከማለት የት እሄዳለሁ ብለሽ አስቢ!" ሲል የተናገረው ለእርሱ አታበይም፣ ለራስሽ ግን ትበያለሽ፤ ለእርሱ አታስቢም ለራስሽ ግን ታስቢያለሽ" ማለቱ ነው ስትለው "ለካስ ነገር ነገር አለው፡፡ ሚስጢሩንም የሚረዳው ባለቤት አለው" አለ ይባላል (ሙሉጌታ ነጋሳ 1976፡74)፡፡

## ተረት 23

ባንድ ዘመን ባንድ አገር ውስጥ አንዲት ገዢ ሴት ነበረች፡፡ ይቺ ገዢ ጨካኝ ስለነበረች ሊሰሩ የማይችሉትን ድርጊቶች ፈጽሙ ብላ በግዛቷ ላይ ያሉትን ሰዎች ታስቸግር ነበር፡፡ በዚሁ ሳለች አንድ ቀን ሽማግሌዎችና አጫጭር ሰዎች ስልጣኔን ያስለቅቁኛል የሚል አሳብ ስላደረባት ህዝቧን ሰብስባ "ሽማግሌዎችንና አጫጭር ሰዎችን እንድትጨርሱ!" የሚል ትዕዛዝ ታስተላልፋለች፡፡ ሰዎችም ሽማግሌዎችንና አጫጭሮችን እየፈጇቸው እንዳለ አንድ አጭር ሽማግሌ "እኔን አትግደሉኝ፤ እጠቅማችኋለሁ" በማለታቸው እሳቸውን ብቻ ይተዋሉ፡፡

ይቺ ገዢ አንድ ቀን የተወሰኑ ሰዎችን ሰብስባ ለከብቶቿ በረት ስታሳጥር ውላ ማታ ላይ የቀሩትን ሰዎች እንዲሰበሰቡ አደረገች፡፡ ህዝቡ ሲሰበሰብ "ነገ ማታ አልጋዬን ከቤት አውጥታችሁ በከብቶቼ በረት በር ላይ አድርጉልኝ፡፡ እኔም እዚያው እተኛለሁ፡፡ ነገር ግን ከእንቅልፌ ከመንቃቴ በፊት እኔን ሳይነኩ ከብቶቼን ከበረት አውጡና ጠብቁ" አለቻቸው፡፡ ሰዎቹ ከብቶችን ከበረት የሚያወጡበት ዘዴ ስለጠፋባቸው ያንን አጭር ሽማግሌ ሄደው መላ ጠየቁት፡፡ ሰውየውም ሲመክራቸው "መጠጥና ምግብ ይዛችሁ ሂዱና እሷ እንዳለችው አልጋዋን በረቱ በር ላይ አድርጉት፡፡ እዚያው በልታችሁና ጠጥታችሁ ጨፍሩ፡፡ እሷም ስለማያስችላት ከእናንተ ጋር ስትጨፍር ይደክማትና ስትተኛ ቀስ ብላችሁ ከእነአልጋዋ ወደ አንድ ጎን አድርጓት፡፡ ከዚያም ከብቶችን አስወጡና በሩን መልሳችሁ ዝጉት" አሏቸው፡፡ እነርሱም እንደተባሉት አደረጉ፡፡ እሷም ጧት ስትነሳ ከብቶቹ ሳይነኳት ከበረት በመውጣታቸው ሃሳቤ ተሳካልኝ ብላ ሰዎቹ ወደቤታቸው እንዲመለሱ አደረገች፡፡

ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ደግሞ ድግስ አዘጋጅታ ህዝቡ እንዲበላና እንዲጠጣ አደረገች፡፡ ህዝቡ ከበላና ከጠጣ በኋላ "የማሳስባችሁ ነገር አለኝ" ብላ ንግግር አደረገች፡፡ "የማርፍበት

ቤት በሰማይና በምድር መካከል ስሩልኝ" አለቻቸው፡፡ አሁንም የሚያደርጉት አጥተው ተጨነቁ፡፡ የአጭሩን ሰውዬ መላ ጠየቁ፡፡ እሱም ሲመክራቸው "በልማዳችን መሰረት ምሰሶውን የሚተክለው ባለቤቱ ስለሆነ መጀመሪያ ምሰሶውን ትከይልን፤ እኛ ቤቱን እንሰራለን" በሏት አላቸው፡፡ ያ አጭሩ ሰውዬ በመከራቸው መሰረት በጧት የቤቱን መስሪያና እንጨት ተሸክመው ቤቷ ደረሱ፡፡ ለእሷም "ምሰሶውን ትከይልን ቤቱን እንሰራለን" አሏት፡፡ እሷ ግን ወዲያ ወዲህ ብትል ለመትከል ስላቃታት በጣም ተናድዳ ወደ ቤቷ ተመለሰች፡፡

ይህ ካለፈ በኋላ እንደ ልማዷ ህዝቡን እንዲሰበሰብ አደረገች፡፡ ህዝቡ ከመጣ በኋላ እንዲህ አለች፡፡ "አገሬን አይቼ ለማዳረስ ስላልቻልኩ 'በሮፋ' የሚባል የዱር እንስሳ ይዛችሁ አምጡና በኮርቻ ጫኑልኝ" አለቻቸው፡፡ ሰዎቹ አሁንም ግራ ስለተጋቡ ያንን አጭር ሰው ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው በጣም ደስ ብሎት "አሁን ችግራችሁ ሊቃለል ነው" አላቸው፡፡ "እንዴት ነው? ቢሉት "ገመድ አዘጋጅታችሁ በሮፋ የሚገኝበት ጫካ ሂዱ፡፡ ከዚያ ክበቡትና በገመዱ ጠልፋችሁ ያዙት፡፡ እሷ ባለችው ዓይነት አምጡና በኮርቻ ጫኑላት፡፡ እሷም እንዳትወድቅ በበሮፋው ላይ ግጥም አድርጋችሁ እሰሯትና ለራሳችሁ ፈረሶቻችሁን ጫኑና እጀቧት" ብለው ነገሯቸው፡፡ ሰዎቹ እንደተባሉት አድርገው አጅበዋት ሲሄዱ ሰፊ ሜዳ ያለበት አካባቢ ደርሰው ፈረሶቻቸውን ሽምጥ ጋለቡ፡፡ እሷም እንደነሱ እጋልባለሁ ብላ በሮፋውን ገረፈችው፡፡ በዚህን ጊዜ በሮፋው ፈረሶቹ በሄዱበት መንገድ ትቶ ጫካ ለጫካ ይዟት ሲሮጥ ገደል ስለገባ እሷም ገደል ገብታ ሞተች ይባላል (ሙሉጌታ ነጋሳ 1976፡89-91)፡፡

## ተረት 24

ጥንት ሁለት ወንድማማቾች ነበሩ፡፡ አንዱ ሃብታም ሌላው ድሃ ነበሩ፡፡ ድሃው ለሃብታሙ ከብት እየጠበቀ፣ እያረሰ፣ እንጨት እየፈለጠ ያገለግለው ነበር፡፡ ይህ ድርጊት በጣም አሳዝኖት ጠዋትና ማታ አምላክን ለምን በደልከኝ ብሎ ያማርረው ነበር፡፡

አንድ ቀን እሱን ድሃ አድርጎ ያኛውን ሃብታም ያደረገው ለምን እንደሆነ አምላኩን ሊጠይቀው ሄደ፡፡ በመንገዱም ላይ አምላክ በሰው ተመስሎ ታየውና የት እንደሚሄድ ጠየቀው፡፡ ድሃውም ሲመልስለት "ወንድሜን አበልጽጎ እኔን ለምን እንዳደኸየኝ አምላኬን እጠይቀዋለሁ" አለው፡፡ "አምላክህ እኔ ነኝና አሁን ከችግርህ እንድትወጣ ከሁለት አንዱን እሰጥሃለሁ ምረጥ" ብሎ ተናገረው፡፡ በዚህ ጊዜ ድሃው ደስ አለውና ምን እንደሆነ

ጠየቀው፡፡ “አንደኛው ከብትና ብር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሁሉም ፍጡር መግባቢያ ነው” ብሎ ምርጫ ሰጠው፡፡ ሰውየውም የሁሉም ፍጡር መግባቢያን መረጠ፡፡ ከዚያም አምላክ ምርጫውን ሲሰጠው “ለማንም አትናገር፤ ከተናገርክ ትሞታለህ” ብሎ አስጠነቀቀው፡፡

ይህ ድሃ ወደቤቱ ለመመለስ ሲሄድ ደክሞት ዛፍ ጥላ ስር ያርፋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለት አሞራዎች እዛፉ ላይ ሆነው ይመለከቱት ነበር፡፡ ከሁለቱ አሞራዎች መካከል አንዱ “ሰውየው ሞቷልና ሄጄ ልብላው” ሲል ለሌለኛው ተናገረ፡፡ ሌላው ደግሞ “ተው! ይይዝሃል” ብሎ ሲከለክለው እምቢ ብሎ ሰውየው ላይ መጥቶ ተቀመጠ፡፡ ሰውየው አሞራውን ቀስ ብሎ ያዝ አደረገው፡፡ በዚህ ጊዜ ዛፍ ላይ ያለው አሞራ “እባክህ ልቀቅልኝ የምትፈልገው ነገር ወዳለበት ቦታ እወስድሃለሁ” አለው፡፡ ሰውየው የሁሉንም ፍጡር መግባቢያ ተሰጥቶት ስላወቀ አሞራውን ሳይለቀው ተነሳ፡፡ ያም አሞራ ፊት ፊት እየመራው ሲሄዱ ጦርነት ተደርጎበት ብርና ወርቅ የተጣለበት ቦታ ደረሰ፡፡ እሱም አሞራውን ለቅቆ ያገኘውን ብርና ወርቅ ሰብስቦ ወደቤቱ ተመለሰ፡፡

ከዚያ በኋላ ባገኘው ብርና ወርቅ ከብቶች ገዝቶ ትዳር መሰረተ፡፡ ከብቶችም እየተራቡ ብዙ ሆነውለት የተደላደለ ኑሮ መኖር ጀመረ፡፡ እንደዚሁ ሲኖር አንድ ቀን ማታ ከሚስቱ ጋር ተኝተው ሳሉ የፍየል ወጠጤ ከጉረኖ አምባባ፡፡ አውራ ዶሮም ከቆጥ ሰምቶት “አንድ ለሚወልድ ስንቱን ያንባባል” ብሎ ታዘበው፡፡ ሰውየው የሁሉንም መግባቢያ ስለሚያውቅ ሁኔታው በጣም ገርሞት ከትከት ብሎ ሳቀ፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስቱ በጣም ተናድዳ “ምን ያስቅሃል? ንገረኝ” አለችው፡፡ ዝም ብዬ ነው የሳቅኩት ሲላት አላመነችውም፡፡ “በዚህ የተነሳ እፈታሃለሁ” አለችው፡፡ እሱም ሚስጥሩን ከተናገረ እሞታለሁ ብሎ ስለሚፈራ በጣም ተጨነቀ፡፡ በዚህም ምክንያት ከሚስቱ ጋር ሲጨቃጨቅ አደረ፡፡

እሱ በማለዳ ተነሳና “በህይወቴ ሳለሁ አንቺን ከምፈታ ምስጢሬን ነግሬሽ ብሞት ይሻለኛል፡፡ ግን ተዝካሬን ከሞትኩ በኋላ የሚያወጣልኝ ስለሌለ እንደግስ፡፡ ከዚያ በኋላ እነግርሻለሁ” አላት፡፡ ከዚያ ለተዝካሩ በሬ አርዶ እሷ ጠላ ጠምቃ ዘመዶቹ እንዲበሉ አደረገ፡፡ ላሳደገው ውሻውም ስጋ ቆርጦ ሰጠው፡፡ በዚህ ጊዜ የጎረቤት ውሻ መጥቶ “እባክህ አካፍለኝ” ብሎ ውሻውን ጠየቀው፡፡ የሱም ውሻ “ባለቤቴ ስለሚሞትብኝ ዛሬ እንኳ ልብላ፤ አልሰጥህም” ይለዋል፡፡ የጎረቤቱ ውሻም ለምን ይሞታል ብሎ ጠየቀው፡፡ ይሄም ውሻ ምክንያቱን ነገረው፡፡ በዚህ ጊዜ የጎረቤቱ ውሻ ሰውየውን ታዝቦት “ሚስት

ቢፈታ ሌላ ማግባት፣ ፈረስ ቢሞት ሌላ መግዛት የተለመደ ነውና ለዚህ ራሱን መግደል የለበትም" አለው፡፡ ሰውየውም የውሾችን ንግግር አዳምጦ ምስጢሩን ሳይነግር ያቺን ፈትቶ በተደገሰው ሌላ ሚስት አግብቶ አብረው ኖሩ ይባላል (ሙሉጌታ ነጋሳ 1976፡102-102)፡፡

## ለ. ከመስክ የተሰበሰቡ ተረቶች

### ተረት 25

በድሮ ጊዜ አንዲት የሴት ንግስት በአንድ አካባቢ ትገዛ ነበር፡፡ ንግስቲቱ በየጊዜው ችሎት ታስችል ነበር፡፡ ንግስቲቷ ካስቸጋሪነቷ የተነሳ ሊሆን የማይችል ነገር ህዝቧን ታዝ ነበር፡፡ ህዝቡም ግራ ሲገባው እቤት የዋሉ አዋቂ ሽማግሌዎችን እያማከረ ፍላጎቷን ይፈጽም ነበር፡፡ ንግስቲቷ ካስቸጋሪነቷ በተጨማሪ ብልህ ነበረችና ባገር ያሉ ሽማግሌዎችን በሙሉ እንዲያጠፏቸው አዘዘች፡፡ በትዕዛዙ መሰረት ህዝቡ ሽማግሌዎችንና ባልቴቶችን ማጥፋት ይጀምራል፡፡ በዚህ መሃል አንድ ድንክ ሽማግሌ "አትግደሉኝ፤ እጠቅማችኋለሁ" በማለታቸው ሊገኙ በማይችሉበት ቦታ ይሸሽጓቸዋል፡፡

በሌላ ቀን ህዝቡ ለችሎት እንደተሰበሰበ ንግስቲቱ "አጥፉ ያልኳችሁን በሙሉ አጠፋችሁ?" በማለት ትጠይቃለች፡፡ ህዝቡም "አዎ!" ይላል፡፡ አስከትላም "በሉ በዚህ በተከበረ አደበባይ መሃል የቅቤ ክምር እንዲከመርልኝ እፈልጋለሁና ፈጥናችሁ አድርጉ" ትላለች፡፡ ህዝቡም እሺ ብሎ በፍርሃት ወደቤቱ ይመለሳል፡፡ የሚያደርጉት ቢጠፋቸው ሸሽገው ወዳስቀመጡት ድንክ ምክር ፍለጋ ይሄዳሉ፡፡ ድንኩ ሽማግሌም "በሉ እሺ በሏት፡፡ ነገር ግን የቅቤውን ክምር ስንከምር ጸሃዩ እንዳያቀልጥብን እርስዎ በንግስትነትዎ ጸሃይዋ እንዳትወጣ ያስቁሙልን በሏት" አሏቸው፡፡ ህዝቡም እንደተመከረው አደረገ፡፡ ንግስቲቱም ይህንን ስትሰማ "አዛውንቶችን ጨርሳችሁ አላጠፋችሁም ማለት ነው፡፡ በሉ ሌላ ትሰራላችሁ፤ እሱም የዱቄት ክምር እንድትከምሩ ይሁን" አለቻቸው፡፡ ህዝቡም እንደተለመደው እሺ ብሎ ወደ አማካሪያቸው ዘንድ በድብቅ ይሄዳል፡፡ አማካሪውም ጉዳዩ እንደተነገራቸው "እሺ በሏት፡፡ ነገር ግን ነፋሱ ክምራችንን ይበትንብናልና በንግስትነትዎ ነፋሱን ይያዙልን በሏት" በማለት ምክራቸውን ይለግሳሉ፡፡ አሁንም ህዝቡ እንደቀደመው መልሳቸውን ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ንግስቲቷ አንድ ሳይገደል የቀረ መካሪ ሽማግሌ መኖሩን ታረጋግጣለች፡፡

ንግስቲቱ አስቸጋሪ ትዕዛዟን ትቀጥላለች፡፡ ህዝቡ በሙሉ እንደተሰበሰበ " እዚህ ከእናንተ ጋር መኖር ሰልችቶኛል፡፡ በዚያ ላይ ሁላችሁንም ልቆጣጠራችሁ አልተመቸኝም፡፡ ስለዚህ በሰማይና በመሬት መሃል ቤተመንግስቴን ስሩልኝ" በማለት ትዕዛዟን ታስተላልፋለች፡፡ ይህን ጊዜ ህዝቡ ከባድ ጭንቅ ውስጥ ይገባል፡፡ እንደተለመደው ወደ አማካሪያቸው ይሄዳሉ፡፡ ሽማግሌውም "የሚያስፈልገውን የቤት መስሪያ እንጨት ይዛችሁ ቅረቡ፡፡ ከዚያም ባገራችን ደንብ መሰረት ቤት ሲሰራ ምሰሶውን የሚያቆመው ባለቤቱ ነውና ምሰሶውን አቁሚልን በሏት" ይሏቸዋል፡፡ ንግስቲቱ ይህንን ስትሰማ በተደበቀው ሽማግሌ መሸነፏን አምና የመጨረሻ ትዕዛዝ ትሰጣለች፡፡ ይህም አጋዘን ከዱር ይዘው በበቅሎ እቃ ጭነው እንዲያመጡላት ነበር፡፡ ይህንኑ ትዕዛዝ ሽማግሌው እንደሰሙ "አሁን መገላገያችሁ ደርሷል፡፡ በመጀመሪያ ከየቤታችሁ ድር ታዋጡና አንድ ላይ በረጅሙ ትፈትሉታላችሁ፡፡ ከዚያም አንድ መሹለኪያ ብቻ ባለበት ቦታ በርከት ያለ ሰው ታስቀምጡና አጋዘኑን ወደዚያው አቅጣጫ ታባርሩታላችሁ፡፡ ከዚያም እንደታዘዛችሁት በበቅሎ እቃ ጭናችሁ ትወስዱላታላችሁ፡፡ እንደወሰዳችሁላት እስኪ ውጡበት ማለቷ አይቀርም፡፡ ይህን ጊዜ የተከበሩ ንግስታችን መቀመጫ ላይ እንዴት እኛ እንቀመጣለን በሏት" ብለው ይመክሯቸዋል፡፡ ህዝቡ በተባለው መሰረት ሁሉንም ፈጽሞ ንግስቲቱ ዘንድ ይቀርባሉ፡፡ እሷም ሽማግሌው እንዳሉት "እስኪ ውጡበት" ትላለች፡፡ ህዝቡም "ንግስታችን መቀመጫ ላይ አይሆንም" ይላል፡፡ ንግስቲቱ ይህን ጊዜ "ይሄ ህዝብ አይቻልም" ትልና "አጋዘኑ ላይ አውጡኝ" ትላለች፤ ያወጧታል፡፡ አጋዘኑም የዱር አውሬ ነውና ይዟት ይበረግጋል፡፡ የት እንደጣላትም ሳይታወቅ ይቀራል፡፡ ከዚያን ጊዜ በኋላ ባገሩ ሴት ነግሳ አታውቅም፡፡ ህዝቡ ይኖርበት የነበረው አገር አይቻል፣ አጋዘኑ የተያዘበት ቦታ አጋዘን በር፣ አጋዘኑ ሲሮጥ ያስነሳው አቧራ ታይቶ አቧራ፣ ነጠላዋ የተገኘበት ቦታ ኩታበር፣ ግራ እግሯ የተገኘበት ግራኝ ሜዳ፣ እጇ የተገኘበት የጁ፣ የአጋዘኑ ልጓም የተገኘበት ልጓማ፣ እራሷ የተገኘበት ቦታ ራሳ የሚሉ የቦታ ስያሜዎች እንደተሰጡ ይነገራል፡፡ (ምስጋናው አቢነው፣ ጌታቸው ጉግሳ፣ ደሳለኝ አያሌው፣ አሳምነው አያሌው፣ ቦረና ወረዳ፣ ነሐሴ 2007)

## ተረት 26

ጥንት ዱሮ ገና ሴትና ወንድ እንደተፈጠሩ ፈጣሪ የሴትንና የወንድን ስሜት ለማወቅ ፈልጎ ሙከራውን በሴትና በወንድ ፈረስ አደረገ አሉ፡፡ ፈጣሪ ከፍተኛ የመጠቃቃት ፍላጎት ያላቸውን (የሻፈዱ) ሴትና ወንድ ፈረሶችን አመጣ አሉ፡፡ ሁለቱንም ጥልቅ ገደል

ካለበት አካባቢ ይወስዳቸዋል፡፡ ከዚያም ወንዱን ከገደል አፋፍ፣ ሴቷን ከገደሉ ስር ያደርግና ወንዱ ሊሰማት በሚችል መልኩ ሴቷ ፈረስ እንድትጮህ ትደረጋለች፡፡ ይህንን ጊዜ ድምጿን የሰማው ፈረስ ወደ ገደሉ አፋፍ ብቅ ብሎ ሴቷን እንዳየ የአጸፋ መልሱን አስካክቶ ወደ ኋላ ይመለሳል፡፡

በተቃራኒው ሴቷን ፈረስ ከገደሉ አፋፍ፣ ወንዱን ከገደሉ ስር ሆነው ወንዱ እንዲያስካካ ይደረጋል፡፡ ድምጹን የሰማችው ሴት ፈረስ ወደ ገደሉ አፋፍ ብቅ ብላ ከገደሉ ስር ስታየው ስሜቷን መቆጣጣር አቅቷት ወደ እሱ ለመድረስ ስትል ገደሉ ውስጥ ዘልላ በመግባቷ ለሞት ተዳረገች፡፡ ይህንን የተመለከተው ፈጣሪም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ድፍረትን ለወንድ፣ ሃፍረትን ለሴት ሰጠ ይባላል፡፡ (ጌታቸው ጉግሳ፣ ቦረና ነሀሴ 2007)

## ተረት 27

በጥንት ጊዜ በአንድ አገር ውስጥ አንድ ዝንጀሮ ከሚስቱ እና ከልጆቹ ጋር ይኖር ነበር አሉ፡፡ ሲኖሩ ሚስትዮዋ የባቄላ ዘር እየቃረመች ታጠራቅም ነበር አሉ፡፡ ባሏ ግን ከመብላት ሌላ አያውቅም ነበር አሉ፡፡ እናም ክረምት ሲመጣ ሌላው እያረሰ ባቄላና ሌላውን ሰብል ሲዘራ እሱ ግን ዝም ብሎ ቁጭ ይላል፡፡ ይህን ጊዜ ሚስት "እባክህ ሁልጊዜ ድህነት ከሚይዘን እረስና ሰብል እናሲዝ" ስትለው "ዘር የት ይገኛል?" ይላታል፡፡ ከዚያም እሷ ዘሩን አስቀምጫለሁ አለችና ሰጠችው፡፡ እሱም ዘሩን ተቀበለና እሩቅ ቦታ ሂዶ ያንን የባቄላ ዘር ቆርጥሞ ተመለሰ፡፡ ከዚያም ማታ "ዘርተህ መጣህ?" ብላ ሚስቱ ስትጠይቀው "አዎ! ዘርቼ መጣሁ፡፡ በጣም ደክሞኛል" ብሎ ያልሰራውን እንደሰራ ተናገረ፡፡ ሚስቱም እግሩን አጥባ ተንከባከበችው፡፡ የአረም ጊዜ ሲደርስ ሚስት "ከቤተሰባችን ጋር ሄደን አረም እንረም" ስትል ባል አልዘራምና እንዳይታይበት "ምንም አረም የለውም፡፡ ጥሩ አድርጌ ነው ያረስኩት" አለ፡፡

እሸቱ ሲደርስ ደግሞ "አሳያቸውና ልጆቹ ያምጡ፤ እኛም እናምጣ" አለችው፡፡ ባልም "የመኸር ድሃ የለውም፡፡ ከሌላ እናምጣ፤ የእኛ ይቆጠብ" አለ፡፡ እንዲህ እያለ በአካባቢው ያለው ሰብል ደርቆ ሲሰበሰብ "ኸረ የእኛ ምን ደርሷል? እንሂድና እንስበር" አለች፡፡ ባልም ማታለል አልቻለምና "ሁላችንም ቤተሰብ እንሂድ" ብሎ ጅሬውን ይዞ ወጣና ከሰው ባቄላ ገቡ፡፡ ባለቤቱም አባረራቸው፡፡ እንደገና ከሌላ ሰብል ገቡ፤ አሱም አባረራቸው፡፡ እንደዚህ እየሆኑ መንከራተታቸውን የጠላችው ሚስት "ለመሆኑ የእኛ የትኛው ነው? እንዲህ መድረሻ ያጣሁት?" ብላ በድጋሚ ጠየቀችው፡፡ እሱም የሰራው በሙሉ ስህተት መሆኑን

ባለማገናዘብ በድጋሚ “አይ! በጉልበት ሲቀሙን አታውቂም? እንግዳ ይህ ዓይንሽ የሚያየው የባቄላ ሰብል በሙሉ የእኛ ነበር” አለ ይባላል (ሰይድ አህመድ ዓሊ፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)፡፡

**ተረት 28**

በድሮ ጊዜ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ባልና ሚስቱ አብረው ሲኖሩ ባልዮው ሚስቱ ስላረጀችበት ሌላ ሚስት ፍለጋ ውጭ ማደር ጀመረ፡፡ ምሳውንም እራቱንም ውጭ መብላት ጀመረ፡፡ ሚስቱም ይህ ሰው ቀረሳ እያለች ቁጭ ብላ ታድራለች፡፡ አንድ ቀን ወደ መንደር ሄዳ ባሏ የት እንደሚቆይ ጠየቀች፡፡ ሰዎችም የት እንደሚውል የት እንደሚያድር ነገሯት፡፡ ከዚህ በኋላ እቤቷ ሄዳ ብዙ አሰበች፡፡ ያዋጣኛል ያለችውን መላ ዘየደች፡፡

በቤቷ ውስጥ ሁለት ዓይነት ወጥ ሰራች፡፡ አንደኛው የተልባ ሲሆን ሁለተኛው የዶሮ ነበር፡፡ ባሏ ከመምጣቱ በፊት የተልባ ወጥ የያዘውን ድስት በአዲስ ጨርቅ፣ የዶሮ ወጥ የያዘውን ድስት በአሮጌ ጨርቅ ሸፈነቻቸው፡፡ ከዚያም ድስቶችን ለባሏ በሚታይ ቦታ አስቀመጠቻቸውና በትዕግስት መጠባበቅ ጀመረች፡፡

ባሏ እንደመጣ እጁን አስታጥባ እንጀራ በሞሰብ አቀረበችለትና “ከየትኛው ድስት ወጥ ልጨልፍልህ?” ስትል ጠየቀችው፡፡ እርሱም በንጹህ ጨርቅ ከተሸፈነው ድስት እንድትጨምረለት አዘዛት፡፡ እርሷም እንደታዘዘችው አደረገች፡፡ ሆኖም ወጡን ሲያየው የማይረባ የተልባ ወጥ ነበር፡፡ ወጡ ያላስደሰተው ባል “ያኛውስ ምንድን ነው?” ብሎ ሲጠይቃት አምጥታ አሳየችው፡፡ ቢያየው የዶሮ ወጥ ሆኖ አገኘው፡፡ ከዚያም ነገሩን ሁሉ አሰበውና “አሃ! ካሮጌም ጥቅም አለ!” ብሎ ወደ መጀመሪያ ሚስቱ ተመለሰ ይባላል (መሃመድ ሁሴን፣ጌታቸው መላኩ፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)፡፡

**ተረት 29**

በድሮ ጊዜ በአንድ አገር አባትና ልጅ አብረው ይኖሩ ነበር አሉ፡፡ ልጁም አባቱን በጥሩ ሁኔታ እየተንከባከበ ይጦረው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ አባት ልጁን በጣም ይወደው ነበር፡፡ አባት ለልጁ ውለታ የሚያወርሰው ሃብት ባይኖረውም “ልጄ! የሴትን መላ፣ የጉንዳንን ጉልበት ይስጥህ” እያለ ሁልጊዜ ይመርቀው ነበር፡፡ ልጁ ግን አባቴ ረገመኝ ብሎ አባቱን ጥሎ ወደ ሌላ ሃገር ተሰደደ፡፡ በመንገድ ላይ ግን አንድ ከብት የሚጠብቅ ትልቅ ሰው

ያገኘዋል፡፡ ሰውየውም "አንተ ልጅ! የት እየሄድክ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል፡፡ ልጅም "አባቴ ስለረገመኝ ወደ ሌላ አገር እየተሰደድኩ ነው" ብሎ ይመልስለታል፡፡ ያ ትልቅ ሰውም ከእኔ ጋር ተቀመጥ ብሎ ከእርሱ ጋር ያደርገዋል፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ያ ትልቅ ሰው ልጁን አስከትሎ የጉንዳን መንጋ ወዳለበት ቦታ ይወስደውና አንዲት ጉንዳን ከእሷ መጠን በላይ የሆነ ምግብ ተሸክማ ስትጓዝ ያሳየዋል፡፡ በተጨማሪም የሞተችዋን ጉንዳን ያልሞተችዋ ተሸክማት ወደ ጉርጓዷ ስትወስዳት ያያል፡፡ ያ ትልቅ ሰው ለልጁ አባቱ እንዳልረገመው ከነገረው በኋላ እንደገና የሴትን መላ ሊያሳየው ወደ ቤት ይወስደዋል፡፡ እቤትም ቁጭ እንዳሉ ሚስትዮዋ ወደ ጓዳ ስትገባ "አሁን ወደ ጓዳ ትገባና የጠላውን ገንቦ ያያዝክላት መስለህ በደንብ ትቆነጥጣታለህ፡፡ ከዚያ በኋላ የሚሆነውን ታያለህ" ይለዋል፡፡ ልጁም እንደታዘዘው ወደ ጓዳ ይገባና ገንቦውን የያዘ መስሎ ይቆነጥጣታል፡፡ ይህንን ጊዜ ሴትዮዋ ትጮሃለች፡፡ ባልም ነገሩን እንዳላወቀ ተንደርድሮ ወደ ጓዳ በመግባት "ምን ሆንሽ" ይላታል፡፡ እሷም "ከገንቦው ስር አይጥ ድንገት ሹልክ ብላ ስትሄድ አይቼ ደንግጨ ነው" ትለዋለች፡፡ ይህን ጊዜ ልጁ የሴትዮዋን መላ ተመልክቶ አባቱ ያልረገመው መሆኑን በማረጋገጡ ያንን ትልቅ ሰው አመስግኖ ወደ አባቱ ቤት ተመለሰ ይባላል (መዝገቡ ሰጠኝ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

## ተረት 30

በድሮ ጊዜ ባልና ሚስት ነበሩ አሉ፡፡ ለብዙ ዘመናት አብረው ሲኖሩ አንድ ጊዜ ባልዮው ወደ ሌላ አገር ለስራ ለመሄድ ተነሳ፡፡ ሚስትም አርፋ የማትቀመጥ ቢጤ ናትና ምን አድርጓት እንደሚሄድ ተቸግሮ ሲያስብ ቆዩ፡፡ በመጨረሻም ብልቷን በክር መስፋት የተሻለ ነው ብሎ በማሰብ ይህንኑ አደረገ፡፡ ለእርሷም "እንግዲህ ሚስቴ ሆይ! ብልትሽን እንደሰፋሁት ስመጣ እንደነበረ ማግኜት አለብኝ" ብሎ አስጠነቀቃት፡፡ ሚስትም "ምንም ችግር የለም፡፡ እንዳኖርከው አደርጌ እጠብቅሃለሁ" አለችው፡፡ ባልም ካሰበበት አገር ደርሶ ጉዳዩን ፈጽሞ በሰላምና በደስታ ወዳገሩ ተመለሰ፡፡ ቤተሰቦቹና ጎረቤቶቹ በጨዋታና በእልልታ ተቀበሉት፡፡ እየተበላና እየተጠጣ ብዙ አመሹ፡፡ ሌሊቱ ሲጋመስ ሁሉም ወደየቤቱ ሲሄድና ልጆቹ ሲተኙ "ያ ነገርሳ እንደምን ሆነ?" በማለት ባል ይጠይቃል፡፡ ሚስትም "እርስዎ በሰላም በመምጣትዎ ተደስቼ እልል ስል ተተረተር" በማለት መለሰችለት ይባላል (መሃመድ አሰን፣ ተሁለደሬ፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 31

በድሮ ጊዜ ሁለት ድሃ ባልና ሚስት ነበሩ። በቤታቸው ውስጥ ያለው አንድ ቦራ በሬ ብቻ ነበር። ባል በሬ ነጋዴ ነበር። ከእለታት አንድ ቀን ሚስቱን "ገበያ ልሄድ ነው ስንቄን ሰንቂልኝ" አላት። እሷም ስንቁን በአገልግል አድርጋ ሸኘችው። እሱም ሄደኩኝ ካለ በኋላ በማይታይበት ቦታ ተደብቆ የሚስቱን ሁኔታ መከታተል ጀመረ። እሷም ቀደም ያለ ውሽማ ነበራትና "ባሌ ዛሬ ስለሌለ ማታ እንድትመጣ" ብላ ቀጠረችው። ለውሽማዋ ማስተናገጃ የሚሆንም ዶሮ አርዳ አዘጋጀች። አመሻሽ ላይ ባል ከገበያ የተመለሰ መስሎ ከተደበቀበት ወጥቶ ውሽማ ከመምጣቱ በፊት ወደ ቤቱ መጣ። ሚስትም ለውሽማዋ የሰራችውን ዶሮ ለባሏ አቀረበችለት። ይህንን ጊዜ ባል "ከየት አመጣሻት?" ብሎ ሲጠይቃት "እከሌ ወፍ ሲጠብቅ በወንጭፍ መትቶብኝ አሳርጃት ነው" ብላ መለሰችለት። ባል እራቱን እየበላ እንዳለ ውሽማ በር አንኳኳ። እሷም "የበሬውን ድርቆ ልሰብስብለት" ብላ ወደ ጋጥ ገብታ ለውሽማዋ፦

ተው ቦራ ተው ቦራ አታፍርሰው ቤቱን፣
ከገበያ መጥቶ ይበላል እራቱን።

አለችው። የዚህን ጊዜ ውሽማ ባል መምጣቱን ስላወቀ ተመለሰ። ባል ነገሩ ስለገባው ነይ ወጥ አድርጊልኝ አላት። እሷም ወጥ ስታደርግለት፦

እኛም እናውቃለን የነገር ሸውራራ፣
ቀን ካልተቀጠረ መች ይመጣል ቦራ።

ብሎ ገደላት ይባላል። (ጫኔ ሰይድ፣ ኩታበር፣ ነሐሴ 2007)።

## ተረት 32

ባልና ሚስት ነበሩ አሉ። ሚስት ሌላ ውሽማ ነበራትና ከእሱው ጋር ለመገናኘት የተለያዩ ዘዴዎችን ትፈጥራለች። አንድ ቀን አሞኛል ብላ ጥቅልል ብላ ትተኛና ባሏን ለመድሃኒት የሚሆን "የጉም ተገድራ "ፈልገህ አምጣልኝ ብላ ወደ ሩቅ አገር ትልከዋለች። ባሏም የዋህ ነበርና ስንቁን ይዞ ፍለጋ ይሄዳል። ታዲያ ይህንን ጊዜ ሚስት ከውሽማዋ ጋር በቤቷ ውስጥ ፍቅራቸውን ይፈጽማሉ። ባል መድሃኒቱን ፍለጋ አገር ለአገር ይንከራተታል። ብዙ ሲደክምና የማይገኝ ነገር ሲፈልግ የተመለከተ አንድ የቆሎ ተማሪ "ምን ሆነህ ነው?" ብሎ ይጠይቀዋል። ባልም "ሚስቴ ታማብኝ የጉም ተገድራ እየፈለግኩ ነው" ይለዋል። የቆሎ ተማሪው ሚስጥሩ ገብቶታልና ሁለት ልምጭ ቆርጦ

በመስጠት አጠቃቀሙን ጭምር ያሳየዋል፡፡ አንደኛው ሰውን ወደ ዝንጀሮ የሚቀይር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ዝንጀሮን ወደ ሰው የሚቀይር ነበር፡፡

አቶ ባል እንደተነገረው በልምጩ ሚስቱን ወደ ዝንጀሮ ይቀይራታል፡፡ አስከትሎም ከዝንጀሮነት ወደ ሰውነት በሌለኛው ልምጭ ይቀይራታል፡፡ በዚህ ሚስት በጣም ትደነቃለች፡፡ ለውሽማዋም ለማሳየት በጣም ትቸኩላለች፡፡ ባል እንደተመከረው ወደ ዝንጀሮ የምትቀይረዋን ልምጭ ከቤት አስቀምጦ ወደ ሰው የምትቀይረዋን ወደ እርሻ ቦታ ይዟት ሄደ፡፡

ውሽሜ እንደለመደው የባልን እግር ጠብቆ ወደ ቤት ይገባል፡፡ ሚስት ሆዬ የልምጩን ገድል ለውሽማዋ ለማሳየት ቸኩላለችና "ትናንትና የእኔ ባል ያመጣውን ጉድ ላሳይህ" አለችና በዚያች በልምጭ ነካ ስታደርገው በአንድ ጊዜ ውሽሜ ግመሬ ዝንጀሮ ሆነ፡፡ ዝንጀሮ ሆዬ እንደዘመዶቹ ከቤት ወጥቶ ካብ ላይ ቁጢጥ አለ፡፡ በዚያው በልምጭ እየደጋገመች ብትመታው ሰው ሊሆን አልቻለም፡፡ ዝንጀሮውን ያየ የሰፈር ሰው እየተጯጯኸ ማሳደድ ይጀምራል፡፡ እየተከታተሉ በውሻ ሲያባርሩት ሚስትም ማንነቱን ስለምታውቅ "ኧረ ተው አቶ ይመሬ ናቸው" ትላለች፡፡ ባልም "ግመሬ ነው በሉት ትላችኂለች" በማለት ውሻውን "ያዝ ጉንዴ እንዲህ ነዶ ሆዴ!" በማለት እንዲህ አድርጎ የሚስቱን ውሽማ ገደለ ይባላል (ገለታው ወርቁ፣ ቦረና፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 33

በድሮ ጊዜ አንዲት እናት ከልጇ ጋር እየተጦረች ትኖር ነበር፡፡ የልጇ ሚስት ምራቷ ግን እያስራበቻት ትቸገር ነበር፡፡ እናት ረሃቡ ስለጠናባት "ዛሬስ ሆዱን ሙሉ በልቶ የሞተ ሰው አስቀናኝ" እያሉ ያማርሩ ገቡ፡፡ እንዲህ እንዲህ እያሉ አንድ ቀን ከምራታቸው ጋር ሲያወሩ ረሃቡ ስለጠናባቸው "ሆዴ እስኪሞላ ድረስ ብበላ እሞት ነበር" እያሉ አወሯት፡፡ ምራቷም ሆድዎ እስኪሞላ ድረስ ቢበሉ ይሞታሉ?" ስትላቸው "አዎ እሞታሁ!" በማለት መለሱላት፡፡

ከልጃቸው ቤት ሞልቶ ተርፎ ስለራባቸው ተንኮል አሰቡና "ልሞት ነው" አሏት፡፡ እሷም እንደተባለችው ጥሩ ወጥ ሰርታ በእርጎ ፈተፍታ ሰጠቻቸው፡፡ እሳቸውም እስከሚጠግቡ ተመገቡ፡፡ በመጨረሻም "ገመድ አምጪና ሙቀጫ ቀጥለሽ ቁመሽ መታነቂያ አዘጋጅልኝ" አሏት፡፡ እሷም አዘጋጀች፡፡ በመጨሻም በደንብ አዘጋጂ ሲሏት አንገቷን ገመዱ ውስጥ አስገብታ "እንዲህ ብለሁ" እያለች ስታሳይ የቆመችበትን ሙቀጫ ገፉት፡፡

ገመዱም አንቋት ሞተች፡፡ ልጁም ከዱር ውሎ ማታ ወደ ቤት ሲገባ "የት ሄደች?" ሲላቸው "ግባና እያት ስትወዛወዝ ነበር" አሉት ይባላል (አህመደ እብራሂም፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡

**ተረት 34**

በድሮ ጊዜ በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ሁለት ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባልዮው ቆላ ልሄድ ነው ብሎ ሚስቱን ስንቅ ጋግሪልኝ ይላታል፡፡ በዚያን ጊዜ "ውሃ ላምጣና እጋግርልሃለሁ" ብላ ውሃ ልትቀዳ ወደ ወንዝ ወረደች፡፡ በዚያን ጊዜ ውሽማዋን ወንዝ ገላውን እየታጠበ ታገኘዋለች፡፡ ስታገኘውም ደስ ብሏት "ዛሬ ባሌ ቆላ ሊወርድ ስለሆነ ማታ እንዲትመጣ" ትለዋለች፡፡ ከዚያ በኋላ ውሃዋን ቀድታ እቤቷ እንደገባች ለባሏ ስንቁን ጋግራ ቆላ ትሰደዋለች፡፡ ከዚያም ማታ ውሽማዋ መጥቶ ተኝተው እንዳለ ባልዮው በመንገዱ ላይ ጥቁር ሰው አግኝቻለሁና መንገዴ አይቀናኝም በማለት ወደቤቱ በድንገት ተመልሶ ይመጣል፡፡ በዚያች ሰዓት ውሽሜ ደንግጦ እርቃኑን እፍየሎች ጉረኖ ገብቶ እንደፍየሎቹ አጎንብሶ ይቆማል፡፡ ባል አይቶታልና ተከታትሎ ገብቶ ከኂላው ቆለጡን ይይዘውና ሚስቱን ቢለዋ አምጭልኝ ሲላት ውሽቷን "ቢለዋውን አጣሁት" ትለዋለች፡፡ ከዚያም ባልዮው ይናደድና "ነይ ያዢልን! እኔ እፈልገዋለሁ" ይላታል፡፡ ውሽሜ ሆዬ "አንተ ሙክት ምጥቻ ሁነኝ" እያለ ሲጸልይ ነበርና ልመናው ደርሶለት ባል ቢለዋ ፍለጋ ይሄዳል፡፡ ሚስት ያዢ የተባለችውን ስትይዝ የውሽማዋ ቆለጥ ሆኖ ታገኘዋለች፡፡ ይህንን ጊዜ የውሽማዋን ቆለጥ ትለቅና የፍየሉን ትይዛለች፡፡ ባሏ ቢለዋውን ይዞ ሲመጣ የፍየሉን ቆለጥ ታስጨብጠዋለች፡፡ ባል በንደት እንደመጣ የፍየሉን ቆለጥ ላፍ አድርጎ ሲጥለው ፍየል ጨኸቱን ይለቀዋል፡፡ በዚህ ጊዜ ሚስት "አንተ እኔን አታምነኝም፡፡ ባለማመንህ ፍየልህን ገደልክ፡፡ በል አሁን ፍየሉ አይድንምና እረደው" ብላ በመላ ውሽማዋን ከሞት ታድነዋለች፡፡ በኋላ ሚስት "ሙክቱ ከታረደ አይቀር ወጥ ልስራና ጎረቤቶቻችንን እንጋብዝ" በማለት ባሏን ታማክራለች፡፡ ባልም ይስማማል፡፡ ከጉድ የወጣው ውሽማ ጎረቤት ነበርና ግብዣው ላይ ይጠራል፡፡ ምግቡ ቀርቦ እየበሉ እንዳለ ሚስት "ወጡ እንዴት ነው?" ብላ ስትጠይቅ ውሽሜ ተሽቀዳድሞ "በጣም ጥሩ ነው፡፡ ከወጥሽ አወጣጥሽ እንደ እግዝትነ ማርያም ነው" ብሎ አደነቃት ይባላል (አግማስ መቆያ፣ ኩታበር፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 35

አንድ ሽማግሌ ከአንዲት ቆንጆና ብልህ ልጃቸው ጋር ይኖሩ ነበር አሉ፡፡ ሽማግሌው እጅግ ቅንና አዛኝ ነበሩ አሉ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ሽማግሌው ገበያ ውለው ሲመለሱ ከቤታቸው አቅራቢያ ካለ ዳገት መካከል ላይ አንድ ወጣት ተቀምጦ ያገኛሉ፡፡ እሳቸውም "እንደምን ዋልክ ልጄ?" ይሉታል፡፡ ልጅ አጸፋውን "እግዚአብሔር ይመስገን!" ይላል፡፡ ኋላ "ምን ሆነህ ነው በምሽት ቁጭ ያልከው?" ይሉታል፡፡ እሱም "ደክሞኝ ነው አባቴ! መቼም የድሮ ሰዎች ጠንካሮች ናችሁ፤ እባክዎ ይህንን ተራራ አዝለው ያውጡኝ! ጅብ ሊበላኝ ነው" ይላቸዋል፡፡ እሳቸውም ሆዳቸው አልችል ብሎ በዚያ ረጅም አቀበት ያንን ጎረምሳ አዝለው አፋፉ ያደርሱታል፡፡ ልጁም ሽማግሌውን ካመሰገነ በኋላ ተለያዩ፡፡

ሽማግሌው እቤታቸው እንደደረሱ ደክሟቸው ላብ በላብ ሆነው ልጃቸው ተመለከተች፡፡ "ምን ሆነህ ነው አባቴ እንደዚህ የደከምከው?" አለችና ጠየቀችው፡፡ አባትም "አንድ ወጣት ልጅ ደክሞት ካቀበቱ መግቢያ ላይ አግኝቸው 'ደክሞኝ ነው እባክዎትን ጅብ ከሚበላኝ አዝለው አቀበቱን ያውጡኝ' ቢለኝ እኔም ጅብ ከሚበላው ብዬ አዝዬ አውጥቸው ነው የደከመኝ" ሲሉ መለሱላት፡፡ ልጅትም ብልህ ናትና "አይ አባቴ! አዝለህ አውጣኝ ያለህ እኮ የዱሮውን እርስቱን፣ ጉልቱን፣ ይዞታውንና የዱሮ ታሪክ እያወራህ አውጣኝ ሲል ነው እንጂ መቼ እንደዚህ ነበር" አለቻቸው፡፡ አባትም "መቼ እንዲህ መሆኑን አወቅኩ ልጄ!" አሉ፡፡

በሌላ ጊዜ ሽማግሌው እንደተለመደው ገበያ ውለው ሲመለሱ ያው ወጣት ቀደም ብለው ያገኙበት ቦታ ተቀምጦ አገኙት፡፡ ልጁ ፈጥኖ "አባቴ ከየት መጡ? ይሄው ዛሬም ደክሜ ተቀምጫለሁ፡፡ እንደልምድዎ አዝለው ያውጡኝ" አላቸው፡፡ እሳቸውም "እሺ ልጄ!" አሉና ካስነሱት በኋላ "ያ የምታየው የእኛ እርስት ነበር፡፡ ያ በጥግ የምታየው ደግሞ የእነ ፊታውራሪ እገሌ እርስት ነበር፡፡ ይሄ የምተየው ተራራ በደን የተሸፈነ ነበር፤ የሽፍታም መነሃሪያ ነበር፡፡ ባሻጋሪው የምታየው ተራራ ላይ ደግሞ ታቦት ነበር ይባላል፡፡ አንዳንድ አባቶች እንዲያውም ዶሮ ጬኸት ላይ የደወልና የከበሮ ድምጽ ይሰማል ይላሉ" ወዘተ. እያሉ ቆም ሄድ እያሉ ተያይዘው አቀበቱን ይወጣሉ፡፡ አፋፉ ላይ እንዳረፉ "አባቴ!" አለ ልጁ፡፡ "አቤት!" አሉት ሽማግሌውም፡፡ "ይህንን መላ ማን ነገረዎት?" አላቸው፡፡ "ሴት ልጅ አለችኝ፡፡ የዛን እለት ምን ሆነህ ደከመህ ብትለኝ አንድ የደከመው ልጅ እዝለኝና ዳገቱን አውጣኝ ብሎኝ አዝዬ አውጥቼ ነው" ብላት "አዬ አባቴ! ዳገቱን ዝግ አድርገህ አውጣኝ ማለቱ ነው" ብላኝ ነው አሉ፡፡

ልጁ ይህንን ጊዜ ልጅዎ "አግብታች?" ብሎ ጠየቀ፡፡ አባት "ኧረ አላገባችም" አሉ፡፡ ልጁ "ለእኔ ይስጡኝ" አለ፡፡ አባትም "ምን ቸገረህ" አሉት፡፡ ልጁ ሽማግሌ ልኮ ካስለመነ በኋላ ሰርጉ ተደግሶ ሙሽራው ከነሚዜው ምግብ ወደሚበላበት ዳስ እንደገቡ አንበላም አንጠጣም አሉ፡፡ ለምን ተብለው ቢጠየቁ "ሙሽራዋ ጋልባት የምትሄደው በቅሎ ጸጉሯ ስንት እንደሆነ ይነገረን፤ አለበለዚያ 30 ጠገራ ብር ይሰጠን" በማለት ጠየቁ፡፡ ሽማግሌው የልጂቷን ብልሃት ያውቃሉና እሷን አማክሩልኝ አሉ፡፡ ከማጀት ገብተው እንደዚህ ተባለ ቢሏት "ብሩን ስጧቸው" አለቻቸው፡፡ ሰርገኞቹ 30 ጠገራ ብራቸውን ተቀብለው፤ በልተው ጠጥተው ሙሽራዋን ይዘው ጉዟቸውን ወዳገራቸው አደረጉ፡፡ ከአንድ ሰፊ ጫካ እንደደረሱ ሙሽራይቱ "ሆዴን አመመኝ! ሽንቴ መጣ! በማለቷ ከበቅሎ አወረዷት፡፡ ከዚያ በኋላ ከተቀመጠችበት አልነሳም አለች፡፡ ምነው ቢሏት "ይሄ ጫካ ተመንጥሮ፣ ታርሶ፣ ሽምብራ ተዘርቶ፣ አብቦ፣ አፍርቶ፣ እሸት ሳልበላ አልሄድም" አለች፡፡ "ባንድ ቀን እንዴት ይቻላል?" ቢሏት "የበቅሎ ጠጉር እንግዳ እንዴት ይቆጠራል? ወይ የሽንብራ እሸት አምጡ፤ ወይ 60 ጠገራ ብር አምጡ" አለች፡፡ ሰርገኞችም ተሳስቀው 60 ጠገራ ብራቸውን ሰጥተው አገራቸው ገቡ፡፡ ልጂትም የአባትና የእናቷን ገንዘብ በእጥፍ አስመለሰች ይባላል (ተስፋዬ ጌታሁን፣ ቦረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

**ተረት 36**

በድሮ ጊዜ ሁለት ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ሰውየው ከፊል ዓይነ ስውር በመሆኑ ለብዙ ጊዜ አልጋ ላይ ተኝቶ ይኖር ነበር፡፡ ሴትዮዋ በህመሙ ሰልችታ በብዙ ታማርር ነበር፡፡ አንድ ቀን ባሏን በመርዝ መግደል አሰበችና ለምሳው የሚሆነውን እንጀራውን በሌማት፣ ወጡን በድስት፣ ጠላውን በገንቦ ካደረገች በኋላ እምግቡ ላይ መርዝ ጨምራበት አሳይታው ወደ ገበያ ሄደች፡፡ ባልዮው ትንሽ ትንሽ ያይ ነበርና ስራዋን ሁሉ ይመለከት ነበር፡፡

ያን እለት የሴትዮዋ 3 ወንድሞች ወደ ኋላ የቀረ የእህታቸውን አዝመራ ለመሰብሰብ ተቃጥረው ነበርና ሲያጭዱ ውለው እንደጨረሱ እህታቸው ከገበያ ሳትመለስ ወደ ቤት ይሄዳሉ፡፡ እቤት እንደደረሱም ያ ዓይነስውር አማቻቸው "እህታችሁ እንጀራውን በሌማት፣ ወጡን በድስት እና ጠላውን በገንቦ አስቀምጣላችኋለችና ብሉ ጠጡ" ይላቸዋል፡፡ እነርሱም ሲሰሩ በመዋላቸው እርቧቸዋልና ያንን ምግብና መጠጥ ከነመርዙ ግጥም አድርገው ይበላሉ፤ ሁሉም በያሉበት ፍንግል ፍንግል ብለው እህታቸው ታገኛቸዋለች፡፡ እሪታዋን ካቀለጠችው በኋላ "አንተ ትበላለህ ብዬ ነው እንጂ እንዲህ

አድርገህ ወንድሞቼን ትገልብኛለህ?" ብላ እብድ ሆነችበት፡፡ ባልዮውም "በቃ ገመድ አምጭልኝና ልታነቅልሽ" አላት፡፡ በፍጥነት ገመዱን ሰጠችው፡፡ ሙቀጫ ላይ ወጣና ገመዱን ጣራ ላይ አሰረውና ለመታነቅ ዝግጁ ሆነ፡፡ መቼም ዓይነ ስውር ነውና የሁሉንም በደንብ መሳካት ስለማያረጋግጥ ሚስቱ እንድትረዳው ጠየቃት፡፡ "በደንብ መታሰሩን ፈትሽልኝ፡፡ በዚያውም ቶሎ ይገድለኝ እንደሆነና እንዳልሆነ ሞክሪው" ይላታል፡፡ እሷም ሙቀጫው ላይ ወጥታ በደንብ መታሰሩን አረጋገጠች፡፡ ሽምቃቁ በትክክል መታሰሩንም ለማረጋገጥ አንገቷ አስገብታ ስትሞክር ባል ትንሽ ትንሽ ያያልና ያንን ሙቀጫ በእግሩ ሲፈነግለው ሴትዮዋ ታንቃ ሞተች፡፡

ቤተሰቡ ሃዘኑን እንደጨረሰ አማቱ ምግብ እያዘጋጀች ልትረዳው አብራው መኖር ጀመረች፡፡ አራት ልጆቿን ጨርሶባታልና እሷም ቂም አርግዛ ቀን እየጠበቀች ትቆያለች፡፡ እሱም ነብሰ ገዳይ ነውና በጥንቃቄ መኖር ይጀምራል፡፡ ታዲያ አንድ ቀን በገንፎ ውስጥ መርዝ ጨምራ ልትገድለው አሰበችና መርዝ የተጨመረበት ውሃ በድስት ትጥድና ውሃ ልትቀዳ ትሄዳለች፡፡ ዓይነ ስውሩ ሁሉንም ነገር አይቷልና የተጣደውን የድስት ውሃ አፍስሶ በንጹህ ውሃ ይተካዋል፡፡ አማቱም እንደተመለሰች ገንፎዋን አዘጋጅታ ታቀርብለታለች፡፡ "እንብላ" ሲላት "አይ እኔ በኋላ እበላለሁ" በማለት እምቢ ትላለች፡፡ ሰውየው ግን ገንፎውን ሳያስተርፍ ሙልጭ አድርጎ ይበላዋል፡፡ በማግስቱ እልልታውን ያቀልጠዋል፡፡ "ምን ሆንክ? ምን አገኘህ?" ሲሉት አማቴ ያበላችኝ ገንፎ አይኔን አበራልኝ" ይላል፡፡ ግን ውሸቱን ነበር፡፡

አማቱ አንድ ዓይና ነበረችና "ይሄማ መድሃኒት ከሆነ እኔም እበላዋለሁ" ትልና የመርዙን መጠን ከፍ አድርጋ በገንፎዋ ትበላለች፡፡ አማትም እንደልጆቿ ትሞታለች፡፡ ሰውየው በብልሃት ጠላቶቹን ገድሎ በነጻነት ኖረ ይባላል፡፡ (መረከቡ ጋሻው፣ ቦረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

### ተረት 37

ሁለት ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ አንድ ቀን ባልዮው ወደ ሩቅ አገር ለገበያ ሲሄድ ሴትዮዋ ውሽማ ትቀጥራለች፡፡ ባል እንደአጋጣሚ ሆኖ የያዘውን እቃ መንገድ ላይ ሸጦ ይመለሳል፡፡ መሽቶ ራታቸውን ሲበሉ የተቀጠረው ውሽማ በር ማንኳኳት ይጀምራል፡፡ ሴትዮዋም ባሏ ሳይሰማት በእንጉርጉሮ በሬዋን አስመስላ፡-

ተው ቦሩ ተው ቦሩ ቤቴን አታፍርሰው፣

ራቱን ይበላል ሩቅ የሄደው ሰው፡፡

በማለት ለውሽማዋ በምስጢር ትናገራለች፡፡ ባለቤቷም የተናገረችው ስለገባው

ይህንን አላውቅም ቲራንቲር ጨዋታ፣

ቀን ካልተቀጠረ ቦሩ አይመጣም ማታ፡፡

የሚል መልስ ይሰጣታል፡፡ ውሽሜ ግን አሁንም በር ማንኳኳቱን አልተወም፡፡ ሚስትም የውሽሜ ፍቅሩ ቢጠናባት፡-

አዲስ አበባ ላይ ይሸጣል ታኒካ፣

እኔስ አሹካኖኛል ልጆችህን እንካ፡፡

በማለት ወደ ውሽማዋ መሄዷን ለባሏ ትገልጻለች፡፡ ባልም ይነደውና፡-

አዲስ አበባ ላይ ይሸጣል መዋጀ፣

ሽጉጥ ይገባታል ላሽካነናት ቆንጆ፡፡

በማለት በያዘው ሽጉጥ ገደላት ይባላል (ሃሊማ ሰይድ፣ ተሁለደሬ፣ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 38

በድሮ ጊዜ አንዲት ጦጣና አንድ ዝንጀሮ በአንድ አገር ውስጥ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ዝንጀሮ ወደ ገበያ ይሄዳል፡፡ ጦጢት ደግሞ በገደል አፋፍ ላይ ተቀምጣለች፡፡ አቶ ዝንጀሮ ያያትና "አንቺ ማነሽ? ገደል ትገቢያለሽ" ይላታል፡፡ እሷም "እኔ ጦጢት ነኝ ገደል ገቢ ነኝ" ትለዋለች፡፡ እሱም "ገደል ከምትገቢ እኔ ላግባሽ?" ይላታል፡፡ እሷም "ምን ታበላኛለህ? ምን ታጠጣኛለህ?" ትለዋለች፡፡ እሱም፡-

እኔ ዝንጀር ጎሹ አውድማ አፍርሼ፣

አበላሽ የለም ወይ አገር አስለቅሼ፡፡

ይላታል፡፡ አስከትላ "ከሆነ ሆነና ይቺን ቂጥህን ምን መለጠብህ? ትለዋለች፡፡ አሱም፡-

ጌታ ቢያዝንልኝ በቅሎ ገዛልኝ፣

ስወጣ ስወርድ ተገጠበብኝ፡፡

ይላታል፡፡ እሷም ጥያቄዋ ማባሪያ የለውምና "ከሆነ ሆነና ይቺን ልብህን ምን መለጠብህ?" ትለዋለች፡፡ እሱም

ጌታ ቢያዝንልኝ በርኖስ ገዛልኝ፣

ሳወጣ ስለብስ ተመለጠብኝ፡፡

ይላታል፡፡ አሁንም "ከሆነ ሆነና ይቺን እጅህን ምን አጠቆራት?" ብትለው እሱም

ጎበዝ ተሰብስበን እሸት ስንጠብስ፣

አጠቆራት እንጂ ያ ሚርተኛ ጭስ፡፡

ይላል፡፡ በመጨሻም "ከሆነ ሆነና ይቺን ዓይንህን ምን አጎደጎዳት? አለችው፡፡ እሱም የሞት ሞቱን

ጎበዝ ተሰብስበን ውሃ ስንራጭ፣

አንዱ በጡሴው መነቋቆላት፡፡

አላት፡፡ ከዚያም ወይዘሪት ጦጢት ነገሩን አውጥታ አውርዳ

ትሰማኝ እንደሆን እኔ አንተን ለማግባት፣

ይቺን አመልህን በሙሉ አስተካክላት፡፡

ብላው ጥላው እየሮጠች ሄደች ይባላል (ዳንኤል ይመር፣ ቦረና፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 39

ከእለታት አንድ ቀን በአንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ማየት የተሳናቸው የባልዮው አባት እየተጦሩ አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ እኚህ አባት ቀኑን ሙሉ ተቀምጠው የሚውሉባት አንዲት ጠፍጣፋ ድንጋይ ከደጅ ነበረች፡፡ የልጅ ሚስት ያቺን ድንጋይ ፈንቅለህ ካልጣልክ ብላ ባሏን ወጥራ ትይዘዋለች፡፡ ባልም ምክንያቱን ሲጠይቅ "ስወጣ ስገባ ያንተን አባት ማየት አልፈልግም" የሚል ይሆናል፡፡ ባል ምንም ማድረግ አልቻለምና እንደተባለው አደረገ፡፡ በሌላ ጊዜ ደግሞ "አባትህን ከዚህ ቤት አውጥተህ ካልጣልክ እኔና አንተ አብረን አናድርም" ብላ ቁርጥ ያለ ትዕዛዝ ትሰጠዋለች፡፡ ልጅ ግራ እየተጋባና እየተከዘ አባቱን በዘዴ ከቤት ይዞ ወጥቶ ሰፊ ሜዳ ላይ ካለ ትልቅ ድንጋይ ላይ አስቀምጦት መጣሁ ብሎት ይመለሳል፡፡

ልጅ እቤቱ ከተመለሰ በኋላ ምግብ ሳይበላ እንደተንጎራደደ እንቅልፍ ሳይወስደው ያድራል፡፡ በማለዳ "እግዚአብሔርዬ! አባቴን እንዴት አሳድረኸው ይሆን?" እያለ አባቱን ወዳስቀመጠበት ሜዳ ይሄዳል፡፡ ከቦታው ቢደርስ አካባቢው ጨፌ ሆኖ ብዙ ከብት ከቦት ያገኘዋል፡፡ "አባዬ! ይህ ሁሉ ከብት ከየት መጣ? መስኩስ እንዴት ለምለም ሆነ?" ብሎ አባቱን ይጠይቃል፡፡ አባትም "እግዚአብሔር ጥሎ አይጥለኝም፡፡ ከየአቅጣጫው እምቧ እያለ መጣ" ብለው ይነግሩታል፡፡ ልጁም በመገረም አባቱን ይዞ ከብቱን እየነዳ ወደ ቤቱ ይሄዳል፡፡ እቤት እንደደረሱ ሚስት "ይህ ሁሉ ምንድን ነው?" ብላ ትጠይቃለች፡፡ ባልም "ካባቴ ጋር አገኘሁት" ይላታል፡፡ "እንግዳውስ የእኔንም አባት መጦር አለብኝ" ብላ ወንድሞቿን አሳምና ተራዋን ልትጦር አባቷን ታመጣለች፡፡ ውለው ካደሩ በኋላ ባሏን "ና የእኔን አባት ያንተን አባት ካስቀመጥክበት ቦታ አድርሰው" አለችው፡፡ እሱም "እኔ

አላስቀምጥም፡፡ አንቺው አስቀምጭው" አላት፡፡ "ቦታውን ንገረኝ" አለችው፡፡ ቦታውን ነግሯት አባቷን አድርሳው መጣች፡፡ በማግስቱ በጧት ተነስታ ብትሄድ ጅብ በልቶት አገኘችው፡፡ እጅና እግሩን ይዛ እያለቀሰች መጣች፡፡ ዘመድ ተላልካ የቀብር ስርዓቱ ላይ ወንድሞቿ መጥተው ሲያለቅሱ የአካባቢው ሰው በምን እንደሞቱ ነገሯቸው፡፡ የቀብር ስርዓቱ እንዳለቀ እህታቸውን "ነይ አገራችን እንሂድና ሃዘናችንን ባንድ እንጨርስ ብለው ወሰዷት፡፡ ከዚያም ባዶ ሜዳ ላይ አስረው ጥለው በጅብ አስበሏት ይባላል (ሰይድ አሰን ሙህዬ፣ ተሁለደሬ፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 40

በዱሮ ጊዜ ባልና ሚስት ነበሩ አሉ፡፡ ሚስት ከባሏ ሌላ ትሄድ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን አቶ ባል በዚሁ ይጠረጥራትና አንድ መላ ያበጃል፡፡ ለሚስቱ "ሩቅ አገር ልሄድ ነው፤ ነገ ነው የምመጣው" ብሎ ኪታቡን ከአልጋው አጠገብ ሰቀለና "ይህንን መጽሃፍ እንዳትነኪ ሌላ ሰው ከመጣ ይነግረኛል" ብሎ ሄደ፡፡ ነገር ግን ተመልሶ ሰው በማያይበት ከቤቱ ታዛ ጣራው ስር ተሸሽጎ የሚሆነውን ሁሉ ለማየት ተዘጋጀ፡፡ ሚስት "አሁን ይህንን ኪታብ ከዚህ ባወርደው ሊናገር?" ብላ ልታወርደው ብላ መልሳ "አይ እስከዛሬ ለምን አይናገርም ነበር? ውሸቱን ነው እንጂ!" ብላ ኪታቡን ተወችው፡፡ መምሸት አይቀርምና ሲመሽ ውሽሜ መጣና "እንዴት ዋልሽ?" ብሎ ከቤት እንደገባ ራታቸውን በሉ፡፡ ከዚያም ሴትዮዋ አልጋዋን አነጠፈችና ወጥተው ሲደባደቡ ከሁለት አንዳቸው ፈሳቸው ዘረጥ አለ፡፡ ያንቺ ነው ያንተ ነው እየተባባሉ ማን እንደፈሳው ሳይታወቅ ስራቸውን ሰርተው እንቅልፍ ወሰዳቸው፡፡

ውሽሜ ጧት ተነስቶ ወደቤቱ ሄደ፡፡ ባለቤት ሲሄድ ያደረ መስሎ ሚስቱ ሳታየው በጧት ከጣራው ስር ወረደና "እንዴምን አደርሽ?" አላትና "ይህንን ኪታብ አልነካሽውም?" ብሎ ከተሰቀለበት አወረደና በዜማ ማንበብ ጀመረ፡፡

ውሽሜ መጣና  
እንዴት ዋልሽ ብሎ ከቤቱ ገባና  
ተሳሳቁና  
ቁጭ በል ብላ እሱም ቁጭ አለና  
ከቆይታ በኋላ ራት ቀረበና  
ራትም በሉና  
የመኝታ ጊዜም ቶሎ ደረሰና

እሷም ለማንጠፍ አልጋ ወጣችና
ከአልጋውም ወጥታ አነጠፈችና
ሁሉም ለመኝታ አልጋ ላይ ወጡና
ከወጡ በኋላ የአልጋ ድብድብ ተደባደቡና
ከሁለት አንዳቸው
ዘረጥ አለ ፈሳቸው
ያንተ ነው ያንቺ ነው ሲጣሉ አየኋቸው
የማን እንደሆነ ሳይታወቅላቸው
ስራቸውን ሰርተው እንቅልፍ ወሰዳቸው

ብሎ አቶ ባል አስመስሎ ሲያነብላት ሚስት ወደሄደችበት ሳይታወቅ ጠፍታ ቀረች ይባላል፡፡ (ሃሰን አበጋዝ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

## ተረት 41

በድሮ ጊዜ ባልና ሚስት አብረው በሰላም ይኖሩ ነበር ይባላል፡፡ በዚህ ሁኔታ እየኖሩ እያለ አንድ ቀን አምሽቶ ይገባል፡፡ እንደመጣም "በደህናህ ነው? ለምን አመሸህ?" ስትለው "ይገርምሻል መንገድ ላይ ሁለት ሆነው ጠብቀውኝ አንዱን በቡጢ አንዱን በእርግጫ ብያቸው መጣሁ" ይላታል፡፡ እሷም በባሏ ጀግንነት ተደስታ ጥሩ እራት ሰርታ ትጋብዘዋለች፡፡ በሁለተኛውም ቀን ያመሸና ሲመጣ "ዛሬ ደግሞ ሶስት ሆነው መንገድ ላይ ጠበቁኝ፡፡ ሶስቱንም እንደለመድኩት አድርጌጣቸው መጣሁ" ይላታል፡፡ በሶስተኛውም ቀን እንደለመደው እየሸለለ እየፎከረ እቤቱ መጣና "ዛሬ ደግሞ ይገርምሻል 15 ሆነው ሙሽራ ይዘው ሲሄዱ ሁሉንም ጭንቅላታቸውን ፈረካክሼ ሙሽራይቱን ቀማኋቸው፡፡ ግን ክርስቲያኖቹ በእግዚአብሔር፣ ሙስሊሞቹ በአላህ ብለው ሲለምኑኝ ሙሽራይቱን ሰጠኋቸው" ይላታል፡፡ ሚስትም እንደተለመደው ግብዣዋን ታደርግና በማግስቱ ሲወጣ ዝም ትልና ትልከዋለች፡፡ የባሏን ጀግንነትም በመጠራጠር ለማረጋገጥ ብላ ማታ መምጫው ላይ የእሱን ልብስ ለብሳ መንገድ ላይ ትጠብቀዋለች፡፡ እንደተለመደው አምሽቶ ሲመጣ "ና!" ትለዋለች፡፡ "እሺ" ብሎ ወደእሷ ይጠጋል፡፡ ተንበርከክ ስትለው ይንበረከካል፡፡ ከዚያም ሱሪዋን አውልቃ "ና ቂጤን ሳም!" ስትለው ይስማል፡፡ በመጨረሻም ጉንዳን ያለው ድንጋይ ፈንቅላ ካሸከመችው በኋላ "በል ዙረህ ሳታይ በዚያ በሩቁ መንገድ ቀጥ ብለህ ወደ ቤትህ!" ስትለው ቀጥ ብሎ ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ እሱ በረጅሙ መንገድ ሲሄድ እሷ በአቋራጩ ቀድማ ወደ ቤቷ ትገባና ልብሷን ቀያይራ

ትጠብቀዋለች፡፡ ሲመጣ "ዛሬስ ምን ሆነህ አመሸህ?" ስትለው "እንደተለመደው አራት ሆነው ጠብቀውኝ አንዱን በእንትን አንዱን ደግሞ በእንትን . . ." እያለ መዘርዘሩን ሳይጨርስ "ቂጥ የላሰው ማን ነው?" ስትለው "ነገሩ ያ ቂጥ አዲስ አልሆነብኝም" አላት ይባላል (የሱፍ ይመር፣ ተሁለደሬ፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 42

በድሮ ጊዜ ሁለት ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ አንዲት የታጨች ሴት ልጅና አንድ ወንድ ልጆችም ነበሯቸው፡፡ አባታቸውም ዘመቻ ሄዶ ነበር፡፡ ዘመቻ እንደሄደ እናታቸው በድንገት ሞተች፡፡ ከብዙ ዘመን በኋላ አባታቸው ከዘመቻ መጥቶ የሚስቱን እርም ካወጣ በኋላ አንዲት ሴት ልጅ ያላት ሴት አገባ፡፡ አዲሲቷ ሚስት ክፉ ስለነበረች ለባሏ ልጆች ምግብ አትሰጣቸውም ነበር፡፡ በዚያ ላይ የባሏን ልጆች ብቻ ከብት እንዲጠብቁ ወደ ዱር ትልካቸው ነበር፡፡ ወንዱ ልጅ በጣም ሲርበው ያለቅስ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ እህቱ "አላህ! እባክህ ወተት! እባክህ ለከት!" እያለች ትለምን ነበር፡፡ ወዲያውም የለመነችው ወተትና ለከት ከሰማይ ይወርድላቸው ነበር፡፡ በየእለቱ እንዲህ እንዲህ እያደረጉ ይውሉ ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ልጆቹ መልካቸው እንደፀሃይ ያበራ ጀመር፡፡ በዚህ ጊዜ እንጀራ እናታቸው "እኔ እቤት ውስጥ የሚያጠግብ ምግብ አልሰጣቸውም፡፡ ምን እየበሉ ይሆን እንዲህ ያማረባቸው?" ስትል አሰበች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ልጇን ከእንጀራ ልጆቿ ጋር ከብት ጥበቃ ወደ ዱር ላከቻት፡፡ እንደተለመደው ወንዱ ልጅ እርቦት ማልቀስ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ እህቱ የእናትያዋን ልጅ "ለእናትሽ የማትነግሪብኝ ከሆነ ለወንድሜ ምግብ ልለምንለት" አለቻት፡፡ ያችኛዋም "አሺ አልናገርም ለምኚለት" አለቻት፡፡ እንደቀደመው ልመናዋን ቀጠለች፤ የለመነችውንም አግኝታ ሁሉም ተካፍለው በሉ፤ ጠጡ፡፡ ሲመሽም ከብቶቻቸውን ይዘው ወደቤታቸው ሄዱ፡፡

ማታ ላይ እናት ያላት ልጅ ለእናቷ በጆሮዋ ቀን የሰሩትን ሁሉ ነገረቻት፡፡ እናቲቱም በመበሳጨት "ከዛሬ ጀምሮ ከብት አትጠብቁም" አለቻቸው፡፡ በማግስቱ የራሷን ልጅ ከብቶችን ወደዱር ይዛ ሄዳ እንድትጠብቅ ላከቻት፡፡ ቀን ላይ ሲርባት እንደ አባትያዋ ልጅ ምግብ ለመነች፡፡ ሆኖም ልታገኝ አልቻለችም፡፡ በተደጋጋሚ ሞከረች፤ ግና አልሆነም፡፡ በዚሁ ተናድዳ ሳይመሽ ከብቶቿን እየነዳች ወደቤቷ ተመለሰች፡፡ ለእናቷም "እኔ ብለምን አልሰጠኝ አለ" ብላ ተናገረች፡፡ እናቲቱ የባሰውኑ ተናድዳ "ነገ ዱር ስትሄዱ ሁለቱንም ገፍትረሽ ባህር ውስጥ አስገቢያቸው" ስትል ልጇን መከረቻት፡፡ ልጅትም እንደተመከረችው በማግስቱ ከባህሩ ዳርቻ ሲጫወቱ ሴቷን ልጅ ገፍትራ ባህሩ ውስጥ

ጣለቻት፡፡ ታናሽ ወንድሟ እህቱ ልትሞት መሆኗን ሲገነዘብ አለቀሰ፡፡ እያለቀሰም "እትየ! እትየ! አባታችን መጣ ከዘመቻ፣ ድሪውን ይዞ አልቦውን ይዞ" አለ፡፡ ልጅቱም

"ድሪውም ይሁን እናት ላላት፣

አልቦውም ይሁን እናት ላላት፣

እኔስ ተይዣለሁ በዘንዶ ጅራት"

በማለት መለሰችለት፡፡ በዚህ ሁኔታ ከዋሉ በኋላ ሲመሽ ወንዱ ልጅ እና ባለ እናቷ ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡ አባትም የልጁ ባህር ውስጥ መግባትና በዘንዶ ጅራት መያዟን አረጋገጠ፡፡

አባት ልጁን ከዘንዶ ለማስለቀቅ ዘዴ ቢያጣ ወደአንድ አዋቂ ቤት አመራ፡፡ አዋቂውም "ወንዙ ዳር ጥቁር በሬ እረድ፡፡ ዘንዶው ደሙን ሊጠጣ ይወጣል፡፡ በዚያን ጊዜ ልጅቱ ከባህሩ ውስጥ ትወጣለች፡፡ ሆኖም ልጅቱ ከባህር ስትወጣ መሬት መንካት የለባትምና የወንዙ ዳር በሙሉ አበባ ምንጣፍ አንጥፍበት" አለው፡፡ አባትዮው የተባለውን ሁሉ አደረገ፡፡ ነገር ግን እንዳጋጣሚ ሆኖ ልጅቱ ከባህር ስትወጣ መሬት ነካች፡፡ ወዲያውኑ ወደአንድ ትንሽ ዛፍነት ተቀየረች፡፡ በዚህም የተነሳ እጮኛዋ የእንጀራ እናቷን ልጅ እንዲያገባ ተደረገ፡፡

የሰርጉ እለት የሙሽራዋ አጃቢዎች ሙሽራዋን ይዘው ወደቤት ሲመጡ ከዚያች ትንሽ ዛፍ ለጥርሳቸው መፋቂያ ሊቆርጡ ቢሉ እምቢ አለቻቸው፡፡ ሙሽራው ነካ ቢያደርግ ግን ንቅል አለችለት፡፡ ከዚያም ሙሽራው ለሚስቱ ከመፋቂያዋ ቆርጦ አካፈላት፡፡ ሙሽራይቱ ጥርሷን ስትፍቅ መፋቂያይቱ ለሙሽራዋ "አንቺ ይሄ ባል የኔ ነበር፤ ያንቺ አልነበረም" ስትላት "ይህንን መፋቂያ እሳት ክተቱልኝ" አለች፡፡ ወዲያው እሳት ውስጥ አስገቧት፡፡ አመድ ሆነች፡፡ አመዱን አህያ ቃመችው፡፡ አህያዋ ፋንድያ ጣለች፡፡ አንዲት ባልቴት ኩበት ሲለቅሙ የአህያ ፋንድያዋ "እማማ! አንሱኝ አነሳኋለሁ፡፡ እሽምብራ ጎታ ክተቱኝ" አለቻቸው፡፡ ባልቴቷም እንደተባሉት አደረጉ፡፡ ከዚያም ፋንድያዋ ሰው ሆነች፡፡ ውበቷም እንደጸሃይ የሚያበራ እንቁ ሆነ፡፡

የልጅቱ እጮኛ የባልቴቷ ጎረቤት ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ከጓደኞቹ ጋር ገና ሲጫወት ሩሯ ተፈናጥራ እባልቴቷ ሽንብራ ጎታ ውስጥ ገባች፡፡ ልጅቷም ሩሯን አውጥታ ስትወረውር ልጁ አያት፡፡ ልጁም በውበቷ በመደነቅ ባልቴቷን "የማን ልጅ ናት?" ብሎ ጠየቀ፡፡ ባልቴቷም "የእኔ ልጅ ናት" አሉት፡፡ ልጁም "ላግባት" ይላቸዋል፡፡ ባልቴቷም "ያገባሃት ሚስትህሳ" አሉት፡፡ እሱም "እሷ ሰራተኛ ትሆናለች" አለ፡፡

ባልቴቷም እሽታቸውን ከገለጹ በኋላ እቤቱ ድረስ የአበባ ምንጣፍ አንጥፎ፣ በወርቅና በእንቁ አስጊጦ በብዙ ፈረሰኞች አጅቦ በሰርግ ማግባት እንደሚችል ገለጹለት፡፡ እሱም የተባለውን ሁሉ አሟልቶ በክብር አገባት፡፡ አዲሲቱ ሚስት የበፊተኛዋን ምላሷን አስወጥታ በምላጭ ቆረጠቻት፡፡ በዚሁም ምክንያት ለመሞት በቃች ይባላል (አያል አበበ፣ ቦረና፣ ነሐሴ 2007)፡፡

**ተረት 43**

በጥንት ዘመን በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ባልና ሚስቶቹ እጅግ ባለጸጋ ልጆች ነበሩ፡፡ ሃብታቸው ተቆጥሮ የሚያልቅ አልነበረም፡፡ በመሆኑም በኑሯቸው እጅግ ደስተኞች ነበሩ፡፡ ድሆችንና የተቸገሩትን የሚረዱ ደጎች ነበሩ፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባል በረሃ ሲሰራና ሲያሰራ ውሎ ማታ ወደቤቱ ሲመጣ ባለቤቱ ከቤቱ ደጅ ላይ ቁጭ ብላ ስትተክዝ አገኛት፡፡ ባልም ሁኔታዋን አይቶ "ውዴ! ምነው ትተክዣለሽ? ካልጠፋ ነገር" አላት፡፡ ሚስትም "እንዲያው ነገሩ ሁሉ እየገረመኝ ነው እንጂ" አለችው፡፡ ባልም "ለመሆኑ ምንድን ነው የሚያስገርምሽ? ይልቁንስ ባል በረሃ ውሎ ሲመጣ ይደሰቱታል፣ ይስቁታል፣ ይዝናኑታል እንጂ ይተክዙታልን?" አላት፡፡ እሷም "ኧረ ወንድሜ አትጨነቅ! ምንም አይደለም" አለችው፡፡ ባልም "ለምን አትነግሪኝም" አላት፡፡ እሷም "ህጻን ልጅ እያለሁ ወላጅ እናቴ ስታደርግ የነበረው ነገር ሁሉ ብቻየን ስቀመጥ ትዝ እያለኝና ሌሊት ሌሊት ትዝታው እየመጣ እየገረመኝ ነዋ!" አለችው፡፡ ባልም "እሱ ምንድን ነው የሚገርምሽ ውዴ?" አላት፡፡ "እንዲህ ነው ነገሩ፡፡ ቀድሞ እናቴ ለቤተሰቡ በሙሉ ስትጋግርበት የነበረው ምጣድ ይህንን ዓለም የሚያክል ነበር፡፡ በዚያ ምጣድ የተጋገረው እንጀራ አንዱን አስር ሰው አይጨርሰውም ነበር፡፡ እንዲሁም ይህ ብቻ አይደለም የደነቀኝ፡፡ የእንጀራው አይን እንጉዳይ ያህል ነበር" አለችው፡፡ ባል "ይህ ነው ታዲያ የሚገርምሽ? አላት፡፡ ሚስት "እንዴት አይገርመኝ! ስለ እናቴ ምጣድ እኔ ቀርቶ ሳር ቅጠሉ በሙሉ እየተደነቀ፡፡ ያ ዘመን ቀረና ሌላ ዘመን መጥቶ ዛሬ እኔ የምጋግርበት ምጣድ ቃጤ የምታክል ናት" አለችው፡፡ እሱም በተራው "አንቺ ይቺ ናት የምትገርምሽ! የእኔ አባት ነጩን ፈረስ ሲጋልብ ሰማይ ለሰማይ ነበር" አላት፡፡ እሷም "እውነትህን ነው? እንደ አውሮፕላን በሰማይ እየበረረ የሚሄድ አደረግከው እኮ" ስትለው ጊዜ "መሬት ለመሬት እንዳይጋልብማ የአንቺን እናት ምጣድ ሊሰብር አይደል" በማለት መለሰላት ይባላል፡፡ (መዝገቡ ወልደ፣ ኩታበር፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተርት 44

በድሮ ጊዜ በጣም የሚዋደዱ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ባልዮው በውጭ የሚሰራውን የወንድ ስራ እየሰራ ውሎ ማታ ወደቤቱ ይገባል፡፡ ሚስቲቱም በቤት ውስጥ የሴትነት ስራዋን ባማረ ሁኔታ እየሰራች ትውላለች፡፡ ባልዋ "እንደምን ዋላችሁ?" ብሎ ሲገባ ሚስት አጸፋውን ሰጥታ በጥሩ ሁኔታ ታስተናግደው ነበር፡፡ የእርሻ መሳሪያዎቹን ተቀብላ፣ በሞቀ ውሃ እግሩን አጥባ፣ ለእራት መዳረሻ የሚሆን ቆሎና ጠላ ሰጥታ በጥሩ ሁኔታ ትንከባከበው ነበር፡፡

ሚስት እጅግ መልከ መልካም ስትሆን ባልዋ ግን ጥርሰ ገጣጣ ስለነበረ "ይህ ጥርሳም ባልሽ" እያሉ ያናድዷት ነበር፡፡ አንድ መልከ መልካም የመንደር አውታታ ይህንኑ መግቢያ አድርጎ አንድ ነገር ለሚስትዮዋ ሌላ ነገር ለባልዮው እያቀበለ ያጣላቸዋል፡፡ በዚህም የተነሳ ሚስት ለባሏ የምትሰጠው ምላሽ ሁልጊዜ ተቃራኒ ሆነ፡፡ ከዚህም አልፎ በቤት ውስጥ ሚስትዮዋ የበላይነቱን በመያዟ ባል መብቱን አጣ፡፡ ሁልጊዜም ተቃራኒ መልስ እንደምትሰጠው በመረዳቱ የሚፈልገውን ነገር በተቃራኒው መጠየቅ ያዘ፡፡ እራት መብላት ከፈለገ "አይ ዛሬ ጠግቤያለሁ እራት አልበላም" ይላል፡፡ ሚስት "አይ መብላት አለብህ!" ብላ እንዲበላ ታደርገዋለች፡፡ በዚህ አይነት ሁኔታ ሲኖሩ ቤታቸው እጅግ ቀዘቀዘ፤ ድህነትም ያዛቸው፡፡

ከእለታት አንድ ቀን በክረምት ወራት አባቷ በመሞታቸው የቀብር ጥሪ መልዕክት ደረሳቸው፡፡ በጥሪው መሰረት ጎረቤቶቿ ተከትለዋት ጉዞ ቀጠሉ፡፡ በመንገዳቸው ላይ ያለው ትልቅ ወንዝ በጣም ሞልቶ ስለነበር አላሻግራቸው ይላል፡፡ በዚህ ጊዜ ባል ተከትለዋቸው ለሄዱት ጎረቤቶቹ "ወንዙ ስለማያሻግረን እስከሚጎድል ድረስ መጠበቅ አለብን" የሚል ሃሳብ ይሰነዝራል፡፡ ይህንን ንግግሩን የሰማቸው ሚስት አሰተሳሰቧ ሁሉ ከባሏ ተቃራኒ ነውና "አይ አልሞላም፤ መሻገር አለብን" ብላ ልትሻገር ወደ ወንዙ ትጠጋለች፡፡ ባል "ቆይ መጀመሪያ ልሞክረው" ሲል ሚስት አይሆንም ብላ ተንደርድራ ትገባለች፡፡ ውሃው በጣም ሞልቶ ስለነበረ ሴትዮዋን እያዳፋ ቁልቁል ይዟት ይነጉዳል፡፡ ይህንን የተመለከቱት ጎረቤቶቻቸው ባልዮውን "ወሰዳት እኮ! ግባና አውጣት እንጂ?!" ሲሉት ዘልሎ ይገባና ወደላይ መዋኘት ይጀምራል፡፡ ሰዎቹ የሰውየው ወደላይ እየዋኘ መሄድ ገርሟቸው "ወደታች እኮ ነው የወሰዳት ወደላይ የምትሄደው ለምንድን ነው?" ቢሉት "የሚስቴን ባህሪ የማውቀው እኔ ነኝ፡፡ እሷ ወደታች አትሄድም፤ ከውሃው

ተቃራኒ ወደላይ ነው የምትሄደው" በማለት መለሰላቸው፡፡ በዚሁ ጨዋው ባል ክፉ ሚስቱን ተገላገለ ይባላል (አባተ ይመር፣ በረና፣ ነሐሴ 2007)፡፡

**ተርት 45**

በድሮ ጊዜ አንድ ሃብታም ገበሬ ነበር፡፡ ከስቡ ብዙ ከመሆኑ የተነሳ የአካባቢውን ሰዎች እየለመነ በደቦ ያሰራ ነበር፡፡ ከደቦኞቹ መካከል በውሽምነት የሚሰራረቁ ወንድና ሴት ነበሩ፡፡ ሁለቱም እደቦው አብረው ሲተያዩ በመዋልቸው ደስ ብሏቸው ነበር፡፡ ማታም ቀደም ብሎ ወደቤቷ መጥቶ ፍላጎታቸውን እንዲፈጽሙ በመጠቃቀስ ተግባብተው ነበር፡፡

ምሳ ላይ ቀርቦላቸው ሲመገቡ ሴቷ በውሽማዋ ሆዳም ላለመባል እንደ ኩራት ቢጤም ተሰምቷት ቀማምሳ ትተወዋለች፡፡ ምሽት ላይም እንደምሳው ነካክታ ትተወዋለች፡፡ ሆኖም ግን ምሳዋንም እራቷንም በደንብ ባለመብላቷ እጅግ እርቧት ነበርና ተጣድፋ ወደቤቷ ትሄዳለች፡፡ እንደደረሰችም በፍጥነት ምጣዷን ትጥድና ቂጣዋን እየጋገረች ትኩስ ትኩሱን መብላት ትጀምራለች፡፡ ሳታስበው መጥና ያልበላቸው ምግብ እጅግ ሆዷን ይወጥራታል፡፡ ወጸዳዳትም ፈለገች፡፡ ግና ወደቤቷ ጓሮ ሄዳ ለመጸዳዳት ጊዜ አልሰጣትምና ከቤቷ ወለል ላይ ትለቀዋለች፡፡

ውሽሜም እራቱን በልቶ ጠላውን ሲጠጣ የቀኑን ቀጠሯቸውን ሲያስታውስ ጊዜ ፍትወት አደረበትና ወደ ውሽማው ዘንድ መሄድ አሰበ፡፡ ባልዮው ከደቦው ቤት ወደቤቱ ሳይመለስ ውሽሜ ፍላጎቱን መፈጸም ስለፈለገ ቀደም ብሎ ከደቦው ቤት ወጥቶ ወደ ውሽማው ቤት ሄደ፡፡ በሚያውቃት በር በኩል በቀዳዳ ጠጋ ብሎ ሲያስተውል አበላሷ አስደነገጠው፡፡ የመጣበትን ጉዳይ ለመፈጸም በር ሊያንኳኳ ሲል ክፍት ሆኖ አገኘው፡፡ ወደበሩ ጠጋ ሲልም አንዳች የቀጠነ ነገር ፊቱ ላይ ተመረገበት፡፡ ለካስ ሴትዮዋ የተጸዳዳቸውን ነገር እየጣለች ኖሯል፡፡ እሱም ምንም ሳይናገር ወደቤቱ ሄዶ ሚስቱ ከደቦው ቤት ሳትመለስበት ታጥቦ ልብሱን ቀየረ፡፡

በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ በጎረቤታቸው አንዲት ልጃገረድ ታገባ ነበርና ሁለቱም በሰርጉ ላይ ተገኙ፡፡ ተበልቶ ተጠጥቶ እንዳበቃ ሙሽራ ሊወጣ ሲል ሴቷ አታሞዋን ይዛ ማቀንቀን ጀመረች፡፡ በጨዋታው ላይ ውሽማዋን ስታይ ጊዜ፡-

> መቼም ውል የለህ መቼም ውል የለህ፣
> እመጣለሁ ብለህ ምነው መቅረትህ?

በማለት ሰው በማይነቃ መልኩ ብሶቷን ገለጸች፡፡ ወንዱ ደግሞ በግጥሟ በሽቆ ስለነበር ግጥም እንድትቀበለው ጠየቃት፡፡ እሷም ተቀበለችው፡፡ ግጥሙ እንዲህ የሚል ነበር፡፡

ከነምልክቱ እደቦው ውለሽ፣
በትልቁ ምጣድ ቂጣሽን ጋግረሽ፣
ምንም ሳታስቀሪ ጠራርገሽ በልተሽ፣
ኧረ ተይ እህቴ ውል ያጣሽስ አንቺ፣
ድፍድፍ አስመስለሽ ባርሽ የምትመቺ፡፡

በማለት አጸፋ ግብሩን መለሰላት፡፡ ባልዮው ከጥንት ጀምሮ ሚስቱ ከውሽማዋ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይጠረጥር ስለነበረ ይከታተላቸው ነበር፡፡ በሰርጉ ቀን ግን ጥርጣሬውን እውን የሚያደርግ መረጃ ስላገኘ ሁለቱንም ገደላቸው ይባላል (አሰፋ ዳኘው፣ በረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

**ተረት 46**

በጥንት ዘመን በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሁለት ሴትና ወንድ ነበሩ፡፡ ወጣቶቹ ከልጅነታቸው ጀምሮ እጅግ ይዋደዱ ስለነበር ፍቅራቸውን የተመለከቱ ቤተሰቦቻቸው ባገራቸው ወግና ባህል መሰረት በወግና በማዕረግ እንዲጋቡ አደረጓቸው፡፡ ትዳራቸውም ደስ የሚልና የተቃና ሆነ፡፡ እግዚአብሔርም ፍቅራቸው ደስ ብሎት የሰሩትን ባርኮላቸው ባለጸጋም አደረጋቸው፡፡

ነገር ግን የሰው ልጅ ጥንተ ጠላት የሆነው ዳቢሎስ ከእለታት አንድ ቀን እንዲጣሉ አደረጋቸው፡፡ ባልዮውም የጥንቱን ፍቅራቸውን እረስቶ የእለቱን ግጭት ብቻ በመመልከት ባለቤቱን እንደ አባኮስኳሴ ጠላት፡፡ ለመፍታትም አሰበ፡፡ አስቦም አልቀረ ቅድመ ዝግጅት አደረገ፡፡ ዳቢሎስ ልቡን በተንኮል ሞላውና በጋራ ሰርተው ያፈሩትን ሃብት መደበቅና መሰወር ጀመረ፡፡ በቤት ውስጥ ያሉትንም በሬዎች፣ ላሞች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ወዘተ. እየሸጠ ብሩን መቅበር ጀመረ፡፡ ይህንን አድርጎ እንደጨረሰ የሁለቱንም ቤተሰቦችና ጎረቤት ሽማግሌዎች ሰብስቦ "እንዳጋባችሁን አፋቱን" ብሎ ጠየቀ፡፡ አስተዋይዋ ሚስት በሁኔታው አዝና "ብትችሉ አስማሙን፤ ካልሆነ ግን ንብረቴን ይስጠኝና ይፍታኝ፤ እሄዳለሁ" በማለት ስትናገር ባል የሰራውን ሁሉ በሆዱ ይዞ "ንብረቱን አብረን በሆን ጊዜ ተጠቅመን ጨርሰነዋል፡፡ የማካፍላት ንብረት የለንም" በማለት መልስ ሰጠ፡፡ የሃገር ሽማግሌዎችም ምንም እንኳ የጋራ ንብረት እንዳላቸው

ሆዳቸው ቢያውቅም "ፈጣሪ ለተበደለ ይገዝ" በማለት የሰማኒያ ወረቀታቸውን አቃደው አፋትተው አለያዩዋቸው፡፡

ሚስት በደሏን ሁሉ ለፈጣሪ ሰጥታ በድህነት እየኖረች ሳለ የፈታት ባሏ ይሞታል፡፡ በቀብር ስነስርዓቱም ላይ እንድትገኝ መልዕክት ደረሳት፡፡ በለቅሶውም ላይ ሙሾ እንዲታውርድ ተጋበዘች፡፡ መቼም የወጋ ቢረሳ የተወጋ አይረሳምና በደሏን ያልረሳቸው ሚስት፡-

ያንተማ አቀባበር መቺ እንደዚህ ነበር፣
ከስር ቀጋ አድርጎ ከላይ አጋም ነበር፡፡

ስትል ሙሾ አወረደች፡፡ ይህንን እንዳለች ግን የጎረቤት ሴቶች "ተይ እንደዚህ አይባልም፡፡ እሱ እንደሁ አንድ ጊዜ ሙቷል ተነስቶ አይሰማሽ፡፡ ለምን ሙት ወቃሽ ትሆኛለሽ! ደግሞ እኮ ሊሞት ሲል በሬና ላም ስጡልን ብሎ አዟል" አሏት፡፡ እሷ ግን በደሏ ከባድ ነበርና በድጋሚ፡-

ላሚቱንም ሰጥቶኝ ከእንግዲህ አልወደው፣
በሬውንም ሰጥቶኝ ከእንግዲህ አልወደው፣
ተሸክሞት ይሂድ እሱን ካልከበደው፡፡

በማለት ሙሾዋን አወረደች፡፡ ከዚያን ጊዜ ወዲህ ባል ሚስቱን ሲፈታ ግማሽ ንብረት መስጠት ጀመረ ይባላል፡፡ (በለጠ መላኩ፣ ተሁለደሬ፣ ነሐሴ 2007)፡፡

## ተረት 47

ባንድ ዘመን ባንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ የወለዱ፣ የከበዱ፣ ቤታቸውን በጥሩ ሁኔታ የሚመሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ባልና ሚስቶቹ የ15 ዓመት ልጃገረድ በቤት ውስጥም ነበረቻቸው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባልና ሚስቶቹ አገር እንይ ብለው ለ7 ቀን ያህል ወደማያውቁት አገር ሄዱ፡፡ በዚሁ ጊዜ አንድ ሽማግሌ ከቤታቸው አቅራቢያ ሲደርስ ይመሽባቸውና የ15 ዓመት ዕድሜ ልጃቸውን አሳድሪኝ ብለው ይጠይቃሉ፡፡ ልጅቷም "እናትና አባቴ የሉም፤ ስለዚህ ላሳድረዎት አልችም፣ እፈራለሁ" አለቻቸው፡፡ ሽማግሌውም "ዕድሜዬን አይተሽ ፍረጂኝ፡፡ በዚህ ዕድሜዬ እንኳን መጥፎ ስራ ልሰራ የሚሰሩትንም እመክራለሁ" በማለት ሲያግባቧት ከቤት እንዲገቡ ፈቀደችላቸው፡፡ ልጃገረዷ ለሽማግሌው የተለየ ክብር በመስጠት መደረግ ያለበትን ሁሉ አደገችላቸው፡፡ ሽማሌው የምታደርገውን ሁሉ አይተው "የምታደርጊው ነገር ሁሉ ለራስሽ ነው" በማለት ተናገሩ፡፡ ልጂቷ አእምሮዋ ቅኔና ፈሊጡን ባለመለየቱ "ይህ ሽማግሌ ሊያታልለኝ ነው

እንዴ ለእሱ የማደርገውን ለራስሽ ነው የሚለኝ?” በማለት በመጥፎ ጎን አሰበችው፡፡ ቀና አስተሳሰቧንም ቀይራ በሌሊት በመነሳት ጧት የሚበሉት የቅቤ ጭብጦ፣ በመንገድ ላይ የሚበሉት የመርዝ ጭብጦ አሰናዳች፡፡ ባዘጋጀችላቸውም መሰረት የመርዝ ጭብጦውን በስንቅ መያዣቸው ውስጥ አስገባችላቸው፡፡

ሽማግሌው ሲሄዱ ውለው እኩለቀን ላይ ከአንድ ዛፍ ስር አረፍ ብለው ያንን የመርዝ ጭብጦ ሊበሉ ሲሉ መርዙን ጨብጣ የሰጠቻቸው ልጅ ወላጆች ወደሽማግሌው ተጠግተው “እባክህ ትተኸን አትብላ፡፡ ለፈጣሪ ብለህ ለእኛም ስጠን፡፡ ከቤታችን ከወጣን 7 ቀናችን ነው” በማለት ሲናገሩ ሽማግሌው ሆዳቸው አዘነና ምንም ሳይቀምሱ ሙሉ በሙሉ ሰጥተዋቸው ሄዱ፡፡ እነርሱም የመርዙን ጭብጦ እንደበሉ ወዲያውኑ በከፍተኛ ህመም ተያዙ፡፡ እንደምንም ብለው ነብሳቸው ሳትወጣ ከቤታቸው ደረሱ፡፡ ልጃቸውም በመጨነቅ “እናቴ! አባቴ! ምን ሆናችሁ ነው?” በማለት ጠየቀቻቸው፡፡ እነርሱም “አንድ ሽማግሌ የመርዝ ጭብጦ ሰጥቶን ሳናውቀው በልተን ነው” አሏት፡፡ አስከትለውም “እኛ መሞታችን አልቀረምና ጠንክሩ፣ሰው ሁኑ” በማለት የኑዛዜ ቃላቸውን ከሰጧት በኋላ ከዚህ ዓለም በሞት ተለዩ፡፡ ልጂትም፡-

ቀኑንም አልቅሼ ልድገመው ሌሊቱን፣

እንዲህ ይጎዳል ወይ ስራ ባለቤቱን፡፡ በማለት ሃዘኗን ገለጠች ይባላል፡፡ (አበበች ሙላት፣ ቦረና፣ ግንት 2008)፡፡

## ተረት 48

በአንድ ዘመን በአንድ አገር ውስጥ በአንድ አካባቢ አብረው የሚኖሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ነበሩ፡፡ ከልጅነታቸው ጀምረው አብረው በማደጋቸው ምክንያት የነበራቸው ፍቅር በጣም የሚያስቀና ነበር፡፡ ዕድሜያቸው እየጠነከረ ሲሄድ ወደከተማ ሄደው ለንጉስ ለማደር አሰቡ፡፡ ከቤተሰቦቻቸውም ጋር ተማክረው ጉዟቸውን ወደከተማ አደረጉ፡፡ ያሰቡትም ተሳካላቸውና ሴቷ ለንጉሱ ምግብ አዘጋጅ፣ ወንዱ ደግሞ ምግብ አቅራቢ ሆነው ተመደቡ፡፡ ስራቸውንም በጥሩ ሁኔታ እያከናወኑ ለብዙ ዘመን ቆዩ፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላ ግን ሴቷ በጓደኛዋ በመቅናቷ ባህሪዋ ሙሉ በሙሉ እየተቀየረ መጣ፡፡ “የንጉሱ ምግብ አቅራቢ ብሆን የተረፋቸውን እየበላሁና እየጠጣሁ ያንን በልቼና ጠጥቼ መልኬ እንደፀሐይ ሲያበራ ንጉሱ ሚስት አድርጎ ያኖረኛል” በማለት አሰበች፡፡ ይህንን ፍላጎቷን ለማሳካት የራሷን መላ አበጀች፡፡ ወደንጉሱ ሄዳ “ጌታዬ! የቀጠሩት ምግብ

አቅራቢ የንጉሱ አፍ በጣም ይሸታል፤ ስለዚህ እኔ ምግብ ይዤ ስሄድ አፉን በመሃረብ ይሸፍን" ብሏል በማለት ነገሯን ሰካች፡፡ ከዚያም ወደጓደኛዋ እንደተመለሰች "ንጉሱ አፍህ ሸቷል፤ ስለዚህ ምግብ ይዘህ ወደእኔ ስትመጣ አፍህን በመሃረብ ሸፍን" ብለውሃል በማለት ሁለቱን ለማጣላት አመቻቸች፡፡ ንጉሱም እንደንጉስነታቸው ነገሩን በጥልቀት ለማየት ፈለጉና ዝም ብለው ሲከታተሉ ምግብ አቅራቢው አፉን በመሃረብ ሸፍኖ ምግብ ይዞ ቀረበ፡፡ ንጉሱም የተነገረው ነገር ትክክለኛ እንደሆነ አመነና በልቡ የሞት ፍርድ ፈረደበት፡፡ ምግብ አቅራቢውን ግን ምንም አላለውም፡፡

በማግስቱ ንጉሱ ሩቅ ላለ ሰራዊታቸው መልዕክት አስተላለፉ፡፡ መልዕክቱም "መጀመሪያ ተልኮ የሚደርሰውን ሰው በበርሚል ውሃ አፍልታችሁ ራሱን ወደታች እግሩን ወደላይ አድርጋችሁ ጨምሩት፡፡ ሁለተኛ ላይ ተልኮ የሚመጣውን ሰው ደግሞ የመጀመሪያውን ሰው እንዴት አድርጋችሁ እንደገደላችሁት ዝርዝር ሁኔታውን አስይዛችሁ እንዲትልኩልኝ" የሚል ነበር፡፡

ውሳኔውም ይፈጸም ዘንድ ንጉሱ ምግብ አቅራቢውን በማለዳ ወደሰራዊታቸው መልዕክት አስይዘው በዘዴ ላኩት፡፡ ያ ምግብ አቅራቢም በማያውቀው ነገር ወደመሞቻው ቦታ ገሰገሰ፡፡ የንጉሱን ትዕዛዝ ባሉት መንገድ ፈጽሞ መመስገን ስለፈለገ በፍጥነት ይጓዝ ነበር፡፡ ሆኖም ግን በጣም ደከመውና ከአንድ ዛፍ ስር አረፍ እንዳለ በዚያው እንቅልፍ ወሰደው፡፡

የምግብ አቅራቢውን አሟሟት አይታ እንዲትመጣ የተላከችው ምግብ አብሳይ ከኋላ ተልካ ኖሮ ስትገሰግስ ቆይታ ከሟቹ ቀድማ ደረሰች፡፡ እንደደረሰችም "እስካሁን ምን አቆየሽ?" ሲሏት "እኔ አይደለሁም ከፈላ ውሃ ውስጥ የምገባው" አለች፡፡ ለእነርሱ ግን የደረሳቸው ደብዳቤ መጀመሪያ የመጣውን ሰው የፈላ ውሃ ውስጥ እንዲገባ፣ ሁለተኛ የመጣው ሰው አሟሟቱን አይቶ እንዲመለስ የሚል ስለነበር የፈጣሪና የንጉስ ትዕዛዝ አይሻርም በማለት ትዕዛዛቸውን ፈጸሙ፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ምግብ አቅራቢው ደርሶ የአሟሟቷን ሁኔታ ይዞ ለንጉሱ አቀረበ፡፡

ነጉሱ እንዲገደል የላኩት ምግብ አቅራቢያቸው በህይወት መመለሱ ገርሟቸው "ጓደኛህ ስለ እኔ ምን ትልህ ነበር?" በማለት ጠየቁት፡፡ እሱም "ምንም አትለኝም፤ ነገር ግን ምግብ ሳቀርብልዎት አፌ እንዳይሸትዎት በመሃረብ እንዲሸፍን ትዕዛዝ ሰጥታኛለች" በማለት መለሰላቸው፡፡ ንጉሱም "እኔ ትክክለኛ ፍርድ ባልሰጥም የሰማይ አምላክ

ትክክለኛውን ፍርድ ሰጥቷል፡፡ አንተ የዋህ ሰው ነህ፡፡ ከአሁን በኋላ ከእኔ ጋር በቤተመንግስቴ ትኖራለህ" በማለት አነገሱት ይባላል (አስቴር ተከስተ፣ ተሁለደሬ፣ ነሐሴ 2007)፡፡

### ተረት 49

በድሮ ጊዜ ባልና ሚስት በአንድ ቤት ውስጥ ተጋግዘውና ተባብረው ይኖሩ ነበር፡፡ ታዲያ ሚስት አርፋ የማትቀመጥ ነበረችና ውሽማ ይዛ ፍላጎቷን ትፈጽም ነበር፡፡ ባልም ይህንን ነገር ሰማና እውነትነቱን አረጋገጠ፡፡ ከዚያም የሚስቱን ውሽማ የሚበቀልበትን ዘዴ ማውጠንጠን ያዘ፡፡ የፈጠረውም መላ አይኔ ጠፋ ብሎ ከቤት መዋል ነበር፡፡ እናም ከቤት መዋል ያዘ፡፡ ሚስትም የባሏን ዓይን መጥፋት አምና የወንዱንም የሴቱንም ስራ ከቤት ከውጭ እያለች መስራት ጀመረች፡፡ ውሽማዋንም በግልጽ ከቤቷ እያመጣች ከባሏ ፊት ለፊት ታስቀምጠው ነበር፡፡ ባልም ያላየ እየመሰለ ዝም ይላል፡፡

ባል አንድ ቀን ወንድ ልጁን ጠራና "መሳሪያዬን አምጣልኝና ልወልውለው" አለው፡፡ ልጁም ጠመንጃውን አመጣለት፡፡ አባት ልጁን ከጎኑ አስቀመጠና "ደማም ልጅና መሳሪያ ሲወለውሉት ይወዳል" አለና ምን ምኑ እንደሚወለወል ለልጁ አሳየውና መሳሪያው ተወለወለ፡፡ ከዚያም "ልጄ ና አተኳኮሱን ላስተምርህ" ብሎ የተቀባበለውን ጠመንጃ አፈሙዝ ፊትለፊቱ ወደተቀመጠው የሚስቱ ውሽማ አነጣጥሮ "በል ተኩስ! ምላጩን ሳበው" አለው፡፡ ልጁም የታዘዘውን ፈጸመ፡፡ የተተኮሰው ጥይት ከነመረቁ በውሽሜ ደረት ላይ ተቀረቀረበት፡፡ ሚስትም ውሽማዋን ብላ ጮኸች፡፡ ጎረቤት ተሰበሰበ፡፡ ባል ለምን ይህንን አደረግክ ተብሎ ሲጠየቅ "እኔ ምን ላድርግ! አይኔ አያይ፡፡ በዚያ ላይ እሷ ሰው አለ አትለኝ እሱ እንዴት ዋልክ አይለኝ" አለ ይባላል (አገሪቱ ጌትነት፣ ቦረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

### ተረት 50

ሁለት የትዳር ጓደኛሞች ነበሩ አሉ፡፡ ባንድ ላይ ሲኖሩ ሚስት እንደሴተኛ አዳሪ በባሏ ላይ ሌላ ወንድ ትይዛለች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ከውሽማዋ ጋር ምክር አደረጉና ባልዮውን ያታልላሉ፡፡ ይህም ውሽማው ሴት መስሎ የሴት ልብስ ለብሶ ለሚስትዮዋ እህት ሆኖ ይመጣል፡፡ እሷም እህቴ መጣች በማለት በድንብ አስተናግዳ መኝታዋን ታዘጋጃለች፡፡ የመኝታ ሰዓት ሲደርስ ለባሏ "ዛሬ ከእህቴ ጋር ስጫወት አድራለሁና አንተ

ብቻህን ተኛ” ትለዋለች፡፡ የዋሁ ባልም እህቷ ጋር ስትጫወት ትደር በሚል ብቻውን ያድራል፡፡

በዚህ ሁኔታ ብዙ ከሰነበቱ በኂላ አንድ ቀን ሚስት ገበያ ልትሄድ ትነሳለች፡፡ ለውሽማዋም “አንቺ እዚሁ ጠብቂኝ! እኔ ገበያ ሄጀ ልምጣ” በማለት ተሰናብታ ትወጣለች፡፡ ባልዮውና ሴት የሆነው ውሽሜ አንድ ላይ እቤት ውስጥ ቁጭ ይላሉ፡፡ ባል ከሚስቱ ጋር አብሮ ሳይተኛ ብዙ ቀናትን አሳልፏልና የሚስቱን እህት ብቻዋን ሲያገኛት ጊዜ ዘሎ እንቅ ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ ወንድ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ውሽሜም “ተነቃብኝ ሳይገድለኝ ላምልጥ” በማለት እግሬ አውጭኝ ብሎ ይፈረጥጣል፡፡ ነብሱ መለስ ሲልለት ውሽማውን መንገድ ላይ ይጠብቃትና “ባልሽ ወንድ መሆኔን አረጋግጧልና እንዳይገድልሽ፤ እኔ ነብሴን አምልጫለሁ” በማለት ነገራት፡፡ እሷም የሴት መላ ይስጥህ እንደሚባለው ከቤቷ አካባቢ ስትደርስ “ጉድ እኔ! ጉድ እኔ!” እያለች ከቤቷ ገባች፡፡ ባለቤቷም በድንጋጤ “ምን ሆንሽ?” አላት፡፡ እሷም “እህቶቼ ሁላ ወንድ መሆናቸውን ዛሬ በገበያ ላይ መላክተኛ ነገረኝ” አለችው፡፡ እሱም “እዚህ የነበረችውም እህትሽ አብቅላ በርራ ጠፍታልሻለች” አላት፡፡ በእንዲህ ዓይነት መልኩ መሰሪዋ ሚስት የዋሁን ባሏን አታለለችው ይባላል (ብሬ አያሌው፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)፡፡

**ተረት 51**

በድሮ ጊዜ አንድ ላይ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ከድህነታቸው በስተቀር ሁለቱም ባንድ ላይ ሲኖሩ በጣም ይዋደዱ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባል በችግር ምክንያት ወደሌላ ሃገር ስራ ለመስራት ሄደ፡፡ ሚስቲቱም ባሏ ከሄደበት አይመለስም በሚል ግምት የጎረቤት ውሽማ ያዘች፡፡ ውሽማውም ማታ ማታ ሰው ሳያየው ተደብቆ እየገባ ማደር ጀመረ፡፡ ከትንሽ ጊዜ በኂላ መቼም ሰማይ ያየውን ነገር ሰው ሳያየው አይቀርምና ባልየው ሚስቱ ውሽማ እንደያዘችበት ሰማ፡፡ እሱም እውነቱን ለማረጋገጥ አንድ ቀን ምሽት ላይ የቆሎ ተማሪ መስሎ እቤቱ ሄደ፡፡ እንደደረሰም “ስለ ቤዛዊት ዓለም” ብሎ ለመና ቆመ፡፡ እሷም ቁራሽ እንጀራ ሰጠችው፡፡ የቆሎ ተማሪውም ቁራሹን ተቀብሎ “ስለመሸብኝ ነው እባካችሁ አሳድሩኝ” ብሎ እየጠየቀ ሳለ ውሽማው በተለመደው ሰዓት መጣ፡፡ ከዚያም ”ተሜ! ማደሪያ እንኳን የለኝም” አለችው፡፡ ውሽሜም ጭራሹኑ ባለቤት ሆኖ “ቤት የእግዜር ነው ተይው ይደር!” አላት፡፡ በዚህ ሁኔታ የቆሎ ተማሪው ወደቤት ገባ፡፡ ውሽምየው፣ “ተሜ! እንዲያው ለመሆኑ ስምህ ማን ይባላል?” አለው፡፡ እሱም

"አሳሩ ማታ እባላለሁ" አለው፡፡ እሱም "አሳሩ ማታ አለችህ! አይ እናት" እያለ ስሙን ከግራ ጉንጩ ወደቀኝ፣ ከቀኙ ወደግራ እያለ በመገረም ሲያላምጥ ቆየ፡፡

እራት ተበልቶ እንዳለቀ ሴትዮዋና ውሽማዋ አልጋው ዘልቀው ተኙ፡፡ ተሜም ትንሽ ቁርበት ተሰጠውና ወለል ላይ ተኛ፡፡ ግማሽ ሌሊት ላይ ሁለቱም በድካም ጭልጥ ያለ እንቅልፍ እንደወሰዳቸው ካረጋገጠ በኋል በያዘው ሳንጃ የውሽማውን አንገት ቆርጦ ጭንቅላቱን እድፍድፉ ጋን ውስጥ ከተተውና ተመልሶ ተኛ፡፡ ሴትዮዋ ከእንቅልፏ ስትነቃ የሰውየው ደም አልጋውን አልፎ ቤቱን አጥለቅልቆት ስታይ በጣም ደነገጠችና "ተሜ! ተሜ!" ብላ ተጣራች፡፡ ተሜም "አቤት! ምን ሆንሽ?" አላት፡፡ "ይሄ ሰው ማታ አንገት የለውም ነበር እንዴ?" አለችው፡፡ እሱም "ኸረ ያለው መስሎኝ ነበር የለውም እንዴ?" አላት፡፡ እሷም "ኸረ አንገቱ ተቆርጧል" አለችው፡፡ እሱም" እዚህ አካባቢ ጠበኛ አለው እንዴ?" ሲል ጠየቃት፡፡ "አዎ ከጎረቤትማ ጠበኛ አለው" ስትለው "እንግዳውማ እነሱ ገድለውት ይሆናል" አላት፡፡ "ታዲያ ምን ይሻለኛ?" ስትል ጠየቀችው፡፡ እሱም "እጠበኞቹ በር ላይ እንጣለው" ሲል ምክር ሰጣት፡፡ ከዚያም በምንጣፍ ጠቅልለው እጠበኞቹ በር ላይ ጣሉት፡፡ ተሜም በጠዋት ተነስቶ ወደነበረበት ተመለሰ፡፡ በማግስቱ ወደቤቱ ተመለሰ፡፡ ሚስቱም በደስታ ተቀበለችው፡፡ እሱ ግን ስራዋን ሁሉ ስላወቀ የሚያወራት ከልቡ አልነበረም፡፡ የመጣ ቀን ምሽት ላይ ሚስቱን "አሁን ሁለት ምርጫዎች እሰጥሻለሁ፡፡ ወይ ህይወትሽን ማጣት አለበለዚያ ላትመለሽ ከሃገር መጥፋት" አላት፡፡ "ምነው?" ስትለው "አሳሩ ማታ ማለት እኔ ነኝ" አላት፡፡ በዚሁ እንደ ውሃ ሽታ ብን ብላ ካገር ጠፋች፡፡ እሱም ሌላ ሚስት አግብቶ በሰላም ኖረ ይባላል (አምሳል ይላቅ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

### ተረት 52

በድሮ ጊዜ አንድ ሃብታም ሰው ነበር፡፡ ይህም ሃብታም አንድ ወንድ ልጅ ብቻ ነበረው፡፡ ከዚህ በኋላ ብዙ ጊዜ ወንድ ልጅ ለመውለድ ሞክሮ ሳይሳካለት ይቀራል፡፡ እሱ ያልተሳካለትን በልጁ ለማግኘት በሚል ልጁ ለአቅመ አዳም እንደደረሰ ቢጤውን ፈልጎ አጋባው፡፡ በጋብቻውም ቀን አባቱ ጠመንጃና ሽጉጥ ሸለመው፡፡ ባገባ ባመቱ ሴት ልጅ ወለዱ፡፡ ሆኖም ግን ሴት ልጅ በመወለዷ ምክንያት አልተደሰቱም ነበር፡፡ በሁለተኛውም ዓመት ሌላ ሴት ልጅ ተወለደች፡፡ ቤተሰቡ በሙሉ አኮረፈ፡፡ ልጁ ሚስቱን "ጎሽ የኔ ቆንጆ! በሴት ልጅ አከበርሽኝ" ሲል በአሽሙር ጠቅ አደረጋት፡፡ የልጁ አባት ከመበሳጨትም አልፈው ምን ማድረግ እንዳለባቸው አሰቡ፡፡ "እንግዲህ ምን ባደርግ

ይሻለኛል? የተወለዱት በሙሉ ሴቶች ሆኑ። ቀዬዬ ብቻውን ሊቀር ጭር ሊል ነው። ፈላሚ ማጣትስ ውርደት አይደለም እንዴ!" እያሉ ሲያሰላስሉ ከቆዩ በኋላ አንድ ዘዴ ብልጭ አለላቸው። ይህም ያገሩ ሰው እንደሚያደርገው ስለት መሳል ነበር።

በዚሁ መሰረት ልጃቸውን ጠርተው "እነዚህ ልጆች ሴቶች ሆኑ። ሴት ልጅ ወደ ባሏ እንጂ ወደ እናትና አባቷ አትቀርብም። ቀየ የሚደምቀው በወንድ ልጅ ነው። ከነተረቱ 'ከብት ዘሩ ሊጠፋ ሲል ወንድ ወንድ ይወልዳል። ሰው ዘሩ ሊጠፋ ሲል ሴት ሴት ይወልዳል' ይባላል። ስለዚህ እትልቁ አድባር ሂድና ተሳል" በማለት ይመክሩታል። ልጁም የተባለውን ያደርጋል። ይህንን ባደረገ ባመቱ ወንድ ልጅ ይወልዳል። እንዲሁ በሁለተኛው ዓመት ሌላ ወንድ ልጅ ይወልዳል። በዚህም ቤተሰቡ በሙሉ አባትዮውን ጨምሮ ደስ ይላቸዋል። በዚህ መሃል አባት ልጃቸውን ጠርተው "ስታገባ የሸለምኩህ ጠመንጃና ሽጉጥ ላንተ ሳይሆን ወንዶች ልጆች ስትወልድ እንዲትሰጣቸው ተመኝቼ ነው። ጠመንጃና ሽጉጥ ወንድ ልጅ ማለት ነው" አሉት ይባላል (አረጉ እብሬ፣ ተሁለደሬ፣ ነሐሴ 2007)።

## ተረት 53

በድሮ ጊዜ አንድ ባልና ሚስት በአንድ ቤት ውስጥ ይኖሩ ነበር። ሲኖሩ ሲኖሩ ከእለታት አንድ ቀን እንደ ጎረቤቷ ውሽማ መያዝ አማራትና እንደምንም ብላ አግባብታ ያዘች። ከዚያም በኋላ ባሏን ከቤት አስወጥታ ከውሽማዋ ጋር ለማደር ዘዴ መዘየድ ጀመረች። በዘዳቸውም መሰረት ከውሽማዋ ጋር ተመካከረችና አዙጥ የሚባል በሽታ ስለመጣ ወንዶችን እቤት ካገኘ እንደማይለቅ እንድትነግረው ተስማሙና ወደቤቷ ተመለሰች። በስምምነታቸው መሰረት የበሽታውን አስከፊነት እየጨማመረች ለባሏ ነገረችው። ባልም በሁኔታው በመደናገጥ "ታዲያ ምን ይሻለኛል?" በማለት ለሚስቱ አማከራት። እሷም በበኩሏ በሽታው እቤት ውስጥ ካገኘ እንደማይለቅ አስረግጣ ነገረችውና እራቁን በልቶ ከቤት እንዲወጣ አስጠነቀቀችው። "አዙጥ" የሚል ድምጽ ከሰማህ በፍጥነት ወጥተህ ሂድ አለችው። አቶ ባልም ራቱን በልቶ ሳይጨርስ በምክክራቸው መሰረት ውሽሜ "አዙጥ" የሚል ድምጽ በበር በኩል አሰማ። በዚህ ጊዜ ደነገጠና ተንቀጠቀጠ። ሚስት የከብቶች እበት እየተገፋ በሚወጣበት ቀዳዳ (መንጎል) ሾልኮ እንድወጣ ነገረችው። በመንጎሉ ሾልኮ ሊወጣ እንዳጎነበሰ በትርኳሽ ቂጡን ለመጠጠችው። አቶ ባል እየታገለ እንደምንም ሾልኮ ከዚያ ግድም ጠፋ። ሚስትም የወደደችውን ውሽማ ይዛ አደረች። ጧት አቶ ባል ብርድና ቁር ሲፈራረቅበት አድሮ ከቤቱ ደረሰ። ከሚስቱ ጋር ሰላምታ

ከተለዋወጡ በኋላ ስለአስተዳደሩ ጠየቀችው፡፡ ባልም በበኩሉ "አንድ ጊዜ ቢያዞጠኝ ቂጤን ለመጠጠኝ" አላት ይባላል፡፡ (በዛብህ እንድሬ፣ ቦረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

**ተረት 54**

በድሮ ጊዜ አንድ አንበሳና አንዲት ዝንጀሮ ተጋብተው አብረው ይኖሩ ነበር፡፡ አብረው ሲኖሩ ልጅም ወለዱ፡፡ አንበሳውም ሚስቱ ስትወልድ አልጋ ሰርቶ ማረስ ጀመረ፡፡ ከእለታት አንድ ቀንም ለማረሻ የሚሆን ምግብ ፍለጋ ወደ ጫካ ሄደ፡፡ አንድ መሄዱን ያየ ግመር ዝንጀሮ ወደአንበሳው ቤት እየተንጎማለለ ሄደ፡፡ ከቤቱ አጠገብ እንደደረሰም "እዚህ ቤት!" አለ፡፡ የአንበሳው ሚስትም ከቤት ውስጥ ሆና "አቤት!" አለች፡፡ "አያ አንበሶ የለም እንዴ?" አለ፡፡ "የሉም" አለችው፡፡ ዝንጀሮ "የእኔና የእሱ ወንድነት ዛሬ ይለያል ብየ ነበር" አለ፡፡ "ይግቡ ማነሁ? አሁን ወጣ ብለው ነው" አለች አራሷ ዝንጀሮ፡፡ ዝንጀሮውም ገባና ቁጭ አለ፡፡ የአንበሳውም ሚስት "ጥያቄ ባቀርብልሁ ቅር ይልኋል?" አለችው፡፡ ዝንጀሮም "ምንም ችግር የለም ጠይቂኝ" አለ፡፡ እሷም "ለመሆኑ የቀድሞ ስራዎ ምን ነበር?" አለችው፡፡ "ወታደር" አለ፡፡ "ዓይንዎ የጎደጎደው ምን ሆኖ ነው?" በማለት ጥያቄዋን ቀጠለች፡፡ "ጥይት ተኳሽ ስለሆንኩኝ የማነጣጣርበት ነው" ብሎ መለሰ፡፡ "ጣትዎ የሰለሰለውስ" ብላ ስትጠይቀው "ምልጭ የምስብበት ነው" ብሎ መለሰ፡፡ "ቂጥዎ የተመለጠውስ?" ስትለው "ፈረስ ጋላቢ ስለሆንኩኝ ነው" አለ፡፡ በመጨረሻም "ደረትዎ የተመለጠውስ?" በማለት ስትጠይቀው "ይሄማ ሰደፍ የማስደግፍበት ነው" በማለት መለሰላት፡፡ ዝንጀሮዋ በጣም በመገረም፣ ባሏንም በልቧ በመናቅ የሚበላ ጥሩ ምግብ ሰጠችው፡፡ በልቧም የእኔ ባል ቢሆን ብላ ተመኘች፡፡ በዚህም አልቀረች እንደምንም አግባብታ አብራው ተኛች፡፡ ዝንጀሮው የልቡን አድርሶ የቀረበለትን ጥሩ ምግብ በልቶ ወደመጣበት ተመለሰ፡፡

ከትንሽ ጊዜ ቆይታ በኋላ አቶ አንበሳ ከሄደበት ተመለሰ፡፡ እንደመጣም ሚስቱ ጥቅጥቅ ብላ አኮረፈችው፤ ጀርባዋን ሰጠችው፡፡ አቶ አንበሳም "ምን ሆነሽ ነው ያኮረፍሽን?" ሲል ጠየቃት፡፡ እሷም በመቆጣት ስሜት የዝንጀሮን የጀግንነት ታሪክ ከነገረችው በኋላ "አንተ ደግሞ ምን ወንድ ነህ? ጎበዞቹ ምላጭ የሚስበቡበት የጣታቸው መሰልሰል፣ የሚያነጣጥሩበት የዓይናቸው መጎድጎድ፣ ሰደፍ የሚያስደግፉበት የደረታቸው መመለጥ፣ ፈረስ የሚጋልቡበት የቂጣቸው. . . ኸረ ስንቱ" አለችው፡፡ አንበሳው "ከእኔ በላይ ማነው ጀግና!" አለና ተናደደ፡፡

የለመደች ጦጣ ሁልጊዜ ሽምጠጣ እንዲሉ አቶ ዝንጀሮ በማግስቱ የአንበሳውን መሄድ ሳያይ አንበሳው ቤት ከተፍ አለ፡፡ ከበር ሲደርስም "እዚህ ቤት" አለ፡፡ የአንበሳውም ሚስት "አቤት!" አለች፡፡ እንደለመደው "አያ አንበሶ የለም?" አለ፡፡ አያ አንበሶም "የለም በይው" አለ ተደብቆ፡፡ ሚስቱም "የሉም" አለች፡፡ "ግባ በይው" አላትና "ግቡ" አለችው፡ አቶ ዝንጀሮም እየተከመረ ከቤት ገብቶ ቁጭ እያለ "የእኔና የእሱ ወንድነት ዛሬ ይለያል ብዬ ነበር፡፡ እንዴት ዛሬም አጣዋለሁ?" ብሎ በልበ ሙሉነት ሲናገር አንበሳው ከተደበቀበት ውልቅ አለ፡፡ አቶ ዝንጀሮም መልከት ሲል የአንበሳው ዓይን ይንቀለቀላል፡፡ በዚህ ጊዜ አቶ ዝንጀሮ ውርጭ እንደመታው የዱባ ቅጠል ኩርትምትም አለ፡፡ ራሱንም ስቶ በቅዘኑ ተጨማልቆ ነበር፡፡ አቶ አንበሳም በጣም ተናድዶ ስለነበር በፈርጣማ ክንዱ ያዝ አድረጎ "ዓይንህ ምን ሆኖ ነው የጎደጎደው?" ሲለው "ከገደል ላይ ስለማድር ከአሁን አሁን ወደቅኩ እያልኩ ስለምጨነቅና እንቅልፍ ስለማልተኛ ነው" አለ ዝንጀሮ፡፡ በመቀጠልም "እጅህስ የለሰለሰው ምን ሆኖ ነው?" ቢለው "የምበላው ስለሌለኝ ምድር የምጭርበት ነው" አለ፡፡ ከዚያም "ቂጥህስ የተመለጠው?" ሲለው "ኑሮየ ገደል ለገደል ስለሆነ የምንፏቀቅበት ነው" በማለት መለሰለት፡፡ ያዝ አድርጎ ቀረጣጥፎ ሊበላው ሲል መቼም ሴት የላከው ጅብ አይፈራም እንደሚባለው "በሞቴ አትብላው" ብላ የአንበሳው ሚስት ከሞት አዳነችው፡፡ ከባሏ ከአራዊት ንጉስ በላይ ጎበዝና ጀግና የሌለ መሆኑን ተረዳችው፡፡ ከዚያን ቀን ጅምሮ ለባሏ እጥፍ ከበሬታ አደረገችለት፡፡ ከዚያ በኋላ ዝንጀሮው "ጎፈሬዬን ባበጣጥር ወንድ መስያታለሁ" ብሎ ተመልሶ ወደገደሉ ሄዶ ከቢጤዎቹ ጋር ተቀላቀለ ይባላል፡፡ (አለባቸው ወርቁ፣ ተሁለደሬ፣ ነሃሴ 2007)

## ተረት 55

በድሮ ጊዜ ባልና ሚስት እጅግ ተከባብረው አንድ ላይ ይኖሩ ነበር፡፡ ሚስትዮዋ ማንም የሚመኛት ውብ ስትሆን ባልዮው ደግሞ ጥሩ ሰው የሚባል ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባልዮው ውሎገብ የማይመለሱበት ወደሩቅ አገር ለገበያ ይሄዳል፡፡ ሚስት ይህንኑ አጋጣሚ ተጠቅማ ውሽማዋን ትቀጥራለች፡፡ ለመስተንግዶ የሚሆንም የዶሮ ወጥና ጠላ አዘጋጅታ መጠባበቅ ትጀምራለች፡፡ በዚያን እለት እንዳጋጣሚ ሆኖ አንድ የመሸበት መንገደኛ አሳድሩኝ ብሎ ሚስትዮዋን ይጠይቃል፡፡ ሴትዮዋም ልቧ ፈቃደኛ ባይሆንም ቤት የእግዜር ነው በሚል እንዲያድር ትፈቅድለታለች፡፡ እንግዳው ለየት ያለ ዝግጅት በማየቱና ሁኔታዋን በማጤኑ ይከታተላት ገባ፡፡ የተሰራውን ወጥና የተጠመቀውን ጠላ አየ፡፡ በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ ውሽማው የቀኑን መምሽት ጠብቆ ወደቤት ዘለቀ፡፡ ሆኖም

የተዘጋጀለትን ምግብና መጠጥ ወዲያውኑ ልትሰጠው አልቻለችም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እንግዳው ሰው እንዳይካፈላቸው ከመንፈጓ የተነሳ ነበር፡፡

ይሄ ሁኔታ የገባው ውሽማ ቶሎ ብሎ ወደቆጡ አልጋ ወጣና ተሳፈረ፡፡ ሴትዮዋም እንደነገሩ ለመንገደኛው እራቱን አቅምሳ ውሽማዋን ተከትላ ወደአልጋው ወጣች፡፡ ሴትዮዋ እንደገና ተመልሳ በመውረድ ለመንገደኛው "ቀበኛ ጥጃ አለችና ልብስህን እንዳትበላብህ፤ ከመጣችብህ በዚህ ብትር ምታት" ብላ ብትር ሰጥታው ተመልሳ ወደውሽማዋ ሄደች፡፡

በዚህ ጊዜ መንገደኛው ተንኮል አሰበ፡፡ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ ልቅም አድርጎ መብላትና መጠጣት አሰበ፡፡ እናም ውሽማውና ውሽሚት ጉዳያቸውን ሲጀምሩ እንግዳው ቀስ ብሎ ተነስቶ የዶሮ ወጡንም ጠላውን ልቅም ካደረገ በኋላ ምንም እንዳልነካ ጥቅልል ብሎ ተኛ፡፡ ሴትዮዋ ጉዳይዋን ስትጨርስ ምግቡ ትዝ አላትና ልታመጣ ካልጋ ወረደች፡፡ ድስቱንም ገንቦውንም ብታይ ባዶ ሆኗል፡፡ "ጥጃይቱ ደፍታው ይሆን እንዴ" ብላ ጥጃይቱን ብታሽታት ምንም የለም፡፡ "አይ ይሄ እንግዳ በልቶታል፤ ጠጥቶታል ማለት ነው" ብላ እንግዳውን ቀረብ ብላ ልታሽት ስትጠጋ እንግዳውም ሁኔታዋን ነቅቶ እየጠበቀ ነበርና "ውስ!" ብሎ በተሰጠው አጭር ብትር አፍንጫዋን አላት፡፡ የመታትም እክፉ ቦታ ላይ ስለነበረ በዚሁ ምክንያት ሞተች ይባላል (አሰን ይማም፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

## ተረት 56

ከእለታ አንድ ቀን ከአንዲት ቆንጆ ሴት ወይዘሮ ቤት አንድ የመሸበት እንግዳ ይደርሳል፡፡ በዚያን ሰዓት ምሽት ስለነበረ ሰውየው "እባክዎ እመቤቴ እኔ የመሸብኝ የእግዜር እንግዳ ነኝ፡፡ ከወለልዎ ተኝቼ ልደር" ሲል ጠየቃቸው፡፡ ሴትዮዋም ትንሽ ከፈጣሪያቸው ጋር ከተነጋገሩ በኋላ ፈጣሪያቸውን በመፍራት እሺ አሉት፡፡ የሴትዮዋም ቤት ጠባብና ባለአንድ ክፍል ብቻ ነበረች፡፡ በመሆኑም ካልጋቸው አጠገብ ካለችው ትንሽ መደብ ላይ እንዲተኛ ፈቀዱለት፡፡ ሴትዮዋም ከመደቡ በላይ ካለችው አልጋቸው እንደተኙ የእግዜር እንግዳው ቀስ ብሎ ይነሳና ከሴትዮዋ ጎን ይተኛል፡፡ እሷም ከእንቅልፏ ስትነቃ ትደነግጥና "አንተ የእግዜር እንግዳ ማን አምጥቶ እዚህ አስተኛህ? ጉድ! ጉድ! ጉድ! ይገርማል፡፡ ኧረ ለመሆኑ እዚህ ማን አስተኛህ?" ስትል ጠየቀችው፡፡ ሰውየውም "አይ እሜቴ ተንከባልዬ ነው" ሲላት "አንተ ባለጌ! ሰው ወደታች እንጂ እንዴት ወደላይ

ይንከባለላል” ትለዋለች፡፡ ሰውየውም “እኔም የገረመኝ ወደላይ መንከባለሌ ነው” ብሎ አሳስቆ ከሴትዮዋ ጋር አደረ ይባላል (አለሙ ሰይድ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

## ተረት 57

በድሮ ጊዜ ባንድነት የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ነበሩ፡፡ ባልና ሚስቱ በባህሪያቸው እንዲህ ናቸው የማይባሉ ነበሩ፡፡ አንዳንድ ቀን ፍቅራቸው ገንፎ ያጓርሳል፡፡ አንዳንድ ቀን ደግሞ ጭልጥ ያለ ጠብ ውስጥ ይገቡና ለጎረቤት ያስቸግራሉ፡፡ ይህ በእንዲህ እያለ አንድ የመሸበት እንግዳ አሳድሩኝ ብሎ ይገባል፡፡ ባልና ሚስቱም ፈቃደኛ ሆነው አስገቡት፡፡ እግሩን አጥበው እራቱን አብልተው ጠላ ሰጥተውት እየጠጣ እንዳለ ጠላው ሰውነቱን አሙቆትም እንደሆነ አይታወቅም የገበሬውን ሚስት ያስተውላል፡፡ ሴትዮዋ ሙያን ከመልክና ከስነምግባር ጋር አዋህዶ የሰጣት ድንቅ ነበረች፡፡ እናም እንግዳው ክፉኛ ተመኛት፡፡ “ይህ ኮሳሳ ገበሬ እንዴት ታድሏል” እያለ በውስጡ ይነጋገር ነበር፡፡ እነሱ የሚያወሩትን ጭራሽ አይሰማም ነበር፡፡

በዚህ መሃል ባልና ሚስቱ በወሬ አለመግባባት መጣላት ጀመሩ፡፡ የወትሮው ጭቅጭቃቸው ተጋጋለ፡፡ ባል ንደቱ ቱግ አለና ትርኳሽ አንስቶ መታት፡፡ እሷም እንደሱ ትርኳሽ አንስታ መታችው፡፡ እንግዳውም የእሳት ትርኳሽ አነሳ፡፡ ይህንን የተመለከተው ባል “እኔ ሚስቴን የእሳት ትርኳሽ አንስቼ መታኋት፡፡ እሷም የእሳት ትርኳሽ አንስታ መታችኝ፡፡ አንተ ማንን ልትማታ ነው ትርኳሽ ያነሳኸው?” በማለት ጠየቀው፡፡ እንግዳውም “ወንድሜ ይቅርታ! የቤቱ ሥነሥርዓት መስሎኝ ነው” (ሴት ስትመታ እንጂ ስትማታ አይቶ ስለማያውቅ ገርሞት ሊሆን ይችላል፡፡) አለ፡፡ ባልና ሚስቶቹ “በአሁኑ ሰዓት የሚያጣላ እንጂ የሚገላግል የለም” ብለው በእንግዳው ሳቁና ታረቁ ይባላል (ካሳሁን ዓለሙ፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)፡፡

## ተረት 58

በድሮ ጊዜ አንዲት ውብ ባሏ የሞተባት አንበሳ በሃዘንና በብቸኝነት ተቆራምዳ ትኖር ነበር፡፡ በዚሁ ምክንያት ለበርካታ ዘመናት “ባሌን የሚመስል የለም” እያለች የመጡላትን ባሎች ሁሉ እየመለሰች ትዳር በቃኝ ብላ ትኖር ነበር፡፡ ቢሆንም ለሚስትነት የሚጠይቋት በርካቶች ነበሩ፡፡

እንደተለመደው ከእለታት አንድ ቀን አንድ የዝንጀሮ ግመር ሲያስጠይቅና ሲጠይቅ አንበሲት "እስኪ አካሄዱን አረማመዱን ልየው" በማለት መለሰች፡፡ ያ የዝንጀሮ ግመርም በግርማ ሞገሱ፣ በኩሩ አረማመዱ ገምሸር! ገምሸር! ገምሸር! እያለ አካሄዱን አሳያት፡፡ አንበሲትም በአካሄዱ ተመስጣ ወደደችው፡፡ ሆኖም "ሟች ባሌን እንኳ አይመስልም፤ እስኪ ካላችሁ እሺ ይሁን" ብላ አገባችው፡፡

ባልና ሚስቶቹ አንበሲትና ግመር ዝንጀሮ አንድ ቀን ሌሊት ለአደን ወደ አንድ ሃብታም ገበሬ የከብት በረት ተያይዘው ሄዱ፡፡ ከቦታው ሲደርሱም አንበሲት ለዝንጀሮው "እኔ በረት ገብቼ አንዱን በሬ ጠቅ አድርጌ አስበርግጌ ከበረት ሳስወጣልህ ውጭ ላይ ይዘህ ጠብቀኝ" አለችው፡፡ በሃሳቡ ተስማምተው አንበሲት በሬውን ጠቅ ስታደርገው በሬው በርግጎ ወጣ፡፡ ዝንጀሮ የደነበረውን በሬ ሲያይ የሚገባበት አጥቶ በፍርሃት ቧ…ቧ…ቧ…ቧ… እያለ በሬውን ሳይዘው ቀረ፡፡ አንበሲትም በድርጊቱ በጣም ተናደደችና "አንተ ባሌን ስለማትተካው ፈትቸሃለሁ" ብላ ጥላው ተመለሰች፡፡

በሌላ ጊዜ ደግሞ ይቺኑ የአንበሳ ቆንጆ አንድ "እኔ ነኝ" ያለ ነጭ የዝንጀሮ ግመር ለሚስትነት ሊጠይቅና ሊያስጠይቅ ወደ አንበሲት ቤተሰቦች ዘንድ ሄደ፡፡ ከመልኩ ማማር የተነሳ "ይሄ እንኳን ከሟቹ ባሌ ጋር ይመሳሰላል" አለች፡፡ አባትና እናቷም "ታዲያ እሺ ማለትሽ ነው?" ብለው ጠየቋት፡፡ "እንዲያው መልኩን እንኳ እያየሁ ሟች ባሌን ላስታውሰው እንጂ" በማለት በማግባባት ፈቃዷን ገለጸች፡፡ በዚሁ ጋብቻው ተፈጸመ፡፡

እንደተለመደው አንድ ቀን ሌሊት ለአደን ወደአንድ ጫካ ሄዱ፡፡ በጫካውም ውስጥ አንድ ባለ ሹል ቀንድ ትልቅ አጋዘን ብቻውን ሳር ሲግጥ አዩ፡፡ አንበሲት "እኔ በዚያ በኩል እቀሰቅሰዋለሁ፤ አንተ በዚሁ በኩል ሆነህ ቀድመህ በመያዝ ጉሮሮውን በጥስህ ትጥላለህ" ብላ ትዕዛዝ ሰጥታው ሄደች፡፡ እንዳለችው ከዚያ በኩል ቀድማ ወደ ዝንጀሮው በኩል ስታሯሩጠው አጋዘኑ ቀንዱን ቀስሮ ወደዝንጀሮው ፈረጠጠ፡፡ ዝንጀሮው ያንን የሾለ ቀንድ ሲመለከት እግሬ አውጭኝ ብሎ ዛፉ ላይ ተንጠላጠለ፡፡ በዚህ የተበሳጨችው አንበሳ "አንተ ጅል! ዛላው መልካም" በማለት ተሳድባ ጥላው ሄደች፡፡ ስራውም አልጥማት ስላለ ቶሎ ፈታችው፡፡

ያለ ትዳር መኖሯን የጠሉት ቤተሰቦቿ "እባክሽ አንዱን ያዝና ትዳርሽን መስርች" አሏት አባቷ በልመና፡፡ እናት ጣልቃ ገባችና "የሚሆናትን እስከምታገኝ ድረስ ማግባት መፍታቷ የማይቀር ነው፤ ያ ከሚሆን የሚስማማትን እስከምታገኝ ድረስ ብትታገስ

አይሻልም?” አለች፡፡ ባልዮው በቁጣ “ኤዲያ! አንቺ ደግሞ የራስሽን ይዘሽ! ባል የሌላት ሴትና አጥር የሌለው ቤት ደፋሪው ብዙ ነው፡፡ ምንም ይሁን ማግባቱ ይሻላል” አለ፡፡ በዚህ ሁኔታ ባል አልመጣላት ብሎ ብዙ ቆየች፡፡

ከእለታት አንድ ቀን አቶ ነብር የአንበሲትን ብቸኝነት አይቶ ለሚስትነት ሊጠይቅ ወደ አንበሲት ቤተሰቦች መጣ፡፡ ቤተሰቦቿ እሽታቸውን ገልጸው ግን በየጊዜው መደገስ ስለሰለቻቸው “ዝም ብለህም ቢሆን ትወስዳታለህ” አሉት፡፡ አንበሲት ግን ፈቃደኛ አልሆን አለች፡፡ እንዲያውም “ደግሞ ይህንን ለባቃ አካሄዱ የማያምር ላገባ ነው እንዴ?” በማለት አይሆንም አለች፡፡ ነገር ግን ባባቷ ተጽዕኖ ምክንያት እንዲታገባ ሆነ፡፡

ከተጋቡ በኋላ እንደቀድሞው ሌሊት አደን ሄዱ፡፡ አንድ በከብቶች የተሞላ ትልቅ በረት አገኙ፡፡ እንደልማዷ “ከበረት ገብቼ የማስወጣልህን ኮርማ በሬ ውጭ ጠብቀህ አንገቱን ጠምዝዘህ ጠብቀኝ” አለችው፡፡ ነብሩም ከበረት የወጣለትን ትልቅ በሬ ብዙም ሳይርቅ በመያዝ አንገቱን ጠምዝዞ፣ ቀንዱን ከመሬት ቸክሎ በፉከራ እያጉራራ ጠበቃት፡፡ አንበሲትም “ዛሬ ነው ባሊቱን ያገኘኋት” በማለት እያመሰገነች በስጋ ኖረች ይባላል (ጌታቸው ገሰሰ፣ ኩታበር 2008)፡፡

### ተረት 59

በድሮው ዘመን በአንድ ቤት ውስጥ ባል፣ ሚስትና ልጅ ሆነው የሚኖሩ ዝንጀሮዎች ነበሩ፡፡ ባል ለሚስቱና ለልጁ ሳይጨነቅ ለብቻው በመሄድ ሲበላ ውሎ ይመለስ ነበር፡፡ እናትና ልጅም እሱን ሳይጠብቁ ያገኙትን በመቅመስ ይኖሩ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ባል በተራው የሚበላው ሳያገኝ በባዶ ሆዱ ወደቤቱ ይመለሳል፡፡ እናትና ልጁ ቤት ዘግተው በመጥፋታቸውና ቤት ውስጥ ምግብ ባማግኘቱ ተቆጥቶ ነበር፡፡ እናትና ልጅ በአንጻሩ የባቄላ እሸት አግኝተው እስኪጠግቡ በልተው በደስታ ወደቤታቸው እየተመለሱ ነበር፡፡ እናትና ልጅ እየተሳሳቁ ሲመጡ እበር ላይ ጉልት ብሎ ሲመለከቱት ማኩረፉን ተረዱት፡፡ ሚስቱ ድሮ አንድ ቀን እሷ እየራባት ብቻውን የበላው ነዶ ትዝ ይላታል፡፡ ሆኖም እንደደረሱ ሁለቱም ሰላምታ አቀረቡለት፡፡ ምላሹ ግን ዝምታ ነበር፡፡ ልጁ አባቷን ለማነጋገር ያልሞከረችው ነገር አልነበረም፡፡ ልጅ የምታደርገው ብታጣ፡-

እዚያ ማዶ ያለ ባቄላ፣
ሲፈለፍሉት እጅ ይሞላ፣
ሲቅሙት አፍ ይሞላ፡፡

በማለት በግጥም የባቄላውን ሁኔታ ስትገልጽለት ፈጠን ብሎ "ወየታ!" አለ፡፡ "እዚያ ማዶ" አለችው፡፡ "ተነሱ እንሂድ" አላቸው፡፡ ሚስቱም "የእህሉ ባለቤት በጣም ክፉ ነው፡፡ ውሻም አለው" አለች፡፡ ልጂትም "ኧረ አባቴ ይገድሉናል!" አለች፡፡ እሱም "እኔ አባትሽ አንድ ጊዜ ቡ! ብልበት ገደል ነው የሚገባው" አላቸው፡፡ ፉከራው እውነት መስሏቸው ተያይዘው ሄዱ፡፡ መብላት እንደጀመሩ ባለቤቱ ውሻና መሳሪያ ይዞ ያደባ ጀመር፡፡ ልጅ "ኧረ አባቴ ውሻ ውሻ እርሳስ እርሳስ ሸተተኝ" አለች፡፡ "ዝም ብለሽ ብይ! ጠግበሽ እንደሆነ ለጦመኛ ፈልፍይ!" አላት፡፡ ያሩን ሳይጨርስ በጥይት ልቡ ላይ ተመታ፡፡ አራት እግሩ ሽቅብ ቆመ፡፡ ሚስት ጓዴ! ጓዴ!፣ ልጅ አባቴ! አባቴ! እያሉ ወደቤታቸው ተመለሱ፡፡

ጎረቤቶቹ ሞቱን ሲሰሙ ማልቀስ ጀመሩ፡፡ ሞቱ ለዘመድ ሁሉ ተነግሮ በማግስቱ ቀብር ሆነ፡፡ አስከሬኑ ወደቀብር ሲሸኝ በየቦታው ሙሾ ይወርድ ነበር፡፡ በሙሾው መሃል ሚስትም፡-

እንኳን ጥይትና ይፍላብህ በረዶ፣
አላቀመስከኝም ከሰረቅከው ነዶ፡፡

አለች፡፡ ልጅም እናቷን ከተል አድርጋ

እንኳን ላንቺ ሚስቱ
አላቀመሰኝም ለእኔ እንኳን ለልጁ፣
አሳዘነኝ እንጂ ቢንቀረፈፍ እጁ፡፡

በማለት አለቀሱ ይባላል፡፡ (ጋሻው ጮረቅ፣ ቦረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

## ተረት 60

በድሮ ጊዜ በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ሚስቲቱ በጣም ያማረችና የተዋበች ነበረች፡፡ ባልዮው ግን መልከ ጥፉ ነበር፡፡ የጎረቤት ሴቶችም የመልካቸውን አለመመጣጠን በግልጽም በአሽሙርም ይነግሯት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ ባሏን እየጠላችው መጣች፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በተኛችበት ይህንኑ ስታሰላስል ቆይታ ድንገት በጣም ጩሃ ከመኝታዋ ተነሳች፡፡ ባሏም ደንግጦ በመነሳት "ምን ሆንሽ የኔ ቆንጆ?" ብሎ እጇን ያዛት፡፡ እሷም "ህልም አየሁ" ብላ ተንቀጠቀጠች፤ ተንዘፈዘፈች፡፡ አሁንም ደግሞ ደጋግሞ "ምን ሁነሽ ነው?" ብሎ ጠየቃት፡፡ "አንድ ቀንድ ያለው ሰይጣን መጥቶ ደህናይቱ ቆንጆ ተበላሸሽ፤ 'ከዚህ ጉንፋን ጋር አብረሽ እየተኛሽ' ብሎ ቀጠቀጠኝ" አለችው፡፡ ባልም ለማስተባበል "ተይው ቅዠት ነው" አለና ተኛ፡፡ ከዚያም ባልዮው

ሲያሰላስል ቆይቶ “እኔንም ቀጠቀጠኝ፡፡ እስኪ ተነሽና እሳት አንድጅ” አላት፡፡ እሷም ተነስታ እሳት አንድዳ አበራችለትና “ምነው?” አለችው፡፡

አንተን አስትቶ ሌላ ካማራት፣

በል ተነስና በብትር በላት፡፡

ብሎኛልና ብሎ ልቧ ሊከዳው ያለችውን ሚስቱን በአለንጋና በጠፍር ሲደበድባት አደረ፡፡ በዚሁ የተከፈለውን ልቧን ወደራሱ መለሰ ይባላል፡፡ (ፈንታይቱ ይመር፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

## ተረት 61

አንድ የቆሎ ተማሪ ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን በአንድ ቤት አሳድሩኝ ብሎ ያድራል፡፡ ባደረበት ቤት ውስጥ ባልና ሚስቱ ከአንዲት ድረገብ ልጃቸው ጋር ይኖሩ ነበር፡፡ በዚያን እለት የቤተሰቡ አባላት በቤታቸው ሊያድር የመጣውን የቆሎ ተማሪ ቤት ያፈራውን ያስተናግዱትና ከድረገብ ልጃቸው ጋር በአንድ መደብ ላይ በመጨጊያ (ከገለባና ከቆዳ የተሰራ ለትራስ የሚያገለግል ባህላዊ ቁስ) ለይተው ጎን በጎን ያሳድሯቸዋል፡፡ ሲነጋ ልጂቱ ተነስታ ከግቢያቸው ውስጥ ካለው መሬት አረም ማረም ትጀምራለች፡፡ የቆሎ ተማሪውም ዘግይቶ ተነስቶ ወደሃገሩ ለመሄድ ጉዞውን ይጀምራል፡፡ ካጥር ውጭ እንደደረሰ ወደግቢ ሲመለከት አንዲት ቆንጆ ልጅ ይመለከታል፡፡ ውበቷ ቀልቡን ነጥቆት ባጥር ላይ ሊገባ ሲል ያቺ ልጅ ታየዋለች፡፡ ኋላ ሁኔታው ገርሟት “ተሜ! ሌሊት መጨጊያ መዝለል ያቃተህ አሁን አጥር ልትዘል ነው እንዴ?!” አለችው ይባላል፡፡ (ቦሰና ያሲን፣ ቦረና፣ ግንቦት 2008)፡፡

## ተረት 62

በድሮ ዘመን በአንድ ቤት ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ሚስቲቱ በጣም ሂያጅ ነበረች፡፡ ሰውየውም ይህንኑ ድርጊቷን ስለሚያውቅ በንደትና በብስጭት ይኖር ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ይህንኑ መጥፎ ባህሪዋን ለማስቀረት ጓደኛውን አማከረው፡፡ በምክራቸው መሰረት ባል ሚስቱን “በሬ ለመግዛት ወደሩቅ አገር ልሄድ ነውና የሶስት ቀን ስንቅ አዘጋጅልኝ” አላት፡፡ እሷም በቀና መንፈስ ለሶስት ቀን የሚበቃ ስንቅ አዘጋጅታ የጎረቤት ውሽማዋ እያየ ሸኘችው፡፡

ሰውየውም ስንቁን ይዞ ከታማኝ ጓደኛው ቤት ሄደና የያዘውን ስንቅ አስቀመጠ፡፡ ምክራቸው ከተጠርጣሪው ቤት ሄደው ሲያወሩ በማምሸት ንግግሩንና አኳኋኑን

ለመከረጅ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ አብረው ካመሹ በኋላ ሁለቱም ወጥተው ሄዱ፡፡ ሁለቱ ጓደኛሞች ተያይዘው ወደየቤታቸው ሲመለሱ የሴትዮዋን ባለቤት "አንተም ወደቤትህ ሂድ፤ እኔም ወደቤቴ ልሂድ፡፡ ነገር ግን ወደቤትህ ስትገባ እንደተነጋገርነው የሰውየውን ንግግር አስመስለህ አናግራት" ብሎ መከረው፡፡ እሱም አስፈላጊውን ጥንቃቄ በማድረግ ከቤቱ ገብቶ ከሚስቱ ጋር አብረው አደሩ፡፡ ምንም አልጠረጠረችም ነበር፡፡ ሚስት ለውሽማዋ ገንፎ አዘጋጅታ ሰው ሳያየው በጧት ለመሸኘት ብላ በሌሊት ተነሳች፡፡ ውሃዋን በድስት ጥዳ ለገንፎ የሚሆነውን ዱቄት ስትነፋ ባሏ በትክክለኛው በራሱ ድምጽ "ምን ያጣድፍሻል ቀስ ብለሽ አዘጋጅው" ሲላት አብሯት ያደረው ውሽማዋ መስሏት ስለነበረ በጣም ደነገጠችና ስትነፋ የነበረውን ዱቄት ይዛ የቤቱን ምድጃ በመዞር እየነፋች፡-

አይኔ ነው ባሌ?
ትናንት መጣህ ዛሬ?
ወይፈን ገዛህ በሬ?

በማለት በጭንቀት ስትናገር ባልዮው ሁኔታዋን በማየት ዳግመኛ የብልግና ስራ እንዳትፈጽም ሙልጭ አድርጎ ገርፎ አስተካከላት፡፡ ከዚያ በኋላ በእምነቷ ጸንታ በሰላም አብረው ኖሩ ይባላል (ጀማል ሰይድ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)፡፡

## ተረት 63

በድሮ ጊዜ በአንድ ግዛት ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ ሚስት ከሌላ የምትወልዳት አንዲት ሴት ልጅ፣ ባልም እንደዚሁ ከሌላ የሚወልዳት አንዲት ሴት ልጅ ነበሯቸው፡፡ ሚስት የባሏን ልጅ ታሰቃያትና ትመታት ነበር፡፡ የእሷ ልጅ ግን ምንም ብታጠፋ እንኳን ልትመታት ይቅርና አትቆጣትም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ለሚስት ሰይጣን ሹክ አላትና "ይቺን ልጅ ከዚህ ቤት ማጥፋት አለብኝ" ብላ አሰበች፡፡ ባሏንም እንዲህ አለችው "ልጅህን በረዶ ከሚፈላበት ጫካ ወስደህ ጣል፡፡ እኔ እሷን እዚህ አጋድሜ አልቀልብም" አለችው፡፡ ባልም ሚስቱን ይወድ ነበርና እንደታዘዘው አደረገ፡፡ ትንሿ ልጅም በበረዶው እየተንሰፈሰፈች ብቻዋን ቁጭ ብላ ሳለች የበረዶው ንጉስ ወደ እሷ ዘንድ መጣ፡፡ "አንቺ ትንሽ ልጅ እንዴት ከረምሽ? ሙቆሻል?" አላት፡፡ እሷም "አዎ" ብላ መለሰች፡፡ አሁን ደግሞ የሚያፏጭ የደጋ የበረዶ ውሽንፍር አወረደባት፡፡ ይሄኛው ዝናብ እጅግ ቀዝቃዛ ከመሆኑ የተነሳ የዛፎችን ግንድ ሳይቀር አደረቃቸው፡፡ "አሁንስ ሞቀሽ?" አላት፡፡ "አዎ ጌታዬ!" አለችው፡፡ በዚች ትንሽ ልጅ የተደነቀው የበረዶው ንጉስ

ጥልቅ ሃዘን ተሰማው። ከቆዳ የተሰራ ጃኬት አምጥቶ አለበሳት። በምትኩም ከፍተኛ ሙቀት ሰውነቷን ተሰማት። "ለመልካምነትሽ ስጦታ ተቀበይኝ" ብሎ በወርቅ፣ በነሃስና በእንቁ የተሞላ ሳጥን አምጥቶ ሰጣት። ከረጅም ጊዜ በኋላ እንጀራ እናቷ ባሏን "እስከ አሁን ልጅህ በበረዶ ደርቃ ትሞታለችና አጥንቷን ለቅመህ ይዘህ ና" ብላ አዘዘችው። ባልዮውም ልጅቷን ሊያመጣ ፈረሱን እየጎተተ ወደጫካ ሄደ። እንጀራ እናቷም መስኮት ላይ ተቀምጣ በር በር ታይ ጀመር። ባልዮውም ፈረስ እየጎተተ ሲመጣ "የልጂቷን አጥንቶች ሰብስቦ መጣ" አለች። ልጅቱ ግን በፈረስ መጣች። የተሰጠችውንም ስጦታ በሳጥን አድርጋ ይዛ መጣች። አምሮባታል። እንጀራ እናቲቱ ይህንን በማየት "የኔዋ ውብ ልጅ ብትሄድ ከዚህ የበለጠ ያምርባታል" ስትል አሰበች። ባልዋንም "የኔዋን ውብ ልጅም ውሰዳት" አለችው። ባልዮውም ወሰዳት። ብቻዋንም ከበረዶው ግግር ተቀመጠች። የበረዶው ንጉስ ወደእሷ መጣና "እንዴት ይዞሻል፤ ሙቆሻል?" አላት። እሷም "ጥፋ ከፊቴ!" ብላ መለሰችለት። ንጉሱም ተበሳጨና የበረዶ ውሽንፍር አወረደባት። "አሁንስ ሙቆሻል?" አላት። "ዓይንህ አያይም!" አለችው። "ስጦታህን ፈጥነህ ስጠኝ፤ ወደመጣሁበት ልመለስ ነው" አለችው። አሁንም ንጉሱ ተበሳጨና የበረዶ ውሽንፍር ለቀቀባት። ከትንሽ ጊዜ በኋላ ወደበረዶነት ተቀየረች። እናትም እንዲህ አለች፡- "ትንሿን ልጄን አምጣልኝ። ስትመጣ ግን የተሰጠችውን ስጦታ ፈጽሞ እንዳትረሳው" አለችው። ባልም እንደታዘዘው ወደጫካው ቢሄድ ሙታ በረዶ ሆና አገኛት። አስከሬኗንም በፈረሱ እየጎተተ መጣ። በዚህ ሁኔታ እንጀራ እናት የእጇን አገኘች ይባላል። (ደመወዝ ገረመው፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)።

ተረት 64

በጥንት ጊዜ በአንድ ከተማ ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስት ልዑልና ልዕልት ነበሩ። ሁለቱም በጣም ይዋደዱ ነበር። ልዑሉ ታዲያ በጣም ጀግና፣ ታዋቂ እና በጣም ደፋር ነበር። ልዕልቷ በበኩሏ በውበቷ ወደር የለሽ ቆንጆ ነበረች።

ከእለታት አንድ ቀን ልዑሉ ለልዕልቷ ጦርነት ሊሄድ እንደሆነ ነገራት። ልዕልቷ በጣም ትወደው ስለነበር ሲነግራት አይኗ እንባ አዘለ። ነገር ግን ልዑሉ መቅረት ስለማይችል ትቷት ሄደ። ልዕልቷም የባሏን መምጣት አለመምጣት ስትጠባበቅ ከሁለት ወር በኋላ በቀስት ተመትቶ መሞቱንና እዚያው የጦር ውጊያ ያካሄደበት በረሃ ላይ መቀበሩን ሰማች። በጣም አለቀሰች፤ በጣም አዘነች።

ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ቀን በሃዘን ተቆራምዳ እንደተኛች መላዕክተኛ መጥቶ ባሏ እተቀበረበት ቦታ ሄዳ እራሷን እንዲታጠፋና ከጎኑ እንድትቀበር ነገሯት፡፡ ልዕልቷም በትዕዛዙ መሰረት የተባለችውን ፈጸመች፡፡ እናም በሰማይ ቤታቸው አብረው መኖር ጀመሩ ይባላል፡፡ (ልዑልሰገድ አሰፋ፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)

## ተረት 65

በድሮ ጊዜ አንዲት የንጉስ ልጅ ነበረች፡፡ አባቷ ለመጨዋቻ የሚሆን የወርቅ ኳስ ይሰጧታል፡፡ በዚያ በወርቅ ኳስ ስትጫወት በቤታቸው አካባቢ በሚወርድ ውሃ ውስጥ ይገባባታል፡፡ ውሃው ዳር ቁጭ ብላ ስታለቅስ አንድ የሚያምር እንቁራሪት ከውሃው ውስጥ ዘሎ ወጥቶ “ምን ሆነሽ ነው የምታለቅሽው?” ሲላት “የወርቅ ኳሴ ውሃ ውስጥ ገብቶብኝ” ትለዋለች፡፡ በዚህ ጊዜ እንቁራሪቱ “አውጥቼ ከሰጠሁሽ ምን ታደርጊልኛለሽ?” ይላታል፡፡ እሷም “የፈለግከውን የሚበላም የሚጠጣም ሌላ መጫወቻም እሰጥሃለሁ” ትለዋለች፡፡ እንቁራሪቱ ግን “የምትይውን ሁሉ አልፈልግም” አላት፡፡ እሷም “ታዲያ ምንድን ነው የምትፈልገው?” አለችው፡፡ እሱም “እኔ ምንም ጓደኛ ስለሌለኝ ጓደኛ እንዲትሆኝኝ ነው የምፈልገው” አላት፡፡ እሷም ኳሷን የማግኘት ጉጉት ስላደረባት “እሺ በቃ ኳሴን ከሰጠኸኝ ጓደኛ እሆንሃለሁ” ትለዋለች፡፡ ከዚያም እንቁራሪቱ ኳሷን አውጥቶ ይሰጣትና በደስታ ወደ ቤቷ ትሄዳለች፡፡ እንቁራሪቱን ግን ጓደኛ ማድረግ አልፈለገችም፡፡ በማግስቱ እንቁራሪቱ ወደ አባቷ ግቢ ይገባና ስሟን ይጠራታል፡፡ በዚህ ጊዜ አባቷ ይሰማል፡፡ እሷም እየሮጠች ሄዳ ወደ መኝታ ክፍሏ ትገባለች፡፡ አባቷም “ምን ሆነሽ ነው?” ብሎ ሲጠይቃት የሆነውን ነገር ለአባቷ ትነግረዋለች፡፡ አባቷም “ቃል ከገባሽለት ጓደኛ ልትሆኚው ይገባል” አላት፡፡ እሷ ግን “አባዬ! እሱ እኮ እንቁራሪት ነው፡፡ በዚያ ላይ በጣም ያስጠላል” ትለዋለች፡፡ አባቷ ግን ያግባባትና እንቁራሪቱ ወደ መኝታ ቤቷ ይገባል፡፡ እንቁራሪቱም በጣም ያለቅሳል፡፡ በዚህ ጊዜ የንጉሱ ልጅ በጣም ትበሳጭና “አሁን ደግሞ ምን ፈለክ?” ምን ጎደለብህ? ትለዋለች፡፡ እሱም “ግን ለምንድን ነው የምትጠይኝ? አንቺንም የፈጠረ ፈጣሪ ነው እኔንም የፈጠረኝ የሚያምረውንም የሚያስጠላውንም ጥሩውንም መጥፎውንም የፈጠረ ፈጣሪ እኮ ነው” ይላታል፡፡ እሷም በጣም ታዝናለች፡፡ በእንቁራሪቱ አነጋገር ልቧ ስለተነካ ታለቅሳለች፡፡ የእንባዋ ዘለላ በእንቁራሪቱ ላይ ሲያርፍ እንቁራሪቱ ወደሚያምር ሰው ተለወጠ፡፡ ከዚያም ልጁቱ በመደንገጥ “እስከአሁን እንቁራሪት አልነበርክም እንዴ? እንዴት ሰው ሆንክ?” አለችው፡፡ እሱም እኔ የንጉስ ልጅ ነበርኩ፡፡ አንዲት ክፉ መናፍስት ረግማኝ ነው እንደዚህ

የሆንኩት፡፡ እሷም የሚወድህ ሰው እስካላገኝህ ድረስ እንቁራሪት ሆነህ ትቀራለህ” እንዳለችው ነገራት፡፡ በእንቁራሪቱ ታሪክ የንጉሱ ልጅ ልቧ ተነካ፡፡ ወጣቱም በጣም ውብና መልከ መልካም ስለነበር በሰርግ ተጋብተው በደስታ መኖር ጀመሩ ይባላል፡፡ (አብዱ ሐሰን፣ ተሁለደሬ፣ መጋቢት 2008)

## ተረት 66

አንድ አጭርና ቀጭን ሰው አንዲት ግዙፍ የሆነች ሴት አግብቶ ሲኖር በጣም ስለናቀችው አንተ አትለው ልማዱ ከለከላት፡፡ አንቱ አትለው ንቄት ስላለባት አንተም አንቱም የማያሰኙ ቃላትን እየተጠቀመች ስትኖር ሰውየውም ብልጥ በመሆኑ አንድ ቀን አንተ ወይም አንቱ የሚያስብል ጥያቄ በማዘጋጀት ሊሞክራት ፈለገ፡፡ እናም የእሱ ንብረት የሆነውንና የእሱ መሆኑን የምታውቀውን ጋቢ “ይህ ጋቢ የማን ነው?” ብሎ ሲጠይቃት “ምን አውቅ!” አለችው፡፡ እሱም ተበሳጭቶ “ያንቺ ሰው መናቅ” ብሎ በጥፊ ደረገማት ይባላል፡፡ (አስፋው ዓሊ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)

## ተረት 67

በአንድ አገር ውስጥ በሰላም አብረው የሚኖሩ ባልና ሚስት ነበሩ፡፡ በኑሯቸውም ሚስት የቤት ውስጥ ስራዎችን ከመስራት ውጭ ባለቤቷን በዱር ስራ አታግዘውም ነበር፡፡ የዱር ስራ ልምድም አልነበራትም፡፡ ባልም በዱር ስራ እንድታግዘው ጠይቋት አያውቅም ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የጎረቤት ጓደኛው “ሚስትህ ለምን በዱር ስራ አታግዝህም፡፡ አንተ ብቻህን ስትለፋ ትውላለህ፡፡ እሷ እቤቷ ተቀምጣ ስትበላና ስትጠጣ ትውላለች” ብሎ ክፉ ምክር ይመክረዋል፡፡ ባልም ምክሩን ሰምቶ በመናደድም ጭምር “በይ ዛሬ ከእኔ ጋር ለስራ እዱር ትሄጃለሽ ይላትና ይዟት ይሄዳል፡፡ ሴትዮዋም ወደቤቷ መሄድ ስለፈለገች “የእከሌን ወንፊት ዘግቸባት፤ የእከሌን ሰፌድ ዘግቸባት” እያለች ምክንያት ብታበዛም ባልዮው ወደቤት እንድትሄድ ስላልፈቀደላት እዚያው አብራው ስራ ውላ ማታ ላይ ወደቤታቸው ለመሄድ ይነሳሉ፡፡

ባልዮው የጓደኛውን ምክር በሙሉ ሰምቷልና ዘዴ ፈጥሮ ቀድሟት ከቤት ገብቶ ይደበቃል፡፡ በዚህ ምክር ጓደኛውም አለበት፡፡ እሷ በጣም እርቧት ስለነበር ቶሎ ምጣድ ትጥድና እንጀራ ትጋግራለች፡፡ ከውጭ ደግሞ የባሏ ጓደኛ “ከብቶች የሰው አዝመራ አጠፉ” ብሎ ይጣራል፡፡ እሷም ወደውጭ ስትወጣ ባሏ እንጀራውን ከምጣዱ ያወጣና ይደብቅባታል፡፡ ስትመለስ ምጣዱ ባዶ ሆኖ ታገኘዋለች፡፡ አሁንም ሌላ እንጀራ ታሰፋና ሳታወጣው መልሶ የባሏ ጓደኝ ይጠራታል፡፡ ስትመለስ ያሰፋቸውን እንጀራ ከምጣዱ

ታጣዋለች፡፡ በመጨረሻ ረሃቡ ሲጠናባት “የዛሬዋስ ቆሌ እንደኔ እርቧታል” ትልና ሲጡን ግጥም አድርጋ ትጠጣዋለች፡፡

ከዚያም ሌሊት ላይ ሆዷን ያማትና ያስቀምጣታል፡፡ ባለቤቷም እገንቦ ውስጥ አድርጊውና ማር ነው ብለን እንሽጠዋለን” ሲላት አሺ ብላ እገንቦው ውስጥ ትለቀዋለች፡፡ በማግስቱ ነጫጭ ልብሷን አልብሶ፣ አፉ ላይ ማር በማድረግ “የማር ገንቦዋን” አሳዝሎ ገበያ ይሄዳሉ፡፡ ገበያ ሲደርሱም ዘመዶቿና ሌሎችም የገበያ ሰዎች ባሉበት ገንቦውን በዱላ ሲተረትረው የሰራ አከላቷ ቅዘን ይለብሳል፡፡ በዚሁ አፍራ ካገር ትጠፋለች፡፡ ብዙ ጊዜ ቆይታ ወዳገሯ ስትመለስ ያገሩን ስም ትጠይቃለች፡፡ እነርሱም “ይህማ ቅዘን ልብሱ ይባላል” ሲሏት “እነቅዘን ልብሱ ዛሬም አልተረሱ” ብላ መልሳ ካገር ጠፋች ይባላል፡፡ (መካሻ አበራ፣ ኩታበር፣ ሚያዚያ 2008)

**ተርት 68**

ባንድ ዘመን ባንድ አገር ውስጥ የሚኖሩ ባልና ሚስቶች ሶስት ሴቶች ልጆች ነበሯቸው፡፡ ልጆቹ ሁሉም የየራሳቸው አመል ነበራቸው፡፡ አንዷ ሌባ፣ አንደኛዋ ሴሰኛ እና አንዷ ደግሞ ነገረኛ ነበሩ፡፡ ይህንን አመላቸውን እንደያዙ ወላጆቻቸው ሶስቱንም ዳሯቸው፡፡ ሆኖም ግን ትዳራቸው ሣይጸና ቀረና ሶስቱንም ባሎቻቸው ፈቷቸው፡፡ የፈቷቸው ደግሞ አንዷ ሌባ፣ ሁለተኛዋ ዝሙተኛ፣ ሶስተኛዋ ደግሞ ነገረኛ በመሆናቸው ነበር፡፡ ወደአባታቸው ቤት እንደተመለሱም ቁጭ ብለው ተመካከሩ፡፡ በምክክራቸው መሰረት መንገድ ጀመሩ፡፡ ከዚያ ሲሄዱ ሲሄዱ ውለው መሸባቸውና አንድ ባለጸጋ ቤት አሳድሩን ብለው ተጠጉ፡፡ ሶስቱም መልከመልካም ነበሩና ባለጸጋው ጥያቄው ሲቀርብለት በደስታ ተቀበላቸው፡፡ ወደየት እየሄዱ እንደሆነና ምን እንደሆኑ ሲጠይቃቸው ሦስቱም የየራሳቸውን ችግር አብራርተው ተናገሩ፡፡ ቀጥሎ ባለጸጋው ሴሰኛይቱን “አንቺ እኔ ጋር ኑሪ፡፡ ምክንያቱም እቤቴ ካለው ወንድ አታልፊም” ብሎ አስገባት፡፡ ሌባይቱንም “ከዚህ ሁሉ ሃብትና ንብረቴ አታልፊምና አንቺም ግቢ” አላት፡፡ ነገረኛይቱን ግን “አንቺ ቤተሰብ ታባቂያለሽ” ብሎ አባረራት ይባላል፡፡ (እነ ብስራት ሃይሌ፣ ሐያቅ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ተማሪዎች፣ መጋቢት 2008)

**ተረት 69**

ጥንት ድሮ ገና ሰማይና መሬት እንደተፈጠሩ ፈጣሪ በሰባት ቀናት ውስጥ ሌሎችን ፍጥረታት ሁሉ ሲፈጥር አዳምን በራሱ መልክ አብሮ ፈጠረው፡፡ ፈጣሪም በሰራው ሁሉ

እየተደሰተ ቀጥሎ ያለውን አንድ ሳምንት የሰራውን ሲከልስና ሲያርም ሰነበተ፡፡ አንድስ እንኳ ስህተት አልነበረውም፤ አዳምን ብቻውን ከመፍጠሩ ውጭ፡፡ በዚህም ፈጣሪ ተጸጽቶ ለአዳም አገልጋይ ሊሰራለት ፈለገ፡፡ ሆኖም ግን እንደቀደመው አንድ ሳምንት ብዙ መልፋትና መጨነቅ ስላልፈለገ ሌላ ቀላል ዘዴ አሰበ፡፡ ይህም ከአዳም የግራ ጎን አጥንት ሴትን መስራት ነበር፡፡

በዚህም መሰረት የቅርብ ታዛዡን ሚካኤልን ጠርቶ ሄዋንን መስራት ይችል ዘንድ “አዳም እንቅልፍ ሲወስደው አይተህ ከግራ ጎኑ አንዲት አጥንት አምጣልኝ” ሲል ላከው፡፡ ሚካኤልም እንደታዘዘው ወደ አዳም ሄደና እንቅልፍ ሲወስደው ጠብቆ የታዘዘውን የግራ ጎን አጥንት አወጣ፡፡ አጥንቷ እጅግ ንጹህና ውብ ስለነበረች እንዳትቆሸሽበትም ሌላ እንዳያይበትም በነጭ ጨርቅ ጠቅልሎ በግራ እጁ ይዞ በቀኝ እጁ በያዘው ሰይፍ ነቅቶ እየጠበቀ ጉዞውን ወደፈጣሪው አደረገ፡፡

ሚካኤል በመንገድ ላይ እያለ መቼም ሰይጣን (ዳቢሎስ) በዚህ ዓለም ላይ የማያየው ነገር የለምና ያቺን ውብና ንጹህ የጎን አጥንት በሚካኤል እጅ ያያታል፡፡ እናም በውበቷና በንጽህናዋ በጣም ይማረካል፤ የራሱ ለማድረግም ይወስናል፡፡ ይህንንም ፍላጎቱን ለማሳካት ሚካኤል ሲዘናጋ አይቶ ያቺን አጥንት ከእጁ ላይ ይልፈውና ወደእንጦርጦሱ ሩጫውን ይቀጥላል፡፡ ሚካኤልም የተነጠቀውን አጥንት ለማስመለስ ሰይፉን መዝዞ ሩጫውን ወደዚያው ያደርጋል፡፡ ተከታትለው ሲሮጡ ሲሮጡ ዳቢሎስ ሊደረስበት ሲል አንድ ዋሻ ውስጥ ጥልቅ ይላል፡፡ ሆኖም የዋሻው በር ጠባብ ስለነበረ እንደልቡ ቶሎ አላስገባው ይልና ጅራቱ ወደኋላ ይተርፍበታል፡፡ ሚካኤልም ያቺን ጅራት ይይዛል፡፡ በዚህ ግብ ግብ ዳቢሎስ አጥንቷን እንደያዘ ወደዋሻው መግባቱ ቁርጥ መሆኑን ሚካኤል ይገነዘባል፡፡ ሚካኤልም በንዴት በእጁ የያዛትን ጅራት በሰይፉ ይቆርጣታል፡፡

በዚህ መሃል ፈጣሪ የሚካኤልን መምጣት በጉጉት ይጠብቅ ኖሮ ወጣ ገባ ይላል፡፡ በመንፈስም ቶሎ እንዲመጣ ይነግረዋል፡፡ ሚካኤልም የሚያደርገው ቢያጣ የቆረጣትን የሰይጣን ጅራ ይዞ ወደፈጣሪው ይቀርባል፡፡ ፈጣሪም ያቺ የሰይጣን ጅራት እንደቀረበችለት ወዲያው ነገር ዓለሙን ሁሉ ጨርሶ ሴት አድርጎ ሰራት፡፡ ከዚያን ጊዜ አንስቶ ሴት ስትሰደብ “አንቺ የሰይጣን ጅራት!” መባል ተጀመረ ይባላል፡፡ (ደረጀ ፈቃዱ፣ የፋይናስ ባለሙያ ባንድ አጋጣሚ የነገረኝ፣ 2005)

## ተረት 70

ሁለት ባለጸጋ ባልና ሚስት ባንድ አገር ይኖሩ ነበር፡፡ ባለጸጎቹ ሲኖሩ ሲኖሩ አንድ ወንድና አንዲት ሴት ልጅ ወለዱ፡፡ ልጆቻቸውን በተድላና በደስታ በሰላም አሳድገው ለወግ ለማዕረግ አበቁ፡፡ የልጆችም ትዳር እንደ እናትና አባታቸው በሃብት የተሞላ ነበር፡፡ ከጊዜ ብዛት እናትና አባት ዕድሜ እየተጫናቸው ሲመጣ ሃብት ንብረታቸው ቀነሰና ለድህነት በቁ፡፡ በዚያ ላይ በስተኋላ መንታ ሴትና ወንድ ልጆች ወለዱ፡፡ በመሆኑም ባል ሚስቱን የሚያርስበት ምንም የሚቀመስ ምግብ እቤቱ ውስጥ አልነበረም፡፡ በዚህም የተነሳ ወደባለጸጋ ልጆቹ ዘንድ ሄዶ መጠየቅና ማምጣት ግዴታ ሆነበት፡፡

አንድ ቀን ከጎረቤቱ አህዮችንና አቅማዳ ተውሶ እህል ለማምጣት ወደ ወንድ ልጁ ቤት አመራ፡፡ ከቦታው የደረሰው ከእኩለቀን በኋላ ነበር፡፡ እንደደረሰም ያገኘው የልጁን ሚስት ነበር፡፡ ልጁ ግን እርሻ ሄዶ ስለነበር በወቅቱ አላገኘውም፡፡ የልጅ ሚስት የባሏን አባት ምንም መስተንግዶ ሳታደርግለት ምሽት ደረሰና ልጁ ከእርሻ መጣ፡፡ ልጅ የአባቱን መስተናገድ አለመስተናገድ በወግ ሳይጠይቅ ተያይዘው ወደቤት ገቡ፡፡ አባትም በእንግድነቱ ከቁብ ሳይቆጠር የተገኘውን ቀማምሶ መሽቶ ነጋ፡፡ ሁሉም በማለዳ ተነሱ፡፡ ልጅም "አባቴ ምን ሁነህ መጣህ?" ሳይል ወደእርሻው ለመሄድ ተነሳ፡፡ ይህን የተገነዘበው አባት የመጣበትን ጉዳይ ሁለቱም ባሉበት አስረዳ፡፡ "ልጆቼ! እናንተን በማሳደግ ጉልበቴንም ገንዘቤን ጨረስኩኝ፡፡ እኛ ወላጆቻችሁ ችግራችንን እንዳንችል እንኳ በስተኋላ እናታችሁ መንታ ወለደች፡፡ አሁን እናታችሁ የምትታረስበት እህል ውሃ በቤታችን የለንምና እባካችሁ ስጡኝ" ሲሉ ይጠይቃሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ልጅ ለሚስቱ "ካለሽ ስጪው" ብሎ ወደ እርሻው ይሄዳል፡፡ ሚስትም እንደነገሩ ሩብ አቅማዳ እንኳን የማትሆን ጥሬ በትናላቸው መንገዳቸውን ታሳያቸዋለች፡፡

አባት በልጃቸው በጣም ያዝናሉ፡፡ እየተራገሙ መንገዳቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በመንገድ ላይ እያሉ "ይቺን ይዤ እንዴት ወደቤቴ እሄዳለሁ? ባዶ እጄን ተመልሸ ብሄድ ያቺ አራስ በረሃብ መሞቷ አይደለም እንዴ?" ይሉና እየተጠራጠሩ ሌላ ሙከራ ለማድረግ ወደሴት ልጃቸው ቤት መሄድ ያስባሉ፡፡ መንገዳቸውንም ወደዚያው ያቀናሉ፡፡ ሴት ልጃቸውም ቤት በደረሱ ጊዜ እሷኑ አገኟት፡፡ ልጃቸው ደስታዋ ከመጠን አለፈ፡፡ በደስታ ሰከረች፡፡ የምታደርገው ቅጡ ጠፋት፡፡ ስትረጋጋ ገላቸውን አጥባ፣ ልብሳቸውን ቀይራ፣ ጥሩ ምግብ ከጠላ ጋር አቅርባ በጥሩ ሁኔታ አስተናገደቻቸው፡፡ አመሻሽ ላይ ባሏ ከእርሻው

ሊመጣ አቅራቢያ ከሳጥኗ አዲስ ጋቢዋን አውጥታ አልብሳ እንዲታዩላት ደጅ ላይ አስቀመጠቻቸው፡፡

ባልዮው ከእርሻ እንደመጣ ደጅ ላይ ተቀምጠው ሲያገኛቸው የእሱም ደስታ እንደሚስቱ ሆነ፡፡ አጥብቆ ሰላምታ አቀረበላቸው፡፡ ከሙክቶቹም መሃል የሰባውን መርጦ አረደላቸው፡፡ ምሽቱ የደስታ ሆነ፡፡ በልተው ጠጥተው እንዳበቁ ማታውኑ የመጡበትን ጉዳይ ባልና ሚስቱ ጠየቋቸው፡፡ እሳቸውም እወንድ ልጃቸው ቤት ባስረዱበት ሁኔታ ጉዳያቸውን ተናገሩ፡፡ ባልና ሚስቱ "እዚያው ሁነህ ለምን አትልክብንም ነበር? እዚህ ድረስ ለምን ለፋህ?" በሚል አዘኔታዊ ቁጣ ሰነዘሩ፡፡ ከዚያም "ሁሉም ነገር ጧት ይዘጋጅልሃል" ሲሉ አበሰሯቸው፡፡

ባልና ሚስቱ መክረው አደሩና በማግስቱ በማለዳ ተነስተው ያዘጋጁላቸው ገቡ፡፡ ይዘዋቸው ከመጡት አህዮች በተጨማሪ በራሳቸውም አህዮች ከሁሉም የእህል ዓይነት፣ ከበርበሬው፣ ከሽሮው፣ ከእርጥቡ የሙክት ስጋ፣ ከቋንጣው፣ ከቅቤውና ከቅመማቅመሙ ሳይቀር ከሁሉም ተዘጋጀላቸው፡፡ በእግራቸው እንዳይሄዱ በቅሎ ተጫነላቸው፡፡ አህያ እየነዱ እንዳይሄዱ አሽከር ተከተላቸው፡፡ በዚህ ዓይነት ተከብረውና ተንቀባረው በደስታ ወዳገራቸው ሄዱ፡፡

ቤታቸው አቅራቢያ ሲደርሱ ለቅሶ ሰሙና ጨነቃቸው፡፡ እቤታቸውም እስከሚደርሱ ተሸበሩ፡፡ ቤታቸው ሊደርሱ ሲሉ አንድ ሰው ፈጠን ብሎ መጥቶ ጓዛቸውን ከእጃቸው ላይ ተቀበለና ወደቤታቸው አስገባቸው፡፡ ሞቱ እራሳቸው ቤት መሆኑን አወቁ፡፡ ማን እንደሞተ የተሰበሰቡትን ሰዎች አጥብቀው ጠየቁ፡፡ ከመካከል አንዱ ብድግ ብሎ "ከተወለዱት መንታ ልጆችዎ መካከል ትናንትና ማታ ወንዱን ልጅዎች ጅብ አውጥቶ በላው" ሲል አረዳቸው፡፡ እሳቸውም "አይ! ምን የቸኮለ ጅብ ነው! ምን አስቸኮለው? እኔ አውጥቼ እጥልለት አልነበረም" ሲሉ ተናገሩ ይባላል፡፡ (ጌታሁን አሰፋ፣ ቦረና ወረዳ)

## ሐ. ከተረት መጻህፍት የተሰበሰቡ ተረቶች

### ተረት 71

### የመጨረሻዋ ታዛዥ ሚስት

በድሮ ጊዜ ሶስት ሴቶች ልጆች የነበሩት አንድ ገበሬ ነበር፡፡ ሶስቱም ቆነጃጅት ከመሆናቸው በስተቀር ለጋብቻም የደረሱ ወጣቶች ነበሩ፡፡ ታላቅ የሆነችው በቁንጅና፣ በቅልጣፌና በብልሃት ከሁለት እህቶቿ የላቀች ስትሆን ጠብ ጫሪ፣ የማትታዘዝ በመሆኗ በቤት ውስጥ ሰላም ተገኝቶ አይታወቅም ነበር፡፡ ምንም እንኳ አባቷ ሩህሩህና ሰላም አፍቃሪ ቢሆንም ዘወትር የሚለውን በሙሉ ከመቃወሟ በላይ መልካም ጠባይ ያላቸው እህቶቿ እንኳን ሊያስደስቷት ሲሞክሩ ዘወትር ትጣላቸው ነበር፡፡

ብዙዎቹ እጮኞችና ብዙዎቹ አማጮች እየመጡ ቆንጆዋንና ታላቅዮዋን ልጅ ለሚስትነት ጠየቁ፡፡ ለመጀመሪያው ሚስት ለማኝ የልጆቹ አባት እንዲህ አለው፡፡ “እኔ ብታገባት ግድ የለኝም፡፡ እንግዳውስ ደስ እያለኝ በአማችነት እቀበልሃሁ፡፡ ግን እውነቱን አፍርጨ እንድነግርህ እወዳለሁ፡፡ ታላቂቷ ልጄ ጠብ ቆስቋሽ፣ ያኗት የማይገባት ተከራካሪና ግትር ናት፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው በሰላም ከእሷ ጋር አብሮ ለመኖር የሚችል አይመስለኝም፡፡ እንዲያውም ይህን ከሰማህ በኋላ አገባታለሁ ብትል ለካሳህ ያህል ለሌሎች ልጆች ከምሰጠው፣ ሴት ልጅ ይዛ ከምትሄደው ጥሎሽ በላይ 3 ሺህ ብር በተጨማሪ እሰጥሃለሁ” አለው፡፡

ብሩ ቢያሳሳውም ወጣቱ እጮኛ በነገሩ ካሰበበት በኋላና ተመላልሶ ከጎበኛቸው ወዲህ ታላቋን ጥሎ የመሃከለኛይቱን ልጅ ለጋብቻ ጠየቀ፡፡ ልጂቱ ደስ እንዳላት ሁሉ አባትዮውም ፈቃደኝነቱን ገልጦ ወዲያው የጋብቻው ሥነሥርዓት ተፈጸመና ሁለቱ የደስታ ኑሯቸውን ቀጠሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ሌላ ሚስት ለማኝ መጣ፡፡ ይኸ ሰው ከሌላ አውራጃ ስለመጣና የልጂቷን ታሪክ ስለማያውቅ ታላቅዮዋን ወደደ፡፡ አባትዮውም ለመጀመሪያው እጮኛ እንዳስጠነቀቀው ሁሉ ለዚህም ሰው ስለመጀመሪያይቱ ልጅ ግትርነት አስረዳው፡፡ በተጨማሪም እሷን ሊያገባ የሚፈልግ ቢሆን ለመጥፎ ጠባይዋ ካሳ 3 ሺህ ብር የሚሰጥ መሆኑን ገለጠለት፡፡ ይሄኛው ሰው እንደመጀመሪያው ሰውዬ ሃሳቡን ለወጠና ሶስተኛዋን

ልጅ ለጋብቻ ጠየቀ። እሷና አባቷ ደስተኛ መሆናቸውን ስላስረዱት ሁለቱ ወጣቶች ተጋብተው አብረው ለመኖር ሄዱ።

ከዚያ የሁለቱ ታላቅ የሆነችው ልጅ ብቻ ካባቷ ጋር ቀረች። ቢሆንም ቀድሞ ታሰቃየው ከነበረው ምንም ለውጥ አላደረገችም። እንዲያውም ሁለቱ እህቶቿ አግብተው እሷ ብቻዋን ቤት በመቅረቷ ነጭናጫነትዋ እየባሰባት ሄደ። ማንኛውም ትንሽ ነገር ያስቆጣት ጀመር። ለማንኛውም ጥያቄ አይደለም! እንጃ! የሚል መልስ ትሰጥ ጀመር። ተከራካሪ፣ ግትርና ያለራሷ ሃሳብ የሌላን የማትቀበል ሆነች። በመጨረሻ አንድ ለሃገሩ ባዳ ለሰው እንግዳ የሆነ የሌላ ሃገር ሰው መጣ። እሱም በቀጥታ ወደገበሬው ቤት ሄዶ ልጁን እንዲድርለት ጠየቀው።

"እንዲታገባ አልፈልግም" አለ ገበሬው። "እሷን መዳር እፍረት ነው። ጠብ ቆስቋሽ፣ ግትርና ለፊቷ እንኳን ፈገግታ ያልፈጠረባት የተረገመች ልጅ ናት። ልጄን አግብተህ ዘወትር ስትበሳጭ እንድትኖር አልፈልግም" አለ። ጠያቂው ግን በነገሩ ከረረ። "ምንም ዓይነት ጥፋት ቢኖራት እኔ በጣም እፈልጋታለሁ" አለ። በመጨረሻም አባትዮው በመረታት እሺ አለ። እንዲያውም ካሳውን ጭምር ሰጥቶ ሊገላገላት በጣም ተነሳሳ። ወዲያውም ወጣቱ ልጅቱን ጠየቃትና ያለምንም ማቅማማት ጨርቋን ጠቅልላ ለመነሳት ተሰናዳች። ቆማ ቀረች መባል ካሰለቻት በቀር በቤት ውስጥ ብቻዋን ተቀምጣ መዋልም ሞት ሆኖባት ነበር።

እጮኛዋም "የሰርጉ ቀን በቶሎ እንዲወሰንልኝ እፈልጋለሁ። አገሬ ሩቅ በመሆኑ ለመመለስ እቸኩላለሁ" በማለት አጣደፋቸው። የሰርጉ ቀንም ከተወሰነ በኋላ "ቤት አትጠብቁኝ፤ እዚያው እቤተክርስቲያን በሰዓቱ እደርሳለሁ" ብሎ ተሰነባበቱ።

የሰርጉ ቀን ታላቅ ሆነ። ገበሬው ልጁን በሰረገላ ይዟት ቤተክርስቲያን ሄደ። ታላላቅ የመንደሩ ሰዎች ሁሉ ተሰበሰቡ። እህቶቿና አማቾቿ በሙሉ እዚያው ነበሩ። ተሰብስበውም የቤተክርስቲያኑን ግቢ አጣበውታል። ግማሹም ሊያይ የመጣው በሰርጓ እለት ጠባይዋ እንደምን ይሆን ብሎ ነው። በዚህም ዓይነት ህዝቡ ሲጋፋ በመጨረሻ ሙሽራው ደረሰ። ግን የመንገድ የሆነውን ተራና መናኛ ልብሱን እንኳ በሰርግ ልብስ አላጌጠም። ቢሆንም ወዲያው ወደቅድስቱ ቀርበው ቄሱ አጋባቸውና ባልና ሚስት ሆኑ።

ሥርዓተ ጋብቻው ተፈጸመ። በመቻኮል ሙሽራው ወደድግሱ መምጣት ስላልቻለ "ይቅርታ አድርጉልኝ። የምሄድበት አገር በጣም ሩቅ ስለሆነ መጣደፍ አለብን" ብሎ

ወደገበሬው አባቷ ልኮ፣ እጇን እየሳበ ከቤተክርስቲያን ወጣ፡፡ ጊዜው እንደሚፈቅደው የጋብቻ ሰረገላ አልነበረውም፡፡ ተራ ፈረስ በተራ ኮርቻ እንደተጫነ እውጭ ቆሞ ይጠብቃቸው ነበርና በዚያ ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ሙሽራው ዘመድ አልነበረውም፡፡ ግን ከኮርቻው ቦርሳ ውስጥ መጠባበቂያ አንድ ሽጉጥና ከፈረሱ አጠገብ አንድ የማይለየው ውሻ ብቻ አብረውት ነበሩ፡፡

ሙሽራዋ የዚህ ዓይነት ነገር አላስደሰታትም፡፡ ግን በሰርጓ እለት ከሙሽራው ጋር ከመጨቃጨቅ ብላ ለጊዜው አፏን ያዘች፡፡ በእንደዚህም ያለ አኳኋን ብዙ ከተጓዙ በኋላ ብታዳምጥ ምንም የማይናገር ሰው በመሆኑ በመጨረሻው ራሷ ጀመረች፡፡ “ይህ ያለንበት ፈረስ በጣም ቆንጆ ነው” አለች፡፡ “አዎ” አላት መልሶ፡፡ “በጋጣዬ ሌሎች ሰባት ፈረሶች አሉኝ፡፡ ቢሆንም የምወደው እሱን ነው” አላት፡፡ ከዚህ በኋላ ቆንጆውን ውሻ ወደድሁት አለችውና ስታበቃ ቀጥሎ “አዎ ከውሾቼ ሁሉ በላይ የሆነ ጥሩ ተከታዬ ነው፡፡ እሱን በገዛሁበት ጊዜ ብዙ ገንዘብ አውጥቻለሁ” አላት፡፡

ወዲያው በሚጓዙበት መንገድ የነበረ አንድ የሚያቋርጡት ጫካ ገቡ፡፡ በጫካው መካከል ሙሽራው ከፈረሱ ጡብ ብሎ ወርዶ አንድ ሃረግ ቆረጠና እንደቀለበት ገምዶ “ይህ የሰርግሽ ስጦታዬ ነውና በምንም ጊዜ እንደነብስሽ እንድትይዢው” ብሎ ሰጣት፡፡ “ከጅሽ እንዳይለይ፤ ይህንን ብታደርጊ አያስጸጽትሽም” አላት፡፡ ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ እንግዳ ነገር ቢመስላትም ወዲያው ኪሷ ከተተችው፡፡

ከዚህ በኋላ ጥቂት እንደተጓዙ ሙሽራዋ የእጅ ሹራቧ ወደቀባት፡፡ በድንጋጤ ጩኸቷ ዞር ብሎ ሙሽራው ውሻውን አዘዘው፡፡ “እሱን የእጅ ሹራብ አንስተህ እንድትይዘው” አለው፡፡ ውሻው ግን አላስተዋለምና ዝም ብሎት አለፈ፡፡ ከዚህም የተነሳ ሙሽራው ሄድ እንዳለ ቢመለከት ውሻው የእጅ ሹራብ እንዳልያዘ ልብ ስላለ ሽጉጡን አውጥቶ ውሻውን አዳፈነበትና መንገዱን ቀጠለ፡፡ “ምነው ምነው አያሳዝንህም እንዴ?” አለችው፡፡ “አዎ” አላት መልሶ፡፡ “ግን ትዕዛዜን አልደገምም”

ከዚህ በኋላ በጸጥታ ሲጓዙ ቆዩና አንድ የሚያቋርጡት ወንዝ ጋ ደረሱ፡፡ ድልድይ ስላልነበረው በወንዙ ውስጥ መሻገር ግድ ነበረባቸውና ሰውየው ለፈረሱ አለው “ተጠንቀቅ! ምንም ዓይነት ፍንጣቂ የሙሽራዬን ልብስ እንዲያበላሽ አልፈልግም” አለው፡፡ ሆኖም በተሻገሩ ጊዜ ይኸ የጎርፍ ውሃ የመሰለው የሙሽራይቱን ልብስ ብክት አድርጎት

ርሶ ተገኘ፡፡ ባልዮውም ሚስቱን ተሸክሞ ከፈረሱ አወረዳትና ሽጉጡን አውጥቶ ፈረሱን ገደለው፡፡

"ውይ! ምስኪኑ ፈረስ ውይ! ምን አለህ ምነው ገደልከው ምን ጨካኝ ነህ" አለችው፡፡ "አዎ ነገሬንና ትዕዛዜን አልደገምም" አለና ኮርቻውን ልጓሙን ፈትቶ ኮርቻውን ለሚስቱ ሰጥቶ ልጓሙንና ሞቼውን ራሱ ተሸክሞ መንገዳቸውን ቀጠሉ፡፡ አንቺ ያንን ተሸከሚ ብሎ ኮርቻውን ሲሰጣት ለማንገራገር ሞክራ ነበር፡፡ ግን ትዕዛዙ አንዴ ብቻ መሆኑን እስካሁን በተፈጸመው አውቃለችና ወዲያው ኮርቻውን አንስታ ጀርባዋ ላይ ጣል አድርጋ ተከተለችው፡፡

ከዚህ በኋላ ብዙም ሳይጓዙ ወዲያው ቤቱ ደረሱ፡፡ እርሱም በጣም ቆንጆ የእርሻ ስፍራ ነበረው፡፡ ቁጥራቸው የበዛ አሽከሮችና ገረዶች ሲሮጡ ወጥተው ተቀበሏቸው፡፡ ወዲያው የሚከተለውን ትዕዛዝ ሰጣቸው፡፡ "ተመልከቱ ይቺ ሚስቴ እመቤታችሁ ናት፡፡ የጠየቀቻችሁን መፈጸም አለባችሁ፡፡ ትዕዛዙን እኔ እንዳዘዝኳችሁ ቁጠሩት" አላቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ወደቤት አገባትና ሁሉንም ነገር አሳያት፡፡ የእንግዳ ቤት፣ የመብል ቤት፣ የጠጅ ቤት፣ የወጥ ቤት እንዲሁም የቀረውን ሁሉ፡፡ "እንግዲህ የቤት ውስጥ ጣጣው ያንቺ ነው" ኣላትና ከውጭ የሚያስፈልገውን ማንኛውም ጣጣ የኔ ነው አላትና እራት ከበሉ በኋላ ወደመኝታ ቤታቸው ገቡ፡፡

ቀናት ሳምንታት ሆኑ፡፡ ሳምንታትም ወራት ሆኑ፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ብዙዎች ወራት አለፉ፡፡ ወጣቷ ባለቤት የቤት ውስጥ ስራዋን ታቀላጥፍ ጀመር፡፡ ባልዮውም የውጭውን እርሻ በሚገባ አከናወነ፡፡ አንድም ቀን እንኳ መጣላት ይቅርና ፊታቸው እንኳ ጠቁሮ አላወቀም፡፡ አሽከሮቹና ገረዶቹ ያለምንም አልገባኝም የጌታቸውን ትዕዛዝ እንዳከናወኑ ሁሉ አሁንም የመቤታቸውን ትዕዛዝ ፈጸሙ፡፡ ባልዮውም ለሚስቱ ማንኛውንም ነገር በድጋሚ ሳይናገር በአንድ ቃል ስትታዘዘው ስድስት ወራት አለፉ፡፡ ባልዮው ደጓና አክባሪዋ ነበርና እሷም ሩህህና ታዛዥ ሆነች፡፡

ከብዙ ጊዜ በኋላ አንድ ቀን "ወላጆችሽን ልታያቸው ትፈልጊያለሽ?" አላት፡፡ "አዎ ውድ ባሌ" አለችው "የሚመችህስ ከሆነ ላያቸው በጣም እፈልጋለሁ" አለች፡፡ "ይመቻል! ግን ምነው አውስተሽ አታውቂ? ከመቅጽበት መነሳት እንችላለን ሰረገላውን እስክጭን ተሰናጂ" አላትና ወጣ፡፡ ጋጣ ሄዶ ፈረሱን አውጥቶ ሰረገላውን እስኪጭን ድረስ ሚስቱ ወደ እልፍኝ ሮጣ ልብሷን ለባበሰች፡፡ ወዲያው ሰረገላውን አምጥቶ በቤቱ ፊት ለፊት

አቁሞ ጅራፉን አጩሆ "ተዘጋጅሽ" አላት፡፡ "አዎ" ብላ ስትሮጥ ወጥታ ተሳፈረች፡፡ በዚህም ጊዜ መልበሷን ስላልጨረሰች ኩታዋን አጣፍታ ያስተካከለችው ሰረገላ ላይ ከተሳፈረች በኋላ ነበር፡፡

መንገዳቸውን ቀጥለው ግማሽ ጉዞ እንዳደረጉ ብዙዎቹ ጥቋቁር የዝይ መንጋ በላያቸው ላይ አንዣበው ሲያልፉ አየ፡፡ "ውይ እንደምን ያሉ ነጫጭ ቆንጆ ዝዪዎች ናቸው" አለ ባልዮው፡፡ "የለም ጥቁር እኮ ናቸው" አለችው፡፡ "እረ ሊዘንብ ነው መሰለኝ" ብሎ ፈረሶችን መልሶ ወደቤቱ ገባ፡፡ ከዚህ በኋላ አንድ ወር እንዳለፈ "ዛሬ ቀኑ ደህና ይመስለኛል" አሁን ወላጆችሽን ማየት አትፈልጊም?" አለ፡፡ እንደቀድሞው ተዘጋጅተው ሲጓዙ የተሰማሩ ብዙ በጎች አዩ፡፡ "ውይ ምኖቹ ቆንጆ የተኩላ መንጎች ናቸው?" አለ፡፡ "የለም በጎች ናቸው" ስትል መለሰች፡፡ "እረ ዛሬም ሊዘንብ ነው መሰለኝ" ብሎ ተመለሰ፡፡ እቤትም እስከደረሱ ድረስ በሰላም ስለትዳራቸው ተወያዩ፡፡

አሁንም አንድ ወር ካለፈ በኋላ እንደቀድሞው ዘመዶቿን ለመጠየቅ መሄድ ትፈልግ እንደሆነ ጠየቃት፡፡ ደግሞ እንደቀድሞው ሰረገላውን ጭኖ ተሳፈሩና ጉዟቸውን ቀጠሉ፡፡ ጥቂትም ሳይሄዱ ዳክዬዎችን በአንድ ጉርጓድ ሲዋኙ አዩ፡፡ "እንዴ ምኖቹ ቆንጆዎች ቁራዎች ናቸው?" አለ፡፡ "አዎ እስከዛሬ የእነሱን ዓይነት አይቼ አላውቅም፡፡ በጣም ቆንጆዎች ቁራዎች ናቸው" አለች፡፡ በዚያ ቀን የቀኑ የአየር ጠባይ አልለወጠም፡፡ ስለዚህ በሰላም አባቷ ቤት ደረሱ፡፡ አባትዮውም በጣም ተደስቶ ወዲያው ሁለቱ እህቶቿ ከነባሎቻቸው እንዲመጡ አዘዘ፡፡ ሶስቱ እህትማማቾች ተያይዘው ለወሬ ጓዳ ገቡ፡፡ ለብዙ ጊዜም ስላልተያዩ ብዙ ተነፋፍቀው ነበር፡፡ ከዚህም በስተቀር እራት ለማዘጋጀት ረዱ፡፡

ሶስቱ ባሎችና አባትዮው እታዛ ያወሩ ጀመር፡፡ አባትዮውም ቀጥሎ አለ "ይሄው እስከዛሬ ድረስ አልተያየንም፤ ብዙ ቀናችን ነው፡፡ ከዚህም በስተቀር ሶስታችሁንም አንድነት ለማገናኘት የመጀመሪያ ቀኔ ነው፡፡ ለመሆኑ ሚስቶቻችሁ እንደምን ወደዷችሁ?" አሉ፡፡ የሁለቱ ታናናሾች ባሎች ምንም የምናማርረው ነገር የለም፡፡ በጣም ደልቶናል፡፡ ተስማምተናልም አሉ፡፡ የታላቅዮዋ ባልም የመጨረሻዋን ታዛዥና ቅድስት ሚስት ለማግባት የቻልኩ እኔ ብቻ ነኝ አለ፡፡

ገበሬው እድሜ ልኩን ያጠራቀመውን ገንዘብ ወርቅ ገዝቶ በማሰሮ ቀብሮት ስለነበር ማሰሮውን አውጥቶ "የመጨረሻ ታዛዥ ሚስት ላለው ይህንን እሰጣለሁ" ብሎ እፊታቸው አስቀመጠው፡፡ ወዲያው የመሃከለኛዋ ባል በራፍ ላይ ቆሞ "አበባ" አለ፡፡

"ወይ" አለችው፡፡ "ነይ እስኪ አንዴ እባክሽ" አለ፡፡ ቆይታ መጣች፡፡ የቆየችበትንም ወዲያው አስረዳች፡፡ የመጨረሻዋም ታናሽ ልጅ ባል ተራውን "ለምለም አንዴ እስኪ ብቅ በይ" አላት፡፡ ቆይታ መጣች፡፡ ለምን እንደቆየች አስረዳቸው፡፡

የታላቅዮዋ ባል ወዲያው በራፍ ላይ ቆሞ "ፍቅሬ እስቲ አንዴ ነይ" አላት፡፡ በዚያ ጊዜ ድስት ታማስል ነበር፡፡ የሚቀበላት ብታጣ ማማሰያውን ወርውራ ያራል አያርም ሳትል ከመቅጽበት ባሏ ወዳለበት መጣች፡፡ "እግረመንገድሽን ብታውቂው ጥሩ ይመስለኛል፤ ያውልሽ ይሄ ማሰሮ ወርቅ ያንቺ ነው" አላት አባቷ (ሉልሰገድ ዓለማየሁ፣ 1955፡ 8-19)፡፡

**ተረት 72**

**ሰዎች ከአንተ ነው ይሉኛል**

ሰውየው ወደዘመቻ ታዝዞ ሄዶ ሳለ ዘመቻውም ከአራት አመት ይበልጥ ቆየ፡፡ መጀመሪያ ከቤቱ ወደዘመቻ ሲሄድ በቤቱ አንድ አገልጋይ አሽከር ስለነበረው ሚስቴን ጠብቅ ማንም ሰው ከሚስቴ ዘንድ እንዳይገባ ብሎ አዝዞት ስለነበረ ወደዘመቻው የሄዱት ሰዎች ከመቆየታቸው የተነሳ ሚስትዮዋ ስጋዋ ስለሳሳ ያንን አገልጋይ አሽከር ወስልታው ኖሮ አረገዘች፡፡

ይህም እርግዝና እየገፋ ስለሄደባት ይህን ጊዜ ሳይታወቅብኝ በመድሃኒት ላስወርደው ብላ መድሃኒት ጠጣችና ለማስወረድ ያደረገችው መድሃኒት እሷንም ጭምር ስለተቃወማት በመድሃኒቱ አደጋ ሞተች፡፡ ከዚያ በኋላ ከዘመቻ ተመለስ ተባለና ያ ጠብቅ የተባለው አገልጋይ ጌታውን ሊቀበል ወደዘማቾች ዘንድ ተጓዘ፡፡

በመንገድ ጌታውን አገኘውና እጅ ነስቶ መሬት ስሞ ተገናኘው፡፡ ጌትዮውም አንድ የሚወደው ውሻ ስለነበረው ካሽከሩ ጋር ሳይመጣ ስለቀረ ከሁሉ በፊት "ውሻውሳ ወደት ቀረ? ምነው ይዘኸው ሳትመጣ?" አለው፡፡ አገልጋዩም "ውሻውስ ሞተ" አለው፡፡ "በምን ነገር ምን ሆኖ?" ቢለው "የበሬ አጥንት ሲበላ አንቆት ገደለው" አለው፡፡ "የምን በሬ?" ቢለው "ለተዝካር የታረደ" "የምን ተዝካር?" "ለሜቴ ተዝካር" "እሜቴ ምን ሆና ሞተች?" "አርግዛ አስወርዷት" "ከማን አርግዛ?" ቢለው "ሰዎች ከአንተ ነው ይላሉ፤ እኔ ግን አይደለም! እላለሁ" ሲል መለሰለት ይባላል (አበበ አይቼህ፣1943፡18)፡፡

## ተረት 73

## አንተ አወቅኸው ወይስ ሰው ነገረህ?

አንድ ሰው ከጎረቤቱ አንድ በግ ሰረቀና አረደ፡፡ ነገር ግን ወላጅ እናቱ አርጅተው ስለተቀመጡ ለእናቱ ያንን የበግ ስጋ ሊሰጣቸው አልፈቀደምና ደበቀባቸው፡፡ ምክንያቱም በእርጅና የጃጁ ናቸውና ምስጢር ያወጣሉ በማለት ነበር፡፡ እሱም ይህንን ጥንቃቄ ለሚስቱ ነግሯት ወደስራው ሲሄድ ሚስቱ በርጎራጌ "እንዴት እናታችንን ትተን እንበላለን?" በማለት "እናቴ ይህ ስጋ የተሰረቀ ነውና ለማንም ሰው እንዳይናገሩ" ብላ ሰጠቻቸው፡፡

እሳቸውም "አልናገርም፤ ድንገትም ተሳስቶኝ ብናገር አላስይዛችሁም" ብለው ያንን ስጋ ተቀብለው እየመረቁ በሉ፡፡ ነገር ግን ስጋውን በልተው ሲያበቁ በደጅ ቁጭ ብለው ፀሃይ እየሞቁ በጥርሳቸው ውስጥ የተሰካውን ስጋ በስንጠር ሲያወጡ ባለቤቱ፣ በጉ የጠፋው ሰውዬ ደረሰና "እሜቴ! ምነው! ስጋ በልተዋል? በግ አርዳችኋል እንዴ?" አላቸው፡፡ እሳቸውም የተመከሩትን እረሱና "ሰው ነገረህ ወይስ አንተ አውቀህ ነው?" ሲሉ መለሱለት፡፡ እሱም "ለካ በጌን እዚህ ቤት ነው የበሉት!" ብሎ ዳኛ ሊያመጣ ሄደ፡፡

አሮጊቷ ነገሩ እንደተሳሳታቸው ተገነዘቡና "ተሳስቼ ምስጢር ገልጫለሁና ማጭድ ስጡኝ" ብለው ከዚያ ከበሩ ላይ ፈቅ አሉና የጤፉን ቡቃያ ዝርዝር በማጭድ አለፍ አለፍ እያሉ እያጨዱ ባለበጉ ዳኛውን ይዞ ከተፍ ቢል አሮጊቷ እንደጃጁ ሆነው አገኟቸው፡፡ ይህን ጊዜ ዳኛው "እኒህ ለራሳቸው የጃጁ አሮጊት ተናገሩ ብለህ ከሰው ቤት ብርበራ ልትገባ ነው? በል ና እንሂድ" ብሎ ዳኛው ባለበጉን ይዞት ተመለሰ ይባላል (አበበ አይቼህ፣1948፡20)፡፡

## ተረት 74

## ስራው መስከረ

አንዲት ሴትዮ ባሏን ጠልታ ውሽማዋን ስለወደደች ያንኑ የጠላችውን ባሏን አንድ በሬውን ልታሳርደውና ውሽማዋን የበሬ ስጋ ልትመግበው ስለፈለገች ባሏን እንዲህ ስትል ለማታለል ተነሳች፡፡ "ዛሬ በገበያ የአንድ በሬ ቆዳ መቶ ብር ያወጣልና በሬው ታርዶ ቆዳው መቶ ብር ይሸጥ" አለችው፡፡ እሱም ለጊዜው ተታለለና እውነት መስሎት በሬውን አርዶ ቆዳውን ወደገበያ ወስዶ "የበሬ ቆዳ በመቶ ብር የሚገዛ" እያለው በየተራ

ቢዞርና ቢለፈልፍ “ምን ሞኝ ነው ያንድ በሬ ቆዳ በማን አገር መቶ ብር ይሸጣል?” እያለ ሳቀበት፡፡

እሱም በጉዳዩ እያዘነ ያንን እርጥብ የበሬ ቆዳ ተሸክሞ ወደቤቱ ሲገባ የሴትዮይቱ ውሽማ ስጋ ሲበላ ከቤት ኖሮ ባልዮውን ሲያይ ዘሎ ካንዲት ትንሽ ጥራር ጎተራ ውስጥ ጥልቅ አለ፡፡ ባልዮውም አይቶት ኖሮ ያላየ መስሎ ያቺን ጎተራ ያንን እርጥብ የበሬ ቆዳ አለበሰና በመጫኛ ጠፍሮ “ዛሬ ጎተራ ሁሉ መቶ ብር ያወጣልና እሸጣለሁ” አለና ጎተራውን ተሸክሞ ወደገበያ ይዞ ሊሄድ ተነሳ፡፡ ሚስቱም “ጎተራዋ ትንሽ ናት፡፡ ከዚች ይልቅ ትልቁ ጎተራ ይሻላልና እሱን ትተው ሌላ ይውሰዱ” አለች፡፡

እሱም “የለም የለም ይችን ትንሽ ጎተራ ብቻ ነው ወስጀ የምሸጥ” ብሎ ጎተራዋን አፏን በእርጥብ ቆዳው ጠፍሮ ወደገበያ ይዞ ሄደና “በመቶ ብር ጎተራ የሚገዛ” ይል ጀመር፡፡ በኋላም “በመቶ ብር ጎተራዋን የሚገዛኝ አጣሁ ምን አባቱንስ ወደረጅም ገደል አዝልቂ ልወርውረው” ብሎ ወደገደሉ አፋፍ ሲያመራ በዚያው በአቅራቢያው የሚገኙ የዚያው የውሽማው ዘመዶች መቶ ብር እጅ በእጅ ከፍለው ከሞት አድነው ሰዋቸውን ከቅርጫት አውጥተው ወሰዱ ይባላል (አበበ አይቼህ፣1948፡31-32)፡፡

**ተረት 75**

***መፍታት ሳለ መሞት***

አንድ ሰውዬ ብዙ ልጆች ነበሯቸው፡፡ እነዚህም ልጆች ራሳቸውን ተቻችለው ሲኖሩ የአንደኛው እድል አልቃናለት ስላለ በችግር ተሰቃይቶ ይኖር ነበር፡፡ ቢያርስም ቢነግድም አልሳካለት አለ፡፡ ዘመዶቹም ጠሉት፤ ወንደሞቹም ራቁት፡፡ ምናምን አላቀምሰው አሉ፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔርን እገድላለሁ ብሎ ጦሩን በትከሻው ተሸክሞ እግዚአብሔርን ፍለጋ ተሰዶ ጉዞውን እንደቀጠለ አንዲት መነኩሴ አገኝና መነኩሴይቱም “ወዴት አገር ትሄዳለህ?” አለችው፡፡ እሱም “እግዚአብሔርን ፍለጋ” አላት፡፡ እሷም “እንግዳውስ ለእኔም ንገርልኝ” አለችው፡፡ ከእሷም ጥቂት ፈቀቅ እንዳለ  አንድ ሰው በባህር ዳር ቆሞ ሲጸልይ አገኘው፡፡ እሱም ሰውየው “ወዴት አገር ትሄዳለህ?” ቢለው “እግዚአብሔር እንደዚህ አድርጎ ስለበደለኝ እሱን ለመግደል ፍለጋ እሄዳለሁ” አለው፡፡ ያም ሰውዬ “እባክህ ለእኔም ንገረኝ” አለው፡፡

እንደዚህ እያለ መንገዱን ከተጓዘ በኋላ እግዚአብሔር አንድ አልባሌ ሰው ተመስሎ በመንገድ ተገለጸለት፡፡ እሱም "ሰውዬ ወዴት አገር ትገሰግሳለህ" ቢለው "እግዚአብሔር እንደዚህ አድርጎ ስለበደለኝ እሱን ለመግደል ፍለጋ እሄዳለሁ" አለው፡፡ እሱም "ብታገኘው ምን ተደርገዋለህ" ቢለው "በዚህ በያዝኩት ጦር ወግቼ እገድለዋለሁ" አለው፡፡ እሱም "እግዚአብሔር ማለት እኔ ነኝ በል እስኪ ግደለኝ በያዝከው ጦር" አለው፡፡ ሰውየውም ደነገጠና ከመሬት ወድቆ ሰገደለት፡፡

ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር "ምንም የማደርግልህ ነገር የለም ብቻ የፍጥረትን ሁሉ የወፍ የአራዊትና የእንስሳ ቋንቋ ሳይቀር እንዲታውቅ ገልጨልሃለሁ፡፡ ብቻ ለማንም ሰው እንዳትናገር፤ ብትናገር ግን ትሞታለህ" አለውና አሰናበተው፡፡ ሰውየውም ከዚያ ተመልሶ በመንገድ ዳር ከአንድ ዛፍ ስር አረፈና አሳቡን ሲያወጣ ሲያወርድ ትልልቅ አሞራዎች መጥተው ከዛፉ ላይ አርፈው እርስ በርሳቸው ሲጨዋወቱ በዚህ ስፍራ ታላቅ ከተማ ነበር፡፡ በዚህም ዛፍ ስር አንድ ባለጸጋ ብዙ ወርቅ ቀብሮበት ለማንም ሳይናገር ስለሞተ ተረስቶ ቀርቷል ሲሉ አባቶቻችን ከአያቶቻችን የሰሙትን ሲናገሩ ሰምቻለሁ፡፡ ይህም ዛፍ የበቀለው ከዚያን ጊዜ በኋላ ነው ብለው ነግረውኛል አለ፡፡

በዚህ ጊዜ ያ ሰው ሰማና በዚያ በያዘው ጦር የዛፉን ስር ጫር ጫር ሲያደርገው የዋርካው ስር ገፍቶት ወደውጭ ስላለው እንዳጋጣሚ ብዙ ወቄት ወርቅ አገኘና በደስታ ወዳገሩ ገብቶ ሚስጥሩን ለማንም ሰው ሳይገልጥ ንብረቱን አቋቁሞ በደስታ ሲኖር አንድ ቀን ሌሊት ውድቅት ሲሆን ከሚስቱ ጋር ጨዋታ እንደጀመረ በጋጥ ያሉ ፍየሎች በቋንቋቸው ሲናገሩ ባለቤቱ እንደተኛ ሰማና ከት ብሎ ሳቀ፡፡ በዚህም ጊዜ ሚስቱ "ከእኔ ጋር ተኝተህ በምን ነገር ከት ብለህ ሳቅህ? የሳቅህበትን ምክንያት ግለጥልኝ" ስትል በማስገደድ አስጨነቀችው፡፡ እሱም ሚስጥሩን ገልጦ እንዳይነግራት ይህን ነገር እንዳትናገር የተናገርህ እንደሆነ ትሞታለህ የሚል የጠበቀ ትዕዛዝ ስላለበት ነገሩን ለመግለጥ ፈራ፡፡ ቢሆንም ሴትዮይቱ በግድ ስለያዘችው "እሺ ቀን ስጭኝ" አለና ቀጠሮ ተቀበለ፡፡ እስከቀጠሮውም ቀን ድረስ የቁም ተዝካሩን አወጣ፡፡ በተዝካሩም ቀን የእሱና የመንደር ውሾች አብረው ከተዝካር የተረፈውን አጥንት ሲናጠቁ የባለቤቱ ውሻ "ለምን ከቤቴ መጥታችሁ ከተዝካር የተረፈውን ትሻሙኛላችሁ? የእኔ ጌታ አሁን ተዝካሩን አውጥቶ ሊሞት ነው" አላቸው፡፡

"የእናንተ ጌታችሁ ይኖራል" ብሎ ሲነጋገራቸው እነሱ ደግሞ በበኩላቸው "በምን ነገር" ቢሉት "የሁሉን ቋንቋ እንዲያውቅ ጌታዬ እግዚአብሔር ገልጦለት ነበር፡፡ ነገር ግን ይህን

ማወቁን ለማንም ሰው ቢናገር ወዲያው በቅጽበት እንዲሞት ጌታው ስለነገረው አሁን ከፍየሎች አንድ ነገር ሰምቶ ቢስቅ ሚስቱ የሳቅክበት ምክንያቱን ግለጥልኝ ብላ ስላስገደደችው ምስጢሩን ገልጦ ሊሞት አስቀድሞ ተዝካሩን ማውጣቱ ነው" ብሎ ስለነገራቸው "እንዴት ለምን ምስጢሩን ይገልጣል? ምክንያቱን አልገልጥልሽም ብትፈልጊ ሂጂ" አይላትም፡፡ "መፍታት ሳለ መሞት?" ሲል አንዱ ለአንዱ ሲነግረው ባለቤቱ ሰማና "ምንም ቢሆን የሳቅሁበትን አልነግርሽም፡፡ ብትፈልጊ ፈትቸሻለሁ" ሲል ተናግሮ ፈታትና እሱም በደህና ኖረ ይባላል (አበበ አይቼህ፣1948፣ ገጽ 18-19)፡፡

**ተረት 76**

**ላሜ ቦራ**

አንድ ሰውየና አንዲት ሴትዮ ወልደው ከብደው በብልጽግና ሲኖሩ ሴትዮዋ ሊሞቱ ጊዜያቸው ስለደረሰና አንዲት ላሜ ቦራ የተባለች የሚወዷት ላም ስለነበረቻቸው "ላሜ ቦራ የልጆቼን ነገር አደራ" ብለው ሞቱ፡፡ ባላቸው ግን ሌላ ሴት ስላገቡ የእንጀራ እናት ሆነችና ለእነኛ እናታቸው ለሞተችባቸው ልጆች ያረረ የማሽላ ቆሎ ያጓት ውሃ እየሰጠች ለራሷ ልጆች ግን አይብ የማሽላ ቆሎ የፈካውን ትሰጣቸው ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ የእንጀራ ልጆቿ እያማረባቸው ሲሄዱ የእሷ ልጆች እየከሱና እየጎሰቆሉ ሄዱ፡፡ በዚህ ነገር ሴትዮይቱ ስለተቸገረች "እነዚህ ልጆች በዱር ውስጥ የሚበሉትንና የሚጠጡትን በድብቅ ሁናችሁ አይታችሁ ንገሩኝ" ብላ ላከች፡፡ እነሱም ሄደው ባዩ ጊዜ ላሚቱ እየጮኸች ቀርባ ስታጠባቸው አዩ፡፡

እነሱም ወዲያው መጥተው ለናታቸው ነገሩ፡፡ ሴትዮይቱም ባሏ በመጣ ጊዜ "ይቺን ላሜ ቦራ የተባለች ላምህን እረድና ስጋ እንብላ፡፡ ያለዚያ አንተና እኔ ባልና ሚስት አንሆንም" አለችው፡፡ እሱም ላሜ ቦራን ሊያርድ በመጫኛ ጠልፎ እንደጣላት ወግሽታ መጫኛውን በጣጥሳ እነዚያን ሁለት ልጆች በሁለት ቀንዶቿ አንጠልጥላ ይዛ ወስዳ ከአንድ በረሃ ላይ አስቀመጠቻቸው፡፡ እነሱም አንድ ትልቅ ዛፍ ስላለ ከሱ ላይ እየተቀመጡ እሷ ወዲያ ወዲህ ብላ ስትመጣ እየወረዱ ይጠቧት ነበር፡፡ ነገር ግን ከእለታ አንድ ቀን አንበሳና ዝኆን አዳኞች መጡና እነኛን ልጃገረዶች ከዛፍ ላይ ሁነው አዩዋቸው፡፡ እነሱም እነዚያን ልጆች አይተው ተገረሙና በዛፉ ስር ባለው ስፍራ በአንድ በኩል ምንጣፍ በአንድ በኩል ጋሻና ጦር አድርገው ዘርግተው "የሰው ልጆች እንደሆኑ ከምንጣፉ ላይ ይወርዳሉ፣ ሌላ ሁኔታዎች እንደሆኑ ከጦሩና ከጋሻው ላይ ይወርዳሉ" አሉና "ኑ ውረዱ!" አሏቸው፡፡

እነሱም "እናታችን ካልመጣች አንወርድም" አሉ፡፡ በዚህም ጊዜ ላሜ ቦራ መጣችና ከዛፉ ተጠግታ ትጮህ ጀመር፡፡ ከዚህ በኂላ እነሱም በምንጣፉ ላይ ወረዱ፡፡ አዳኞችም አንዷቱን ትልቅዮው፣ አንዷቱን ትንሽዮው አግብተው ወሰዷቸው፡፡ ላሜ ቦራም አብራ ሄደች፡፡ አብራም ብዙ ዘመን ከኖረች በኂላ ባልዮው "ላሜ ቦራ እንግዲህ አረጀች እንረዳት" ሲል ለሚስቱ ነገራት፡፡ እሷም "እንደምን አድርጌ የናቴን ስጋ እበላለሁ?" አለቻው፡፡ ከዚህ በኂላ "እሺ አላርዳትም" አለና ሚስቱ ሳታይና ሳትሰማ በሌላ ጊዜ ላሜ ቦራን አርዶ ስጋዋን በገበታና በሞሰብ አቅርበው ሲበሉ ሴትዮይቱ "ኧረ ይሄ ስጋ በምን ነገር ጣፈጠ? እንደዛሬም ያለ የሚጣፍጥ ስጋ ቀምሼ አላውቅም" ብላ አለችው፡፡ በዚህ ጊዜ ሰውየው "የላሜ ቦራ ስጋ ነው" ብሎ ቢላት በድንጋጤ ወዲያው ሞተች ይባላል፡፡ (አበበ አይቼህ፣ ቢልጮ፣1948፣ ገጽ 54-55)

## ተረት 77

## ስለ አንዷት ገበያተኛ ሴት

አንዷት ሴተኛ አዳሪ ገበያ ወጥታ ወደቤቷ ስትመለስ ከመንገድ ዳር አንድ ማሽላ ጠባቂ አገኘችና ሰላምታ ሰጠችው፡፡ እሱም "እህቴ ሆይ! ዛሬ አንቺ ዘንድ መጥቼ ነው እራቴን የምበላው፤ ተዘጋጅተሽ እንድትቆይኝ" አላት፡፡ እሷም "እሺ ወንድሜ እንዳልክ ፈቃድህን እፈጽማለሁ፡፡ ነገር ግን የማሽላ እሸት አምሮኛልና አንድ ሸክም ይዘህልኝ ና" አለችውና መንገዷን ቀጠለች፡፡ ሁለተኛ ደግሞ አንድ የፍየል እረኛ አገኘችና እሱም እንደዚያኛው እንደፊተኛው ሰውዬ "ዛሬ አዳሬ ካንቺ ዘንድ ነውና እንዷትጠብቂኝ" አላት፡፡ አሁንም "እሺ ወንድሜ እንደፈቃድህ ነገር ግን ስጋ አምሮኛልና ከነዚህ ከፍየሎችህ አንድ ደህና ጠቦት ይዘህልኝ እንዷትመጣ" አለችው፡፡

ከሱም አጠገብ ገና ምንም ያህል ሳትርቅ አንድ የላሞች እረኛ አገኘች፡፡ ለዚህም ሰላምታ ሰጥታው አለፍ ስትል "አንቺ ሴት እስኪ እባክሽ ቆይኝ አንድ የምነግርሽ ጉዳይ አለኝ" አላት፡፡ እሷም ወደ እሱ መለስ ብላ "ወንድሜ ምነው በደህና ነውን ቆይኝ የምትለኝ" ስትል ጠየቀችው፡፡ "ጉዳዩስ ቀላል ነው፡፡ እህቴ ሆይ! ዛሬ እራቴን ካንቺ ቤት ለመብላት አስቤያለሁና ፈቃድ ታደርጊልኝ እንደሆነ" ብሎ መለሰላት፡፡ "ምን ቸገረኝ ነገርግን ወተት ስላማረኝ አንተ ይሄው እንዳየሁህ ባለብዙ ላሞች ነህና አንድ ቅል እርጎ ይዘህልኝ እንዷትመጣ እኔም ተደራጅቼ እጠብቅሃለሁ" በማለት ሸንግላው ሄደች፡፡

አራተኛ ደግሞ አንድ ዱግ ሲጋር በሆነች በቅሎ ተቀምጦ አሽከሩን ነፍጥ አስይዞ ሲያስግር ደረሰባት። "ከወዴት ትመጫለሽ?" ብሎ ጠየቃት። እሷም "ከገበያ ነው ጌታዬ" ብላ መልሳለት እየተጨዋወቱ ጥቂት መንገድ እንደሄዱ ሎሌውን "ከበቅሎ ላይ አውጣት" አለውና አፈናጧት እስከ ቤቷ ድረስ ይዟት ሄደ። "እንግዲህ ማታ መጥቼ ከዚሁ ቤት ራት እበላለሁና ሌላ ሰው እንዳትነጋገሪ። አሁን ግን ከቤቴ ደርሼ ልምጣ" አላት። ጥቂት ቆይቶም ጊዜው መምሸት ስለጀመረ ያ ከገበያ ስትመጣ የቀጠረችው እህል ጠባቂ እንዳዘዘችው አንድ ሸክም የማሽላ እሸት ተሸክሞ መጣ። እሷም የያዘውን ከተቀበለች በኋላ ሰውየውን ከማጀት ገብቶ እንዲቀመጥ አደረገችው። ከእሱ በኋላ ደግሞ ያ የፍየል እረኛ መልካም ሰናፊል አጥልቆ ረጅም ጥብቆ ለብሶ ድጉን ታጥቆ ኩታውን አጣፍቶ ፍየል እየሳበ መጣ። እሱንም ከብቱን ተረከበችና ከድብኝት ውስጥ ደበቀችው። ሶስተኛው ባለላሙ እርጎውን ይዞላት ደረሰ። የወተቱንም ቅል ተቀብላ ከማዘንቱ በላይ ከውሲያኑ ላይ ከሰቀለችው በኋላ ሰውየውን ካልጋ ስር አስገብታ ሸሸገችው። በመጨረሻም በበቅሎ ይዟት የመጣው መኮንን አሽከሩን አስከትሎ ነፍጡን አስይዞ ከተፍ አለ። እሷም ቤቷን አንጥፋ ተዘጋጅታ ትጠብቀው ስለነበር እርጎ የያዘው ጮጮ ከተሰቀለበት በታች ማዘንቱ ላይ አስቀመጠችው።

ጥቂት ጭውውት እንደያዙም ያ ማሽላ ጠባቂ ከጦጣና ከዝንጀሮ ጋር ወዲያና ወዲህ ሲሮጥ በመዋሉ ደክሞት እንቅልፍ ይዞት ኖሮ ከማጀት እንደሆነ ሲቃዥ "ተው በር በሩን ቅደመው" አለ። በዚህ ጊዜ ዱጉ ተነስቶ እሸሻለሁ ሲል የተሰቀለውን የወተት ቅል በራሱ ስለመታው እርጎው በጭንቅላቱ ላይ ተከለበሰበት። ተደናግጦም ነፍጡን እንኳ ሳይዝ ከነሎሌው ፈረጠጠ። ባለፍየሉም ድብኝቱን በታትኖ ኩታውን ጥሎ አውጭኝ እግሬ አለ። ባለወተቱም ከተሸሸገበት ብድግ እላለሁ ሲል አልጋውን አንስቶ በውሃ እንስራውና በቡሃ እቃው ላይ ስለጣለው ሸክላው እንክትክት ስብርብር ብሎ ገደል አፈር ሆነ። መውጫውም ጠፍቶበት ሲደናበር መዝጊያውን ከስር ሰቅስቆ ወንዴውን ነቅሎ እልም ብሎ ጠፋ።

ያ ወተት የተደፋበት ሹም ነፍጡን ጥሎ ነፍሱን አጥቶ እየተክነፈነፈ ከሮጠ በኋላ ከመንገድ አሽከሩን "አንተ ራሴን ተመትቻለሁና እስኪ እባክህ ጎድቶኝ እንደሆነ ቆም ብለህ አይተህ ንገረኝ" አለው። ሎሌውም ጭንቅላቱ ነጭ ነገር ለብሶ አየና "ኧረ ጌታዬ ምንም አልተረፉ ደምዎ አልቆ አንጎልዎ ወጥቷል እንዲያው የሚድኑ አይመስልም፤ አሁን ግን በጠላት እጅ ከምንገባ እናምልጥ" ብሎ ሸሽታቸውን ቀጠሉ።

ባለፍየሉም ባለወተቱም እንደዚሁ እየተከታተሉ ሄዱና ያው በፊት ያገኛት ባለማሽላው ሰው ብቻ ቀረ፡፡ እሱም ይህንን ፍጅትና ሽብር ሳይሰማ ቆይቶ በመጨረሻ ከእንቅልፉ ከነቃ በኋላ ከዚያች ሴት ቤት አድሮ በማግስቱ ጧት አፉን አሟሽቶ ወደማሽላ ጥበቃው ሄደ ይባላል፡፡ (ማኅተመ ስላሴ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ 1960፣ 27-30)

**ተረት 78**

**አንድ ሚስቱ የተጫወተችበት ሰው**

አንድ ሰው ሚስት አግብቶ ይኖር ነበር፡፡ ነገር ግን እሷ ሳያማት ዘወትር አሞኛል እያለች ዝም ብላ በመተኛት ጊዜዋን ስታሳልፍ እሱ ውሃውን ቀድቶ፣ ወፍጮውን ፈጭቶ፣ ከበረት የከብት እበት አውጥቶ ጠፍጥፎ፣ በወንዶች ሙያ ረገድ እርሻውን አርሶ፣ ቆፍሮና አጭዶ ከስራው ሲመለስ ምጣድ ጥዶ እየጋገረ ወጥም እየሰራ ይኖር ነበር፡፡ ከቶ በእድሜው ልክ ምሳ የሚባል ነገር አያውቅም፡፡ ማታ ከስራው ሲገባ መክሰሱንም ሆነ እራቱን እሱው ራሱ አሰናድቶ ይበላል፡፡ ሚስቱ ግን ከሰው ቆጥራ ደክሞታል ብላ ማናቸውንም ነገር ቢሆን አሰናድታለት አታውቅም፡፡

እንደዚሁ ስትጫወትበት ኖራ ሞት አይቀርምና ብትሞት ያለመጠን አድርጎ ፊቱን በዝተት ነጭቶ በገመድ ታጥቆ ደረቱን በድንጋይ እየደበደበ "ከማን እለምዳለሁ፣ እንግዲህ ባህሪዬን ማን ያውቅልኛል፣ እንዳንቺ ማነው የሚያሽሞነሙነኝ፣ እንግዲህ በማነው የምንቀባረረው፣ ኩራቴ በማን ነው፣ እንግዲህ ንብረቴ ተፈታ" እያለ ያለቅስ ጀመር፡፡ በዚህ ሁኔታ አንዱ ባልንጀራው "ምነው ወንድሜ ጓዴ ከሞት የሚቀር የለም ሁሉም እንደምታየው ሟች ነው፡፡ እኛስ ብንሆን ነገ ይህን ትተን ተነገ ወዲያ መሞታችንን መቼ እናውቀዋለን፡፡ ለምን እንደዚህ አድርገህ አጥበቀህ ታዝናለህ ሃዘኑን ተወት አድርገው እንጅ፡፡ በሃዘን መቼ ይገፋል ብለህ ነው፡፡ ትርፉ ዓይንን ማጥፋት ብቻ ነው" ብሎ ቢመክረው "እንደሷ ያለ አይገኝም እንጂ ሴትማ ሞልቶ የለምን እንደሷ ያለ ማንን አገኛለሁ አላገኝም" ሲል መለሰለት፡፡

ከዚህ ወዲያ ሃዘኑን ሲጨርስ ያ ጓደኛው "ወንድ ልጅ ያለ ሴት እንዴት አድርጎ ለመቀመጥ ይችላል" በማለት አስቦ የጨዋ ልጅ ትዳር የምታውቅ ፈልጎ አመጣለት፡፡ በጧት ገና ሴትዮዋ አልጋ ላይ ሆና ሳለች እንደ ልማዱ እንስራውን አንስቶ ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ ለመውረድ ተነሳ፡፡ በዚህ ጊዜ ያቺ ሴት "ወዴት ሊሄዱ ነው ገና

ሳይነጋ ጉድጉድ የሚሉት" ብትለው "የትም አልሄድ ከወንዝ ውሃ ለመቅዳት ነው አሁን እመጣለሁ ዝም ብለሽ ተኚ" አላት፡፡ "እንዴት እርስዎ ውሃ ከቀዱማ ታዲያ እኔ ምን ላደርግልዎ መጣሁ ኧረ በሉ አምጡ" ብላ ሽንጧን ታጥቃ ባንገት ልብሷ አንገቷን ጠምጥማ እንስራውን ከባሏ ተቀብላ ስትንደረደር እወንዝ ወርዳ ውሃዋን ቀድታ ተመለሰች፡፡ ወዲያው ቶሎ ብላ ድስት ጥዳ ለእጅ መታጠቢያ ውሃ በኩስኩስት ወዝታ ማታ ካባት ከእናቷ ቤት ይዛው የመጣችውን የቅቤውን፣ የድልሁን፣ የሽሮውን ቅል አቅርባ ማማሰያዋን አበጅታ ወጧን አሳምራ ከሰራች በኋላ እጁን በሙቅ ውሃ አስታጥባ ምሳውን በደንብ አብልታ "በሉ እንግዲህ ወደ እርሻዎ ይሂዱ" አለችው፡፡ እሱም የማያውቀውን ምሳ በማግኘቱ ሰውነቱ በደስታ ተሞልቶ ከብቶቹን ነድቶ ወደ ግብርና ስራው ሄደ፡፡

እርሻው ወደ ደጋ ነበርና አፋፉን ከወጣ በኋላ ቢያስታውስ ምራኑን ትቶታል፡፡ ስለዚህ ካፋፉ ላይ ብቅ አለና ሚስቱ እንግዳ በመሆኗ በስሟ ለመጥራ ስለፈራ "ኧረ አንቺ ሴትዮ!" ብሎ ተጣራ፡፡ እሷም "ወዲህ ነው ወይ የምትጣሩት" አለችው፡፡ "አዎን" ቢላት "ምነው ምን ሆነዋል?" ስትል ጠየቀችው፡፡ "ኧረ ምራኑን እረስቸዋለሁና አቀብይኝ" አላት፡፡ ያንን ምራን እውሻው አንገት ላይ አሰረችና "እንግዲህ ውሻውን" ይጥሩት አለችው፡፡

እሱም "ኧረ እኔ ውሻ ምን ያደርግልኛል አንቺ ምራኑን ይዘሽልኝ ነዪ" አላት፡፡ "ይጥሩት አልኩዎት" አለችና በቁጣ ቃል ተናገረችው፡፡ ከዚህ በኋላ "ና ቡች! ና! ና! ና!" ብሎ ቢጣራ ውሻው ያንን ምራን ባንገቱ ይዞለት ከተፍ አለ፡፡ በዚህ ጊዜ ልቡ በደስታ ተነካና እዚያው እንደሆነ ተጣርቶ "ከቶ ለመሆኑ አንቺም ትሞቺ ይሆን?" ብሎ ተናግሮ ወደ ስራው ሄደ ይባላል (ማኅተመ ስላሴ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ 1960፣ 53-55)፡፡

### ተረት 79

### አንበሳና አንዲት ሴት

አንዲት ጌኔሆይ ድንቅነሽ የምትባል ሴት ባሏ የጎረቤት ሴት ወዳጅ አበጅቶ በመብልና በመጠጥ ጭምር እየተዳለለ ልቡ ስለተማረከ ጨቅጫቃ ሆኖባት ተቸግራ ትኖር ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ከመጨነቋ ብዛት የተነሳ ምክር አዋቂ ሰው ዘንድ ሄዳ ብትጠይቅ "የአንበሳ ቅንድብ ካመጣሽ እኔ መድሃኒት አደርግልሻለሁ" አላት፡፡ ጌኔሆይ ድንቅነሽም "ይህንንማ ከወዴት አባቴ አግኝቼ" አለችው፡፡ አዋቂውም "እንግዲያውማ ምን ላደርግ

እችላለሁ፤ ያለ እሱ አይሆንም" አላት፡፡ ጌኒሆይ ድንቅነሽ ይህንን በመስማቷ እየተከዘች ወደቤቷ ስትመለስ በመንገድ ላይ ወዳጇ የሆነችውን አንዲት ሴት አገኘችና "ከወደየት ትመጫለሽ" አለቻት፡፡ እሷም "የባሌ ባህሪ ስለተለዋወጠብኝ አዋቂ ዘንድ ብሄድ የአንበሳ ቅንድብ ካላመጣሽ አይሆንም" አለኝ፡፡ "ስለዚህ በጣም ተቸግሬያለሁና ከምን ቦታ እንደሚገኝ እባክሽ ምክር አካፍይኝ" ስትል ጠየቀቻት፡፡ ሴቲቱም "በሬ አርደሽ አንድ አንዱን ብልት እየያዝሽ ከጫካ ከሄድሽ አታጭውም፤ የፈለግሽውን ታገኛለሽ" አለቻት፡፡

ባለጉዳዋም ይህንን ምክር ተቀብላ ከግል ከብቷ ውስጥ ደህናውን መርጣ አሳርዳ ታናሹን በሙዳ በሙዳ ከፋፍላ ተሸክማ እጫካ ሄዳ ስትዞር ስትዞር ውላ አንድ አንበሳ አገኘች፡፡ ገና በሩቅ ሳለ በቁጣ አስተያየቱ በዓይኑ መቅላት በግርማው ማስፈራራት ደንግጣ በመንቀትቀጥ ቆማ ቀረች፡፡ እሱም ጋማውን ነስንሶ ተቆጥቶ ወደሷ መንገድ ጀመረ፡፡ ድንቅንሽም አጠገቧ ሊደርስ ትንሽ ሲቀረው ስጋውን ጣል አደረገችለትና ራቅ ብላ ትመለከተው ጀመር፡፡ የአራዊት ንጉስም ዝም ብሎ ስጋውን መብላት ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ድንቅነሽ ቶሎ ብላ ስጋውን ሳይጨርስ ወደቤቷ ተመለሰች፡፡

ዳግም በሶስተኛው ቀን እንደልማዷ ከዚያው ስጋ ይዛለት ሄደች፡፡ አንበሳውም ልምድ አድርጎ ይጠባበቃት ነበርና የእሷን መምጣት ባየ ጊዜ አውቋት ጭራዋን ነሰነሰ፡፡ ድንቅነሽም በእንደዚህ ያለ ሁኔታ እየተመላለሰች ስጋውን እስኪያልቅ ከመገበችው በኋላ መፍራቷ ቀረና ምግቡን በእጇ ይዛ ልታበላውና ልታጎርሰው ደፈረች፡፡ በልቶ ከጨረሰ በኋላም ታከክ ታከክ እያለ በጠጉሩ ስለሚያሻሻት ሁለቱም ተላመዱ፤ ወዝም ተጣገቡ፡፡ ስለዚህ አብራው ውላ ማታ እቤቷ ሄዳ አደረችና በአራተኛው ቀን እንደዚያው እንደመሰንበቻዋ ያለውን ስጋ ሁሉ ልቅም አድርጋ ይዛለት እጫካው ገባች፡፡ ገና በሩቅ ስትመጣ ባያት ጊዜም ከደስታው ብዛት የተነሳ እየፈነደቀ እየቦረቀ ካጠገቧ ደረሰ፡፡ ድንቅነሽም ባለመፍራት ዝም ብላ እያስተዋለች ስጋውን ሳትሰጥ አቆየችው፡፡ ቢሆንም በማዘግየቷ ዝም ብሎ ይለማመጥ ጀመር፡፡ እሷም እጅግ ደጅ ሳታስጠና ምግቡን አቀበለችው፡፡ በልቶ እንደጠገበ ከላይዋ ላይ ተደግፎ ሽለብ አደረገው፤ እንቅልፍም ድብን አድርጎ ያዘው፡፡ በዚህ ጊዜ ቅንድቡን ልጭት አደረገችው፡፡ እሱም ደንግጦ ምን ነካኝ አለና ተነስቶ ቢያይ ቀላቢው ሆነችበት፡፡ ጥቂት ቆይታም የመጣችበትን ጉዳይ ስለጨረሰች አንበሳውን አሻሽታ አባብላ አገርማ ወደቤቷ ተመለሰች፡፡

ላፍታ ወዲያው እዚያ አዋቂ ሰው ዘንድ ሄደችና "ያልኸኝን ያንበሳውን ቅንድብ አመጣሁ" አለችው፡፡ እሱም ተገርሞ "እንደምን አድርገሽ አገኘሽው? እባክሽ እስኪ

ንገሪኝ?" አላት፡፡ ከዚህ በኋላ ከስር ጀምራ አንድም ሳይቀራት ሁሉንም ዘርዝራ አስረዳችው፡፡ ሰውየውም በጣም አድርጎ ተደነቀ፤ ተገረመ ፡፡ እሱ ግን አስቀድሞ ይህንን አምጪ ያላት አታገኝም በማለት ነበርና መሸነፉን ባወቀ ጊዜ "አንቺ የአራዊትን ንጉስ ያገረምሽ ባልሽ ምን ያቅተኛል ብለሽ ነው እኔ ዘንድ የመጣሽው? አሁንም አንበሳውን እንዳለሰለስሽው ባልሽንም አባብለሽ ተለማምጠሽ ማሸነፍ ትችያለሽ፡፡ ምግብ እንኳን ሰው አውሬ ያለምዳል፡፡ ወንድም ጎኑን ቢጠብቁለት ምግቡንም ባያጎድሉበት ይወዳል፤ ከዚህ በቀር ሌላ መድሃኒት የለውም" ብሎ መከራት፡፡ ድንቅነሽም ተመልሳ ምክሩን ተቀብላ መልካም ምግብና መጠጥ እያዘጋጀች በመስጠት እየተለማመጠች ሲቆጣትም እየቻለች ተስማምታ ቤቷንና ንብረቷን አደርጅታ በሰላምና በጤና ከባሏ ጋር ኖረች ይባላል (ማኅተመ ስላሴ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ 1960፣ 88-90)፡፡

## ተረት 80

## ሴቶች ሹመት እንደለመኑ

ሴቶች ተሰብስበው መሳፍንት፣ መኳንንት፣ አገር ገዢዎችም ሁሉ ባሉበት "እኛስ ብንሆን ሰዎች አይደለንም ምነው አገር ግዛት ሹመት አይሰጠን" ሲሉ አመለከቱ፡፡ የተሰበሰቡት ታላላቅ ሰዎች መልስ ለመስጠት ስለተጨነቁ ምክር አደረጉ፡፡ "ብንሾማቸው ስርዓትና ፍርድ አያወቁ፤ አይሆንም ብንላቸው በየቤታችን ይበድሉናል" የሚል ክርክር ተነሳ፡፡

ከዚህም በኋላ "ወፍ እንያዝና ባገልግል ቀልፈን ከንጉሱ ዘንድ እንላካቸው፤ ያደርሱ እንደሆነ ይሾሙ ካላደረሱ ግን ይቅርባቸው" ብለው ወሰኑ፡፡ ለንጉሱም ይህን ሃሳብ ገለጹለት፡፡ ወዲያው ይዘው ባገልግል ከተው "ይህንን እቃ ለንጉሱ አድርሱ፤ ነገር ግን ምስጢር ነውና ከፍታችሁ እንዳታዩት" ብለው አስጠንቅቀው ላኳቸው፡፡

እነሱም የተሰጣቸውን እቃ ይዘው ሲሄዱ ሳለ በመንገድ ላይ በውስጡ ያለው ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጉ፡፡ በመካከላቸው አንድ እንኳ አይሆንም ባይ ጠፍቶ ባደራ የተቀበሉትን አገልግል ከፈቱት፡፡ ያቺም ወፍ ቱር ብላ ወጥታ አመለጠች፡፡ በዚህ ጊዜ የሚያደርጉትን አጥተው በጣም ተቸገሩ፡፡ በመጨረሻም በወፏ ምትክ ሌላ ነገር ጨምረው ቀልፈው አገልግሉን ወስደው ለንጉሱ አቀረቡለት፡፡ ንጉሡም በዚህ ጉዳይ አስቀድሞ ከመሳፍንቱ፣ ከመኳንንቱ፣ ከአገር ገዢዎችና ከሹማምንቱ ጋር የተነጋገሩበት ስለሆነ "ላኩልኝ ያልኳቸው ይህ አይደለም ወፍ እንጂ ወዴት አለች" አኳቸው፡፡ እነሱም

ነገሩን እንዳወቀባቸው ተረድተው እውነቱን አውጥተው በመንገድ የሰሩትን ስራ ገልጠው ነገሩት፡፡ “እንግዲያውማ በዚህ በትንሹ ነገር ያልተጠነቀቃችሁ ምስጢር ያልጠበቃችሁ ከፍ ያለ ሃላፊነት እንዴት ሊጣልባችሁ ይችላል?” ብሎ የጠየቁትን ሹመት ከለከላቸው ይባላል፡፡ (ማኅተመ ስላሴ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ 1960፣ 95-96)

**ተረት 81**

**የሚስት ዓይነቷ ሶስት ነው፡፡**

ሚስት ይስማው አገር፣ ትሁን ባቦ፣ እናት ለምኔ በመባል አንዷ ካንዷ በጠባይም በምግባርም ትለያለች፡፡ የይስማው አገር የንብረት አያያዝ ዘዴ እንደሚከተለው ነው፡፡

መጀመሪያ ጧት ሰው ሁሉ ገና ከመኝታው ሳይነሳ አስቀድማ ብድግ ትልና ወደጎረቤት ሄዳ አስፈላጊው እቃ በቤቷ እያለ “ዛሬ ጥንስስ እጠነስሳለሁና እባካችሁ መጠንሰሻ ገንቦ አወሱኝ” ብላ ትጠይቃለች፡፡ በሁለተኛውም እቤቷ ገበር ምጣድ እያለ “እንኩሮ አነኩራለሁና ምጣድ አውሱኝ” ትላለች፡፡ ሶስተኛ በማግስቱ “ውሃ እሞላለሁና ድፍድፍ ቅመሱልኝ” እንዲሁም ደግሞ ሶስት ቀን ሲሞላው “ጠላ እሞላለሁና ቅናሽ ቅመሱልኝ” ትላለች፡፡ በመጨረሻም አቀጣጥና ሞልታ ጋኑን ትመርግና ጠላው ሲደርስ አስቀድማ እንደተለመደው እጎረቤት ሄዳ “ዛሬ ጋኑን ከፍቼ ጠላ ስለማነሳ ኑ ቅመሱ” ብላ ትጠራለች፡፡ መጀመሪያ ለመጣው ሁሉ አንዳንድ አንኮላ ከሰጠች በኋላ የተረፈውን ከቅራሪው ጋር ደባልቃ ለዚያ ላቡን ለሚያፈስ ባሏ ታቀርብለታለች፡፡ ባጭሩ የሚያስፈልጋት ማናቸውም እቃና መሳሪያ ተሟልቶ በቤቷ ሲገኝ እጎረቤት ሄዳ ሳታወራና ሰው ሳይሰማው ከቶ የምታደርገው ነገር የለም፡፡ ስለዚህ የዚች ዓይነት ሚስት በማናቸውም ረገድ ለቤቷና ለባለቤቷ ጠንቅ ከመሆን በቀር ጠቃሚነት የላትም፡፡

ሁለተኛ የትሁን ባቦ ስራና ኑሮ፡- ትሁን ባቦ የምትባለው ሚስት ባል አግብታ ስትኖር ልጆች ትወልዳለች፡፡ ባሏ ጧት በረቱን ከፍቶ በሮችን አስወጠወቶ ሲያበላ አርፍዶ ሙሽት ሳያገኝ ወደስራው ሄዶ አርፍዶ ወደቤቱ ሲመለስ አይታ ከልጆቿ ጋር አልጋ ላይ እንደተጋደመች ትቆይና አንደኛውን ህጻን ድብን አድርጋ ትቆነጥጠዋለች፡፡ እሱም ያመውና ምርር ብሎ ያለቅሳል፡፡

ወዲያው ይሄውልህ አፍህን የምታሟሽበት እህል እንዳላሰናዳ ልጆች አውከውኝ አላስነሳ አሉኝ ትለዋች፡፡ ያልታደለውም ሰው አንጀቱ እንደተጣጠፈ ሞፈር ቀንበሩን ተሸክሞ

ወደእርሻው ይሄዳል፡፡ ምናልባት አስባ አሰናድታ ይዛልኝ ትመጣ ይሆናል በማለት ፊቱን ወደቤቱ መለስ አድርጎ ሲያርስ ይውላል፡፡ በቀትርም የሚመገበው ሲያጣ ይደክመውና ጥቂት እንዲግጡ በሮችን ፈትቶ ይለቅና ከጥላ ስር ካረፈ በኂላ እንደገና ጠምዶ ሲያርስ ያመሻል፡፡ ነገር ግን እህል ባለማግኘቱ ይደክምና ተበሳጭቶ ገና ገበሬዎቹ ሳይፈቱ በጊዜ በሮቹን ይለቃል፡፡ ከንዴቱም የተነሳ "ዛሬ በዚህ ጅራፍ ልቧ እስኪጠፋ ገርፌ አባርራለሁ" እያለ በመፎከር ወደቤቱ ይሄዳል፡፡ ነገር ግን ሴቲቱ የመምጫውን ሰዓት ስለምታውቅ ምጣዱን ጥዳ ጭሱ ሲግፈጠፈጥ ልጆቿን በምድጃው ዙሪያ ታደርግና ሁሉንም በተራ ልምዝግ እያደረገች ትቆነጥጣቸዋለች፡፡ እነሱም እርር እያሉ በሚያለቅሱበት ጊዜ አባትዮው ሲደርስ "ስራ አታሰሩኝ እንግዲህ እናንተ ምን ልሁነው ምን ላድርጋችሁ ሊጡን ቀድቼ ልስጣችሁ" እያለች ስትበሳጭ ያገኛታል፡፡ ተናዶ እገርፋለሁ ብሎ የነበረውም እንደገና ያዝንና "አሁን እሷን ያባረርኩ እንደሆነ ልጆቼን ምን አደርጋቸዋለሁ፤ ምናባቱ እነሱ ከሚበደሉ፣ የእንጀራ እናት ፊት ከሚገርፋቸው እኔው እራሴ ልጎዳ 'ትሁን ባቦ' ትቀመጥ" ይልና እንደዋለ ምሳውን ሳይበላ አጣፊኙን ተከናንቦ ለበሮቹና ለላሞቹ በግርግም ገለባ ሊሰጥ ይወጣል፡፡ ከመሸም በኂላ ከብቹን እበረት አጉሮ ወደቤቱ ይገባና ያገኘውን አሹቁንም ምኑንም በልቶ እግሩን ሳይታጠብ ከነጭቃው ይተኛል፡፡ ዘላለም ህይወቱ አለፈ ድረስ እንደዚሁ ሲበሳጭና ሲጎዳ አንድ ቀን የትዳርን አቅድና ዘዴ ሳያይ ይኖራል፡፡

ሦስተኛ እናት ለምኔ፡- የዚችም የትዳሯና የኑሮዋ ዘዴ እንደሚከተለው ይዘረዘራል፡፡ ቀደም ብላ ተነስታ ለባሏ ሙሽት ለቤ አሰናድታ ከመኝታው ቀስቅሳ ታቀርባለች፡፡ እሱም የተዘጋጀለትን እስኪበላ በረቱን ከፍታ የእርሻ በሮችን ወደጓሮ አዙራ ታግጥለታለች፡፡ ሞፈሩን አንስቶ ወደእርሻው ለመሄድ ሲዘጋጅ ቶሎ ብላ ቀንበሩን ተሸክማ ትሸኘዋለች፡፡ እንደተመለሰችም ላሞችን ከጥጆቹ አገናኝታ ወተቱን አልባ ካበቃች በኂላ ከብቶቹ ከመሰማራታቸው በፊት ለረኞቹ ሙሽታቸውን ትሰጣቸዋለች፡፡

የምሳ ሰዓት ሲደርስ ደግሞ የባሏን ምግብ በደህና አገልግል ፈትፍታ የሚጠጣውንም ጠላ በቡይት ይዛ እርሻው ድረስ ትሄዳለች፡፡ እስኪበላ ድረስም በሮችን ወደወንዝ ወስዳ ውሃ አጠጥታ ሳር አግጣ ታቀርብለታለች፡፡ እሱም ይህች መልካም ሚስቱ ባመጣችለት መልካም ምሳና መጠጥ እየተደሰተ እንደገና ጠምዶ ሲያርስ ያመሻል፡፡ እቃዋን ይዛ ስትመለስ በመንገድ ላይ የምታገኘውን ማገዶ ትለቃቅምና ወደቤቷ ገብታ መቆያውንና እራቱን ታሰናዳለች፡፡ በተረፈውም ጊዜ ስፌት ትሰፋለች ወይም ጥጥ ትፈትላለች፡፡

መሸት ሲል ታይናም ወደውጭ ወጥታ ከመንገድ ላይ ቀንበሩን ከባሏ ተቀብላ እያጫወተችው ወደቤት ትገባለች፡፡ ለበሮቹ አስቀድማ ገለባ አቅርባ ወዲያው ለባሏ መቀያውን ካቦሬ ጠላ ጋር ከሰጠችው በኂላ የማታ ስራዋን ታሰናዳለች፡፡ ከብቶችም ከዱር ሲገቡ ከረኞቹ ተቀብላ የቀንድ ከብቶችን ከበረት፣ በግና ፍየሉን ከጋጣ፣ ታጉራለች፡፡ ባሏንም ጥቂት ረፍት እንዳደረገ አይታ ከብቶችን አውሬ እንዳይበላቸው "የላላውን አጥር ውጣና አጥብቅ" ትለዋለች፡፡ እሱም ደስ እያለው በጓሮ ያስቀመጠውን አረግ ወይም ገመድ በውሃ ያርስና የላላውን አጥርና በር ያጠብቃል፡፡ ጨርሶ ወደቤቱ ሲገባም ውሃ በኩስኩስት ታሞቅና እግሩን አጥባ በቅባት ታሽለታለች፡፡ እራት ከበሉም በኂላ ቆጡን አንጥፋ ታስተኛውና የቀራትን ስራ ታጠናቅቃለች፡፡

በእንደዚህ ያለ ደስታ ሲኖሩ ሳለ ከእለታት አንድ ቀን ወንድዮው እሁድ እለት ቤተክርስቲያን ስሞ ሲመለስ በጣም አድርጎ የሚወደውን የድሮ ጓደኛውን እመንገድ ላይ አገኘና "አረፍ ብለህ ውሃ ጠጥተህ ትሄዳለህና ወደቤት እንግባ" ብሎ ለመነው፡፡ እሱም ሳይግደረደር እሺ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ ምናልባት "የሚበላውና የሚጠጣው ይታጣ ይሆን?" እያለ በመጨነቅ በልቡ ሲያወጣ ሲያወርድ ከቤቱ ደረሰና እንግዳውን እደጅ አስቀምጦ ወደሚስቱ ሄደ፡፡ "እህቴ ሆይ ጉድ ፈላብን! ዛሬ የድሮ ጓደኛዬን እመንገድ አግኝቼ ስግደረደር ብጋብዘው እምቢ ሳይለኝ ዝም ብሎ ተከትሎኝ መጣ፡፡ እንግዲህ ምን ላድርገው ላንችም ምንም አልሰጠሁሽ" አላት፡፡ እሷም "አይዞህ ሞልቷል አንተ ብቻ ደህና ሁን እንጂ ግድ የለህም ሂድና እንግዳውን አጫውተው" ብላ ወዲያው ድስቷን ጥዳ ወጡን አድርሳ አፍ ማሟሻ ሰጠቻቸው፡፡ በየጃቸውም አንዳንድ ሽክና ጠላ አስያዘቻቸው፡፡ ቡናም አንድ ጊዜ ወቅጣ ስለምታስቀምጥ እነሱ እስቲበሉ ውሃውን ጥዳ አፍልታ ወዲያው አመጣች፡፡ ቀጥሎም አዲስ የተመረገ ጠላ ስለነበራት በዶጮ ሞልታ "በሉ እየተጫወታችሁ ጠጡ" ብላ አቀረበችላቸው፡፡ ወደደጅም ወጣ ብላ ባሏን ጠቅሳ ጠርታ "ለጓደኛህ አንድ በግ እረድለት ደስ ብሎት ይደር" አለችው፡፡ እሱም እሺ ብሎ ቃሏን ተቀብሎ ከበጎቹ መሃል ደህናውን ሙክት መርጦ አረደ፡፡ ባለቤቱም ቶሎ ብላ አፋጥና ዱለቱን አዘጋጅታ ወጡን በያይነቱ ከሰራች በኂላ ገበታ ጥላ እንግዳውን በመልካም አኳኂን አንድም ነገር ሳይጎድል ጋበዘችው፡፡ አድሮ እንዲሄድም ስለተጠየቀ የናፍቆቱን ያህል ሲጫወት አምሽቶ አኩለ ሌሊት ሲሆን ከድንክ ላይ ተነጥፎለት ተኛ፡፡

ባለቤቲቷም ቀደም ብላ ተነስታ ወጡን ሰርታ ከሰፋቻቸው አገልግሎች ባንዱ ስንቁን አዘጋጀችለት፡፡ ስለእቃውም ሳይቆጫት "ባይመለስ ግድ የለም ነገ ሰፍቼ እተካዋለሁ

አክርማው እንደሆነ ከደጇ ነው እቀጨዋለሁ” እያለች ራሷን በራሷ አጽናንታ “መንገድ በጧት ነውና ተነሱ” ብላ መንገደኛውን ቀሰቀሰች፡፡ ባሏንም ተነስተህ ሸኘው ብላ አስነሳችው፡፡

ከዚህ በኋላ ላፍ ማሟሻ ካሰናዳቸው ምግብ አቀረበችለት፡፡ ለመሄድ ሲነሳም ለመሸኘት እመንገድ ድረስ ወጥታ በሚለያዩበት ሰዓት ባሏን ወደጎን ጠርታ “ደክሞት ሲያርፍ የሚበላው ምሳውን በዚህ አገልግል አድርጌለታለሁ፤ የሚጠጣውንም ጠላ በዚህ ቅል ሞልቸለታለሁና እንካ አስይዘው” ብላ ደብቃ የያዘችውን ሰጠችው፡፡ እሱም እጅግ ተደስቶ ለእንግዳው “ይሄውልህ ወንድሜ ባለቤቴ አስባ ስንቅ አዘጋጅታልሃለች” ብሎ አገልግሉንና ቅሉን ሰጠው፡፡ በዚህ ገዜ በሁሉም ፊት ላይ የሚነበበው የደስታ መጠን ከቶ ወሰን አልነበረውም፡፡

መንገደኛውንም ሸኝተው ወደቤታቸው ሲመለሱ ባልዮው ይህችን ሴት በምን ልመስላት? በእህቴ እንዳልመስላት እህቴም እንደዚህ ያለ አታደርግልኝ፡፡ በእናቴ ልመስላትን? አይ እናቴም ብትሆን ይህንን አታደርገውም፡፡ በጭራሽ ተመሳሳይ የሌላት ናት፡፡ ኧረ የምን እናት እንዲያው ባጭሩ እናት ለምኔ ልበላት እንጂ እያለ ሲናገር እረኞች ከብት ሲጠብቁ ሰምተው ኖሮ እመንደር ወስደው አቶ እከሌ ዛሬ ሚስቱን እናት ለምኔ ሲል ሰማነው ብለው ተናገሩ ይባላል፡፡ (የሴቶችን ባህሪ ለወንዶች እንዲመች አድርጎ ባህሪያቸውን የመቅረጽ አላማ ያለው ተረት ነው፡፡ ወደሌሎችም እንዲደርስ ታስቦ በጎን የሚያደምጡ እረኞች አሉ፡፡ እነሱም ጉዳዩን ወደመንደራቸው ሄደው ሲያወሩ ይስተዋላል፡፡ ሴት የወንድ አገልጋይ እንዲትሆን ታስቦ የተተረከ ተረት ነው፡፡ (ማኅተመ ስላሴ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ 1960፣156-161)

### ተረት 82

### ስለአንዲት ልጃገረድ መታጨት

አንድ የሃገር ቀንደኛ የሆነ ትልቅ ባለጠጋ ሽማግሌ ሰው አንዲት መልከ መላካም ልጃገረድ ልጅ ነበረችው፡፡ ልጂቷም በጣም ስላደገች **ትልቁም እየኮራ ትንሹም እየፈራ** ጠያቂ አጥታ ባባቷ ቤት ብዙ ጊዜ ቆየች፡፡ ከእለታት አንድ ቀንም ሁለት ሰዎች ሊያጯት መጡ፡፡ በዚህ ጊዜ አንደኛውን አስቀድማ ስለጠባዩ ስለባህሪው ብዙ ትሰማ ኖሮ “ይህ እገሌ የሚባለው ሰው አይደለምን?” ብላ ጠየቀች፡፡

ሰዎቹ እሱ መሆኑን አረጋገጡላት፡፡ ከዚህ በኋላ በሌላ ቀን ሁለቱም ፈላጊዎች በየበኩላቸው አማላጅ ልከው ልጅህን ስጠን ብለው አጥብቀው ለመኑት፤ አስቸገሩትም፡፡ አባትዮው የልጂቱን አስተያየት ለመገመትና ለማወቅ ሲል ቀን ወስኖ ሁለቱንም ጠያቂዎች ጠራቸውና መርፌ እና ክር ሰጥቶ "እነዚህን ወርዳቸውና ቁመታቸው እኩል የሆኑ ሽማዎች እኩል ጀምሩና ቀድሞ ሰፍቶ ለጨረሰው ልጄን እሰጣለሁ ብሎ የፈተና ትዕዛዝ ሰጣቸው፡፡ ወዲያው ሁለቱም ተወዳዳሪዎች እንደተባለው መስፋት ጀመሩ፡፡ በዚህ ጊዜ ያ ልጂቱ በህሊናዋ ፈቅዳው የነበረው ሰው በረጅም ክር ይሰፋ ነበርና ክሩ እየተተባተበ እንዳያስቸግረውና በፈተናው እንዳይወድቅባት አስባ ወዲያ እንደሚሄድ ሰው በፊቱ አንድ እቃ ይዛ አለፍ ስትል ጠቀስ አድርጋ "ሰውየው ክር ባጭር" አለችው፡፡ እሱም ነገሯ ቶሎ ገባውና ያንን ረጅም ክር በጥሶ ባጭር ባጭሩ አድርጎ ስለሰፋ ቀድሞ ለመጨረስ ቻለ፡፡ ስለዚህም አባትዮው "ልጂቷን ላንተ ሰጥቸሃለሁ" ብሎ መረቀለትና አሸናፊው ጫማ ስሞ ሄደ ይባላል (ማኅተመ ስላሴ፣ እንቅልፍ ለምኔ፣ 1960፣170-171)

## ተረት 83

### ከአንተ የባሰ እንዳይመጣ ነው፡፡

አንዲት ብዙ ዘመን ያደረጉ ባልቴት ሴትዮ ጧት ማታ ሌት ከቀን "ለንጉስ እድሜ ስጥልኝ" እያሉ ይጸልዩ ነበር፡፡ ይህም ነገር ከጊዜ ብዛት ንጉሡ ሰሙና ተደነቁ፡፡ የተደነቁበትም ምክንያት ሌላ ሳይሆን እራሳቸው ሃይለኛ ነበሩና እንዴት ለእኔ እድሜ የሚለምን ሰው ይገኛል በማለት ነው፡፡ ነዋሪዎችም "ንጉስ ሆይ እርግጥ ያለ ጥርጥር አንዲት አሮጊት ለንጉስ ዕድሜ ትለምናለች" ብለው ለንጉሱ አረጋገጡ፡፡ ከዚህ በኋላ ንጉሡ ያቺ አሮጊት ወዳለችበት ሄዱና ጠየቋት፡፡

"እኔ ክፉና ሃይለኛ ነኝ፡፡ ሰው ሁሉ ሞቴን እንጂ መኖሬን አይደፍግም፡፡ አንቺ በምን ምክንያት ነው ለእኔ እድሜ የምትለምኚው? ለመሆኑ እንደ እኔ አሳብ ቢሆን ሁሉም ይጠላኛል እንጂ ለእኔ እድሜ የሚጸልይ ይኖራል አላልኩም ነበር" ብለው ቢናገሩ አሮጊቷ "ንጉስ ሆይ! በእኔ ዕድሜ ከአንተ ጋራ አራት ንጉስ ማየቴ ነው፡፡ የፊተኛው ደግ ነበር፤ የኋለኛው ክፉ ሆነ፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ሦስተኛው የበለጠ ክፉ ሆነ፡፡ አንተ ደግሞ ከሁሉ የባስክ ክፉ ሆንክ፡፡ ስለዚህ ደግሞ ከአንተ የባሰ እንዳይመጣ ለአንተ ዕድሜ እለምናለሁ" ስትል መለሰችላቸው ይባላል፡፡ (አበበ አይቼህ፣ ጉራማይሌ፣ 1948፣35)

## ተረት 84

### ተናግራ አናግራኝ

ሰውየው ከሰው ጋር ተቀያይሞ ኖሯል፡፡ አንዲት ሴትዮ ለዚያ ለተጣላው ሰው ወዳጁ ኖራለች፡፡ ታዲያ በዘዴ ሄደችና የነገሩን ምክንያት እየዘረዘረች ታወራው ጀመር፡፡ እሱም የእሷን ውስጣዊ ተንኮል አያውቅምና እየተበሳጨና እየተናደደ በዚያ በተጣላው ሰው ላይ ወደፊት የሚያደርገውን የጠብ እርምጃ ዘርዝሮላት ኖሯል፡፡ እሷም የመጣችበትን ከሰውየው ንግግር ሰብስባ ወስዳ ለወዳጇ ለዚያ ሰው ነገረችው፡፡ ያም ሰው ለዚያች ላልታመነች ሴት የነገራት ነገር ሄዶ ከባለጋራው ደረሰና እሱ ያቀደውን መንገድ ቀድሞ ይዞበት ተገኘ፡፡ ሰዎች ግን አንተ መያዝ ይገባህ ነበር አሉት፡፡ እሱም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፡-

> ተናግራ አናግራኝ፣
> ያንን ወስዳ ለሰው ነግራብኝ፣
> ያቺን ሰው ሰው አትበሉብኝ፡፡

አለ ይባላል፡፡ (አበበ አይቼህ፣ጉራማይሌ፣1948፣35)

## ተረት 85

### እኔውም

በጥንት ዘመን ነው ይባላል፡፡ ታዲያ አንድ ተማሪ የጨዋ ሚስት ለምዶ ኖሮ ያቺን ውሽማውን "እኔ ባልና ሚስት የሚያዋድድ አውቃለሁ" አላት፡፡ እሷም "እንግዳስ ካልክስ እኔም ባሌ እንዲወደኝ መድሃኒት ስጠኝ" አለችው፡፡ ተማሪው ግን በውስጥ ተንኮል የሴትዮይቱን ባል ለመግደል አስቧልና አንድ የሚገድል መድሃኒት ቀምሞ "በይ ይህንን መድሃኒት በወጥ አድርገሽ ስጪው" አላት፡፡ እሷም ዘዴኛ ናትና "አስቀድሜ ለባሌ ከማበላው ለእሱ ለውሽማዬ ላብላውና ማስወደዱና አለማስወደዱን ልፈትነው" ብላ በስውር መልሳ ለሱው አበላችው፡፡ መድሃኒቱ የሚገድል መድሃኒት ስለሆነ ወጡን በቀመሰ ጊዜ አመመውና በጣር ተያዘ፡፡ በዚህም ጊዜ "አንቺ! ያን የሰጠሁሽን ከዚህ ወጥ ላይ ጨምረሽዋልን?" ሲል ጠየቃት፡፡ እሷም "አዎን አንተ ውሽማዬ እንዲትወደኝ በማለት አብልቸሃለሁ" አለችው፡፡ እሱም "እውነት ነው! እኔም አብዝቸው ነበር" አለና ወዲያው በዚያ መድሃኒት ድብን ብሎ ሞተ ይባላል፡፡ (አበበ አይቼህ፣ ጉራማይሌ፣ 1948፣60-61)

## ተርት 86

## እስከዛሬ የት ነበርሽ

አንድ ሰውየ ሚስት አግብቶ ሲኖር ከዚያ በፊት ሌላ ሴት አግብቶ አያውቅም ነበርና ለዚህ ለሚስቱ ውሃ ቀድቶ፣ ሙቀጫ ወቅጦ፣ እግር አጥቦ፣ ሲኖር ያቺ ሞተችበትና ሌላ ሚስት አገባ። እሱም የባልና የሚስት አስተዳደር እንደዚህ ይመስለው ነበርና እንደዚያው እንደለመደው በሮቹን አቁሞ ጅራፉን በትከሻው አድርጎ መጣና "አንቺ! እንስራውን አምጪ" ብሎ አለ። "ለምንድን" ብትለው "ውሃ ላምጣልሽ ብዬ ነው" አለ። እሷም "ኧረ እኔ አምጥቻለሁ" አለችው። ደግሞም ሁለተኛ "አምጭ ገብስ ልውቀጥልሽ" አላት። እሷም "ግድ የለም እኔው እሰራዋሁ" አለችው። ሦስተኛ ማታ ከእርሻ ሲመለስ እግርህን ልጠብህ አምጣ ብትለው እሱም እንደገና አምጪ ያንቺን እግር ልጠብልሽ አላት። አምጣ ያንተን አምጪ ያንቺን በመባባል ተጣሉና እሱም ጠልታኝ ነው እንጂ ብትወደኝ ኖሮማ ቢሆን እግሯን ታሳጥበኝ አልነበረም በማለት በሃሳብ ሲበሳጭ ሳለ እሷ ደግሞ በበኩሏ እንደዚህ ስትል ሰማት።

ቢሄዱ ብዙ ነገር አለ፤ እንዴት ወንድ ልጅ የሴት ስራ ልስራ ይላል? እንዴትስ የሴትን እግር ልጠብ ይላል? ብላ ስትገረም ሰማት። እሱም አሳቡን መለሰና ለካ እንደዚህ ነውን? ብሎ በነገሩ ተገነዘበና ዝም ብሎ የወንድ ስራውን ይሰራ ጀመር። እሷም ውሃ ቀድታ፣ ወቅጣና ፈጭታ ወጥና እንጀራውን መልክ ባለው ሁኔታ አዘጋጅታ፣ የዶሮዓይን የመሰለ ጠላዋን ጠምቃ፣ እግሩን በሙቅ ውሃ አጥባ፣ ሰውነቱን ገደፍ የሚልበትን አንድ ምቹ ነገር አሰናድታ፣ በእኔ ሞት እያለች በማጉረስ ደስ በማሰኘት አስመሸችው። እሱም ባለፈው ጊዜ ባላዋቂነት ያሳለፈውን ጊዜ በመመልከት "እስከዛሬ የት አባሽ ኑረሻል?" ብሎ በጥፊ አላት ይባላል። በዚህ ጊዜ እሷ እሪ ብላ ጮኸችና ጎረቤት ሁሉ ተሰበሰበና "ምነው እንደዚህ ታደርጋለህ?" ቢሉት "እንደዚህ ያለችው ሴት እስከዛሬ የት አባቷንስ ነበረች?" አላቸው ይባላል። (አበበ አይቼህ፣ጉራማይሌ፣1948፣60-61)

## ተርት 87

## ጣያት

በድሮ ጊዜ ነው ይባላል። ሰውዬው ሚስቱ እየቀናች ስታስቸግረው ጊዜ ለአንዱ ጓደኛው አማከረው። ያም አንድ ምክር ሰጠውና እንደመከረው አንድ ነገር መሳይ በጉያው ይዞ

መጣና እንደተለመደው ሴትዮይቱ ጭቅጭቅ ስትጀምር "ያውልሽ ቆርጬ ጣልኩልሽ" ብሎ ሰውነቱን አስመስሎ ለድመቷ ጣል አደረገላት፡፡ ድመትም ያንን ያዝ አድርጋ ስትበር ሴትዮይቱ ብትር መሳይ ይዛ "ጣያት! ጣያት!" እያለች ታባርር ጀመር፡፡ ነገሩ ለማሳቅ ነው እንጂ የውነት አይደለም፡፡ (አበበ አይቼህ፣ጉራማይሌ፣1948፣82)

## ተረት 88

### አሁን ይዤው!

ሴትዮይቱ ባል አገባችና ባለሙያ ልትመስል ወንድ ሞኞን ልታሞኝ እሱ ሲመጣ ሲመጣ እንዝርቱን ብድግ እያደረገች ትፈትላለች፡፡ ባሏ ሲሄድ ግን እንዝርቱን ታስቀምጥና ጊዜዋን በከንቱ ታሳልፋለች፡፡ ባልዮውም "የእኔ ሚስት ፈታይ ናት፤ ነገር ግን በቤታችን ውስጥ የለት ልብስ የለም" እያለ ስለምን ልብስ አይሰራም ብሎ ሲጨነቅ ከእለታት አንድ ቀን ሴትዮይቱ ወጣ ስትል እንዝርቱን አንስቶ ደበቀባትና ዝም ብሎ ወደ ስራው ሄደ፡፡

እሷም እንደልማዷ ስታስበው ውላ ባሏ ሲመጣ እንዝርት ልታነሳ ከቦታው ብትፈልግ አጣችውና ትዘብር ጀመር፡፡ እሱም የት አድርገሽው ነበር ቢላት "ኧረ አሁን ይዤው ነበር ስፈትልበት" አለችው፡፡ እሱ ግን በዚህ ነገሩን ስለተረዳው ከቤቱ አስወጣት ይባላል፡፡ (አበበ አይቼህ፣ጉራማይሌ፣1948፣89)

## ተረት 89

### የታል ግርግሩ

ሰውየው ያለ ወትሮው ዘዋሪና መሸተኛ ስለሆነ ሚስቱ ከእለታት አንድ ቀን በያይነቱ ምግብ አዘጋጅታ፣ ቤቷን በሚገባ አጽድታ፣ አበቦችንና ልምላሜዎችን በጠረጴዛ ላይ አድርጋ፣ ራሷን አጽድታ፣ ጥሩ የክት ልብሷን ለብሳ ተቀመጠች፡፡ እሱም ያንን ሁሉ ዝግጅት ትቶ እንደልማዱ ሊሄድ ተነሳ፡፡ በዚህ ጊዜ እንዲህ ስትል ጠየቀችው፡፡ "ወዳጄ ሆይ! ከእኔስ የምታምርና ከእኔስ የበለጠ ጌጥ ያጌጠች፣ ከእኔስ ቤት የበለጠ መጠጥና ጽዳት የምታገኝ ይመስል ወዴት ልትሄድ ነው? ሁሉም በቤትህ ሞልቷል" አለችው፡፡ እሱም "እውነትሽን ነው ካንቺ የበለጠ ሴትና ከዚህ የበለጠ መጠጥ፣ ከዚህ የበለጠ ጽዳት አላገኝም፡፡ ነገር ግን ግርግሩ የታል?" አላት፡፡ ብዙዎች እንደሚሉት ከመጠጥ ቤት የምንሄደው ለጨዋታ ነው ይላሉ፡፡ እውነቱ ቢሆን ግን ለጨዋታ ሳይሆን ለልማድ ነው፡፡ (አበበ አይቼህ፣ጉራማይሌ፣1948፣97)

## ተረት 90

### ወንደላጤውና ፈላስፋው

አንድ ሰው ባንድ አገር ሲኖር ገንዘብ ቢያገኝም አይጠራቀምለትም ነበርና በችግር ይኖር ነበር። አንድ ፈላስፋ አገኝና "ወንድሜ ምከረኝ፤ ገንዘብ አገኛለሁ፣ አልሰበሰብ አለኝ። ስለዚህ ነገር ምከረኝ" አለ። ያም ፈላስፋ ሲመክረው እንዲህ ብሎ መከረው "ምሽት አግባ" አለው። ያም ሰው እንዲህ አለ። "እኔ እበላውና እለብሰው ሳጣ ደግሞ የምሽት ልብስና ቀለብ ታገኛለህ ትለኛለህ። ይህስ ክፉ ምክር ነው እንጂ የቀና ምክር መስሎ አልታየኝም" አለው። ያም ፈላስፋ እጅግ ብዙ አድርጎ የእሸት አዝመራ አለው። ከዚያ ገብስ ያንን ድሃ "በቀኝ እጅህ ቆርጠህ በግራ እጅህ ሳትቀበል የሚያጠግብህን ያህል በብዙ አምጣ" አለው። ያም ድሃ ከእርሻው ገብቶ ይቆርጥ ጀመር። ያ ባለጸጋ አንድ ሰዓት ያህል ቆይቶ ጠራው። ጥቂት ገብስ እሸት ቆርጦ መጣ። "ምነው እስከ አሁን ድረስ ቆይተህ ይህንን ጥቂቱን ይዘህ መጣህ?" አለው። ያ ድሃ እንዲህ ብሎ መለሰ። "የኋለኛውን እሸት ስቆርጥ የቆረጥኩት እየወደቀብኝ በአንድ በቀኝ እጄ ስለሆነ ነው" አለው። ሁለተኛ ባለጸጋው እንዲህ አለ ለድሃው ሲነግር "በቀኝ እጅህ እየቆረጥህ በግራ እጅህ እየተቀበልህ ገብስ እሸት አምጣ" አለው። ያም ድሃ ከባለጸጋው እርሻ ገብቶ በቀኝ እጁ እየቆረጠ በግራ እጁ እየተቀበለ ባንድ ጊዜ የሚያጠግብ አመጣ። ፈላስፋው ለድሃው እንዲህ አለው። "እየው ተመልከተው ቀኝ እጅና ባለቤት አንድ ነው። ግራ እጅና ሴት አንድ ነው። በተቀባይነት በግራ እጅህ እንደተቀበልክ ምሽትህም ትቀበላለች፤ ገንዘብም ይሰበሰባል። በአንድ እጅህ ቆርጠህ በአንድ እጅህ እንዳልተሰበሰበልህ ያለሴትም የአንድ ሰው ብርቱ የለውም። አንተም ብቻህን ብትሆን ነው" አለው። ከዚህ በኋላ ነገሩን ተረዳና ምሽት አገባ። አንድ ዓመት ሳይሞላው እጅግ ብዙ ንብረት አገኘ።

(ተስፋዬ አካሉ፣ የ2007፣ 34)

## ተረት 91

### የዝሙተኛዋ ሴት ማታለል

አንዲት ሴት ነበረች፤ ነጋዴ አገባች። እሱም አንድ ዓይና ነው። ለንግድ እሩቅ አገር በሄደ ጊዜ ውሽማ ያዘች። ያም ነጋዴ ባሏ ብዙ ቀን ቆይቶ መጣ። የሚስቱም ውሽማ ደንግጦ ከማጀት ተሸሸገ። ሚስቱም ውሽማዋን ከማጀት ለማስወጣት ዘዴ ፈለገች። ባሏን እንዲህ አለችው። "አሁን እግዚአብሔር አያድርግብህና ይህንን አንዱን ዓይንህን እንዲህ

አድርጎ ቢጨፍንህ ምን ባልህ?" አለችውና ስትጨፍነው ውሽማዋ ከማጀት አይቶ ወደ እዳሪ እወጣሁ ብሎ ከደጃፍ ሲደርስ ወደቀ። እሷም ምሽቱ እንዲህ ብላ ምክንያት አመካኘች። "የሁለታችሁ ፍቅር ከቶ ምን ይበዛ ነው፤ ናፈቁና ባሌን ለማየት ሲቸኩሉ ክፉኛ ወደቁ" ብላ ስትናገር ሰምቶ ውሽማዋ ከእዳሪ የመጣ መሰለና ከባሏ ጋር አንገት ላንገት ተቃቅፈው ተገናኙ። ሳይታወቅ ቀረ። ምሽቱ በምክንያቷ በጥበቧ ውሽማዋን ከባሏ እጅ አዳነችው። ተስፋዬ አካሉ፣ የኣማራ ህዝብ ተረቶች፣ 2007፣ 46)

## ተረት 92

### ቢከፍቱት ተልባ

ሰውየው ከጓደኛው ጋር ሲጫወት የምድር እምብርቱን፣ የኮከብ ብዛቱን፣ ሳላውቅ ብቀር ንብረቴ ሁሉ ልቅ ይሁንብኝ ብሎ ተወራርዶ ነበር። ነገሩ በስህተት የሆነና ንብረቱም በተወራረደበት ተረትቶ የሚወሰድበት መሆኑን ስለተገነዘበው እራቱን አልበላም፣ ምኝታም አልተኛም፣ ስላለና በሃሳብ ባህር ገብቶ መዋኘት ስለሆነ ሚስቱ ምን ሆንክ ብላ ብትጠይቀው እሱም አልናገርም በማለት ጥቂት ከቆየ በኋላ የእሷ ጥያቄ ስለበዛበት "እኔ ዛሬ ከጓደኞቼ ጋር በጨዋታ ምክንያት አንድ ነገር ተስቶኝ በቁም ነገር ገብቼ ንብረቴ ልቅ ይሁንብኝ ብዬ ስለተወራረድኩኝ አሁን የምድርን እንብርት፣ የሰማይን ኮከብ ብዛት ለማወቅ አልቻልኩም" ሲል ተናገረ።

ሚስቱም እውቀት የተመላች ስለሆነች እስዋም እንዲህ ስትል ምክርዋን ሰጠች። "ወዳጄ ሆይ! ይህ በጣም ቀላልና እጅግ የማያስቸግር ጉዳይ ስለሆነ አንድ ዘንግ ቁረጥና እሱን ይዘህ የምድር እንብርት በዚህ ዘንግ ይህንን ያህል እልፍ ይሆናል። እስከዚህ ድረስ ነው በል። ቢፈልጉና አሰት ቢሉህ በዚህ ዘንግ ለክታችሁ እርቱኝ በላቸው። የሰማይም ኮከብ በአንድ ማድጋ ጤፍ ልክ ነው  በላቸው። አሰት ቢሉ ቆጥረሁ እርቱኝ በል" አለችው። እሱም ከዚህ በኋላ እፎይ ብሎ አሳቡን አረጋና እራቱን በልቶ ውሃ ጠጥቶ አደረ። በነጋታው ያንን ዘንግ ያዘ ሄደና "የምድር እምብርቱ ይሄውና። አሰት ብትሉ ለኩት። እንዲሁም የሰማይ ኮከብ በአንድ ማድጋ ጤፍ ልክ ነው። ይህንንም አሰት ብትሉ ተቆጥሮ ይለካ" አለ። ይህንን ጊዜ ዳኛው መስፍኑ "ምን ዓይነት ትምህርት ቢኖርህ ነው ይህንን ብልሃት ለማወቅ የቻልከው ወይስ ምን መክሮህ ነው?" ሲል አስጨንቆ ጠየቀው። እሱም "ጌታዬ ሆይ! ሚስቴ እጅግ ብልህና አዋቂ ናት። ከዚህም ሌላ መልኳ እጅግ የተዋበ ቆንጆ ነው። ስለዚህ ይቺ ብልህና ቆንጆ የሆነች ሚስቴ መከረችኝ" አለው።

መስፍኑም ይህንን ነገር ከተገነዘበ በኂላም “ይኸ ከመልክ የበለጠ መልክ ያላት ከእውቀት የበለጠ እውቀት ያላት ከሁሉም አሟልቶ የሰጣት ሴት ለአንተ የምትገባ አይደለችም ለእኔ ነው እንጂ። አሁንም ደግስና ቆየኝ እኔ እወስዳታለሁ። ሚስትነቷ ለእኔ ነው የሚገባው” አለው።

እሱም ከፊተኛው የበለጠ ድንጋጤ ወደቀበትና ወደቤቱ ሄዶ እህልም አልበላ፣ ውሃም አልጠጣ፣ አልተኛምም በማለት በአሳብ ባህር ገብቶ ይዋኝ ጀመር። ሚስቱም “ደግሞ ዛሬ ምን አገኘህና ነው አሳብ ገብቶ የሚወዘውዝህ” አለችው። እሱም መኮንኑ እንደነገረው አድርጎ ነገራት። እሷም ብልህነት ያደረባት ሴት ናትና “ይህስ ትንሽ ጉዳይ ነው። ይምጡና ይውሰዷት በላቸው። ድግስም እንደግስ” ብላ ድግሱን ደግሳ መሳፍንቱ እንድጠራ አደረገች። ለድግሱም ብዙ ድስት ሰበሰበችና በሁሉም ተልባ በጠበጠችበት። በመጀመሪያው ድስት የወርቅ ሙካሽ፣ ቀጥሎም የሃር፣ የከፋይ፣ የሹት፣ ማንሰሻ እስከለበሰው ድረስ አልብሳ አቀረበች። መኮንኑም ባለበት አዳራሽ ድስቱ ሁሉ ቀረበና የመጀመሪያው የወርቅ ሙካሽ የለበሰው ቢገለጥ በውስጡ ያለው ተልባ ሆነ። ሁሉንም መደዳውን ያለውን ቢከፍቱት እንደዚያው ተልባ ሆነ። በዚህ ጊዜ መስፍኑ ተቆጣና “ምንድን ነው ይሄ ነገር?” ሲል ጠየቀ።

ያቺም ሴት ወደዚያው ከባሏ ጋር ሆና ቀረብ አለችና “ጌታዬ ሆይ! እኛ ሴቶች የውጭ መልካችን በየዓይነቱ ቢሆን የውስጡ አካላችን የሁላችንም አንድ ዓይነት ነው። ስለዚህ የእኔን የውጭ መልክ አይተው ይህንን ባሌን በማሳዘን እግዚአብሔርን እንዳያስቀይሙት” አለችው። መስፍኑም ሴትዮይቱን በማመስገን የእርዳታ ገንዘብ ወርቅና ብር ሰጥቶ ከግፍ ስራ ታግሶ ወደነበረበት ተመለሰ ይባላል። (አበበ አይቼህ፣ጉራማይሌ፣1948፣109-110)

## ተረት 93

### በምራቱ የተበደለ ሰው

አንድ ሰው በአንድ ሃገር ምሽት አግብቶ ሲኖር አረጋዊ የሸመገለ አባት ነበረው። ከቤቱ ይዞ ይረዳው ነበር። ምሽቱ የባሏን አባት አትወደውም ነበር። ትጠላዋለች። ባሏም ወንድ ነውና አያይም። ከምግብ የከፋውን ለባሏ አባት ታበላዋለች። የጣፈጠ ምግብ አቅርባለት አታውቅም። ከጥሩ ውሃ በቀር የሚጠጣ ነገር ሰጥታው አታውቅም። አንድ ቀንም ጠላ ብታደርግ መጥፎ ሆነባት። ስለዚህ የባሏን አባት እንዲህ አለችው። “አባቴ

ጠላ ልስጥዎት” ብትለው “ክፉስ ልጁ!” አላት፡፡ ወትሮ ከመልካሙ ጠላ ሰጥታው አታውቅምና “ክፉስ!” አላት፡፡ (ተስፋዬ አካሉ፣ የኣማራ ህዝብ ተረቶች፣2007፣ 52)

**ተረት 94**

***ሦስቱ ሞኞች***

ሦስት ሞኞች ሰዎች ነበሩ፡፡ እነዚያም እህል ወቅተው መሸባቸው፡፡ ወንበዴ ያስፈራል፤ ገለባ ለብሰው ተኙ፡፡ ወንበዴዎች በጊዜ አይተዋቸዋልና ገለባውን በጦር እየወጉ ሲፈልጉ እህል ያለበትን ዳውላ ወጋው፡፡ አንዱ ሞኝ “እኔን ወጋሁ ብሎ ዳውላውን ወጋው” አለ፡፡ ያን ሰምቶ ራሱን ወጋው፡፡ አሁንም ሁለተኛው እንዲህ አለ፤ “ወይ አፍ አለማረፍ፤ አፉ አላርፍ ብሎ ወጋው” ብሎ ከንቱ ፍርድ ፈረደ፡፡ የእሱንም ቃል ሰምቶ ወጋው ሁለተኛ፡፡ አሁንም ሶስተኛ የተሸሸገው የሞኝነት ፍርድ ፈረደ፡፡ “እኔ እሻል ዝም ያልኩ፤ አላርፍ ብለው ሞቱ ወንድሞቼ” ሲል ቃሉን ሰምቶ ገደለው፡፡ ሶስቱንም ስለሞኝነታቸው ፈጃቸው፡፡ አንድም አልዳኑ ሽፍታ ገደላቸው፡፡ (ተስፋዬ አካሉ፣ የኣማራ ህዝብ ተረቶች፣2007፣ 66)

**ተረት 95**

***ፈጣኑ መልስ***

አንድ ሰው ነገር አዋቂ እጅግ ተጨዋች ነበር፡፡ በአንድ ሃገር ያደረለት ጌታ ነበር፡፡ ጌታውም ማር አስገዛለሁ ብሎ ተጨዋች አሽከሩን አስከትሎ ወደገበያ ሄደ፡፡ ገበያም ቢደርስ ማር ተወደደበትና ከማር ገበያ ተቀምጦ ሳለ ከጌታው ጫንቃ ላይ አንዲት ንብ ተቀመጠች፡፡ አሽከሩም “ጌታዬ! ከጫንቃዎ ላይ ተቀምጣለች” አለው፡፡ ጌታውም ለአሽከሩ እንዲህ አለው፤ “አንቺ ትላለህ ሴትነቷን በምን አወቅክ” ቢለው አሽከሩም እንዲህ ብሎ መለሰለት፤ “በመንደፏ፣ እንጀራ በመጋገርዋ” አለ፡፡ ስለዚህ ነገር ባለቤቱ ተሸነፈ፤ አልመለሰለትም፡፡ (ተስፋዬ አካሉ፣ የኣማራ ህዝብ ተረቶች፣2007፣ 73)

**ተረት 96**

***አቅም ያጣ ቁጣ***

አንድ ሰው ባንድ አገር ይኖር ነበር፡፡ እሱም ከስራ ውሎ ወደቤቱ በመጣ ጊዜ ምሽቱ እግርህን ልጠብህ ብላ ልታጥበው እግሩን ብታነሳው ጣጥ አድርጎ ፈሳባት፡፤ እሷም ደንግጣ “ታጠቅ!” ብላ በጥፊ ፊቱን መታችው፡፡ ከዚህ በኋላ በቁጣ ቃል እንዲህ ሲል

ተናገረ፡፡ “እኔ ብርቱ ቅጣት እቀጣሽ ነበር፡፡ ነገር ግን ምን ይሆናል ነገር በምን ተነሳ ብሎ ገላጋይ ይጠይቀኛል” ብሎ ሳይመታት ቀረ፤ ዝም አለ፡፡ (ተስፋዬ አካሉ፣ የአማራ ህዝብ ተረቶች፣2007፣ 86)

**ተረት 97**

**የዝናቡ ጊዜ**

በአንድ መንደር በግ ይጠፋና ሰዎች አውጫጭኝ ይጀምራሉ፡፡ ሆኖም ግን ፍንጭ ይጠፋል፡፡ ሽማግሌዎቹ ቁጭ ብለው መምከር ሲጀምሩ ከመሃል አንድ ሽማግሌ ይነሱና “ወዳጆቼ! የጀመርነው ስራ ወጤት አልባ መሆኑን አየነው፡፡ እንደ እኔ ከሆነ አዋቂዎችን ትተን ህጻናቱን እየጠራን የአውጫጭኙን ስራ ብንቀጥል ጥሩ ይመስለኛል፤ ህጻናቱ አይዋሹም” ይላሉ፡፡ የሽማግሌዎቹ ጉባኤ በነገሩ ይስማማና ትኩረቱን ህጻናቱ ላይ ያደርጋል፡፡

የተሰረቀው በግ ገብቶ በታረደበት ቤት አንድ ህጻን አለ፡፡ ወላጆቹ የሰረቁትን በግ ለምግብነት አዘጋጅተው ሲያበቁ የእራት መብያ ሰዓት ይደርስና የህጻኑ እናት ልጁ ይቀስቀስና እራቱን ይብላ ትላለች፡፡ አባት ግን እንኳንስ በልቶ ሳይበላም የሚቀባጥር ልጅሽን ይቀስቀስ ማለትሽ እብደት ይመስለኛል ብሎ በጭራሽ አይሆንም አለ፡፡ እናቲቱ ግን ስጋትህን ህጻኑ ያወራብኛል ከሆነ በእኔ ጣለው ብላ ስታበቃ አንድ ሙሉ ጣሳ ውሃ ይዛ ህጻኑ ወደተኛበት አመራችና በላዩ ላይ ቸለሰችበት፡፡ “አንተ ተነስና ራትህን ብላ ዝናቡ እኮ እየዘነበ ነው” አለችው፡፡ ህጻኑ በእንቅልፍ ልቡ ነተስቶ እናቱ ያለችውን በአፅምው ቀርጾ እራቱን በልቶ ተኛ፡፡ ጠዋት ላይ ሽማግሎቹ ቤት ደርሰው ህጻኑን ወደውጭ አውጥተው ይመረምሩት ጀመር፡፡ “ማሙሽዬ እናንተ ቤት ስጋ አለ እንዴ? ስጋ በልታችኋል እንዴ?” ብለው ይጠይቁታል፡፡ ህጻኑ ቀበል ያደርግና “እኔ ያን ጊዜ ዝናቡ የዘነበ ጊዜ በልቻለሁ” አለ፡፡ ይሄኔ ሽማግሌዎቹ “እኛ የጠየቅነው የዘንድሮውን እሱ የሚነግረን ያምና የክረምቱን ልቀቁት ይሂድ ዋጋም የለው ብለው ለቀቁት ይባላል፡፡ (ምትኩ አበራ፣ ምጥን ቅመም፣ 2006፣5-6)

**ተረት 98**

አንዲት ፊቷን እሳት የጠበሳት እናት ነበረች ይባላል፡፡ አንድ ባካባቢው የተከበረ ልጅ ነበራት፡፡ ይህ ልጅ ባልንጀሮቹ ወደቤቱ ሲመጡ እናቱን አይተው እንዳይንቁት በማሰብ

"ገረዶ ናት" እያለ ያስተዋውቃቸው ነበር፡፡ እናት ግን ይህንን ተመልክታ ቅር አልተሰኘችም ነበር፡፡

ከእለታት አንድ ቀን እናት ለልጇ እንዲህ ስትል አወጋችው፡፡ "ልጄ! መልኬ እንዲህ ተጠብሶ የተበላሸው አንተን በእሳት ከተያያዘ ቤት ውስጥ አወጣለሁ ብዬ በመግባቴ ነው፡፡ አንተን በያዝኩት ብርድ ልብስ ጠቅልዬ ከእሳቱ ሳተርፍህ እኔን ግን እሳቱ ክፉኛ አቃጠለኝና በጠባሳ የተበላሸ ገላ ይገኝ ቀረሁ" አለችው፡፡ ልጇም በራሱ ድርጊት ተጸጽቶ ባልንጀሮቹን ሁሉ ሰበሰበና "ተመልከቱ ይቺ ሰማዕቷ እናቴ ናት፡፡ የእሷ ውበት ከእኔ ላይ ነው፤ የእኔ ጠባሳ ደግሞ እሷ ላይ ነው" በማለት ነገራቸው ይባላል (ቅድስተ ማሪያም የርቀት ማስተማሪያ ሞጁዩል ገጽ 29)፡፡

ተረት 99

የሴት ጦረኞች

አስር የሴት ጦረኞች ወደውጊያ ሄዱ አሉ፡፡ በጦርነቱም ብዙ ከብቶችንና ቁሳቁሶችን ማርከው ወደሰፈራቸው ይመለሳሉ፡፡ ሆኖም ግን የተዘረፉ ከብቶቻቸውንና ቁሳቁሳቸውን ለማስመለስ ጠላቶቻቸው ይከተሏቸው ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የሴቶቹ ጦር አዛዥ ለወታደሮቿ "ጠላቶቻችን ከብቶቻቸውን ሊያስመልሱ ይችላሉ፡፡ ሽቶዎችን ግን በፍጹም ልንለቅላቸው አይገባንም" ስትል ትዕዛዟን አስተላለፈች፡፡ ወታደሮችም ትዕዛዟን በመቀበል ሽቶዎችን በእጃቸው አድርገው ጉዟቸውን ይቀጥላሉ፡፡ በመንገድ ላይ እያሉ አዛዧ በጦርነቱ የሞተች መኖር አለመኖሯን ለማረጋገጥ ቆጠራ ትጀምራለች፡፡ ስትቆጥር ግን ዘጠኝ ብቻ ይሆኑባታል፡፡ ግን እያንዳንዳቸውን በስም ስትለይ የጎደለ አልነበረም፡፡ ሁሉም በየተራ እንዲቆጥሩ ከተደረገ በኋላ የሁሉም ያው ዘጠን ነን የሚል ነበር፡፡ በቆጠራቸው መሰረት አንዲት ወታደር ጠፍታለች ተብሎ ሪፖርት ተደረገ፡፡ በመጨረሻም እርግጠኛ ለመሆን ፈልገው አንድ ወንድ እንዲቆጥራቸው አደረጉ፡፡ ሰውየው እንዲቀመጡ ካደረጋቸው በኋላ ቆጠራቸው፡፡ ቁጥራቸው አስር መሆኑን ነግሯቸው የሞተች እንደሌለች አረጋገጡ፡፡ በዚህም የብቃት ማነስ ችግራቸው የተነሳ ሴቶች ለጦርነት ብቁ አለመሆናቸውን ራሳቸው አወጁ ይባላል (Ayalew Getachew 2012:50)፡፡

## ተረት 100

## የጉጂ ኦሮሞ ንግስት ታሪክ

አንዲት አኮ መኖየ (Akko Manoyye) የምትባል የጉጂ ንግስት ነበረች፡፡ በንግስናዋ ዘመን ማንኛውም የቤት ስራ ልጅ መንከባከብን ጨምሮ የሚከናወነው በወንዶች ነበር፡፡ ውሳኔዎች የሚተላለፉት ግን በሴቶች ነበር፡፡ አኮ መኖየ አንድ ቀን ህዝቧን አንድ አቅማዳ ሙሉ ቁንጫ እንዲያመጡላት አዘዘች፡፡ ህዝቡም የተባለውን ለመፈጸም ይቸገራል፡፡ በዚህም የተነሳ HiyyoKulle የተባለውን ብልህና ድሃ ሰው ያማክራሉ፡፡ እሱም አንድ አቅማዳ የአህያ ፋንድያ እንዲሰበስቡና መሬት ላይ እንዲያሰጡት ይመክራቸዋል፡፡ እነርሱም የተባሉትን ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሃል ፋንድያው በወባ ትንኝ ይሞላል፤ ለንግስቷም ይህንኑ ያቀርቡላታል፡፡ እሷም የወባ ትንኞችን ቁንጫ ናቸው ብላ በማሰብና ትዕዛዟ እንደተፈጸመ በመቀበል ሌላ ከባድ ትዕዛዝ ትሰጣቸዋለች፡፡ ይህም ቤት በአየር ላይ እንዲሰሩላት ነበር፡፡ ህዝቡም ነገሩ ቢከብዳቸው በድጋሚ ወደ ብልሃተኛው ዘንድ በመሄድ ቤቱን እንዴት አድርገው እንደሚሰሩ ያማክሩታል፡፡ እሱም "በባህላችን መሰረት ምሰሶውን የሚያቆመው ባለቤቱ ነውና አቁሚልን በሏት" ሲል መከራቸዋል፡፡ ይህንን እንድታደርግ ሲጠይቋት ባለማድረጓ ትረታለች፡፡ ብልሁ ሰው ምክሩን ይቀጥላል፡፡ አንድ ጥልቅ ጉርጓድ እንዲቆፍሩና አፉን በከብት ቆዳ እንዲሸፍኑት ይመክራቸዋል፡፡ እናም እዚያ ላይ ለንግስቷ መቀመጫ የሚሆን ወንበር እንዲያዘጋጁ ይነጋራቸዋል፡፡ ንግስቷም በተዘጋጀላት ወንበር ላይ ስትቀመጥ ወደ ጥልቁ ጉርጓድ ተምዘግዝጋ ትገባለች፡፡ ከጥልቁ ጉርጓድ ውስጥ እንደሆነች ለሴቶች "ካንገት በላይም ቢሆን የወንዶችን የበላይነት አክብሩ" ስትል ታስተላፋለች፡፡ ከዚያ በኋላ የንግስቷን ሞት ተከትሎ ዱሪ ዱሉ (Durii Dulloo) የሚባል ሰው ነገሰ ይባላል (Ayalew Getachew 2012:49)፡፡

# አባሪ 2

## የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር

### ሀ. በቃለምልልስ እና በጽሑፍ ተረቶችን የሰጡ

| ተራ ቁጥር | የመረጃ ሰጪው(ዋ) ስም | ጾታ | ወረዳ | መረጃውን የሰጠበት/ የሰጠችበት ቀን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ምስጋናው አቢነው | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 2 | ጌታቸው ጉግሳ | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 3 | ደሳለኝ አያሌው | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 4 | አሳምነው አያሌው | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 5 | ገለታው ወርቁ | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 6 | ተስፋዬ ጌታሁን | ወ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 7 | መርከቡ ጋሻው | ወ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 8 | ዳንኤል ይመር | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 9 | አያል አበበ | ሴ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 10 | አባተ ይመር | ወ | ቦረና | ነሐሴ 2007 |
| 11 | አሰፋ ዳኘው | ወ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 12 | አበበች መላኩ | ሴ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 13 | አገሪቱ ጌትነት | ሴ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 14 | በዛብህ እንድሪ | ወ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 15 | ጋሻው ጮረቅ | ወ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 16 | ቦሰና ያሲን | ሴ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 17 | ጌታሁን አሰፋ | ወ | ቦረና | ግንቦት 2008 |
| 18 | ጋሻው ዓቢ | ወ | ቦረና | ረዳት መረጃ ሰብሳቢ |
| 19 | ሰይድ አህመድ | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 20 | መሃመድ ሁሴን | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 21 | ጌታቸው መላኩ | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 22 | መሃመድ አሰን | ወ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |
| 23 | ሃሊማ ሰይደ | ሴ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 24 | ሰይድ አሰን | ወ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |
| 25 | የሱፍ ይመር | ወ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |
| 26 | በለጠ መላኩ | ወ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |
| 27 | አስቴር ተከስተ | ሴ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |
| 28 | ብሬ አያሌው | ሴ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 29 | አረጉ እብሬ | ሴ | ተሁለደሬ | ነሐሴ 2007 |
| 30 | አለባቸው ወርቁ | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 31 | ካሳሁን አለሙ | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 32 | ደመወዝ ገረመው | ሴ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 33 | ልዑልሰገድ አሰፋ | ወ | ተሁለደሬ | ረዳት መረጃ ሰብሳቢ |
| 34 | አብዱ ሐሰን | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 35 | ብስራት ኃይሌ | ወ | ተሁለደሬ | መጋቢት 2008 |
| 36 | መዝገቡ ሰጠኝ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 37 | ጫኔ ሰይድ | ወ | ኩታበር | ነሐሴ 2007 |
| 38 | አህመድ ኢብራሂም | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 39 | አግማስ መቆያ | ሴ | ኩታበር | ነሐሴ 2007 |
| 40 | ሃሰን አበጋዝ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 41 | መዝገቡ ወልደ | ወ | ኩታበር | ነሐሴ 2007 |
| 42 | አምሳል ይላቅ | ሴ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 43 | አሰን ይማም | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 44 | አለሙ ሰይድ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 45 | ጌታቸው ለገሰ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 46 | ፈንታይቱ ይመር | ሴ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 47 | ጀማል ሰይድ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 48 | አስፋው ዓሊ | ወ | ኩታበር | ረዳት መረጃ ሰብሳቢ |
| 49 | መካሻ አበራ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 50 | ጥሩወርቅ ካሳው | ሴ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 51 | ደረጀ ፍቃዱ | ወ | ኩታበር | ሚያዚያ 2008 |
| 52 | ታምሩ ደምሴ (ሳጅን) | ወ | ደሴ | 25/10/2008 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 53 | አባ ፍቅረማርያም | ወ | ተሁለደሬ | 29/06/2008 |
| 54 | ሸህ ሁሴን አህመድ | ወ | ደሴ | 15/07/2008 |

## ለ. በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሳተፉ

| ተራ ቁጥር | የተሳታፊው/ዋ ስም | ጾታ | ዕድሜ | የትዳር ዘመን | የወረዳ | ውይይቱ የተካሄደበት ቀን |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ፋጡማ መሃመድ | ሴ | 36 | 12 | | |
| 2 | አስናቀች በቀለ | ሴ | 40 | 24 | | |
| 3 | የሺ መሃመድ | ሴ | 30 | 7 | ተሁለደሬ | 28/06/2008 |
| 4 | ተናኘ አሰፋ | ሴ | 26 | 4 | | |
| 5 | ወሰኔ መኮንን | ሴ | 41 | 21 | | |
| 6 | ሰብለ ወርቅነህ | ሴ | 38 | 20 | | |
| 7 | መስፍን ደመቀ | ወ | 45 | 23 | | |
| 8 | ታደሰ ይመር | ወ | 51 | 26 | | |
| 9 | ይመር ዓሊ | ወ | 27 | 3 | ተሁለደሬ | 27/06/2008 |
| 10 | ልዑልሰገድ አሰፋ | ወ | 48 | 22 | | |
| 11 | ደምሴ ተገኝ | ወ | 41 | 14 | | |
| 12 | አለምፀሃይ አሰፋ | ሴ | 27 | 5 | | |
| 13 | ገነት እርገጤ | ሴ | 24 | 3 | | |
| 14 | ተምሪቱ እንድሬ | ሴ | 22 | 1/2 | | |
| 15 | ሳምራዊት ከበደ | ሴ | 22 | 6 | ቦረና | 30/05/2008 |
| 16 | አበበች ምህረቱ | ሴ | 22 | 2 | | |
| 17 | አስካማርያም አፈወርቅ | ሴ | 36 | 9 | | |
| 18 | አለምዬ አንዳርጌ | ሴ | 36 | 10 | | |
| 19 | ፋጡማ ኑሩ | ሴ | 26 | 3 | | |
| 20 | ስጦታው ዝጋለ | ወ | 46 | 18 | | |
| 21 | ባምላኩ ጋሻው | ወ | 36 | 7 | | |
| 22 | ደምሰው ዘለቀ | ወ | 27 | 4 | | |
| 23 | ተሸመ አበበ | ወ | 38 | 18 | ቦረና | 27/05/2008 |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | ተመቸው ታደሰ | ወ | 26 | 1 | | |
| 25 | አስማማው ጋሻው | ወ | 50 | 26 | | |
| 26 | ሰርካለም አበበ | ሴ | 45 | 21 | ኩታበር | 15/08/2008 |
| 27 | አለም ሰይድ | ሴ | 36 | 8 | | |
| 28 | ሃዋ ይመር | ሴ | 47 | 26 | | |
| 29 | ረሂማ አብዱ | ሴ | 25 | 2 | | |
| 30 | ሰዓዳ ሰይድ | ሴ | 32 | 10 | | |
| 31 | እሸቴ አበበ | ወ | 42 | 12 | | 17/08/2008 |
| 32 | ታደሰ መሃመድ | ወ | 51 | 22 | | |
| 33 | መኮንን አህመድ | ወ | 35 | 6 | | |
| 34 | ሽመልስ መብሬ | ወ | 25 | 2 | | |
| 35 | ሙራድ አበጋዝ | ወ | 37 | 11 | | |
| 36 | ወርነህ ካሳው | ወ | 43 | 4 | | |

## አባሪ 3፤- ለተተኳሪ የቡድን ውይይት የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች

## ሀ. ለወንድ የተተኳሪ ቡድን ተወያዮች የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች

1. የሥርዓተ ጾታ እኩልነት ማለት ለእናንተ ምንድን ነው?
2. አንዲት ሴት ጥሩ ሚስት ናት የምትባለው ለባሏ ብሎም ለቤቷ ምን ስታደርግ ነው?
3. ከሚስት የማይጠበቁ ተግባራት የምትሏቸው ምን ምን ናቸው?
4. አንድ ወንድ በሚስቱ የሚናቅባቸው አጋጣሚዎች ምን ምን ናቸው?
5. አንድ ወንድ በባልነቱ የተነሳ ከማኅበረሰቡ ክብርና ሞገስ የሚያገኘው ምን ሲያደርግ ነው?
6. ከጥንት ጀምሮ አሁንም ቢሆን የወንድና የሴት ስራ ተብለው የተለዩ አሉ፡፡ እናንተ ለሴት ተብለው ተለይተው የተቀመጡ ስራዎችን ታከናውናላችሁ? የማታከናውኑ ከሆነ ምን ከለከላችሁ?
7. ከባልና ከሚስት የቤቱ አለቃ ማን ነው? ባንድ ጉዳይ ላይ ሁለታችሁ ባትስማሙና ግን ጉዳዩ የግድ ውሳኔ የሚያስፈልገው ቢሆን የማን ሃሳብ ተፈጻሚ ይሆናል?
8. ሚስትህ የነገርካትን ባትሰማ፣ ተይ ካልክባት ቦታ ባትመለስ ምን ታድርጋለህ?
9. ሚስትህ ሌላ ወንድ ይዛ ብታገኛት ወይም ብትሰማ ምን ታደርጋታለህ?
10. ባጋጣሚ በትዳራችሁ ባትስማሙና ብትለያዩ ከቤት ወጥቶ የሚሄደው ማን ነው? ለምን?
11. ብዙውን ጊዜ ወንዱ ከሴት ቤት ሄዶ ተከርቸም ለመግባት አይፈልግም፤ አይገባምም፡፡ ምክንያቱ ምንድን ነው?
12. ሚስትህ ከጓደኞቿ ጋር ስትጫወት ጠጥታ ሞቅ ብሏት ብትመጣ ምን ይሰማሃል?
13. በአሁኑ ጊዜ ሴት ከወንድ ጋር እኩል ናት የሚባለውን አስተሳሰብ ትቀበሉታላችሁ?

## ለ. ለሴት የተተኳሪ ቡድን ተወያዮች የቀረቡ መነሻ ጥያቄዎች

1. የስርዓተ ጾታ እኩልነት ማለት ለእናንተ ምንድን ነው?
2. ሃይማኖታችሁን ከስርዓተ ጾታ እኩልነት አጠባበቅ አንጻር ምን ይላል?
3. ባልሽን የምትንቂው ምን ጊዜ ነው?
4. ባልሽ ምን ዓይነተ ሰው እንዲሆንልሽ ተፈልጊያለሽ?
5. የመንግስት ሰራተኛ በመሆንሽ ከወንድ እኩል ነኝ ብለሽ ታምኛለሽ? (ለመንግስት ሰራተኞች ብቻ የሚቀርብ)
6. የሁለታችሁን መገኘት በሚጠይቁ እና ገንዘብ መክፈልን ግድ በሚሉ ማኅበራዊ ቦታዎች ላይ ለምሳሌ ሰርግ፣ ክርስትና፣ ቤት ምረቃ ወዘተ. ላይ ብትገኙ የምትከፍሉት ገንዘብ በማን ስም ይመዘገባል? ለምን?
7. ከባልና ከሚስት የቤቱ አለቃ ማን ነው? ባንድ ጉዳይ ላይ ሁለታችሁ ባትስማሙና ግን ጉዳዩ የግድ ውሳኔ የሚያስፈልገው ቢሆን የማን ሃሳብ ተፈጻሚ ይሆናል?
8. በጎረቤትሽ ባሎች ለሚስቶቻቸው ልብስ ሲያያጥቡ ምግብ ሲያበስሉ፣ ቤት ሲያጸዱ ብታስተወዪ ምን ይሰማሻል?
9. ባልሽ ባንቺ ላይ ሌላ ሴት ደርቦ መያዙን ብትሰሚ ምን ታደርጊያለሽ?
10. ትዳር ስትመሰርቺ አንቺ ወደባልሽ አገር ከምትሄጅና ባልሽ ወዳንቺ አገር ከሚመጣ የቱን ትመርጫለሽ?
11. በአሁኑ ጊዜ ሴት ከወንድ ጋር እኩል ናት የሚለውን አስተሳሰብ ትቀበሉታላችሁ?